# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የሁለተኛው አምስት ዓመት (2008-2012)
# የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጨረሻ ረቂቅ

ሚያዝያ 2007
አዲስ አባባ

ተ.ቁ. ማውጫ ርዕስ ገፅ


መግቢያ ........................................................................................................ 1

ክፍል ፩ የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም ........................................ 2

1.1 የማክሮ ኢኮኖሚ አፈፃፀም ........................................................................... 2

1.2 የግብርናና ገጠር ልማት ዕቅድ አፈፃፀም ........................................................... 19

1.2.1 የግብርናና ገጠር ልማት ዕቅድ ዓላማና አቅጣጫዎች ........................................ 19

1.2.2 የግብርናና ገጠር ልማት ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም ..................................... 19

1.2.3 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች .................................... 22

1.3 የኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ አፈጻጸም ............................................................. 23

1.3.1 የኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ አቅጣጫዎች ..................................................... 23

1.3.2 የኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም ......................................... 23

1.3.3 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች ..................................................................... 26

1.4 የንግድ ዘርፍ ዕቅድ አፈፃፀም ....................................................................... 26

1.4.1 የንግድ ዘርፍ ዕቅድ ዓላማና አቅጣጫዎች .................................................... 26

1.4.2 የንግድ ዘርፍ ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም ............................................... 27

1.4.3 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች ..................................................................... 27

1.5 የማዕድን ልማት ዕቅድ አፈፃፀም ................................................................... 28

1.5.1 የማዕድን ልማት ዕቅድ ዓላማና አቅጣጫዎች ................................................ 28

1.5.2 የማዕድን ልማት ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም ............................................ 28

1.5.3 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች .................................... 29

1.6 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አፈፃፀም ............................................................. 29

1.6.1 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ አፈፃፀም በተመለከተ ........................ 29

1.6.2. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በመሠረተ ልማት ግምባታው ያሳየው አፈጻጸም ............... 29

1.6.3. ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች ................................... 30

1.7 የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት ዕቅድ አፈፃፀም ......................................................... 31

1.7.1 የመሠረተ ልማት ዕቅድ ዓላማና አቅጣጫዎች ................................................ 31

1.7.2 የመሠረተ ልማት ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም ................................................... 31

1.7.3 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች ..................................................................... 40

1.8 የማህበራዊ ዘርፍ ልማት ዕቅድ አፈፃፀም ........................................................ 40

1.8.1 የማህበራዊ ዘርፍ ልማት ዕቅድ ዓላማና አቅጣጫዎች ........................................ 40

1.8.2 የማህበራዊ ዘርፍ ልማት ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም .................................... 41

1.8.3 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች .................................... 47

**1.9 የማስፈጸም አቅም ግንባታና ልማታዊ መልካም አስተዳደር አፈጻጸም ....................................47**

1.9.1 ዓላማዎችና አቅጣጫዎች ....................................................................................47

1.9.2 የዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም ....................................................................................48

**1.10 የሕዝብ ተሳትፎ፣ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና ብሔራዊ መግባባት ....................................55**

**1.11 የባለ ብዙ ዘርፎች ዕቅድ አፈጻጸም....................................................................55**

1.11.1 የሴቶች፣ የህፃናትና ወጣቶች ዘርፍ ልማት....................................................55

1.11.2 የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ............................................................................58

1.11.3 የስፖርት ዘርፍ ዕቅድ አፈጻጸም ........................................................................60

1.11.4 የማህበራዊ ደህንነትና የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዘርፍ ዕቅድ አፈጻጸም ..........................62

1.11.5 ባህልና ቱሪዝም አፈጻጸም ................................................................................63

1.11.6 የሥነ ሕዝብና ልማት ዕቅድ አፈፃፀም...................................................................66

1.11.7 የአካባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች አፈጻጸም ......................................68

**1.12 የክትትልና ግምገማ ሥርዓት...........................................................................70**

**1.13 በዕቅዱ የትግበራ ሂደት የታዩ ጥንካሬዎችና ያጋጠሙ ፈተናዎች ....................................71**

**ክፍል ፪ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) ...................................75**

**ምዕራፍ I የዕቅዱ መነሻዎች፣ ልዩ የትኩረት መስኮች፣ ዓላማዎችና መሠረታዊ አቅጣጫዎች..............75**

**1.1 የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻዎች ...........................................75**

**1.2 የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ልዩ የትኩረት መስኮች .................................77**

**1.3 የዕቅዱ ዓላማዎች ..........................................................................................78**

**1.4 የዕቅዱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች..........................................................................79**

1.4.1 የተጀመረውን ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ማስቀጠል፣ ......................79

1.4.2 የኢኮኖሚው የማምረት አቅም ላይ ለመድረስ ቅልጥፍና መጨመርና አምራች ዘርፎችን በማጐልበት በጥራት፣ በምርታማነትና በተወዳዳሪነት የላቀ ዕድገት ማምጣት፣ ............................80

1.4.3 የተፋጠነ የሀገራዊ ልማታዊ ባለሀብት ትራንስፎርሜሽን ማምጣትና ብቁ የልማት ኃይል ማድረግ ......................................................................................................81

1.4.4 የኮንስትራክሽንን ዘርፍ አቅም በማጐልበት፣ የመሠረተ ልማት ተደራሽነትን መጨመር እና የአገልግሎቱን ጥራት ማረጋገጥ፣ ......................................................................82

1.4.5 የከተሞችን ፈጣን ዕድገት በአግባቡ በመምራትና በማስተዳደር ለአጠቃላይ ፈጣን ዕድገት አስተዋፅዖ እንዲያጐለብት ማድረግ...................................................................83

1.4.6 የሰው ኃብት ልማትንና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታን ማፋጠንና ዘላቂነቱን ማረጋገጥ.................84

1.4.7 የመንግሥትን የማስፈፀም አቅም በመገንባት እና የህዝቡን ተሣትፎ በማጐልበት ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ መልካም አስተዳደርን ማስፈን ................................................................84

1.4.8 የሴቶችንና የወጣቶችን ብቃት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ ...........................................86

1.4.9 ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት...........................................87

**1.5 የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች ትንበያ ማጠቃለያ.........................88**

ምዕራፍ II የማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፍ ዕቅድ ....................................................................93
2.1 የማክሮ ኢኮኖሚ ዋና የፖሊሲ ግቦች ....................................................................93
2.2 የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ግቦች ዝርዝር ትንተና ....................................................................93
2.2.1 ባለሁለት አሀዝ ዓመታዊ ዕድገትን አጠናክሮ በማስቀጠል በመሠረታዊ የዕድገት አማራጭ ኢኮኖሚው በአማካይ በ11 በመቶ እንዲያድግ ማድረግ....................................................................93
2.2.2 የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት ....................................................................96
2.2.3. የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ማድረግ ....................................................................98
2.2.4 የሀገር ውስጥ ቁጠባ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻን 29.6 በመቶ ማድረስ ይህንን በማድረግም ኢንቨስትመንት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻው በዕቅዱ መጨረሻ ዓመት ወደ 41.3 በመቶ እንዲሆን ማድረግ....................................................................99
2.3 የፋይናንሲንግ ዕቅድ (Financial Plan) ....................................................................101
2.3.1 በጀት ነክ የፋይናንስ ዕቅድ ....................................................................101
2.3.2 ከበጀት ውጪ የሆነ የፋይናንስ ምንጭና የኢንቨስትመንት ፋይናንስ ፍላጎት....................................................................102
2.4 የሥራ ፈጠራና የድህነት ቅነሳ ዕቅድ ....................................................................102
2.5 የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማኔጅመንትና ተቋማዊ ብቃትን ማጠናከር ....................................................................103
2.6 ማጠቃለያ ....................................................................103
ምዕራፍ III የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ልማት ዕቅድ ....................................................................105
3.1. የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት ዕቅድ ....................................................................105
3.1.1. ግብርናና የገጠር ትራንስፎርሜሽን....................................................................105
3.1.2 የኢንዱስትሪ ልማትና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ....................................................................117
3.1.3 የማዕድን ልማት ....................................................................126
3.1.4 የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት....................................................................132
3.1.5 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ....................................................................144
3.1.6 ከተማ ልማትና ቤቶች ....................................................................150
3.1.7 የንግድ ዘርፍ ልማት....................................................................151
3.1.8 ባህልና ቱሪዝም....................................................................154
3.2 የሰው ሀብት ልማትና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ዘርፍ ልማት ዕቅድ....................................................................156
3.2.1. ትምህርትና ስልጠና....................................................................156
3.2.2. ጤና ዘርፍ ልማት ....................................................................161
3.2.3 ሳይንስና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ....................................................................164
3.3 የማስፈፀም አቅም ግንባታና ልማታዊ መልካም አስተዳደር ....................................................................167
3.4 የሕዝብ ተሳትፎ፣ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና ብሔራዊ መግባባት ....................................................................173
ምዕራፍ IV የባለብዙ ዘርፎች ልማት ዕቅድ ....................................................................178
4.1 የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ....................................................................178
4.2 የወጣቶችና የስፖርት ዘርፍ ....................................................................180

4.3 ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ....181
4.4 የአካባቢ እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት....183
4.5 ሥነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች ....186
ምዕራፍ V  በዕቅዱ አፈፃፀም ሂደት የሚጠበቁ ዕድሎችና ስጋቶች ....188
5.1 ዕድሎች....188
5.2 ስጋቶች....189
5.3 የስጋት መከላከያ ስትራቴጂዎች....189
ምዕራፍ VI  የአፈፃፀምና ክትትል ግምገማ ሥርዓት ....190

# መግቢያ

የመጀመሪያው አምስት ዓመት (2003-2007) የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሠረታዊ ዓላማዎች (1) ኢኮኖሚውን በየዓመቱ ቢያንስ በአማካይ 11 በመቶ በማሳደግ የሚሌኒየም የልማት ግቦችን ማሳካት (2) የትምህርትና ጤና አገልግሎት ሽፋንን በመጨመርና ጥራቱን በማረጋገጥ ላይ የተመሠረተ ማህበራዊ ልማት በማካሄድ የሚሌኒየም ልማት ማህበራዊ ግቦችን ማሳካት (3) የተረጋጋ፣ ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ መንግስትን በመፍጠርና በማጠናከር ለቀጣይ የሀገር ግንባታ ሥራ ምቹ መደላድል መፍጠር እና (4) የተረጋጋ ማክሮ-ኢኮኖሚ በማስፈን የልማቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ ናቸው፡፡

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ አራት ዋና ዋና ዓላማዎችንና ሰባት መሠረታዊ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ሲዘጋጅ በከፍተኛ ደረጃ ቅርብ የፖለቲካ አመራር የተሰጠበትና በተለያዩ ደረጃዎች በተዘጋጁ የህዝብ ውይይት መድረኮች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በቀጥታና በተወካዮቻቸው አማካኝነት በማሳተፍ ከምንጊዜውም በተሻለ መልኩ ሰፊ ውይይት ተካሂዶበት የመላውን ህዝብ ከፍተኛ ድጋፍ አግኝቶ እና በመጀመሪያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ ቀጥሎም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዝርዝር ተመክሮበት የፀደቀ እና በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ሥራ ላይ እንዲውል የተደረገ ዕቅድ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ያለፉት አራት ዓመታት (2003-2006) አፈፃፀም ከዕቅዱ ዓላማዎች፣ አቅጣጫዎች እና ዋና ዋና ግቦች አንፃር ተገምግሟል፡፡ በዚህም መሠረት በኢኮኖሚ ዕድገት፣ በመሠረተ ልማት፣ በማህበራዊ ልማት፣ በአቅም ግንባታና በመልካም አስተዳደር እና በባለብዙ ዘርፎች ዙሪያ ቀጣይነት ያላቸው ስኬታማ ውጤቶች መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዕቅዱ የትግበራ ሂደት ቁልፍ በሆኑ ሀገራዊ የልማት ጉዳዮች ዙሪያ ከሀገሪቱ ጫፍ እስከ ጫፍ ከፍተኛ ህዝባዊ መነሳሳትና የጋራ የልማት መንፈስ የተፈጠረበት እንደነበር ታይቷል፡፡ ይህም ለቀጣይ የልማት ሥራዎች የተደራጀና የተቀናጀ ጠንካራ አቅም እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል ባለፉት አራት ዓመታት የዓለም ኢኮኖሚ ከፍተኛ ውጣ ውረዶች የነበሩበት ሆኖ መቆየቱ በተለይም የዓለም የምግብና የነዳጅ ዋጋ በመጀመሪያዎቹ ሁለት የዕቅዱ የትግበራ ዓመታት ከፍተኛ ዕድገት ያሳየበት የነበረ እና አጠቃላይ የዓለም የኢኮኖሚ ዕድገትም ዕቅዱ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ከነበሩት ሁለት ዓመታት ብዙ መሻሻል ሳያሳይ የቆየ መሆኑ በሀገር ውስጥ ዋጋ ንረትና በውጪ ምርት ዕድገታችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሮ እንደነበረ ግምገማው ያሣያል፡፡ ነገር ግን መንግስት በወሰዳቸው የፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎች የገበያ ጉድለቶችን በማስተካከል ከዓለም ገበያ የመጣውን አሉታዊ ተጽእኖ ለመቋቋም ተሞክሯል፡፡

የአፈፃፀም ግምገማው በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከተቀመጡ ግቦች አንፃር እስከ 2006 በጀት ዓመት በተለያዩ ደረጃዎች በተከናወኑ የተቀናጁና የተደራጁ የልማት ሥራዎች የተሳኩትን፣ ለስኬት የተቃረቡትን፣ በታቀደውና በተጠበቀው ልክ ውጤት ያልተመዘገበባቸውን ዋና ዋና ግቦች በመለየት፣ በዕቅዱ የትግበራ ሂደት ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችን እና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በግልፅ አስቀምጧል፡፡ የአፈፃፀም ግምገማ ውጤቶችም ለሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ረቂቅ ዕቅድ ዝግጅት የመነሻ ግብዓት ተደርገው ተወስደዋል፡፡

የሁለተኛው የዕድገትና ትራስፎርሜሽን ረቂቅ ዕቅድ በሁለት ክፍሎች እና በስድስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለህዝብ ውይይት ቀርቦ በሚገኙ ግብዓቶች መሠረት እንደሚሻሻልና እንደሚዳብር ይጠበቃል፡፡ ረቂቅ ዕቅዱ በክፍል ፩ የመጀመሪያውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም፣ በክፍል ፪ የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ረቂቅ ዕቅድ በመያዝ የቀረበ ሲሆን ክፍል ፪ በስድስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው፡፡ እነዚህም ምዕራፍ I የዕቅዱ መነሻዎች፣ መለያዎች፣ ዓላማዎችና መሠረታዊ አቅጣጫዎች፣ ምዕራፍ II የማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፍ ዕቅድ፣ ምዕራፍ III የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ልማት ዕቅድ፣ ምዕራፍ IV የባለብዙ ዘርፎች ልማት ዕቅድ፣ ምዕራፍ V በዕቅዱ አፈፃፀም ሂደት የሚጠበቁ ዕድሎችና ስጋቶች እና ምዕራፍ VI የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ናቸው፡፡

# ክፍል ፩
# የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም

# ክፍል ፩
# የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም

## 1.1 የማክሮ ኢኮኖሚ አፈፃፀም

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ከተጀመረ ይኸው አምስተኛው ዓመት እየተጋመሰ ነው፡፡ ዕቅዱ ሲዘጋጅ በከፍተኛ ደረጃ በቅርብ የፖለቲካ አመራር የተሰጠበትና በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለያየ ደረጃ ውይይት ተደርጎበት በመጨረሻ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት መክሮበት መጽደቁ የሚታወስ ነው፡፡ ዕቅዱ የያዛቸው ዋና ዋና ግቦችም በተደራጀ፣ በፍጥነትና በጥራት ከተተገበሩ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽ በማምጣት ለኢትዮጵያ ህዳሴ ፅኑ መሠረት እንደሚጥል ተስፋውና እምነቱ ትልቅ ነበር፡፡

በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በማክሮ ደረጃ የሚታዩ ቁልፍ ግቦች ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

ሀ) ባለሁለት አሀዝ አመታዊ የኢኮኖሚ ዕድገትን አጠናክሮ ማስቀጠል፣
ለ) የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ማድረግ፣

- የዋጋ ንረትን በነጠላ አሀዝ መገደብ፣
- የውጭ ምንዛሪ ተመን የተረጋጋና የወጪ ንግድን ተወዳዳሪነት የሚያበረታታ ማድረግ

ሐ) የሀገር ውስጥ ቁጠባ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻን 15 በመቶ ማድረስ፣
መ) የወጪ ንግድን የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ 22.5 በመቶ ማድረስ፡፡

በአሁኑ ወቅት ተተኪው የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እየተዘጋጀ በመሆኑ የመጀመሪያውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ጉዞ መዳሰሱ መልካም መነሻና ግብአት ይሆናል፡፡ ስለዚህ ይህ አጭር ጽሁፍ ከማክሮ ኢኮኖሚ ዕይታ አንፃር ከላይ የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀማቸውንና በትግበራ ሂደት ያጋጠሙ ፈተናዎችን ይዳስሳል፡፡

### 1.1.1 ባለሁለት አሀዝ የኢኮኖሚ ዕድገትን አጠናክሮ ማስቀጠል

#### ሀ) የተቀመጡ ግቦችና ታሳቢዎች

አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገትን በሚመለከት ዕቅዱ ሁለት አማራጮችን አስቀምጦ ነበር፡፡ የመጀመሪያውና መሠረታዊ አማራጭ ቀደም ባሉ ዓመታት የነበረውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በማስቀጠል በዓመት በአማካይ 11.2 በመቶ እንዲሆን ግብ ተቀምጦ ነበር፡፡ ይህንን ግብ ለማሳካት ለዕድገት ዋና ምንጭ የሆኑት ግብርና በአማካይ በ8.6 በመቶ ኢንዱስትሪ ደግሞ በ20 በመቶ እንደሚያድጉ ግብ ተጥሎ ነበር፡፡

በተጨማሪ በግብርና ዘርፍ በአብዛኞቹ አርሶ አደሮች ዝቅተኛ ምርታማነትና በጥቂቶቹ ምርጥ አርሶ አደሮች ከፍተኛ ምርታማነት መካከል ያለውን ልዩነት ቢያንስ በግማሽ ማጥበብ ከተቻለ የግብርና ምርት በዕጥፍ እንዲያድግ ስለሚያስችለው አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት 14.9 በመቶ ሊደርስ ይችላል በሚል የከፍተኛ አማራጭ ግብ ተቀምጦ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ሰፋፊ የእርሻ መሬት ባለባቸው አካባቢዎች ኮሜርሺያል ፋርሚንግን በማስፋፋት ለግብርና ዘርፍ ዕድገት ተጨማሪ የዕድገት ምንጭ እንደሚሆኑም ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ለአማራጮቹ ቁልፍ መሠረት የማምረት ድንበር (Production Frontier) የሚለው ንድፈ ሃሣብ ነው፡፡

የግብርና ምርት እና ምርታማነት ዕድገት በዕቅዱ በተቀመጠው መሠረት ከተመዘገበ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ የዋጋ ንረት ግሬትን በአስተማማኝ ለማስወገድ፣ ኢንዱስትሪ ከሴክተሩ በግብአትነት

የሚፈልጋቸውን ጥሬ ዕቃዎች ለማቅረብ እና ወጪ ንግድን በማጠናከር የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ለማስፋት እንደሚያስችልና ለተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው በዕቅዱ አጽንኦት የተሰጠው ጉዳይ ነበር፡፡ በኢንዱስትሪ በኩል ሴክተሩ ከሌሎች ሴክተሮች በላይ በላቀ ደረጃ በማደግ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው ዕድገት ፍጥነትና ቀጣይነት አስተዋጽኦ እንዲያደርግ በዕቅዱ ከምንጊዜውም የበለጠ ድርሻ ተሰጥቶት ነበር፡፡ ልክ እንደግብርናው ያሉትን ኢንደስትሪዎች (ማለትም የጨርቃ ጨርቅ፣ የቆዳና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ) የማምረት አቅም አሟጦ መጠቀም ማለትም ወደ ማምረት ድንበሩ እንዲደርሱ ማስቻል አንዱ የተቀመጠ አቅጣጫ ነበር፡፡

የኢንዱስትሪ ዕድገት ዕቅድ ያተኮረባቸው ዘርፎች አንደኛ፣ ለውጪ ንግድ በስፋት ማምረት፤ ሁለተኛ፣ የገቢ ንግድን በመተካት ላይ ያተኮሩ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት እና ሦስተኛ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማፋጠንና ለሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆኑ ምርቶችን የሚያመርቱ የሜታልና ኢንጂነሪንግ ፋብሪካዎች የሚሉት ናቸው፡፡

የወጪ ንግድን በተመለከተ የጨርቃጨርቅ፣ የቆዳና የስኳር ፋብሪካዎች ትኩረት የተሰጠባቸው ዘርፎች ሲሆኑ የገቢ ንግድን በመተካት በኩል ደግሞ የማደበሪያ፣ የፕላስቲክ ምርቶችና ሲሚንቶ በዋናነት የተለዩ ናቸው፡፡ የቴክኖሎጂ ሽግግርንና የሀገር ውስጥ መለዋወጫ ግብአቶችንና ቀላል ፋብሪካዎችን በማምረት የገቢ ንግድን ለመተካት እንዲቻል ደግሞ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ፋብሪካዎችን ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ዕቅዱ ያስቀምጣል፡፡ በተለይ በብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ በኩል በመንግሥትና በግሉ ያሉትን አቅሞች አቀናጅቶ በመጠቀም ወደ ማምረት ድንበሩ እንዲቀርብ በማድረግ ለኢንዱስትሪ ሴክተር ብሎም አጠቃላይ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል በዕቅዱ የተቀመጠ ሌላው አቅጣጫ ነበር፡፡

ሌላው በኢንዱስትሪ ዘርፍ ሥር የሚካተተውና የግብርናውና የኢንዱስትሪውን ዕድገት ማነቆ ከመፍታት አኳያ ትልቅ ትኩረት የተሰጠው የመሠረተ ልማት በተለይ ኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት የተያዘው ዕቅድ ነበር፡፡ ከዚህ አኳያ በአምስት ዓመቱ የዕቅድ ዘመን የሀገሪቱን የኃይል ማመንጨት አቅም በአራት እጥፍ በማሳደግ 8000 ሜ.ዋ. ማድረስ ነበር፡፡ በአገልግሎት ዘርፍ የሚካተቱና ዕቅዱ ትኩረት የሰጠባቸው የመሠረተ ልማት ዘርፎች ደግሞ መንገድ፣ ቴሌኮሚኒኬሽን፣ ትምህርትና ጤና ናቸው፡፡ ለምሳሌ ዝርዝር ዕቅዱ በየዘርፎቹ ግምገማ ላይ የሚታይ መሆኑ ታሳቢ በማድረግ በመንገድ ዘርፍ የሀገሪቱን ጠቅላላ የመንገድ ርዝመት በ2002 የበጀት ዓመት ከነበረበት 48,800 ኪ.ሜ. በ2007 መጨረሻ 64,522 ማድረስ እና የቴሌኮሚኒኬሽን ሽፋንን በተመለከተ የገመድ አልባ ስልክ አገልግሎት የቆዳ ሽፋን ከ50 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማሳደግና የገጠር ቴሌኮም አገልግሎት በ5 ኪ.ሜ. ርቀት ከ62 በመቶ ወደ 100 መቶ ማድረስ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩ ግቦችን ለማሳካት ከ2003-2007 ባሉት አምስት ዓመታት በድምሩ ብር 976.1 ቢሊዮን የኢንቨስትመንት ፍሰት እንደሚያስፈልግ የተቀመጠ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከመንግሥት በጀት ውጪ የሚፈለግ ብር 569.2 ቢሊዮን ሲሆን ከመንግሥት ለካፒታል ወጪ ደግሞ ብር 406.9 ቢሊዮን ነበር፡፡ ይህ የኢንቨስትመንት ፍላጎት በዋናነት ከቁጠባ የሚሸፈን ሲሆን ቀሪው ከውጭ ብድርና ዕርዳታ እንደሚሸፈን ታሳቢ ተደርጎ ነበር፡፡ የፋይናንስ ምንጭ ያልተገኘላቸው ፕሮጀክቶች ደግሞ በዕቅዱ ዓመታት ከውጭ ብድርና ዕርዳታ በማፈላለግ እንደሚሸፈኑ በማቀድ በፋይናንስ ክፍተት (financing gap) መልክ እንዲታዩ ተደርጎ ነበር፡፡


## ለ) ያለፉት አራት ዓመታት (2003-2006) አፈፃፀም

ከአፈፃፀም አንፃር ባለፉት አራት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዓመታት (2003-2006) ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በየዓመቱ በአማካይ በ10.1 በመቶ ያደገ ሲሆን ይህ አፈፃፀም በየዓመቱ በአማካይ ይደረስበታል ተብሎ ከተቀመጠው ግብ ጋር ሲነፃፀር ጉድለት ያሳያል፡፡ ሆኖም የተመዘገበው አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት በዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም የ2014 መረጃ መሠረት በተመሳሳይ ወቅት ከሰሀራ በታች

ባሉ ሀገሮች ከተመዘገበው የ5 በመቶ አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ሲነፃፀር በጣም ከፍተኛ እና ፈጣን እንደሆነ መመልከት ይቻላል፡፡ በሀገራችን እየተመዘበ ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት በዓለም አቀፍ ደረጃም እጅግ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ተብለው ከተመዘገቡት መካከል መመደቡ የሚታወስ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በአለፉት አራት ዓመታት የግብርና፣ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎች በቅደም ተከተል በየዓመቱ በአማካይ የ6.6 በመቶ፣ የ20 በመቶ እና የ10.7 በመቶ ዕድገት አስመዝግበዋል፡፡ የዘርፎቹ አማካይ ዓመታዊ የዕድገት አፈፃፀም ለእያንዳንዱ ዘርፍ ከተቀመጠው ግብ ጋር ሲነፃፀር የግብርና ዕድገት አፈፃፀም ጉድለት የታየበት ሲሆን በኢንዱስትሪና በአገልግሎት የተመዘገቡ የዕድገት አፈፃፀሞች ለዘርፎቹ የተቀመጡ ግቦችን እንዳሳኩ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ባለፉት አራት ዓመታት ይደረስበታል ተብሎ የተቀመጠው የ11.2 በመቶ አማካይ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት ዝቅ ብሎ ተፈፃሚ መሆን ከግብርና ዘርፍ ዕድገት ዝቅተኛ አፈፃፀም ጋር የተሳሰረ መሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡

*ሥዕል* 1.1 **ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት በ2003 በተሰራበት ዋጋ በመቶኛ**




በሌላ በኩል ባለፉት አራት ዓመታት (2003-2006) የተመዘበው የኢኮኖሚ ዕድገት ፈጣን ብቻ ሳይሆን ከግብርና፣ ከኢንዱስትሪና ከአገልግሎት ዘርፎች የመነጨ በመሆኑ መሠረቱ ሰፊ ነበር፡፡ ይህም የዜጎችን አቅም ከማሳደግ፣ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፈጠር ዜጎችን በየደረጃው ፍትሀዊ ተጠቃሚ ከማድረግ እና ድህነትን ከመቀነስ አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡


የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ለውጥ በሚመለከት የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከሁሉም ዘርፎች በላቀ ፍጥነት እንዲያድግ በማድረግ ለሀገራችን ቀጣይ የልማት መሠረት የሚሆንበትን መደላድል መፍጠርና የኢኮኖሚ መዋቅሩም ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ በተለይም ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ደረጃ በደረጃ እንዲሸጋገር ማድረግ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዳችን በግልፅ የተቀመጠ አቅጣጫ እንደነበረ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡

ባለፉት አራት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዓመታት (2003-2006) የግብርና፣ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎች ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በቅደም ተከተል በአማካይ 37.8 በመቶ፣ 16.9 በመቶ እና 45.3 በመቶ ይደርሳል ተብሎ ይጠበቅ ነበር፡፡ ከዚህ አንፃር ዘርፎቹ በ2006 የበጀት ዓመት በቅደም ተከተል የ40.2 በመቶ፣ የ14.3 በመቶ እና የ46.2 በመቶ አፈፃፀም አስመዝግበዋል፡፡

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ አራት የትግበራ ዓመታት የተመዘገበው የዋና ዋና ዘርፎች ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ አፈፃፀም በዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት (2007) በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች በቅደም ተከተል ይደረስበታል ተብሎ የተቀመጠውን የ36.9 በመቶ፣ የ18.8 በመቶ እና የ44.3 በመቶ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ ግብ ለማሳካት እንደማያስችል መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ከዚህ አኳያ በአንፃራዊ ሁኔታ በአገልግሎት ዘርፍ የተመዘገበው አፈፃፀም ወደ ተቀመጠለት ግብ የተጠጋ ቢሆንም በግብርና እና በኢንዱስትሪ ዘርፎች የተመዘገቡ የአፈፃፀም ውጤቶች ግን ወደ ግቦቹ የተቃረቡ አይደሉም፡፡

*ሥዕል* 1.2 የዋና ዋና ዘርፎች ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በመቶኛ




በግብርና ዘርፍ በኩል በዕቅዱ የተቀመጡለትን ግቦች ማለትም የዋጋ ንረት ማረጋጋት፣ የወጪ ንግድን በማጠናከር የውጭ ምንዛሬ ግኝት ማስፋት እና ለኢንዱስትሪ ግብዓቶች የሚሆኑ ምርት በመጠንና በጥራት ማቅረብ የሚሉትን በተቀመጠው ግብ መሠረት ሊያሟላ አልቻለም፡፡ በተለይ በአንዳንድ ምርቶች የሀገር ውስጥ ፍላጎት ማሟላት ባለመቻሉ በውጭ ምንዛሬ ስንዴ ከውጭ ሀገር እንዲመጣና ለዋጋ መረጋጋት አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ተደርጓል፡፡ በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት በኩልም በ2002 ዓ.ም. ከነበረበት 0.41 ሚሊዮን ቶን በ2007 ወደ 3 ሚሊዮን ቶን ለማድረስ የተቀመጠው ግብም የሚደረስበት አይሆንም፡፡ ከዘርፉ የተገኘ የውጭ ምንዛሬም ከዕቅዱ ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ነው የሚታየው፡፡ በአጠቃላይ ዘርፉ በዕቅድ ዓመታት የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር በማድረግ በኩል የአንበሳ ድርሻ የተሰጠው ቢሆንም ተልዕኮውን በተሟላ ሁኔታ አላሳካም፡፡

በኢንዱስትሪ ዘርፍ በተለይም የውጭ ምንዛሬ ያስገኛሉ ተብሎ የሚጠበቁት የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት እና የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች መሻሻል እያሳዩ ቢመጡም የእስካሁን አፈፃፀማቸው ከተያዘው ግብ አንፃር ብዙ ወደ ኋላ የቀረ ነው፡፡ በሌላ በኩል የገቢ ምርቶችን የሚተኩ አምራች ፋብሪካዎችን ለማስፋፋት የተደረገ ጥረት በተለይ በሲሚንቶ፣ ስኳር፣ ፓወር ኢንጂነሪንግ፣ ብረታ ብረት እና ማዳበሪያ መልካም አቅጣጫ እየያዘ የመጣ ቢሆንም ከተቀመጠው ግብ አንፃር ተመጣጣኝ ደረጃ ላይ አይገኝም፡፡ በአጠቃላይ ገቢ ምርቶችን በስፋት ተክቶ የውጭ ምንዛሬ ለማዳን ከተቀመጠው ግብ አንፃር ሥራዎች ተጀመሩ እንጂ ብዙ ርቀት አልተጓዙም፡፡ ይህም በመሆኑ የኢንዱስትሪ ዘርፍ በብዙ ነገሩ በገቢ ንግድ ላይ ጥገኛ ነው፡፡ በመሆኑም የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ችግሩን ከማቃለል ይልቅ እያባባሰው ይገኛል፡፡ የሜታልና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ በዕቅዳችን ትልቅ አገራዊ ፋይዳ በተሰጣቸው ፕሮጀክቶች ላይ ንቁ ተሳትፎ እያደረገ ለቀጣይ ቴክኖሎጂ አቅም መሠረት እየጣለ የመጣ ቢሆንም በዕቅዳችን በተቀመጠው ልክ ወደ ማምረት ድንበር አልተደረሰም፡፡ በመሆኑም በአለፉት አራት ዓመታት በዋነኝነት ኢኮኖሚው የሚጠበቀውን መዋቅራዊ ለውጥ አላሳየም፡፡ ይህም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የግብርናን ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ፣ የአምራች ኢንዱስትሪውን ኢንቨስትመንት ትርጉም ባለው ሁኔታ ማስፋፋትና ምርታማነትን ማሻሻል፣ በአጠቃላይ ኢንዱስትሪው ዘርፍ እስካሁን ካስመዘገበው የላቀ ዕድገት እንዲያስመዘግብ ማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ይሆናል፡፡

### 1.1.2 የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ማድረግ

የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲሰፍን ማድረግ ቀጣይነት ያለውና ከፍተኛ ኢንቨስትመንትን ከመሳብና የወጪ ንግዳችን በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚታይ መሆኑን ዕቅዱ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ከዚህ አኳያ የዋጋ ንረትን በነጠላ አሀዝ መገደብ እና የውጭ ምንዛሬ ተመን የተረጋጋና የወጪ ንግዳችንን ተወዳዳሪነት ከግምት ውስጥ ያስገባ ማድረግ የሚሉ ግቦች ተቀምጠዋል፡፡ እስካሁን የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በፍላጎትና በአቅርቦት ምክንያት የሚፈጠር ክፍተት እስከ 40 በመቶ ለሚሆነው የሀገር ውስጥ ዋጋ ንረት መንስኤ ሲሆን ከዓለም የሸቀጦች (ምግብና ነዳጅ) ዋጋ ንረት፣ የዋጋ ንረት ስበት (expectation) እና ያልተጠበቀ የግብርና ምርት ውድቀት (agricultural supply shock) ደግሞ በድምሩ 60 በመቶ ለሚሆነው የሀገር ውስጥ የዋጋ ንረት መንስኤ እንደሆኑ ያሳያል፡፡

#### ሀ) የዋጋ ንረትን በነጠላ አሀዝ መገደብ

የዋጋ ንረትን በነጠላ አሀዝ መገደብ እንዲቻል በቅድሚያ የዋጋ ንረት መንስኤዎች እንዲለዩ የተደረገ ሲሆን እነዚህም በፍላጎትና በአቅርቦት ማካከል የሚፈጠር ክፍተት እና ከዓለም ገበያ በገቢ ንግድ ሸቀጦች አማካይነት የሚተላለፍ የዓለም የሸቀጦች ዋጋ ንረት ናቸው፡፡

#### ሀ.1) በፍላጎትና በአቅርቦት መካከል የሚፈጠር ክፍተት

የሀገር ውስጥ የሸቀጦች አቅርቦትን በተመለከተ መፍትሄው የግብርና ምርትና ምረታማነትን ማሳደግ ተብሎ በዕቅዱ ውስጥ በዋናነት የተቀመጠ ሲሆን ከኢንዱስትሪ ዘርፍ በተለይ እንደ ስኳር፣ ዘይትና ሲሚንቶ አይነት ኢንዱስትሪዎች የሚገኘው የምርት ዕድገትም የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር እንደሚረዱ ታሳቢ ተደርጎ ነበር፡፡ በሌላ በኩል የገንዘብና የፊስካል ፖሊሲ ደግሞ አጠቃላይ ፍላጎትን በመቆጣጠርና የዋጋ ንረት እንዳይከሰት ከማድረግ አኳያ ተቃኝተው እንደሚቀረጹ በዕቅዱ ውስጥ በግልፅ ተቀምጦ ነበር፡፡

#### የገንዘብ ፖሊሲ

ከገንዘብ ፖሊሲ አኳያ ዝቅተኛ የቁጠባ ወለድ ተመን ከዋጋ ንረት ተመን እኩል ወይም በመጠኑ ብቻ ዝቅ እንዲል በማድረግ ቁጠባን የሚያበረታታ እንዲሆን ታሳቢ የተደረገ ሲሆን፣ የመሠረታዊ ገንዘብ ዕድገት መጠን ከሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት (በጊዜው የገበያ ዋጋ) እንዳይበልጥ ገደብ ተጥሎ ነበር፡፡

#### ፊሲካል ፖሊሲ

የሀገር ውስጥ ቁጠባ ግብን ከማሳካት አኳያ የመንግሥት የታክስ ገቢን ለማሳደግ ከሚሰራው ሥራ ጎን ለጎን፣ የመንግሥት ወጪ ከፍተኛ የበጀት ጉድለት በማምጣት ለዋጋ ንረት እንዳያጋልጥ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚበደረው ብድር ከመሠረታዊ ገንዘብ ዕድገት ግብ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ገደብ ተደርጎበት ነበር፡፡

#### ሀ.2) የዓለም የምግብና ነዳጅ የሸቀጦች ዋጋ ንረት ተፅዕኖ

የ2003-2007 ዕቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት ከ1999-2000 ባሉት የበጀት ዓመታት ተከስቶ የነበረው የዓለም የምግብ ዋጋ ንረት የረገበበትና በሀገር ውስጥ የዋጋ ንረት ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ በከፍተኛ መጠን የቀነሰበት ወቅት ስለነበር ለዕቅዱ ዘመን ታሳቢ ተደርጎ የተወሰደው የዓለም የምግብ ዋጋ ንረት የተረጋጋና ዝቅተኛ ሆኖ ይቀጥላል የሚል ነበር፡፡

#### ሀ.3) አፈፃፀም

በዕቅዱ ዘመን የመጀመሪያዎች ሁለት ዓመታት ከፍተኛ ተግዳሮት ሆኖ የነበረው የዋጋ ንረት ዕድገት መጠን ነበር፡፡ ለዋጋ ንረቱ መንስኤዎች ሆነው የተለዩ ችግሮች (1) በዕቅዱ ዘመን የመጀመሪያ ዓመት የተወሰደውን የውጭ ምንዛሬ ተመን ማስተካከያ ተከትሎ የሸቀጦች ወጪ ንግድ ዕድገት እመርታ በማሳየት 38 በመቶ

ደርሶ ስለነበርና የአገልገሎት ወጪ ንግድና የሬሚታንስ ዕድገትም ከፍተኛ ስለነበር የውጭ ምንዛሬ ግኝት ከታቀደው በላይ የአንድ ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ትርፍ በማሳየቱ የመሠረታዊ ገንዘብ ዕድገት ከዕቅድ በላይ መውጣት (2) የአለም የምግብ ሸቀጦች ዋጋ ንረት ሳይታሰብ በማሻቀቡ በአብዛኛው የምግብ ሸቀጦች ላይ እስከ 60 በመቶ ጭማሪ ያሳየበት ሁኔታ መፈጠሩ ዋና ዋና ተብለው የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ በ2003 የበጀት ዓመት የሀገር ውስጥ የዋጋ ንረት 38 በመቶ የደረሰበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ይህንን የዋጋ ንረት ለመቆጣጠር መንግሥት የተለያዩ የፖሊሲ እርምጃዎችን ለመውሰድ ተገዷል፡፡ አንደኛ፣ በገንዘብ ፖሊሲ በኩል ከዕቅድ በላይ የተገኘውን የውጭ ምንዛሬ ክምችት በመሸጥ የመሠረታዊ ገንዘብ መጠን ዕድገትን ከዜሮ በታች በ4.4 በመቶ እንዲሆን ማድረግ፣ ሁለተኛ፣ በፊስካል ፖሊሲ በኩል መንግሥት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለበጀት ጉድለት እንዳይበደር ማድረግ እና የመሠረታዊ ሸቀጦች ዋጋን ለማረጋጋት መንግሥት የዘይት፣ ስንዴና ስኳር ምርቶችን ከውጭ በማስገባት ለህብረተሰቡ ማቅረብ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህ የፖሊሲ እርምጃዎች በመወሰዳቸው የዋጋ ንረት በ2004 የበጀት ዓመት ወደ 20.8 በመቶ ዝቅ እንዲል የተደረገ ሲሆን ከ2005 የበጀት ዓመት ጀምሮ በዕቅዱ በተቀመጠው መሠረት ወደ ነጠላ አሀዝ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት የዋጋ ንረት በ2005 የበጀት ዓመት 7.4 በመቶ፣ በ2006 የበጀት ዓመት 8.5 በመቶ፣ እና በ2007 የበጀት ዓመት የመጀመሪያ አምስት ወር 5.9 በመቶ ላይ ይገኛል፡፡

### ለ) የተረጋጋ ውጭ ምንዛሬ መጣኔ እንዲኖር ማድረግን በተመለከተ

ዕቅዱ በ1999 እና 2000 የበጀት ዓመት የዓለም የምግብ ዋጋ ንረትን ተከትሎ በብር በውጭ ምንዛሬ ተመን ላይ የተፈጠረውን መናር በማስተካከል የወጪ ንግድን የሚያበረታታና የገቢ ንግድን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት በሚል ግብ አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት በዕቅዱ የመጀመሪው ዓመት የብር የውጭ ምንዛሬ ተምን የ20 በመቶ ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡ ይህንን ተከትሎ ትክክለኛው የብር የውጭ የምንዛሬ ተመን (real exchange rate) ከሚዛናዊው የውጭ ምንዛሬ ተመን (equllibrium exchange rate) ጋር የተስተካከለበት ሁኔታ በመፈጠሩ የወጪ ንግዳችን በበጀት ዓመቱ የ38 በመቶ ዕድገት አሳይቶ ነበር፡፡

ሆኖም ግን ሳይታሰብ ለሁለተኛ ጊዜ ከዓለም አቀፍ የሸቀጦች ዋጋ ንረት ጋር በተያያዘ የሀገር ዉስጥ ዋጋ በ2002 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 7.3 በመቶ በ2003 የበጀት ዓመት ወደ 38 በመቶ፣ በ2004 በጀት ዓመት 20.8 በመቶ ከፍ በማለቱ ትክክለኛዉ የዉጭ ምንዛሪ ተመን አመልካች በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 121.2 በ13.5 በመቶ ከፍ ብሎ በ2004 በጀት ዓመት 139.4 ደርሶ ነበር፡፡ ይህም በወጪ ንግዳችን ተወዳዳሪነት ላይ የራሱን አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

የወጪ ንግዱ መቀዛቀዝ በመንግሥትና በግል ዘርፍ የኢንቨስትመንት ግብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር ተግዳሮቱን ለመቋቋም ጥንቃቄ የተሞላበት የዉጭ ምንዛሪ ፍሰት (foreign exchange cashflow) አስተዳደር እና የዉጭ ምንዛሪ ኢንተርቬንሽን (forex intervention) የመሳሰሉ የፖሊሲ እርምጃዎችን በመውሰድ የዉጭ ምንዛሬ ገበያውን የተረጋጋ ለማድረግ ተችሏል፡፡ የተወሰዱት የፖሊሲ ርምጃዎች ውጤታማ የነበሩ ለመሆናቸዉ ዋናው ማሳያ የዉጭ ምንዛሬ ጥቁር ገበያ ፕሪሚየም በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 6.1 በመቶ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 4.2 መውረዱ ነዉ፡፡ ይህም ወደ ጥቁር ገበያ የሚሄደውን የዉጭ ምንዛሪ ፍሰት ለመግታት አስችሏል፡፡ በተጨማሪም የውጭ ምንዛሬ ክምችታችን በዕቅዱ መሠረት 2.2 ወራት የገቢ ምርት ወጭ መሸፈን የሚያስችል በማድረግ ባለፉት አራት ዓመታት ማቆየት ተችሏል፡፡

### 1.1.3 የሀገር ውስጥ ቁጠባን የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ 15 በመቶ ማድረስ

የአምስት ዓመቱን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠይቀው የኢንቨስትመንት መጠን ከፍተኛ ስለነበረ ከዚህ ጋር በተያያዘ አንዱና ዋናው ፈታኝ ጉዳይ ለኢንቨስትመንቱ መሸፈኛ የሚያስፈልገው የአገር ውስጥ ፋይናንስ ግኝት ነው፡፡ በተለይም የሀገሪቱ የቁጠባ መጠን በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝ በመሆኑ ልማቱን ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን ፋይናንስ ለማቅረብ የዜጎችን ቁጠባ ባህል ማሳደግ

ይጠይቃል። በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ በተቀመጠው ግብ መሠረት በዕቅዱ መጨረሻ ዓመት የአገር ውስጥ ቁጠባ መጣኔን ወደ 15 በመቶ ማድረስ ነበር።

**ሀ) የግል ቁጠባን ማሳደግ**

ይህንን የአገር ውስጥ ቁጠባን የማሳደግ ግብ ለማሳካት በዋናነት የግል ዘርፉን ቁጠባ ማሳደግ የማይተካ ሚና እንዳለው በዕቅዱ በግልፅ ተቀምጧል። ከዚህም አኳያ በአለፉት አራት ዓመታት በርካታ እርምጃዎች ተወስደዋል። ከነዚህም መካከል የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል ለማሳደግ እየተደረጉ ያሉ የማስተማርና የማነሳሳት እንቅስቃሴዎች፣ የፋይናንስ አገልግሎቶች የሚሰጡባቸውን ተቋማት ማስፋፋት፣ ኢኮኖሚ ዕድገቱ ያመጣው የገቢ ለውጥ፣ የግል ማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት መዘርጋት፣ የመንግሥት የማህበራዊ ዋስትና ሽፋንን ይበልጥ ማጠናከር፣ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቁጠባ ቦንድና ሌሎች በጅምር ላይ ያሉ የቁጠባ መሳሪያዎች (የመኖሪያ ቤት ቁጠባ ፕሮግራም፣ የኢንቨስትመንት መሣሪያዎች የቁጠባ ፕሮግራም) እና የመንግሥት ወጪን በዋነኝነት የካፒታል ክምችት ለሚፈጠር የኢንቨስትመንት ወጪ በመመደብ በቁጠባ ለታለመለት ዓላማ ማዋል ዋና ዋናዎች ናቸው።

በእነዚህ ማሻሻያዎች ሳቢያ ባለፉት አራት ዓመታት ተስፋ ሰጪ ውጤት መገኘት ጀምሯል። በብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንት መረጃ መሠረት የቁጠባ መጣኔ በ2002 ከነበረበት 9.5 በመቶ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 22.5 በመቶ አድጓል። በፋይናንስ ቁጠባ ረገድ አበረታች ውጤት የተመዘገበ ሲሆን አጠቃላይ የፋይናንስ ቁጠባ በ2002 ከነበረበት ብር 98.4 ቢሊዮን በ2006 ብር 322 ቢሊዮን ደርሷል። ከዚህም ውስጥ በባንኮች የተሰበሰበው ቁጠባ 89.8 በመቶ (ብር 289.6 ቢሊዮን) ይሸፍናል። በባንኮች በኩል ለተመዘገበው ውጤት ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው የባንኮች ቅርንጫፍ መስፋፋት ሲሆን በአለፉት አራት ዓመታት የባንኮች ቅርንጫፍ ብዛት በየዓመቱ በአማካይ በ34 በመቶ እያደገ በ2002 የበጀት ዓመት ከነበረበት 681 በ2006 በጀት ዓመት ማገባደጃ ላይ 2208 ሊደርስ ችሏል። የንግድ ባንኮች የሰበሰቡት ተቀማጭ መጠንም በአንደኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጀመሪያ ዓመት ከነበረበት ብር 95.8 ቢሊዮን በመነሳት በ2006 መጨረሻ ላይ ብር 289.6 ቢሊዮን ሊደርስ ችሏል። በተመሳሳይ ጊዜ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ተቀማጭ ከብር 2.7 ቢሊዮን ተነስቶ ብር 11.8 ቢሊዮን ደርሷል። በመሆኑም የንግድ ባንኮችና አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሰበሰቡት የፋይናንስ ቁጠባ ከአጠቃላይ ፋይናንስ ነክ ቁጠባ ያለው ድርሻ በጣም ከፍተኛ ነው።

በጡረታ ማስተካከያው ከተገኘው ቁጠባም በመንግሥት ግምጃ ቤት ሠነድ ላይ የዋለው ብር 18.3 ቢሊዮን ያህል ደርሷል። በ2006 በጀት ዓመት ማገባደጃ ላይ የመንግሥት እና የግል ድርጅቶች ሠራተኞች በድምሩ የብር 18.3 ቢሊዮን የግምጃ ቤት ሠነዶች ክምችት ይዘዋል።

ምንም እንኳን በመጀመሪያው የምዝገባ ወቅት የነበሩት ተቀማጮች ከሌሎች የቁጠባ ሂሳቦች የተዛወሩ ቢሆንም ወደኋላ ላይ በቤቶች ቁጠባ የተሰበሰበው ተቀማጭ ግን ከፍጆታ የተቀነሰ ቁጠባ እንደሆነ ይታመናል፡ ፡ በዚህ ፕሮግራም መሠረትም የተሰበሰበው ተቀማጭ በህዳር ወር መጨረሻ ላይ ብር 11 ቢሊዮን ደርሷል።

ለመንግሥት እና የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ከተደረገው የቦንድ ሽያጭም እስከ ህዳር ወር መጨረሻ ብር 3.2 ቢሊዮን ተሰብስቧል። አጠቃላይ ከቦንድ ሽያጭ የተሰበሰበ ገንዘብ ብር 5.5 ቢሊዮን ደርሷል።

የፋይናንስ ነክ ቁጠባዎች ከላይ እንደተጠቀሰው በከፍተኛ መጠን በመጨመራቸው የተነሳ ለኢንቨስትመንትና ለንግድ አገልግሎቶች የተሰጡት ብድሮች በከፍተኛ መጠን አድገዋል። ለምሣሌ በ2002 በጀት ዓመት በአጠቃላይ ለኢኮኖሚ ዘርፎች የተሰጠ ብድር ክምችት ብር 72.0 ቢሊዮን ሲሆን በ2006 በጀት ዓመት በ250 በመቶ በማደግ ብር 251.8 ቢሊዮን ደርሷል።

### ለ) የመንግሥት ቁጠባን ማሳደግ (Fiscal Policy)

በሌላ በኩል በልማት ዕቅዱ ዘመን ተግባራዊ የሆነው የፊስካል ፖሊሲ ተፈላጊውን የፋይናንስ ምንጭ እንዲያመነጭ የታክስ ገቢን ማሳደግ፣ የወጪ አመዳደብ በካፒታል ኢንቨስትመንት እና ድህነትን በመቀነስ ረገድ ቁልፍ ሚና ባላቸው ዘርፎች የሚመደበው በጀት ከታችኛው የአስተዳደር አካል ጀምሮ በየደረጃው በየዓመቱ ትልቁን ድርሻ የያዘና የማይዋዥቅ እንዲሆን የማድረግ መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የፊስካል ፖሊሲው ዓላማም የወጪ በጀትን በሂደት በሀገር ውስጥ ገቢ በመሸፈንና የበጀት ጉድለት ዝቅተኛ እንዲሆን በማድረግ ለዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ምቹና የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ማስፈን ነው፡፡

በመሆኑም መንግሥት የሚከተለው የፊስካል ፖሊሲ ተፈላጊውን የፋይናንስ ምንጭ የሚያመነጭ፣ የተገኘውን የፋይናንስ አቅም ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሀዊ ዕድገትን ለማስመዝገብ የተያዘውን ስትራቴጂያዊ አቅጣጫ በተከተለ መልኩ ስራ ላይ ለማዋል ተሞክሯል፡፡ በዚሁ መሠረት ባለፉት አራት ዓመታት በሥራ ላይ ያለውን የታክስ ፖሊሲ አስተዳደር ስርዓቱን ይበልጥ በማሻሻል የሀገር ውስጥ ገቢን በማሳደግና ለልማት የሚያስፈልገውን ፋይናንስ በውስጥ አቅም ለመሸፈን እየተደረገ ያለውን ጥረት በማስቀጠል ረገድ አበረታች ውጤት የተመዘገበባቸው ዓመታት ናቸው፡፡

አጠቃላይ የመንግሥት ወጪ በአብዛኛው የዕድገት መሠረት የሆኑ በድህነት ተኮር ዘርፎችና የመሠረተ ልማት ማስፋፋት ላይ የዋለ ነው፡፡ እንዲሁም የመንግሥት የበጀት ጉድለት አሸፋፈን አስመልክቶ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ዘመን ታሳቢ የተደረገው ጥብቅ የፊስካል ፖሊሲ በመተግበር ዓመታዊ የጉድለት መጠን ከአጠቃላይ ኢኮኖሚው 3 በመቶ በላይ እንዳይሆን እና በአማካይ 2 በመቶ አካባቢ እንዲሆን የተቀመጠውን ግብ የተከተለ ነበር፡፡

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ዘመን በመንግሥት ገቢ ረገድ በዋነኛነት ትኩረት የተደረገው የሀገር ውስጥ ገቢ የማመንጨት አቅምን በማጎልበት ለልማት የሚያስፈልገውን ፋይናንስ በወሳኝነት በውስጥ አቅም መሸፈን መቻል ሲሆን የውጭ እርዳታ በማፈላለግ ወሳኝ ለሆኑ የመንግሥት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ማዋል ነው፡፡ ይህንንም መሠረት በማድረግ በተደረገው የዕቅድ ትግበራ ባለፉት አራት የበጀት ዓመታት የመንግሥት ጠቅላላ ገቢ እርዳታን ጨምሮ በየዓመቱ በአማካይ ከ20 በመቶ በላይ ዕድገት የተመዘገበ ሲሆን አማካይ ዓመታዊ የመንግሥት ገቢው እርዳታን ጨምሮ ብር 124.15 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ ለዚህም እየተተገበረ ባለው የታክስ ማሻሻያ ፕሮግራም ከታክስ የሚገኘው ገቢ ማደግ ከሀገር ውስጥ ለሚመነጨው የመንግሥት ገቢ ማሻሻያ ከፍተኛውን ሚና ተጫውቷል፡፡ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ ባለፉት አራት ዓመታት የ29 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ አማካይ ብር 110.58 ቢሊዮን ገቢ ሲሰበሰብ ከጠቅላላው ገቢ ያለው ድርሻ እየጨመረ በመምጣት 89 በመቶ ደርሷል፡፡ ያለፉት አራት ዓመታት የአገር ውስጥ ገቢ አፈፃፀም ዕድገት እየጨመረ መምጣቱ የመንግሥት ገቢ ከጊዜ ወደ ጊዜ በራስ አቅም ላይ እየተመሠረተ መምጣቱን ያሳያል፡፡

ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ በዕቅዱ መጨረሻ ዓመት እና የ5 ዓመቱ አማካይ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ ያለው ድርሻ በቅደም ተከተል 20.4 በመቶ እና 19.2 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሎ ሲተገበር ቆይቷል፡፡ አፈፃፀሙ ሲታይ አማካይ ጠቅላላ የመንግሥት ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ ያለው ድርሻ 15.8 በመቶ የደረሰ ሲሆን በዕቅዱ መጨረሻ ዓመት የተቀመጠውን የ20.4 በመቶ ድርሻ እና የ19.2 አማካይ ድርሻ ለማሳካት አይቻልም፡፡ ለዚህም በቀጣይ የሀገር ውስጥ ገቢን በተለይ የታክስ ገቢን ለማሳደግ የተጀመሩትን ፕሮግራሞች አጠናክሮ መቀጠል ይገባል፡፡


የታክስ ገቢን በሚመለከት ባለፉት አራት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዓመታት የታክስ አሰባሰቡ በአማካይ በየዓመቱ የ32.7 በመቶ ዕድገት ያስመዘገበ ሲሆን ከጠቅላላ የመንግሥት ገቢ ያለው ድርሻ በ2003 ከነበረበት 69 በመቶ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 84 በመቶ አድጓል፡፡ በሌላ በኩል ከታክስ የተሰበሰበው ገቢ በአማካይ 87 በመቶ ድርሻ በማስመዝገቡ ለሀገር ውስጥ ገቢ ዕድገት ከፍተኛውን ድርሻ አበርክቷል፡፡ በዚህም የመንግሥት ገቢ በአብዛኛው በአስተማማኝ የታክስ የገቢ ምንጭ ላይ እየተመሰረተ መምጣቱን የሚያመለክት ነው፡፡ በሌላ በኩል ለታክስ ገቢ መጨመር ከአገር ውስጥ ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች አማካይ

ዕድገት ከሌሎች የሀገር ውስጥ ታክስ ምንጮች የበለጠ ሲሆን ለዚህም የአገር ውስጥ የፍጆታ ታክሶች ለመንግሥት ገቢ እያደረጉት ያለው አስተዋፅኦ እያደገ መምጣቱንና የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም እየጎለበተ መምጣቱንም ይጠቁማል፡፡ ለተገኘው የተሻለ የታክስ አሰባሰብ በስራ ላይ የዋሉት የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የቁርጥ ግብር አስተዳደር፣ የተጠናከረ የታክስ ኦዲትና የካሽ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀም፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሥርዓት መጎልበት፣ ሰፊ የታክስ ክፍያ የግንዛቤ ትምህርትና ቅስቀሳ መካሄድ እንዲሁም አስፈጻሚ ክፍሎች በሰው ኃይል አቅምና በቁሳቁስ በመታገዛቸው ለተገኘው መልካም አፈጻጸም አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

ባለፉት አራት የትግበራ ዓመታት (2003-2006) የተሰበሰበው አገራዊ አማካይ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 12.1 በመቶ ሲሆን ከዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የ15 በመቶ የአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ ግምት እንዲሁም ከሰሀራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገራት አማካይ 15.2 በመቶ አፈጻጸም አንጻር ሲታይ ተጨማሪ የታክስ አስተዳደር ጥረት መደረግ እንዳለበት ይጠቁማል፡፡

በውጭ እርዳታ ግኝት ረገድ በ2003 በጀት ዓመት ብር 16.5 ቢሊዮን የተገኘ ሲሆን በቅደም ተከተል በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመት ከውጭ እርዳታ የተገኘው ገቢ ወደ ብር 12.8 ቢሊዮን እና ብር 13.1 ቢሊዮን ዝቅ ብሏል፡፡ በ2006 በጀት ዓመት ከልማት አጋሮች በመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ የተገኘውን ብር 2.5 ቢሊዮን ጨምሮ ከውጭ አገር እርዳታ ብር 11.9 ቢሊዮን ገቢ ተገኝቷል፡፡ ይህም የፋይናንስ ምንጭ በአብዛኛው የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ከማሳካት አንፃር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላላቸው የወጪ ዘርፎች በቀጥታ በልማት አጋሮች የሚመደብ የፋይናንስ አይነት ነው፡፡ ባለፉት አራት ዓመታት የውጭ እርዳታ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ እየቀነሰ የመጣ ሲሆን ድርሻው በ2003 ከነበረው 3.2 በመቶ በ2006 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 1.1 በመቶ ዝቅ ሊል ችሏል፡፡ በአንድ በኩል ሀገሪቱ የምታገኘው የነፍስ ወከፍ እርዳታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ሲያሳይ በሌላ በኩል የፊስካል አፈጻጸሙ ደረጃ በደረጃ ታክስና ታክስ ካልሆኑ የመንግሥት ገቢ ምንጮች መሠረት ላይ የቆ መሆኑን ያመለክታል፡፡

**ሥዕል 1.3 የመንግስት ገቢና ወጪ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ (በመቶኛ)**




ባለፉት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት ሥራ ላይ የዋለው የፊስካል ፖሊሲ የመንግሥትን ገቢ ለማሳደግ ትኩረት ከመስጠት ባሻገር የተሰበሰበው ገቢ የመንግሥትን ኃላፊነት ለመወጣት በሚያስችሉ ድህነትን ለመቀነስ፣ በመሠረተ ልማት ግንባታና መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ በሚረዱ የወጪ ዘርፎች እንዲውል ተደርጓል፡፡ በዚህም የመንግሥት የበጀት ድልድል እና የወጪ አስተዳደር በዋነኛነት ዕድገትን በሚያፋጥኑና ድህነትን ለመዋጋት ቁልፍ ሚና ባላቸው ዘርፎች ላይ የሚያተኩር ሆኖ የመደበኛ ወጪን ከሀገር ውስጥ


ከሚሰበሰብ ገቢ የመሸፈን እና የካፒታል ወጪን ደረጃ በደረጃ ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ገቢ ለመሸፈን የሚያስችል መርህን የተከተለ ነው፡፡

በኢንቨስትመንት ረገድ መንግሥት ባለፉት አራት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት ጠቅላላ የመንግሥት ወጪ በአማካይ በ26.5 በመቶ እያደገ የመጣ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ በተለይ ለድህነት ተኮር ዘርፎች የዋለው ወጪ በአማካይ በ27.9 በመቶ አድጓል፡፡ በዚህም በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት ጠቅላላ የመንግሥት ወጪ 93.8 ቢሊዮን በ2006 በጀት ዓመት ብር 185.5 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ ከዚህ ወጪ ውስጥ ባለፉት አራት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት በአማካይ 58 በመቶው ለካፒታል ወጪ የዋለ ሲሆን፣ ቀሪው 42 በመቶ ደግሞ ለመደበኛ ወጪ መሸፈኛ ውሏል፡፡ ይህም የወጪ ድልድሉ የፊስካል ፖሊሲውን ተከትሎ ተጨማሪ ሃብት ለሚፈጥሩ የኢንቨስትመንት ሥራዎች የዋለ መሆኑን ያሳያል፡፡ አገራችን ዘርፈ ብዙ የልማት እንቅስቃሴዎችን በማድረግ የዜጎችን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሕይወት በማሻሻል ድህነትን ለማጥፋት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ ላይ ትገኛለች፡፡ ለዚህም አላማ መሳካት ለግሉ ዘርፍ ልማትና ዕድገት አመቺ ሁኔታዎችን ከመፍጠር ባሻገር ድህነት ተኮር በሆኑ የልማት ተግባራት ላይ በስፋት እየሰራች ትገኛለች፡፡

### ሐ) የሀገር ውስጥ ቁጠባ የኢንቨስትመንት ሽፋን

የሀገር ውስጥ ቁጠባ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ከዕቅዱ በላይ የ7 መቶኛ ነጥብ (percentage point) ከፍ ብሎ 22 በመቶ በ2006 በጀት ዓመት መድረሱ ከፍተኛ አፈፃፀም እንደሆነ ቢታወቅም ከኢንቨስትመንት ሽፋን አንፃር አሁንም ሰፊ ክፍተት እንዳለ ያመለክታል፡፡ በኢኮኖሚ ውስጥ የተደረገው የኢንቨስትመንት መጠን ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2002 ከነበረበት 24.7 በመቶ በ2006 ወደ 40.3 በመቶ አድጓል፡፡ ይህ የኢንቨስትመንት መጣኔም በዕቅዱ ከተቀመጠው ግብ በላይና መልካም የሚባል ቢሆንም ችግሩ አብዛኛው በአገር ውስጥ ቁጠባ ገንዘብ ሳይሆን በውጪ አገር ቁጠባ ገንዘብ መሸፈኑ ነው፡፡ በመሆኑም ለኢንቨስትመንት ሊውል የሚችል የሀገር ውስጥ ቁጠባ በበቂ መጠን ከማሰባሰብ አንጻር ብዙ የሚቀር እንዳለ እና ከዚህ አንጻር የፋይናንስ እጥረት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ አንዱ ዋና ፈተና እንደነበር መመልከት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የዜጎችን ቁጠባ ከፍ ለማድረግና በዕቀድ ዓመቱ ውስጥ የታየውን አበረታች እንቅስቃሴ አጠናክሮ ማስቀጠል በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ይሆናል፡፡

*ሥዕል 1.4 ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቁጠባና ኢንቨስትመንት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ በመቶኛ*




ቁጠባንና ኢንቨስትመንትን በሚመለከት እዚህ ላይ መወሳት ያለበት አንዱ ጉዳይ ቁጠባ በብር፣ በመጠን ማደጉ ብቻውን በቂ አይሆንም፡፡ የልማታችንን ማነቆ ለመፍታት በውጭ ምንዛሬ ክምችት መደገፍ አለበት፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ሁኔታ ኢንቨስትመንት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት የሚያስከትል በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ከሌለ የሀገራችንን ኢንቨስትመንት በራሳችን ወቅት፣ ፍጥነትና መጠን ለመፈጸም አዳጋች ይሆናል፡፡

ሌላው መወሳት ያለበት ጉዳይ የኢንቨስትመንት መጠን ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ውጤታማ ኢንቨስትመንት መኖሩን ማረጋገጥም ተገቢና አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም ጥራት ያለው የፕሮጀክቶች ዝግጅት፣ ቀልጣፋ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ፣ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ብቃት ወዘተ. ትኩረት ማድረግ ይገባል፡፡

**መ) ባንኮችን በማቀናጀት የልማት ፕሮጀክቶችን የሚደግፉበትን አሠራር መዘርጋት**

ባንኮች በተናጠል ያላቸው አቅም ውስን በመሆኑ እርስ በእርስ በመቀናጀት ለኢኮኖሚ ዕድገት ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችሉ ማመቻቸት እንደሚገባ በኢንዱስትሪ ስትራቴጂ ሰነድ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ መካከለኛና ታላላቅ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግ የሚጠየቀውን ብድር ብቻውን ማቅረብ ስለማይችል ከሌሎች ባንኮች ጋር በመቀናጀት የብድር ፍላጎትን ማሟላት የሚቻልበት ሁኔታ መፍጠር ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ ሊጠቀስ የሚችለው ባንኮች ከሚያበድሩት ብድር ውስጥ 27 በመቶ በሚሆነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሰነድን (NBE Bill) የሚገዙበትን ሁኔታ በማመቻቸት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በኩል ፈሰስ ተደርጎ የኢትዮጵያ ልማት ባንክን የማበደር አቅም ማጠናከር የተቻለበት ሁኔታ መፈጠሩ ሲሆን በዚህም ስትራቴጂም የግል ባንኮችን ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጋር ማቀናጀት ተችሏል፡፡ እስከ የካቲት 2007 ዓ.ም. በዚህ ፕሮግራም ከ31 ቢሊዮን ብር በላይ ማሰባሰብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪ ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለኢንቨስትመንት የሚያስፈልገውን ፋይናንስ ሲያቀርብ ንግድ ባንኮች (የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ጨምሮ) የሥራ ማስኬጃ በማቅረብ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ያደርጉ የነበረ ቢሆንም የንግድ ባንኮቹ ከልማት ባንክ ጋር በመወያየትና በመናበብ ያልተሰራና በተናጠል የተፈፀመ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ በመጀመሪያው የዕቅድ ዘመን ክፍተቶች ነበሩበት ማለት ያስችላል፡፡ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በቅንጅት እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

**1.1.4 የወጪ ንግድ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ 22.5 በመቶ ማድረስ**

ባለፉት አራት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዓመታት የውጭ ኢኮኖሚን ለማሳደግ በዋናነት የወጪ ንግድን ለማሳደግና የገቢ ንግድን በአገር ውስጥ በማምረት የመቀነስ ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ለማድረግ በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በመሆኑም የ2007 የበጀት ዓመት ግምትን ጨምሮ የወጪ ንግድ አገልግሎትን ጨምሮ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 12.4 በመቶ ብቻ ሆኗል፡፡ ይህም በ2007 ይደረስበታል ተብሎ የተቀመጠውን የ22.5 በመቶ ድርሻ ማሳካት እንደማይቻል ይጠቁማል፡፡ በሌላ በኩል ጠቅላላ ገቢ ንግድ አገልግሎትን ጨምሮ ለጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በአማካይ 30.4 በመቶ ነበር፡፡ በመሆኑም የሀብት ክፍተቱ በአማካይ -18.0 በመቶ ሲሆን በ2007 የሀብት ክፍተቱን ወደ -13.1 በመቶ ለማጥበብ የተያዘውን ዕቅድ ማሳካት እደማይቻል አፈፃፀሙ ያሳያል፡፡ ይህም በዋናነት ከሸቀጦች ወጪ ንግድ የሚገኘው ገቢ በታቀደው መሠረት ባለመፈፀሙ ነው፡፡ ባለፉት አራት ዓመታት የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢ አፈፃፀም በአማካይ 3.1 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሆኖአል፡፡ ነባሮቹ ወጪ ንግድ ምርቶች የመጠን ድክመት ታይቶባቸዋል፤ በሌላ በኩል አዳዲስ ምርቶች ወደ ወጪ ንግዱ አለመቀላቀላቸውን የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በዋናነት የወጪ ንግድን ለማሳደግ እንደ ስኳርና ሌሎች የኢንዱስትሪ ውጤቶች ኤክስፖርት አለመደረጋቸው ለአፈፃፀሙ ማነስ ዋና ምክንያቶች ሲሆኑ በተለይም የማምረት አቅምና ሀገሪቱ በዋናነት ወደ ውጭ በምትልካቸው ዕቃዎች (ቡናና ወርቅ) የተከሰተው የዓለም ገበያ የዋጋ መቀነስ በሌላ በኩል ባለፉት አራት አመታት ወደ ውጭ ከሚላኩ ምርቶች መካከል ቡና (25.6 በመቶ) አሁንም ቀዳሚ ስፍራውን ሲይዝ ወርቅ (17.2 በመቶ) እና የቅባት እህሎች (15.5 በመቶ) ቀጥለው ይገኛሉ፡፡ ይህም በዋናነት በሀገሪቱ የኤክስፖርት ምርቶች ውስጥ ምንም አይነት መሠረታዊ ለውጥ እንዳልታየና በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡ በስኳር፣ ቆዳ፣ ጨርቃጨርቅና የሥጋ ወጪ ንግድ ዙሪያ የተጣሉት ግቦች እንዳልተሳኩ መረዳት ይቻላል፡፡ የሆርቲካልቸር ኤክስፖርትም አፈፃፀም በዕቅዱ ከተቀመጠው ግብ አንፃር ተመጣጣኝ ዕድገት አላሳየም፡፡


በአጠቃላይ ባለፉት አራት ዓመታት በውጭ ንግድ አፈፃፀም ዙሪያ በርካታ ችግሮች የታዩ ሲሆን በተለይም የሀገሪቱ የማምረት አቅም አናሳ መሆን አንዳንድ የወጪ ምርቶችን የጎዳ ሲሆን የተጠበቁት የማኑፋክቸሪንግ ውጤቶችና ሌሎች አዳዲስ ምርቶችን በስፋት ለውጭ ገበያ ማቅረብ አለመቻሉና የወጪ ንግድ ስብጥሩ ደካማ መሆን ዋና ዋናዎቹ ነበሩ፡፡ የማምረት አቅምን ማሳደግ፣ አለም አቀፍ የገበያ እድሎችን መጠቀምና እያደገ ያለውን የአምራች ዘርፍ ወደ ወጪ ንግድ እንዲገባ ማድረግና ሌሎች የቁጥጥርና ክትትል ተግባራትን በሚገባ ማከናወን ተገቢ እንደሆነ የተገኘው የአፈፃፀም ተሞክሮ ይጠቁማል፡፡

የሸቀጦች ገቢ ንግድን በተመለከተ ባለፉት አራት ዓመታት በአማካይ በዓመት 11.13 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚያወጡ ሸቀጦች ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ሲሆን በዋናነት የካፒታል ዕቃዎች፣ የፍጆታ ዕቃዎች፣ የኢንዱስትሪ ዕቃዎችና ነዳጅ ላይ የወጣ መሆኑን የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ነገር ግን ለሌሎች አላቂና አላቂ ላልሆኑ የፍጆታ ዕቃዎች የወጣው ወጪ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በመሆኑም እነዚህን ሸቀጦች በሀገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሬን ለማዳን የሚያስችል የገቢ ሸቀጦችን የመተካት (import substitution) ስትራቴጂ በዕቅዱ በተለዩት አግባብ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ በተለይም የውጭ አገር ሸቀጦች ከኢኮኖሚ ዕድገቱ ጋር ተያይዞ በአገር ውስጥ ተፈላጊነታቸው ስለሚጨምር ወደፊትም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

የንግድ ሚዛን ወደ ውጭ በሚላኩና ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ሸቀጦች መካከል ያለውን ልዩነት የሚያሳይ ሲሆን ባለፉት አራት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት የአገራችን የወጪ ንግድ ምርት መጠን አነስተኛ መሆን፣ መሠረቱ ጠባብና በአብዛኛው በግብርና ምርቶች ላይ ጥገኛ በመሆኑ ምክንያት ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የገቢ ዕቃዎች መጠን መሸፈን ባለመቻሉ ጉድለቱ እየሰፋ እንዲሄድ ምክንያት ሆኗል፡፡ በዚህም በ2003 ዓ.ም. የነበረው የ5.5 ቢሊዮን የንግድ ሚዛ ጉድለት በ2006 በጀት ዓመት ወደ 10.5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሊሰፋ ችሏል፡፡ በመሆኑም ባለፉት አራት ዓመታት ከሸቀጦች ወጪ ንግድ የተገኘው የውጭ ምንዛሬ የሸቀጦች የገቢ ንግድ ወጪን በ2003 33.3 በመቶ እና በ2006 23.7 በመቶ ብቻ በመሸፈን በተከታታይ እየቀነሰ መምጣቱን ያሳያል፡፡ ይህም ባለፉት አራት ዓመታት አማካይ ከወጪ ንግድ የተገኘው የውጭ ምንዛሬ የሸቀጦች የገቢ ንግድ ወጪ ሽፋን 27.5 በመቶ አካባቢ ብቻ ነው፡፡

በሌላ መልኩ ባለፉት አራት ዓመታት በድምሩ 5.01 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ንጥር የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰት የተመዘገበ ሲሆን በ2003 1.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣ በ2004 1.1 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣ በ2005 1.2 በሊዮን የአሜሪካን ዶላር እና በ2006 1.5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር አፈጻጸም ተመዝግቧል፡፡ በመሆኑም የ2006 በጀት ዓመት የሀገሪቱ የክፍያ ሚዛን 91.4 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጉድለት አሳይቷል፡፡ ይህም በ2005 የበጀት ዓመት ከተመዘገበው የ114.2 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጉድለት እና በ2004 ከተመዘገበው 972 ሚሊዮን ጉድለት ጋር ሲነፃፀር መሻሻል አሳይቷል፡፡ ለዚህም በዋናነት የወጭ ንግዱ ገቢ፣ የአገልግሎት ወጭ ንግድ ገቢ፣ የግል ሐዋላ እና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ካለፈው ዓመት አንፃር የተሻለ ዕድገት በማሳየታቸው ለጉድለቱ መጥበብ አጋዥ ሆኗል፡፡ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ባለፉት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዓመታት የሀገራችንን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ለማሳደግ በሁሉም ዘርፍ ርብርብ ቢደረግም ኢኮኖሚው የሚፈልገው የገቢ ዕቃዎች መጠን በየጊዜው እያደገ በመምጣቱ በውጭ ምንዛሬ ክምችት ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ አልቀረም፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበረው የውጭ ምንዛሬ ክምችት 2.3 ያህል ወራት የገቢ ሸቀጦች ሊሸፍን የሚችል ነው፡፡

ሥዕል 1.5 የወጪና የገቢ ንግድ አገልግሎትን ጨምሮ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ በመቶኛ




### 1.1.5 የማክሮ ኢኮኖሚክ ፖሊሲ ማኔጅመንት አቅም ግንባታ አፈፃፀም

#### ሀ) ሀገራዊ የመካከለኛና የረጅም ዘመን የልማት ዕቅድ ዝግጅት አቅም ግንባታ አፈጻጸም

የመካከለኛና የረጅም ዘመን የልማት ዕቅድ ዝግጅትና የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ በብሔራዊ ደረጃ ለመምራትና ለማስተባበር ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን በ2005 ተቋቋሟል፡፡ ይህን ተከትሎ የልማት ዕቅድ ዝግጅት፣ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ አሰራር ሥርዓትን ከማጎልበት አንጻር የመካከለኛና የረዥም ዘመን ጠቋሚ ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ዝግጅትና ክትትልን በሞዴል ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ለማስቻል በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የባለሙያዎችን የመፈፀም አቅም ከመገንባትና ከማጠናከር አንጻር በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ የኢኮኖሚ ሞዴል እና የመካከለኛና የረዥም ዘመን ጠቋሚ የልማት ዕቅድ አዘገጃጀት ተግባርን በብቃት ለማዘጋጀትና ለመምራት እንዲቻል የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከአ.አ. ዩኒቨርሲቲ ጋር በአደረገው ስምምነት መሠረት ባለሙያዎች በኢኮኖሚክ ሞዴሊንግና ፎርካስቲንግ የሁለተኛ ዲግሪ ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል የዕቅድ ክትትልና ግምገማ ሥርዓትን ለማጠናከር በየአምስት ዓመቱ የሚዘጋጀውን የኑሮ ደህንነትና የድህነት ሁኔታ ለመተንተን የሚያስችል አቅም ለመፍጠር ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

#### ለ) የሞኒተሪ ፖሊሲ ማኔጅመንት አቅም ግንባታ አፈፃፀም

በመጀመሪያ የዕቅድ ዘመን ትኩረት ተሰጥቶት የተሠራው የማክሮ ኢኮኖሚ ማኔጅመንት አቅምን የማጠናከር ሥራ ነው፡፡ በዚህ ረገድ አንደኛ፣ የጥናትና የፖሊሲ ምርምር ሥራን ለማሳደግ በዘርፉ የሚገኙ በዚህ ሥራ የተሰማሩ ሠራተኞችን አቅም ለማጠናከር ከለጋሽ ሀገሮች በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር ከገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከ50 የማያንሱ ሠራተኞችን በሁለተኛ ዲግሪ ድርጅቶቹ በመረጧቸው ዘርፎች (አሁን በመማር ላይ ያሉትን ጨምሮ) በሦስት ዙር ማሰልጠን ተችሏል፡፡ በተጨማሪ ከዓለም የገንዘብ ድርጅትና ከዓለም ባንክ ጋር በመተባበር በየዓመቱ በተለያዩ የሥልጠና መስኮች ሠራተኞች አጫጭር ሥልጠናዎች እንዲያገኙ እየተደረገ ሲሆን በዓለም ባንክ ድጋፍ የተዘጋጀውን የፋይናንስ ዘርፍ አቅም ግንባታ መርሀ ግብሩን በማሰልጠኛ ቦታ እጥረት ምክንያት በታቀደው መሠረት ማስኬድ አልተቻለም፡፡ በአጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ ማኔጅመንት ተቋማትም ሆነ የፋይናንስ ተቋማት በኢንዱስትሪ ስትራቴጂ ሰነድ ላይ የተቀመጠውን ተልዕኮና የዕድገትና ትራንስፎረሜሽን ዕቅድ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የማስፈፀም አቅም ያለመጠናከር ተግዳሮቶች ነበሩአቸው፡፡ በተጨማሪም በዕቅድ ዘመኑ ከፍተኛ ተግዳሮት የነበረው በመንግሥት የፋይናንስ ተቋማት (የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን ጨምሮ) ከፍተኛ የሰው ኃይል ፍልሰት መታየቱ ነበር፡፡ መንግሥት ይህንን ችግር ለመፍታት የደሞዝ ማሻሻያ ማድረጉ ለጊዜውም ቢሆን የፍልሰቱን መጠን መግታት የተቻለበት ሁኔታን የፈጠረ ቢሆንም ማስቆም ግን አልተቻለም፡፡

## ሐ) የፊስካል ፖሊሲ ማኔጅመንት አቅም ግንባታ አፈፃፀም

የማስፈጸም አቅምን ከመገንባት አንጻር ሠራተኞች ተገቢውን ክህሎት እንዲያገኙ ለማድረግ በርካታ የአጭርና የረዥም ጊዜ ሥልጠናዎች እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ የማክሮ ኢኮኖሚ ማኔጅመንት ተግባርን በብቃት ለመምራት በአ.አ. ዩኒቨርሲቲ እና በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ድግሪ ስልጠና በቋሚነት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ሠራተኞች የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎች በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ የሠራተኞች አመለካከት እንዲሻሻል በልማታዊ መንግስት አሠራርና በመንግስት ፖሊሲዎች ላይ ያላቸው ግንዛቤ እንዲጨምር እና ደንበኛ ተኮር አገልግሎት አሰጣጥ እንዲጠናከር ስልጠናዎች የተሰጡ ሲሆን የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትን ለመናድ የሚያስችሉ ሥርዓቶችም ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡

የመንግስት ፋይናንስ አሠራርን ቀልጣፋና ዘመናዊ ከማድረግ አንጻር በርካታ ማሻሻያዎች የተደረጉ ሲሆን፣ የፕሮግራም በጀትን በፌዴራል መ/ቤቶች ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፣ እንዲሁም የቴክኖሎጂ አቅርቦትን ማሳደግ ተችሏል፡፡ በተለይም ባለፉት ዓመታት እስከ አሁን የተገነቡትን የፋይናንስ ሥርዓቶች በተሻለና በተቀላጠፈ መንገድ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል የቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር የመረጃ ሥርዓት (IFMIS) ተዘጋጅቶ በተወሰኑ የፌዴራል መሥሪያ ቤቶች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት ከፊስካል ፖሊሲው አንፃር የተሳካ የማክሮ ኢኮኖሚ ማኔጅመንት ማካሄድ የተቻለበት አፈፃፀም ነበር ማለት ይቻላል፡፡

## መ) የገቢዎችና ጉምሩክ አቅም ግንባታ አፈፃፀም

በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ፊሲካል ፖሊሲ ዓላማዎች መካከል አንዱ የአገር ውስጥ ገቢ የማመንጨት አቅምን በማጐልበት ለልማት የሚያስፈልገውን ፋይናንስ በወሳኝነት በውስጥ አቅም እንዲሸፈን ማስቻል ነበር፡፡ ይህንን ዓላማ ከማሳካት አኳያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትኩረት መስኮች የተቋሙን የማስፈፀም አቅም መገንባት፤ ዘመናዊ የታክስ የመረጃ ሥርዓትን ዝርጋታ አጠናክሮ መቀጠል፤ የደንበኞችን ትምህርትና ግንኙነትን ማሳደግ፤ የተገልጋዮች አገልግሎትና ድጋፍ፤ የታክስ ሕግን ማስከበር ነበሩ፡፡

የተቋሙን የማስፈጸም ዐቅም ለማጎልበት ለባለሥልጣኑ በመዋቅር ከሚያስፈልገው 19,269 ሠረተኞች መካከል 47.8 በመቶውን ሠራተኞች ያሟላ ሲሆን ከሰው ሀይል ልማት አኳያም የሥልጠና ፍላጎት በመለየትና የተሻለ ልምድ ያላቸውን የአገር ውስጥና የውጭ አገራት ተቋማትን በመለየት በድምሩ ለ9,637 አመራሮች እና ፈፃሚዎች የተለያዩ የአጭርና የረዥም ጊዜ ሥልጠና እና ትምህርት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከታክስ አሠራር ሥርዓት ማሻሻያም አኳያ **የጉምሩክ የአሰራር ሥርዓትን ለማሻሻል** አዲሱ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም (የዕቃ አወጣጥ፣ የትራንዚት፣ የመጋዘን አሰራር) በተቀረፀ ሥርዓት መሠረት በሁሉም የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ማሻሻያውን ተከትሎም የተከለሰው የጉምሩክ አዋጅ እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡ ሌላው **የአገር ውስጥ ታክስ አሠራር ሥርዓት ማሻሻያ ሲሆን** በ2005 በጀት ዓመት ተሻሽሎ የተዘጋጀ የአገር ውስጥ ታክስ አሠራር ሥርዓት እና ሕግ ማዕቀፍ የመጨረሻውን ቅርፅ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ **አደረጃጀትን ከማሻሻል አኳያ፣** ጥናቶችንና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ታሳቢ ባደረገ ስድስት አዳዲስ የታክስና የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች፤ አንድ የጉምሩክ የመቅረጫ እና አራት የጉምሩክ የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች እንዲሁም ሰባት የአገር ውስጥ የታክስ ማዕከላት ተከፍተው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

**ዘመናዊ የታክስ መረጃ ሥርዓትን አጠናክሮ ከመቀጠል አኳያ** የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን በጣት አሻራ የማስደገፍ (Biometric TIN)፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አቅርቦትንና አጠቃቀምን የማስፋፋት፣ የመረጃ ቴክኖሎጂ አቅርቦትን ማሳደግና አጠቃቀምን ማስፋፋት/በኤሌክትሮኒክ ግብርን ማሳወቅ፣ የተቀናጀ የመንግሥት የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ወደ ክልሎች የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች ማስፋትን አጠናክሮ መቀጠል (SIGTAS Regional Deployment)፣ የኤሌክትሮኒክስ የተሽከርካሪ የመንገድ መቆጣጠሪያ መሳሪያ ትግበራ መከታተል (Electronics Cargo Tracking)፣ የኤሌክትሮኒክስ የዕቃ ፍተሻ መሣሪያ ተከላ

(Scanning Machine) ማጠናቀቅ፣ የጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ ትግበራ፣ የተገልጋዮች የጥሪ ማዕከል ትግበራ፣ የጉምሩክ መረጃ አስተዳደር ሥርዓትን (ASYCUDA++) ወደ ተሻለ አቅም ማሳደግና የአንድ መስኮት አገልግሎት ሥርዓት (Single Window) ፕሮጀክት ትግበራ እየተካሄደ ነው፡፡

**የደንበኞች ትምህርትና ግንኙነትን ከማሳደግ አንጻር** ባለፉት ዓመታት የአንድ ዓላማ እኩል ባልደረቦች ነን በሚል መሪ ቃልና በሶስት ‹‹መ›› መርህ (መማማር፣ መመካከርና መጠያየቅ) የህትመትና የኤሌክትሮኒክ ሚዲያዎችን በመጠቀም፣ ከግብር ከፋዮች ጋር የገጽ ለገጽ ውይይት እና የጋራ የምክክር መድረኮችን በማመቻቸት ግንዛቤ የማስረጽ ሥራ ተሠርቷል፡፡

**በተገልጋዮች አገልግሎትና ድጋፍ ረገድ** የግብር ከፋዮችንና የአስፈፃሚውን መብትና ግዴታዎች ያካተተ የተገልጋዮች ቻርተር ተዘጋጅቶ እንዲዳብሩ የተደረገ ሲሆን የታክስና የጉምሩክ የአሰራር ሥርዓቶቻችንና የአገልግሎት አሰጣጡን በሚያደፋፍርና ኪራይ ሰብሳቢውን በሚያገል መልኩ እንዲቃኙ እና አላሰራ ያሉ የህግ ማዕቀፎች እንዲሻሻሉና እንዲፀድቁ ተደርጓል፡፡

ከላይ ከተገለጹት በተጨማሪ ፍትሐዊ የንግድና የታክስ ሥርዓት እንዲሰፍን የሚያስችሉ የህግ ማስከበር ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ የፌደራልና የክልል መንግሥታት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት የተጣጣመ እንዲሆን ለክልል መንግሥታት እና የከተማ አስተዳደሮች የገቢ ሰብሳቢ ተቋማት አስፈላጊው ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

### 1.1.6 የሥራ ፈጠራና የድህነት ቅነሳ አፈፃፀም

የኢትየጵያ መንግስት በየአምስት ዓመቱ የድህነት ትንተና ጥናት የሚያካሂድ ሲሆን በ2003 በወጣው የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ መረጃ መሠረት ከአጠቃላይ ድህነት ወለል በታች የሚገኘው ህዝብ 29.6 በመቶ ነበር፡፡ በ2003 የወጣውን የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ መሠረት በማድረግ የተደረገው የድህነት ትንተና የ1 በመቶ ኢኮኖሚ እድገት በ1.943 በመቶ ድህነትን መቀነስ ማስቻሉ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንፃር በ2003 የበጀት ዓመት ከአጠቃላይ የድህነት መስመር በታች የነበረው የህዝብ መጣኔ (29.6 በመቶ) የነበረው የህዝብ ቁጥር ባለፉት አራት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዓመታት ከተመዘገበው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትና ማህበራዊ ልማት አንፃር በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀንስና ከአጠቃላይ ድህነት መስመር በታች የሚኖረውን ህዝብ በ2007 በግማሽ ለመቀነስ የተቀመጠው ግብ ሊሳካ እንደሚችል የአፈፃጸም ግምት ተወስዷል፡፡

ከሥራ ዕድል ፈጠራ አኳያ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በርካታ የሰው ሀይል ማሰማራት የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ ይህም በተለይ በኮንስትራክሽን ዘርፉ በጉልህ የሚታይ ሲሆን ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፐራይዞች ሠፊ የሥራ ዕድል አስገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት ባለፉት አራት ዓመታት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች ለ4,229,202 እና በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ለ2,441,810 በአጠቃላይ ለ6,671,012 ዜጎች የስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የከተማ ሥራ አጥነት በ2002 ከነበረበት 18.9 በመቶ (ወንዶች 11 በመቶ እና ሴቶች 27.4 በመቶ) በ2005 ወደ 16.5 በመቶ (ወንዶች 10.5 በመቶ፣ ሴቶች 23 በመቶ) ዝቅ ብሏል፡፡

### 1.1.7 በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ፈተናዎችና በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

ባለፉት አራት ዓመታት ዕቅዱ በሀገራችን ሁሉም አካባቢዎች በጥሩ ሁኔታ የተተገበረ ቢሆንም በሂደቱ ፈታኝ ሁኔታዎች ማጋጠማቸው አልቀረም፡፡ ለአብነት ያህል ካጋጠሙ ፈተናዎች አንዱ የዋጋ ንረት ነበር፡፡ በዕቅዱ የመጀመሪዎች ሁለት የትግበራ ዓመታት የዋጋ ንረት ከተቀመጠለት ግብ በላይ ማደጉ በኤክስፖርት ተወዳዳሪነትና በህብረተሰቡ መግዛት አቅም ላይ ጫና በማሳደር ትልቅ ፈተና ሆኖ ነበር፡፡ በተጨማሪ በአለፉት አራት ዓመታት የወጪ ንግድ እንቅስቃሴ በተቀመጠው ግብ መሠረት ተመጣጣኝ አፈጻጸም ባለማሳየቱ የውጭ ምንዛሬ እጥረት አስከትሏል፡፡ ሌላው ትኩረት ከሚሹ ጉዳዮች የሚመደብ የአምራች ዘርፉ የተጠበቀውን ያህል ዕድገት ያለማሳየቱ ነው፡፡ አምራች ዘርፉ ኢኮኖሚው የሚፈልጋቸውን ምርቶች በመጠን፣ በስብጥር፣ በጥራትና በተወዳዳሪነት ለውጪ ንግድ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓት እና ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ማቅረብ

ተስኖት ታይቷል፡፡ ለአብነት ያህል ስኳር፣ ስንዴ፣ ጥጥ…ወዘተ. ከውጭ ማስገባት ግድ ብሎናል፡፡ ይህም የነበረውን የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንዲባባስ አድርጎታል፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ የዓለም የገበያ ሁኔታ መቀዛቀዝና የዋና ወጪ ንግድ ምርቶች ዋጋ (ቡና፣ ወርቅ) መቀነስ፣ የነዳጅ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሮ በዚያው ላይ መቆየት ማክሮ ኢኮኖሚ ማኔጅመንቱን አወሳስቦት ቆይቷል፡፡

### ሀ) የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ቀጣይነት

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጀመሪያዎች የትግበራ ዓመታት የዋጋ ንረት ኢኮኖሚውን በከፍተኛ ደረጃ የተፈታተነበት ሁኔታ ነበር፡፡ ለዚህም የሚከተሉት ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ አንደኛ፣ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት ባልተጠበቀ ሁኔታ ዓለም አቀፍ የምግብና የነዳጅ ዋጋ መናር በምናስገባቸው የገቢ ንግድና የወጪ ንግድ ፍላጎታችን ላይ ያሳደረው ተጽእኖ በሀገር ውስጥ የሸቀጦች ዋጋ እንዲንር አድርጓል፡፡ ሁለተኛ፣ የግብርና ምርት በተቀመጠለት ግብ መሠረት ባለማደጉ በሀገር ውስጥ ፍላጎትና አቅርቦት መካከል ያለውን ክፍተት በታቀደው መሠረት ማጥበብ ያለመቻሉ፤ እና ሦስተኛ፣ የገቢ ንግድን ለመተካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ በዕቅዱ ላይ የተቀመጡ የኢንዱስትሪ ምርቶች (ለምሳሌ እንደ ስኳር) በታቀደው መሠረት ያለመመረታቸው የአቅርቦት እጥረት እንዲኖር አድርጓል፡፡ በመሆኑም በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የግብርናን ምርታማነት የማሳደግ፣ የኢንዱስትሪ በተለይም ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት ዕድገቱን የማፋጠን፣ በተለያዩ ዘርፎች እስከአሁን የተገነባውን አቅም ይበልጥ በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ አሟጥጦ በልማት ሥራዎች ላይ ማዋል አጠቃላይ አቅርቦቱን በአስተማማኝ ያሳድጋል፡፡ ይህም በበኩሉ በአጠቃላይ ለዋጋ መረጋጋት አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

የሚፈጠረው አጠቃላይ ዋጋ መረጋጋት እያደገ የመጣው የከተማ ነዋሪው ሕዝብ የመግዛት አቅም እንዳይደክም ያደርጋል፣ ኢንዱስትሪ ላይ የተሰማራው ሠራተኛ የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻል ያግዛል፡፡ ከዚህም የኢንዱስትሪ ሠራተኛ ደመወዝ/ምንዳ ጭማሪ ተከታታይ ጫና እንዳይከሰት በማድረግ ለኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነትና ትርፋማነት የጎላ አስተዋጽኦ ያደርጋል፣ ቁጠባና ኢንቨስትመንት ይስፋፋል፣ አጠቃላይ ኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ የዋጋ ንረት አንዱ ምንጭና ኪራይ ሰብሳቢነት የነገሰበትና ሕብረተሰቡን እያማረረ ያለውን የንግድ ሥርዓታችንን በተጀመሩ ንግድ ሪፎርም ሥራዎችን በፍጥነት ግልፅነትና ተወዳዳሪነትን ማስፈን ወሳኝ ነው፡፡ ይህም በአስተማማኝ ዋጋ ንረትን ለመቆጣጠርና ማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን ለማስፈን አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

### ለ) በቁጠባና ኢንቨስትመንት መካከል ያለ ክፍተት /Imbalance/

ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቁጠባ ባለፉት አራት ዓመታት በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል አሳይቷል፡፡ ለዚህም በዕቅድ ዘመኑ የፋይናንስ ተደራሽነት ማደግ፣ አዳዲስ የቁጠባ መሳሪያዎች በመተግበራቸው እና ከኢኮኖሚው ዕድገት ጋር ተያይዞ የህብረተሰቡ ገቢ በማደጉ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዕቅድ ዘመኑ በኢንቨስትመንትና ቁጠባ መካከል ያለው ክፍተት በየጊዜው እየሰፋ በመምጣት በ2006 ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የ17.8 በመቶ ድርሻ ይዟል፡፡ ይህም በቁጠባና በኢንቨስትመንት መካከል ከፍተኛ ክፍተት እንዳለ እና የኢንቨስትመንት ክፍተቱ ከውጭ በሚገኝ ቁጠባ እየተሸፈነ መሆኑን ያሳያል፡፡

ይህ ሁኔታ ሀገሪቷ እስከአሁን ስታስመዘግብ ላመጣችው ፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነት ትልቅ ስጋት ነው፡፡ ስለሆነም ኢኮኖሚው ከሚፈልገው ከፍተኛ ኢንቨስትመንት እና ኢኮኖሚ ዕድገቱን በአስተማማኝ ለማስቀጠል እንዲቻል የሀገር ውስጥ ቁጠባን ማሳደግ የወቅቱ ጥያቄ ሆኖአል፡፡ የኢኮኖሚያችን ዓይነተኛ መገለጫ የሆነውንና እየሰፋ የመጣው በቁጠባና በኢንቨስትመንት መካከል ያለው ክፍተት /Imbalance/ በሂደት እየጠበበ መሄድ ይኖርበታል፡፡

ከዚህ አንፃር በመጀመሪያው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተለያዩ የቁጠባ መሳሪያዎችን በመጠቀም የሕብረተሰቡን ቁጠባ ለማሳደግ የተጀመረው ሥራ ይበልጥ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

በመንግሥት ቁጠባ በኩል ወጪን በመቆጣጠርና የሀገር ውስጥ ገቢን በአስተማማኝ በማሳደግ ለሀገር ውስጥ ቁጠባ ማደግ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም የታክስ አፈፃፀማችንን ትርጉም ባለው ሁኔታ ለማሻሻል የታክስ ማሻሻያና አስተዳደር ሥራዎችን ከእስከአሁኑ በላቀ ደረጃ አጠናክሮ ተፈፃሚ ማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ይሆናል፡፡

ይበልጡን የግሉ ሴክተር ቁጠባና ኢንቨስትመንት እንዲያድግ ከወትሮው የተጠናከረ ድጋፍ ማድረግና ሳቢ ቢዝነስ ኢንቫይሮሜንት መፍጠር ይጠይቃል፡፡ ይህ በበኩሉ የግሉን ሴክተር ወደ አምራች ሴክተሮች በጥራትና በብዛት ለመሰማራት ያስችለዋል፡፡ የአምራች ዘርፍ ማደግ የኢኮኖሚውን አጠቃላይ አቅርቦት ያሳድጋል፣ የሥራ ዕድል ይፈጥራል፣ የገቢ መሠረትም ያሰፋል፡፡ በሂደትም የተባዛ ቁጠባና የተጠናከረ ኢንቨስትመንት አቅም ይፈጠራል፡፡

በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የብር ቁጠባ ማደግ ብቻውን በቂ አይሆንም፡፡ እያደገ በሚሄድ የውጭ ምንዛሪ ክምችት ሊደገፍ ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ በመጀመሪያው በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዓመታት የታየውን ደካማ የኤክስፖርት አፈፃፀማችን መሠረታዊ ለውጥ ሊያመጣ እንደሚገባው ያሳያል፡፡ የወጪ ንግድ ሸቀጦቻችንን በዓይነት በመጠንና በጥራት በማሳደግ በዋጋ ተወዳዳሪ የሆነ የወጪ ንግድ ሸቀጦችን በከፍተኛ መጠን ማቅረብ የውጭ ምንዛሬ ግኝታችንን ያሰፋል፡፡ ይህም ሁኔታ አሁን ኢኮኖሚውን እየተፈታተነ የሚገኘውንና የውጭ ምንዛሬ ማነቆን በሂደት በአስተማማኝ ለማስወገድ ያስችላል፡፡

ከዚህ በላይ የተገለፁት ቁም ነገሮች እውን ሊሆኑና ቀጣይነት ሊኖራቸው የሚችለው የአምራቹ ዘርፍ በተለይም ግብርናና ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የማምረት አቅም በላቀ ደረጃ ማደግ ሲችል ነው፡፡ ይህ በበኩሉ እስከአሁን የተፈጠሩትን አቅሞች አሟጦ መጠቀምን ይጠይቃል፡፡ ለዚህ ማነቆ የሆኑትን ጉዳዮች በሙሉ መፍትሔ መስጠት ይገባል፡፡ ከዚሁም በላይ ግን በተለይ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ጥራት ያለውን መጠነ ሰፊ ኢንቨስትመንት ወደ ሴክተሩ እንዲፈስ የተመቻቸ ሁኔታ ሊፈጠር ይገባል፡፡ በአጠቃላይ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪና የግብርና ሴክተርን ኢንቨስትመንት፣ ምርታማነትን፣ የምርት ጥራትን እና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡

### ሐ) ተቋማዊ ብቃት ማረጋገጥ

ሀገሪቷ በከፍተኛ የዕድገት ጎዳና ላይ እንደምትገኝ የሚታወቅ ነው፡፡ የኢኮኖሚውን ዕድገት የበለጠ ለማፋጠንና ድህነትን ለማጥፋት በሚደረገው ርብርብ ውስን በሆነው የመንግሥት ሀብት እየተገነቡ ያሉ መሠረተ ልማቶችና የማህበራዊ ልማት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም በተቀናጀ ሁኔታ መከታተል ወሳኝ ነው፡፡ በሌላ በኩል በተለይ ከወጪና ገቢ ንግዳችን ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለውን የሎጂስቲክስ አገልግሎትና የጉምሩክ አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ የሚታዩ ችግሮች በኢንቨስትመንትና በንግዱ እንቅስቃሴ ላይ የሚፈጥረውን አሉታዊ ተጽዕኖ ሙሉ በሙሉ መቅረፍ እንደሚገባ የእስከአሁኑ አፈፃፀም ይጠቁማል፡፡

በተያያዘም መሠረተ ልማቶች በጥራት አለመቅረብ በዕቅድ ትግበራ ላይ የራሱን ተጽእኖ አሳድሮአል፡፡ በተለይ የኃይል አቅርቦት መቆራረጥ ለሚካሄድበት ኢንቨስትመንት ማስፋፋት ሥራ፣ ያለውን የማምረት አቅም በሙሉ ለመጠቀምና ጥረት ለመጨመር ከፍተኛ እንቅፋት ሲፈጥር የቆየ ነው፡፡

### መ) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አመራር

መንግሥት በፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራሙ በርካታ የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ እንዲዞሩ አድርጓል፡፡ ነገር ግን ለፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ወሳኝ የሆኑ ስትራቴጂክ የልማት ድርጅቶች በመንግሥት ይዞታና አመራር ሥር እንዲቆዩ ተደርጓል፡፡ ከእነዚህም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ኢትዮ ቴሌኮም፣ ምድር ባቡር፣ ስኳር ኮርፖሬሽን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የሚጠቀሱት ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው እነዚህ ተቋማት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ይዘው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ የሚመደበውና የሚያስተዳድሩት ፋይናንስና ሌሎች ሀብቶች ከፍተኛ ነው፡፡

ምንም እንኳን ለእያንዳንዳቸው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የተሰየመ እና ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ሪፎርም ሥራዎች እየተሰሩ የቆየ ቢሆንም ከተሰጣቸው ተልዕኮና ከሚያስተዳድሩት ሀብት አንፃር በከፍተኛ ደረጃ የተቀናጀና የቅርብ አመራር፣ ክትትልና ድጋፍ በተሟላ ሁኔታ እያገኙ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ እነዚህ ድርጅቶች ብቁና ተወዳዳሪ ሆነው ውጤታማ አመራር ተሰጥቶአቸው ኢኮኖሚው የሚፈልገውን አገልግሎት በበቂና በጥራት ማቅረብ ከቻሉ ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽናችን መፋጠን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ለትራንስፎርሜሽናችን ሥጋት ይሆናሉ፡፡ ማክሮ ኢኮኖሚ ማኔጅመንቱም ይወሳሰባል፡፡ ስለዚህ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ወቅት ያሉትን አሰራሮች፣ አደረጃጀቶችና አመራርና ድጋፍ አሰጣጥ ገምግሞ በከፍተኛ ደረጃ የቅርብና የተቀናጀ አመራር የሚያገኙበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡

## 1.2 የግብርናና ገጠር ልማት ዕቅድ አፈፃፀም

### 1.2.1 የግብርናና ገጠር ልማት ዕቅድ ዓላማና አቅጣጫዎች

በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የግብርናውን ዘርፍ ዋና የዕድገት ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል የማድረግ በዚህም ውስጥ የሞዴል አርሶ አደሮችን ተሞክሮ ወደ አብዛኛዎቹ አርሶ-አደሮች በማስፋፋት የአርሶ-አደሩ እርሻ ዋናው የግብርና ዕድገት ምንጭና መሠረት እንዲሆን፣ በግብርናው ዘርፍ የግል ባለሀብቱ ተሳትፎ ከፍተኛ ድርሻ እንዲኖረው እና በዋናነት ሀገሪቱ ያላትን የሰው ኃይልና መሬት በአግባቡ በመጠቀም ዘርፉን ማሳደግ የሚሉት የግብርናና ገጠር ልማት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡ እነዚህን አቅጣጨዎች መሠረት በማድረግ ግቦችና የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ተቀምጠው ወደ ትግበራ ተግብቷል፡፡

### 1.2.2 የግብርናና ገጠር ልማት ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም

ባለፉት አራት ዓመታት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ፈጣንና ዘላቂ የግብርና ልማት ሊያረጋግጡ የሚችሉ በርካታ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ የተሟላ የግብርና ግብዓት አቅርቦት እንዲኖርና የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ለማስፋፋት ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ሲሆን በየዓመቱ በአማካይ 6.6 በመቶ የግብርና ተጨማሪ ዕሴት ዕድገት ለማስመዝገብ ተችሏል፡፡ የተመዘገበው የግብርና ተጨማሪ ዕሴት ዕድገት በብዙ መለኪያዎች ፈጣን ቢሆንም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዳችን ካስቀመጥነው 8.6 በመቶ ዓመታዊ አማካይ ግብ አንፃር ወደኋላ ቀርቷል፡፡ የግብርና ዘርፍ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2006 የበጀት ዓመት 40.1 በመቶ የደረሰ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የሰብል ልማት 28.4 በመቶ እና የእንስሳት ልማት 8.3 በመቶ ድርሻ አላቸው፡፡

**የሰብል ምርታማነትና ምርት፡-** ባለፉት አራት ዓመታት በዋና ዋና የምግብ ሰብሎች (የብርዕና የአገዳ፣ የጥራጥሬ እና የቅባት ሰብሎች) በዓመት በአማካይ 17.61 ኩንታል በሄክታር የምርታማነት አፈፃፀም ተመዝግቧል፡፡ ይህም በየዓመቱ በአማካይ ከተያዘው 19.44 ኩንታል በሄክታርና በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት ይደረስበታል ተብሎ ከተቀመጠው 22 ኩንታል በሄክታር ምርታማነት ግብ አንፃር ወደኋላ የቀረ ነው፡፡ በሌላ በኩል የዋና ዋና የምግብ ሰብሎችን ምርት በ2002 ከነበረበት 191.30 ሚሊዮን ኩንታል በ2006 ወደ 274.42 ሚሊዮን ኩንታል ከፍ ለማድረግ የተቻለ ሲሆን ይህ አፈፃፀም በ2007 ይደረስበታል ተብሎ የተያዘው 267.74 ሚሊዮን ኩንታል ግብ አስቀድሞ መሳካቱን ያሳያል፡፡ ከዋና ዋና የምግብ ሰብሎች ጠቅላላ ምርት የብርዕና የአጋዳ ሰብሎች 86 በመቶ፣ የጥራጥሬ ሰብሎች 11 በመቶና የቅባት እህሎች ደግሞ 3 በመቶ ድርሻ አላቸው፡፡ ይህም አርሶ አደሩ የተሻለ ዋጋ ወዳላቸው ምርቶች የሚያደርገው ሽግግር አዝጋሚ እንደሆነ ያሳያል፡፡

ባጠቃላይ ባለፉት አራት ዓመታት በዋና ዋና ሰብሎች ምርትና ምርታማነት ዙሪያ መሻሻሎች ቢታዩም የእነዚህን ሰብሎች ምርት በከፍተኛ ሁኔታ ለማሳደግ የሚያስችል የምርታማነት እመርታ ማምጣት ግን አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የግብርናው ዘርፍ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው ዕድገት ዋና ምንጭ በመሆን ከሚጠበቅበት አስተዋፅኦ አንፃር ዕጥረቶች እንደነበሩበት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም በዋናነት የዋና ዋና

የምግብ ሰብሎችን ምርታማነት በሚጠበቃው ደረጃ ካላማሳደግ በተጨማሪ ከእነዚህ ሰብሎች ምርት ውስጥም የተሻለ የገበያ ዋጋ ወዳላቸው የሰብል ምርቶች ሽግግር ከማድረግ አንፃር ውስንነቶች እንደነበሩ መመልከት ይቻላል፡፡

**የግብርና ግብዓት አቅርቦት፡-** የግብርና ግብዓት አቅርቦትን ለማሳደግና የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ለማስፋፋት በተከናወኑ የልማት ሥራዎች አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም የግብዓት አቅርቦቱን አሁንም አስተማማኝ ደረጃ ላይ ማድረስ አልተቻለም፡፡ በዚህ ረገድ ባለፉት አራት ዓመታት የማዳበሪያ አቅርቦት 1148 ሺህ ቶን የደረሰ ሲሆን በ2007 ከተቀመጠው ግብ ማሳካት የተቻለው 79 በመቶ ብቻ ነው፡፡ በምርጥ ዘር አቅርቦት ደግሞ 75 በመቶ ያህሉን በማሳካት 2726 ሺህ ኩንታል ማድረስ ተችሏል፡፡ ሌላው ምርታማነትን ለማሳደግ የተቀመጠው ግብ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቱን ማስፋፋትና ውጤታማ ማድረግ ሲሆን የተጠቃሚዎችን ቁጥር 13.09 ሚሊዮን ማድረስ ተችሏል፡፡ ይህም ከ2007 ዕቅድ ግብ ጋር ሲነፃፀር 89 በመቶ ማሳካት መቻሉን ያሳያል፡፡ የአገልግሎቱን ውጤታማነት ለማሳደግ የተለያዩ አደረጃጀቶችና ማበረታቻዎች የተዘጋጁ ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ ተግባረዊ መሆን አልቻሉም፡፡ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቁጥር የጨመረ እና በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ የተቀመጠውን ግብ ማሳካት የሚቻል ቢሆንም የአገልግሎቱን ውጤታማነት ይበልጥ ማጎልበትና በሰብልና እንስሳት ምርትማናት ዙሪያ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት ይገባል፡፡

**የእንስሳት ሀብት ልማት፡-** ሌላው በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ትኩረት የተሰጠው የእንስሳት ሀብት ልማት ሲሆን ከሞላ ጎደል በሁሉም አርሶ አደሮች ሊፈፀም የሚችል ዘርፍ ነው፡፡ በንዑስ ዘርፉ የተሻሻሉ የዳልጋ ከብቶች ቁጥር በዕቅዱ የመነሻ ዓመት ከነበረበት 10.37 በመቶ በ2006 ወደ 13.97 በመቶ ክፍ ያለ ሲሆን የተሻሻሉ ዲቃላ የዳልጋ ከብቶች ቁጥር ከ390,078 በ2006 ወደ 744,120 ከፍ ብሏል፡፡ በተመሳሳይ የተሻሻሉ ታላቢ ላሞችን ቁጥር ከ140,428 በ2006 ወደ 245,560 ማሳደግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በተመሳሳይ በጥራት የተመረተ አባለዘር በ2002 ከነበረበት 350 ሲህ ዶዝ ወደ 758.24 ሺህ ዶዝ ያደገ ሲሆን ፈሳሽ ናይትሮጂንም በ2002 ከነበረበት 55 ሺህ ሊትር በ2006 ወደ 317.86 ሺህ ሊትር ከፍ ብሏል፡፡

የእንስሳትን ምርታማነትና ምርት ለማሳደግ የእንስሳት ጤና ጥበቃና መኖ አስፈላጊ ግብዓቶች ሲሆኑ ባለፉት አራት ዓመታት በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ የተሻሻለ መኖ አቅርቦት በዕቅዱ የመነሻ ዓመት ከነበረበት 50 ሺህ ኩንታል በ2006 ወደ 128 ሺህ ኩንታል ማድረስ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በመደበኛ ፕሮግራም የህክምናና ክትባት አገልግሎት ማግኘት የሚችሉ እንስሳት ቁጥር ከ40 በመቶ በ2006 ወደ 70 በመቶ አድጓል፡፡ የእንስሳት ጤና ኬላዎች ቁጥር ከ2275 በ2006 ወደ 2764 ከፍ ያለ ሲሆን የእንስሳት ክትባት ምርት መጠን ከ93.8 ሚሊዮን ዶዝ በ2006 ወደ 122.56 ሚሊዮን ዶዝ አድጓል፡፡ እንዲሁም የተሸጠ ክትባት ምርት መጠን ከ96.8 ሚሊዮን ዶዝ በ2006 ወደ 152.32 ሚሊዮን ዶዝ ከፍ ብሏል፡፡ ባጠቃላይ ባለፉት አራት ዓመታት የእንስሳትን ምርታማነትና ምርት ለማሻሻል በርካታ ተግባራት የተከናወኑ ቢሆንም ሀገራችን ካላት ሊለማ የሚችል ከፍተኛ የእንስሳት ሀብት ዕምቅ አቅም አንፃር እጅግ በርካታ ሥራዎች እንደሚቀሩ መገንዘብና በቀጣይ ለንዑስ ዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ መንቀሳቀስ ይጠይቃል፡፡

**የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም፡-** የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀምን በሚመለከት ባለፉት አራት ዓመታት የውሀ፣ የአፈር እና የስነ-ህይወታዊ ተለያይነት (Biodiversity) ሀብታችንን የሚያጎለብቱ እና የአርብቶ/አርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት በዘላቂነት ከማሳደግ አንፃር መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጡ ስኬታማ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ ባለፉት አራት ዓመታት 60,460 የማህበረሰብ ተፋሰሶች የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቶላቸዋል ይህም በመሬት ስፋት በአማካይ 30.23 ሚሊዮን ሄክታር ይሆናል፡፡ ይህ አፈፃፀም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት ይደረስበታል ተብሎ ከተቀመጠው የ19,560 የማህበረሰብ ተፋሰሶች የልማት ዕቅድ አንፃር እጅግ የላቀ ነው፡፡ በተመሳሳይ በአለፉት አራት ዓመታት

እንዲያገግም የተከለለ የመሬት መጠን በዕቅዱ የመነሻ ዓመት ከነበረበት 3.208 ሚሊዮን ሄክታር በ2006 ወደ 11.74 ሚሊዮን ሄክታር ያደገ ሲሆን አፈፃፀሙ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት ይደረስበታል ተብሎ ከተቀመጠው 10.208 ሚሊዮን ሄክታር ግብ አንፃር ከፍተኛ የሚባል ነው፡፡

ባለፉት አራት ዓመታት አርሶ አደሮች በፈቃደኝነት ነፃ አገልግሎት በመስጠት ለግብርና ምርታማነት መሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያላቸው የአፈር መከላትን የሚከላከሉና የውኃ ሥርገትን የሚያጐለብቱ የማህበረሰብ ተፋሰስ የመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎችን አካሂደዋል፡፡ በዚህም በዕቅዱ የመነሻ ዓመት 3.772 ሚሊዮን ሄክታር የነበረውን የማህበረሰብ ተፋሰስ መሠረተ-ልማት ግንባታ በ2006 ወደ 20.157 ሚሊዮን ሄክታር ማድረስ የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህ አፈፃፀም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከተቀመጠው አጠቃላይ ግብ አንፃር በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም ዘርፈ ብዙ ጥቅም በሚሰጡ የዛፍ ዝርያዎች በመሸፈን እንዲያገግም የተደረገ የመሬት ስፋት በመነሻ ዓመት 6.058 ሚሊዮን ሄክታር የነበረ ሲሆን ይህንን የመሬት መጠን በዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት ወደ 10.154 ሚሊዮን ሄክታር ከፍ ለማድረግ ግብ ተይዞ በተከናወኑ ሥራዎች 12.167 ሚሊዮን ሄክታር ማድረስ ተችሏል፡፡

ባጠቃላይ ባለፉት አራት ዓመታት በተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ዙሪያ ከተከናወኑ ስኬታማ የተፋሰስ ልማቶች ምርጥ ተሞክሮዎች ተገኝተዋል፡፡ እነዚህን ምርጥ ተሞክሮዎች ወደ ሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በማስፋት በየደረጃው ያሉ አመራሮችና አርሶ አደሮች ስለተፋሰስ ልማት የጋራ ግንዛቤና አቅጣጫ እንዲይዙ ተደርጓል፡፡ በተወሰኑ የሀገራችን አካባቢዎች አርሶ አደሮች ባካሄዷቸው የተፋሰስ ልማቶች ተጠቃሚ መሆናቸውን እንደማሳያ በመውሰድ እና ስለ አየር ንብረት ለውጥ ግንዛቤ በመፍጠር በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ በተከናወኑ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ልማት መልካም ውጤቶች መታየት ጀምረዋል፡፡ መታየት የጀመሩት መልካም ውጤቶች እንዲሰፉና ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤው የግብርና ምርትንና ምርታማነትን በፍጥነት ከማሳደግና የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አንፃር ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ይሆናል፡፡

**የምግብ ዋስትና እና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት፡-** የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ሥር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸውን ቤተሰቦች በሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ ማድረግ፣ የቤተሰብ ጥሪት እንዲገነቡ ማድረግና ከልማታዊ ሴፍቲኔት ተመርቀው ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ በመንግስት የተዘረጋ ሥርዓት ነው፡፡ በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም 5.1 ሚልዮን ሥር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸው ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ቢታቀድም ከአፋርና ሶማሌ ክልሎች 64 ወረዳዎች በዕቅዱ ወቅት ያልታዩ 2.6 ሚሊዮን ዜጎች በፕሮግራሙ በመታቀፋቸው በ2003 የበጀት ዓመት ሥር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸው የሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች ብዛት 7.7 ሚሊዮን መድረሱ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንፃር ባለፉት አራት ዓመታት በተከናወኑ የልማት ሥራዎች የምግብ ዋስትናቸውን ያረጋገጡ 739,166 የቤተሰብ ኃላፊዎችን ለማስመረቅ ተችሏል፡፡ ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት አንፃር በአለፉት አራት ዓመታት ከዕቅዱ የመነሻ ዓመት የነበረውን የምግብ መጠባበቂያ ክምችት ለማስቀጠል የተቻለ ሲሆን በዚህ ዙሪያ ተጨማሪ አቅም አልተፈጠረም፡፡ በሌላ በኩል ባለፉት አራት ዓመታት ለ14.2 ሚሊዮን ህዝብ የምግብ ድጋፍ ለማድረግ የታዘው ዕቅድ መቶ በመቶ በሚባል ደረጃ ተፈፃሚ ሆኗል፡፡ እንዲሁም ከቅጽበታዊ አደጋ ክስተት ጋር በተያያዘ የአደጋ ክስተቱና የድጋፍ ፈላጊው ህዝብ ቁጥር  እየቀነሰ በመምጣቱ ለ1.6 ሚሊዮን ህዝብ ብቻ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

**የግል ባለሀብቶች ልማታዊ ተሳትፎን በተመለከተ** ባለፉት አራት ዓመታ (2003-2006) በአበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ እና የመድኃኒት ዕፅዋት በቅደም ተከተል 2647 ሄክታር፣ 11591 ሄክታር፣ 11513 ሄክታር እና 2264 ሄክታር መሬት ለመሸፈን ታቅዶ በቅደም ተከተል 1467 ሄክታር(55.4 በመቶ)፣ 807.3 ሄክታር (7 በመቶ)፣ 10707 ሄክታር (93 በመቶ) እና 101.9 ሄክታር (4.5 በመቶ) መሸፈን ተችሏል፡፡ ምርትን በሚመለከት ባለፉት አራት አመታት የአበባ ምርት 5134.9 ሚሊዮን ዘንግ፣ አትክልት 432.6 ሺህ ቶን፣

ፍራፍሬ 310.7 ሺህ ቶን እና የመድኃኒት ዕፅዋት 11.3 ሺህ ቶን ለማግኘት ታቅዶ በቅደም ተከተል አፈፃፀሙም በአበባ 46.5 በመቶ፣ በአትክልት 29 በመቶ፣ በፍራፍሬ 6 በመቶ እና በመድሀኒት ዕፅዋት 901.8 በመቶ ነው፡፡ ሰፋፊ እርሻዎችን በተመለከተ በ2003፣ 2004 እና 2005 በጀት ዓመታት በቅደም ተከተል 3.4 ሚሊዮን ሄክታር፣ 3.32 ሚሊዮን ሄክታር እና 3.31 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ከክልሎች ወደ መሬት ባንክ እንዲጋባ ተደርጓል፡፡ ለአገር ውስጥና ለውጭ ባለሃብቶች በክልሎችና በፌደራል መንግስት ባጠቃላይ 2.3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት የተላለፈ ሲሆን ከዚህ ውስጥ አስፈላጊውን ድጋፍ ለባለሀብቶች በመስጠት መልማት የቻለው 840 ሺህ ሄክታር መሬት ብቻ ነው፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት አንዳንድ ባለሀብቶች የተረከቡትን መሬት አልምተው ባለመጨረሳቸው እና ሌሎቹ ደግሞ የማልማት ሥራቸውን በማቋረጣቸው ነው፡፡

### 1.2.3 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች

#### 1.2.3.1 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች

ሀ) የአርሶ-አደሮችን የሰብል ምርታማነት በተጠበቀውና በታቀደው መሠረት ከመፈፀም አንፃር የታዩ ጉድለቶች በዋነኛነት ከአመራር ብቃት መጓደል የመነጩ መሆኑ ይህም የፈፃሚ አካላትን አስተሳሳብ ቀይሮ ከማነሳሳት፣ ከማደራጀት፣ አሰልጥኖም በማስማራት ጉድለት እንዳለ መታየቱና ከክህሎትና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት ጋር የተያያዙ ውስንነቶች ያሉ መሆኑ፣

ለ) የእንስሳት ኃብት ልማት ሥራው በቂ የአመራር ትኩረት አግኝቶ በተደራጀ የመፈፀም አቅም አማካኝነት የተፈፀመ አለመሆኑ፣ የዘርፉ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ሥርዓት የተዘረጋ አለመሆኑ (በተነፃፃሪ የክትባት፣ መድሃኒት፣ የአባለዘርና ፈሳሽ ናይትሮጂን አቅርቦቶች መሻሻል ማሳየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ)፣ የክህሎት ጉድለቱም በትኩረቱ ማነስ ልክ ሰፊ መሆኑ፣ የጤና አገልግሎት ተደራሽነቱም በቦታ ሽፋን የተሻሻለ ቢሆንም በአገልግሎት ሽፋኑ በአብዛኛዎቹ ክልሎች አንድ የእንስሳት ጤና ተቋም ሦስት ቀበሌዎችን የሚያገለግል ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ችግር ያለበት መሆኑ፣

ሐ) የአርብቶ አደሩ ግብርናን በማስፋፋቱ ሂደት ከመስኖ ልማት ስራዎች ጋር በተያያዘ በተለይ በርጭት መስኖ ግንባታ የዳበረ ልምድ ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ በሲቭል ስራዎች ግንባታ ሂደት ተደጋጋሚ የዲዛይን ማሻሻያ እንዲሁም የግንባታ እቃዎች በሚፈለገው ፍጥነትና መጠን ያለማቅረብ ችግር፣ በአፋርና ሶማሌ ክልሎች ለመስኖ አገልግሎት የሚውሉ እስከ 150 የውሃ ጉድጓዶች በአማካይ 250 ሜትር ጥልቀት ያላቸው በማስቆፈር ሂደት የቁፋሮ ድርጅቶች አቅም ውስንነት በአከባቢዎቹ ካለው ጂኦሎጂካል ፎርሜሽን ጋር ተዳምሮ እጅግ ፈታኝ መሆን፣

መ) የኤሌክትሮሜካኒካል ዕቃዎች ማለትም ሰብመርሰብልና ቡስተር ፓምፖች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የጠየቀ ከመሆኑም በላይ የተቆፈሩ ጉድጓዶች የሚያመነጩት ውሃ ከፍተኛ ሙቀት ያለው ሆኖ በመገኘቱ የሚቀርቡ ፓምፖች ሙቀቱን የሚቋቋሙ እንዲሆኑ የስፔስፍኬሽን ለውጥ በማድረግ እንዲመረትና ሃገር ውስጥ እንዲገባ የማድረግ ሂደት ከፍተኛ ጊዜ መጠየቁ፣

ሠ) ከመስኖ ልማቱ ጋር ተያይዞ በሁለቱ በአፋርና ሶመሌ ክልሎች ከ20 ሜጋ ዋት በላይ የኤሌክትሪክ ኃይል እንደሚያስፈልግ በጥናት በተረጋገጠው መሰረት የመስመር ዝርጋታና ዕቃ አቅርቦት ለማከናወን ከፍተኛ በጀትና ጊዜ መጠየቁ፣

ረ) የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች በተለይ ረጃጅም ኪሎሜትሮች በሚፈለገው ፍጥነት ከማስፈጸም አንጻር የታየው አቅም ችግርም አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ነበሩ፡፡

#### 1.2.3.2 የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች

ሀ) በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና በተፋሰስ ልማት ዙሪያ የታየው ህዝባዊ ንቅናቄ አበረታችና በሌሎች ዘርፎችም ማሳደግ እንደሚገባ የሚያመላክት የዕቅድ ዘመኑ ምርጥ ተሞክሮ ሲሆን በዚሁ ዙሪያ የተከናወኑ የልማት ሥራዎችም ወደፊት በምርታማነትና በምርት ላይ ጉልህ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንደሚኖራቸው ይታመናል፡፡ በመሆኑም የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎች በቀጣይ የማስፋት ሥራ ተጠንክሮ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ሊቀጥል የሚገባ መሆኑ፡፡

ለ) በሰብል ልማትና በመስኖ አጠቃቀም ዙሪያ የልማት ሠራዊት በመገንባት የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገበ ክልል መኖሩ በሌሎች ክልሎችም በዞን፣ በወረዳ፣ በቀበሌ እንዲሁም በልማት ቡድን ደረጃ ምርጥ ተሞክሮዎችን የተገኙትን ማስፋት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑ፡፡

## 1.3 የኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ አፈጻጸም

### 1.3.1 የኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ አቅጣጫዎች

የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ የኢንዱስትሪ ልማት መሠረታዊ የትኩረት አቅጣጫዎች ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት መስፋፋት ግባር ቀደም ትኩረት መስጠት፣ የግሉ ዘርፍ በኢንዱስትሪ ልማቱ ውስጥ የሚጠበቅበትን ሚና ለመጫወት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና ለመካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎችም አስፈላጊውን ትኩረት መስጠት ናቸው፡፡

### 1.3.2 የኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም

ባለፉት አራት ዓመታት የኢንዱስትሪ ዘርፍ በየዓመቱ በአማካይ 20 በመቶ አድጓል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመካከለኛና ትላልቅ አምራች ኢንዱስትሪ 17.2 በመቶ እና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪ 4.1 በመቶ ዓመታዊ አማካይ ዕድገት አስመዝግበዋል፡፡ በ2006 የበጀት ዓመት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ 14.3 በመቶ የደረሰ ሲሆን (ማኑፋክቸሪንግ 4.4 በመቶ፣ ኮንስትራክሽን 7.6 በመቶ፣ ኤሌክትሪክና ውሀ 1.1 በመቶ፣ ማዕድን 1.2 በመቶ) ይህ አፈፃፀም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት ይሳካል ተብሎ ከተያዘው 18.8 በመቶ ግብ አንፃር ጉድለቱ የሰፋ ነው፡፡ በተጨማሪም የተመዘገበው አፈፃፀም የኢንዱስትሪ ዘርፉ በዋናነት በኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ የሚመራ መሆኑንና በኢኮኖሚው ውስጥ የተፋጠነ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ተግዳሮቶች እንዳሉ ያመለክታል፡፡

**የኢንዱስትሪ ምርቶች የወጪ ንግድ አፈፃፀምን በተመለከተ** ባለፉት አራት ዓመታት የተገኙት ውጤቶች ቀደም ባለው የዕቅድ ዘመን ከተመዘገቡት መሻሻል ያሳዩ ቢሆንም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከተቀመጡት ግቦች አንፃር ግን ብዙ የራቁ ናቸው፡፡ በ2006 የበጀት ዓመት የተገኘው 398 ሚሊዮን ዶላር ገቢ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ሊሳካ ከሚጠበቀው 1.82 ቢሊዮን ዶላር ግብ አንፃር አፈጻጸሙ 21.9 በመቶ ብቻ ነው፡፡ ይህ ውጤት ከተያዘው ዕቅድ በጣም ርቀ የሚገኝ ከመሆኑም በተጨማሪ በአገር ደረጃ ከተገኘው አጠቃላይ የውጭ ምንዛሬ ውስጥ ያለው ድርሻ 12 በመቶ ብቻ ነው፡፡

በወጪ ንግድ የሚሳተፉ ጥራት ያላቸውን አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች በብዛት በመሳብ ረገድ ከታየው ጉድለት በተጨማሪ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡት ምርቶች የእሴት መጠን ዝቅተኛ መሆን፣ ስብጥራቸውና የገበያ መዳረሻዎቹ ውስንና በጥራት ደረጃም ብራንድ መፍጠር የሚያስችሉ ባለመሆናቸው የሚያስገኙት ዋጋ ዝቅተኛ ሲሆን የዓለምን የኢኮኖሚ መዋዠቅና የገዢዎችን የድርድር ጫና የመቋቋም አቅማቸው ደካማ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኢንዱስትሪዎቹ የሚጠቀሙት ቴክኖሎጂ በአብዛኛው የኋላ ቀርነትና የቅልጥፍና ችግር ያለባቸው በመሆኑ የጥራት ጉድለትና የምርታማነት ማነስ የሚታይባቸው ሲሆን፣ ግብዓቶችን በአገር ውስጥ በበቂ መጠን፣ ጥራትና ዋጋ በወቅቱ ያለማግኘት፣ ግብዓት ከውጭ ለማምጣትም ሆነ ምርት ወደ ውጭ

ለመላክ የሚወስደው ጊዜና ውጣ ውረድ፣ ከፍተኛ የትራንስፖርት፣ የሎጂስቲክስና የፋይናንስ አገልግሎት ወጪዎች በዓለም ገበያ የተወዳዳሪነት አቅምን ለመገንባት ያላስቻሉ ችግሮች ናቸው፡፡

**የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ዕቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ** በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በጨርቃጨርቅና አልባሣት ኢንዱስትሪ 2.55 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ዋጋ ያለው ምርት ለማምረት ታቅዶ እስከ 2006 የበጀት ዓመት 678 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ዋጋ ያለው ምርት ተመርቷል፡፡ የተመዘገበው የኤክስፖርት ገቢ በዕቅዱ የመነሻ ዓመት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ዕድገት ያሳየ ቢሆንም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ከተያዘው 1 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ግብ አንፃር ሲታይ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ የማምረት አቅም አጠቃቀም በአማካይ በኢንዱስትሪዎቹ 62 በመቶ የደረሰ ቢሆንም ከተቀመጠው የ90 በመቶ ግብ አንፃር ዝቅተኛ ነው፡፡ ባለፉት አራት ዓመታት በንዑስ ዘርፉ ለ40 ሺህ ዜጐች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ተይዞ የተሠራ ቢሆንም ማሳካት የተቻለው የዕቅዱን 40 በመቶ ያህል ብቻ ነው፡፡

**የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ** በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ባጠቃላይ 1.7 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ዕቅድ ተይዞ ባለፉት አራት ዓመታት በተከናወኑ ሥራዎች 472.2 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡ በአለፉት አራት ዓመታት በንዑስ ዘርፉ ለ18,149 ዜጎች የሥራ እድል ተፈጥሯል፡፡ ጥራት ያለውና በቂ የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅርቦት አለመኖር፣ ምርቶች ያለ እሴት ጭማሪ ወደ ውጭ መውጣታቸው፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና የማጠናቀቅ አቅም ውስንነቶች መኖር፣ በተጨማሪ ኢንቨስትመንት የማምረት አቅም ያለማዳበርና አክሰሰሪዎችን የማምረት አቅም አለመፍጠር፣ የአቅም አጠቃቀምና የሰራተኛ ምርታማነት ከአለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮ ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ መሆን የንዑስ ዘርፉ ዋነኞቹ ማነቆዎች ናቸው፡፡

**የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ዕቅድ አፈጻጸም በተመለከተ** ባለፉት አራት ዓመታት የንዑስ ዘርፉ የምርት ዋጋ ብር 30.14 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን የብረት አማካይ የነፍስ ወከፍ ፍጆታም 20.36 ኪ.ግ. ነው፡፡ የንዑስ ዘርፉ የማምረት አቅም አጠቃቀም 54 በመቶ ላይ ያለ ሲሆን እስከ 2005 የበጀት ዓመት ለ22,697 ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ ከዚህ ቁጥር ውስጥ የሴቶች ድርሻ 18 በመቶ ነው፡፡ ንዑስ ዘርፉ ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት የውጭ ምንዛሬን ከማዳን አንፃር ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ ንዑስ ዘርፉ አቅሙን በየጊዜው በማሳደግ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ከማሟላት ጎን ለጎን ምርቶቹን ኤክስፖርት ማድረግ ጀምሯል፡፡ በዚህም በ2006 ወደ ውጭ ከላካቸው ምርቶች 3.19 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ አግኝቷል፡፡ የሌሎች ንዑስ ዘርፎችን የመለዋወጫ አካላት ፍላጐት በሀገር ውስጥ በሚመረት ምርት ለማሟላት ለስኳር ፋብሪካዎች ግንባታ የሚውሉ ኮምፖነንቶችን የማምረት አቅም 80 በመቶ ደርሷል፡፡ እንዲሁም 1,000 የሚደርሱ የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች፣ 5,000 የሚደርሱ የእርሻ መሣሪያዎች /ትራክተሮች/ እና 4,000 የሚደርሱ ተቀጥላዎችን መገጣጠምና ማምረት ተችሏል:: በንዑስ ዘርፉ ባለፉት አራት ዓመታት ከአራት ሺህ በላይ አውቶሞቢሎችን እና ከ1 ሺህ በላይ የጭነት ተሽከርካሪዎችን መገጣጠምና መፈብረክ ተችሏል:: እንዲሁም ከ1 ሺህ በላይ የተለያዩ አውቶብሶችን መገጣጠምና አካላቸውን መፈብረክ የሚያስችል አቅም ተፈጥሯል:: የኤሌክትሪክ ትራንስፎርመሮችን፣ የኤሌክትሪክ መቆጣጠሪያና የማከፋፈያ ቦርዶችን፣ ኢኩዊኘመንቶችን፣ ባትሪና ሀይል የሚያጠራቅሙ አኩሙሌተሮችን፣ የቴሌቪዥንና ከ10 በላይ የሚሆኑ የሞባይል መገጣጠሚያ ፋብሪካዎችን በማቋቋም የሀገር ውስጥ ፍላጐትን ሙሉ ለሙሉ ለማሟላትና ኤክስፖርት ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ ግብአቶች በማቅረብ፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግር አስተዋፅኦ በማድረግ፣ የውጭ ምንዛሬን በማዳን፣ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ መሠረት በማስፋት አቅም በማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

**የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ዕቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ** በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የንዑስ ዘርፉ ዕቅድ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት በተከናወኑ ሥራዎች የብርዕና አገዳ እህል ኢንዱስትሪዎችን ቁጥር 586፣ የቅባት እህሎች ፕሮሰሲንግ የኢንዱስትሪዎች ብዛት 62 እና የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንዱስትሪዎችን ብዛት 21፣ የመጠጥ ኢንዱስትሪዎች ቁጥር 109 ደርሷል፡፡ ንዑስ ዘርፉ ለ52 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል

ከመፍጠሩም ባሻገር 196 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጪ ምንዛሪ ገቢም አስገኝቷል። በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙ ዋና ዋና ማነቆዎች የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ውስንነት (ማነስ፣ ጥራት መጓደልና ተከታታይነት ማጣት)፣ በምርምርና ሥርፀት አለመደገፍ፣ የቴክኖሎጂ አቅም ውስንነት፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ እና የፓኬጂንግ ኢንዱስትሪው በተፈለገው መጠን ማደግ አለመቻል ናቸው።

**የስኳር ኢንዱስትሪን በተመለከተ** በሀገራችን በስኳር ልማት ላይ የተሰማሩ ሶስት የመንግስት ፋብሪካዎች ይገኛሉ። እነዚህም ወንጂ፣ ፊንጫና መተሐራ ሲሆኑ ፊንጫ እና ወንጂ የማስፋፊያ ፕሮጀክት ተጠናቀዋል። ሦስቱም በአጠቃላይ በ30,000 ሄክታር ሸንኮራ አገዳ እያለሙ ሲሆን በ2006 በጀት ዓመት በእቅድ ከያዙት 418,321 ቶን ስኳርና 25,118 ሜትር ኩብ ኢታኖል ውስጥ 313,536 ቶን ስኳርና 19,445 ሜትር ኩብ ኢታኖል አምርተዋል። የአገሪቱ የስኳር ፍጆታ በዓመቱ 560,000 ቶን የሚገመት በመሆኑ 200,000 ቶን ያህል ከሌሎች አገራት እየተገዛ ክፍተቱ ተሞልቷል። 12 የመንግሥት ፕሮጀክቶች (አርጆ ዴዴሳ፣ በለስ 1፣ 2 እና 3፣ ከሰም፣ ኩራዝ 1፣2፣3፣4 እና 5፣ ተንዳሆ፣ ወልቃይት) በ372,000 ሄክታር መሬት ላይ የሸንኮራ አገዳ በማልማት በሙሉ አቅማቸው ወደ ሥራ ሲገቡ ከ4.07 ሚሊዮን ቶን በላይ ስኳር እንደሚያመርቱ ይጠበቃል። በ2007 በጀት አመት 5 የስኳር ፕሮጀክቶች (ተንዳሆ ምዕራፍ አንድ፣ ከሰም፣ ኩራዝ 1፣ በለስ1፣ አርጆ ደዴሳ) ማምረት እንደሚጀምሩ ይጠበቃል። በዚህም በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ላይ ከወጪ ንግድ 1.2 ቢሊዮን ዶላር ገቢ እንደሚገኝ ታቅዷል። ከዚህ በተጨማሪ የስኳር ልማት ዘርፍ 128,521 ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድልን መፍጠር ችሏል።

**የሥጋ፣ ወተትና ማር ኢንዱስትሪ የልማት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ** ባለፉት አራት ዓመታት ከሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ 290 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ተገኝቷል። የንብ ሀብትን በተመለከተ በዓመት እስከ 550,000 ቶን ማር የማምረት አቅም ቢኖርም በተጨባጭ በዓመት በአማካይ 45,951.2 ቶን እየተመረተ ይገኛል። የሀገሪቱ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ የሥጋ ፍጆታ 8.4 ኪ.ግ እና ዝቅተኛ ነው። የግብዓት ጥራትና አቅርቦት ችግር፣ የሰለጠነ የሰው ሀይል በበቂ አለመኖር፣ በቂ የመሠረተ ልማትና ሎጅስቲክ አለመኖር የንዑስ ዘርፉ የዕቅድ አፈፃፀም ዋነኛ ማነቆዎች ናቸው።

**የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት ኢንዱስትሪ ዕቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ** በሲሚንቶ ንዑስ አንዱስትሪ ባለፉት አራት ዓመታት ዕቅዱን ለማሳካት መንግስት ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታዎች በማመቻቸትና ሰፊ የኢንቨስትመንት የማስታዋወቅ ስራ በመስራት በሲሚንቶ ኢንቨስትመንት ለመሰማራት ፍላጎት የወሰዱ ባለሀብቶች የፕሮጀክት ትግበራቸውን በዕቅዳቸው መሰረት እንዲያከናውኑ ድጋፍ በማድረግ የአገራችን የሲሚንቶ ፍላጎት ሙሉ ለሙሉ በ2004 በጀት ዓመት እንዲሸፈን ከማስቻሉም በላይ በ2005 በጀት ዓመት ምርቱን ወደ ውጪ መላክ ተጀምሯል። በማስፋፊያና በአዳዲስ ፕሮጀክቶች አማካይነት በ2006 በጀት ዓመት 12.5 ሚሊዩን ቶን ሲሚንቶ የማምረት አቅም የተፈጠረ ሲሆን በዚህም ከሲሚንቶ የወጪ ንግድ 10.8 ሚሊዩን ዶላር ተገኝቷል። በማዳበሪያ ንዑስ አንዱስትሪ በእቅድ ውስጥ የተያዘው 300 ሺ ቶን የዩሪያ ማዳበሪያ የሚያመርት ፋብሪካ ማቋቋም ኘሮጀክት ትግበራ አፈጻጸም 75 በመቶ ላይ ደርሷል። የሣሙናና ዲተርጀንት ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ 166,000 ቶን የሣመናና ዲተርጀንት ምርት ለማምረት እንዲቻል 100 ፋብሪካዎች ለማቋቋም በተያዘው እቅድ 187 ፋብሪካዎችን በማቋቋም 300,000 ቶን የማምረት አቅም ላይ ተደርሷል። ንዑስ ኢንዱስትሪው የማምረት አቅም አጠቃቀሙ 50 በመቶ ላይ ይገኛል። የፋይናንስ አቅርቦት ችግር፣ የሰው ሀይል አቅም ውስንነት የቴክኖሎጂ አቅም ውስንነት፣ የአማራጭ የሀይል አቅርቦት አለመኖር የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት ንዑስ ዘርፍ_እቅድ አፈጻጸም ላይ ማነቆዎች ነበሩ።

**የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ** በዕቅዱ የመነሻ ዓመት 13 የነበሩትን የመድሃኒትና ህክምና መገልገያ አምራች ኢንዱስትሪዎች በ2006 በጀት ዓመት መጨረሻ ቁጥራቸው ወደ 22 ከፍ ብሏል። የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች አምራች ኢንዱስትሪዎች ቁጥር ወደ ሰባት ያደገ ሲሆን፣ የንዑስ ዘርፉ አማካይ የምርት አቅም አጠቃቀምም 60.8 በመቶ ደርሷል። በንዑስ ዘርፉ የተፈጠረው የሥራ ዕድል በ2006 የበጀት ዓመት 2,586 ደርሷል። በዕቅድ ዘመኑ ከዘርፉ 17.9 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ

ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በኢንዱስትሪው ያሉት አምራች ተቋማት አቅም አጠቃቀም እና አዲስ ኢንቨስትመንት ፍሰት ውስን መሆን፣ በሃገር ውስጥ ጥራት ያላቸው የማሸጊያ ምርት እና አቅርቦት አለመኖርና ከውጭ በሚመጣ ግብዓት ላይ ጥገኛ መሆን፣ በማስፋፊያ ፕሮጀክት ላይ ያሉትም ሆነ አዳዲስ ፕሮጀክቶች በታቀደው ጊዜ ምርት ወደ ማምረት አለመሸጋገር፣ የማኔጅመንት ችግር እና የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ የመልካም አመራረት ደረጃ /GMP level/ ዝቅተኛ መሆን፣ በምርምርና ስርፀት አለመታገዝ፣ እንዲሁም ህገወጥ የሆነ የመድሃኒት ዝውውር መኖሩ የንዑስ ዘርፉ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

**ጥራትና ምርታማነትን ማሳደግን በተመለከተ** ሀገራችን ለኢንዱስትሪ ትራንስፎርሜሽን የካይዘንን ጠቀሜታ በመረዳትና በማሸጋገር ከ2005 ጀምሮ እየተገበረች ትገኛለች፡፡ በኤክስፖርት ኩባንያዎች ውስጥ በተደረገው የካይዘን ፍልስፍና የሙከራ ትግበራ የተገኘው ውጤት ኩባንያዎቻችንን ካሉበት የተወሳሰበ ገቺ የኢንዱስትሪ ባህል በተፋጠነ ሁኔታ በማላቀቅ በዓለም ገበያ የሚፈለጉትን መሥፈርቶች አሟልተው ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማብቃት እንደሚቻል ተረጋግጧል፡፡ ስትራቴጂክ ጠቀሜታ ባላቸው ምርቶች ለምሳሌ እንደ ስኳርና ሲሚንቶ ባሉ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የአመለካከት ለውጥና ማሳያ የሚሆኑ በአሀዝ የሚገለፁ የጥራትና ምርታማነት ለውጦች ታይተዋል፡፡ በሰው ሀይል ልማት ዘርፍና በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥም ትግበራው አበረታች ውጤት አሳይቷል፡፡ ከ2005-2006 ወደ ከይዘን ፍልስፍና ትግበራ ከገቡ 93 ኩባንያዎች ውስጥ 20,467 ወንድ 12,556 ሴት በአጠቃላይ 32,950 አመራርና ፈፃሚዎችን በማሰልጠንና በ3,590 የካይዘን ልማት ቡድን በማደራጀት ለውጡን ለማስቀጠልና የጥራትና የምርታማነት ንቅናቄ ለማቀጣጠል አሰኳል የሚሆኑ የለውጥ ሠራዊት አቅም መፍጠር ተችሏል፡፡ ቤንችማርኪንግ ሌላው የምርታማነት ጥራትና ተወዳዳሪነት ማምጫ ዘዴ መሆኑ ታምኖበት የተለያዩ ሀገሮች ተሞክሮ በመቀመር ሙከራ እየተደረገ ይገኛል፡፡

**የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ዕቅድ አፈፃጸምን በተመለከተ** በመንግስት፣በግልና በሽርክና አጠቃላይ 9 ኢንዱስትሪ ፓርኮች ተከልለው የልማት እንቅስቃሴ የተጀመረ ሲሆን፣ ከነዚህ ሁለቱ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የመጀመርያ ዙር ግንባታቸው በከፊል የተጠናቀቀ በመሆኑ፣የተገነቡ የማምረቻ ኢንዱስትሪ ህንፃዎች ለግል ባለሀብቶች በኪራይ በማስተላለፍ ማምረት ጀምሯል፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ቁልፍ ማነቆዎች የተሟላ የስትራቴጂ ፍሬም ወርክ፣ የህግ ማዕቀፍ እና እይታ አለመኖር የመፈፀም አቅም ውስንነት፣ የንዑስ ዘርፎች ተኮር ኢንዱስትሪ ፓርኮች አለመኖራቸው፣ የፋይናንስ፣ የመሬት እና ማበረታቻ ውስንነት፣ የመሠረተ ልማትና ሌሎች አገልግሎት አቅራቢ ተቋማት የአቅም ውስንነትና የቅንጅት ጉድለት እና የተቀናጀ የማስተዋወቅ እና የባለሀብት መሳብ ክፍተት ዋነኞቹ ናቸው፡፡

#### 1.3.3 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች

ባለፉት አራት ዓመታት የኢንዱስትሪ ዘርፉን ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች የአመራርና የቴክኒክ ሥራ አመራር ብቃት ማነስ፣ የግብዓት አቅርቦት ዕጥረት፣ የኃይል አቅርቦት ዕጥረትና መቆራረጥ፣ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ዕጥረት፣ የቴክኖሎጂ አቅም ውስንነት፣ የትስስርና ቅንጅት ውስንነት፣ ኪራይ ሰብሳቢነት፣ ኢንቨስትመንትን በጥራትና በብዛት መሳብ አለመቻል፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል ዕጥረት፣ የትራንስፖርት፣ የሎጅስቲክስና የፋይናንስ አቅርቦት ውስንነት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 1.4 የንግድ ዘርፍ ዕቅድ አፈፃፀም

### 1.4.1 የንግድ ዘርፍ ዕቅድ ዓላማና አቅጣጫዎች

የንግዱ ዘርፍ ከሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ባለው ቁርኝትና ለሀገሪቱ ዕድገትና ልማት የሚያበረክተውን ጉልህ ሚና ለማረጋገጥ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግልጽነትን፣ ተደራሽነትንና ውድድርን መሠረት ያደረገ፣ ሸማቹን፣ የንግዱን ማህበረሰብና አምራቹን የሚያረካ የተረጋጋ ገበያና ፍትሃዊ

የንግድ ሥርዓት እንዲኖር የማድረግ፣ ሀገሪቱን ከዓለም አቀፍ የንግድ ሥርዓቱ ተጠቃሚና ተዋናይ እንደትሆን የማስቻል እና የውጭ ምንዛሪ ገቢ ግኝትን የማሳደግ አቅጣጫ አስቀምጦ ወደ ትግበራ ገብቷል፡፡

### 1.4.2 የንግድ ዘርፍ ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም

**ልማታዊ የንግድ ሥርዓት መፍጠሪያ ሪፎርም አፈፃፀምን በተመለከተ** የንግድ አሰራርን ግልጽና ፍትሃዊ ለማድረግ እንዲሁም በንግዱ ዘርፍ የተሻለ ሀገራዊ መረጃ እንዲኖር፣ የሸማቾች መብት እንዲጠበቅና ተገልጋዩ የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ረገድ በሀገሪቱ ውስጥ ወጥና ተመሳሳይነት ያለው የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ የንግድ ውድድርን የማፋጠን እና የሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣንን የማደራጀት ሥራዎችም ተሰርተዋል፡፡

**በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ** መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥን በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የማድረግ ተግባር ተከናውኗል፡፡ በዕቅዱ የትግበራ ዓመታት በኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ለባለሀብቶች የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት የአንድ መስኮት አገልግሎት እንዲያገኙ የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋ ሲሆን በተቋሙ ለውጭ ባለሃብቶች፣ ከክልል ለሚመጡና በኤክስፖርት ሥራ ለተሰማሩ ባለሃብቶች የተለዩ የአገልግሎት መስኮቶች በመክፈት የተሻለ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል፡፡

**በንግድ ግንኙነትና ድርድር** ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት አንፃር ባለፉት አራት የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዓመታት ሀገሪቱን የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ለማድረግ የእንድምታ ጥናቶችን የማኬድና የመገምገም፣ የድርድር ሰነዶችን የማዘጋጀት፣ ከአባል ሀገራት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ የማዘጋጀትና የመልቲ-ላተራልና የባይ-ላተራል ድርድሮችን የማካሄድና የማጠናቀቅ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ የገበያ መዳረሻዎችን ለመለየት የሚያስችሉ ጥናቶችን የማካሄድ፣ የተገኙ የገበያ ዕድሎችን አሟጦ የመጠቀም፣ የዕንድምታ ጥናቶችን የማካሄድና የመገምገም፣ ከተመረጡ የገበያ መዳረሻ ሀገሮች ጋር የንግድ ድርድር የማካሄድ፣ ስምምነቶችን የመፈራረም፣ የጋራ ኮሚሽን ስብሰባዎችን እና የአካባቢያዊ ድርድሮችን የማካሄድ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

**ዘመናዊ የምርት ግብይት ሥርዓት ከማጎልበት አንፃር** የምርት ግብይቱን ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ግልፅና ፍትሀዊ በማድረግ፣ በአቅርቦትና በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የምርት ዋጋ እንዲኖርና አምራቹ ላመረተው ምርት ተመጣጣኝ ዋጋ በማግኘት የማምረት ሥርዓት ውስጥ በማስገባት በሀገራችን የተጀመረውን የግብርና ትራንስፎርሜሽን ለማሳካት የቡና 1,500፣ የሰሊጥ 229 እና የነጭ ቦሎቄ 170 የመጀመሪያ ደረጃ ገበያን የማደራጀት ሥራ ተከናውኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግብረ-ሃይል አባላትን በማቋቋምና ግንዛቤ በመፍጠር ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት በመዘርጋት በተቀመጠው የግብይት ሥርዓት ብቻ የሚገበያዩበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡ በተመሳሳይ ባለፉት አራት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት ገበያ ተኮር ምርቶችን በዘመናዊ ግብይት ሥርዓቱ ውስጥ በማስገባት የሀገር ውስጥ ግብይቱን በሥርዓት ለመምራት እንዲያስችል በቋሚነት የግብይት ተሳታፊ አባላትን ቁጥር ወደ 347 እንዲሁም የአገናኝ አባላት ደንበኞችን ቁጥር ወደ 12,612 ማድረስ ተችሏል፡፡ የኤሌክትሮኒክስ ግብይትን ለመጀመር የሚያስፈልጉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማከናወን ኤሌክትሮኒክስ ግብይትን ተግባራዊ የማድረግና የተጀመረውን የግብይት ሥርዓት የማዘመን ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡

### 1.4.3 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች

በንግድ አሠራርና ውድድር ላይ በቂ ግንዛቤ አለመኖር፣ የአቅም ውስንነት፣ በአመለካከትና በተግባር የሚገለፅ ኪራይ ሰብሳቢነት፣ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱን በአገር አቀፍ ደረጃ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግ የተጀመረው ጥረት አዝጋሚ መሆን፣ የገበያ እድሎችን በበቂ

መጠን መጠቀም አለመቻል፣ የግብይት ማዕከላት በበቂ ሁኔታ አለመደራጀት ለተደራጁትም ማዕከላት በቂ የመሰረተ ልማት አለመሟላት፣ በዘመናዊ የግብይት ሥርዓቱ የታቀፉ ምርቶች አነስተኛ መሆን፣ የአገሪቱ የአመራረት ዘዴ ገበያ መር ያለመሆንና ምርት በሚፈለገው መጠንና ጥራት በተከታታይነትና በተወዳዳሪ ዋጋ ለገበያ ማቅረብ አለመቻል፣ በሀገሪቱ ሎጂስቲክስ አቅርቦት አለመዳበር ምክንያት ምርትን ለገበያ በወቅቱ በማድረስ፣ በዋጋ ተወዳዳሪነትና በተፈላጊነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ፣ የገበያ ማስፋፊያና ትስስር ሥራዎች ደካማ መሆን ባለፉት አራት ዓመታት የንግድ ዘርፉን ያጋጠሙ ፈተናዎች ናቸው፡፡

## 1.5 የማዕድን ልማት ዕቅድ አፈፃፀም

### 1.5.1 የማዕድን ልማት ዕቅድ ዓላማና አቅጣጫዎች

በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች፤ ኢንቨስትመንትን የሚያስፋፉ ፖሊሲዎችንና ሕጎችን በመቀየስ ልማቱን መምራት፣ የጂኦሳይንስ መረጃዎችን አሰባስቦ ለተጠቃሚዎች የማቅረብና ዝርዝር የማዕድናት ፍለጋና ጥናት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ ሲሆኑ የማዕድን ዘርፍ ለኢኮኖሚው የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ለማጉላት እንዲሁም የግሉ ዘርፍ በማዕድን ልማት ዙሪያ ከፍተኛ ሚና እንዲኖረው ማድረግና የውጭ ምንዛሬን ማስገኘትና ለሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆኑ ማዕድናት እንዲመረቱ በማድረግ ለዚህ ተብሎ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ማዳን ነው፡፡

### 1.5.2 የማዕድን ልማት ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም

መሠረታዊ የሥነ-ምድር መረጃ ሽፋንን ከማሳደግ አኳያ በ1፡250,000 መስፈርት የሀገሪቱን የሥነ-ምድር መረጃ ካርታ ሽፋን በአማካይ በ2002 ከነበረበት 34 በመቶ ወደ 63 በመቶ ለማድረስ የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የሀገሪቱን የጂኦሎጂ ካርታ ሽፋን በ2002 ከነበረበት 51 በመቶ ወደ 82 በመቶ ለማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የሀገሪቱን የሀይድሮጂኦሎጂ ካርታ ሽፋን በ2002 ከነበረበት 42 በመቶ ወደ 79 በመቶ ለማድረስ የተቻለ ሲሆን የሀገሪቱን የጂኦሃዛርድ ጥናት ሽፋን በ2002 ከነበረበት 9.6 በመቶ ወደ 29 በመቶ ለማድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በሀገሪቱ ውስጥ በተለያዩ አካቢዎች የኢንዱስትሪ ማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግምት ከ1፡50,000 መስፈርትና በላይ በማካሄድ በ2002 ከነበረበት 48 አለኝታ ቦታዎች ቁጥር ወደ 74 ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

የሀገሪቱን የቆዳ ሽፋን በአየር ወለድ ጂኦፊዚክስ ሰርቬይ ወደ 95 በመቶ ለማሣደግ፣ የድንጋይ ከሰል ክትትል ፍለጋና ክምችት ወደ 20 አለኝታ ቦታዎች ለማሣደግ፣ የኦጋዲን ቤዚን ፔትሮሊየም ፍለጋን ወደ 165,000 ስ.ኪ.ሜ ለማድረስ የተያዙት ግቦች አፈፃፀማቸው በሰለጠነ የሰው ኃይል እና በበጀት እጥረት ምክንያቶች ደካማ ሆኗል፡፡ እንዲሁም ሰባት ኩባንያዎች አሥራ አምስት የነዳጅ ፍለጋና ምርት ክፍፍል ስምምነቶችን ወስደው በተለያዩ ሀገሪቱ ክፍሎች በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙ ሲሆን የተወሰኑ የነዳጅ ፈላጊ ኩባንያዎች የሳይዝሚክ ጥናታቸውን አጠናቀው የቁፋሮ ሥራ አካሂደዋል፡፡

የውጭ ምንዛሬን ከማሳደግ አኳያ በኩባንያዎችም በኩል ተመርተው ለገበያ ከቀረቡ ማዕድናት 846 ሚሊዩን የአሜሪካ ዶላር እና ከባህላዊ አምራቾች ለገበያ ከቀረቡ ማዕድናት 1.94 ቢሊዩን ዶላር በአጠቃላይ 2.8 ቢሊዩን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሬ መስገኘት ተችሏል፡፡ የሀገር ውስጥ ገቢ መሰብሰብን በተመለከተ በማዕድን ሥራ ላይ ከተሰማሩ ባለፍቃዶች ዓመታዊ ገቢው 385 ሚሊዮን ብር የደረሰ ሲሆን ይህም በ2002 ከተገኘው ዓመታዊ ገቢ 69 ሚሊዮን ብር ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ነው፡፡ ከፔትሮሊየም ፍለጋና ጥናቶች ላይ ከተሰማሩ ኩባንያዎች 34 ሚሊዩን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡

በማዕድን ዘርፍ ከቻይና ጋር ያለውን ግኑኙነት ለማጠናከር በተሠራው ሥራ የኢትዮ-ቻይና የጋራ ትብብር ፕሮጀክት በመቅረፅ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በ148 ካሬ ኪሎ ሜትር ላይ የማዕድን ፍለጋ እና ጥናት

በመካሄድ ላይ ነው፡፡ የባህላዊ ማዕድን አምራቾችን ከመደገፍ አኳያ ለባህላዊ ማዕድናት አምራቾች ምርትን የሚያሣድጉ የአመራረት ዘዴና የአካባቢ ጥበቃ ሥልጠናዎች፣ የማምረቻ መሣሪያዎች እና የገበያ ትስስር ድጋፍ ተሰጥቷቸዋል፡፡ እንዲሁም የሴቶችን ተጠቃሚነት ባገናዘበ መልኩ የህብረት ሥራ ማህበራትና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞችን የማደራጀትና የማጠናከር ተግባራት ተሰርተዋል፡፡

በልማት ዕቅዱ ዘመን ዘርፉን ካጋጠሙት ተግዳሮቶች መካከል ዘርፉን የማስተዳደር አቅም ውስንነት፣ ጥራቱን የጠበቀ መረጃ ያለማቅረብና በቂ የማስተዋወቅ ሥራ አለመስራት፣ አቅም ያላቸውን ባለሀብቶች መልምሎ ወደ ሥራ አለማስገባት፣ የክልሎችን አቅም አለመገንባት፣ ተቀናጅቶ አለመስራትና ከሌሎች ተቋማት ጋር የነበረው ቅንጅታዊ አሠራር ደካማ መሆን ዋና ዋናዎቹ ችግሮች ነበሩ፡፡

### 1.5.3 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች

ባለፉት አራት ዓመታት በዘርፉ የአፈፃፀም ሂደት ካጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች መካከል ዘርፉን በብቃት ለማስተዳደር የሚያስችል የአቅም ውስንነት፣ ጥራቱን የጠበቀ መረጃ በጊዜው ማቅረብ አለመቻልና አለማቅረብ የማስተዋወቅ ሥራ በሚገባ አለመስራት፣ አቅም ያላቸው ባለሀብቶችን መልምሎ ወደ ሥራ ለማስገባት ያለው አቅም አናሳ መሆን፣ የክልሎች የማስፈፀም አቅም ደካማ መሆንና በቅንጅት ለመስራት ያለው ዝንባሌ አናሳ መሆን፣ ከሌሎች ተቋማት ጋር የነበረው ቅንጅታዊ አሠራር ደካማ መሆን የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 1.6 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አፈፃፀም

### 1.6.1 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ አፈፃፀም በተመለከተ

በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን የማስፈፀም አቅም ለመገንባት ብዙ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከነዚህም ዉስጥ በታህሳስ 26 ቀን 2006 የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ማዕቀፍ በመንግስት ፀድቆ ሥራ ላይ እንዲዉል የተደረገ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩትም ተቋቁሞ ሥራ እንዲጀምር ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዓመታት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን የማስፈፀም አቅም ብሎም ተወዳዳሪነት አቅም ለመገንባት የሚያስችል የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ስትራቴጂክ ሪፎርም ፕሮግራም ተዘጋጅቷል፡፡ ክልሎችና ከተሞች አሁን ያሉበትን ደረጃ በማመዛዘን የሕንፃ አዋጅ፣ ደንብ እና ተንዳኝ መመሪያዎች ተግባራዊ በሚሆንባቸው 248 ከተሞች አስፈላጊ አደረጃጀት እንዲፈጠሩና ወደ አፈፃፀም እንዲገቡ ለማድረግ ታቅዶ በ126 ከተሞች አስፈላጊ አደረጃጀት ተፈጥሮ ወደ አፈፃፀም ገብተዋል፡፡ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በአራት ተከታታይ ዓመታት 12 ዓለም አቀፍ የተወዳዳሪነት አቅም ያላቸው ሥራ ተቋራጮችን ለማፍራት ታቅዶ 8 የሚሆኑ በዚህ ደረጃ የደረሱ ተቋማት እና 17 አለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ደረጃ ያላቸው አማካሪዎችም ተፈጥረዋል፡፡

### 1.6.2. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በመሠረተ ልማት ግምባታው ያሳየው አፈጻጸም

ባለፉት አራት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዓመታት የኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ አማካይ ዕድገት 29.9 በመቶ የነበረ ሲሆን ዘርፉ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት የነበረው ድርሻ በ2002 ከነበረበት 4.0 በመቶ በ2006 ወደ 7.6 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በለፈው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታ የነበረው አፈጻጸም ከፍተኛ ነበር፡፡ ከዚህም አንፃር በንጹህ ውሃ አቅርቦት ልማት ዘረፍ 66,345 አዳዲስ የውሃ ተቋማት ግንባታ ያከናወነ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 66,139 በገጠር፤ 206 በከተማ ነው፡፡ ይህ አፈጻጸም በገጠር የእቅዱን 98 በመቶ እና በከተማ የዕቅዱ 44.5 በመቶ ነበር፡፡ በመካከለኛና የሰፋፊ መስኖና ድሬኔጅ ልማት ዘርፍ በመጀመሪያው የዕትዕ የዕቅድ ዘመን የ672,537 ሄክታር

የጥናትና የዲዛይን ስራ ዕቅድ መሰረት፤ 650,470 ያህሉን ሄክታር የጥናትና የዲዛይን ስራ ያከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 96.7 በመቶ ነው፡፡ በግንባታ በኩል ከታቀደው የ559,865 ሄክታር የመስኖ የግንባታ ስራ 199,304 ሄክታር ግንባታ ማከናወን የቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 35.6 በመቶ ነው፡፡

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ያለፉት አራት ዓመታት አፈጻጸም የፌደራልና ክልል መንገዶችን ከ48,800 ኪ.ሜ. ወደ 61,771 ኪ.ሜ ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሎ 11,666 ኪ.ሜ. ርዝመት ያለው ተጨማሪ መንገድ በመገንባት በ2006 የመንገድ አውታሩን ወደ 60,466 ኪ.ሜ. ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተያያዘም ክረምት ከበጋ የሚያስኬዱ 55,790 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው የወረዳ መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 39,056ኪ.ሜ ወይም የዕቅዱ 54.6 በመቶ ተከናውኗል፡፡ በኃይል ማመንጫ መሰረተ ልማት ግንባታ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በ2002 ዓ.ም ተደርሶበት ከነበረው 2000 ሜዋ ወደ 8,000 ሜዋ ከፍ ለማድረግ በተያዘው ግብ መሰረት ከተያዙት ፕሮጀክቶች 1,870 ሜ.ዋ. የሚያመነጨው የግልገል ግቤ 3ኛ ግንባታ፣ 153 ሜጋ ዋት የሚያመነጨውን የነፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ግንባታ እንዲሁም ከደረቅ ቆሻሻ 50 ሜጋ ዋት ማመንጫ ፕሮጀክት ግንባታ በተያዘለት የግዜ ገደብ በመገንባት ሥራ ላይ እንዲውል አድርጓል፡፡

በተጨማሪም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመኑ በከተሞች የተቀናጀ ቤቶች ልማት ፕሮግራም እና በከተማ መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም ላይ ጉልህ ሚና ተጫውቷል፡፡ በመሆኑም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመኑ የመጀመሪያ ሶስት ተከታታይ ዓመታት በድምሩ 95 ሺህ ቤቶችን መግንባት የተቻለ ሲሆን የግቡ የሶስት ዓመታት አፈጻጸም ከአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ ቤቶችን ጨምሮ 105.6 በመቶ ላይ አድርሶታል፡፡ የከተማ መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራምን ከማስፈፀም አንፃር ኢንዱስትሪው በ2005 በጀት ዓመት በከተሞች 765.3 ኪ.ሜ. ርዝመት ያለው የድንጋይ ንጣፍ መንገድ (Coble Stone) ለመገንባት ታቅዶ 829.4 ኪ.ሜ ያህል ርዝመት ያለው የድንጋይ ንጣፍ መንገድ መገንባት ተችሏል፡፡

የኮንስትራክሽን ኢንድስትሪዉ የትምህርት እና የጤና ተቋማትን ከመገንባት አንፃር በመጀመሪያዎቹ ሦስት ተከታታይ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት በድምሩ 3,680 የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶችን(1-8) ግንባታ አከናዉኗል፡፡ በተጨማሪም ኢንዱስትሪዉ 1,856 የጤና ኬላዎች እና 1,058 ጤና ጣቢያዎች ግንባታ ማካሔድ የቻለ ሲሆን፤ በዕትዕ መጀመሪያ 116 የነበረውን የሆስፒታል መጠንም ወደ 127 ከፍ እንድል አድርጓል፡፡

### 1.6.3. ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ ከሚታዩት ችግሮች አንዱ የተቋራጮች አቅም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር 95 በመቶ ያህሉ የሥራ ተቋራጮች ከደረጃ 4-10 ዉስጥ የሚገኙና ዝቅተኛ ቴክኖሎጂዎችን እና የግንባታ ዘዴዎችን የሚጠቀሙ፣ በዘመናዊ የአስተዳደርና የፋይናንስ ሥርዓት የማይመሩና ብዙ ልምድ በሌላቸውና በተቋሙ አጭር የቆይታ ጊዜ ባላቸው ባለሙያዎች የሚካሄዱ በመሆናቸው በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አፈጻጸም ወቅቱ በሚጠይቀው ደረጃ ምርታማ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል:: ሌላው የኢንዱስትሪው ችግር መንስኤ የልዩና ንዑስ ተቋራጭነት ልምድ ያለመኖር ነው:: በተለይ እንደ ኮንክሪት ሥራ፣ የመሰረት ሥራ፤ የብረት ሥራ፣ ኤሌክትሮሜካኒካል፣ የሳኒታሪና የውስጥ ማስዋብ የሥራ ዲሲፕሊኖች የተደራጁ ልዩና ንዑስ ተቋራጮች በኢንዱስትሪው ውስጥ አለመኖር በፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ ትልቅ ጫና አሳድሯል፡፡

በአማካሪ ድርጅቶች በኩልም በአቅምና የብቃት ማነስ ሳቢያ ሥራዎች በውለታ መሠረት በተፈለገው ጊዜና የጥራት ደረጃ ያለመጠናቀቅ፤ ዲዛይኖች በጥንቃቄ የማይሰሩና የተሟሉ አለመሆናቸው፣ በዚህም ምክንያት የገንዘብ መጠን ለውጥ የሚከሰት መሆኑ እንደ አንድ ተግዳሮት ሊገለጽ የሚችል ነዉ፡፡ የኮንስትራክሽን ግብዓት ጥራት መቆጣጠሪያ ማዕከላዊ ላቦራቶሪ አለመኖርና እንዲሁም ኢንዱስትሪው በዘርፉ የተፈጠሩ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የሚቀዳበትና የሚያላምድበት ፈጣን የመረጃ ምንጭ አለመኖሩና ስርዓትም

አለመዘርጋቱ ሌላው የዘርፉ ተግዳሮት እንደሆነ ተለይቷል፡፡ የሚመረጡ የግንባታ ዕቃዎች በአገር ውስጥ የማይገኙ፣ያልተሞከሩና በአጠቃቀማቸው ላይ በቂ ዕውቀት ያለመኖር፣በባለቤቱና በሥራ ተቋራጩ መካከል ለሚነሱ ጥያቄዎችና አለመግባባቶች ወቅታዊ ምላሽ ያለመስጠት ወዘተ ችግሮች በስፋት ይስተዋላል፡፡

## 1.7 የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት ዕቅድ አፈፃፀም

### 1.7.1 የመሠረተ ልማት ዕቅድ ዓላማና አቅጣጫዎች

በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የኢኮኖሚ ዕድገቱ እንዲፋጠን የሚያስፈልጉ የትራንስፖርት፣ የኮሙዩኒኬሽንና የኃይል አቅርቦትን በጥራትና በተወዳዳሪ ዋጋ ማቅረብ፣ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ለመሠረተ ልማት መስፋፋት የሚያስፈልጉ አገልግሎቶችና ቁሳቁሶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱና ሀገራዊ ኢንዱስትሪው እንዲስፋፋ ማድረግ የመሠረተ ልማት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡ እነዚህን አቅጣጫዎች በመያዝና ግቦችን በማቀመጥ ባለፉት አራት ዓመታት በመሠረተ ልማት ዙሪያ ስኬታማ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

### 1.7.2 የመሠረተ ልማት ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም

### ሀ) የመንገድ መሠረተ ልማት

በመንገድ ዘርፍ ባለፉት አራት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዓመታት የተጀመረውን የዋና ዋና መንገዶች ግንባታ ሥራ አጠናክሮ መቀጠል፣ የገጠር መንገድን ማሻሻልና ክረምት ከበጋ የሚያገለግሉ መንገዶችን ከሞላ ጎደል በሁሉም ቀበሌዎች እንዲዳረሱ ለማድረግ ትኩረት ተሰቶ ርብርብ ሲደረግ በመቆየቱ የሀገሪቱ የመንገድ መሠረተ ልማት ሽፋንን ከምንጊዜውም በተለየ ሁኔታ ለማሳደግ ተችሏል፡፡ ከዚህም አኳያ ሁሉንም የገጠር ቀበሌዎች ክረምት ከበጋ በሚያገናኝ የገጠር መንገድ እርስ በእርስ ለማገናኘት በተያዘው ትልቅ ትልም ተስፋ ሰጪ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ በዚህም የገጠር መንገድ ተደራሽነቱን ከማሳደግ ባሻገር የግንባታ ሥራ ተቋራጮችን እና አማካሪዎችን በማደራጀት ወደ መስኩ በስፋት እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሥራ እድል በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ ሥራ ተሰርቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ባለፉት አራት ዓመታት የፌዴራል እና ክልል ጠቅላላ የመንገድ ርዝመት (በኪ.ሜ) በዕቅዱ የመነሻ ዓመት በ2002 ከነበረበት 48,800 ኪ.ሜ. በ2006 በጀት ዓመት 60,466 ኪ.ሜ ደርሷል፡፡ ባለፉት አራት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት 39,056 ኪ.ሜ ክረምት ከበጋ የሚያስኬድ የወረዳ መንገድ ተገንብቷል፡፡ ክረምት ከበጋ በሚያስኬድ መንገድ የተገኙ ቀበሌዎች ሽፋን በ2002 ከነበረበት 39 በመቶ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 68 በመቶ ደርሷል፡፡ እንዲሁም የመንገድ ጥግግት በ2002 ከነበረበት የ44.5 ኪ.ሜ/1000ኪ.ሜ$^2$ በ2006 ወደ 90.5 ከፍ ያለ ሲሆን በአማካይ ወደ ክረምት ከበጋ የሚያስኬዱ መንገዶች ላይ ለመድረስ የሚወስደው ጊዜ በ2002 ከነበረበት የ3.7 ሰዓት በ2006 ወደ 1.8 ሰዓት ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡ ተሽከርካሪ በአማካይ በቀን የሚሸፍነው ርቀት በ2002 ከነበረበት 9.6 ሚሊዮን ኪ.ሜ. በ2006 በጀት ዓመት ወደ 13.6 ሚ.ኪ.ሜ.ከፍ ብሏል፡፡

### ለ) የባቡር መሠረተ ልማት

የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋና መለያ (Major Departure) ከሆኑት መካከል አንዱ የባቡር መሠረተ ልማት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በሶስት ኮሪደሮችና በአምስት መስመሮች የ2,395 ኪ.ሜ. ሀገራዊ የባቡር መስመር ለመገንባት ግብ ተጥሎ ነበር፡፡ ይህንን ግብ ለማሳካት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችና የውጭ የልማት ፋይናንስ ፍሰት ጊዜ የወሰዱ ቢሆንም ባለፉት አራት ዓመታት ወደ ግንባታ በመግባት በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚህም የአዲስ አበባ/ሰበታ-ሚኤሶ (317 ኪ.ሜ.) እና የሚኤሶ-ደወንሌ (የ339 ኪ.ሜ.) የባቡር መስመር ግንባታ 45 በመቶ ተጠንቅቋል፡፡

የመቀሌ-ሀራ ገበያ (268 ኪ.ሜ.) እና የሀራ ገበያ-ሰመራ-አሳይታ (229 ኪ.ሜ.) ከሥራ ተቋራጮች ጋር የEPC/Turnkey የኮንትራት ስምምነት ተፈርሞላቸው ወደ ግንባታ ለመግባት በዝግጅት ላይ ይገኛሉ። ከእነዚህ ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ያለው ትልቅ ፈተና ለፕሮጀክቶቹ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልገው የውጭ ብድር ያለመለቀቁ ነው። የግንባታ ዝግጅት እየተደረገላቸው ያሉ ፕሮጀክቶች ደግሞ የአሳይታ-ታጁራህ ወደብ (210ኪ.ሜ.)፣ የአዲስ አበባ/ሰበታ-ኢጃጂ-ጂማ-በደሌ (496 ኪ.ሜ.) እና የሞጆ-ሻሸመኔ-ቦዲቲ-ወይጦ (556 ኪ.ሜ.) ናቸው። እነዚህን የባቡር ፕሮጀክቶች በተመለከተ የኮንትራት ዝግጅትና የፋይናንስ ማፈላለግ ሥራ በመሠራት ላይ ይገኛል። በባቡር የመሠረተ ልማት ዘርፍ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተያዘው ሌላው ዕቅድ የ34 ኪ.ሜ. የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ግንባታ ፕሮጀክት ነው። ይህንን ፕሮጀክት በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ መሠረት ተፈፃሚ ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ በመደረግ ላይ ሲሆን እስከ 2006 የበጀት ዓመት መጨረሻ የፕሮጀክቱ የግንባታ ሥራ 73 በመቶ ተጠናቅቋል። የፕሮጀክቱ የግንባታ ሥራ እስከ 2007 መጨረሻ ሙሉ በሙሉ ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል።

የባቡር መሠረተ ልማት በሀገራችን አዲስ እንደመሆኑ በዘርፉ ያለው ዕውቀት፣ የቴክኖሎጂ ደረጃ፣ ፕሮጀክቱን የማስተዳደርና ፋይናንስ የማፈላለግ አቅም ውስንነቶች ቢታዩም የፕሮጀክቶችን የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በማጠናቀቅና ለተወሰኑት ፕሮጀክቶች የውጭ የልማት ፋይናንስ በማፈላለግ የግንባታ ሥራዎችን መጀመርና ፕሮጀክቶችን አሁን ባሉበት ደረጃ ማድረስ በራሱ ትልቅ ስኬት እና ቀጣይ ሀገራዊ አቅም ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል።

## ሐ) የኢነርጂ መሠረተ ልማት

በሀገራችን ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማምጣት እየተደረገ ያለውን ጥረት ለመደገፍ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ጠቅላላ የሀይል ማመንጨት አቅምን በ2002 ከነበረበት 2000 ሜጋ .ዋት በ2007 ወደ 8,000 ሜጋ ዋት ለማድረስ ታቅዶ ነበር። ይህንን ዕቅድ ተፈፃሚ ለማድረግ የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋና መለያ የሆኑ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት (6,000 ሜጋዋት)፣ የግልገል ጊቤ ሶስት የውሀ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት (1,870 ሜጋ ዋት)…ወዘተ እና የነፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ግንባታ በመካሄድ ላይ ይገኛል። እስከ 2006 የበጀት ዓመት መጨረሻ የታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት አፈፃፀም 40 በመቶ የደረሰ ሲሆን የግልገል ጊቤ ሶስት የውሀ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክትም የ89 በመቶ አፈፃፀም አስመዝግቧል። እንዲሁም የገናሌ ሶስት የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት (254 ሜጋ ዋት) አፈፃፀም 65 በመቶ ደርሷል። የፊንጫ አመርቲ-ነሸ የውኃ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ግንባታ ተጠናቅቆ ኃይል ማመንጨት ጀምሯል። ባለፉት አራት ዓመታት ከታዳሽ ምንጮች ኃይል የማመንጨት አማራጮችን በማስፋት የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ግንባታ ሲካሄድ ቆይቷል። በዚህም የአሸጎዳ የነፋስ ኃይል ማመንጫ እና የአዳማ ቁጥር አንድ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ግንባታ ተጠናቅቆ ኃይል ማመንጨት ጀምረዋል። በአጠቃላይ በኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች በአማካይ (weighted average) የ52 በመቶ የግንባታ አፈፃፀም የተመዘገበ ሲሆን በ2006 መጨረሻ የ2,220.5 ሜጋ ዋት ኃይል የማመንጨት አቅም ተፈጥሯል። ለዕቅዱ አፈጻጸም በዚህ ደረጃ ላይ መገኘት በተለይ የግዙፍ የሀይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ግንባታ ከአምስቱ ዓመት የዘለለ የትግበራ መርሀ ግብር እንደሚኖራቸው ታቅዶ የነበረ በመሆኑ ነው። በተመሳሳይ 4,775 ኪሎ ሜትር የሀይል ማስተላለፊያ መስመር ለመዘርጋት ታቅዶ 1,385 ኪሎ ሜትር (29 በመቶ) ተከናውኗል። በዚህም በ2002 በጀት ዓመት የነበረው ጠቅላላ የማስተላለፊያ መስመሮች ርዝመት ከ11,440 ኪሎ ሜትር በ2006 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 12,825 ኪሎ ሜትር ከፍ ብሏል። ባለፉት አራት ዓመታት ተጨማሪ 85,800 ኪሎ ሜትር የኃይል ማሰራጫ መሥመር ለመዘርጋት ታቅዶ 30,147.5 ኪሎ ሜትር (35.1 በመቶ) ተከናውኗል። ባለፉት አራት ዓመታት ከተዘረጉ የሀይል ማስተላለፊያ መስመሮች መካከል 397 ኪ.ሜ ባለ 400 ኪ.ቮ. መስመር ይገኝበታል። በዚህም አጠቃላይ የሀይል ማስራጫ መስመር ርዝመትን በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 126,038 ኪ.ሜ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 156,185.5 ኪ.ሜ. ከፍ ማድረግ ተችሏል። እንዲሁም የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሽፋንን በ2002 ከነበረበት 41 በመቶ በ2006 ወደ 54.44 በመቶ ከፍ ማድረግ ተችሏል። የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ደንበኞችን ብዛት በ2002 ከነበረበት 2.03 ሚሊዮን በ2006 በጀት ዓመት ወደ 2.58 ሚሊዮን ማድረስ ተችሏል።

**የአማራጭ የኢነርጂ ንዑስ ዘርፍን በተመለከተ** በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 9.415 ሚሊዮን የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን ለማሰራጨት ታቅዶ ባለፉት አራት ዓመታት 6.58 ሚሊዮን የተሰራጨ ሲሆን የባዮጋዝ ቴክኖሎጂ ሥርጭትም በዕቅድ ዘመኑ 26,000 ፕላንቶችን ለመገንባት ታቅዶ ባለፉት አራት ዓመታት 9,139 ፕላንቶች ተገንብተዋል፡፡ በቴክኖሎጂው ሥርጭት ሳቢያ 96,361 ሄክታር የሚሸፍን ደን ለማገዶነት ከመጨፍጨፍ ድኗል፣ ወደ አየር ይለቀቅ የነበረው 6,675,485 ቶን የካርቦን ልቀት መጠን ቀንሷል፡፡ የፀሐይ ኃይል ቴክኖሎጂ ሥርጭትና ተከላን በተመለከተ በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 3.16 ሚሊዮን እንዲሁም ባለፉት አራት ዓመታት አፈጻጸም 2.02 ሚሊዮን የፀሐይ ኃይል ቴክኖሎጂዎች ሥርጭትና ተከላ በማካሄድ ሕብረተሰቡን የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ የ1.02 ሚሊዮን (51 በመቶ) ቴክኖሎጂዎች ሥርጭትና ተከላ ተካሂዷል፡፡

ለባዮፊውል የሚውል መሬት መረጃን ከማደራጀት አኳያ ለባዮፊውል ልማት ሊውል የሚችል 23 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለመለየት ታቅዶ 16.6 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በባዮ ዲዝል ተክሎች (ጃትሮፋ፣ካስተር ወዘተ…) በመልማት ላይ ያለና የሚለማ መሬት የተለየ ሲሆን አፈጻጸሙም 73 በመቶ ነበር፡፡ በነዳጅ ተቋማት የመቀየጫ ፋሲሊቲዎች እንዲገነቡና ለቅይጥ የሚውል ባዮፊውል እንዲቀርብ ከማስተባበር ጋር በተገናኘ 4 የኢታኖል መቀየጫ ፋሲሊቲዎችን ለመገንባት ታቅዶ 3 የተገነቡ ሲሆን አፈጻጸሙም 75 በመቶ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የኢታኖል ምርት 77.38 ሚሊዮን ሊትር ለማምረትና የኢታኖል ቅይጥ 64.38 ሚሊዮን ሊትር ለመቀየጥ ታቅዶ 50.33 ሚሊዮን ሊትር ለማምረትና 46.87 ሚሊዮን ሊትር ለመቀየጥ የተቻለ ሲሆን ይህም አፈጻጸሙ በቅደም ተከተል 65.04 በመቶ እና 72.38 በመቶ ነው፡፡

### መ) ቴሌኮሙኒኬሽን

ኢትዮ-ቴሌኮም በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የኔትዎርክ አቅሙን በማሳደግ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትንና የዋጋ ተወዳዳሪነትን በማረጋጥ፣ የአገልግሎት ተደራሽነትን በማስፋት እና ዘመኑ ያፈራቸውን ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም የአገልግሎቱን ጥራትና ፍታሃዊነት በጠበቀ መልኩ በመላ ሀገሪቱ ያለውን የመረጃ አቅርቦት ክፍተት ለማጥበብ ሰፋፊ ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ የተቋሙን ብቃት ወደ ላቀ ደረጃ ከማሸጋገር እና አለም አቀፍ ተወዳዳሪነቱን ከማረጋገጥ አኳያ የሥራ ሂደቶቹ አደረጃጀት ዓለም አቀፍ ልምድና ስታንዳርድን በመከተል እንዲደራጅ የተደረገ ሲሆን በዚህም መሰረት የተቀረፁት የሥራ ሂደቶችና የተለያዩ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች ልምድ ባለው ማኔጅመንት ተደግፎ ለመፈጸም እንዲቻል ከፍራንስ ቴሌኮም ጋር የማኔጅመንት ኮንትራት ውል በመፈራረም ከፍተኛ የማኔጅመንት ልምድ መቅሰም ተችሏል፡፡ በዚህም ዓለም አቀፍ ልምዶችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን መሠረት ያደረገ አደረጃጀትና የሥራ ሂደት ሥርዓት መፍጠር፣ ውጤታማ የሆነ የቢዝነስ ሥርዓት መዘርጋት እንዲሁም ዓለም የሚጠቀምበትን ቴክኖሎጂ መተግበር የሚችል የሰው ኃይል ማፍራት ተችሏል፡፡

የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ከማረጋገጥ አኳያ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የቴሌኮም አገልግሎትን በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ለደንበኞች ማድረስ እንዲቻል የጥራት ቡድኖችን በማቋቋም አበረታች ሥራ ተሰርቷል፡፡ በአዲስ አበባ እና በክልል ከተሞች ከፍተኛ የኔትዎርክ ችግር ለነበረባቸው አከባቢዎች ትኩረት በመስጠት አማራጭ የኔትወርክ መስመሮችን ለመፍጠር ነበሩን የኦፕቲካል ፋይበር መስመር ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል (Optical Ground Wire Network) ጋር የማገናኘት ሥራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም የኔትወርክ የጥራት ደረጃን መለካት የሚያስችል ሥርዓት (End-to-end Service Quality Test System) ሥራ እንዲጀምር ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል 298,639 የመደበኛ ስልክ ደንበኞችን ከነባር ማዞሪያ (legacy PSTN) ወደ ቀጣዩ ትውልድ ኔትወርክ (FL-NGN) ማዛወር የተቻለ ሲሆን 239 የZTE የሞባይል ጣቢያዎችን በአዲሱ የሞባይል ቴክኖሎጂ የመቀየር እና የኦፕቲማይዜሽን ሥራዎችን በመስራት 3.1 ሚሊዮን የነበረው የሁለተኛው ትውልድ የኔትወርክ አቅም ወደ 3.9 ሚሊዮን እና 300 ሺህ የነበረው የሦስተኛው ትውልድ የኔትወርክ አቅም ወደ 755 ሺህ ከፍ እንዲል በማድረግ ከፍተኛ የሆነ የኔትወርክ ጥራት ማምጣት ተችሏል፡፡

የአገልግሎት ተደራሽነትን በሚመለከት በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በሁሉም የአገልግሎት ዓይነቶች የደንበኞች ብዛት በ2002 ከነበረበት 24.7 ሚሊዮን በ2006 ወደ 29.63 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን የሞባይል ደንበኞች ብዛት በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 6.25 ሚሊዮን ባለፉት አራት ዓመታት ተጨማሪ 22 ሚሊዮን ደንበኞችን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በማድረግ የደንበኞቹን ብዛት ወደ 28.3 ሚሊዮን ማሳደግ ተችሏል፡፡ ይህም በ2007 በጀት ዓመት ይደረስበታል ተብሎ የተቀመጠውን 40 ሚሊዮን ደንበኞችን የማፍራት ግብ 71 በመቶ ይሸፍናል፡፡ በሌላ በኩል የዳታና ኢንተርኔት ደንበኞች ቁጥር በዕቅዱ መነሻ ዓመት ከነበረበት 0.19 ሚሊዮን በ2006 በጀት ዓመት ወደ 6.17 ሚሊዮን ከፍ ብሏል፡፡ ይህም በ2007 በጀት ዓመት የተቀመጠውን የ3.69 ሚሊዮን ደንበኞችን የማፍራት ግብ ከእጥፍ በላይ ማከናወን መቻሉን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የዓለም አቀፍ ሊንክ አቅም በGB/S በዕቅዱ መነሻ ዓመት ከነበረበት 3.26 ወደ 12.3 ማድረስ የተቻለ ሲሆን ይህም በዕቅዱ መጨረሻ ዓመት ላይ የተቀመጠውን ግብ 61 በመቶ ይሸፍናል፡፡ በተመሳሳይ በ5 ኪ.ሜ ራዲየስ የቴሌኮም አገልግሎት ተጠቃሚ የገጠር ቀበሌዎችን ሽፋን በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 62.1 በመቶ ወደ 96 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

### ሠ) የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 39 የሚሆኑ መ/ቤቶችን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ሕብረተሰቡን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ተጠቃሚ ማድረግን በተመለከተ 40 (80 በመቶ) ማዕከላት በፌዴራል መስሪያ ቤቶች የተቋቋሙ ሲሆን 19 (63 በመቶ) የኮሚኒቲ ራዲዮ ማዕከላት ተከፍተዋል፡፡ እንዲሁም 150 (50 በመቶ) የሕዝብ የመረጃ አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተቋቁመዋል፡፡ በተጨማሪም ሥራ የጀመሩ የተቀናጁ የክፍያ ሥርዓቶች (Unified Billing Systems) አገልግሎቶች በቁጥር 3 (60 በመቶ) ደርሰዋል፡፡ የሀገሪቱን የግብርና መር ኢንዱስትሪ ልማትና የኤክስፖርት መር ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂና የልማት ግቦችን ለማስፈፀም የሚረዳ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማትን በመፍጠርና በመዘርጋት ረገድ 126 (323 በመቶ) ተቋማት መደበኛ ያልሆነ (Informational Service) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማቱ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በዓለም አቀፍ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መመዘኛዎች (UN Index) የደረጃ ዕድገት ረገድ 39ኛ (78 በመቶ) መድረስ ተችሏል፡፡ ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገዝ ማህበራዊ ልማትን ማፋጠንና የትምህርትና የጤና አገልግሎትን ጥራትና አቅርቦት አድማስ ለማስፋት እገዛ ማድረግን በተመለከተ በጤና ዘርፍ የተተገበሩ አገልግሎቶች ብዛት 15 (68 በመቶ)፣ በትምህርት ዘርፍ የተተገበሩ አገልግሎቶች ብዛት 15 (83 በመቶ)፣ የፌዴራልና የክልል ሁለተኛ ዳታ ማዕከል (Secondary data Ceneter) ብዛት 7 (50 በመቶ)፣ የኢኮቴ ምርምሮች ብዛት 10 (77 በመቶ) ደርሰዋል፡፡

### ረ) መጠጥ ውሀና መስኖ መሠረተ ልማት

**የመጠጥ ውሀ አፈጻጸምን በሚመለከት፡-** የዕቅዱ መነሻ ዓመት መረጃ የሚያሳየዉ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፋን በ□□ር 65.8 በመቶ በከተማ **91.5** በመቶ እና በአጠቃላይ **68.5** በመቶ ሲሆን የውሀ ተቋማት ብልሽት ሽፋን ደግሞ **20** በመቶ ነው፡፡ ይህንን መረጃ መሠረት በማድረግ የንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፋንን በዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት (በ2007 የበጀት ዓመት) በ□□ር 98 በመቶ፣ በከተማ 100 በመቶ እና ጠቅላላ ሽፋኑን **98.5** በመቶ ማድረስ ቢታቀድም ከዕቅዱ በኋላ በ2003 የበጀት ዓመት በተካሄደዉ ሀገር አቀፍ የዉሃ ሳኒቴሽንና ሀይጅን ተቋማት ቆጠራ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፋን በ□□ር 48.85 በመቶ በከተማ 74.64 በመቶ እና በአጠቃላይ **52.12** በመቶ እንዲሁም የውሀ ተቋማት ብልሽት ሽፋን **25.5** በመቶ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህም በዕቅዱ መነሻ (በ2002) የነበረው የንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርባት ሽፋን በ□□ር 43.45 በመቶ፣ በከተማ 72.6 በመቶ እና በአጠቃላይ **47.3** በመቶ□ እንደነበርያሳያል::

ከዚህ አንፃር ባለፉት አራት ዓመታት በተከናወኑ ሥራዎች በአጠቃላይ 74,255 የመጠጥ ዉሃ ተቋማትን (73,909 በገጠር እና 346 በከተማ) ለመገንባት ታቅዶ በአጠቃላይ 66,345 አዳዲስ የዉሃ ተቋማት ግንባታ

(66,139 በገጠር እና 206 በከተማ) ተከናውኗል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አራት ዓመታት 29,776,220 ህዝብ (27,140,044 ህዝብ በገጠር እና 2,636,176 ህዝብ በከተማ) የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ በአጠቃላይ 31,214,380 ህዝብ (28,126,973 በገጠርና 3,132,978 በከተማ) የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ተጠቃሚ ሆናል፡፡ በዚህም መሠረት በ2006 ዓ.ም የንጹህ መጠጥ ዉሃ አቅርቦት ሽፋን በገጠር 75.5 በመቶ በከተማ 84.1 በመቶ አጠቃላይ በገጠርና በከተማ 76.7 በመቶ ደርሷል፡፡

**የመስኖ ልማት ንዑስ ዘርፍ አፈጻጸምን በሚመለከት፡-** በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ባለፉት አራት ዓመታት(2003-2006) በአገር አቀፍ ደረጃ (በፌዴራል መንግስት፣በክልል መንግስታት እና ባለሃብቶች) መካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማትን በተመለከተ በ672,537 ሄክታር መሬት ላይ የጥናትና የዲዛይን ሥራ ለመስራት ታቅዶ 679,352 ሄክታር መሬት ላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ በተመሳሰይ ጊዜ የ559,865 ሄክታር መሬት የመስኖ የግንባታ ሥራ ለማከናወን ታቅዶ 199,304 ሄክታር የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም 35.6 በመቶ ነው፡፡ ይህም በዋናነት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት አቅም ውስንነትና የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ አናሳ መሆን አፈፃፀሙ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ መልሶ መቋቋምና ማስፋፊያ ሥራን በተመለከተ ደግሞ በ5,570 ሄክታር መሬት ላይ ለማከናወን ታቅዶ የ5,100 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም 91.6 በመቶ ነው፡፡

**የተፋሰስ ልማት ንዑስ ዘርፍ አፈጻጸምን በሚመለከት፡-** የተከዜ እና የኦሞ-ጊቤ ተፋሰስ ባለሥልጣን የማቋቋሚያ እና የአደረጃጀት ጥናቶች ተጠናቀዋል፡፡ በመቀጠል ረቂቅ ሰነዶች ተፋሰሱ ማእከል በሚያደርጋቸው በክልሎች ባለድርሻ አካላትና በሚመለከታቸው ፌዴራል ተቋማት አማካኝነት እንዲገመገሙ ተደርገዋል፡፡ በተሰጠው አስተያየት መሰረት የመጨረሻ ሰነድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ወደፊት ተፋሰስ ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች አቅም ፈጥረው ራሳቸውን ችለው እንዲንቀሳቀሱና በቀጣይነት እንዲሰሩ ለማድረግ የከፍተኛ ምክር ቤትና የባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ የማሻሻል ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የተፋሰስ ባለሥልጣን የማቋቋም እና የአደረጃጀት ሂደት በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 25 በመቶ ወደ 55 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡

የታዳሽ ኃይል ማመንጫ ግድቦችን ከደለል ክምችት አደጋ ለመታደግ የተከዜና የግልገል ጊቤ የተፋሰስ ልማትና እንክብከቤ ማዕቀፍ ጥናት የተዘጋጀ ሲሆን በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተገምግሞ የመጨረሻ ሰነድ በማዘጋጀት በ2005 በጀት ዓመት ፕሮጀክቶቹ ሥራቸውን እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡ በአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን በኩል የላይኛው አዋሽ ተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ጥናት ተጠናቋል፡፡ በአራት ዓመት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጊዜያት በሚሌ–ዲርማ እና በላይኛዉ ከሰም፣ በጣና ዙሪያ፣ ስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ፣ በተከዜ ጽራሬ፣ በግልገል ጊቤ እና በተመረጡ በአባይና አዋሽ ንዑስ ተፋሰሶች በአጠቃላይ 652,504.2 ሄ/ር መሬቶች ላይ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ማለትም በአፈርና ውሃ ጥበቃ እንዲሁም የተራቆቱ መሬቶችን በማልማትና በመከለል እንዲያገግም ተደርጓል፡፡ ይህም የዕቅዱ 65.25 በመቶ ተከናውኗል፡፡

**የከርሰ ምድር ንዑስ ዘርፍ አፈጻጸምን በሚመለከት፡-** በአጠቃላይ በየፕሮጀክቶቹ የተከናወኑት የፊዚቢሊቲ ጥናቶች በመጀመሪያ የተቀመጠውን የ1፡50,000 ስኬል ካርታ ግብ ለመምታት የሚረዱ መነሻ ተግባራት ሲሆኑ በአሁኑ ወቅት የካርታ ሽፋኑ በ2002 ማብቂያ ከነበረበት 3 በመቶ ወደ 12 በመቶ አድጓል፡፡ ለጥናትና መስኖ አገልግሎት የሚውሉ በአራት ዓመታት ውስጥ 459 ጥልቅ የውሃ ጉጓዶችን ለመቆፈር ታቅዶ 242 ጉድጓዶችን ለመቆፈር ተችሏል፡፡ እስከ 2007 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ለዕቅድ ዘመኑ ከታቀደው 651 ጉድጓዶች መካከል 292 እንደሚጠናቀቁና ይህም የዕቅዱ 44.9 በመቶ ይሆናል፡፡ ለዕቅድ ዘመኑ የተያዘው በጀት ብር 1.446 ቢሊዮን ብር ሲሆን እስከ 2006 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በሥራ ላይ የዋለው ብር 906,813,297.5 ሲሆን ለ2007 በጀት ከታቀደው ብር 230,510.00 ጋር በድምሩ ብር 1,137,323,297.50 ሥራ ላይ እንደሚውል ተገምቷል፡፡

**የሀይድሮሎጂና የውሃ ጥራት ንዑስ ዘርፍ አፈጻጸምን በሚመለከት፡-** በተመረጡ ቦታዎች 17 የገጸምድር እና 7 የከርሰምድር ጣቢያዎች ተቋቁመዋል፡፡ በዚህም መሠረት የሀይድሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎችን

ሽፋን ከ85 በመቶ □□ 89.5 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ በ 40 የገጸምድር እና 7 የከርሰምድር የሃይድሮሎጂ ጣቢያዎች አውቶማቲክ የውሃ ከፍታ መሳሪያ ተተክሏል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የውሃ መጠን ለመቆጣጠር 10 የሃድሮሎጂ ጣቢያዎች ላይ የቴሌሜትሪክ ሲስተም ተዘርግቷል፤ በ2007 የበጀት ዘመን 59 የገጸምድር የሃይድሮለጂ ጣቢያዎች ወደ አውቶማቲክ የውሃ ከፍታ መሳሪያ ማሻሻያ ይደረግላቸዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ከ49 የገጸምድር የሃይድሮለጂ ጣቢያዎች በየ15 ደቂቃው መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችሉ የቴሌሜትሪክ ሲስተም ይዘረጋል:: በሁሉም ተፋሰሶች በሚገኙ የ473 የሃድሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች በየአመቱ ወቅታዊ የውሃ ከፍታ፤ በ200 ጣቢያዎች የውሃ ፍሰትና በተመረጡ ጣቢያዎች የደለል መረጃ ተሰብሰቦና ተጠናቅሮ በየአመቱ መረጃ ዝግጁ ተደርጓል፡፡

በዋና ዋና ስምንት የሃይድሮፓወርና መስኖ ልማት ግድቦች ላይ /ቆቃ፤ መልካዋከና፤ ጣና በለስ፤ ተከዜ፤ ፍንጫ፤ ግልገልጊቤ I እና II፤ ከሰምና ተንዳሆ ግድቦች/ በክረምት የጎርፍ አደጋ እንዳያስከትሉና በበጋው ወቅት ውሃን ለተገቢው ልማት ለመጠቀም የሚያስችል በየአመቱ ወቅታዊ የውሃ ሚዛን ስሌትና የውሃ አለቃቀቅ ስርዓት በማውጣትየጎርፍ መከላከልና የውሃ አጠቃቀም ሥራ ተከናውኗል፡፡ ግልገል ጊቤ ግድብ እና ጣና ሃይቅ የሚይዙትን የዉሃ መጠን እና የደለል ይዘት ለመገመት የሚያስችል የባዚሜትሪክ ቅየሳ ሥራ ተጠናቅቆ ለተለያዩ የልማት ሥራዎችና ለውሳኔ ሃሳብ የሚረዱ መረጃዎችን የያዙ ዶክመንቶች ቀርበዋል፡፡

የውሃ ጥራትና ናሙና በመመርመር በውሃው ሃብት ላይ ያለውን የተለያየ የውሃ ጥራት መመዘኛ መስፈርቶች /ፓራሜትርስ/ አናሊሲስ ለመስራት እንዲሁም በሁሉም ተፋሰሶች በሚገኙ ወንዞች የሚጓጓዘውን የደለል መጠን አናሊሲስ ለመስራት የሚያስችል የሴድመንት እና የውሀ ጥራት ላቦራቶሪ በአዲስ መልክ የማደራጀት ሥራ ተሰርቷል፡፡ ለሃይድሮሎጂ ቴክኒሻኖች በተለያዩ ጊዚያት የመረጃ መሰብሰብ የመሳሪያዎች አጠቃቀም ላይ፤ ለመረጃ ማጠናቀርና ትንተና ባለሙያዎች (በመረጃ ማጠናቀርና ትንተና፤ በሃድሮሎጂና ሃይድሮሊክስ ሞዴል፤በጂ.አይ.ኤስ፤ በሪሞት ሴንሲግ)፤ ላይ ቴክኒካዊና ሞያዊ ሥልጠና በመስጠት የአቅም ግንባታ ሥራ ተሰርቷል፡፡

**የሚቲዎሮሎጂ ንዑስ ዘርፍ አፈፃፀምን በሚመለከት፡-** በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻ ዓመት ብዛታቸው 1,135 የሆኑ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎችን ወደ 1,200 ለማሳደግ ታቅዶ መቶ በመቶ ተፈፃሚ ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ የአየር መረጃ መዝጋቢና ሌሎች ዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎችን ለማሳደግ በእድገትና ትራንሰፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መነሻ 2 የነበረውን የሳተላይት መረጃ መቀበያ ወደ 11 ለማድረስ ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ ሲሆን 37 የነበረውን የሰው አልባ ጣቢያዎች (AWS) ብዛት ደግሞ 140 ማድረስ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በዕቅዱ መጀመሪያ 4 የነበረውን የAutomatic weather Observing System ወደ 5 ለማሳደግ ተችሏል:: የመረጃ አቅርቦትና ስርጭትን በተመለከተ ደግሞ ከሳተላይት መረጃ የዝናብ ግምት /RFE/ መተንተን በዕቅዱ መነሻ ዓመት 36 የነበውን ወደ 180 ከፍ ለማድረግ ታቅዶ 159 ማድረስ ተችሏል፡፡ የተሻለ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ጥራት ያለው የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለመሰብሰብ የWAN እና የLAN የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ሁሉንም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች ከዋናው መስሪያቤት ጋር በማገናኘት የመረጃ ፍሰቱ ቀልጣፋና የተሳለጠ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል የአየር ትራንስፖርት ዘርፍ በአስተማማኝ ሁኔታ ደህንነቱ የተጠበቀና ቀልጣፋ እንዲሆን በዕቅዱ መነሻ ዓመት በሁለት አለም አቀፍ አየር ማረፊያዎች ብቻ ሲሰጥ የነበረውን የኤሮኖቲካል የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ወደ 6 አየር ማረፊያዎች ማሳደግ ትችሏል፡፡

## ሰ) የትራንስፖርት ዘርፍ አፈጻጸም

### ሰ.1 የመንገድ ትራንስፖርት

የሀገር አቋራጭ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትን ለማሻሻል በአንድ አውቶብስ በዓመት የሚሸፈን ርቀትን በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 70,000 ኪ.ሜ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 93,115 ኪ.ሜ ከፍ

ለማድረግ ግብ ተጥሎ 94384 ኪ.ሜ (101.4 በመቶ) ርቀት ተሸፍኗል፡፡ በዓመት የተጓጓዙ ተሳፋሪዎች ብዛት በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 148.1 ሚሊዮን በ2006 በጀት ዓመት ወደ 260.3 ሚሊዮን ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሎ 314.13 ሚሊዮን ማደረስ ተችሏል፡፡ ለ2007 የተጣለው ግብ ካለፉት አራት ዓመታት አፈጻጸም አኳያ እንደሚሳካ ይገመታል፡፡ የብዙሃን ትራንስፖርት አቅርቦት ድርሻን በ2006 በጀት ዓመት ወደ 38 በመቶና በ2007 በጀት ዓመት ወደ 48 በመቶ ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሎ 33.8 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ በዚህም የ2006 በጀት ዓመት አፈጻጸም ከ2006 እና ከ2007 በጀት ዓመት ግቦች አኳያ በቅደም ተከተል የ4.2 በመቶና የ14.2 በመቶ ቅናሽ ያሳያል፡፡ አገልግሎት ለማግኘት አማካይ የመጠበቂያ ጊዜን በ2006 በጀት ዓመት ወደ 19 ደቂቃ ዝቅ ለማድረግ ግብ ተጥሎ 30 ደቂቃ ሆኗል፡፡ በአዲስ አበባ የሞተራይዝድ ትራንስፖርት ወንበር አቅርቦትን በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 2,162,162/ቀን በ2006 በጀት ዓመት ወደ 2,872,083/ቀን ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሎ ወደ 2,526,744/ቀን (51.4 በመቶ) ተከናውኗል፡፡ ከ2007 በጀት ዓመት ግብ (3,083,360/ቀን) አኳያ ደግሞ 39.6 በመቶ ብቻ ተከናውኗል፡፡ በየ10,000 ተሽከርካሪ የሚደርስ የሞት አደጋን በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 70/10,000 በ2006 በጀት ዓመት ወደ 30 ዝቅ ለማድረግ ግብ ተጥሎ ወደ 64 (15 በመቶ) ዝቅ ሲል በ2007 በጀት ዓመት ወደ 27 ዝቅ ለማድረግ ከተጣለው ግብ አኳያ 14 በመቶ ብቻ እንደተከናወነ ያመለክታል፡፡

### ሰ.2 የባህርና ማሪታይም አገልግሎት

የሞጆ እና ሰመራ ደረቅ ወደቦች አጠቃላይ የካርጎ የገቢና ወጪ ዕቃዎችን የማስተናገድ አቅም በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 12 በመቶ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 90 በመቶ ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሎ 85 በመቶ ደርሷል፡፡ ከሀገሪቱ ገቢ ዕቃዎች በደረቅ ወደቦች የተስተናገደ የገቢ እቃ ድርሻ በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 8 በመቶ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 100 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሎ 28 በመቶ ብቻ ተስተናግዷል፡፡ ከሃገሪቱ የወጪ ዕቃዎች በደረቅ ወደቦች የተስተናገደ የወጪ ዕቃ ድርሻ በ2006 40 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 0.1 በመቶ ደርሷል፡፡ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የሚጓጓዘው አጠቃላይ የገቢ ጭነት መጠን በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 2 በመቶ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 38 በመቶ ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሎ 68 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ አንድ የጭነት ተሽከርካሪ በዓመት በአማካይ የሚሸፍነው ርቀት በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 80,000 ኪ.ሜ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 110,653 ኪ.ሜ ከፍ ለማድረግ ታቅዶ ወደ 95,238 (49.7 በመቶ) ከፍ ብሏል፡፡

### ሰ.3 የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት

የመንገደኛ መቀመጫ አቅርቦት በ2002 ከነበረበት 15 ቢሊዮን ኪ.ሜ. በ2006 ወደ 30.1 ቢሊዮን ኪ.ሜ. ማድረስ ተችሏል፡፡ በዕቅዱ የመነሻ ዓመት (በ2002) ዓለም አቀፍ የበረራ ጣቢያዎች ቁጥር 58 የነበረ ሲሆን ይህ ቁጥር በ2006 በጀት ዓመት ወደ 81 አድጓል፡፡ የሀገር ውስጥ የበረራ ጣቢያዎች ቁጥር በ2002 በጀት ዓመት 16 የነበረ ሲሆን በ2006 ወደ 19 ከፍ ብሏል፡፡ በዓለም አቀፉ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት እንዲሟሉ የሚጠበቁ የሴፍቲና ሴኩሪቲ ጉድለቶች የተሟሉበት ደረጃ መጣኔ በ2002 ከነበረበት 70 በመቶ በ2006 በጀት ዓመት 95 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ የአውሮፕላን ማረፊያ እና መነሻ ጊዜን በ2002 ከነበረበት 25 ደቂቃ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 3 ደቂቃ ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡ በየ10,000 በረራ የሚደርሱ የአውሮፕላን አደጋ አጋጣሚዎች ብዛት በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 30 በ2006 በጀት ዓመት ወደ 17 ቀንሷል፡፡ እንዲሁም ፈቃድ የወሰዱ የግል የአየር ትራንስፖርት አንቀሳቃሾች ብዛት 9 ደርሰዋል፡፡

በአጠቃላይ በአየር ትራንስፖርት ዘርፍ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በአህጉር ደረጃ ለሌሎች የመንግስት የልማት ኢንተርፕራይዞች ምሳሌ የሆነ ሲሆን ባለፉት አራት ዓመታት ተጨማሪ አውሮፕላኖችን በመግዛት ከዚህ ውስጥ ለአገራችንና ለአፍሪካ አህጉር የመጀመሪያ የሆነው ድሪምላይነር አይሮፕላን ባለቤት መሆኑ፣ የአገርውስጥና የውጭ የበረራ መዳረሻዎችን ቁጥር ከፍ ማድረጉና የተሳፋሪዎችን ፍላጎት ማርካት መቻሉ፣ የአገልግሎት የወጪ ንግድ ገቢን በማሳደግ የንግድ ሚዛኑን ትርፋማ ለማድረግ ማስቻሉ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## ሸ) ከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን

የዘርፉን የማስፈጸም አቅም ከማጠናከርና ብቁ ተቋም ከመፍጠር አንጻር ባለፉት አራት ዓመታት የመሬት፣ የቤት ልማት፣ የኮንስትራክሽን እና የጽዳትና የአረንጓዴ ልማት ዘርፎች አደረጃጀታቸው እየተፈተሸ እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡ በዘርፉ ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎች እየተቀመሩ ለማስፋፋት ጥረት ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ መካከለኛና ትላልቅ ከተሞችም በየዓመቱ የሚመዘኑበት ሥርዓት ተገንብቷል፡፡ ይህንኑ የሚያጠናክርና የዘርፉን ሥራዎች ለማሳለጥ አጋዥ የሆኑ እንዲሁም ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያሰፍኑ የፖሊሲ መዘርዝር፣ የመመሪያዎችና ማንዋሎች ማዘጋጀት፣ የፓኬጆች መቅረጽ እና የማሰባሰብ ሥራ ተሰርቷል ሥራ ላይ እንዲውሉም ሰፊ ርብርብ ተደርጓል፡፡ በክልሎችና ከተሞችም አበይት ተግባሮቻቸውን በሰራዊት ግንባታ አግባብ ያስፈጽሙ ዘንድ አጀንዳ በመለየት የሥልጠና፣ የድጋፍና የክትትል ሥራዎችም በቀጣይነት ተሰርተዋል፡፡

### ሸ.1) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት እና የሥራ ዕድል ፈጠራ

የሥራ ዕድል ፈጠራን በተመለከተ በዕቅድ ዘመኑ በዘርፉ በመደበኛ እንዲሁም በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ከተያዘው የ3.2 ሚሊዮን ዕቅድ በእጥፍ ተሳክቷል፡፡ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በ2002 በጀት ዓመት የነበሩት 13,175 በእጥፍ እንዲያድጉ ሰፊ ርብርብ ተደርጓል፡፡ ለአንቀሳቃሾች የተደረገ ድጋፍን በተመለከተም 15,745 ሄክታር ቦታ፣ 567 ህንፃዎች እና 16,753 ሼዶች ተዘጋጅተው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ እነዚህ ሥራዎችም ከተጣለው ግብ በላይ ተፈጽመዋል፡፡ የገበያ ትስስርን በተመለከተ ለ2.9 ሚሊዮን የሚሆኑ አንቀሳቃሾች የብር 25.6 ቢሊዮን በሀገር ውስጥ የገበያ ትስስር የተፈጠረላቸው ሲሆን፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርቶቻቸውን ኤክስፖርት አድርገው 65 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚደርስ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ችለዋል፡፡ የብድር አቅርቦትን በተመለከተም ብር 9.8 ቢሊየን ቀርቧል፡፡

### ሸ.2) የከተሞች የልማታዊ መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ሥራዎች አፈጻጸም

የከተማ ህዝብ ራሱን በራሱ በማስተዳደርና ልማቱን በማፋጠን ረገድ የተሟላ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚችልበት የጋራ መግባባት የሚፈጠርበት ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችልና የከተሞች የልማታዊ መልካም አስተዳደር ግንባታ ማዕቀፍና የማስፈጸሚያ ስልቶች የያዘ መሪ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የመግባቢያ ስምምነት በመፈረም በከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት፤ በአረንጓዴ ልማትና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ በከተማ ሥራ አመራር፣ በከተማ ፕላን እና ሌሎች ኮርሶች ሥልጠና የመስጠት ሥራዎች ተጀምረዋል፡፡ በከተሞች ስታንዳርድ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን ለነዋሪዎቻቸው ለማቅረብ የሚያስችሉ ጥናቶች በየከተሞቹ እየተጠኑ መተግበር ጀምረዋል፡፡ በከተሞች መካከል የመልካም ተሞክሮው ልውውጥ እንዲኖር ለማስቻል የከተሞች ፎረም እስከ 2007 በጀት ዓመት በየዓመቱ በማካሄድ ጥሩ ውጤት ተመዝግቦበታል፡፡

የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን በተመለከተ የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ የሚመራ ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡ ሀገራዊ የከተማ ልማትና አሰፋፈር ፕላን (National Urban Development Spatial Plan) እና የአዲስ አበባ ከተማን ተወዳዳሪ ሆና ማስቀጠል የሚያስችል ጥናት በአለም አቀፍ አማካሪዎች እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በዚህ ዘርፍ የተሻለ ልምድ ካላቸው የውጭ ሀገር ዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበርም በአዳማ፣ ባህርዳር፣ መቀሌና ሐዋሳ ከተሞች የከተማ ልማታችን ቀጣይነት ለመደገፍ የሚያስችል ከ30-40 ዓመት የሚደርስ የከተማ ማስፋፊያ ፕላን ሥራ ተከናውኗል፡፡ የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት በተመለከተ ዘርፉ የሚመራበት ግልጽ ፖሊሲና ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ በመንግስት የጸደቀ ሲሆን፣ ይህን መነሻ በማድረግም የተሻሻለው የሊዝ አዋጅ ፀድቆ የሊዝ አዋጁን በተሟላ መልኩ ወደ ተግባር ከማሸጋገር አንጻር 540 ከተሞች ወደ ሊዝ ሥርዓት ገብተዋል፡፡ የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ለማስፈጸም የከተማ ካዳስተር ቅየሳ ደንብ እንዲጸድቅ ተደርጓል፡፡

የከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ እና ምዝገባ ደንብና ማስፈጸሚያ መመሪያዎች ጸድቋል፡፡ የመሬት ይዞታ ምዝገባን ለማስተግበር የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን በመዘርጋት እንዲሁም የአየር በረራ የተደረገባቸው 23 ከተሞችና በሳተላይት ስትሪዮ ምስል ለ44 ከተሞች መሰረታዊ ካርታ ተዘጋጅቷል፡፡ ህጋዊ ካዳስተር ሥርዓቱ በዋናነት በአገር ደረጃ መናበብ የሚያስችለውን ቴክኖሎጂ የሚገነባበትን ደረጃ የሚያስጠብቅ የሕግ ማዕቀፍ እስከ መመሪያ ድረስ ተዘጋጅቶ ፀድቋል፡፡ ለመሬት መረጃ ሥርዓቱ አጋዥ የሆነ የሰው ኃይል ክህሎት ለመገንባት እንዲቻል ለከተማ መሬት ዘርፍ በተዘጋጁት 12 የሙያ ደረጃዎች የዘርፉን ባለሙያዎችን ብቃት ማረጋገጥና የክህሎት ክፍተት በመለየት አሰልጥኖ የብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

### ሸ.3) የመኖሪያ ቤቶች ልማት አፈፃፀም

የመኖሪያ ቤት ልማት ፕሮግራም ተጠናክሮ በቀጠለበት በአዲስ አበባ ከተማ በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 150,000 ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ ባለፉት አራት ዓመታት በተለያዩ ፕሮግራሞች የተገነባና በግንባታ ላይ ያሉ 157,070 (105 በመቶ) ቤቶች ናቸው፡፡ በቤት ልማትና ትስስር ባላቸው ፕሮጀክቶች አማካይነት 240,000 አዲስ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በሦስት እጥፍ ማሳካት ተችሏል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ በዘርፉ በመሠረተ ልማት ግንባታ ሊከናወኑ ከተቀመጡ ግቦች አንጻር ባለፉት አምስት ዓመታት 2700 ኪ.ሜ (73 በመቶ) የድንጋይ ንጣፍ መንገድ፣ 3700 ኪ.ሜ (103 በመቶ) የሚደርስ የጎርፍና የዝናብ ማስወገጃ መስመሮች ግንባታ፣ 1,100 (300 በመቶ) በላይ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች፣ 382 (178.5 በመቶ) የፍሳሽ ቆሻሻ መድፊያ ቦታዎች እና 26 (86 በመቶ) ዘመናዊ ቄራዎች ግንባታ ተከናውኗል፡፡ በቤት ልማትና ትስስር ባላቸው ፕሮጀክቶች አማካይነት 240,000 አዲስ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በሦስት እጥፍ ማሳካት ተችሏል፡፡ በቤት ልማትና ትስስር ባላቸው ፕሮጀክቶች ግንባታ ላይ ከአስፈፃሚ ባለቤቶች፣ ከአማካሪዎች፣ ከሥራ ተቋራጮች እና ኢንተርፕራይዞች ለተውጣጡ ከአንድ ሺህ አንድ መቶ በላይ አመራሮችና ባለሙያዎች በተለያዩ ጊዜያት የክህሎት ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

የከተሞችን መሰረተ ልማት አቅርቦት ፋይናንስ ማድረግ እና የሥራ አመራር አቅም ከማጠናከር አንጻር ለከተሞች ቀደም ሲል ከልማት አጋሮች ከተገኘው የ150 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ብድር በተጨማሪ 150 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እና በክልሎችና ከተሞች መዋጮ 116 ሚሊዮን በማካተት በድምሩ 416 ሚሊዮን ዶላር ለዘርፉ ተመድቦ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

### ሸ.4) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ አፈጻጸም

የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪውን በአግባቡ ለመምራት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ በ2006 በጀት ዓመት ወጥቶ ሥራ ላይ ውሏል ከዚህ በተጨማሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን የማስፈጸም ዐቅም ብሎም ተወዳዳሪነት ዐቅም ለመገንባት የሚያስችል የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ስትራቴጂክ ሪፎርም ፕሮግራም ተዘጋጅቷል፡፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱትሪውን ፖሊሲ ለማስፈጸም የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩትም ተቋቁሞ ሥራ ጀምሯል፡፡ የኢንስቲተየቱ ዋና ዋና ዓላማዎች የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪወ በላቀ ደረጃ ውጤተ እንዲያስመዘግብ ለማድረግ የሚያግዙ ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠር፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሠራር ማስፈን፣የቴክኖሎጂ ዐቅምን መሠል ዐቅሞች መፍጠር እና ኢኮኖሚው ከኮንስትራክሽን ኢንደስትሪው የሚጠብቀውን ሀገራዊ ምርት ድርሻ ማሳደግ ናቸው፡፡ ክልሎችና ከተሞች አሁን ያሉበትን ደረጃ በማመዛዘን የሕንፃ አዋጅ፣ ደንብ እና ተጓዳኝ መመሪያዎች ተግባራዊ በሚሆንባቸው 248 ከተሞች አስፈላጊ አደረጃጀት እንዲፈጠር እና ወደ አፈፃፀም እንዲገባ ለማድረግ ታቅዶ በ126 (50 በመቶ) ከተሞች አስፈላጊ አደረጃጀት ተፈጥሮ ወደ አፈፃፀም ገብተዋል፡፡ በአራት ዓመቱ 12 ዓለም አቀፍ የተወዳዳሪነት አቅም ያላቸው ሥራ ተቋራጮችን ለማፍራት ታቅዶ 8 የሚሆኑ በዚህ ደረጃ የደረሱ ተቋማት እና 17 አለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ደረጃ ያላቸው አማካሪዎችም ተፈጥረዋል፡፡

### ሸ.5) የከተማ ፅዳትና የአረንጓዴ ልማት አፈጻጸም

የከተሞች የፅዳትና የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች በህዝብ ንቅናቄ ለማስፈፀም የሚያስችሉ የከተሞች የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስትራቴጂ እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የከተሞች አረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡ ስትራቴጂዎችን ለማስፈጸም የሚያስችሉ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስታንዳርድ፣ የስታንዳርዱ ገላጭ ሰነድ እና የተቀናጀ የከተሞች ተፋሰስ ማንዋል ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ በፌዴራል፣ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች 13 የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓትን የሚያሳልጡ የጥናት ሰነዶች፣ ስታንዳርዶችና የሕግ ማዕቀፎች፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ፣ የህዝብ መፀዳጃ እና መታጠቢያ ቤት ማንዋል በማዘጋጀት በ727 ከተሞች ለሚገኙ ከ6 ሺህ በላይ ለሚሆኑ የከተማ አመራሮችና ፈጻሚዎች በሰነዶቹ ዙሪያ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

### 1.7.3 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች

ባለፉት አራት ዓመታት በመሠረተ ልማት ዘርፍ ካጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች መካከል የፕሮጀክት ማኔጅመንት (የማቀድ፣ የመተግበር፣ የመከታተል፣ ኮንትራት የማስተዳደር) አቅም ውስንነት፣ የቅንጅት ችግር፣ የቴክኖሎጂ ክፍተት፣ የፋይናንስ ዕጥረት፣ የኃይል አቅርቦትና የአገልግሎት ችግር፣ በአመለካከትና በተግባር የሚገለፅ የኪራይ ሰብሳቢነት ችግርና የመልካም አስተዳደር ዕጥረቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አንፃር በጥራትም ሆነ በሙያ ስብጥር በቂ ባለሙያ አለመኖር የኢኮቴ የግሉ ዘርፍ የአቅም ውስንነት፣ የተቋማዊ ቅንጅትና ተነሳሽነት ውስን መሆን፣ ህገወጥ መሳሪያዎች ማስገባትና ህገወጥ አገልግሎቶች የመስጠት አዝማሚያ መስፋፋት እና

ከመጠጥ ውሀ አቅርቦት አንፃር በከተማና በገጠር ካለው የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና አስተዳደር ለማከናወን የሚያስችል በቂ አቅም (የመንግስት፤ የግሉ ሴክተርና የማህበረሰብ) አለመፈጠር፣ በከተሞች አካባቢ ከፍተኛ የውሀ ብክነትና የመልካም አስተዳደር ችግር፤ በከተሞች በመሰረተ ልማት አቅርቦት ዙሪያ በሚመለከታቸው አካላት መካከል የቅንጅት ችግር መኖር፣ የፋይናንስና የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት፤ ከአገሪቱ መልክአ ምድር አቀማመጥ ጋር ተያይዞ የገጠሩ ህዝብ አስፋፈር የተበታተነ በመሆኑ የቧንቧ ዉሀ አገልግሎት ለማቅረብ አመቺ አለመሆኑ እንዲሁም የከርሰምድርና የገጸምድር ውሃ መገኛዎች የውሀ መመናመንና ለብክለት መጋለጥ በዚህም ምክንያት የውሃ መገኛዎች ህዝብ በሰፈረበት አካባቢ ለማግኘት ችግር እየሆነ መምጣቱ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 1.8 የማህበራዊ ዘርፍ ልማት ዕቅድ አፈፃፀም

### 1.8.1 የማህበራዊ ዘርፍ ልማት ዕቅድ ዓላማና አቅጣጫዎች

የማህበራዊ ዘርፍ የሕዝቡን ኑሮ በማሻሻልና ድህነትን በመቀነስ ለኢኮኖሚ ዕድገትና ለተረጋጋ አስተዳደር ካለው ከፍተኛ አስተዋፅኦ በመነሳት በትምህርት፣ በጤና፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ አገልግሎት መስፋፋትና የአገልግሎት አቅርቦት ጥራት ላይ ማተኮር የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡

### 1.8.2 የማህበራዊ ዘርፍ ልማት ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም

### ሀ. ትምህርትና ሥልጠና

***የቅድመ መደበኛ ትምህርት፡-*** *የቅድመ መደበኛ ትምህርት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻ ዓመት ጥቅል ሽፋን 4.8 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2007 በጀት ዓመት ወደ 43.24 በመቶ ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ ጥሩ የነበረ ቢሆንም አሁንም 56.76 በመቶ የሚሆኑት ህጻናት ዕድሜያቸው ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ደርሰው ተጠቃሚ አለመሆናቸው በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ብዙ መስራት እንደሚጠይቅ አመላካች ነው፡፡*

**የአንደኛ ደረጃ ትምህርት (ከ1-8)፡-** የአንደኛ ክፍል ጥቅል ቅበላ መጣኔ በዕቅዱ የመነሻ ዓመት ከነበረበት 131 በመቶ በ2007 በጀት ዓመት ወደ 153 በመቶ  ከፍ ብሏል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት (1-8) ንጥር ተሳትፎ መጣኔም በ2002 ከነበረበት 82 በመቶ በ2007 በጀት ዓመት ወደ 92 በመቶ አድጓል፡፡ ይህ ስኬት አገሪቱ የምዕተ ዓመቱን የትምህርት ግቦች ካሳኩት አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ያደረገ ሲሆን የዚህ ስኬት ምንጭ መንግሥትና ሕዝቡ በትምህርት ግብዓት ላይ ያደረጉት ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ርብርብ ነው፡፡

**የሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን (9-10)፡-** ጥቅል ተሣትፎ መጣኔ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻ ከነበረበት 39.7 በመቶ በ2007 ወደ 62 በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ የ39.3 በመቶ ዝቅተኛ አፈፃፀም ተመዝግቧል፡፡ ለተመዘገበው ዝቅተኛ አፈፃፀም በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋና ዋናዎቹ ግን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ከመስፋፋቱና የትምህርት ተሳተፎ እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ አሁን ያለን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የማስፋፋት ሥራ ከታች የሚመጣውን ሰፊ የተማሪ ኃይል ሊሸከም የሚችል አለመሆኑ፣ ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ተማሪዎችን በማብቃት ወደ ቀጣዩ ክፍል እንዲሸጋገሩ ከማድረግ አንጻርም እጥረት ያለ መሆኑ፣ ወደ ቀጣዩ ክፍል የተሸጋገሩት ተማሪዎችም ቢሆን ከተቋማቱ ርቀት አንፃር ተደራሽ ባለመሆናቸው ወላጆች ልጆቻቸውን በተለይ ሴት ልጆቻቸውን በርቀት ምክንያት ባላቸው ስጋት ለመላክ የዝግጁነት ማነስና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የሁለተኛ ደረጃ የመሰናዶ ትምህርትን (ከ11-12) በሚመለከት ጥቅል ተሳትፎ በ2002 ከነበረበት 7 በመቶ (ወንዶች 8.9 በመቶ እና ሴቶች 5 በመቶ) በ2006 ወደ 10 በመቶ (ወንዶች 10.7 በመቶ እና ሴቶች 9.1 በመቶ) እንዲሁም የ2007 ጥቅል ተሳትፎው ወደ 19.8 በመቶ ገደማ አድጓል፡፡ የዚህ እርከን ጥቅል ተሳትፎ በዕቅዱ ትግበራ ዘመን ማብቂያ 9.5 በመቶ ለማድረስ ከተጣለው ግብ አኳያ እቅዱን ቀድሞ በከፍተኛ ደረጃ ማሳካት ተችሏል፡፡ ለዚህ ግብ መሳካት የሁለተኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት ክፍሎች ዝቅተኛ አቅርቦት ባለባቸው አካባቢዎች በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቅጥር ግቢ የማስፋፋት ሥራ በመሠራቱና ተደራሽነቱን ማሳደግ በመቻሉ ነው፡፡

የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትን በተመለከተ ዕድሜያቸው ከ15-60 ዓመት ያሉና መጻፍና ማንበብ የማይችሉ 20,451,706 ጎልማሶችን በመለየት ሁሉም ፕሮግራሙን እንዲያጠናቅቁ ታቅዶ 10 ሚሊዮን ትምህርታቸውን አጠናቀዋል፡፡

**የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና ብቃትን በተመለከተ**

**የትምህርት አመራር፡-** በሁሉም ትምህርት ቤቶች ስታንደርዱን በሚያሟሉ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ለማሟላት በተያዘው አቅጣጫ መሠረት በሁሉም በሚባል ደረጃ ትምህርት ቤቶች አመራር እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በትምህርት አመራርና በመምህራን ገዢ መመሪያ በተቀመጠው ስታንደርድ መሠረት የአጭርና የረጅም ጊዜ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ጠንካራ ርእሰ መምህራንና

ሱፐርቫይዘሮች ባሉባቸው ትምህርት ቤቶች የትምህርት ልማት ሠራዊት በመገንባት የተማሪዎች ውጤት እንደተሻሻለና ትምህርት ቤቶችን ወደ ሞዴልነት መቀየር ችለዋል፡፡

***የመምህራን ልማት፡-*** *የመምህራን ልማት መርሃ ግብር በተመለከተ የመምህራኑን ብቃት ለማጎልበት በዕቅድ ዘመኑ በሁሉም ደረጃዎች መምህራን ሙሉ በሙሉ ለደረጃው ብቁ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም በመጀመሪያ ደረጃ 77 በመቶ፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ 97 በመቶ ብቁ ማድረግ ተችሏል፡፡*

በ2002 በጀት ዓመት በ4ኛ ክፍል በተካሄደው ሀገር አቀፍ የትምህርት ቅበላ ጥናት መሰረት 40.9 በመቶ የነበረው ውህድ አማካይ ውጤት በ2005 በጀት ዓመት 40.06 በመቶ ሲሆን የ8ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የትምህርት ቅበላ ጥናት ውህድ ውጤትም ከነበረበት 35.6 በመቶ በ2005 በጀት ዓመት ወደ 35.32 በመቶ በመድረሱ ከክልል ክልል ልዩነት ቢኖርም በአገር አቀፍ ደረጃ መሻሻል አላሳየም፡፡ በ2003 በጀት ዓመት በ10ኛ ክፍል በተካሄደው ሀገር አቀፍ የትምህርት ቅበላ ጥናት መሰረት 36 በመቶ የነበረው ውህድ አማካይ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 40.6 በመቶ ሲደርስ በተመሳሳይ ወቅት የ12ኛ ክፍል ውህድ አማካይ ከነበረበት 47.8 በመቶ ወደ 45.5 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ ይህ ምዘና በቋንቋ በሒሳብና በሣይንስ ትምህርቶች ላይ ኘሮፋይልን መሠረት አድርጐ የተሰጠ ምዘና ነው፡፡ ውጤቱ ከመነሻው መሻሻል ያሳየ ቢሆኑም ከሚጠበቀው ውጤት ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው፡፡ ለዚህም ዋና ዋና ምክንያቶች የመምህራን ብቃትና የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል የቤተሰብ ድጋፍ እንዲሁም ስታንደርዱን በተቀመጠው አግባብ ባለ አቅምና ግብአት አሟጦ አለመጠቀም ናቸው፡፡

ትምህርት ቤቶች በግብአት በአሠራርና አደረጃጀት እንዲሁም በውጤት የሚለኩበት የትምህርት ቤቶች የምደባ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ በተካሄደው የትምህርት ቤቶች ምደባ በአራት ደረጃዎች ተለይተዋል፡፡ በዚህም መሠረት የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ደረጃ ምደባ ከተደረገላቸው 29,975 ት/ቤቶች ውስጥ 3.05 በመቶ በከፍተኛ ደረጃ፣ 18.89 በመቶ በደረጃ ሦስት የሚገኙ ስታንደርዱን የሚያሟሉ ሲሆኑ ብዙዎቹ (53.7 በመቶ) የሚሆኑት ት/ቤቶች በመሻሻል ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ (24.36 በመቶ) ከስታንደርድ በታች የሆኑ ት/ቤቶች በመሆናቸው ተማሪዎችን ወደ ት/ቤት እንዲመጡ እና እንዲቆዩ እንዲሁም የትምህርት አቀባባላቸው ላይ ቀጥታ ግንኙነት ስለሚኖረው ይህን ከማረጋገጥ አኳያ በቀጣይ ሰፊ ሥራ ይጠይቃል፡፡

***ሥርዓተ ትምህርት፡-*** በሥርዓተ ትምህርት ትግበራም ከአጸደ ህፃናት እስከ 12ኛ ክፍሎች አዲስ የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ አለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት ታትመው ተሰራጭተዋል፡፡ ከዚህ አኳያ የታተመው የተማሪ መጽሐፍ የተማሪ ጥምርታው 1 ለ1 ቢሆንም በአንዳንድ አካባቢዎችና በተወሰኑ የትምህርት አይነቶች ግን በሥርጭትና በአጠቃቀም ምክንያት ሁሉም ተማሪዎች አንድ ለአንድ መጻሕፍት ይዘው እየተገኙ አይደሉም፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በክፍልና ከክፍል ውጪ መጻሕፍቱን በመጠቀም ሊያገኙት የሚችለውን እውቀትና ክህሎት እንዲሁም ውጤት መሻሻል ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአገር ውስጥ የሕትመት ኢንዱስትሪው የአቅም ውስንነት ምክንያት በወቅቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአገር ውስጥ አሳትሞ ማቅረብ አልተቻለም፡፡ ከዚህ አንጻር በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶት የሕትመት ኢንዱስትሪው የሚጐለብትበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

***የትምህርት ኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጅ ማስፋፊያ፡-*** ትምህርትን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ዘመናዊና ቀልጣፋ በማድረግ ለሁሉም ተማሪዎች በፍትሐዊነት ማዳረስ የዚህ መርሃ ግብር ዋና አላማ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በአዲሱ ሥርዓት ትምህርት የተዘጋጁትን የሳተላይት ኘላዝማ ኘሮግራም ተዘጋጅቶላቸው እንዲሠራጩ ተደርጓል፡፡ አዳዲስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ኘሮግራሞች ዲጂታይዝ በማድረግ ተሠራጭቷል፡ ፡ ለሁሉም 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ደረጃ በደረጃ የቪሳትና ኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የክላውድ ኮምፒዩቲንግ ሶሉሽን የመዘርጋት እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡ ይሁንና ኘሮግራሙን ውጤታማ ለማድረግ ማነቆ ከሆኑት ውስጥ የአመለካከት እና የመሠረተ ልማት ግብአት ችግሮች፣ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ትምህርት የሚያስተምር የሰለጠነ መምህር እጥረትና

የመሣሰሉት ችግሮች ሲሆኑ በዚህ ምክንያት ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ት/ቤቶች የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ሊሆኑ አልቻሉም፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊሠሩ ይገባል፡፡

**ውስጣዊ ብቃትን (Internal Efficiency) በተመለከተ**

በዚህ ሥር በዋነኛነት የሚካተቱት ትምህርትን ተከታትሎ የማጠናቀቅ ምጣኔ ማደግ እና የመጠነ ማቋረጥና መጠነ መድገም መቀነስ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻ ዓመት የ5ኛ ክፍል የማጠናቀቅ ምጣኔ 75.6 በመቶ ነበር፡፡ በ2006 በጀት ዓመት አፈጻጸሙ መሻሻል ሳያሳይ 75.2 በመቶ ላይ ይገኛል፡፡ ስምንተኛ ክፍልን የማጠናቀቅ ምጣኔ በተመለከተም ከነበረበት 47.8 በመቶ በ2006 በጀት ዓመት አፈጻጸሙ 51.5 በመቶ ሆኗል፡፡ ምንም እንኳን ከመነሻው መሻሻል የታየ ቢሆንም 48.5 በመቶ የሚሆኑት ሕጻናት በተለያዩ ምክንያቶች የስምንት ዓመት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ ያቋረጡ ወይም ክፍል የደገሙ በመሆኑ አሳሳቢ የሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ብክነት መኖሩን ያመላክታል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነትና ተሳትፎን በፍትሐዊነት ከማሳደግ አኳያ ሰፊ ሥራ በመሠራቱ አበረታች ውጤት ቢታይም መጠነ ማቋረጥና መድገምን መቀነስ ላይ ያለው አፈጻጸም ከፍተኛ ችግር የሚስተዋልበት ነው፡፡ በ2005 በጀት ዓመት 1ኛ ክፍል ከተመዘገቡት 3,936,538 ተማሪዎች ውስጥ 22.5 በመቶ እንዳቋረጡ የትምህርት ስታቲስቲካዊ መረጃው ያሳያል፡፡ ይህም 885,721 ያህሉ የ1ኛ ክፍል ትምህርትን ሳያጠናቅቁ ማቋረጣቸውን ያስረዳል፡፡ በተመሳሳይም ከ1ኛ-8ኛ ክፍል ያለፉት አስር ዓመታት የማቋረጥ መጠን በአማካኝ 15.7 በመቶ ነበር፡፡ ከማቋረጥ ምጣኔ ባልተናነስ መልኩ የመድገምም ምጣኔ ሌላው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተግዳሮት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በ2002 በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት (ከ1-8ኛ) 5.8 በመቶ የነበረውን የመድገም መጣኔ በ2006 ወደ 2.0 በመቶ ለማውረድ ታቅዶ አፈጻጸሙ ግን 8.4 በመቶ ሆኗል፡፡

የማቋረጥንና የመድገምን ምጣኔ ለመቀነስ በየዓመቱ ግብ ቢጣልም እስከ 2004 ድረስ የመቀነስ ሳይሆን የመጨመር አዝማሚያ እያሳየ ቆይቶ በ2005 ቀንሷል፡፡ በተለይ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የማቋረጥ ምጣኔ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሶ 7.9 በመቶ ደርሷል፡፡ ለማቋረጥና መድገም ምጣኔ መጨመር ምክንያት ከሆኑት ችግሮች ውስጥ የመጀመሪያው ድህነት ነው፡፡ ራሱንም ሆነ ልጆቹን መመገብ ያልቻለ ወላጅ ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት ከመላክ ይልቅ ገቢ ወደሚያስገኝ ሥራ ያሰማራቸዋል፡፡ አንዳንዶቹም ልጆቻቸውን ለመላክ ቢሞክሩም ለትምህርት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች ማሟላት ስለማይችሉ በትምህርቱ ሳይዘልቁ ይቀራሉ፡፡ ሌላው የማቋረጥ ምክንያት በአንዳንድ ቦታዎች የትምህርት ቤቶች ተደራሽ አለመሆን ነው፡፡ ሕፃናትና ወጣቶች በተለይ ሴት ልጆች በተለይ ወደ አምስተኛ እና ዘጠነኛ ክፍሎች ተማሪዎች ሲዛወሩ በኢኮኖሚ ወይም ከቤተሰብ ርቀው እንዲማሩ አስቸጋሪ መሆኑ ነው፡፡ ከትምህርት ጥራት ጋር ተያይዞ ተማሪዎች በክፍል ደረጃቸው ማወቅ የሚጠበቅባቸውን እውቀትና ክህሎት ባለማግኘታቸው ምክንያት በወላጆቻቸው እንዲያቋርጡ መደረጋቸው ሌላው ምክንያት ነው፡፡ በስታንደርዱ መሠረት የተማሪ ክፍል ጥምርታው 50 መሆን ሲገባው በአንዳንድ ክፍሎች ከ70 እና 80 በላይ ተማሪዎች ተፋፍገው እንዲማሩ መደረጋቸው እንዲሁም ልዩ ፍላጐት ለሚሹ ወገኖች ት/ቤቶችን ለእነሱ ምቹ ካለማድረግ እና አስፈላጊውን ቁሳቁስ ስለማይማሉላቸው ትምህርት ጀምረው የሚያቋርጡት በርካታ ሕጻናት ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ችግሮች በቀጣይ በመፍታት የትምህርት ተደራሽነትና ጥራት የማረጋገጥ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

**የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና፡-** በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፋ ባለው የትምህርት ሥርዓት ውስጥ አብዛኛውን የሰው ሀይል ምርታማና ተወዳዳሪ ለማድረግ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ ባለፉት አመታት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ በሰልጣኝ ልማት፣ በሙያ ደረጃ ምደባና የምዘና መሳሪያዎች ዝግጅትና የተቋማት አቅም ግንባታ ሥራዎች ለመስራት ታቅዶ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት የልማት ፕሮግራሞችን መነሻ በማድረግ ከትኩረት ዘርፉ መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን ከተቀመጠው ግብ በላይ የሙያ ደረጃ ምደባና የምዘና መሳሪያዎች ከመዘጋጀታቸውም በላይ

ባለፉት ዓመታት የምዘና ማዕከላትን በማስፋፋትና ከ180 ሺ በላይ ወጣቶችን በመመዘን 71 በመቶ የሚሆኑት ለምዘናው ብቁ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ የሚፈፀመው በመደበኛው የትምህርት የሚያልፉትን ብቻ ሳይሆን ሁሉም ክህሎቱን አሻሽሎ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚሻን ዜጋ የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ መሠረት የአርሶ አደር ምዘና የተጀመረ ሲሆን የአርሶ አደሩን ትራንስፎርሜሽን ለማረጋገጥ ራሱን የቻለ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በተወሰኑ ክልሎች የአርሶ አደር ስልጠናና የምዘና ሥርዓት ተካሂዶ እስከ አሁን ወደ 900 ሺህ የሚጠጉ አርሶ አደሮች ተመዝነው ብቁ ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩል ሰልጣኞች ክህሎትንና እውቀትን በተሟላ ሁኔታ እንዲገበዩ ለማድረግ አንዱና ዋነኛው አቀጣጫ የትብብር ስልጠና ማካሄድ ሲሆን ከዚህ አንጻር ከኢንዱስትሪዎች ጋር የተሻለ መተሳሰር የተጀመረበትና በትብብር ሥልጠናው ላይ ከተሰማሩት ሰልጣኞች 83 በመቶ የሚሆኑት በትብብር ሥልጠና መታቀፍ የቻሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ከፍተኛ ትምህርት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብዛት 10 የቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዩቶችንና 2 የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎችን ጨምሮ በ2006 በጀት ዓመት 31 የደረሰ ሲሆን የቅበላ አቅምም 387,685 ደርሷል፡፡ የቅድመ ምረቃ አፈጻጸም 83 በመቶ ሲሆን፤ በመንግስትና በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የቅድመ ምረቃ መርሃ ግብሮች ተደራሽነትን በየደረጃው በማስፋፋት የከፍተኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎው በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 5.3 በመቶ በ2007 በጀት ዓመት 9 በመቶ ገደማ የደረሰ ሲሆን ለዚህ አመላካች ያስቀመጥነውን የ9.3 በመቶ ግብ ከሞላ ጎደል አሳክተናል ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ሆኖ የመጀመሪያ ደረጃ መካከለኛ ገቢ አገራት ከሚኖራቸው የ22 በመቶ ጥቅል ተሳትፎ አንጻር ሲታይ ገና ብዙ ርቀት መጓዝ ይጠይቃል፡፡ የድህረ ምረቃ ፕሮግራም ተሳትፎን ከማሳደግ አንጻር አመታዊ ቅበላን 16,100 (3,000 ሶስተኛ ዲግሪ) ለማድረስ የታቀደ ሲሆን ነባሮቹና አዳዲሶቹ ዩኒቨርሲቲዎች በፈጠሩት እድል የሁለተኛ ዲግሪን የማስተናገድ አቅም 24,474 እና የሶስተኛ ዲግሪን 3,169 ማድረስ ተችሏል፡፡ የሴት ተማሪዎችን ድርሻ በቅድመ ምረቃ 40 በመቶ እና በድህረ ምረቃ 25 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ የቅድመ ምረቃውን 32 በመቶ እንደዚሁም የድህረ ምረቃውን 19 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡ አካል ጉዳተኛ የሆኑ ዜጎችን በሁሉም መስኮች ከፍተኛ ትምህርትን ጨምሮ እኩል ተጠቃሚ ለማድረግ በከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችን 946 አካል ጉዳተኛ ዜጎች ይኖራሉ ተብሎ ታቅዶ የነበረ ሲሆን ዕቅዱን ሙሉ ለሙሉ ማሳካት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ለሚኖሩን 467,000 ተማሪዎች በ1 ለ19 ጥምርታ 23,000 መምህራን እንዲኖሩን ግብ ተጥሎ ነበር፡፡ የመምህራኑ ስብጥርም 75 በመቶ የሁለተኛ ዲግሪና 25 በመቶ የሶስተኛ ዲግሪ እንዲኖራቸው ለማድረግ ግብ ተጥሎ ነበር፡፡ አፈፃፀሙም የመምህራኑን ቁጥር ከ23,000 በላይ ማድረስ የተቻለ ቢሆንም ስብጥሩን ወደ ታቀደው ለማምጣት አልተቻለም፡፡ በ2006 በጀት ዓመት ማጠናቀቂያ የነበረው የመምህራን ቁጥር 30 በመቶ የመጀመሪያ ዲግሪ 58 በመቶ የሁለተኛ ዲግሪ እና 12 በመቶ እና የሶስተኛ ዲግሪ ሲሆን ይህ በ2007 በጀት ዓመት መጨረሻ አካባቢ እንደሚሻሻል የሚጠበቅ ቢሆንም ግቡን በተሟላ ሁኔታ ማሳካት እንዳልቻልን ያመላክታል፡፡

በአገራችን ከፍተኛ ትምህርትን የማስፋፋት ሥራ ፈጣን ልማታችንን በሚደግፍና በሚያስቀጥል አግባብ ለማካሄድ በቅድመ ምረቃ ከሚኖሩ ተማሪዎች 70 በመቶ በሳይንስና ኢንጂነርንግ የተቀሩት 30 በመቶ በማህበረሰብ ሳይንስ በማድረግ የኢንዱስትሪዎች የሰው ኃይል ፍላጎት ታሳቢ ተደርጎ መስፋፋት እንዳለበት እቅድ ተቀምጦ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ በዚህም አፈጻጸሙ 71:29 የደረሰ ከመሆኑም በላይ ከ70 በመቶ ዉስጥ 40 በመቶ የሚሆነዉ የኢንጂነሪንግ ተማሪዎች መሆናቸዉ ምጥጥኑ በዕቅዱ መሰረት እየተፈጸመ መሆኑን ያሳያል፡፡

**በትምህርት ዘርፍ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች አፈጻጸም**

በትምህርት ዘርፍ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎንና ፍትሀዊነትን ሙሉ ለሙሉ ማሳካት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አንደኛ እና ሁለተኛ ርከን መጠነ ማጠናቀቅን ትርጉም ባለው መልኩ ማሳካትና የጎልማሶች ትምህርትን ማስፋፋት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር በ2007 የተደረሰበት የመጀመሪያ ደረጃ (1-8) ትምህርት የ94 በመቶ ንጥር ተሳትፎ መጣኔ፣ በ2006 የተደረሰበት የ75.2 በመቶ የአምስተኛ ክፍልን የማጠናቀቅ መጣኔ እና በተመሳሳይ የ51.5 በመቶ የስምንተኛ ክፍልን የማጠናቀቅ መጣኔ አንጻር ሲታይ በንጥር ተሳትፎ ረገድ አገሪቱ የምዕተ ዓመቱን የትምህርት ግቦች ካሳኩት አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ አድርጓታል፡፡ ይሁን እንጂ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የመጀመሪያ ርከን የማጠናቀቅ መጣኔ አበረታች ቢሆንም የሁለተኛ ርከን የማጠናቀቅ መጣኔን በተመለከተ 48.5 በመቶ የሚሆኑት ተማሪዎች 8ኛ ክፍልን እንዳላጠናቀቁ ያመለክታል፡፡ በጎልማሶች ትምህርት ረገድ ስኬቶች ቢመዘገቡም በዕቅዱ ከተያዘው ግብ አንጻር ሲታይ አመርቂ እንዳልነበር መረጃው ይጠቁማል፡፡

## ለ. ጤና

ባለፉት ዓመታት በተለይም ከመጀመሪያው የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም ጀምሮ የጤናው ዘርፍ የልማት ፕሮግራም ተቀርጾ መከላከልን መሠረት ላደረገው የጤና ፖሊሲ ለጤና መሠረተ ልማት መስፋፋትና በጤናው ዘርፍ ለሰው ሀብት ልማት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ሲተገበር ቆይቷል፡፡ መሠረታዊ የጤና አገልግሎትን ለሁሉም ዜጎች ለማዳረስ እንዲቻል የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር ተቀርጾ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ መርሃ ግብሩ በአራት ዋና ዋና ዘርፎች የተዋቀሩ 16 የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ አገልግሎቶችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህ የጤና ኤክስቴንሽን ዘርፎች የቤተሰብ ጤና፣ በሽታ መከላከል፣ የአካባቢ ንጽህና፣ እንዲሁም የጤና ትምህርት ናቸው፡፡ በዚህም የጤና ኤክስቴንሽ ሠራተኛ የሕዝብ ጥመርታውን 1:2500 ለማድረስ ታቅዶ ሲተገበር ቆይቷል፡፡ በእነዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ያሉትን ቁልፍ ተግባራት ወደ ህብረተሰቡ ለማድረስ ከ38,000 በላይ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ሠልጥነው የተሰማሩ ሲሆን እስከ 2005 በጀት ዓመት ጥመርታውን 1:2436 ማድረስ ተችሏል፡፡ በዚህም በክትባት፣ በቤተሰብ ምጣኔ፣ በወሊድ፣ በቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ፣ በሥርዓተ ምግብ፣ በወባ፣ ቲቢና ኤች አይቪ መከላከል እንዲሁም በመፀዳጃ ቤት ግንባታና አጠቃቀም ዙሪያ ጉልህ መሻሻሎች እንዲኖሩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

### ሀ) የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ሽፋንን በተመለከተ

በ2006 በጀት ዓመት በተደረገው የሥነ ህዝብና ጤና ዳሰሳ ጥናት መሰረት የቤተሰብ መጣኔ ተጠቃሚዎች በ1990 በጀት ዓመት ከነበረበት 6 በመቶ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 42 በመቶ አድጓል፡፡ ይህም በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ አንዲት ሴት በአማካይ የምትወልዳቸውን የልጆች ብዛት ወደ 4 ዝቅ የማድረግ ግብ መሳካቱን ያመለክታል፡፡ በባለሙያ የተደገፈ የወሊድ አገልግሎት መጣኔ 41 በመቶ የደረሰ ሲሆን የድህረ ወሊድ አገልግሎት ሽፋንም 66 በመቶ ደርሷል፡፡ እንዲሁም ንጽህና ደኅንነቱ የተጠበቀ የወሊድ አገልግሎት ሽፋን ከ50 በመቶ በላይ ደርሷል፡፡ ይህም በዕቅዱ መነሻ ዓመት (2002) ከነበበረት 10 በመቶ አፈጻጸም አንጻር ጥሩ መሻሻል ቢያሳይም በ2007 ከተቀመጠው የ67 በመቶ ግብ አንጻር ዝቅተኛ ነው፡፡ ለዝቅተኛ አፈፃፀሙ ዋና ዋና ምክንያቶች በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው የግንዛቤና አመለካከት ችግር፤ በጤና ተቋማት ለወላዶች የሚሰጡ አገልግሎቶች በሚጠበቀው ደረጃ አለመሟላት እና እንዲሁም የመንገድና የትራንስፖርት ችግሮች አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ የእናቶችንና የሕጻናትን ጤና ከማሻሻል አንፃር ዕድሜያቸው 5 ዓመት ሳይሞላቸው የሚሞቱ ህፃናት ቁጥር በ1982 ከነበረበት 204/1000 በ2006 በጀት ዓመት ወደ 68/1000 ዝቅ ብሏል፡፡ ይህ ስኬት የጤና ማበልጸግ፣ በሽታ መከላከልና የመጀመሪያ ደረጃ ፈውስ ህክምና በስፋት መተግበራቸው እንዲሁም ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ጋር ተዳምሮ ያስገኘው ውጤት ነው፡፡

በተጨማሪም ሲተገበሩ ከነበሩ አስፈላጊ ፕግራሞች መካከል የተቀናጀ የጨቅላና ህጻናት ህመምን በጤና ጣቢያ እና በጤና ኬላ የማከም፣ የወባ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር፣ የክትባት ሽፋን ማደግ እና ማህብረሰብ አቀፍ ስርዓተ ምግብ ፕሮግራሞች መተግበር ለውጤታማ ስኬቱ የሚጠቀሱ ናቸው። የእናቶች ሞት በ1982 ከነበረበት በ69 በመቶ የቀነሰ ሲሆን ባለፉት አራት የትግበራ ዓመታት በአማካይ በየዓመቱ በ11 በመቶ ቀንሷል። ለተመዘገበው ውጤት የተጠናከረ የልማት ሠራዊት አደረጃጀት በማህበረሰብ ደረጃ በመፈጠሩ፣ የልማት ሠራዊት አደረጃጀትና የልማት ቡድኖች ባሉባቸው አካባቢዎች ቤት ውስጥ ከመውለድ ነጻ የሆኑ ቀበሌዎችን መፍጠር በመቻሉ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። ኤች አይ ቪ/ኤድስን ከመከላከል አንጻር አዲስ በቫይረሱ የሚያዙ ሰዎች መጣኔ በ90 በመቶ የቀነሰ ሲሆን የበሽታው ሥርጭትም ወደ 0.03 በመቶ ወርዷል። ለዚህም ኤች አይ ቪ ኤድስን ከመከላከል አንጻር የህዝብ ንቅናቄን ማእከል ያደረገ የመከላከልና የመቆጣጠር ፖሊሲና ስትራቴጂን በመተግበሩ ነው። ከእናት ወደ ልጅ የሚተላለፈውን የኤች. አይ. ቪ. ሥርጭት ለመከላከል የፀረ ኤች. አይ. ቪ. ህክምና ያገኙ እናቶች መጣኔ በ2002 ከነበረበት 8 በመቶ በ2006 ወደ 61 በመቶ ከፍ ብሏል። ይህ አፈጻጸም ከፍተኛ የሚባል ቢሆንም በ2007 መጨረሻ ከተጣለው የ85 በመቶ ግብ አንጻር ዝቅተኛ ነው፡፡ በሌላ በኩል የወባ በሽታን ከመከላከል አንፃር በተፈጠረው የልማት ሰራዊት አደረጃጀት አተገባበር ስልት የወባ መከላከልና ቁጥጥር ሥራዎችን ለማሻሻል በመቻሉ የወባ በሽታ ገዳይነት ወደ ዜሮ በመቶ ማውረድ ተችሏል።

### ለ) የሆስፒታል አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ

ተላላፊ በሽታዎችን ከመከላከል ረገድ አመርቂ ውጤቶች ተመዝገበዋል። መድኃኒቱን የተለማመደ ቲቪ ህሙማን ቁጥር እየጨመረ በመሄዱ ከ2001 እስከ 2006 ለ1599 በሽተኞች ሁለተኛ ደረጃ ፀረ ቲቪ ህክምና ተሰጥቷል። በኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ ቲቪ እና ወባ የሚከሰቱ ሞትና ህመም መጣኔ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል። አዲስ በኤች አይ. ቪ. የሚያዙ ሰዎች ቁጥር በ90 በመቶ ሲቀንስ በኤች አይ. ቪ. ምክንያት የሚከሰት ሞት ከ50 በመቶ በላይ ቀንሷል። ለቲቪ ህሙማን የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ የጤና ተቋማት ቁጥር ወደ 32 እና ክትትል የሚያደርጉ ተቋማት ቁጥር ወደ 332 በማደጉ በቲቪ በሽታ ምክንያት የሚከሰት ሞትና የህመም መጣኔ ከ50 በመቶ በላይ ቀንሷል። ባለፉት አራት ዓመታት (2003-2006) የሆስፒታል ማሻሻያ ሰነድ አዘጋጅተው ወደ ትግበራ የገቡ ሆስፒታሎች ቁጥር ከዓመት ዓመት እየጨመረ መጥቷል። በተጨማሪም የህሙማን ቅብብሎሽ በተቀናጀ መልኩ ለመተግበር የቅብብሎሽ መረብ በየክልሉ የተዘረጋ ሲሆን ራሱን የቻለ የድንገተኛ ህሙማን አገልግሎት መስጫ ክፍሎች በየሆስፒታሉ በማደራጀት የአገልግሎት አሰጣጡ በመሻሻል ላይ ይገኛል። የሆስፒታል አገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል ሆስፒታሎች ንጹህና ከአደጋ የተጠበቀ ለማድረግ በሁሉም የመንግሥት ሆስፒታሎች የሚተገበር የCash Clean and Safe Health Facility የተሰኘ እርምጃ መተግበር ተጀመሯል። የደም ባንክ አገልግሎትን በተመለከተ ቀደም ሲል የነበሩትን 12 የደም ባንኮች ቁጥር ወደ 25 ከፍ በማድረግ የሚሰበሰበውን የደም መጠን በዓመት ወደ 88000 ዩኒት ለማድረስ ተችሏል።

### ሐ) የሰው ኃይልና የጤና መሰረተ ልማትን በተመለከተ

ከሰው ኃይል ልማት አንጻር የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን፣ ነርሶችን፣ ላቦራቶሪና ፋርማሲ ባለሙያዎችን በማፍራት ረገድ አበረታታች ውጤት ተገኝቷል። ሀኪሞችን፣ ሰመመን ሰጪ ባለሙያዎችን፣ አዋላጅ ነርሶችን እና ሌሎች የጤና ባለሙያዎችን አሰልጥኖ ወደ ሥራ የማሰማራት ተግባራት እየተካሄደ ይገኛል። የጤና ተቋማት ግንባታን በማስፋፋት የጤና አገልግሎት የማያገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጏል።

የጤና መሠረተ ልማትን በተመለከተ የጤና ተቋማት ግንባታን በማስፋፋት ከዚህ በፊት ምንም ዓይነት የጤና አገልግሎት የማያገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል። የጤና ኬላዎች ቁጥር በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 14192 በ2006 በጀት ዓመት ወደ 16,251 አድጓል። የጤና ጣቢያ ብዛትን በተመለከተ በ2002 ከነበረበት 2142 በ2006 በጀት ዓመት ከ3,500 በላይ ከፍ ማድረግ ተችሏል። በሌላ በኩል የሆስፒታሎች ግንባታና ማስፋፋት ሥራን በተመለከተ የመንግስት ሆስፒታሎች ብዛት በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 116 በ2006 በጀት ዓመት ወደ 155 ከፍ ብሏል። ለዚህም ባለፉት አራት ዓመታት 39 አዳዲስ ሆሰፒታሎች ከመገንባታቸው ጎን ለጎን በነባሮቹ ሆስፒታሎች የማስፋፊያ ግንባታ ተካሂዷል። የጤና

ጣቢያዎች መስፋፋት የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን በማሳደግ ጉልህ ሚና በመጫወታቸው በ2006 የጤና አገልግሎት ሽፋን ወደ 93 በመቶ አድጓል፡፡

**መ) በጤናው ዘርፍ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች አፈጻጸም በተመለከተ**

በጤናው ዘርፍ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ከማሳካት አንጻር ማለትም ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ሞት፣ የእናቶችን ሞት፣ በኤች.አይ.ቪ ኤድስ፣ ወባና ቲቢ የሚከሰቱ ህመሞችና ሞት ከመቀነስ አንጻር አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ ዕድሜያቸው 5 ዓመት ሳይሞላቸው የሚሞቱ ህፃናት ቁጥር በ1982 ዓ.ም ከነበረበት 204/1000 በ2006 በጀት ዓመት ወደ 68/1000 ዝቅ ብሏል፡፡ በዚህም አገሪቱ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግብ 4 አስቀድመው ካሳኩ ጥቂት አገሮች መካከል አንዷ አድርጓታል፡፡ የእናቶችን ጤንነት ከማሻሻል ግብ አንጻር በ1982 የነበረውን 140/100,000 የእናቶች ሞት መጣኔ በ2007 ዓ.ም በ75 በመቶ ለመቀነስ በተቀመጠው ግብ መሠረት እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ በ69 በመቶ በመቀነስ ጥሩ ለውጥ ተመዝግቧል፡፡ በዚህም እስከ ዕቅዱ ማጠናቀቂያ ዓመት ድረስ የእናቶችን ሞት በ75 በመቶ መቀነስ ማሳካት እንደምትችል ይጠቁማል፡፡ በሌላ በኩል በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር ትርጉም ባለው መልኩ መቀነስ፡፡ በወባ ምክንያት የሚከሰተው ሞትም ዜሮ መሆን እና ባለፉት ስድስት ዓመታት በሀገር አቀፍ ደረጃ ምንም ዓይነት የወባ ወረርሽኝ አለመከሰት፣ የቲቢ በሽታን ከመከላከል አንጻር የተገኘው አበረታች ውጤት በጤናው ዘርፍ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግብ የተሳካ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

### 1.8.3 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች

**ሀ. ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች**

በጤናው ዘርፍ በጤና ባለሙያዎችና አመራሮች በኩል የአመለካከት ችግር መኖር በተለይ በባለቤትነት ስራን አለመስራት፣ የተጠቃሚን ደህንነትና ምቾት ያማከለ አገልግሎት አለመስጠት፣ በመንግስት የሥራ ሰዓት በግል የጤና ተቋማት ውስጥ መስራት፣ ከአያያዝ ጉድለት የህክምና መሳሪያዎች ቶሎ ቶሎ መበላሸት፣ የመድኃኒትና ሌሎች የህክምና ግብዓቶች ብክነትና ሥርቆት መኖር፣ የመድኃኒት አቅርቦት እጥረት መኖር፣ የከፍተኛ ባለሙያዎች እጥረትና ፍልሰት መኖር እና የስፔሻላይዝድ ህክምና አገልግሎት አናሳ መሆን በሆስፒታል አገልግለቶች ከሚታዩ ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 1.9 የማስፈጸም አቅም ግንባታና ልማታዊ መልካም አስተዳደር አፈጻጸም

### 1.9.1 ዓላማዎችና አቅጣጫዎች

ጠንካራ የማስፈፀም አቅም ያላው መንግስታዊ መዋቅር መፍጠር፣ ግልፅነትን ማስፈንና ሙስናን ከምንጩ ማድረቅ፣ የህዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ እና የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ማካተትና መተግበር በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የማስፈፀም አቅም ግንባታና ልማታዊ መልካም አስተዳደር የትኩረት አቅጣጫዎች ሲሆኑ የሲቪል ሰርቪሱን የተቀናጀ አቅም በማሳደግና በማጎልበት የመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በብቃት እንዲፈፀሙ ማስቻልና በመንግስታዊ ሥራዎች የተሟላ ግልፅነትና ተጠያቂነት ማስፈን የዕቅዱ ዓላማዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ ዓላማዎችና አቅጣጫዎች መሠረት ባለፉት አራት ዓመታት በአንድ በኩል በትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ውስጥ አልፈው በተለያየ ደረጃ ከሚገኙ የትምህርት ተቋማት ሠልጥነው የወጡ አዳዲስ ወጣት ምሩቃንን በስፋት ወደ ሲቪል ሰርቪሱ እንዲገቡ የማድረግ በሌላ በኩል ደግሞ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ያለውን ነባር የሰው ሃይል የማልማት ጉዳይ ትኩረት ተሰጥቶት ሲተገበር ቆይቷል፡፡

### 1.9.2 የዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም

**የሰው ሀይል የመፈጸም ብቃትን ማሳደግ፡-** ባለፉት አራት ዓመታት በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ብቻ በረጅም ጊዜ የሥልጠና መርሀግብር 3,955 (2,890 ወንድና 1,065 ሴቶች) ሲቪል ሰርቫንቶችን በመጀመሪያ ዲግሪ፣ 4,885 (4,171 ወንድና 714 ሴት) ሲቪል ሰርቫንቶችን በሁለተኛ ዲግሪ እንዲሁም 24 ሲቪል ሰርቫንቶችን በሶስተኛ ዲግሪ ተመርቀዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ስፔሺላይዝድ ተብለው የሲቪል ሰርቪስ ሴክተርን እንዲደግፉ የተለዩና በተለያዩ የትምህርት መስኮች ለአብነትም የከተማ ልማት፣ በፋይናንስ ሥራ አመራር፣ የታክስ አስተዳደር፣ የፌደራሊዝም፣ የአመራርና መልካም አስተዳደር ሥልጠና በመስጠት የመጀመሪያ ዲግሪን ሳይጨምር በሁለተኛ ዲግሪ ብቻ በርካታ (እስከ 2006 ድረስ ከ800 በላይ) የሰው ሀይል አስመርቋል፡፡ በዚህም የታቀደውን ያህል ሙሉ በሙሉ ማሟላት ባይቻልም በክልልም ሆነ በፌደራል ደረጃ የሰው ሀይል ግንባታው በመደገፍ ረገድ ከፍተኛ እገዛ አድርጓል፡፡ ባለፉት አራት ዓመታት በተሰሩ የአቅም ግንባታ ስራዎች በተለይ በሠራዊት ግንባታ ማዕቀፍ በዕለት ተዕለት የተግባር እንቅስቃሴ የሰው ሀይሉን ለመገንባት በተደረገ ጥረት በአመራርም ሆነ በፈጻሚ የሰው ኃይል የመፈጸም ብቃት መሻሻል አሳይቷል፡፡ ሆኖም በመንግስት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ከመሥራትና ከመምራት አኳያ፣ እንዲሁም የአቅም መገንቢያ ተቋማት ተለይተዉ ሚናቸዉን ከመወጣት አኳያ አሁንም ውስንነቶች ያሉ በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠበቃል፡፡

**የመንግስት ተቋማትን አደረጃጀትና አሠራር ማሻሻል፡-** የዚህ ግብ ዋነኛ ትኩረት የመንግስት ተቋማት ከነበሩበት ኋላቀር አሠራር ተላቀው በአደረጃጀትና በአሰራር መንግስትንና ህዝብን የሚያረካ ቅልጥፍና (efficiency) እና የተልዕኮ ውጤታማነትን (effectiveness) እንዲያመጡ ማስቻል ነው፡፡ በክልሎችም ሆነ በተቋማት የውጤት ተኮር ስርዓት የትግበራ ደረጃዎችን ተከትለው ስትራቴጂዎቻቸውን በመንደፍ ወደ ፈጻሚዎቻቸው በማውረድ ረገድ አበረታች ስራዎች አከናውነዋል፡፡ ይሁንና የወረዱትን ስራዎች የትግበራ ደረጃ በውጤት ተኮር ስርዓቱ መሰረት በሚፈለገው ፍጥነትና ጥራት እየተከናወነ አይደለም ምክንያቱም አመራሩ የውጤት ተኮር የምዘና ሥርዓትን በቁርጠኝነትና በትግል ባለመፈፀሙ ነው፡፡ የዜጎች ቻርተርን በተመለከተ አብዛኞቹ ተቋማት ቻርተር ማዘጋጀት የቻሉ ሲሆን በቻርተሩ መሰረት አግልግሎት በመስጠት ረገድ ግን ክፍተት ይታያል፡፡ ስራን በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ኢ.ኮ.ቴ) ታግዞ ከመስራት አንጻር አንዳንድ የፌዴራል ተቋማት ስራዎቻቸውን በኢ.ኮ.ቴ. በመደገፍ ለመተግበር የሚያስችሉ ሶፍትዌሮችን በማልማት ተግባራዊ ማድረግ ጀምረዋል፡፡ ግቡን ከማሳካት አንጻር በዕቅድ ዘመኑ ከታዩ ክፍተቶች መካከል የተቋማት ማወዳደሪያ ሥርዓት እንዲሁም የሠራተኛ የማበረታቻ ሥርዓት በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ አለመሆኑ፣ የውጤት ተኮር ስርዓትን በተጠናከረ የመረጃ ስርዓት አለመደገፍ፣ ተቋማት አፈጻጸማቸውን በሁሉም ደረጃ በመለካት የተሟላ አፈጻጸም ውጤታቸውን እንዲያውቁ አለመደረጉ፣ ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች የውጤት ተኮር ሥርዓት ገንብተው ወደ ትግበራ አለመግባታቸው እንዲሁም በየተቋማት ሠራተኞችን ወደ ሲቪል ሰርቪሱ ለመሳብና ለማቆየት የሚያስችል ስትራቴጂ በመንደፍና በመተግበር ረገድ ያለው ጉድለት ሰፊ ነዉ፡፡

**የለውጥ ኮሙኒኬሽንን ማሳደግ፡-** ይህ ግብ ለውጥን በሚፈለገው ደረጃና ፍጥነት ኮሙኒኬት በማድረግና ለውጡንና በለውጡ የተገኙ ውጤቶችን በማስረጽ ሲቪል ሰርቫንቱንና ህብረተሰቡን በለውጡ ዙሪያ ለማሰለፍና የለውጥ አጋዥ ኃይል ለማድረግ የተቀረጸ ነው፡፡ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ከፌዴራል ከፍተኛ የመንግስት ተቋማት ኃላፊዎችና ከክልል ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ አመራሮች ጋር በየወሩና በየሶስት ወሩ የሚያከናውነው የለውጥና መልካም አስተዳደር አፈጻጸም ግምገማ ለውጡን ኮሙኒኬት ከማድረግ አንጻር ትልቅ ድርሻ የነበረው ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የበላይ አመራሩ የመካከለኛ አመራሩንና የፈጻሚዎችን የለውጥ ግንዛቤ የበለጠ ለማሳደግ የሚያግዝ ስርዓት ዘርግቶ ቋሚ የሆነ መደበኛ የግንኙነት ጊዜ በመመደብ፣ የህዝብ ክንፉንና የመንግስት ክንፉን በመለየት ኮሙኒኬት ማድረግ መጀመሩ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በየተቋሙ የለውጥ አመራሩ የኮሙኒኬሽን ስራ የፖለቲካ አመራሩ ሥራ እንደሆነ ተገንዝቦ ትኩረት

አለመስጠቱና የኮሙኒኬሽን ሥራውን ሁሉም አውቆት እንደ ሥርዓት አለመተግበሩ በዕቅድ ዘመኑ የተስተዋሉ ክፍተቶች ናቸው፡፡

**የግልጽነትና የተጠያቂነት አሠራርን በማስፈን የኪራይ ሰብሳብሳቢነትን አመለካከትና ተግባራትን መቀነስ፡-** ግልጽነትን በማስፈን ረገድ ሁሉም የመንግስት ተቋማት ለዜጎች የሚሰጡትን አገልግሎትና የልማት ሥራ ከዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ የአፈፃጸም ሂደቱን ለህዝቡ ግልፅ ማድረግ ጀምረዋል፡፡ የዜጎች ቻርተር የአዘገጃጀትና የአተገባበር ማኑዋል ተዘጋጅቶ ለተቋማት እንዲደርስ መደረጉና ተቋማት ለዜጎች የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች በመለየትና የአገልግሎት መስጫ ስታንዳርድ በማዘጋጀት መተግበር መጀመራቸው ዋና ዋና ክንውኖች ናቸው፡ ፡ የታክስ ሥርዓቱን ከኪራይ ሰብሳቢነትና ሙስና የጸዳ ለማድረግ ወሳኝ የሚባልና ንቅናቄን ያስከተለ በኪራይ ሰብሳቢነትና በሙስና የተጠረጠሩና ከታክስ ስርዓቱ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸውን ከፍተኛ የሥራ ሃላፊዎችንና ነጋዴዎችን በማጋለጥ በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ ተከናውኗል፡፡ ከስኬት አንፃር ሲታይ ዜጎች/ተገልጋዮች በቻርተሩ መሠረት ከመ/ቤቶች አገልግሎት ለማግኘት ጥያቄ ማቅረብ ጀምረዋል፡፡ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ለተገልጋዮች ግልፅ ከማድረግ አንፃር መሻሻል ታይቷል፡፡ የመንግስት ተቋማት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርታቸውን በወቅቱና በተሻለ ጥራት ማቅረብ ችለዋል፡፡ የተቀናጀ የፋይናንስ አሠራር ሥርዓት መዘርጋቱ በመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ግልፅነትን በመፍጠር ተጠያቂነትን በቀላሉ ለማረጋገጥ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር አስችሏል፡፡ ቻርተሩን በተሟላ ሁኔታ በሁሉም የመንግስት ተቋማት ሥራ ላይ በማዋል ቀጣይነት ባለው መልኩ በተቀመጠው የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ መሠረት አፈጻጸሙን ተከታትሎ በመገምገም አለመተግበርና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር አሁንም የስርዓቱ ፈተና መሆኑ በቀጣይነት ትኩረት የሚሹ ጉድለቶች ናቸው፡፡

**የህብረተሰብ ተሳትፎን ማሳደግ፡-** በዕቅድ ዘመኑ የህዝብ ተሳትፎን ከማረጋገጥ አንፃር ትኩረት ከተሰጠባቸው ዋና ዋና ተግባራት መካከል የተሳትፎ ስርዓትን የመዘርጋት፣ የዜጎች፣ የህዝብ አደረጃጀቶች (የብዙኃንና የሙያ ማህበራትን) እና የመንግስት ተቋማት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎን ማሳደግ ይገኙበታል፡፡ ዕቅዱን በመፈጸም ረገድም በፌዴራልና በክልሎች በየደረጃው ባሉ ተቋማት የህዝብ ክንፍን የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ የተለዩ የህዝብ ክንፍ አካላትና ፈፃሚው በዕቅድ ዝግጅትና ግምገማ እንዲሁም በሌሎች የልማት ስራዎች ላይ ሚናቸውን አውቀውና አምነው እንዲሳተፉ የሚያስችሉ የግንዛቤ መፍጠሪያና የአቅም ግንባታ መድረኮች ተካሂደዋል፡፡ የህዝብ ክንፉ ተሳትፎ የሚጠናከርበትና ከመንግስት ተቋማት ጋር ቋሚ ግንኙነት የሚፈጥርበት አሰራር ተዘርግቷል፡፡

የህብረተሰብ ተሳትፎን አስመልክቶ ከሚጠቀሱት ክፍተቶች መካከል የዕቅድ ዝግጀትና ግምገማ ላይ የሚደረገው የህብረተሰብና የብዙሀን ማህበራት ተሳትፎ በተሟላና ቀጣይነት ባለው መልኩ ግለቱን ጠብቆ ተግባራዊ አለመሆን እና ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች የተሳትፎ ስርዓት ገና በጅምር ላይ መሆኑ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ዜጎች በግላቸውም ሆነ በጋራ በሚያከናውኗቸው የተለያዩ የልማት ሥራዎችና የቴክኖሎጂ አጠቃቀሞች ህዝቡን በማሳመንና የጋራ መግባባት ፈጥሮ እንዲሳተፍ በማድረግ ከማሰራት ይልቅ የማስገደድ አዝማሚያ አልፎ አልፎ መከሰቱ በክፍተት የሚታይ ነው፡፡

**የወረዳና የአካባቢ ምክር ቤቶችን አቅም ማሳደግ፡-** ባለፉት ዓመታት በሁሉም ክልሎች የከተማና የወረዳ አመራሮች ያሉባቸውን ችግሮች በመፈተሽ አመለካከታቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን ሊያጎለብቱ የሚችሉ ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ፕሮግራሞች ዙሪያ የምክር ቤት አባላት የሆኑ አመራሮችና ፈጻሚዎች ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

**ልማታዊ የከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ሪፎርም አፈጻጸም**

ዘርፉ የሚመራበት ግልጽ ፖሊሲና ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ በመንግስት የፀደቀ ሲሆን ይህን መነሻ በማድረግም የተሻሻለው የሊዝ አዋጅ እና የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ፀድቆ ለክልል የመሬት ተቋማትና ሌሎች

የሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን ስልጠና በመስጠት ወደ አፈጻጸም ተገብቷል፡፡ የደቀቁ እና የተጎዱ የከተሞች አካባቢዎችን ከነበረበት የ60 በመቶ ሽፋን በግማሽ በመቀነስ 30 በመቶ ለማድረስ የታቀደ ቢሆንም በሚፈለገው ደረጃ አልተከናወነም፡፡ የሊዝ አዋጁን በተሟላ መልኩ ወደ ተግባር ከማሸጋገር አንጻር 750 ከተሞችን ወደ ሊዝ ለማስገባት ታቅዶ፣ 663 የገቡ ሲሆን 87 ከተሞች እስከ ዕትዕ ዘመኑ መጨረሻ ወደ ሊዝ እንደሚገቡ ይጠበቃል፡፡ የለማ መሬት በሊዝ ጨረታ እና ሊዝ ምደባ 204000 ሔክታር ታቅዶ፣ በምደባ 10000 ሔክታር፣ በጨረታ 19647 ሔክታር በድምሩ 29647 ሔክታር ለተገልጋዩ ተላልፏል፡፡ ከእቅድ አፈጻጸም አኳያ ሲታይ ጥሩ የሚባል ቢሆንም በከተሞች ለኢንቨስትመንት የሚውል የለማ መሬት ከገበያው ፍላጐት አንጻር ቀጣይነት ባለው መልኩ በስፋት በማቅረብ ረገድ አሁንም ሰፊ ክፍተት የሚታይበት ነው፡፡

በ86 ከተሞች ሰነድ አልባ ይዞታዎችን ሥርዓት ለማስያዝ ታቅዶ በሰነድ አልባነት ከተለዩት 357,744 ይዞታዎች 95 በመቶው የይዞታ ማረጋገጫ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል በህገ ወጥ የተያዙ ይዞታዎችን ሥርዓት ከማስያዝ አንጻር በ86 ከተሞች ለመተግበር ታቅዶ፣ በትግራይ እና በአማራ ክልላዊ መንግስት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ስርዓት እንዲይዙ ተደርጓል፡፡ የህገ-ወጥ የመሬት ይዞታ ስርዓት ከማስያዝ አኳያ ሰፊ ሥራ የሚቀር መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ማስፈፀሚያ የከተማ ካዳስተር ቅየሣ ደንብና የከተማ መሬት ይዞታ ማረጋገጥ እና ምዝገባ ደንብም ፀድቋል፡፡ የመረጃ ግብአትን ከማሟላት አንጻር የመሬት ይዞታ ምዝገባን ለማስተግበር የማረዱ የቅየሣ መቆጣጠሪያና ነጥቦችን በመዘርጋት እና የ23 ከተሞች የአየር ፎቶ ማንሣት እና ካርታ ሥራ በማጠናቀቅ፣ በተጨማሪ በሣተላይት ስትሪዩ ምስል ለ62 ከተሞች መሠረታዊ ካረታ ተዘጋጅቷል፡፡

ለመሬት መረጃ ሥርዓቱ አጋዥ የሆነ የሰው ኃይል አቅም ለመገንባት እንዲቻል ለከተማ መሬት ዘርፍ ከተዘጋጁት 16 የሙያ ደረጃዎች በ12ቱ ከደረጃ- II እስከ ደረጃ IV 4,800 የዘርፉን ባለሙያዎች በመመዘንና በማሰልጠን ለማብቃት ታቅዶ እስከ ህዳር 30/2007 1,369 የመሬት ዘርፍ ባለሙያዎች ተመዝነው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ተደረጓል፡፡ ክልሎች የከተማ መሬት መረጃ ማሰባሰብ እና ማደራጀት አቅም እንዲፈጥሩ ለማስቻል፣ የቅየሣ እና ካርታ ሥራ ዩኒት እንዲያደራጁ የማድረግ ስራ በአራት ክልሎች ተከናውኗል፡፡ የተዋቀረውን የቅየሣ እና ካርታ ሥራ ዩኒት በዘመናዊ የመሬት መረጃ ማሰባሰብና ማምረቻ መሣሪያዎች የማሟላት ስራ ተሰርቷል፡፡

ከኮንስትራክሽን ዘርፍ አንጻር የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ተዘጋጅቷል፡፡ የኮንስትራክሽን ኘሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩትም ተቋቁሞ ሥራ ጀምሯል፡፡ ክልሎችና ከተሞች አሁን ያሉበትን ደረጃ በማመዛዘን የሕንጻ አዋጅ፣ ደንብ እና ተጓዳኝ መመሪያዎች ተግባራዊ ለማድረግ በ126 ከተሞች አስፈላጊ አደረጃጀት ተፈጥሮ ወደ አፈጻጸም ተገብቷል፡፡ የህንጻ ሹም አደረጃጀቱና የሰው ሀይል መዋቅሩ በሁሉም ክልሎች ዘግይቶ የጸደቀ ቢሆንም ከግማሽ በላይ በሚሆኑ ከተሞች የህንጻ ሹም ተሰይሞ ትግበራ ያለመጀመሩ በቀጣይ ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ ነው፡፡

### ልማታዊ የታክስና የጉምሩክ አስተዳደር ሪፎርም ስራ አፈጻጸም

በአገር አቀፍ ደረጃ በጣት አሻራ የተደገፈ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 1.6 ሚሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ እስከ እቅድ ዘመኑ መጨረሻ 2.5 ሚሊዮን መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ለ1.8 ሚሊዮን ያህሉ መታወቂያ ታትሟል፡፡ ከታተመው ውስጥም 1.7 ሚሊዮን ያህሉ ለግብር ከፋዩ ተሰራጭቷል፡፡ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ከመጠቀም አንጻር 101.097 ግብር ከፋዮች 106.782 መሳሪያዎችን ገዝተው በስራ ላይ ያዋሉ ሲሆን አፈጻጸሙ አበረታች ቢሆንም በየክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ተመሳሳይ ግንዛቤና እርምጃዎች ያለመኖርና የትኩረት ማነስ የአቅራቢዎች አቅም ማነስ እና ተጠቃሚ ግብር ከፋዮች ዘንድ አሁንም የአመለካከት ችግሮች በመኖራቸው ይህ ውጤት ውስን ሊሆን ችሏል፡፡ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን የግብር ከፋዩን ግንዛቤ በማሳደግና መረጃንም ተደራሽ ለማድረግ የተሰሩ ስራዎች አበረታች ናቸው፡፡

### የመንሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ሪፎርም አፈፃፀም

በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ሪፎርም ኘሮግራም ዋና ዓላማ ውጤታማና ቀልጣፋ፣ ግልጽና ተጠያቂ የመንግስት የፋይናንስ ስርዓት ማስፈን ነበር፡፡

የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ፣ ወደ 15 የሚጠጉ መመሪያዎችና ልዩ ልዩ ዝርዝር የአሠራር ማንዋሎች ተቀርፀው ከፌደራል እስከ ክልሎች ድረስ በሥራ ላይ ውለዋል፡፡ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅና የአፈፃፀም መመሪያ ወጥቶለትና ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው ተቆጣጣሪ ኤጀንሲም ተቋቁሞ ሥራው እየተመራ ይገኛል፡፡ ሰፊ ዕቃዎች (Common User Item) ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ በማዕከል በመግዛትና የንብረት አወጋገድ ሥርዓቱን ከማጠናከር አንፃር የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎትን የሚያስተባብር ራሱን የቻለ የመንግሥት መስሪያ ቤት በማቋቋም ግልጽና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ የዕቃዎችና አገልግሎቶችን ግዥ በመፈፀም የመንግሥት ሀብትና ንብረት ለታቀደለት ዓላማ እንዲውል እየተደረገ ነው፡፡

የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደሩን በዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት እንዲመራ ለማድረግ በዕቅድ ዘመኑ IBEX የተባለ ሶፍትዌር ለበጀት፣ ለሂሣብና ለትሬዥሪ አሠራሮች ተቀርጾ ከፌደራል እስከ ወረዳዎች ድረስ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሶፍትዌር ውስንና ሁሉን አቀፍ ባለመሆኑ ዘጠኝ ሞጁሎች ያሉት IFMIS (Integrated Financial Management Information System) የተባለ የተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት በመላ አገሪቱ በመዘርጋት ቀጥተኛ በሆነ የኮምፒውተር መረብ የተገኘ ፍሰት እንዲኖር እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

በአምስት አመቱ የዕቅድ ዘመን በሁሉም ደረጃ ይተገበራሉ ተብለው ከተቀመጡት ግቦች የኘሮግራም በጀት ትግበራ ወደ ክልሎች አለመውረድ፣ IFMIS በሁሉም የፌደራልና የክልል መስሪያ ቤቶች አለመዳረስ፣ በአካውንቲንግና ኦዲቲንግ ሕጎቹን ከማውጣት ባለፈ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የማጣጣሙ (Customization) እና የኘሮፌሽናል የስልጠና ማዕከል በማቋቋም ስልጠና መስጠት መጀመሩ ያልተጠናቀቁና በቀጣይነት እየተከናወኑ የሚገኙ ሥራዎች ናቸው፡፡

በአሠራር ሂደቱ አፈፃፀም ውስንነቶች ያሉበት በመሆኑ በ2ኛው የዕትዕ ዘመን ደካማ ጎኖችን በማስወገድ ለኪራይ ሰብሳቢነት ያልተጋለጠ፤ ውጤታማና ግልጽ የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡

### ልማታዊ የንግድ ሥርዓት መፍጠሪያ ሪፎርም አፈፃፀም

የተደራጀ የንግድ ዘርፍ የለውጥ ሠራዊት ለመገንባትና ውጤታማ አደረጃጀት ለመፍጠር የተጣለውን ግብ ለማሳካት የሚኒስቴር መ/ቤቱን፣ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣንን የማደራጀት ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቡና ግብይትን በተሻለ ሁኔታ ለመደገፍና የወጪ ንግድን ለማስፋፋት የቡና ግብይት ዳይሬክቶሬትና የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል እንዲሁም በንግድ ምዝገባ ፈቃድ አገልግሎት ዙሪያ የሚያዩትን የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶች እና በአክሲዮን ማህበራት አደረጃጀት ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመቅረፍ በአዲስ አበባ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና የአክሲዮን ማኀበራት ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ተደርጓል፡፡

የሰው ኃይሉን እውቀትና ክህሎት ለማዳበር የታቀደውን ዕቅድ በመከወን ሂደት የንግድ ዘርፉን በሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ የህግ ማዕቀፎች ፓኬጅ ላይ ከ5000 ያላነሱ በየደረጃው ያሉ አመራርና ፈፃሚ አካላት እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፡፡

የምርት ግብይቱን ዘመናዊና ፍትሀዊ ለማድረግና የተጀመረውን የግብርና ትራንስፎርሜሽን ለማሳካት ለቡና፣ ሰሊጥ እና ነጭ ቦሎቄ የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት፣ የቡና 1,500፣ የሰሊጥ 229 እና ነጭ ቦሎቄ 170

የመጀመሪያ ደረጃ ገበያን በማደራጀት እና በየደረጃው ያለውን የግብረ ኃይል አካላት በማቋቋም፣ የክትትልና ድጋፍ ስርአት በመዘርጋት በተቀመጠው የግብይት ስርአት ብቻ የሚገበያዩበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

**ልማታዊ የባህር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት አፈፃፀም**

ዘጠኝ መርከቦች (ሰባት ዕቃ ጫኝ እና ሁለት የነዳጅ መርከቦች) ግንባታ ኘሮጀክት በዕቅድ በተያዘላቸው ጊዜ ተጠናቀው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በዕቅድ ዘመኑ የመጀመሪያ ሁለት አመታት 111,528 ቶን ብቻ የነበረው የድርጅቱ መርከቦች በአንድ ጊዜ ዕቃ የማንሳት አቅም ወደ 307,528 ቶን ማሳደግ ተችሏል፡፡ ይህም የ275 በመቶ ተጨማሪ አቅም መገንባቱን ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ ሌላ አገሪቷ ከዕቅድ ዘመኑ በፊት ያልነበራትን ነዳጅ የመጫን አቅም ለመገንባት በተያዘው መሠረት በአንድ ጊዜ 83,000 ቶን ነዳጅ መጫን የሚችሉ የሁለት መርከቦች ግንባታ ተጠናቀው ሥራ የጀመሩ ሲሆን እስከ 45 በመቶ የሚሆነውን የሀገሪቱን የነዳጅ ፍላጎት ማጓጓዝ የሚችል አቅም መገንባቱን ያሳያል፡፡

ከቻይና ወደቦችና ከሩቅ ምሥራቅ አገሮች ከ45 እስከ 60 ቀናት የነበረው የምልልስ ጊዜና ዕቃን የማንሳት ሁኔታ በመርከቦች ቁጥርና አቅም መጨመር ከ2-3 ሣምንታት ጊዜ ውስጥ ዕቃዎችን ማንሳት ተችሏል፡፡ ከህንድ እና ሌሎች መስመሮችም ተመሳሳይ መሻሻል የታየበት አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡ ለኮንስትራክሽን ዘርፍ ከፍተኛ የአርማታ ብረት ከሚጫንባቸው ቱርክና ዩክሬን ሁለት ትላልቅ መርከቦችን በመመደብ በራሳችን አቅም አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡ ይህም ሆኖ በአገራችን መርከቦች ሙሉ በሙሉ የማይስተናገዱ ዕቃዎች በተለይም የተሽከርካሪ ካርጎና የኮንቴይነር ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የሚያስችል የመርከብ አቅም የማሳደግ ጉዳይ በቀጣይ ዘመን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ በአሁኑ ወቅት የድርጅቱ መርከቦች ወደ አገራችን ከሚመጣው ጠቅላላ ገቢ ዕቃዎች ያላቸው የገበያ ድርሻ ከ20 በመቶ በታች ነው፡፡

የደረቅ ወደቦችን በሞጆና ሠመራ ላይ የማደራጀቱ ሂደት ከእቅድ ዘመኑ ሁለት ዓመት አስቀድሞ የተጀመረ ቢሆንም ቴክኖሎጂውና አሠራሩ ለአገራችን አዲስ ከመሆኑ የተነሣ እንዲሁም ሞጆ ደረቅ ወደብን በዘመናዊ መልክ እንዲያደራጅ ሥራውን በማኔጅመንት ኮንትራት የወሰድው የሆላንድ ኩባንያ በሚፈለገው ፍጥነትና ጥራት ባለመፈፀሙ የተቀመጠውን እቅድ ለማሣካት አልተቻለም፡፡

በ2003 ዓ.ም በቀይ አሸዋ የተዘጋጁ ቦታዎችን ጨምሮ በሞጆና በሠመራ በአንድ ጊዜ 4,116 ኮነቴይነሮችን ብቻ ማስተናገድ የሚችል 2.5 ሔ/ር ቋሚና 3.0 ሔ/ር በድምሩ ጊዜያዊ 5.5 ሔ/ር ተርሚናል አገልግሎት ይሰጥ ከነበረበት ደረጃ በአሁኑ ወቅት በአንድ ጊዜ 18,284 ኮንቴይነሮችን ማከማቸት የሚችል 19.2 ሔ/ር ቋሚና 13.0 ሔ/ር ጊዜያዊ በድምር 32.2 ሔ/ር የደረቅ ወደብ ተርሚናል አቅም ተገንብቷል፡፡ ባለፉት አምስት ዓመታት ከሞጆና ከሠመራ በተጨማሪ በመቀሌ፣ በኮምቦልቻ፣ /አማራ ክልል/፣ በድሬዳዋ፣ በዱከምና ቃሊቲ ኮሜት ግቢ ጊዜያዊና ቋሚ ግንባታዎችን በመሥራት አገልግሎት መስጠት ተጀምሯል፡፡

በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከተያዘው 80 በመቶ ገቢ እቃዎችን በመልቲ-ሞዳል ሥርዓት ለማስተናገድ ከተያዘው ግብ አኳያ ሲመዘን የኮንቴይነር እቃዎች አፈፃፀም በተያዘው እቅድ መሠረት የሚፈፀም ሲሆን የተሽከርካሪ ካርጎ አፈፃፀም ከተያዘው እቅድ 50 በመቶ እንደሚደርስ ይጠበቃል፡፡ በዓመት ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገባው ገቢ እቃዎች አኳያ የመልቲ ሞዳል ሥርዓት ሽፋን ብትን እቃዎች /ማዳበሪያ፣ ስንዴ፣ ስኳርና ሌሎችን ሣይጨምር በ2007 በጀት ዓመት መጨረሻ 30 በመቶ እንደሚደርስ የሚጠበቅ ሲሆን ይህ ከተያዘው የ80 በመቶ ሽፋን ግብ አንፃር ሠፊ ክፍተት ያለው በመሆኑ ሥርዓቱን ለማስፋት የሚያስፈልጉ ዝግጅቶችን ማፋጠንና ተገቢውን ትኩረት በመስጠት መንቀሣቀስ የሚገባው ጉዳይ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት በመተግበር የእቃዎችን የጅቡቲ ወደብ ላይ ቆይታ ትርጉም ባለው ደረጃ በመቀነስ ከእቅድ ዘመኑ በፊት በአማካይ 30 ቀናት የነበረውን ቆይታ ወደ 20 ቀናት ለማውረድ ከተያዘው እቅድ አንፃር የመልቲ ሞዳል ኮንቴይነሮች አፈጻጸም በአማካይ ወደ 8 ቀናት ለማውረድ ተችሏል፡፡ ይህ አፈጻጸም ከዕቅድ ብቻ ሣይሆን ዛሬም ድረስ በነባሩ የዩኒ-ሞዳል ሥርዓት ከሚጓጓዘው እቃዎች ቆይታ ከ20-30 ቀናት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ውጤት የተገኘበትና የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ልማት ሥርዓት

መሆኑን የተረጋገጠበትና ደንበኞች ቅሬታ ለመፍታት ሪገድ ቁልፍ እርምጃ መሆኑ በተጨባጭ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### የፍትህ ሥርዓት የለውጥ ሪፎርም አፈጻጸም

የአገራችን የወንጀል ፖሊሲ ተቀርጾ መጽደቁ፣ የቅጣት ማኑዋል ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዲሆን መደረጉ ለተመሣሣይ ወንጀሎች ተመሣሣይ ወይም /ተቀራራቢ/ ቅጣት ለመጣል መቻሉ፣ በወንጀል የተጠረጠሩና ሊያዙ የሚገባቸውን ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር የማዋል፣ የፎረንሲክ ላቦራቶሪዎች አቅም እየተፈጠረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የምርመራ ስራው በይንሣዊ ግብዓቶች በታገዘ ውጤታማነቱ እየጨመረ መምጣቱ፣ የክስና የክርክር መዛግብት ላይ ውሣኔ የመስጠት ጥፋተኛ የማስባልና የማስቀጣት አቅም እየተሻሻለ መምጣቱ የፍትሀ ብሔር ጉዳዩችን በድርድር የመጨረስ ሁኔታ የመሻሻል ጅምር በማሣየቱ በክርክር ሲጠፋ የነበረውን ጊዜ፣ ገንዘብና ጉልበት መቆጠብ መጀመሩ ከውጤታማነት አንጻር የሚታይ ነው፡፡

የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጥን በተመለከተ የፌዴራልም ሆነ በክልል ተገልጋዩን የሚያረካ የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠቱና ተጠናክሮ በመቀጠሉ በህብረተሰቡ አድናቆትን አግኝቷል፡፡ የዜጎች  የምዝገባ ስርዓትን ለመዘርጋት የወሣኝ ኩነቶችት ምዝገባ ብሔራዊ መታወቂያ ስርዓት አዋጅና ደንብ የወጣና የፀደቀ ሲሆን ለክልሎችም ሞዴል ደንብ ተዘጋጀቷል፡፡ አዋጅንና ደንቡን ወደ ተግባር ለማሸጋገርም ተቋማት ተቋቁመው የቅድመ ዝግጅት ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡ ከዚህ አኳያ የተመዘገበው አፈጻጸም ከዝግጅት ያልዘለለ በመሆኑ በቀጣይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የሚከናወን ይሆናል፡፡

ልዩ ትኩረት የሚሹ ወንጀሎች የራሣቸው ችሎት ኖሯቸው እንዲታዩ የሚደረግበት አሠራር ተጠናክሮ ቀጥሏል፣ የመንጠባጠብ ምጣኔ /ATTRITION/ ቀንሷል፣ በፍርድ ቤቶች ያለው የመዝገቦች ክምችት እየቀሰ መጥቷል፡፡ በዚህም የተነሣ ባለፉት ዓመታት ከስድስት ወራት በላይ እልባት የማያገኙ ፋይሎች ቁጥር እየቀነሰ መምጣቱ በዋነኝነት የተገኘ ውጤት ነው፡፡

ህረተሰቡ የመልካም ስነ-ምግባር ጥቅምን እንዲረዳ ሙስናን እንዲጠየፍና ሙሰኞችን እንዲያጋልጥ  ለበርካታ ዜጎች የአሰልጣኞች ስልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶች ተሰተዋል፡፡ የጸረ ሙስና ትግሉ ያለበትን ደረጃ ለማወቅ የሚያስችሉ በፌዴራልና በክልል ደረጃ ከ32 በላይ መለስተኛ የዳሰሳ ጥናቶች ተካሄደው ለግብአትነት እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ ሀብትን ለመመዝገብና ለማሳወቅ የሚያስችሉ አዋጆችን ደንቦችና መመሪያዎች በማውጣት በአገር አቀፍ ደረጃ  የ198,148 የአስመዝጋቢዎች ሀብት ለመመዝገብ ተችሏል፡፡ ከዚህ ወስጥ የ111,413 ሀብት አስመዝጋቢዎች መረጃ የማደራጀት ስራ ተከናውኗል፡፡

የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ የሚያግዙ የተለያዩ እቅዶች ተነድፈው ተግባራዊ ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ ከዚህ አንጻር በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ  የሰብአዊ መብቶች ድርጊት መርሀ ግብር ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ መጀመሩ፣ የወንጀል ስነ ስርአት ህግ ዝግጅትን በሚመለከት የመጀመሪያው ረቂቅ በመጠናቀቅ ላይ መሆኑ፣ የንግድ ህጉና የወንጀል የፍትሀ ብሄር ስነ ስርአት ህጎቹ አንዳንድ ድንጋጌዎችንም የማሻሻል ጥናት መጀመሩ፣ እንዲሁም የማህበረሰብ አቀፍ ቅጣት አዋጅ ተዘጋጅቶ ለውሳኔ መቅረቡ ይጠቀሳሉ፡፡

ታራሚዎችን በተመለከተ እቅዱን ለማሳካት በተሰሩት የተለያዩ የማረምና የማነጽ ስራዎች በታራሚዎች ሰብአዊ መብት አያያዝ  ላይ መሻሻል ታይቷል፡፡ ታራሚዎች በልማት ስራ በመሳተፋቸው ተጠቃሚ የመሆን ጅማሮ አሳይተዋል፡፡ ታርመው ወጥተው የባህሪ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል በቂ ስልጠና አግኝተው ወደ ህብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ ተደርጓል፡፡

### ለውጡን በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመደገፍ የመጠቀም አቅምን ማሳደግ

ለውጡን በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ከመደገፍና ከመጠቀም አንጻር ከተገኙ ስኬቶች መካከል ተገልጋዮች ባሉበት ሆነው መረጃዎችን እንዲያገኙ መቻሉ፣ ጉዳዮቻቸውን ለማስፈጸም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ተቋማት መረጃዎችን በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አማካኝነት በቀላሉ ማሠራጨት መቻላቸው፣

የተቋማት ተደራሽነት መጨመሩ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋመ ብሄራዊ የተቀናጀ መረጃ አያያዝ የዳሰሳ ጥናት መጠናቀቁ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ከመጠቀም አንጻር በዕቅድ ዘመኑ ከታዩ ጉድለቶች መካከል የውጤት ተኮር ስርአትን በአውቶሜሽን የመደገፍ ስራ አለመጠናቀቁ፣ የመረጃና የመዛግብት አያያዝ ሥርአቶች በሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረሳቸው፣ በፌደራል ደረጃ የተጀመሩት ሥራዎች ወደ ክልሎች አለመዘርጋታቸው፣ የፌደራልና የክልል አካላት በዋይድ ኤሪያ ኔትዎርክ አለመገናኘታቸው፣ በዘርፉ የሰለጠኑ ባለሙያዎች ዕጥረት ያለ መሆኑ፣ ብሔራዊ የተቀናጀ የፍትሕ መረጃ ሥርዓት (NIJIS) መዘግየቱ፣ የሽብርና ዓለም አቀፋዊ ባህሪይ ያላቸውን ወንጀሎች በቀላሉ ለመለየትና ለመከላከል የሚያስችሉ ሶፍትዌሮች አለመልማታቸው በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡

**የባለብዙ ዘርፍ ሥራዎችን አካቶ መተግበር**

በየተቋማቱ በባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችና ተያያዥነት ባላቸው የተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ለሠራተኞቻቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን፤ሥልጠናዎችና ኩነቶችን በማዘጋጀት እንዲሁም በህትመት ውጤቶች ውስጥ የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን በማካተት የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል፡፡

በተቋማቱ የሠራተኞች ቅጥር፣ እድገት፣ በሥልጠና ዕድል አሰጣጥ ሂደት እና በሹመት የጾታ ምጣኔንና የብሄር ተዋፅኦን መሠረት ያደረገ እንዲሆን ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በርካታ ሴት ሠራተኞች በተለያዩ የትምህርት ተቋማት የነጻ ትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

የተገኙት ስኬቶች እንደተጠበቁ ሆነው በህገ መንግስቱም ሆነ በሌሎች ህጎች በሴቶች፣ በህፃናትና አካል ጉዳተኞች መብትና ጥቅም ለማስከበር የተሰጠውን ኃላፊነት በማጤን ትኩረት ሰጥቶ አለመስራት፣ በቅጥር፣ በእድገትና ሹመት የሴቶችን ተሳትፎ በማሳደግ ተጠቃሚነታቸውን በሚገባ ለማረጋገጥ የተሰራው ስራ በቂ አለመሆኑ፣ ሴት ሰራተኞችን በማሳተፍ  በሴቶችና ህፃናት የወንጀል ጥቃት የተቀናጀ የመከላከል ስራ አለመሰራቱ፣ የአካል ጉዳተኞች ጉዳዮች፣ በስነ-ሕዝብና የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ዙሪያ የሚጠበቀውን  ያህል ውጤት  አለመገኘቱ ፤እንዲሁም የመልካም አስተዳደርና ሪፎርም ክላስተር ከተሰጠው ስልጣንና ሃላፊነት አንፃር በኤች አይ ቪ ኤድስ ዙሪያ የሚፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች ላይ ጥናት አካሂዶ ህግ የማርቀቅና የማፀደቁ ተግባር በቂ አለመሆኑ በጉድለት የታዩና በቀጣዩ የዕቅድ ዘመን ተኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

## 1.9.3 ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች

### *ሀ. ያጋጠሙ ፈታኝ ሁነታዎች*

ባለፉት አራት ዓመታት (ከ2003-2006 በጀት ዓመት) በአቅም ግንባታ ዙሪያ መልካም የሚባሉ አፈጻጸሞች ማዝመዝገብ ቢቻልም ይህ ውጤት እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግስት የፖሊሲ አቅጣጫዎች፣ በህዳሴ ጉዞና በልማት ዕቅዶች ዙሪያ የተሟላ ግንዛቤ ይዞ ከመሥራት እና ከመምራት አኳያ አሁንም ውስንነቶች ይታያሉ፡፡ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለከካከቶችንና ተግባራትን በመዋጋት የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት ረገድ ከበላይ አመራሩ ጀምሮ የታዩ ክፍቶች ሲጠቀሱ፣ የአቅም መገንቢያ ተቋማት ተለይተው ሚናቸውን ሲወጡ የነበሩ ቢሆንም እንዚህ ተቋማት የትኩረት ማዕከላቸውን ለይተው እና የአመራሩንና የሲቪል ሰርቪሱን ክፍተቶች አንጥሮ በማውጣትና አቅም ለመገንባት ውስንነቶች የነበሩባቸው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

## 1.10 የሕዝብ ተሳትፎ፣ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና ብሔራዊ መግባባት

**የህዝብ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎን በተመለከተ** በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት የህዝብ የውክልና ተሳትፎ ሁለት መገለጫዎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሲሆን ሁለተኛው የምርጫ ውጤት የሆኑና ያልሆኑ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን የመፍጠር፣ የማደራጀት፣ የማጠናከርና በአግባቡ የማንቀሳቀስ ሥራ ነው፡፡ ባለፉት ዓመታት የምርጫ ሂደቶችን ሰላማዊ፣ ነጻ፣ ዴሞክራሲያዊና በህዝቡ ዘንድ ተአማኒነት ያላቸው እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ በምርጫ ሂደቶቹ ላይ የህዝቡ ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጐለበተ መጥቷል፡፡ የዲሞክራሲ ተቋማት የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ጥረት ሲያደርጉና ሚናቸውን ሲጫወቱ ቆይተዋል፡፡ ለዚህም በርካታ ፖሊስዎችና ስትራቴጂዎችን ወደ ተግባር የቀየሩ የህግ ማዕቀፎች እንዲወጡና ሥራ ላይ እንዲውሉ የተደረገ ሲሆን የሀገሪቱ ህዳሴ በተደራጀ መንገድ የተገለጸበት የመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የሀገራችን ህዝቦች በየደረጃው ተወያይተውበትና ሙሉ ድጋፋቸውን ሰጥተውት ከዲሞክራቲክ ተቋማት አንዱ በሆነው በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ፀድቆ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሀገራችን ህዝቦች በየደረጃው በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ በዕቅዱ የትግበራ ሂደት የተሳተፉ ሲሆን የዕቅዱን አፈፃጸም በየዓመቱ በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲገመግሙ ተደርጓል፡፡

**ህዝቡንና የህዝብ አደረጃጀቶችን አቅም መገንባትን በተመለከተ** በፌደራልና በክልሎች በየደረጃው ባሉ ተቋማት የህዝብ ክንፍን የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ የተለዩ የህዝብ ክንፍ አካላትና ፈጻሚው በእቅድ ዝግጅትና ግምገማ እንዲሁም በሌሎች የልማት ስራዎች ላይ ሚናቸውን አውቀውና አምነው እንዲሣተፉ የሚያስችሉ የግንዛቤ መፍጠሪያና የአቅም ግንባታ መድረኮች ተካሂደዋል፡፡ የህዝብ ክንፉ አቅሙ የሚገነባበት፣ ተሣትፎው የሚጠናከርበትና ከመንግስት ተቋማት ጋር ቋሚ ንግኙነት የሚፈጥርበት አሰራር ተዘርግቷል፡፡ በተለይም ህዝባዊ መሠረት ያላቸውና አብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል የሚወክሉ የብዙኃንና የሙያ ማህበራት በቀበሌና በወረዳ ም/ቤቶች በመሣተፍ የአባሎቻቸውን መብትና ጥቅም የሚያስከብሩበትና በመልካም አስተዳደር፣ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በልማት ስራዎች በንቃት የሚሣተፉበት አሠራር ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ህዝቡ በምክር ቤቶች በበጀትና በስትራቴጂያዊ እቅድ ዝግጅት፣ በአፈጻጸም ግምገማ እና በሚቀረጹ የውይይት እና አጫጭር የሥልጠና አጀንዳዎች ላይ እንዲሣተፉ በመደረጉ ያለው ግንዛቤ፣ የውሣኔ አሰጣጥ አቅሙና እውቀቱ በገጠር ወረዳዎችና በከተማ አስተዳደሮች እየተገነባ መጥቷል፡፡

**ብሄራዊ መግባባት የመፍጠር አቅምን በተመለከተ** በየጊዜው እያደገ ይገኛል፡፡ በህገ-መንግስታዊ ስርዓት መርሆዎች፣ በፀረ-ድህነት ትግልና ፈጣን ልማት የማረጋገጥ ራዕይ አፈፃፀም፣ የዘላቂ ሰላም የማረጋገጥ ስራ፣ ብዝሃነትን የማክበር አቋም፣ የህዳሴ ጉዞ ጅምር ስኬትና ሀገራዊ ገፅታ እየተቀየረ መሆኑ፣ በትምህርት፣ በጤናና በመሰረተ ልማት መስፋፋት የተገኙ ውጤቶች ላይ ጥሩ የመግባባት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች የሚነሱ ችግሮችን ከመሰረታዊ የለውጥ አቅጣጫዎች ጋር በማገናዘብ ትክክለኛ አቋም የመያዝ ብቃት በሂደት በመገንባት ላይ ይገኛል፡፡

## 1.11 የባለ ብዙ ዘርፎች ዕቅድ አፈጻጸም

### 1.11.1 የሴቶች፣ የህፃናትና ወጣቶች ዘርፍ ልማት

#### 1. ዓላማና አቅጣጫዎች

ሴቶች በሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል፣ ህፃናት በሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ተጠቂ እንዳይሆኑ መብትና ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ፣ ወጣቶች በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ መልካም አስተዳደር፣ በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ልማት በተደራጀ አግባብ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ቀደም ብለው የተጀመሩ ውጤታማ ሥራዎችን አጠናክሮ የማስቀጠል አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡ የዕቅዱ ዓላማዎችም በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ

ዘርፍ በማህ የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥና ጎጂ ልማዳዊ ድርጅቶችን ማስወገድ፣ ህፃናት ከሀገሪቱ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፣ የሚደርስባቸውን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መቀነስ፣ መብትና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ማድረግ እና የወጣቶችን ብቃት በማሳደግ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና መልካም አስተዳደር ግንባር ቀደም ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ናቸው፡፡

## 2. የዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም

**የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አኳያ፡-** በዕቅዱ ዘመን ሰፋፊ የግንዛቤና የንቅናቄ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በመሆኑም 8.6 ሚሊዮን የሚሆኑ ሴቶች በግብርናና ከግብርና ስራ መስክ ውጭ ተደራጅተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ የሴቶችን የመሬት ተጠቃሚነት መብት ከማረጋገጥ አንጻር 11.11 ሚሊዮን (2 ሚሊዮን እማወራ እና 9.11 ሚሊዮን በጥምር ሴቶች የመሬት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አግኝተዋል፡፡ በግብርና ዘርፍ ተጠቃሚነት፣ የሀብት ባለቤትነት መረጋገጥ፣ የነፍስ ወከፍ ገቢ እያደገ መጥቷል፡፡እንዲሁም የሥራ ጫና ለመቀነስ 3.4 ሚሊየን ሴቶችን በአማራጭ ኢነርጂና በሌሎች የተለያዩ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በኢንዱስትሪ ዘርፍ የሴቶች ተሳትፎ እያደገ በመምጣቱ ስራ አጥነት እየቀነሰ፣ ገቢያቸው እያደገ መጥቷል፡፡ በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ዘርፍ በንግድ ሥራ አመራር 1.13 ሚሊዮን ፣ በየደረጃው በተካሄዱ የግንዛቤና ንቅናቄ ስራዎች 2.2 ሚሊዮን ሴቶች በጥቃቅንና አነስተኛ እና 1.8 ሚሊዮን በራስ አገዝ ማህበራት ተደራጅተው ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

ሴቶችን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግና ከሚያገኙት ገቢ የቁጠባ ባህል በማዳበር መቆጠብ እንዲችሉ በተሰሩ የተለያዩ የግንዛቤ ሥራዎችና ከአበዳሪ ድርጅቶች ጋር በተፈጠረው ቅንጅታዊ አሰራር 6.62 ሚሊዮን ሴቶችና 80,148 የሴት አደረጃጀቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በመሆን በአጠቃላይ ብር 2 ቢሊዮን ብድር በመውሰድ ስራ ላይ ያዋሉ ሲሆን የቁጠባ ባህልን እንዲያዳብሩ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ብር 2.82 ቢሊዮን መቆጠብ ችለዋል፡፡ በአጠቃላይ በጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ዘርፍ ከተፈጠረው የስራ ዕድል ከተመቻቸው የብድር አገልግሎት ከተሰጠው ሥልጠናና የገበያ ትስስር የሴቶች ድርሻ በቅደም ተከተል 41.47 በመቶ፣ 40.8 በመቶ፣ 39.7 በመቶና 36.1 በመቶ ደርሷል፡፡ እንዲሁም በቤቶች ልማት ፕሮግራም 50 በመቶ የሚሆኑ ሴቶች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

**ከማህበራዊ ዘርፍ አኳያ፡-** የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ በተመለከተ በአንደኛ ደረጃ 94 በመቶ፣ የሁለተኛ ደረጃ መጀመሪያ ሳይክል 47.3 በመቶ፣ በመሰናዶ 44 በመቶ፣ በቴክኒክና ሙያ 51.25 በመቶ፣ በቅድመ ምርቃ 32 በመቶ እና በድህረ ምርቃ 19 በመቶ ደርሷል፡፡ በጤና ዘርፍም የእናቶች ሞት ምጣኔ 420 /100000፣ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት 60 በመቶ፣ የቅደመ ወሊድ አገልግሎት ተጠቃሚ 98 በመቶ፣ በሰለጠነ ባለሙያ የወለዱ ሴቶች 41 በመቶ፣ የድህረ ወሊድ አገልግሎት 66 በመቶ ደርሷል፡፡ በአንጻሩ ከ5 ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ የህጻናት ሞት መጣኔ 68/1000 በማድረስ የምዕተ ዓመቱን ግብ ማሳካት ተችሏል፡፡ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና የሀይል ጥቃቶችን በተመለከተ የሴት ልጅ ግርዛት ከነበረበት 37.7 በመቶ ወደ 23 በመቶ፣ ጠለፋ ከ23.3 በመቶ ወደ 12.7 በመቶ፣ ያለዕድሜ ጋብቻ ከ21.4 በመቶ ወደ 8 በመቶ ቀንሰዋል፡፡

**የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ከማጎልበት አንጻር** በፌዴራል ደረጃ የሴቶችን የዉሳኔ ሰጪነት ሚና ለማሳደግ በፓርላማ 30 በመቶ፤ በህግ ተርጓሚ 23 በመቶና በአስፈፃሚ አካላት 23 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ በፓርላማ 27.8 በመቶ፣ በህግ ተርጓሚ 20.6 በመቶና በአስፈጻሚ አካላት የፖለቲካ አመራር 9.2 በመቶ ለማድረስ ተችሏል፡፡ የሴቶችን ማህበራት በማደራጀትና በማጠናከር ረገድ 3.94 ሚሊዮን ሴቶች በተለያዩ ነባር ማህበራት ውስጥ በአባልነት ከመደራጀታቸውም በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት 6.3 ሚሊዮን ሴቶች እንዲደራጁ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ 11.9 ሚሊዮን ሴቶችን በአባልነት ያቀፉ 477,369 የሴቶች ልማት ቡድኖች እና 2.2 ሚሊዮን (1ለ 5) የሴቶች ኔትዎርኮችን አደራጅቶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ በሁሉም የልማት ዘርፎች

የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማሳደግ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሴቶችን ጉዳይ በየፕሮግራሞቻቸው እንዲያካትቱና ተቋማዊ እንዲያደርጉ በታቀደዉ መሰረት ሁሉም ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሴቶችን ጉዳይ ያካተቱ እና 20 በመቶ የሚሆኑት ሴክተር መስሪያ ቤቶች ደግሞ ተቋማዊ ያደረጉ ናቸው፡፡

**የህጻናት ዘርፍ፡-** የህጻናትን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንጻር በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የኃይል ጥቃቶችን ለመከላከል 15.7 ሚሊየን የህብረተሰብ አባላትን ግንዛቤ ማሳደግ ተችሏል፡፡ 10,652 የህጻናት ምክር ቤቶችና ክበባት አደረጃጀቶች ተጠናክረዋል፡፡ 2.96 ሚሊዬን ህጻናት ስለመብታቸው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተደርጓል በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ህጻናት የሚሰጠውን ድጋፍና እንክብካቤ ከማሳደግ አኳያ በዕቅድ ዘመኑ 4.5 ሚሊየን ህጻናት በተለያዩ የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና 598,000 የህጻናት ቤተሰቦች በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡

**የወጣቶች ዘርፍ፡-** ወጣቶች የስራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ 4.89 ሚሊዮን ወጣቶች በጥቃቅንና አነስተኛ የገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች ተደራጅተው በተለያዩ የስራ መስኮች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡ በግብርና የሥራ መስኮች 2.21 ሚሊዮን እንዲሁም ከግብርና ውጭ በሆኑ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች 2.43 ሚሊዮን በመሰማራት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በዕቅዱ ዘመኑ በ553 ወረዳዎች 1684 የወጣት ማዕከላት በማስፋፋት በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት ነባሮችን ጨምሮ የማዕከላት ቁጥር 2284 ደርሶል፡፡ በነዚህ ማዕከላት 6.74 ሚሊዮን ወጣቶች የተለያዩ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በተለያዩ መስኮች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በ2002 አ.ም ከነበረበት 3 ሚሊዮን ወደ 12.2 ሚሊዮን ማድረስ ተችሏል፡፡ ወጣቶችን በሁሉም መስክ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል 17.2 ሚሊዮን ወጣቶች የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በዕቅድ ዘመኑ የ14.3 ሚሊዮን ወጣቶችን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ለመገንባት በተለያዩ ስልጠናዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና አግኝተዋል፡፡ ለ358,175 አመራሮች በተለያዩ ርዕሶች ላይ ስልጠና በመስጠት አቅማቸውን ማጎልበት ተችሏል:: 3.97 ሚሊዮን ወጣቶች በተለያዩ ነባር ማህበራት ውስጥ አባል የሆኑ ሲሆን በአሁኑ ወቅት 8.7 ሚሊዮን ወጣቶች እንዲደራጁ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

### 3. ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች

### ሀ. ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች

**በሴቶች ዘርፍ** የሥራ ጫና የሚያቃልል ቴክኖሎጂ ተደራሽ አለመሆን፣ እማወራ ሴቶች በተለያየ ምክንያት መሬታቸው መነጠቅ፣ የማምረቻና የመሸጫ ቦታ እጥረትና የገበያ ትስስር ከማመቻቸት አንጻር ሰፊ ችግር መኖሩ፣ የሴቶች በተለያዩ ዘረርፎች አቅም ማነስ መሰረተ ልማት በበቂ ሁኔታ ለሴቶች ተደራሽ አለመሆን፣ ለሴቶች ትምህርት የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን፣ የጤና አገልግሎት ተደራሽ አለመሆን፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሀይል ጥቃቶች አለመቀረፍና በማህበረሰቡ ዘንድ የተሟላ የአመለካከት ለውጥ አለመምጣቱ፣ የሴት አደረጃጀቶች ከጠባቂነት የጸዱ አለመሆን፣ የሴቶችን ጉዳይ ተቋማዊ በማድረግ በኩል የአመራር ቁርጠኝነት ማነስ፣ ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ሴቶችና ወጣቶች ህጻናት ተገቢውን ድጋፍ አለማግኘት፣ ባለፈው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የታዩ ችግሮች ሲሆኑ በቀጣዩ የዕቅድ ዘመን ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

**በሕጻናት ዘርፍ** ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የህጻናትን መብትና ደህንነት በማስጠበቅ ረገድ ያሉ ችግሮች፣ አለመቅረፍ፣ ህብረተሰቡ በሁሉም ዘርፍ ለሕጻናት ያለው አመለካከት የተዛባ መሆን የሀገር ውስጥ እና በውጭ ጉደፈቻ ዙሪያ የህብረተሰቡ የተዛባ አመለካከት መኖር ባለፈው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የታዩ ችግሮች ሲሆኑ በቀጣዩ የዕቅድ ዘመን ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

**በወጣቶች ዘርፍ** በወጣቶች ዘንድ የሚታየው የጠባቂነት አመለካከት፣ በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ውጭ መፍለስ፣ ዝቅተኛ የስራ ባህል፣ ሰርቶ ከመለወጥ ይልቅ በአቋራጭ የመበልጸግ ዝንባሌ፣ የስራ አጥነት ችግር

መኖር፣ የማምረቻና የመሸጫ ቦታ አቅርቦት ዕጥረት፣ የብድርና ቴክኖሎጂ አቅርቦት እጥረት፣ የገበያ ትስስር ችግሮች፣ የወጣት አደረጃጀቶች እስከ ታችኛው አስተዳደር እርከን የተሟላ አወቃቀር አለመኖራቸው፡፡ የወጣት ማዕከላት በቂ አለመሆንና ያሉትም ሥርጭት የተመጣጠነ አለመሆን ባለፉት አራት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት የታዩ ችግሮች ሲሆኑ በቀጣዩ የዕቅድ ዘመን ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

### 1.11.2 የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት

#### 1. ዓላማና አቅጣጫዎች

የኢኖቬሽን ሥርዓት ዝርጋታን በሚመለከት ተቋማዊ ማዕቀፍ መፍጠር፣ ፖሊሲዎችንና ህጎችን የማስደቅ፣ የቴክኖሎጂ ፍላጎት መለየት፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ምርምርና ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት የቴክኒክ ክህሎትና ሳይሳዊ ዕውቀትና ብቃት ያለው የሰው ኃይል ማፍራት እና የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃን በተመለከተ የፈጠራ ሥራዎች እንዲበረታቱ ጥቅም ላይ የሚውሉበትን መንገድ ማመቻቸት የሳይስና ቴክኖሎጂ ልማት የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን አቅጣጫዎች ሲሆኑ ምርታማነትን ለመጨመርና የምርት ጥራትን ለማሻሻል የሚያስችሉ የምርምር ተቋማትን ማደራጀትና የኢኖቬሽን ሥርዓትን መተግበር የዘርፉ ዓላማዎች ናቸው፡፡

#### 2. የዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም

**የኢኖቬሽን ሥርዓት አስተዳደር ዙሪያ** ባለፉት አራት ዓመታት ለሀገራችን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለማላመድና ለመጠቀም የሚደረጉ ጥረቶችን መምራት የሚያስችል የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲን ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ለህብረተሰቡ ስለፖሊሲው እና ስትራቴጂው የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ እንዲሁም በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በባዮቴክኖሎጂ ዘርፎች ግንኙነት የሚደረግባቸውን መስኮች በመለየት የተሻለ ልምድ ካላቸው ሀገራት የትብብር ስምምነት ተፈርሞ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

**የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ረገድ** የቴክኖሎጂ ሽግግሩን ለማቀላጠፍ የሚያስችል ደንብና የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ስልት በ2005 በጀት ዓመት በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቷል፡፡ ባለፉት አራት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት ለኢንዱስትሪዎች ግብአት የሚሆኑ 3529 እሴት አከል የቴክኖሎጂ መረጃዎችን በማደራጀትና በመተንተን ለሚመለከታቸው 3167 አካላት ተሰራጭቷል፡፡

**የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ** በሀገር አቀፍ ደረጃ ምርምርና ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የ70፡30 ቅበላ ቀጣይነት እንዲኖረው በማስቻል አተገባበርን ከልማት ፍላጎት ጋር ተጣጥሞ እንዲቀጥል ለማደረግ የፍላጎትና አቅርቦት ጥናት እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በቴክኖሎጂ ፈጠራ፣ ማላመድ እና ምርምር ሥራ የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ 673 የሂሳብና የሳይንስ ተማሪዎችና መምህራን፣ የቴ/ሙ/ት/ስ ሰልጣኞችና አሰልጣኞች፣ የፈጠራ ሰዎች እና ተመራማሪዎች የማበረታቻ ሽልማት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሙያ ማህበራትና የሳይንስ ክበባትን ለማጠናከር የሚደረገውን ድጋፍ አጠናክሮ ለመቀጠል እንዲያስችል ለ54 የሙያ ማህበራት፣ ለ39 የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተቋማትና የሳይንስ ክበባት ያቀረቡትን የፋናንስና የሥልጠና ድጋፍ በመገምገም እገዛ ተደርጓል፡፡

**የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታን በመቀነስ ረገድ** ከአቅም ግንባታ ድጋፎች መካከል በግብርና መስክ በተለይም የቆላ ዝንቦችን በማምከን ሀገራችን ከቆላ ዝንብና ከገንዲ በሽታ የፀዳች እንድትሆን ለማስቻል ይረዳ ዘንድ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታን ከ90-95 በመቶ ለመቀነስና ከዚህ ውስጥ 25,000 ስኴር ኪሎ ሜትር ከቆላ ዘንብና ገንዲ በሽታ ለማፅዳት በዕቅድ ተይዞ ባለፉት አራት የበጀት ዓመታት 115,700 ስኴር ኪሎ ሜትር ቦታ ለመሸፈን ተችሏል፡፡

**የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃና ልማትን በተመለከተ** የፈጠራ ባለቤትነት (የፓተንት) መረጃ ክምችትና ሥርጭትን ለማሳደግ የፓተንት መረጃዎች ክምችትን በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 30 ሚሊዮን ተይዞ ባለፉት አራት ዓመታት 23.5 ሚሊዮን የፓተንት መረጃዎችን የማሰባሰብ ሥራ ተሠርቷል፡፡ እንዲሁም በነዚህ ዓመታት 8.9 ሚሊዮን የፓተንት መረጃ ለማሠራጨት ግብ ተይዞ በአራቱ የዕቅድ ትግበራ ዓመታት ለተለያዩ አካላት 6.9 ሚሊዮን የፓተንት መጃዎች ተሠራጭቷል፡፡

**የጨረራ መከላከያና መቆጣጠሪያን በተመለከተ** ሀገራዊ የጨረራና ኑክሌር አደጋ ዝግጁነትና ምላሽ ሰጪ አካል ማቋቋሚያና የአሰራር መርሐ-ግብር ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም ከዓለም አቶሚክ ኢነርጂ ድርጅት ጋር በተደረገ ምክክር የጨረራና ኑክሌር ደህንነትና አካላዊ ጥበቃ ብሔራዊ መዋቅር ረቂቅ መርሐ-ግብር ተጠናቋል፡፡ የሬድዮ-አክቲቭ ዝቃጭ አስተዳደር ማከናወንና ዝቃጩን ማስወገድን በተመለከተ ባለፉት አራት የትግበራ ዓመታት ውስጥ በጤና፣ በኢንዱስትሪና በኮንስትራክሽን ዘርፍ የጨረራ አመንጪ ተጠቃሚ በሆኑ 1448 ተቋማት ላይ የምርመራ (የኢንስፔክሽን) ሥራ የተከናወነ ሲሆን የኢኒስፔክሽን ውጤቱን ባገናዘበ ትንተና መሠረት ለፈቃድ የተቀመጡ መስፈርቶችን ላሟሉ 1,061 ተቋማት ፈቃድ በመስጠት ጨረራው ጉዳት እንዳያደርስ ጥረት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የተመረጡ ምርቶች ላይ ክትትል በማድረግ በሬዲዮ አክቲቭ የተበከሉ ግብዓቶች በምርት ሂደት ውስጥ በመቀላቀል በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ የመከላከል ስራ ተሰርቷል፡፡

**የደረጃዎች ዝግጅትና ትግበራን በተመለከተ** ባለፉት አራት የትግበራ ዓመታት በተለያዩ መስኮች 5 ሺህ አዳዲስ ደረጃዎችን ለማዘጋጀትና 5 ሺህ ነባር ደረጃዎችን ለመከለስ ዕቅድ ተይዞ 4,924 ነባር እና 4,424 አዳዲስ በድምሩ 9,348 ደረጃዎችን ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

**የብሔራዊ ሥነ-ልክ ሥራዎች ረገድ** የመጀመሪያ ደረጃ ኢታኖሎች የወሰን ሽፋን በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 10 በመቶ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ወደ 75 በመቶ ከፍ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ በ2003 በጀት ዓመት 20 በመቶ፣ በ2004 በጀት ዓመት 30 በመቶ፣ በ2005 በጀት ዓመት ወደ 42.5 በመቶ እና በ2006 በጀት ዓመት ወደ 51.6 በመቶ ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የብሔራዊ አክሬዲቴሽን ሥራዎችን በተመለከተ ባለፉት አራት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዓመታት** ዘመን ብሔራዊና ዓለም አቀፍ የደረጃ መስፈርቶችን ላሟሉ 60 ተቋማት ዕውቅና ለመስጠት በተያዘው ዕቅድ መሠረት በ2005 በጀት ዓመት ለ6 እና በ2006 በጀት ዓመት ለ11 ላቦራቶሪዎች የአክሬዲቴሽን ዕውቅና መስጠት ተችሏል፡፡

**የተስማሚነት ምዘና ሥራዎች፡-** ባለፉት አራት የትግበራ ዓመታት ሰርተፊኬሽን፣ የላቦራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት በመስጠት የምርትና አገልግሎት ጥራትን የማረጋገጥ፣ የአገልግሎቱን ተደራሽነት የማስፋትና የማኔጅመንት ስርዓት ግንባታዎችን የማካሄድ ሥራዎች የተሠሩ ሲሆን አራት የቅርጫፍ ላቦራቶሪዎች በሀዋሳ፣ ደሴ፣ ድሬዳዋ እና ባህር ዳር ላይ ግንባታዎች ተጠናቀዋል፡፡

## 3. ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች

### ሀ. ፈታኝ ሁኔታዎች

የትምህርት ሥልጠና ሥርዓቱ በቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ መስክ ወሳኙን አቅም ለማጎልበት አቅጣጫ ተይዞ ፈርጀ ብዙ እንቅስቃሴ እየተደረገ ቢሆንም ጥራትና ብቃት ያለው ዕድገቱ በሚፈልገው ደረጃ እያቀረቡ አለመሆኑ፣ በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ የሚታዩ በቴክኖሎጂ ሽግግርና ምርምር እንዲሁም የምርምር ሥራዎችን ከኢንዱስትሪና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በቁርኝት ያለመሥራት ክፍቶች ከመታየታቸውም በላይ የምርምር ውጤቶችን ወደ መሬት በማውረድ ተግባራዊ በማድረግ ላይ የሚታዩ ክፍተቶች፣ በግብርና ምርምር ረገድ የተሻለ ሥራ እየተሠራ ቢሆንም የምርምር ሥርዓቱ አጋራዊ ፍላጎት

ላይ የተኮረና ችግር ፈቺ ምርምር በማድረግ በኩል ሰፊ እጥረት መኖሩና የግብርና ዕድገታችንን የሚመጥን ድጋፍ እያደረገ አለመሆኑ፣ በጤናው ዘርፍ የሚታዩ ተወዳዳሪ ያልሆነ የጤና ምርምር፣ ብቁ የምርምር መሠረተ ልማቶች ዕጥረት መኖርና የተመራማሪዎች በቁጥርም ሆነ በብቃት ዝቅተኛ መሆን የታዩ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

## 1.11.3 የስፖርት ዘርፍ ዕቅድ አፈጻጸም

### 1. ዓላማና አቅጣጫዎች

በባህላዊና ዘመናዊ ስፖርት ህብረተሰቡ በሁሉም የመዝናኛ ዓይነቶች አቅሙ በፈቀደ መጠን እንደፍላጎቱ የሚያደርገውን ተሳትፎ ማጎልበትና ከአጠቃላይ ህብረተሰቡ የስፖርት እንቅስቃሴ በመነሳት በተለይ የወጣቱን ግንዛቤና ተሳትፎ በማጠናከር የላቀ ችሎታ ያላቸውን ምርጥ ስፖርተኞች በማፍራት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ውጤት ለማስመዝገብ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እና የስፖርት ዘርፉን የማስፈፀም አቅምን በመገንባት መላውን ህበረተሰብ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚያደርግ ስፖርት ማስፋፋት የዕቅዱ አቅጣጫዎችና ዓላማዎች ናቸው፡፡

### 2. የዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም

**ማህበራት አደረጃጀትንና ድጋፍን በተመለከተ፡-** አደረጃጀትን በተመለከተ 61,934 የሚሆኑ የስፖርት ማህበራትን፤ ክለቦችን ቡድኖችን፣ መዝናኛ ኮሚቴዎችን የማህበረሰብ ኮሚቴዎችና የስፖርት ም/ቤቶችን ለማደራጀትና ለማጠናከር ግብ ተይዞ ክንውኑ 74,304 ወይም 119 በመቶ ሊደርስ ችሏል፡፡ በአራት አመት ጊዜ ውስጥ ለ57,826 የስፖርት ማህበራት፣ የስፖርት አሶሴሽኖች፣ ክለቦች፣ የማህበረሰብ ስፖርት ኮሚቴዎችና ቡድኖች ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ክንውኑ 47,249 ወይም 82 በመቶ ደርሷል ፣በፌደራል ደረጃ 20 ፌዴሬሽኖች፣ 7 አሶሴሽኖች 2 ኮሚቴዎች ተደራጅተው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡ አደረጃጀትን በተመለከተ በየደረጃው የሚዋቀሩ የስፖርት ምክር ቤቶች፣ በየደረጃው የሚቋቋሙ የስፖርት ፌዴሬሽኖች በተለያዩ የስራ ዘርፎች የተሰማሩ ታዋቂ የስፖርት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች ስፖርቱን ህዝባዊ መሠረት ለማስያዝ የበኩላቸውን እንቅስቃሴ እያበረከቱ ያሉ ናቸው፡፡

ድጋፍን በተመለከተ በፌደራል ስፖርት ኮሚሽን በኩል ለሀገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት የ104 ቋሚ ሠራተኞች የደመወዝ ወጪ፣28,070,000 ለስራ ማስኬጃ የስፖርት ትጥቆችና ቁሳቁሶች የቀረጥ ክፍያ 70,909,469 ለአለማቀፍ ውድድር 37,449,164 በድምሩ 136,428,633 ብር ድጋፍ አድርጓል፡፡ በተመሳሳይ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ስፖርት ኮሚሽኖች በየደረጃው ላሉ የስፖርት አደረጃጀቶች 48,307,231 ብር ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ስፖርቱን ቀስ በቀስ ከመንግስት ድጎማ ለማላቀቅ በታሰበዉ መሠረት ከተለያዩ የማህበረሰብ አካላት ብር 293,134,969 ከስፖርት ማህበራት ብር 166,291,924 በድምሩ ብር 459,426,891 ማሰባሰብ ተችሏል፡፡

ከቀበሌ እስከ ፌዴራል በህዝባዊ አካላትና በግል ባለሀብቶች ተሣትፎ ከ2003-2006 በድምሩ 16,055 ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ለመገንባት ታቅዶ አፈፃፀሙ 13,943 (87%) ላይ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ በኦሮሚያ 40ሺህ ሰው የመያዝ አቅም ያላቸው ስታዲየሞች ከ300-700 ሚሊዮን ብር የሚገመት የካፒታል ኢንቨስትመንት ተመድቦ እየተሰራ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የአፈፃፀም ደረጃቸው ከ41-91 በመቶ ደርሷል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ከ300 ሚሊዮን ብር በላይ በመመደብ 4 ዞናል ስታዲየሞች በመገንባት ላይ የሚገኙ ሲሆኑ በቤንሻንጉል ጉሙዝ በ40 ሚሊዮን ብር ግንባታ ተጀምሯል፡፡ በአማራ ክልል የወልዲያ ስታዲየምም በግል ባለሀብትና በአካባቢው ህብረተሰብ ተሣትፎ 30 ሺህ ሰው የሚይዝ ስታዲየም ግንባታ 70 በመቶ ላይ ይገኛል፡፡

**የስፖርት ፋሲሊቲዎችን ማስፋፋትን በተመለከተ፡-** በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በ2002 በጀት ዓመት ከነበሩት 7 የስልጠና ማዕከላት ተጨማሪ 15 በመገንባት በ2007 በጀት ዓመት መጨረሻ 22 እንደሚደርስ ታስቧል፡፡ በዚሁ መሠረት ባለፉት አራት ዓመታት አፈፃፀም በፌዴራል ደረጃ የሚገነባው አንድ ማዕከል ግብ አፈፃፀምን በሚመለከት በ2004 በጀት አመት መጨረሻ በ224 ሚሊዮን ብር ካፒታል ኢንቨስትመንት በአሰላ ከተማ የተጀመረዉ የግንባታው አፈፃፀም 60.5 በመቶ ላይ ደርሷል፡፡ በሌላ በኩል ለዚሁ ማዕከል በብር 23 ሚሊዮን ብር የአጥር ግንባታ ተጀምሮ አፈፃፀሙ 57 በመቶ ላይ ይገኛል፡፡ በስፖርት ኢንቨስትመንት የባለሀብቶችን ተሳትፎ ማሳደግን በተመለከተ በዘርፉ ለሚሰማሩ አካላት በአራት አመት ውስጥ 76 ባለሀብቶችን ፈቃድ ሰጥቶ ወደ ዘርፉ ለማስማራት ታቅዶ ክንውኑ በፌደራል ደረጃ 88 ባለሀብቶች በክልል ደረጃ 31 በድምሩ 119 (156 በመቶ) ሊሆን ችሏል፡፡ እነዚሁ ባለሀብቶች በድምሩ 234,192,321 ብር የሚሆን ካፒታል አስመዝግበዋል፡፡ ፌስቲቫሎችን በማዘጋጀት የህብረተሰቡን ተሣትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግን በተመለከተ፤ ባለፉት አራት ዓመታት በፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን፣ በሀገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት፣ በታዋቂ ስፖርት ድርጅቶች፣ ከቀበሌ እስከ ክልልና ከተማ አስተዳደሮች የሚካሄዱ ውድድሮችና ፌስቲቫሎችን ልዩ ልዩ የተሣትፎ መድረኮችን ጨምሮ 193,118,189 የሚሆን የህብረተሰብ ክፍል ለማሳተፍና ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ክንውኑ 186,862,436 አፈፃፀሙ ደግሞ 96.8 በመቶ ሊሆን ችሏል፡፡ ውጤት ካስመዘገብንባቸው ስፖርቶች መካከል አትሌቲክስ፣ እግር ኳስ፣ ብስክሌት፣ ጅምናስቲክ፣ ቮሊቮል /በክለብ/፣ ወርልድ ቴኳንዶ፣ውሃ ዋና፣ ፓራሎምፒክ፣ ጠረጴዛ ቴኒስ፣ ቼዝ፣ ውሹ፣ ኢንተርናሽናል ቴኳንዶ ይጠቀሳሉ፡፡

የስፖርት ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞችን በማስፋፋት ረገድ የሴክተሩን የመፈጸም አቅም መገንባት እንዲቻል በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ባለሙያዎችን ማሰልጠን፣ በሌላ በኩልምርጥ ስፖርተኞችን በማፍራት በአለም አቀፍ የስፖርት መድረኮች የሀገራችንን ውጤታማነት ማረጋገጥ ከትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

**የታዳጊ ወጣቶችን ሥልጠና በተመለከተ፡-** የታዳጊ ወጣቶች ሥልጠና ፕሮጀክት ትግበራን በተመለከተ ከ2004 በጀት አመት ጀምሮ ከፌዴራል እስከ ወረዳ ባለው የአስተዳደር እርከን በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ የመደበኛ ት/ቤቶች በ13 የስፖርት አይነቶች በ972 የሥልጠና ጣቢያዎች በሁሉቱም ፆታዎች በሀ-13፣ በሀ-15 እና በሀ-17 ወንድ 10,000 ሴት 10,000 በድምሩ 20,000 የሚሆኑ ታዳጊዎችን መልምሎ በማሰልጠን ላይ ያተኮረ ነዉ፡፡ በመሆኑም በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በ916 የሥልጠና ጣቢያዎች ወንድ 10,887 ሴት 10,870 በድምሩ 21,757 ታዳጊዎችን ማሰልጠን የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ ከጣቢያ ብዛት አንጻር 94.2 በመቶ ከተሳታፊ ብዛት አንጻር ወንድ 108 በመቶ ሴት 108 በመቶ መሆኑን ያሳያል፡፡ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በራሳቸው ወጪ የሚያሰለጥኗቸውን ሲጨምር ቁጥሩ ከ38 ሺህ በላይ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የሚሰለጥኑትን ታዳጊዎች ብዛት ስንመለከት ትግራይ 2950፣ አማራ 3250፣ አፋር 970፣ ኦሮሚያ 2815፣ ቤንሻንጉል ጉምዝ 1165፣ ሀረሪ 1320፣ ደቡብ 2545፣ ጋምቤላ 1435፣ ሶማሌ 1100፣ ድሬዳዋ 1560 እና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 2673 የሚሆነውን ይሸፍናሉ፡፡ በሌላ በኩል በማሰልጠኛ ማእከላት 519 ታዳጊ ወጣቶች፣ በክለቦች በብሄራዊ ቡድን 4980 በድምሩ 5499 ኤሊት ስፖርተኞች ስልጠና እየተከታተሉ ይገኛል፡፡

በባለሙያዎች ሥልጠናን ረገድ፡- ባለፉት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት እንደ ሴክተር የሚስተዋለውን የሰለጠነ የሰው ሀይል እጥረት ለመቅረፍ በአጫጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ የስልጠና ፕሮግራሞች አሰልጣኞችን፣ ዳኞችን፣ ኢንስትራክተሮችን የስፖርት ሳይንስ እና በስፖርት አስተዳደር 16,000 ባለሙያዎችን ለማሰልጠን ታቅዶ ክንውኑ 16,825 ሲሆን አፈጻጸሙ ደግሞ 105 በመቶ ሆኗል፡፡ የረጅም ጊዜ ስልጠና አፈጻጸም በዝርዝር ሲታይ በዲፕሎማ 32 በስፖርት ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪ 9,453 በሁለተኛ ዲግሪ 404 ባለሙያዎች እንዲሁም በስፖርት አስተዳደር በመጀመሪያ ዲግሪ 225 በድምሩ 10,114 ባለሙያዎች ስልጠና እየተከታተሉ ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል በአጭር ጊዜ በ1ኛ እና በ2ኛ ደረጃ አሰልጣኝነትና ዳኝነት እንዲሁም በኢንስትራክተርነት ሥልጠና ለ6711 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰቷቸዋል፡፡ የስፖርት ህክምና፣ ፊዚዮቴራፒ፣

ሪሀብሊቲሽንና የዶፒንግ አገልግሎትን መስጠትን በተመለከተ 10,902 ግለሰቦች አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ክንውኑ 16,419 ሆኗል፡፡ አፈጻጸሙም ከ100 በመቶ በላይ ሊሆን ችሏል፡፡ በተጨማሪም 156 የጥናትና ምርምር ሥራዎች ለማከናወን ታቅዶ ክንውኑ 148 ሲሆን 94.9 በመቶ ደርሷል፡፡

የባለብዙ ዘርፍ ተግባራት በዋነኛነት የሴቶችን ተሳትፎ ከአጠቃላይ የህብረተሰብ ተሳትፎ ከ35 በመቶ በላይ ሽፋን ያለው ሲሆን በወድድር ስፖርቶች ደግሞ እስከ 45 በመቶ ደርሷል፡፡ በታዳጊ ወጣቶች ሥልጠና ፕሮጀክት የሴቶች ተሳትፎ 49 በመቶ በላይ የሚሆነውን ይዟል፡፡ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ሥርዓት በመዘርጋት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱን ለማሳካት የሚያስችል የኮሚዩኒኬሽን ስትራቴጂ ተቀርጾ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

### 3. *ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች*

### *ሀ. ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች*

ባለፉት አራት ዓመታት በስፖርት ዘርፍ ካጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች መካከል በሁሉም ዘርፍ የሚታዩ የአመለካከትና የክህሎት ክፍተቶች፣ የታዳጊ ክልሎች የማስፈጸም አቅም ውስንነት፣ የበጎ ፈቃድ አገልጋይነት ስሜት ያለማደግና ክለቦች በዘመናዊ መንገድ ያልተደራጁ እና ያልተጠናከሩ መሆኑ፣ አርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ፣ በገጠር ያሉ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ጋር በመድረስ በኩል ክፍተቶች መኖራቸው፣ ባለሀብቶች በስፖርት ትጥቆች፣ በስፖርት መሳሪያዎች ማምረት እና በመሰረተ ልማት ግንባታ ያላቸው ተሳትፎ አነስተኛ መሆኑ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 1.11.4 የማህበራዊ ደህንነትና የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዘርፍ ዕቅድ አፈጻጸም

### 1. ዓላማና አቅጣጫዎች

የማህበራዊ ደህንነት ዋንኛ የትኩረት አቅጣጫ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን በአገሪቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፎች ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል እኩል ተጠቃሚና ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲሁም የዜጎች የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት ሽፋንን ማሳደግ ነው፡፡

### 2. የዋና ዋና ግቦች አፈፃጸም

አካል ጉዳተኞች የአካላዊ ተሃድሶ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሶስት ማዕከላት በአዲስ መልክ ተቋቁመዋል ሰባት ነባር ማዕከላት ደግሞ በቁሳቁስና በጥሬ ዕቃዎች ተጠናክረው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ ለ245637 ዜጎች የአካላዊ ተሃድሶ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ208634 /84 በመቶ/ አካል ጉዳተኞች የተሃድሶ አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ የዘርፉን ሥራ ለማቀላጠፍ የሚያስችል ሥርዓት ከመዘርጋት አንፃር የአካላዊ ተሃድሶ አገልግሎት እና የአረጋውያን አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ እና ብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አስተግባሪ ኮሚቴ መመሪያ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ ተዘጋጅቶ በመንግሥት ፀድቋል፡፡ ነባሩም የአረጋውያን የድርጊት መርሃ ግብር ተከልሷል፡፡

ለመንግሥት ሠራተኞች ይሰጥ ከነበረው የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት በተጨማሪ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች በአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ለ1,530,606 ዜጎች የማኅበራዊ ደህንነት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ታቅዶ ለ1,617,820 የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ የማህበራዊ ችግሮችን ለመከላከል የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫና ሥልጠና ለ3,152,165 ዜጎች ለመስጠት ታቅዶ ለ20,527,658 ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ የተያዙትን ግቦች ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ቢሆንም የአካል

ጉዳተኞችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የማህበራዊ ዋስትናን ለዜጎች የማዳረስ ሽፋንና ተደራሽነት አልተረጋገጠም፡፡ ለዚህም በቀጣይ የሚመለከታቸው አካላት ርብርብ በማድረግ መፍትሄ ማምጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

**የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዘርፍ፡-** የዚህ ዘርፍ ዋንኛ የትኩረት አቅጣጫ የአገሪቱን የሰው ኃይል ሀብት ፍላጎትና አቅርቦት ለማጣጣም የሚያስችል የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት መዘርጋት፣ የሥራ ስምሪት አገልግሎትን ማስፋፋት፣ የሥራ ሁኔታዎች ቁጥጥር አገልግሎትን ማሳደግ እና የማህበራዊ ምክክር አገልግሎትን ማስፋፋት ነው፡፡ የአገሪቱን የሰው ኃይል ሀብት ፍላጎትና አቅርቦት ለማጣጣም የሚያስችል የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት ለመዘርጋት በታቀደው መሠረት የአገሪቱ የሥራ ገበያ ሁኔታ ዳሰሳ ጥናት ተካሂዶ በዘጠኝ /129 በመቶ/ ቁልፍ የሥራ ገበያ አመልካቾች ላይ መረጃዎች ተሰብስበው፣ (Labour Market Dynamics in Ethiopia: Analysis of nine Key Indicators of Labour Market) ጥናታዊ ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ በሲቪል ሰርቪስ ከሚተዳደሩ መ/ቤቶች፣ ከግል ድርጅቶችና ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች በጠቅላላው የ4,773,912 የሰው ኃይል መረጃዎች ተደራጅተው ተሰራጭተዋል፡፡ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች 4,820,227 ሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ ተካሂዶ ለ1,385,698 ሥራ ፈላጊዎች የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል፤ 1,174,301 ክፍት የሥራ ቦታዎችን በመመዝገብ ሥራና ሠራተኛን ማገናኘት ተችሏል፡፡ ለዜጎች የሥራ ስምሪት አገልግሎት ለመስጠት በታቀደው መሠረት ለ3,883,072 ሥራ ፈላጊዎች በሀገር ውስጥ፣ 447,626 ኢትዮጵያውያን በውጪ አገር ለሥራ እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል 142,450 የውጪ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ አግኝተው በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ ተሰማርተዋል፡፡

በዕቅድ ዘመኑ በ132,455 ድርጅቶች ውስጥ መሠረታዊ የሥራ ሁኔታዎች መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ በ125,159 ድርጅቶች ላይ ቁጥጥር የማድረግ፣ በ4,515 ድርጅቶች ጥምር የሙያ ደህንነትና ጤንነት ኮሚቴዎች የማቋቋም፣ በ5,523 ድርጅቶች የሚገኙ ጥምር ኮሚቴዎችን የማጠናከር ሥራ በመሥራት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ተችሏል፡፡ የሥራ ላይ አደጋ መረጃን በተመለከተ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ7,029 ድርጅቶች መረጃ ተሰብስቦ በ12,677 ሠራተኞች ላይ የሥራ ላይ አደጋ፣ በ207 ሠራተኞች ላይ የሞት አደጋ መከሰቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመግታት 16,642,045 የሕብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ 94,723 ሠራተኞች የታቀፉበት 1,214 አዲስ የሠራተኛ ማህበራት ተመዝግበዋል፡፡ የ658 የሠራተኛ ማህበራት አመራር ለውጦች፣ የ380 መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያዎችና 804 አዲስ እና ነባር ስምምነቶች ተመዝግበዋል፡፡ በ1834 ድርጅቶች የሁለትዮሽ ምክክር ሥርዓት ለመዘርጋትና በ7 ክልሎች የሦስትዮሽ ምክክር ሥርዓት ለመዘርጋት በተያዘው ዕቅድ መሠት በ3,867 ድርጅቶች በአሠሪ እና ሠራተኞች መካከል የሁለትዮሽ ምክክር ሥርዓት ተመስርቷል፡፡

## 1.11.5 ባህልና ቱሪዝም አፈጻጸም

### 1. ዓላማና አቅጣጫዎች

በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የባህልና ቱሪዝም ዘርፍ የብዝሀ ባህል፣ የቅርስና የተፈጥሮ መስህቦች ቀጣይነት ባለው መልኩ በመጠበቅና በማልማት፣ እንደዚሁም የሕዝቦችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት በማጎልበት የባህልና ቱሪዝም ዘርፉ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት እና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት ተገቢውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ማስቻል ነው፡፡ ይህን ለማስፈፀም የተቀመጡ አቅጣጫዎችን፣ ግቦችና የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችን መሠረት በማድረግ ወደ ትግበራ ተግብቷል፡፡

## 2. የዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም

የባህል ልማት ዘርፍ የቋንቋዎችን ልማት ለማሳደግ እንዲረዳ የባህል ፖሊሲ ክለሳ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሰረት አስፈላጊው ግብዓት ከሚመለከታቸው አካላት ከተሰበሰበ በኋላ ፖሊሲው ተከልሶ እንዲጸድቅ ለመንግስት ቀርቧል፡፡ በሀገራችን የሚነገሩ የ5 ቋንቋዎችን ፕሮፋይል ለማዘጋጀት በታቀደው መሰረት የሴምና የናይሎ ሳህራ የቋንቋ ፕሮፋይሎች የተዘጋጁ ሲሆን እንደ አጠቃላይ የቋንቋ ፕሮፋይል ለማዘጋጀት ከፌደሬሽን ምክር ቤትና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ቋንቋዎች አካዳሚ) ጋር የሶስትዮሽ ስምምነት ተፈርሞ ዝግጅት ተጀምሯል፡፡ በመጥፋት ላይ ያሉ ቋንቋዎች ሥነ-ልሳናዊ ጥናት ማካሄድ፣ በሥነ-ልሳን ሳይንስ መሰረት ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የባለድርሻ አካላትን በማስተባበር እና በመምራት በ54 ቋንቋዎች ላይ የተሟላ ጥናትና ምርምር እንዲኖር ሲያስችል በ17 ቋንቋዎች ከፊልጥናቶች እንዲሁም በ 8 ቋንቋዎች ጅምር ጥናቶች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡ እንዲሁም የ7 ቋንቋዎችን የአገልግሎት ደረጃን ለማሳደግ በታቀደው መሰረት የሥርዓተ ጽህፈት ቀረጻ በትግራይ ክልል ለሚገኙ ሁለት ቋንቋዎች/ኩናማ እና ኢሮብ /፣ በአማራ ክልል ለሚገኙ ሶስት ቋንቋዎች (አዊንጊ፣ ህምጣንጋ፣ አርጎባ)፣ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል አምስት እና በደቡብ/ብ/ብ/ህ ክልል ቤንች ማጂ ዞን ስድስት፣ በጋምቤላ ክልል ለሚገኙ ቋንቋዎች በአለ ቋንቋ ውሳኔ እና በፀማኮ ሥነ-ድምጽ ጥናት እንዲሁም በጓማ ሥርዓተ ጽሕፈት ዝግጅት ላይ በሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ድጋፍ ፣ ለሀረሪ ቋንቋ በክልሉ ባህል ቅርስ ቱሪዝም ቢሮ አማካኝነትና በሌሎች አካባቢዎችም በየብሔረሰቡ ምሁራን በተለያዩ መስተዳድር እርከኖች ለማከናወን ተችሏል፡፡

የብሄር ብሄረሶችን ባህላዊ እሴቶችን በጥናት ለይቶ ለመሰነድ በተደረገው ጥረት የ5 ብሄር ብሄረሰቦች ባህላዊ እሴቶች ተጠንተው በመጽሀፍ መልክ ታትመው ተሰራጭተዋል፡፡ በመሆኑም እስካሁን የ73 ብሄሮችና ብሄረሶችን የባህል እሴቶች ተጠንተው ተሰንደዋል፡፡ የቅርስ ሀብቶቻችንን በዓለምአቀፍ ደረጃ በማስመዝገብ ረገድ እስከአሁን ካስመዘገብናቸው 9 ግዙፍነት ያላቸው የዓለም ቅርሶችና 12 የፅሁፍ ቅርሶቻችን በተጨማሪ በዕቅድ ዘመኑ 7 ቅርሶችን በዓለም አቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ ታቅዶ የኮንሶ ባህላዊ መልክዓ ምድር እና የመስቀል ደመራ በዓል በዓለም ወካይ ቅርስነት እንዲመዘገቡ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የድሬ ሼህ ሁሴን መካነ ቅርስ፣ ሶፍ ኡመር ዋሻ፣ የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣ የመልካ ቁንጡሬ አርኪዮሎጂ ስፍራ እና የጌዲዮ ባህላዊና የተፈጥሮ መልክዓ ምድር በአለምአቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ በዩኔስኮ ጊዜያዊ መዝገብ እንዲካተቱ ተደረገዋል፡፡ በሀገርአቀፍ ደረጃ 9 የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች ምዝገባ ለማከናወን ታቅዶ የ323 ቋሚ ቅርሶች ተመዝግበዋል፣ 1202 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ለማስመዝገብ ታቅዶ 6863 ተመዝግበዋል፣

በአገር አቀፍና በዘርፉ ያሉ የታተሙና ያልታተሙ ጽሁፎች፣ መዛግብት፣ የጥናትና ምርምር ሥራዎች፣ ቀረጸ-ድምጽ፣ ቀረጸ-ምስል እና ድምጽ፣ ጥንታዊ ጽሁፎች፣ የተመዘገቡ የጽሁፍ ሀብቶች ለመጠበቅ የተለያዩ የመረጃ ሃብቶችን በማሰባሰብ ክምችቱን 300,000 ለማድረስ ታቅዶ 704,371 ማድረስ ተችሏል፤ ለ35095 የመረጃ ሀብቶች ጥበቃና እንክብካቤ በማድረግ ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ ለ85,221 የመረጃ ሀብቶች ጥበቃና እንክብካቤ ተደርጓል፡፡ 70 ትውፊታዊ ትውን ጥበባት በተለያዩ መድረኮች ለህዝብ ዕይታ ለማቅረብ ታቅዶ 110 ተከናውኗል፣ 15 የቴአትርና የሙዚቃ ዝግጅቶች ለህዝብ ለማቅረብ ታቅዶ 249 ቀርቧል፤ ሴቶችንና ወጣቶችን ያሳተፍ የኪነ ጥበባት ስልጠና ለሙያተኞችን ሥልጠናዉን ለመስጠት ተችሏል፡፡ የወጣቱን ልማታዊ አስተሳሰብ በመሸርሸር ስንፍናንና ሱስን የሚያዛምቱ አሉታዊና መጤ የሆኑ ልማዳዊ ድርጊቶችንና አመለካከቶችን የመከላከል ተግባር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በአገራችን አሉታዊ መጤና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ የተከናወነ ሲሆን አሉታዊ መጤና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል የሚያስችል አገራዊ ስትራቴጂ እንዲዘጋጅ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረትም መነሻ አገራዊ ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፤ በዚህ መሰረት ችግሩን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመከላከል እንዲቻል አስቀድሞ የችግሩን ስፋትና ጥልቀት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመለየት በ20 የሀገሪቷ ከተሞች ላይ መረጃው በማሰባሰብ የማጠናቀር ሥራ ተከናውኗል፡፡

የቱሪዝም ልማታችንን ለማሳደግ በቀየስናቸው ግቦቻችንም ዙሪያ ከፍተኛ ርብርብ አድርገናል፡፡ በዚህ ረገድ በቀዳሚነት የሚነሳው በዘርፉ ለረጅም ዘመናት ሲጠበቅ የነበረው ሀገር አቀፍ የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ካውንስል፣ የቱሪዝም ቦርድና የቱሪዝም ድርጅት መቋቋምና ወደ ሥራ ማስገባት ነው፡፡ የሀገር ውስጥና የውጪ ቱሪስቶችን ወደ መስህብ ቦታዎቻችን እንዲጎዙ ለማድረግ ሰፊ የማስተዋወቅና ገበያ የማፈላለግ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ ቱሪስት አመንጪ በሆኑ የአውሮፓ፣ እስያ፣ ላቲን አሜሪካና ሰሜን አሜሪካ ሀገራት ላይ በተዘጋጁ የቱሪዝም አለምአቀፍ ገበያ ንግድ ትርኢት ላይ ክልሎችንና አስጎብኚ ድርጅቶችን ባሳተፈ መንገድ ተንቀሳቅሰን እቅዳችንን አሳክተናል፡፡ በሌላ መንገድ የታወቁ የውጪ የጉዞ ፀሃፊዎች፣ አስጎብኚ ድርጅቶችና አለምአቀፍ ጋዜጠኞችን በመጋበዝ የሀገራችንን መስህቦች ጎብኝተው እንዲፅፉና እንዲያስተዋውቁ በታቀደው መሰረት ተከናውኗል፡፡ የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማሳደግም በክልልና በፌደራል ደረጃ ሳምንታዊ የሬዲዮና የቴሊቪዥን ፕግራሞች ተቀርፀው አመቱን በሙሉ በክልሎችና በፌዴራል መገናኛ ብዙሓን ተሰራጭተዋል፡፡ በርካታ ዜናዎችና ልዩ ዘገባዎችም ተስተናገደዋል፡፡ በመሆኑም ከመቼውም ጊዜ በተሻለ የተግባቦትና የማስተዋወቅ ስራ ተከናውኗል፡፡በዚህም የሀገር ውስጥ ቱሪዝም መነቃቃት ጀምሯል፡፡

የተፈጥሮ ቅርሶቻችንና መስህብ ሀብቶቻችንን በመጠበቅና በማልማት ረገድ በፌዴራል ደረጃ 13 ፓርኮችና 2 መጠለያዎችን ፣ በክልሎች ደረጃ 14 ፓርኮችና የማህበረሰብ ጥብቅ ቦታዎችን ፣ በማጠናከር ለአደንና ቱሪዝምን ለጉብኝት ምቹ የማድረግ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ ሕገ ወጥ የዱር እንስሳት ዝውውርን ፣ ሰፈራና አደንን ለመከላከል በተወሰደው እርምጃ በርካታ ሕገ ወጦች ለሕግ ቀርበው የጥፋተኝነት ውሳኔ አግኝተዋል፡፡ በመሆኑም 60 በመቶ ፓርኮች ደህንነታቸውና በተሻለ ሁኔታ ተጠብቀዋል ፡፡ ይሁን እንጂ የሁለት ክልሎች አዋሳኝ በሆኑ ፓርኮች ዙሪያ የሕገ ወጥነት ተግባራት ሙሉ በሙሉ ሊቀረፉ ባለመቻላቸው የጥፋት ድርጊቱ እንደቀጠለ ይገኛል ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኝ የአመራሩን ትኩረትና ውሳኔ የሚሻ ሆኖ ቀጥሏል፡፡

የቱሪስት አገልግሎት አሰጣጣችንን ለማሻሻል የመስተንግዶ ተቋማትን ብቃት የማረጋገጥና የሱፐርቪዥን ሥራዎች ለማድረግ በታቀደው መሰረት የብቃት ማረጋገጥና የሱፐርቪዥን ሥራዎች ተካሂደው የአገልግሎት አሰጣጣቸውን መሻሻል ታይቶባቸዋል፡፡ በዘርፉ የተሰማሩ ሥልጠና ያላገኙ ሰራተኞችንና ሥራ አስኪያጆችን በአጫጭር ሥልጠና ለመደገፍ ታስቦ 8390 የሰው ሃይል ሥልጠና አግኝተዋል፡፡ በአጠቃላይ በዘርፉ በመካከለኛ የሰለጠነ የሰው ሀይል ፍላጎትን ለማርካት ከትምህርት ሚኒስቴርና ከህዝብ ጋር በመተባበር 83 የሙያ ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፣ 40 የመመዘኛ መሳሪያዎች ተዘጋጅተው ወደ ማስልጠኛ ተቋማት እንዲላክ ተደርጓል፡፡ የዘርፉ የአገልግሎት ተቋማት ዓይነትና መጠን ለማሳደግ መንግስት በሚሰጠው ድጋፍና ማበረታቻ የግል ባለሀብቱ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት በማከናወን ላይ መሆኑ ተደራሽነቱ እንዲሰፋ አድርጎታል፡፡ በነዚህና በመላ ሀገራችን በሰፈነው ሰላምና መረጋጋት፤ በፈጣን ደረጃ በማደግ ላይ ያለው የመሰረተ ልማት ግንባታ፤ በላቀ የአየርና የየብስ አገልግሎት ዕድገት ተደማምሮ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 724 ሺ በገቢ ደግሞ ወደ ሁለት ቢሊዮን ዶላር አድጓል፡፡ የባህልና የቱሪዝም ዘርፍ ሰፊ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ኢንደስትሪ እንደመሆኑ ይህንን ታሳቢ በማድረግ ከጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ማስፋፊያ ኤጀንሲና ከቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ጋር በመተባበር የሥልጠና የገበያ ትስስር በመፍጠር ለ213,760 ዜጎች በልዩ ልዩ የሥራ መስኮች የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸው ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

## 3. ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች

### ሀ. ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች

ባለፉት አራት ዓመታት ካጋጠሙ የዘርፉ ተግዳሮቶች መካከል የማስፈፀም አቅም ውስንነት፣ የባህል ጉዳይ በየደረጃው በሚገኙ አመራር አካላትና ፈጻሚዎች ዘንድ በቂ ትኩረት ያለማግኘት፣ መንግሥታዊ አስፈጻሚ አካላት እና የግል ዘርፉ ትስስር የጠነከረ አለመሆን፣ ቅርሶቻችን በቁጥር አለመለየታቸውና የተለዩትም

ተገቢው ጥገናና እንክብካቤ እየተደረገላቸው አለመሆኑ፣ የዱር እንስሳትና መጠለያዎቻቸው ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነጻ አለመሆናቸው፣ አምዳዊና የጎንዮሽ ቅንጅታዊ አሰራርን በሚፈለገው ደረጃ አለመጠናከር፣ የተደራጀ የመረጃ ሥርዓት አለመፈጠሩ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

### 1.11.6 የሥነ ሕዝብና ልማት ዕቅድ አፈፃፀም

የኢትዮጵያ ሥነ-ህዝብ ፖሊሲ ዋና ዓላማ የህዝብ ብዛትን ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ማመጣጠን ነው። በሥነ-ህዝብ ዙሪያ የሚመዘገቡ ውጤቶች በአንድ የዕቅድ ዘመን በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የሚገደቡ ሳይሆኑ ተደማሪ (Cummulative) ናቸው። ዋናው ጉዳይ ከአንድ የዕቅድ ዘመን ወደ ቀጣዩ በሚደረገው ሽግግር ሂደት አመለካከቶች የመቀልበስ አዝማሚያ ሳያሳይ በቀጣይነት ወደሚፈለገው ግብ ለመድረስ በሚያመለክት አዝማሚያ ላይ መሆናቸው ነው።

በዚህ ረገድ የሥነሕዝብ ፖሊሲው ወጥቶ መተግበር ከጀመረበት ከ1985 ጀምሮ አመርቂ ውጤቶች ተመዝግበዋል። በፖሊሲው ከተቀመጡት ዓላማዎች አኳያ ሲታይ በህዝብ ብዛት ዕድገት፣ በዘመናዊ የዕርግዝና መከላከያ ዘዴዎች አጠቃቀም፣ አጠቃላይ የውልደት መጣኔ፣ የጨቅላ ህጻናት ሞት፤ የእናቶች ሞት መጣኔ እና በህይወት የመኖር አማካይ ዕድሜ ረገድ መሻሻሎች ታይተዋል። የሕዝብ ብዛት ዕድገት በ1990ዎቹ መጀመሪያ ከነበረበት ዓመታዊ 3 በመቶ ዕድገት በ1980ዎቹ መጨረሻ ወደ 2.7 በመቶ በቀጣይም በ2006 መጨረሻ ወደ 2.4 በመቶ ቀንሷል።የቤተሰብ ዕቅድ ተጠቃሚ የሆኑ በወሊድ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ሴቶች በ1990ዎቹ መጀመሪያ ከነበረበት 8 በመቶ በ2006 መጨረሻ ወደ 42 በመቶ አድጓል። የእናቶች ሞት መጣኔ በ1990ዎቹ አጋማሽ ከነበረበት 871/100,000 በህይወት ከተወለዱ ህጻናት በ2005 ወደ 420/100,000 መቀነሱ፣ የጨቅላ ህጻናት ሞት በ1980 ዎቹ መጨረሻ ከነበረበት 128/1000 በ2004 ወደ 59/1000 መቀነሱ፣ አጠቃላይ የውልደት መጣኔ በ1980ዎቹ መጀመሪያ ከነበረበት 7 ልጆች በ2006 ወደ 4 ልጆች መቀነሱ እና በህይወት የመኖር አማካይ እድሜ በ1980ዎቹ መጀመሪያ ከነበረበት 42 አመት በ2005 ወደ 59.5 ዓመት ማደጉ ዋና ዋና የአፈጻጸም ውጤቶች ናቸው።

ለእነዚህ ውጤቶች መገኘት አስዋጽኦ ያደረጉ የሥነሕዝብ ፕሮግራሞችና መርሐ ግብሮች አፈጻጸምና በአፈጻጸም ሂደት የታዩ ችግሮችና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች እንደሚከተለው ቀርቧል።

**የጤና ኤክስቴንሽንን በማስፋፋት የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን ማጠናከር፣** በሥነሕዝብና ጤና ጥናት በ2006ዓ.ም በወሊድ ዕድሜ ከሚገኙ ያገቡ ሴቶች መካከል የቤተሰብ ዕቅድ ተጠቃሚዎች ወደ 42 በመቶ ከፍ ማለቱ ተመልክቷል።በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠናክሮ በመሰጠት ላይ በመገኘቱ በቀጣይም የተሻለ ውጤት እንደሚያስመዘግብ ይጠበቃል።

**ብሔራዊ የሥነሕዝብ ምክር ቤትን ማቋቋም፡-**የብሔራዊ የሥነሕዝብ ምክርቤትን ለማቋቋም የሚያስችል ደንብ ለሚኒስቴሮች ምክርቤት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል። ደንቡ ተስተካክሎ እስኪቀርብና ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ አንደ አማራጭ የሥነ-ሕዝብ ግብረ ኃይል ለማቋቋም ጥረት ተደርጓል። በስነሕዝብና ልማት የፓርላማ አባላት የጋራ መድረክ ለማቋቋም የሚረዳ የምክክር ስብሰባ ተካሂዶ የጋራ መድረክ እንዲቋቋም ከተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎች የተዉጣጡ የፓርላማው አባላት በጉዳዩ ዙሪያ በዩጋንዳና ፍሊፒንስ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት አድርገዋል። ብሔራዊ የሥነ-ሕዝብ የድርጊት መርሐ-ግብር ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ፖሊሲውን ይበልጥ በተቀናጀ ሁኔታ ለመፈጸም የብሔራዊ የሥነ-ሕዝብ የድርጊት መርሐ-ግብር ተዘጋጅቶ ለተለያዩ ፈጻሚ አካላት ተሰራጭቷል። በመርሀ ግብር አዘጋጃጀትም ዙሪያ ለክልሎች የቴክኒክ ድጋፍ ተሰጥቷል።

**በሥነ ሕዝብ ዙሪያ ወቅታዊ መረጃዎች እንዲሰባሰቡና በጥቅም ላይ እንዲውሉ እንዲሁም የጥናትናምርምር ተግባራት እንዲከናወኑ ማድረግ፡-** በፌደራል ሴክተር መስሪያ ቤቶችና በክልሎች ያለው የአቅም ግንባታ ፍላጎት ዳሰሳ፣ ከ2003 እስከ 2004 ያለውን የሥነ ህዝብና ልማት አመልካቾች፣ የኢትዮጵያን የሥነ ህዝብ፣

ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ያካተተ ፕሮፋይል (1992-2005)እና የምርምር አጀንዳ (2004-2007) ሰነዶች ተዘጋጅተው ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል፡፡ በምርምር አጀንዳዉ መሰረትም "Taming Ethiopian Youth Bulge" በሚል ርዕስ ጥናት ተካሒዶ የጥናቱ ሪፖርት ለህትመት ዝግጁ ሆኗል፡፡ "ICPD Beyond 2014" አገራዊ ሪፖርት ባለድረሻ አካላት በማሳተፍ ረቂቁ ተዘጋጅቷል፡፡ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በሥነ ሕዝብ፣ተዋልዶ ጤና እና ኢኮኖሚ ልማት ዙሪያ የኢትዮጵያ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ አፈጻጸምና የምዕተ አመቱ የልማት ግቦች በሚል ርዕሰና ከፖሊሲና ልማት ግቦች አንጻር የተጠኑ የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ፤ በዉሳኔ ሰጪዎች፤ ተመራማሪዎችና ባለድረሻ አካላት ዘንድ ግንዛቤ መፍጠር በሚል ጭብጥ አገር አቀፍ ኮንፈረንስ ተካሄዷል፡፡

**የፈጻሚ አካላትን አቅም በተለያዩ ደረጃዎች ማጠናከር፡-** በተለያዩ የሥነሕዝብና ልማት ጉዳዮች ላይ በፌደራልና በክልል የሥነሕዝብ ጉዳዮችን የሚተገብሩ መሥሪያ ቤቶች ባለሙያዎችን አቅም ለመገንባት በአገር ውስጥ እና ከአገር ውጪ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪ የዳይሬክቶሬቱ ባለሙያዎች በተለያዩ ርዕሶች ላይ የአጭርና የረጅም ግዜ ስልጠና ወስደዋል፡፡

**ብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ኮሙኒኬሽንና አድቮኬሲ ስትራቴጂ መተግበር፡-** ብሔራዊ የሥነ-ሕዝብ ኢንፎርሜሽን ትምህርትና፣ኮሚኒኬሽን እና አድቮኬሲ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ተሰራጭቷል፡፡ ከፌደራልና ከአማራ፣ ኦሮሚያ፣ሶማሌ እና ደበቡ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች ምክር ቤት አባላት ጋር በመሆን በክልሎቹ ያለውን የቤተሰብ ዕቅድ፣የወጣቶች ተዋልዶ ጤና እና አካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን ለመገምገም በአራቱም ክልሎች ጉብኝትና በፌደራል ደረጃ ላሉ ቀሪ የምክር ቤት አባላት የግንዛቤ ማስጨበጫ አውደጥናት ተካሂዷል፡፡የሥነ-ህዝብና ልማት ኮንፈረንስ እ.አ.አ ከ2014 በኋላ በሚል ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ በአማራ፣ደቡብ እና ኦሮሚያ ክልሎች የመገናኛ ብዙሀን ተከታታይ የሬዲዮ ፕሮግራሞች እንዲተላለፍ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በሥነ ሕዝብና ልማት ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር እንዲቻል በየዓመቱ ሐምሌ 4 ቀን የሚከበረውን አለማቀፍ የሥነሕዝብ ቀን በተለያዩ ክልሎች ተከብሯል፡፡

**የሴቶች የመጀመሪያ የጋብቻ ዕድሜን በቤተሰብ ሕጉ መሰረት 18 ዓመትና ከዚያ በላይ እንዲሆን ማድረግ፡-** የሴቶች የመጀመሪያ ጋብቻ ዕድሜ ከፍ እንዲልና የሥነ ተዋልዶ ጤና መብቶች እንዲከበሩ ከሚመለከታቸው የባለድረሻ አካላት ጋር በመተባበር በተለያዩ ሥልጠናዎች፣ አውደጥናቶች፣የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎችና ታትመው በተሰራጩ የግንዛቤ ማዳበሪያ ማቴሪያሎች አማካይነት የሚመለከታቸው አካላት ትምህርት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በሥነ ሕዝብና ልማት ዙሪያ ለፖሊሲ ግብአት የሚሆኑ በቂና ደረጃቸውን የጠበቁ ችግር ፈች የሆኑ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ያለመከናወናቸው፣ በፌደራልም ሆነ በክልል ያሉ የስነ ሕዝብ አስተባባሪ አካላት ወጥነትና ጠንካራ አደረጃጀት የሌላቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከዘርፍ መስሪያ ቤቶች ጋር ያለው ግንኙነት ደካማ መሆንና ስራውን በተቀናጀ ሁኔታ ለማከናወን ውስንነት መታየቱ፣ የስነ ሕዝብ ጉዳዮችን የመከታተያና የመገምገሚያ ማዕቀፍ ደካማ መሆን አንደ ዋና ችግሮች የታዩ ሲሆኑ ብሄራዊ የፕላን ኮሚሽን በመቋቋሙ ምክንያት የሥነ- ሕዝብና ልማት ጉዳይ ወደ ኮሚሽኑ መዛወሩና በአዲስ አደረጃጀት መዋቀሩ የሥነ- ሕዝብና ልማት ጉዳዮችን በተሻል ሁኔታ ለማስተባበር ረገድ እንደ መልካም አጋጣሚ የሚታይ ነው፡፡ በሌላ በኩል በሥነ ሕዝብና ልማት ጉዳዮች ላይ የአጋሮች ተሳትፎ አበረታች መሆኑና የውሳኔ ሰጪ አካላት በተለይም የህዘብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት እስከታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ በመውረድ የሥነ-ህዝብ፣ ተዋልዶ ጤናና የአካባቢ ጉዳዮች ላይ በአካል ተገኝተው ምልከታ ማድረጋቸውና የመፍትሄ ሀሳብ መስጠታቸው በአፈጻጸም ወቅት የተገኙ መልከም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡

## 1.11.7 የአካባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች አፈጻጸም

### 1. ዓላማና አቅጣጫዎች

የአየር ንብረት ለውጥና ነባር የአካባቢ እንክብካቤ ሥርዓቶችን ማጠናከር፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚካሄደውን ሀገራዊ ጥረት ለማሳካት የሚያስችል አቅም መግባት የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አቅጣጫዎች ናቸው፡፡ እነዚህን አቅጣጫዎች መሠረት በማድረግ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት የሰውን በጎ ሁኔታ እንዲሁም የአካባቢ ደህንነት በዘላቂነት ለማራመድ በተለይም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣ ህጎችንና ደረጃዎችን ማደራጀት፣ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን በመገንባት ውጤታማ አፈፃፀም ማስመዝገብ የዕቅዱ ዓላማዎች ናቸው፡፡ በተለይም ዘርፉ እንደ አዲስ ከተዋቀረ በኋላ የደንን ዘርፍ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ማሳደግ ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ነበር፡፡

### 2. የዕቅዱ ዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም

በመጀመሪው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባታ ስትራቴጂ ተቀርፆ፣ በየደረጃው የህዝብ ውይይት ተደንበት እና በመንግስት ፀድቆ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ ይህንንም ተፈፃሚ ለማድረግ አዲስ አደረጃጀት ተፈጥሯል፡፡ ለአየር ንብረት ለውጥ በቀላሉ የማይበገሩ የመሰረተ ልማቶች ደህንነትን ለማረጋገጥ በ225 ወረዳዎች፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ በወረዳ ለመገንባት በ97 ወረዳዎች እስከ 2007 ስድስት ወራት ድረስ 126 የአካባቢ እንክብካቤ ፕሮጀክቶች ተተግብረዋል፣ በተጨማሪም በ136 ወረዳዎች 38 ቴክኖሎጂዎች በፈጣን ትግበራ ኢንቬስትመንት (Fast Track Investment) ሊተገበሩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ 92 የሚደርሱ የአረንጓዴ ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተው የክህሎት ስልጠና በመውሰድ ወደ ስራ ገብተው ተጠቃሚ በመሆን ላይ የሚገኙ ሲሆን 270,000 ሀይል ቆጣቢ አምፖሎች ከቻይና መንግስት በድጋፍ ተገኝተው በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በኩል ተሰራጭተው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጓል፡፡

የአርንጓዴ ልማት ግንባታ ሌላው ትኩረት ተጨማሪ ሀብት በማሰባሰብ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አርንጓዴ ኢኮኖሚ ስለትን ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን በዚህ ዙሪያ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ የአካባቢ ተንከባካቢዎችን በገንዘብ ለመደገፍ በተደረገው እንቅስቃሴ ከልዩ ልዩ የድጋፍ ሰጪ አካላት በድምሩ 4.6 ቢሊዮን ብር ድጋፍ የተደረገ ሲሆን ከግሎባል ኢንቫይሮንሜንት ፋሲሊቲ ቋት( GEF) 5ኛና 6ኛ ዙር በቅደም ተከተል 7.5 ሚሊዮን እና 27.23 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የገንዘብ ድጋፍ ተፈቅዷል፡፡ ከስድስት የዘርፍ መ/ቤቶች 48 ፕሮጀክቶች እንዲቀርቡ ተደርጎ 38 ፕሮጀክቶች ፀድቀው በአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ የገንዘብ ቋት ወይም ፋሲሊቲ በኩል በተገኘ 23 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ድጋፍ በተመረጡ ቦታዎች ላይ በአሁኑ ጊዜ በትግበራ ላይ ይገኛሉ፡፡ የREDD+ National Secretriat በማደራጀት ኢትዮጵያን ከደን ዘርፍ የካርበን ንግድ እድሎች ተጠቃሚ ለመሆን ብቁ የሚያደርጋትን የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎች በማከናወን ላይ ስትሆን ለዚህ ማስፈፀሚያ የሚሆን 13.5 ሚሊዮን ዶላር ከኖርዌይ መንግስት አግኝታለች፡፡ በተመሳሳይ በኦሮሚያ ክልል ለታቀደው የኦሮሚያ የደን ልማትና ጥበቃ የሙከራ ፕሮጀክት /Oromiya Forested Landscape Project/ የሚውል 50 ሚሊዮን ዶላር እና በሌሎች ክልሎች ለሚካሄድ የደን ልማትና አቅም ግንባታ 9 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ከኖርዌይ መንግስት ማግኘት ተችሏል፡፡

**የአካባቢ እንክብካቤ ህጎች ዝግጅት፡-** ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት በሚደረገው እንቅስቃሴ የአካባቢ እንክብካቤ ህጎችን ተግባራዊ ማድረግ ወሳኝ ናቸው፡፡ በመሆኑም እስከ 2007 በጀት ዓመት መጨረሻ 14 የአካባቢ እንክብካቤ ሥርዓቶችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 15 የአካባቢ እንክብካቤ

ሥርዓቶችን ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ እነዚህም የውሀ አዘል መሬቶች አያያዝ እና አጠቃቀም ረቂቅ አዋጅ፣ የኤሌክትሪክና የኤሌክትሮኒክ ነክ ቆሻሻዎች አያያዝ እና አወጋገድ ረቂቅ ደንብ፣የአበባ ልማት ዘርፍ የአሰራር ሥነ-ምግባር የሚወስን የደንብ ማስፈፀሚያ መመሪያ፣የደህንነት ህይወት አዋጅ ማሻሻያ፣ ከተሽከርካሪዎች የሚለቀቁ በካይና ሙቀት አማቂ ጋዞችን የልቀት መጠን መወሰኛ ደረጃ እና በልማት የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ሂደትና የህዝብ ተሳትፎን ለማጎልበት የሚያግዙ መመሪያዎች ናቸው፡፡

**በአካባቢ ዘርፍ የህጎችንና መርሐግብሮችን አፈፃፀም መከታተል፣መገምገምና ውጤታማነት ማረጋገጥ፡-** ከግብርናው ዘርፍ ወደ ውጭ ሀገር ለተላኩ ሰብሎች ከልውጥ ህያው ነፃ ስለመሆናቸው፣ በኢነርጂ እና በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ላይ ለቀረቡ የንፁህ ልማት ዘይቤ ፕሮጀክቶች፣ በኢነርጂ እና በትራንስፖርት ዘርፎች ላይ ለቀረቡ የልማት ፕሮጀክቶች፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ሰነዶች፣ በአካባቢ እንክብካቤ ዘርፍ ለቀረቡ የአካባቢ ሙያ ብቃት ማረጋገጫዎች፣ በኢንዱስትሪ እና በግብርና ዘርፎች ላይ ለቀረቡ የአደገኛ ኬሚካልና ቆሻሻ ዝውውር በድምሩ በፌደራል ደረጃ ለቀረቡ 382 ጥያቄዎች ፈቃዶች ተሰጥተዋል፣ በክልልና በከተማ አስተዳደር ደረጃ ለቀረቡ ጥያቄዎች 2811 የይሁንታ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡

በተጨማሪም ስድስት የአካባቢ ሁኔታና ለውጥ ዘገባዎች ለማዘጋጀት ታቅዶ 5 ዘገባዎች የተዘጋጁ ሲሆን ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልት ትግበራን በተመለከተ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን እና ተግባራትን መረጃ ለመመዝገብና ለመከታተል የሚያስችል የምዝገባ ዘዴ ተዘጋጅቷል፡፡ የኢትዮጵያን ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልት የትግበራ ደረጃን የሚያመላክት ሪፖርት (2003--2006)" የተሰኘ የዘገባ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

**የደን ልማት ዘርፍን በተመለከተ፡-** በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ለ815.3 ሺህ ሄክታር የደን ቦታዎች የማኔጅመንት ፕላንና ካርታ ለመስራት ታቅዶ እስከ 2006 በጀት ዓመት ድረስ ለ1440.8 ሺህ ሄክታር ደን የማኔጅመንት ፕላንና ካርታ ተዘጋጅቷል፡፡ በተመሳሳይ የደን ሀብት አያያዝና አጠቃቀም ለማሻሻል 13 ሚሊዮን ሄክታር የነበረውን የአገሪቱን የደን ሽፋን ወደ15.9 ሚሊዮን ሄክታር ለማሳደግ ታቅዶ የዕቅዱ ዘመናት 15.93 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በደን እዲሸፈን ማድረግ ተችሏል፡፡ በደን ዘርፍ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 16.2 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታ ባላቸው ዛፎች ለመሸፈን ታቅዶ እስከ 2006 በጀት ዓመት 16.77 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታ ባላቸው ዛፎች በመሸፈን ከዕቅድ በላይ የሆነ አፈፃፀም ተመዝግቧል፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ የተራቆቱ አካባቢዎች መልሰው እንዲያገግሙ ለማስቻል በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 10.21 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለመከለል ታቅዶ ከ11.7 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላይ በመከለል እንዲያገግም እየተደረገ ነው፡፡ በሌላ በኩል ለደን ልማቱ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ 4808.43 ኩንታል የዛፍ ዘሮች በአምስት አመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ለማቅረብ ታቅዶ እስከ 2006 በጀት ዓመት ድረስ 22515 ኩንታል ዘር ተሰብስቦ ተሰራጭቷል፡፡ የሀገሪቱን የደን ሽፋን ካለው አጠቃላይ የመሬት ስፋት ምን ያህል ድርሻ እንዳለው ለማወቅ ከሳተላይት ምስል በተወሰደ መረጃ በ2006 በጀት ዓመት የሀገሪቱን ጠቅላላ መሬት 53 በመቶ ማፕ በማድረግ የሀገሪቱን የደን ሽፋን ለማወቅ በተደረገው ጥረት የሀገሪቱን መሬት 55 በመቶ የሚሆነውን ማፕ ማድረግ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በዘርፉ ላይ የነበረው የአመራሩ ቁርጠኝነት፣ የተፈጠረው መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ የህብረተሰቡ ንቁ ተሳትፎ ፣ ሊያሰሩ የሚችሉ ፖሊሲዎች፣ ስልቶችና መርሀ ግብሮች መዘርጋታቸው እና ከባለድርሻ አካላት፣ ከፈፃሚዎች እንዲሁም ከህብረተሰቡ ጋር መልካም ግንኙነት መገንባቱ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የተገኙ ተሞክሮዎች ነበሩ፡፡ በሌላ በኩል የማስፈፀም አቅም ውስንነት፣ የአረንጓዴ ቴክኖሎጂ ፓኬጆችን ማላመድ ማስተዋወቅና ማስፋፋት አለመቻሉ፣የሚኒስቴር መ/ቤቱ መዋቅር እስከታችኛው አስተዳደር እርከን ባለመውረዱ በክልሎች መካከል የአደረጃጀት ወጥነት ማጣት የዘርፉ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ነበሩ፡፡

## 1.12 የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

### ሀ) በአጠቃላይ ኢኮኖሚ ደረጃ

ባለፉት ሶስት ዓመታት (2003-2005) የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶች ተዘጋጅተው በመንግስት እንዲፀድቁ ተደርጓል፡፡ በፌዴራልና በክልል ደረጃዎች የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት በአፈፃጸም ሪፖርቶቹ ላይ የግሉ ዘርፍ ተወካዮች፣ የልማት አጋሮች ተወካዮች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮች፣ የኃይማኖት ተቋማት ተወካዮች፣ የወጣቶችና የሴቶች አደረጃጀቶች ተወካዮች፣ የሙያ ማህበራት ተወካዮች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች የተሳተፉበት ግምገማ ተካሂዷል፡፡ ከግምገማውም የተለያዩ ልምዶች እና ሀሳቦች ለቀጣይ የልማት ሥራዎች በግብዓትነት ተወስደዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በመንግስትና በልማት አጋሮች በተዘጋጁ የጋራ መድረኮች በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የአፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ ግምገማዎች ተካሂደዋል፡፡ በግምገማው የተገኙ ጠቃሚ ግብረ መልሶችም ለቀጣይ ሥራ በግብዓትነት ተወስደዋል፡፡

በሀገር አቀፍ የክትትል ሥርዓቱና የአምስት ዓመት ብሔራዊ የስታቲስቲክስ ልማት ስትራቴጂ መሠረት ኢኮኖሚውን ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው አግባብ አቀናጅቶ ከመምራት አኳያ የዋጋ መረጃዎችን በየጊዜው ወቅታዊ በማድረግና ለፖሊሲ ውሳኔዎች በግብዓትነት በመጠቀም፣ የፊስካልና የሞኒተሪ ፖሊሲዎችን አፈፃጸም በቅርብ በመከታተል፣ የኤክስፖርት አፈፃጸምን በቅርብ በመከታተል፣ የመንግስት የፋይናንስ ሥርዓቱን በየደረጃው ተናባቢና ተመጋጋቢ ሆኖ መፈፀሙን በማረጋገጥ፣ የማክሮ ኢኮኖሚ አፈፃጸሙን በቅርብ በመከታተል ማስተካከያ የሚሹ ጉዳዮች ሲከሰቱ ፈጣን እርምጃ በመውሰድ በበጀት ዓመቱ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ቀጣይነትን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### ለ) በዘርፍ ደረጃ

የአምስት ዓመቱን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሠረት በማድረግ በተዘጋጁ ዓመታዊ የዘርፍ ዕቅዶች በመታገዝ በቅርብ ክትትል የተደገፉ የልማት ሥራዎች በተለያዩ ደረጃዎች በዘርፍ አስፈፃሚ አካላት ተከናውነዋል፡፡ በተለያዩ ዘርፎች በየበጀት ዓመቱ የተከናወኑ የልማት ሥራዎች አፈፃፀም በተለያዩ ደረጃዎች በተዘጋጁ የምክክር መድረኮች የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ተገምግመው ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት ለመንግስት ቀርበዋል፡፡ ከዘርፍ አስፈፃሚ መ/ቤቶች የቀረቡ ዓመታዊ የአፈፃጸም ሪፖርቶች በሀገር ደረጃ ለተዘጋጁት የተጠቃለሉ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የአራት ዓመታት (2003-2006) አፈፃጸም ሪፖርቶች ዝግጅት እንደ ግብዓት ተወስደዋል፡፡ የክትትል ሥርዓቱን በተጠናከረ ሁኔታ ተፈፃሚ ከማድረግ አኳያ የዘርፍ አስፈፃሚ መ/ቤቶችን የዕቅድና ክትትል የሥራ ክፍሎችን በመረጃ አያያዝና አጠቃቀም፣ በዕቅድ ዝግጅት፣ በትግበራ ክትትልና በግምገማ ይበልጥ ማጠናከር በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራበት የሚገባ ይሆናል፡፡

### ሐ) የመስክ ናሙናና ቆጠራ ጥናት ሀገራዊ መረጃዎች

የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ የክትትል ሥራዎች በአስተዳደራዊና በመስክ ናሙና ጥናት መረጃዎች ተደግፈው የሚከናወኑ ናቸው፡፡ አስተዳደራዊ የክትትል መረጃዎች ከዘርፍ አስፈፃሚ መ/ቤቶች በሪፖርት የሚቀርቡ ሲሆን የመስክ ናሙና ጥናት መረጃዎች በማዕከላዊ ስታቲስቲክ ኤጀንሲ አማካኝነት በሚደረጉ ጥናቶች የሚመነጩ ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ባለፉት አራት ዓመታት በዋና ዋና ዘርፎች የዕቅዱን የአፈፃጸም ሂደት የሚያሳዩ የመስክ ናሙና ጥናት መረጃዎች በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ እንዲመነጩና ለሪፖርቱ በግብዓትነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ከየዘርፉ አስፈፃሚ አካላት በአስተዳደራዊ እና በመስክ ክትትል ምልከታ መረጃዎች ተደግፈው የቀረቡ የአፈፃፀም ሪፖርቶች በየዓመቱ ለተዘጋጁ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተጠቃለሉ የአፈፃፀም ሪፖርቶች ዝግጅት በግብዓትነት ተወስደዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አራት ዓመታት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ትግበራ በተለይም የትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች (Mega Projects) ትግበራ የቅርብ የፖለቲካ አመራርና ድጋፍ ተሰጥቶት ተፈፃሚ የተደረገ በመሆኑ የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንፎርሜሽን ዕቅድ መለያ የሆኑ ዋና ዋና ግቦችን ማሳካት እንደተቻለ የአፈፃፀም ሪፖርቶች ያሳያሉ፡፡

## 1.13 በዕቅዱ የትግበራ ሂደት የታዩ ጥንካሬዎችና ያጋጠሙ ፈተናዎች

ባለፉት አራት ዓመታት (2003-2006) በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በህዝቦች የተደራጀና የተቀናጀ ተሳትፎ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ እንደ ዝግጅቱ ሁሉ የቅርብ የፖለቲካ አመራርና ድጋፍ እየተሰጠ ሲፈፀም ቆይቷል፡፡ በትግበራ ሂደቱ መልካም ውጤቶች ተመዝግበዋል፣ ፈተናዎችም አጋጥመዋል፡፡ ከዚህ አንፃር በዕቅዱ የትግበራ ሂደት የታዩ ጥንካሬዎችና ያጋጠሙ ፈተናዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 1.13.1 ጥንካሬዎችና መልካም ተሞክሮዎች

#### ሀ) በዕቅድና ግዙፍ ፕሮጀክቶች ትግበራ፣ ቴክኖሎጂ በመማር የታየ ከፍተኛ ቁርጠኝነት፣ የተፈጠረ አቅምና የተመዘገበ ውጤት

የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መለያ የሆኑ ግዙፍ ፕሮጀክቶች (Mega Projects) (ለምሳሌ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት፣ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች፣ የባቡር መሠረተ-ልማት ፕሮጀክቶች፣ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች…ወዘተ) የቅድመ ዝግጅት ሥራቸው ተጠናቅቆ በቁርጠኝነት ወደ ግንባታ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ይህ በራሱ ትልቅ ሀገራዊ ትርጉምና ፋይዳ ያለው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በሀገራችን ህዝቦች የተደራጀና የተቀናጀ ተሳትፎ እና በመንግስት የቅርብ የፖለቲካ አመራርና ድጋፍ ተግባራዊ ተደርጎ የሀገራችንን ትራንስፎርሜሽን የሚያፋጥኑ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ እነዚህ ውጤቶች የሀገራችንን መልካም ገፅታ ግንባታ በከፍተኛ ደረጃ አጉልተው ለማሳየት ከማስቻላቸውም በላይ በቀጣይ ለሚሠሩ የልማት ሥራዎች ትልቅ ሀገራዊ አቅም እና ጉልበት እንደሚሆኑ ይጠበቃል፡፡

#### ለ) በልማት ሠራዊት አደረጃጀት የተመዘገቡ የላቁ ውጤቶች

በግብርና ዘርፍ የአብዛኛዎቹን አርሶ-አደሮች ምርታማነት ከምርጦቹ አርሶ-አደሮች ደረጃ ለማድረስ በግብርና ኤክስቴንሽን ሥርዓቱ በልማት ሠራዊት አግባብ ለመተግበር ከፍተኛ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በሰብል ልማትና በመስኖ አጠቃቀም ዙሪያ የልማት ሠራዊት በመገንባት የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገበ ክልል መኖሩ በሌሎች ክልሎችም በዞን፣ በወረዳ፣ በቀበሌ እንዲሁም በልማት ቡድን ደረጃ የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎችን በማስፋት በቀጣይ የዘርፉን ምርታማነት በላቀ ደረጃ ለማሳደግ ለሚከናወኑ የልማት ሥራዎች የአሠራርና የአደረጃጀት ዕውቀት እና የክህሎት አቅም መፈጠሩ፣

በተመሳሳይ ህዝቡን አስረድቶና አሳምኖ በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ ከጫፍ እስከ ጫፍ በማንቀሳቀስ በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ዙሪያ የተሠሩ የልማት ሥራዎችና የተመዘገቡ ውጤቶች ፈጣንና የላቀ ልማት ማሳካት እንደሚቻል ትልቅ ማሳያዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በትክክለኛ የልማት ፖሊሲዎች ላይ ተመስርተን ካለፍንባቸው የልማት ሂደቶች ያገኘናቸው ትምህርቶች ለቃጣይ የልማት ሥራዎቻችን ጠንካራ ጉልበትና አቅም መሆናቸው፡፡

#### ሐ) በኢንዱስሪ ዘርፍ አዲስ ኢንቨስትመንት መፍሰሱና ተጨማሩ አቅም መፈጠሩ

በኢንዱስትሪ ዘርፍም በተለይ አዲስ ኢንቨስትመንት እንዲፈስ ከፍተኛ የልማት ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ በሚጠበቀው መጠንና ፍጥነት ባይሆንም ውጤቶች መታየት ጀምረዋል፡፡ በተለይ በብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ከፍተኛ ሀገራዊ አቅም መፍጠር ተችሏል፡፡ በዚህም የገቢ ምርቶችን የሚተኩ ግብአቶች በማቅረብ፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግር አስተዋፅኦ በማድረግ፣ የውጭ ምንዛሬን በማዳን እና የኢንዱስትሪውን ዘርፍ መሠረት በማስፋት ከፍተኛ የልማት ሥራ ተሠርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግሉ ዘርፍ ማነቆ የሆነውን የለማ የኢንዱስትሪ መሬት የማግኘት ችግር ለመፍታት በተለያዩ ከተሞች የኢንዱስትሪ ዞኖችን በማቋቋምና መሠረተ ልማታቸው እንዲሟላ በማድረግ ለልማታዊ ባለሀብቱ

ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው አሠራር ለማስተላለፍ የኢንዱስትሪ ዞኖች ልማት ፕሮግራም ትግበራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ይህንንም በአግባቡ ለመምራትና ለመደገፍ ህጋዊ ተቋማዊ ማዕቀፍ ተፈጥሯል፡፡ ይህም በቀጣይ በተለይ በማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፍ ለሚጠበቀው ትራንስፎርሜሽን የተደራጀና የተቀናጀ አቅም ነው፡፡

**ሠ) በተረጋጋ ማክሮኢኮኖሚ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ማረጋገጥ መቻሉ**

በተወሳሰበ ሀገራዊና ዓለም-አቀፋዊ የኢኮኖሚ ሁኔታ ውስጥ የተረጋጋ የማክሮ-ኢኮኖሚ ለማስፈን ውጤታማ የፖሊሲ ርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ እንዲሁም የቅርብ ክትትልና ግምገማ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም (1) አስተዳደራዊና ጥብቅ የፊስካልና የገንዘብ ፖሊሲዎች እርምጃዎች በመወሰዳቸው በዕቅዱ የመጀመሪያዎቹ ሁለት የትግበራ ዓመታት ተከስቶ የነበረውን የዋጋ ንረት ወደ ነጠላ አሀዝ ማውረድ መቻሉ (2) በዕቅዱ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ቁልፍ የመሠረተልማትና የአምራች ዘርፍ ፕሮጀክቶች እንዲሁም የኤክስፖርት የውጭ ምንዛሬና የሀገር ውስጥ ብድር እንዲያገኙና ሥራቸው እንዲፋጠን መደረጉ (3) በዕቅዱ የትግበራ ሂደት የውጭ ሀብት በማሰባሰብ ቁልፍ የሆኑ የመሠረተ-ልማት ፕሮጀክቶች (ለምሳሌ የባቡር ፕሮጀክቶች) እንዲጀመሩና የግንባታ ሥራቸው እንዲፋጠን መደረጉ (4) መሠረታዊ የሸቀጦችን ዋጋ በማረጋጋት በተከናወኑ ሥራዎች ኢኮኖሚው ላልታሰበ ቀውስ እንዳይጋለጥና የዕቅዱ ወሳኝ ትግበራ እንዳይደናቀፍ ለማድረግ መቻሉ በዕቅዱ የትግበራ ሂደት ለታዩ ጥንካሬዎች ዋና ዋና መገለጫዎች ናቸው፡፡

## 1.13.2 በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ፈተናዎች

ባለፉት አራት ዓመታት መንግስት የልማት ኃይሎችን አስተባብሮ በመምራት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በተደራጀና በተቀናጀ የህዝብ ተሳትፎ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ተፈፃሚ ሲደረግ የቆየና በዚህም መልካም ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም በዕቅዱ የአፈፃፀም ሂደት ፈታኝ ሁኔታዎች ሳያጋጥሙ አልቀረም፡፡ በዕቅዱ የመጀመሪያዎቹ ሁለት የትግበራ ዓመታት (2003 እና 2004) የዋጋ ንረት በሀገራችን የወጪ ንግድ ተወዳዳሪነትና በህብረተሰቡ የመግዛት አቅም ላይ ጫና በማሳደር ፈተና ገጥሞ ነበር፡፡ እንዲሁም ባለፉት አራት ዓመታት በተለይ የሸቀጦች የወጪ ንግድ እንቅስቃሴ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ በተቀመጠው ግብ መሠረት ተመጣጣኝ አፈፃፀም ባለማሳየቱ የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት አስከትሏል፡፡ በተመሳሳይ አምራች ዘርፉ ዕድገት ያሳየ ቢሆንም ኢኮኖሚው የሚፈልጋቸውን ምርቶች በመጠን፣ በዓይነት፣ በጥራትና በተወዳዳሪነት ለውጭ ንግድ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓት እና ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ማቅረብ ተስኖት ታይቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የዓለም የገበያ ሁኔታ መቀዛቀዝና የሀገራችን ዋና ዋና ሸቀጦች የወጪ ንግድ ዋጋ ( ቡና፣ ወርቅ) መቀነስ፣ የነዳጅ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሮ በዚያው ላይ መቆየት የማክሮ-ኢኮኖሚ ማኔጅመንቱን አወሳስቦት ቆይቷል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አራት ዓመታት የኢኮኖሚው ተቋማዊና መዋቅራዊ ማነቆዎች በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የአፈፃፀም ሂደት ትልቅ ፈተናዎች የነበሩ ሲሆን ዋና ዋናዎቹም፡-

- **ሀ. የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ውስንነት፡-** በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዘመን በተለያዩ ዘርፎች የተቀመጡትን ግቦች ከማሳካት አንፃር በተለያዩ ደረጃዎች የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ውስንነቶች ፈተናዎች ነበሩ፡፡ በተለይ በፕሮጀክት ማኔጅመንት (በማቀድ፣ በመተግበር፣ በመከታተል፣ ኮንትራት በማስተዳደር) የታዩ የአቅም ውስንነቶችና የቅንጅት ችግሮች፣ የግብርናን ምርታማነት በተጠበቀውና በታቀደው መሠረት ከመፈፀም አንፃር የፈፃሚ አካላትን አስተሳሳብ ቀይሮ ከማነሳሳት፣ ከማደራጀት፣ አሰልጥኖም ከማስማራት አንፃር የታዩ ጉድለቶች፣ ወዘተ ዋና ዋና ፈተናዎች ናቸው፡፡ ከወጪ ንግዳችን ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው የሎጂስቲክስ አገልግሎትና የጉምሩክ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ችግሮች በኢንቨስትመንት እና በንግድ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል፡፡ በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ብዙ ኢንቨስትመንት ቢፈስም በየተቋማቱ ያለው አቅም ውስንነት አሁንም የተፈታ ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም በሲቪል ሰርቪሱ ብቁ፣ ተነሳሽነት ያለው፣ በክህሎት የዳበረና ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥ የተላበሰ የሰው ኃይል ለማደራጀት እየተደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

**ለ. ኪራይ ሰብሳቢነት (የአመለካከትና የተግባር) የመልካም አስተዳደር ችግር፡-** የኪራይ ሰብሳቢነት (በአመለካከትም ሆነ በተግባር) እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች የኢኮኖሚና ማህበራዊ አገልግሎቶች በታቀደውና በተጠበቀው ደረጃ እንዳይሳለጡ በመግታት፣ በዚያው ልክ በተለያዩ ዘርፎች የተቀመጡ የኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት ግቦች በተጠበቀው ደረጃ እንዳይፈፀሙ ከፍተኛ ጫና በማሳደር አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥረዋል፡፡ ግልፅነትንና ተወዳደሪነትን ለማስፈን የተዘረጋው የንግድ ሥርዓትና የንግድ ሥርዓት ሪፎርም በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በተሟላ ሁኔታ ተፈፃሚ አልሆነም፡፡ ከዚህ አንፃር የወጪ ንግዳችንን እና የሀገር ውስጥ ገበያችንን ግልፅነት የሰፈነበትና ተወዳዳሪ በማድረግ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች እየተመዘገበ ካለው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም እስካሁን እየተከናወኑ ያሉ ውጤታማ ሥራዎችን ማስቀጠልና ኪራይ ሰብሰቢነትን በተለያዩ ደረጃዎች መታገል ለአፍታም ችላ የማይባል ጉዳይ ይሆናል፡፡

**ሐ. የዋጋ ንረት፡-** በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የመጀመሪያና ሁለተኛ የትግበራ ዓመታት (2003 እና 2004) የዋጋ ንረት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበትና ለአጠቃላይ ማክሮ-ኢኮኖሚው መረጋጋት ፈተና የሆነበት አጋጣሚ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ይህንን ተከትሎ የዋጋ ንረቱን ለመቆጣጠር በመንግስት ከተወሰዱ ዕርምጃዎች መካከል ጥብቅ የፊስካልና የሞኒታሪ ፖሊሲዎች ተፈፃሚ ተደርገዋል፡፡ እንዲሁም መሠረታዊ ሸቀጦች (ስኳር፣ ዘይትና ስንዴ) ከውጭ ተገዝተው ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የህበረተሰብ ክፍሎች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርቡ እና የንግዱን ዘርፍ የሚደግፍና ተወዳዳሪ የሚያደርግ ደንብ ወጥቶ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በዚህም የተከሰተውን የዋጋ ንረት በ2006 በጀት ዓመት ወደ ነጣላ አሀዝ ማውረድ ተችሏል፡፡ የዋጋ ንረት ለማክሮኢኮኖሚው መረጋጋት ስጋት ሆኖ እንዳይቀጥል በቀጣይ የግብርናን ምርታማነት ማሳደግ፣ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት በማስፋፋት ዕድገቱን ማፋጠን እና በተለያዩ ዘርፎች እስካሁን የተገነባውን አቅም በተደረጀና በተቀናጀ አግባብ አሟጥጦ በልማት ሥራዎች ላይ በማዋል አቅርቦትን አስተማማኝ ማድረግ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

**መ. በአጠቃላይ አቅርቦትና አጠቃላይ ፍላጎት መካከል ያለው ሚዛን መዛነፍ፡-** ለዚህ አንዱ ማሳያ የንግድ ሚዛን ጉድለት እየሰፋ መምጣት ነው፡፡ ባለፉት አራት ዓመታት ያጋጠመው ትልቅ ፈተና የወጪ ንግዳችን በታቀደውና በተጠበቀው ልክ ባለመፈፀሙ የሀገራችን የንግድ ሚዛን ጉድለት እየሰፋ መምጣቱ ነው፡፡ ይህም ከሸቀጦች ወጪ ንግድ የተገኘው የውጭ ምንዛሬ ገቢ የሸቀጦች የገቢ ንግድ ወጪን በ2003 ይሸፍን ከነበረበት 33.3 በመቶ በ2006 ወደ 23.7 በመቶ ወርዷል፡፡ ያለፉት አራት ዓመታት አማካይ አፈፃፀምም 27.5 በመቶ ብቻ ነበር፡፡ ለዚህ ፈታኝ ሁኔታ አንዱ ምክንያት የሸቀጦች የወጪ ንግድ በተለይ የወርቅና የቡና የዓለም ገበያ ዋጋ ቅናሽ ማሳየቱ ሲሆን ዋናው ምክንያት ግን የወጪ ንግድ ሸቀጦቻችን በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት እና በዋጋ በዓለም ደራጃ ተወዳዳሪ የማድረግ አቅማችን ደካማ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የወጪ ንግድ ዕመርታን ለማምጣት የማዕድንና የግብርና ጥሬ ምርቶች ለወጪ ንግድ ከማቅረብ ይልቅ እሴት በመጨመር መላክ፣ እንዲሁም በወጪ ንግድ ላይ የተሠማሩ ባለሀብቶች በምርቶች ላይ እሴት እየጨመሩ መላክ እንዲችሉ በቂ ክትትልና ድጋፍ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ አቅርቦትና አጠቃላይ ፍላጎት መካከል ያለው ሚዛን መዛነፍ ሌላው መሳያ ደግሞ በቁጠባና ኢንቨስትመንት መካከል ያለው ሰፊ ጉድለት ነው፡፡ ባለፉት አራት ዓመታት የሀገር ውስጥ ቁጠባ መጣኔ በ2002 ከነበረበት 9.5 በመቶ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 22.5 በመቶ አድጓል፡፡ በተመሳሳይ ወቅት በኢኮኖሚ ውስጥ የተደረገው የኢንቨስትመንት መጠን ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2002 ከነበረበት 24.7 በመቶ በ2006 ወደ 40.3 በመቶ አድጓል፡፡ ይህም በቁጠባና በኢንቨስትመንት መካከል ያለው ጉድለት ሰፊ መሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡ ባለፉት አራት ዓመታት የተመዘገበው የኢንቨስትመንት መጣኔ መልካም የሚባል ቢሆንም ችግሩ አብዛኛው በአገር ውስጥ ቁጠባ ገንዘብ ሳይሆን በውጪ ሀገር ቁጠባ ገንዘብ መሸፈኑ ነው፡፡ በመሆኑም ለኢንቨስትመንት ሊውል

የሚችል የሀገር ውስጥ ቁጠባ በበቂ መጠን ከማሰባሰብ አንፃር ብዙ የሚቀር እንዳለና የፋይናንስ ዕጥረት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ አንዱ ዋና ፈተና እንደነበር መመልከት ይቻላል፡፡

ሠ. **የመሠረተ ልማት አቅርቦት፡-** የመሠረተ ልማት የኢኮኖሚ ዕድገቱ እንዲፋጠን የሚያስፈልጉ የትራንስፖርት፣ የኮሙኒኬሽን እና ኃይል አቅርቦትን በጥራትና በተወዳዳሪ ዋጋ ለማቅረብ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ከዚህ አንፃር ባለፉት አራት ዓመታት የመሠረተ ልማት አቅርቦትን አስተማማኝ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚህም መልካም ውጤቶች ተመዝገበዋል፡፡ ሆኖም አሁንም እየታዩ ያሉ የመሠረተ ልማት፣ የኃይል አቅርቦት፣ የሎጂስቲክስ አገልግሎት…ወዘተ ችግሮች በርካታ ናቸው፡፡ እነዚህን የመሠረተ ልማት አቅርቦት ችግሮች በቅርብ ክትትልና ድጋፍ መፍታት በእነዚህ ማነቆዎች ተተብትቦ የተያዘውን ልማታዊ አቅም ያለተጨማሪ ኢንቨስትመንት ጥቅም ላይ ለማዋል ያስችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ውስን ሀብትን ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ስኬታማ በሆነ አግባብ መድቦ ሥራ ላይ ለማዋል ምርታማነትንና የምርት ጥራትን ለማሳደግ በድምር ውጤት በምርት ዓይነት በመጠን፣ በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ የተጀመሩ ጥረቶች ለምሳሌ የካይዘን፣ የቤንችማርኪንግ ትግበራዎች ይበልጥ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡

ረ. **የማስፈፀሚያ ፋይናንስ፡-** ባለፉት አራት ዓመታት የታክስ ሪፎርሙንና የታክስ አስተዳደር ሥርዓቱን ተፈፃሚ በማድረግ የሀገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ እና የውጭ የልማት ፋይናንስ ለማሳባሰብ ከፍተኛ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በዚህም መልካም ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ ሆኖም ከውጭ የሚፈለገውን የልማት ፋይናንስ በጊዜ ከማግኘትና የልማት ፕሮጀክቶችን የግንባታ ሂደት ከማፋጠን አንፃር ከፍተኛ ተፅዕኖ እንደነበረው ታይቷል፡፡ በቀጣይ የሀገር ውስጥ ገቢ አቅማችንን በላቀ ደረጃ በማሳደግ እና የውጭ የልማት ፋይናንስ ፍሰትን ትርጉም ባለው ደረጃ በማሻሻል በሚፈለገው ጊዜ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡

ከፍ ብሎ በዝርዝር የቀረቡና በአፈፃፀም ሂደት ያጋጣሙ ፈተናዎችን ለማቃለል በየደረጃው እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ እነዚህ እርምጃዎች የኢኮኖሚ ዕድገቱ ፈጣንና ቀጣይ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ ለሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድም እንደ መልካም ተሞክሮ ተወስደዋል፡፡

# ክፍል ፪
# የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012)

# ክፍል ፪
# የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012)

## ምዕራፍ I
## የዕቅዱ መነሻዎች፣ ልዩ የትኩረት መስኮች፣ ዓላማዎችና መሠረታዊ አቅጣጫዎች

### 1.1 የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻዎች

የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ይዘትና ዋና ዋና ግቦች በአግባቡ ለመወሰን መነሻ የሆኑ ወሳኝ ጉዳዮችን በግልፅ ማመላከት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ይህም የዕቅዱን ይዘትና ዋና ዋና ግቦች በግልፅና በተጨባጭ ለማስቀመጥ፣ ዕቅዱም ተግባራዊ የሚደረግ፣ ተግባራዊ ሲደረግም የሚፈለገውንና አግባብ ያለው ውጤት የሚያመጣ ሆኖ መፈፀሙን ለመከታተል፣ ለመደገፍና ለማረጋገጥ ያግዛል፡፡ በመሆኑም ዋና ዋና የዕቅዱ መነሻዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

#### ሀ. የአገራችን ራዕይ እንደመነሻ

ሁለተኛው የአምስት ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በሀገራችን የተጀመረውን የትራንስፎርሜሽንና የህዳሴ ጉዞ በማፋጠን በ2017 ዓ.ም ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሳለፍ በሚደረገው ጥረት ወሣኙን ምዕራፍ የያዘ ሲሆን፣ የዜጐችን ዕኩል የልማት ተሳታፊነትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና በዚህም ልማታዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ እና አንድ የጋራ ማህበረሰብ ለመገንባት የላቀ አስተዋፅኦ ያለው ዕቅድ ነው፡፡ ስለሆነም የዕቅዱ ዋና መነሻ በ2017 ዓ.ም ኢትዮጵያን የመጀመሪያ ረድፍ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ የማሰለፍ ሀገራዊ ራዕይ ነው፡፡ ስለሆነም በቀጣዩ የአምስት ዓመት የዕቅድ ዘመን ውስጥ እስከ 2012 ድረስ የሚከናወኑ የልማት ተግባራት ወደዚህ ግብ በሂደት በአስተማማኝ የሚያደርሱን መሆን አለባቸው፡፡

#### ለ. አገራዊ እና የሴክተር ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች እንደመነሻ

የሀገራችንን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ለማምጣት፣ በየደረጃው የሕዝቡን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የዲሞክራሲ ሥርዓታችንን ለመገንባት በሚገባ የተዘረዘሩ አገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች ተዘጋጅተው በመተግበር ላይ ናቸው፡፡ እነዚህ ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች ከአንድ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ተሻጋሪ ከመሆናቸውም በላይ እስከአሁን ባለው ትግበራ መልካም ውጤቶች እያስገኙና ለህዳሴ ጉዞአችን ጽኑ መሠረት እየጣሉ የመጡ ስለሆኑ በማክሮ እና በሴክተሮች ደረጃ በሚዘጋጀው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርማሽን ዕቅድ እንደመነሻ ይወሰዳሉ፡፡

#### ሐ. የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም እንደመነሻ

የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ እየተጠናቀቀ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ተተኪው የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዝግጅት በሰፊው እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ከዚሁ በመነሳትም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በመጀመሪያ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተመዘገቡ መልካም ውጤቶችንና በትግበራ ሂደት የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች የበለጠ ተጠናክረው ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ የበለጠ ውጤቶች ለማስገኘት እና ያጋጠሙ ፈተናዎችን በማስወገድና ወደ መልካም አጋጣሚዎች በመቀየር የሚዘጋጀው ዕቅድ ተፈፃሚነት ይበልጥ ስለሚጠናከር እንደመነሻ ተወስዷል፡፡ ከዚህም ሌላ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ወቅት የተጀመሩና በግንባታ ላይ ያሉ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ኘሮጀክቶች በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ ተካተው መጠናቀቅ ስለአለባቸው እንደመነሻ ይወሰዳሉ፡፡

### መ. አገራችን የተስማማችባቸው የድህረ-2015 የልማት ግቦች እንደመነሻ

የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሲዘጋጅ የሚሊንየም የልማት ግቦችን ማሳካት እንደ አንድ መነሻ ተወስዶ ሰፊ ሥራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ የሚሊኒየም የልማት ግቦች ተብለው ከተያዙት ስምንቱ ግቦች መካከል አብዛኛዎቹን ለማሟላት የተቻለ ሲሆን ቀሪዎቹንም ለማሳካት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመንም እ.ኤ.አ ከ2016 እስከ 2030 ያለውን ጊዜ የሚሸፍኑ አዲስ አለም አቀፍ "ዘላቂ የልማት ግቦች" (Sustainable Development Goals) የሚባሉት ተዘጋጅተው በውይይት ላይ ይገኛሉ፡፡ ሀገራችንም አፍሪካን ወክለው ከሚደራደሩ አምስት አገሮች አንዷ ናት፡፡ አፍሪካም የጋራ አቋሟን ቀድማ አዘጋጅታለች፡፡ በዚህም መሠረት በ2015 መስከረም ላይ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የሚፀድቀውን ይህንን የልማት ግቦች ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሃገራችን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ልማት ቅደም ተከተል ጋር በተጣጣመ መንገድ ተግባራዊ እንዲሆኑና ሀገራችንም ኃላፊነቷን እንድትወጣ ያስችላል፡፡ በተጫማሪ በ50 ዓመታት ውስጥ በኢንደስትሪ የዳበረችና የበለፀገች አፍሪካን እውን ለማድረግ በአፍሪካ ሕብረት መሪዎች ጉባኤ ያፀደቀውን "አጀንዳ 2063" ራዕይንና ዝርዝር ኘሮግራሙን ግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ይሆናል፡፡

### ሠ. አለም አቀፍ እና ከባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን እንደመነሻ

በአሁኑ ዘመን የዓለም ኢኮኖሚ ሁኔታ ፈጣን ተለዋጭነት የሚታይበት ነው፡፡ እነዚህ ለውጦች እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በመልማት ላይ የሚገኙ አገሮች ኢኮኖሚ ላይ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራሉ፡፡ ለምሣሌ የኤክስፖርት ዕቅዎች ዋጋ መዋዥቅ ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡ ዕቅዱ ሲዘጋጅ የንግድ፣ የኢንቨስትመንት እና የቴክኖሎጂ አዝማሚያዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡፡

ከዚህ ሌላ የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሶስት ጉዳዮችን በተለይ መነሻ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በመጀመሪያ የአለም የንግድ ድርጅት እና የክፍለ-አህጉር የንግድና ኢኮኖሚ ቀጠናዎች አባል ለመሆን የተለያዩ ዝግጅቶች እና የድርድሮች ሂደቶች ስናከናውን ቆይተናል፡፡ ባለፉት ዓመታት ኢኮኖሚያችን በፍጥነት እያደገ በመምጣቱ እና በቀጣይ የማደግ አቅሙ ሳቢያ የውጪ አካላትን ትኩረት እየሳበ ይገኛል፡፡ በቀጣይም ዕድገታችን በተፋጠነ ቁጥር እነዚህን ሂደቶች እንዲፋጠኑ ገፍተው መምጣታቸው አይቀርም፡፡ ስለሆነም ቀጣዮቹ አስር ዓመታት በተለይም ደግሞ የመጀመሪያዎቹ አምስት አመታት በዓለም የንግድ ድርጅት አባልነት እና በአህጉር /ክፍለ-አህጉር/ የነፃ የንግድ ቀጠና አባልነት በብቃት ለመሳተፍ እና የአገራችንን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስቀጠል የመወዳደር አቅማችንን ይበልጥ የምናጐለብትባቸው ጊዜያት እንደሆኑ መነሻ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ከዚህ አንፃር በሁለተኛ ደረጃ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ የኢኮኖሚያችንን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት በአጠቃላይ የማሳደግ ጉዳይ ቢሆንም በተለይ ደግሞ የማኑፋክቸሪንግ አቅማችንን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ፣ የኤክስፖርት ምርቶቻችንን ተወዳዳሪነት ከፍ ማድረግ እና በታዳጊነት ደረጃ ላይ የሚገኙ ዘርፎችን ቢያንስ በአህጉራችን ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማብቃት ለዕቅዳችን መነሻ መደረግ አለባቸው፡፡

ሦስተኛው ጉዳይ የለሙ አገሮች አነስተኛ ኢኮኖሚ ላላቸው አገሮች የሰጡት የቀረጥና ኮታ ነፃ የገበያ ዕድሎች የሚመለከት ነው፡፡ እስከአሁን ባለው ሁኔታ አገራችን በስፋት ተጠቅማለች ማለት አይቻልም፡፡ እነዚህ የገበያ ዕድሎች በመልካም ፈቃድ የተሰጡ ስለሆነ በማንኛውም ጊዜ ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በስፋትና በተጠናከረ ሁኔታ በወቅቱ መጠቀም የግድ ይላል፡፡ በዚህም ኤክስፖርታችን ይስፋፋል፣ ውጭ ምንዛሪ ግኝታችን ይጠናከራል፣ በሂደትም የኢኮኖሚው ዘላቂ ተወዳዳሪነት እየጐለበተ ይመጣል፡፡ በመሆኑም ለዕቅዱ ዝግጅት መነሻ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

## 1.2 የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ልዩ የትኩረት መስኮች

የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) በመሠረቱ የመጀመሪያውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻዎች፣ ዓላማዎችና የትኩረት አቅጣጫዎች የሚያስቀጥል ሆኖ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈፃፀም ሒደት የተመዘገቡ ውጤቶች፣ በአፈፃፀም ሒደት ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችና መልካም ተሞክሮዎች እንደ መነሻ ተወስደዋል፡፡ ይህም ሆኖ ሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ልዩ ትኩረት ማድረግ ያለባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሀ) ግብርና በዚህ ዕቅድ ዘመንም የልማታችንና ፈጣን ዕድገታችን የማይተካ አስተዋፅኦ የሚያደርግና የዘመናዊ አምራች ዘርፍ ዕድገት ዋና ምንጭ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ ከዚህ አኳያ ለውጥ ማምጣት የጀመሩትን የስትራቴጂክ የምግ ሰብሎች ምርታማነትና ጥራት የበለጠ ከማሳደግ በሻገር የላቀ ዋጋ የሚያወጡ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችና የኤክስፖርት ምርቶች ላይ የልማት ቀጣናን ማዕከል ያደረገ ርብርብ በማድረግ ልዩ ነትኩረት ይሰጣል፡፡ በዚህም መሠረት የመስኖ ግብርና የአበባ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሥራን በከፍተኛ ደረጃ ማስፋፋት ላይ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በምርት ሂደት ውስጥ ተዋና የሆኑ የአርሶ-አደሩና የአርብቶ-አደሩ የቤተሰብ ግብርና ተጠናክሮ የሚቀጥል ሆኖ ለአርሶ-አደሩ የተማሩ ወጣቶችና የግል ባለሀብቱ ቅንጅት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡ ይህንን ለማድረግም በግብርና ልማትና ግብይት ውስጥ ያሉ የሥርዓት ማነቆዎችን በአስተማማኝ ደረጃ መፍታት ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

ለ) ራሱን የቻለ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ራእይ መቀመጡና ላለፉት 10 ዓመታት በተከታታይ የተመዘገበውን ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማስቀጠልና የመካከለኛ ገቢ ራዕዩን ለማሣካት በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚመዘገበው እመርታና ከዚሁ ጋር በኢኮኖሚው አወቃቀር ላይ የሚጠበቀው ለውጥ በቀጣዩ አምስት ዓመት የልማት ዕቅድ ዘመን ልዩ ትኩረት የተሰጠው መሆኑ፣

ሐ) የኢኮኖሚው የማምረት አቅም ላይ ለመድረስ ቅልጥፍና መጨመርና የአምራች ዘርፎች /ማኑፋክቸሪንግ እና ግብርና/ በሚመረቱ ምርቶች ለጥራት፣ ለምርታማነት እና ተወዳዳሪነት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራና ይህንንም ለማስፈፀም ቀደም ብሎ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን የተጀመረው ካይዘን በስፋትና በጥልቀት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል፣ የቤንች ማርኬንግ እንቅስቃሴም እንደሚስፋፋ ግልፅ ግቦች መቀመጣቸው፣

መ) በጠቅላላ ፍላጎትና አቅርቦት መካከል ለሚታየው መዛባት ልዩ ትኩረት መሰጠቱና ፈጣን እድገት የማስመዝገብ ግብም ይህን የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ከማስተካከል አኳያ እንዲቃኝ ለማድረግ ልዩ ትኩረት መሰጠቱ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ይህ መዛባት ሁሉት መልክ አለው፡፡ በቁጠባና በኢንቨስትመንት መካከል ያለው ክፍተት በየጊዜው እየሰፋ መሄዱና በሌላ መልኩ ደግሞ በወጪና በገቢ ንግድ መካከል ያለው ክፍተት እየሰፋ መሄዱ ናቸው፡፡ እነዚህ ደግሞ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ይህን መዛባት ለማስተካከል የግልና የመንግስት ቁጠባን የማስፋፋትና የወጪ ንግድ ምርቶችን ምርታማነት ጥራትና ተወዳዳሪነት የማሣደግ እንቅስቃሴ ከመቸውም ጊዜ የላቀ ጥረት እንደሚጠይቅና ይህንንም ለማሳካት ግልፅ ግቦች መቀመጣቸው፣

ሠ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ፕሮጀክቶች ማኔጅመንት አቅምን የማጎልበት ስራ በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል የፖሊሲና ስትራቴጂ ማዕቀፍ መዘጋጀቱና ይህም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በተለይ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን /የግድቦች ግንባታ፣ የመንገድ ግንባታ፣ የመስኖ ግንባታ… ወዘተ/ የማስተዳደርና የመምራት እንዲሁም በተያዘላቸው ወጪ እና ጊዜ የመፈፀም አቅም እስካሁን በተገኘው ተሞክሮም በተሻለ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ግብ መጣሉ፣

ረ) የከተማነት መስፋፋት (Urbanization) ፈጣን እድገትና መዋቅራዊ ለውጥ አስተዋፅኦ የጎላ እንዲሆን ለማስቻል እና ከሚጠበቀው ፈጣን ኢንዱስትራላይዜሽን እንቅስቃሴ ጋር ለማጣጣም ለከተማ አስተዳደርና አመራር ልዩ ትኩረት መሰጠቱ፣

ሰ) ለሀገር ውስጥ የግል ባለሀብቶች ትራንስፎርሜሽን ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ ይህም በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በተለይም ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶችን በማምረት ላይ ለሚገኙት ተቋማዊ፣ ሪጉላቶሪና የፋይናንስ ድጋፍ በመስጠት አቅማቸውን በማሳደግ /ምርታማነት፣ ጥራትና ተወዳዳሪነት/ እና በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩትን ደግሞ ልዩ ልዩ ማበረታቻዎችን በመስጠት ወደ አምራች ዘርፉ /ማኑፋክቸሪንግ/ እንዲገቡ በማድረግ የሚገለፅ ነው፡፡ በተጨማሪም በአነስተኛና ጥቃቅን ደረጃ የሚገኙትን ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ እና ከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ የማሸጋገርና በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩትን ደግሞ በተደራቢ ለራሳቸቸው የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በማምረት የገቢ ምርትን በመተካት ላይ እንዲያተኩሩ አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት ይገለፃል፡፡ የሀገር ውስጥ ባለሀብቱን እንዳመችነቱ ከውጭ ባለሀብቱ ጋር በማቀናጀት የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማፋጠን ይገለፃል፡፡

ሸ) የተጀመረውን ፈጣን ዕድገት ለማስቀጠል የሰው ኃብት ልማቱን በቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ እንዲደገፍ ለማድረግ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ በዚህ ረገድ ዋናው ጉዳይ የትምህርትና ጤና አገልግሎትን ተደራሽነት እና ጥራት በማረጋገጥ የሥራ ኃይሉን የተማረና ጤናማ ከማድረግ በተጨማሪ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀም በማስቻል ጥራቱን በማሳደግ ዕውቀት ያለውና ተወዳዳሪ የሥራ ኃይል በመፍጠር ለሚጠበቀው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ቁልፍ ሚና እንዲጫወት ማስቻል ነው፡፡ በመሆኑም ከሀገሪቱ የዕድገት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማፋጠን ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡

ቀ) ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂን በማዘጋጀትና በመተግበር ከአፍሪካ ግንባር ቀደም ናት፡፡ ከዚህ አንፃር የአካባቢ ሙቀት ሳቢ ጋዞችን ልቀት በመቀነስ አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት የእንስሳትና የሰብል ምርታማነትን በማሳደግ የአርሶ/አርብቶ አደሩን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፣ የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ ደንን መጠበቅና ማልማት፣ ከታዳሽ ኃይል ምንጭ የኤሌክትሪክ ኃይል በሰፊው ማመንጨትና ዘመናዊና ኃይል ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በትራንስፖርት፣ በኢንዱስትሪና በህንፃ ኮንስትራክሽን ዘርፎች በመጠቀም ረገድ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡

ተ) ከላይ የተዘረዘሩ ሥራዎችን ስንሠራ የፖለቲካ ኢኮኖሚው ኪራይ ሰብሳቢነት የበላይነት ከያዘበት ወደ ልማታዊ የበላይነት ወደያዘበት የበላይነት ትራንስፎርሜሽን እንዲረጋገጥ ማድረግ የሞት ሽረት ሥራ የሆነበት የዕቅድ ዘመን ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በአንድ በኩል ልማታዊነትና የሚጐለብቱ ድጋፎችን በጥራት በማቅረብ በሌላ በኩል የኪራይ ሰብሳቢነት ዋነኛ ምንጭ ሆነው የተለዩትን ጉዳዮች በልዩ ትኩረት በማድረቅ ኪራይ ሰብሳቢነት፣ ሙስናና ብልሹ አሠራሮችን በቁጥጥር ሥር በማዋል ልማታዊነት የበለጠ እንዲጐመራና የበለይነት እንዲይዝ የሚደረግ ይሆናል፡፡ ይህ እንዲሆንም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡ ህዝባችን የሥራው ባለቤት ሆኖ እንዲሠማራ ይደረጋል፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከቱት የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትኩረት መስኮች ከዚህ በታች ቀጥሎ በቀረቡት የዕቅዱ ዓላማዎች፣ መሠረታዊ አቅጣጫዎች እና በቀጣይም በማክሮ-ኢኮኖሚና በዘርፉ ዕቅዶች ቀርበዋል፡፡

## 1.3 የዕቅዱ ዓላማዎች

የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓላማዎች እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2017 ሀገራችንን የመጀመሪያ ደረጃ መካከለኛ ገቢ (Lower Middle Income) ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተቀመጠውን ሀገራዊ ራዕይ ለማሳካት የተጀመረውን ፈጣን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽንና ሕዳሴ ጉዞ በላቀ ደረጃ ለመፈፀም የሚያስችሉ ይሆናሉ፡፡ በዚህም መሠረት ዕቅዱ የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት፡፡

ሀ) የተረጋጋ ማክሮ-ኢኮኖሚ በመከተል በኢኮኖሚው መታየት የጀመሩትን የሚዛኖች ክፍተቶች በማስተካከል ኢኮኖሚውን በአማካይ በ11 በመቶ ማሳደግና ለሀገሪቱ ራዕይ መሳካት አስተዋጽዖ ማድረግ፣

ለ) አገራዊ የኢንጂነሪንግና ፋብሪኬሽን አቅማችንን በማሳደግና የአምራች ዘርፎች ምርታማነትን፣ ጥራትንና ተወዳዳሪነትን በማጐልበት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ትራንስፎርሜሽን ማጐልበት፣

ሐ) የሕዝቡን የተደራጀ አቅም በቀጣይነት መገንባትና የልማቱ ባለቤትና ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል፣

መ) ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግስትን በማጠናከር ልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚን መገንባት፣

## 1.4 የዕቅዱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች

የሁለተኛው አምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሠረታዊ አቅጣጫዎች በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሠረታዊ አቅጣጫዎች ላይ የተገነቡ ሲሆን ዕቅዱን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት በሚያስችል መልኩ ለመምራትና ከፍ ብሎ የተቀመጡ ዋና ዋና ዓላማዎችን በቀጣይነት ለማሳካት የሚያስችሉ እና ለዋና ዋና ሴክተሮች ዕቅዶችም እንደመነሻ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ እነዚህ መሠረታዊ አቅጣጫዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) የተጀመረውን ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ማስቀጠል፣

ለ) የኢኮኖሚው የማምረት አቅም ላይ ለመድረስ ቅልጥፍና መጨመር እና አምራች ዘርፎችን በማጐልበት በጥራት፣ በምርታማነትና በተወዳዳሪነት የላቀ ዕድገት ማምጣት፣

ሐ) የተፋጠነ የሀገራዊ ባለሃብት ትራንስፎርሜሽን ማምጣትና ብቁ የልማት ኃይል ማድረግ፣

መ) የኮንስትራክሽን ዘርፍ አቅም በማጐልበት የመሠረተ ልማት ተደራሽነትን መጨመርና የአገልግሎቱን ጥራት ማረጋገጥ፣

ሠ) የከተሞችን ፈጣን ዕድገት በአግባቡ በመምራትና በማስተዳደር ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው ፈጣን ዕድገት አስተዋፅዖ እንዲጐለብት ማድረግ፣

ረ) የሰው ሃብት ልማትንና የቴክኖሎጅ አቅም ግንባታን ማፋጠንና ዘላቂነቱን ማረጋገጥ፣

ሰ) የመንግሥትን የማስፈፀም አቅም በመገንባት እና የህዝቡን ተሳትፎ በማጐልበት ዲሞክራሲያዊና ልማታዊ መልካም አስተዳደር ማስፈን፣

ሸ) የሴቶችንና የወጣቶችን ብቃት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣

ቀ) ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት፣

ከፍ ብሎ ከ"ሀ" - "ቀ" የተዘረዘሩት መሠረታዊ አቅጣጫዎች ማብራሪያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1.4.1 የተጀመረውን ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ማስቀጠል፣

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት (2008-2012) ሁሉን-አቀፍ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ማስቀጠል የሀገራችንን የህዳሴ ጎዞ ከማሳካት፣ የኢኮኖሚ መሠረተ-ልማቶችንና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለዜጎች በፍጥነትና በጥራት ተደራሽ ከማድረግ፣ የሥራ ስምሪትን በማሳደግ ድህነትን ትርጉም ባለው ሁኔታ ከመቀነስና በሂደትም ከማስወገድ እና የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ከማሻሻል አንፃር ቁልፍ ስትራቴጂ ነው፡፡ በመሆኑም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አጠቃላይ ኢኮኖሚው በ2017 ኢትዮጵያን የመጀመሪያ ደረጃ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተቀመጠውን ሀገራዊ ራዕይ ሊያሳካ በሚያስችል ፍጥነት እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ፈጣን ብቻ ሳይሆን ቀጣይና ሁሉን አቀፍ ይሆናል፡፡ በዚህም እንደአለፉት ዓመታት ሁሉ የሀገሪቱ ዜጎች በየደረጃው በሚካሄዱ የልማት ሥራዎች ዕኩል ተሳታፊና

ፍትሀዊ ተጠቃሚ መሆናቸው ይቀጥላል፡፡ በተለይ ለማኑፋክቸሪንግ ፈጣን ዕድገት ብሎም የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ዕውን ለማድረግ የተደራጀና የተቀናጀ እንቅስቃሴ ይደረጋል፡፡

የኢኮኖሚ ዕድገቱ እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ መሠረተ ሰፊ እና በዋናነት ግብርና የዕድገቱ ዋና ምንጭ ሆኖ ኢንዱስትሪ በላቀ ፍጥነት የሚያድግበትና፣ የአገልግሎት ዘርፍ የበኩሉን ሚና የሚጫወትበት ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ኢኮኖሚው በአማካይ በየአመቱ በ11 በመቶ እንደሚያድግ ትንበያው ያመለክታል፡፡ ይህ ስትራተጂክ ግብ ሊደረስበት እንደሚችል ያለፉት ዓመታት አፈፃፀሞች ማረጋገጫ ናቸው፡፡ ይህም ሆኖ በግልጽ መታወቅ ያለበት ጉዳይ የተቀመጠው አማካይ ዓመታዊ ዕድገት ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅና ከዓመት ወደ ዓመት እየከበደና እየተወሳሰበ የሚሄድ መሆኑን ነው፡፡ በአጠቃላይ በሁሉም የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች የሥራ ሥምሪትን በማሳደግ፣ ምርታማነትን በማሻሻል፣ ጥራትንና ተወዳዳሪነትን በማረጋገጥ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚጠበቀውን የመዋቅር ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራ ሲሆን ይህንኑ ለማረጋገጥ በዘርፎች መካከል ጠንካራ ትስስር እና ተመጋጋቢነት እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ የሚጠበቀው ፈጣንና ቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

ከዚህ አኳያ የማኑፋክቸሪንግን መሠረት የሚያሰፉ የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በከፍተኛ ፍጥነት እንዲበራከቱና ትላልቅ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችም ጉልበትን በስፋት የሚጠቀሙ ሆነው ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ ለማድረግ ይሰራል፡፡

### 1.4.2 የኢኮኖሚው የማምረት አቅም ላይ ለመድረስ ቅልጥፍና መጨመርና አምራች ዘርፎችን በማጐልበት በጥራት፣ በምርታማነትና በተወዳዳሪነት የላቀ ዕድገት ማምጣት፣

የሀገራችን ኢኮኖሚ አሁን ባለበት ደረጃ የማምረት አቅሙ ላይ ለመድረስ ገና ከፍተኛ ቅልጥፍና መጨመር እንዳለብን ይታወቃል፡፡ የአምራች ዘርፍ የምንላቸው የግብርና የተለያዩ ንዑስ ዘርፎችና ከኢንዱስትሪም የተለያዩ የማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፎች ናቸው፡፡

ከግብርና አኳያ ሲታይ የዕድገቱ ምንጭ በአነስተኛ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ቤተሰቦች በሚካሄድ ልማት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በእጃችን ያሉ ቴክኖሎጅዎችን በአግባቡ አባዝተን ብናሰራጭና የኤክስቴሽን ሥርዓቱን ባስቀመጥነው አቅጣጫ መሠረት ተግባራዊ ብናደርግ ማለትም የማስፋት ስትራተጅያችንን በልማት ሠራዊት አማካይነት ብንፈፅም እጅግ የላቀ የምርታማነትና የምርት መጠን መድረስ የሚያስችለን ይሆናል፡፡ ስለሆነም ከግብርና አኳያ በሰብል ልማትም ሆነ በእንስሳት ሀብት ልማት እንዲሁም የተፈጥሮ ሃብት ልማትና የመስኖ ሥራን ጨምሮ የማምረት አቅማቸው ድረስ እንዳንደርስ ያገዱንን ማነቆዎች መፍታት ወይም ቅልጥፍናን ማሻሻል የልማታችን ዋነኛ አቅጣጫ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ አሁን ባለው ቴክኖሎጅ የማምረት አቅማቸው ደረጃ ለተቃረቡ ሞዴሎች ተጨማሪ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን የማዘጋጀት የማባዛትና የማሰራጨት ሥራ በተጨማሪነት መሠራት ያለበት ይሆናል፡፡ ከስትራቴጂክ የምግብ ሰብሎች ምርታማነት መሥመር በተጓዳኝ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ የማምረት አቅማችንን ማሻሻል ያለብን በሆርቲካልቸርና በእንስሳት ሀብት ልማት እንዲሁም ሌሎች የኢንዱስትሪ ግብዓቶችና የኤክስፖርት ምርቶች ላይ ይሆናል፡፡

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን መሠረት ለማስፋት የግብርና ምርቶችን በግብአትነት የሚጠቀሙ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪያችን ማስፋት አማራጭ የሌለው ተነፃፃሪ መወዳደሪያችን ነው፡፡ የአገራዊ ባለሃብቶቻችንንም በስፋት እንዲሰማሩ ማድረግ የምንችለውም በዚሁ ዘርፍ ነው፡፡ ይህ በመሆኑ የፋብሪካ አካላቶችንና መለዋወጫዎችን በአገር ውስጥ ለማምረት የሚያስችል ገና ያልተሚጠጠ የማምረት አቅም እንዳለንና በዚህም ዘርፍ ማነቆ የሆኑ የቴክኖሎጅ የመቅዳት ዲዛይን የማድረግ፣ ፍብረካ እና የማላመድ ሥራዎችን በፍጥነት ለመሻገር መሥራትና እንዲሁም የተመረቱትን ፍብረካዎች የማሠራጨትና የማስተግበር ሥራ ዋነኛው አቅጫጫችን ይሆናል፡፡ ይህን በማድረግም አዳዲስ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት እንችላለን፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ በአገር ውስጥ ሊፈበረኩ አቅማችን ያልደረሰባቸውን የካፒታል ዕቃዎችን ኢምፖርት በማድረግ የዘርፉን ዕድገት ማፋጠን ይኖርብናል፡፡

ስለሆነም የኢንጂነርንግና ፋብሪኬሽን አቅማችንን ማጐልበትና የማምረት አቅማችን መድረስ የምንችልበት ደረጃ በማድረስ የዘርፉን ትራንስፎርሜሽን ማረጋገጥ ዋነኛ አቅጣጫ መሆኑ በትኩረት መያዝ ያለበት ይሆናል፡፡

ከላይ የተገለፁትን ሥራዎች በማከናወን በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የያዝነው ፈጣን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዕድገት ሊረጋገጥ የሚችለው በአገር ውስጥ ባለሃብቶች እና በተመረጡ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስተሮች አማካይነት ሰፊ ኢንቨስትመንት ሲካሄድ ነው፡፡ በመሆኑም ነባር ኢንዱስትሪዎችም ሆነ አዳዲሳቹ ይህንን ተልዕኮ ማሳካት የሚችሉት የቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸውን፣ ምርታማነታቸውን፣ የጥራት አመራር አቅማቸውን እና ተወዳዳሪነታቸውን በቀጣይነት እንዲገነቡ አስፈላጊው ድጋፍና ተቋሞቹም የሚጠበቅባቸውን ጥራት ሲያሟሉ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ይህን ሥራ እንዲሰሩ ተልዕኮ የተሰጣቸው ኢንስቲትዮቶች፣ ዩኒቨርስቲዎች፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት እና የምርምር ተቋማት ወ.ዘ.ተ. በቂ አቅምና አመራር የሚያገኙበትና ስኬታማ ከሆኑ አገሮች የቴክኒክና ሙያተኛ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት የምንከተለው አቅጣጫ ይሆናል፡፡

ጥራትን፣ ምርታማነትን እንዲሁም ተወዳዳሪነትን ለማጐልበት አገራችን የመረጠችው የካይዘን የአመራር ፍልስፍና በዚሁ የዕድገትና ትራንስፍሮሜሽን ዕቅድ ዘመን በሁሉም ትኩረት በተሰጣቸው ኢንዲስትሪዎችም ሆነ ለኤክስፖርት ዘርፎች ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲተገበር አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ ቤንችማርኪንግ ሌላው የምርታማነት ጥራትና ተወዳዳሪነት ማምጫ ዘዴ በመሆኑ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

### 1.4.3 የተፋጠነ የሀገራዊ ልማታዊ ባለሀብት ትራንስፎርሜሽን ማምጣትና ብቁ የልማት ኃይል ማድረግ

ፈጣን፣ ሁሉን-አቀፍና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት የግሉ ዘርፍ ዋና የዕድገት አንቀሳቃሽ ኃይል እንዲሆንና ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት፣ ኢንቨስትመንት፣ የሥራ ሥምሪት፣ የወጭ ንግድና የቴክኖሎጂ ሽግግርጉልህ ሚና እንዲኖረው የማድረግ አቅጣጫ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

በአምራች ዘርፍ ማለትም በግብርና ኢንዱስትሪና አይሲቲ ዘርፎች ቀደም ብለው የተሰማሩ ልማታዊ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ለይቶ መደገፍና ማጠናከር እንደተጠበቀ ሆኖ አዳዲስ ልማታዊ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በመመልመልና በማብቃት በግብርናና በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ እንዲሁም በአይሲቲ በስፋት እንዲሳተፉ ማድረግ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተለየ ትኩረት የሚሰጠው ሥራ ይሆናል፡፡ ይህም በስኬት እንዲፈፀም መንግስት የተጠናከረና ቀጣይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

በዚህም መሠረት የሀገር ውስጥ ባለሀብቱን ልማታዊ ተሳትፎ የሚገቱ የማኔጅመንት፣ የቴክኖሎጂና የፋይናንስ አቅርቦት ችግሮችን ለመቅረፍ መንግስት የተቀናጁ የመፍትሄ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡ በተጨማሪም የውጭ ባለሀብቶችን በጥራት በመመልመል ከሀገር ውስጥ ልማታዊ ባለሀብቶች ጋር በማስተሳሰር መደገፍና በተለይ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ የተመረጡ መስኮች እንዲሰማሩ ማድረግ ሌላው የዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡ ይህም የማኔጅመንት ዕውቀትና ክህሎት እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር በመፍጠር የሀገር ውስጥ ልማታዊ ባለሀብቶችን አቅም ለማሳደግ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡

እጅግ ጠባብ የሆነውን ባለሃብቱ የሚመለመለበት መሠረት በማስፋት በመጀመሪያ ደረጃ በአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተሰማሩትን ወደ መካከለኛና ትልልቅ ኩባኒያዎች በማሸጋገር እንደዚሁም በቅድሚያ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩትን ቀጥሎም በንግድና አገልግሎት ዘርፎች የተሰማሩትን በጥንቃቄ

በመመልመና አስፈላጊውን የቴክኖሎጂና የፋይናንስ አቅርቦት በማመቻቸትና የአመለካከትና የኢንዱስትሪ አመራር አቅም እንዲያገኙ በማድረግ የልማታዊ አቅጣጫ እንዳይዙ ይደረጋል፡፡

### 1.4.4 የኮንስትራክሽንን ዘርፍ አቅም በማጐልበት፣ የመሠረተ ልማት ተደራሽነትን መጨመር እና የአገልግሎቱን ጥራት ማረጋገጥ፣

የአንድ አገር ዕድገት የሚገለጽበትና የዕድገትም ውጤት የሆነው መሠረተ ልማት በከፍተኛ ደረጃ ማስፋፋትና ጥራቱ የተጠበቀና በዋጋም ተወዳዳሪ የሆነ አቅርቦት መኖር ለአገሩ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ብሎም ኢኮኖሚያዊ ተወዳዳሪነት ያለው ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ባለፉት ዓመታት የኢኮኖሚ መሠረተ ልማትን ለማስፋፋት ከፍተኛ ጥረት የተደረገና የሚያበረታታ ውጤት የተገኘ ቢሆንም አሁንም የመሰረተ ልማት አገልግሎት ዕጥረት ከፍተኛ የዕድገት ማነቆ ነው፡፡ ዘርፉ የሚጠይቀው ኢንቨስትመንት ከፍተኛ ከመሆኑም ባሻገር ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚፈልግ ነው፡፡ የማስፈፀም አቅምን ከመገንባት አንፃር ባለፉት አምስት ዓመታት በርካታ ሥራዎች የተከናወኑ ቢሆንም የዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይልና የማስፈፀም አቅም አሁንም ውስን በመሆኑ በተለይ የትላልቅ ፕሮጀክቶችን ዲዛይንና ግንባታ በሚመለከት በቀጣዮዎቹ አምስት ዓመታት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በውጭ አቅም ላይ ጥገኛ መሆናችን አይቀርም፡፡

የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት በሚፈለገው ደረጃ ለማሳደግ ባለፉት የዕቅድ ዓመታት በዘርፉ የታዩ ፈታኝ ሁኔታዎች የማቃለልና መልካም ተሞክሮዎችን አጠናክሮ መቀጠል ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡ በዘርፉ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት እንዲካሄድ ማድረግ፣ ከውጭ የሚገቡ ቁሳቁሶችን በአገር ውስጥ እንዲመረቱ ማድረግ፣ በዚህም የውጭ ምንዛሪ ፍላጎቱ ላይ የሚፈጠረውን ጫና መቀነስ አሁንም ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ ይህ ማለት በሁሉም የመሠረተ ልማት መስኮች የሰለጠነ የሰው ኃይልና የፋይናንስ ዕጥረትን ማቃለል፣ የፕሮጀክት፣ ፋይናንስ የማፈላለግና የማስተዳደር አቅም የማጎልበት፣ የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር የማምጣት፣ወዘተ. ማለት ነው፡፡

የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት በ2017 ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሳለፍ የተቀመጠውን ራዕይ ለማሳካት የሚያስፈልገውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት በሚደግፍ ደረጃ፣ ጥራትና ፍጥነት እንዲያድግና ኢኮኖሚው ተወዳዳሪ እንዲሆን እንዲሁም ሁሉን-አቀፍ ዕድገት እንዲመጣ ለማድረግ የላቀ ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራል፡፡

የግሉ ዘርፍ በመሠረተ ልማት ዘርፍ የሚጠበቅበት ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑ እንዳግባቡ ለግሉ ዘርፍ በተፈቀዱ ንዑስ ዘርፎች ውስጥ ያለው ተሳትፎ እንዲያድግ አስፈላጊውን ማበረታቻና ድጋፍ ማድረግ የተለየ ትኩረት የሚሰጠው ነው፡፡ በግሉ ዘርፍ ከሚጠበቁ ተሳትፎዎች ውስጥ ጥራት ያለው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እንዲበረታታ በማድረግ የገንዘብ ብቻ ሳይሆን የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲያመጣ ማድረግ ነው፡፡ አብዛኞዎቹ መሠረተ-ልማቶች አሁንም በመንግስት መቅረባቸው እንደሚቀጥል የሚታወቅ ቢሆንም በተመረጡት ላይ በመንግስትና በግል አጋርነት ሊለሙና ሊቀርቡ የሚችሉበት መንገድ በጥናት ተለይቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ከመሠረተ ልማት ዘርፍ ዕድገት ጋር የተገናኙ የድህረ-2015 ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የልማት ግቦች ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ሀገራዊ የልማት አጀንዳዎች ጋር ተጣጥመው ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

በአጠቃላይ የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት ዕድገት ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፣ አዳዲስ የገበያ ዕድሎችን ለመፍጠር፣ የሸቀጦች ዋጋን ለመቀነስ፣ የተወዳዳሪነት አቅም ለመፍጠር፣ የቀጠና የኢኮኖሚ ትስስርን ለመፍጠር ካለው ፋይዳ አኳያ የመንገድ፣ የባቡር፣ የደረቅ ወደብ፣ የአየር ትራንስፖርት፣ የኢነርጂ፣ የቴሌኮም፣ የውሃና የመስኖ ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡

በሌላ በኩል የመንግስትና የግል ኢንቨስትመንት እየተስፋፋ መምጣት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እንዲስፋፋ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ መንግስትም የዘርፉን አቅም ለማሳደግ በርካታ የአቅም ግንባታ ሥራዎች በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ኢኮኖሚያችን ፈጣንና ቀጣይ የዕድገት ምዕራፍ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን አቅም የሚጠይቅ ሆኗል፡፡ ይህም በመሆኑ መንግስት ኢንዱስትሪው የሚመራበትን የኢትዮጵያ የኮንትራክሽን ፖሊሲ ማዕቀፍ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል፡፡

ኢንዱስትሪው እያደገና ለሥራ ፈጠራ የበኩሉን አስተዋፅኦ እያደረገ ቢሆንም ዘርፉ በብዙ ችግሮች ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ከእነዚህ ችግሮች መካከል የአቅም ውስንነት፣ ዝቅተኛ የቴክኖሎጂ መሠረት፣ ዝቅተኛ ስልጠትና ውጤታማነት እንዲሁም ቀላል የማይባል የሀብት ብክነት በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የእነዚህ ችግሮች ድምር ውጤት በአምራች ዘርፉ ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ስለሆነም በአንድ በኩል እያደገ የመጣውን የኮንስትራክሽን ፍላጎት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ተወዳዳሪነታችንን ማጎልበት እንዲሁም በሌላ በኩል ከኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር የተላቀቁ በርካታ ልማታዊ ባለሀብቶችን ማፍራትና አቅማቸውን መገንባት ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ማኔጅመንት እና በዘርፉ የተሠማራውን የሰው ኃይል በዓይነትና በመጠን በሚፈለገው ደረጃ አሠልጥኖ አሁን ያለውን የሰው ኃይል ዕጥረት መፍታት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

### 1.4.5 የከተሞችን ፈጣን ዕድገት በአግባቡ በመምራትና በማስተዳደር ለአጠቃላይ ፈጣን ዕድገት አስተዋፅ እንዲያጐለብት ማድረግ

የአገራችን አከታተም ሁኔታ በአፍሪካ ደረጃ ካለው አማካይም ጋር ሲነፃፀር ገና በዝቅተኛ ደረጃ ያለ ነው፡፡ ይህም ሆኖ የነባር ከተሞች ዕድገትም ሆነ ከገጠሩና ግብርና ፈጣን ዕድገት ጋር ተያይዞ አዳዲስ ከተሞችን ጨምሮ በፈጣን ሁኔታ እያደጉ ይገኛሉ፡፡ ይህ ፈጣን ዕድገት በኘላን ላይ ተመስርቶ በአግባቡ የማይመራና የማይተዳደር ከሆነ ከተሞቻችን በጣም የተጨናነቁና የተፋፈጉ፣ በቂ መሠረተ ልማት የማይቀርብላቸውና አስፈላጊውን የሥራ ዕድል የማይፈጠሩ ለኢኮኖሚ ፈጣን ዕድገት ሳይሆን ድቀት የራሣቸውን አስተዋፅዖ ማበርከታቸው አይቀርም፡፡ በመኖሪያ ቤት እጥረትና የደቀቁ ሰፈሮች በመበራከታቸው ምክንያት ለኑሮ የማይመቹ ይሆናሉ፡፡

ስለሆነም ከተሞቻችንን በአግባቡ በተጠና የስፓሻል ኘላን ጀምሮ በተለያዩ የኘላን ደረጃዎች በማዋቀር በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች ይህንኑ መሠረትና ታሳቢ ያደረገ አቅጣጫ ይዘን መጓዝ ይገባናል፡፡ በዚህም መሠረት ከተሞቻችን በሚቀጥለው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በቂ የሥራ ዕድል የሚፈጥርባቸው፣ የመኖሪያ ቤት እጥረት የተቃለለባቸው፣ ከገጠሩ ልማት ጋር በአግባቡ የተሳሰሩና ለግብርና ዘርፍ ምርታማነት ዕድገት አስፈላጊውን አስተዋፅዖ የሚያበረክቱ፣ ለመሠረተ ልማት አቅርቦታቸው በተለይም ለመንገድ፣ ለውሃና ለመብራት እንዲሁም ለፍሳሽና የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ በቂ ትኩረት የተሰጠባቸው እንዲሆኑ የማድረግ አቅጣጫ እንከተላለን፡፡ የትራንስፖርት፣ የቴሌኮም እንዲሁም የመረጃና ኮሙኒኬሽን ተጠቃሚ የኀብረተሰብ ክፍል የተበራከተባቸው እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገሩ ከተሞች እንዲኖሩን የማድረግ የታቀደ ሥራ የመሥራት አቅጣጫም እንከተላለን፡፡

ያልተማከለ የከተሞች አስተዳደርና የፋይናንስና ገቢ ሥርዓት እንዲሁም የከተማ ነዋሪው ቀጥተኛ የልማትና የመልካም አስተዳዳር የተደራጀ ተሣትፎ ወሣኝ በመሆኑ ይህንኑ ቀልጣፋ በሆነ መንገድ እንዲከተል የማድረግ አቅጣጫ እንከተላለን፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን አቅጣጫዎች በማጐልበት ከተሞቻችን ለአገራዊ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ትራንስፎርሜሽን የበኩላቸውን የማይተካ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል፡፡

### 1.4.6 የሰው ኃብት ልማትንና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታን ማፋጠንና ዘላቂነቱን ማረጋገጥ

እንደሚታወቀው የአንድ አገር ትልቁ ሃብት የሰው ኃይል ነው፡፡ በመሆኑም የሰው ኃይል ልማት ከሁሉም የልማትና ኢንቨስመንት ጉዳዮች በላይ ወሣኝ ነው፡፡ ወሣኝነቱ ለተያያዝነው ኢኮኖሚ ዕድገት ብቻ ሣይሆን ለዘላቂ የሕዳሴ ጉዞ እንደጽኑ መሠረተ ልማት የሚወሰድ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ዘላቂና ስኬታማ ሊሆን የሚችለው ቴክኖሎጂን የማልማትና የመጠቀም አቅም ተፈጥሮ ሲጠናከር ይሆናል፡፡

የሚለማው የሰው ኃይል ለዛሬ ብቻ ሳይሆን በሩቁ አይቶ አገራዊ ራዕይ ላይ ሲደረስ ኢኮኖሚው የሚፈልገው የሰው ኃይል ዓይነትና መጠን ግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡ ከዚህም አልፎ በሂደት ወደ ከፍተኛ መካከለኛ ደረጃ ብሎም ብልፅግና ደረጃ ሊወስደን የሚችል የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ከወዲሁ ማሰብና በተቀናጀ ሁኔታ በረጅም ጊዜ ዕይታ ውስጥ ማቀድ ይጠይቃል፡፡

የሰው ሀብት ልማት በወሳኝነት የሥራ ሀይሉ ጤናማ፣ የተማረና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም የሚችል እንዲሆን በማድረግ ይበልጥ ምርታማ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የትምህርት አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ጥራቱን በማሳደግ ዕውቀት ያለውና ተወዳዳሪ የሥራ ሀይል መፍጠር ኢኮኖሚው በፍጥነት እንዲያድግ ከማድረግ አኳያ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ በተለይ የመካከለኛና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚከተሉት ስትራቴጂ የገበያውን የሠለጠነ የሰው ሃይል ፍላጎትን መሠረት በማድረግ ለጥራት ቅድሚያ ትኩረት የመስጠት አቅጣጫ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ ከሀገራችን የትምህርት ግቦች ጋር የሚጣጣሙ የድህረ 2015 ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የልማት ግቦች የዕቅዱ አካል ተደርገው እንዲፈፀሙ ይደረጋል፡፡ የሰው ኃብት ልማት በወሳኝነት የሥራ ኃይሉን ጤና በማስጠበቅ ይበልጥ ምርታማ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ጥራቱን በማሳደግ ጤናማና ተወዳዳሪ የሥራ ሀይል መፍጠር ኢኮኖማው በፍጥነት እንዲያድግ ከማድረግ አኳያ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

ከሀገሪቱ የዕድገት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ፣ ለዘላቂ ልማት የቴክኖሎጂ ፈጠራን የሚደግፍና በአጠቃላይም ለምርምርና ልማት አስፈላጊውን ተቋም መፍጠርና በገንዘብ መደገፍ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት ለሀገሪቱ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ፖሊሲና ስትራቴጂ ፈጣን ትግበራ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡

ተስማሚና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ማፈላለግ፣ መምረጥ፣ ማለማመድና መጠቀም ብሎም ማበልፀግ ምርታማነትን ከፍ ከማድረግ አኳያ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ከምርምርና ልማት እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ምርምርና ልማት በመንግስት ብቻ ሳይሆን በግሉም ዘርፍ እንዲካሄድ ይበረታታል፣ የቴክኖሎጂና ሌሎች የምርምር ግኝቶችን መሠረት በማድረግም በምርምር ተቋማት፣ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መካከል ቅንጅት እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ ዩኒቨርሲቲዎችና የዘርፍ ምርምር ተቋማት ከዚህ አኳያ የራሳቸውን የማይተካ አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

### 1.4.7 የመንግሥትን የማስፈፀም አቅም በመገንባት እና የህዝቡን ተሣትፎ በማጐልበት ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ መልካም አስተዳደርን ማስፈን

ባለፉት አስር ዓመታት ሥራ ላይ በዋሉ መርሐ-ግብሮች በኢኮኖሚ ዕድገትና በማህበራዊ ልማት አመርቂ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ መልካም ልማታዊ አስተዳደርን ለማስፈንም በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ህብረተሰቡን በተደራጀ መልኩ የማንቀሳቀስ ሥራዎች ተጀምረዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የህዝቡን የተደራጀ እንቅስቃሴ ማዕከል ባደረጉ ሥራዎች የሚያበረታቱ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በመልካም ልማታዊ አስተዳደር ዙሪያ የተደረሰበት የአፈፃፀም ደረጃ ግምገማ በቀጣይ ጠንካራ ሥራዎች መሥራትና መልካም ልማታዊ አስተዳደርን ይበልጥ ማስፈን ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት እንዳለበት

ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት መልካም ልማታዊ አስተዳደርን ይበልጥ ለማስፈን ህብረተሰቡን ማዕከል ያደረጉ፣ የተቀናጁና የተደራጁ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዳችን እና ለህዳሴ ጉዟችን ዋነኞቹ አደጋዎች ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት ናቸው፡፡ እነዚህን አደጋዎች ለመዋጋትና በአሸናፊነት ለመውጣት ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ይበልጥ መጠናከርና ኢኮኖሚውን በልማታዊ መንገድ በብቃት መምራት ይጠበቅበታል፡፡ ለዚህም የመንግስትን ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ይበልጥ የማስፈፀምና አገልግሎቶችን ለዜጎች በብቃት የማድረስ ዋና ተልዕኮ የተሸከሙት ልማታዊ የፖለቲካ አመራሩና የሲቪል ሰርቪሱ የሰው ኃይሉን በሁሉም የአስተዳደር ዕርከኖች በተከታታይ አጠናክሮ ማብቃት የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ቁልፍ ተግባር ይሆናል፡፡ ይህንን በማድረግም ተወዳዳሪ የሆነ በሥራው ውጤት እየተመዘነ የሚገባውን ቦታ ይዞ አስተዋፅኦውን የሚያበረክት የፖለቲካ አመራርና ሲቪል ሰርቪስ ሠራተኛ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በትግበራ ላይ ያሉት ሁሉም የሪፎርም ፕሮግራሞች በሁሉም የአስተዳደር ዕርከኖች በተሟላ ሁኔታ እንዲተገበሩና ለውጡ ሥር እንዲሰድና ተቋማዊ ባህል እንዲሆን ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡ ከዚህ አኳያ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ኪራይ ሰብሰቢነትንና ሙስናን ከምንጩ ለማድረቅ በመሬት አስተዳደር፣ በታክስ አስተዳደር፣ በመንግስት ግዢ አስተዳደር እንዲሁም በንግድ ውድድር ሥርዓት የተጀመሩት የሪፎርም ሥራዎች የበለጠ ጥልቀት እንዲያገኙ፣ዳር እንዲደርሱና ተቋማዊ ባህል እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

የታክስ ሥርዓቱን የማሻሻል ሥራ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ በማድረግ የግብር ከፋዩ ገቢና ንብረት በትክክል የሚታወቅበት፣ ህጋዊ ዕውቅናና ጥበቃ የሚያገኝበት ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ የጉምሩክ ሥርዓት ልማታዊ ባለሀብቱን ተወዳዳሪ እንዲሆን የሚያደረግ ይሆናል፡፡ የሽያጭ ማሽኖችን መጠቀምና ግብይት የማካሄድ ሥራ በሁሉም የንግድ ማህበረሰብ አካላት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የተጀመረው የከተማ መሬትና በመሬቱ ላይ ያለውን ንብረት በዘመናዊ መረጃ ሥርዓት የመመዝገብና የማወቅ፣ በመሬቱ ላይ ማን ምን መብት እንዳለው የተሟላና ወቅታዊ መረጃ የመያዝ፣ ህጋዊ ዕውቅናና ጥበቃ እንዲያገኙ የማድረጉ ሥራ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ በዚሁ መረጃ ላይ በመመሥረት መሬት ይበልጥ ልማታዊ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል በዕቅድ የሚመራ የመሬት አቅርቦት ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

የገቢና መሬትን ጨምሮ የንብረት መረጃና የንግድ እንቅስቃሴ መረጃ ሥርዓት መፍጠር በኢኮኖሚና በፖለቲካው መስክ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን በማስፈን ረገድ የሚጫወተውን ሚና ከግምት ውስጥ በማስገባት በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ሥራው ዓላማውን እንዲያሳካ ልዩ ትኩረት ይደረጋል፡፡ የዜጎች መሠረታዊ የመረጃ ሥርዓት በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ወደ ተሟላ ትግበራ እንዲሸጋገርና ዜጎች ብሔራዊ መታወቂያ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ ሌሎች መሠረታዊ መረጃዎች (የጋብቻ፣ የሞት፣ የወሊድ እና የልደት) የበለፀጉ ሀገሮችን የልምድ ተሞክሮ በመውሰድ ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ የማድረግ ሥራ ይጀመራል፡፡

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የህዝብ ተመራጮችን አቅምና የሕዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎን ለማጐልበትና የተደራጀ እንቅስቃሴ ለማጠናከር ተቋማዊ አቅምን ለማሳደግና እንዲሁም የዴሞክራሲ ባህልን ለማጎልበት ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡ በዚህም መሠረት በየደረጃው የሚገኙ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤቶች፣ የፌደሬሽንና የብሔረሰብ ም/ቤቶች፣ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድና ቅርንጫፎች፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ የዕንባ ጠባቂ ተቋምና ትምህርት ቤቶች የዲሞክራሲ ባህልንና አቅምን ከማዳበርና የዴሞክራሲ ልምድ በተጠናከረ ሁኔታ ከማካሄድ አኳያ ያላቸው ሚና ይበልጥ እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡

የፌዴራልና የክልል የህዝብ ተወካዮች ም/ቤቶች ሕግ የማወጣት ሥልጣናቸውን በብቃት እንዲፈጽሙ እና አስፈጻሚውን አካል የመከታተልና የመቆጣጠር ተልዕኳቸውን በተሟላ ሁኔታና በብቃት እንዲወጡ ለማድረግ አቅማቸው ይበልጥ እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡ በተለይም ህዝቡ በቅርቡ በስፋት የሚሳተፍባቸው የቀበሌና የወረዳ ም/ቤቶች በጥራት እንዲመረጡና ተልዕኳቸውን በብቃት እንዲወጡ ልዩ ትኩረት ተሠጥቶ ይሠራል፡፡ የፌዴሬሽና የብሔረሰብ ምክር ቤቶች የፌዴራል ሥርዓቱ ይበልጥ እንዲጠናከር የህገ-መንግስቱ መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበራቸው በህዝብ ዘንድ የበለጠ እንዲሰርፅ፣ የብሔሮች፣ ብሔራሰቦችና ሕዝቦች እኩልነትና አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር ጉዞ ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ የሐይማኖቶች እኩልነትና የሴኩላሪዝም መርሆዎች ይበልጥ እንዲሰርፁና የመቻቻልና የጋራ ዕሴቶች እንዲጎለብቱና አክራሪነትና ጽንፈኝነት ቦታ እንዲያጡ የሚያደረጉ እንቅስቃሴዎች በሚመለከታቸው አካላት በመቀናጀት በትጋት የሚሠራ ይሆናል፡፡

ከፍ ብሎ በተጠቀሱ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት የበለጠ ጥልቀትና ስፋት እንዲያገኝ በት/ቤቶች፣ በኃይማኖት ተቋማት፣ በመንግስት የተለያዩ አካላት፣ በብዙኃን ማህበራት፣ በሙያ ማህበራት፣ በምርምርና ሀሳብ አመንጪ ተቋማት፣ በህዝብና በግል ሚዲያዎች በዕቅድ ላይ የተመሠረተ ብሔራዊ እንቅስቃሴ ይደረጋል፡፡ በሕዝብ ተመርጠው በየደረጃው ባሉ ምክር ቤቶች ከሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆነ የምክር ቤት መቀመጫ ባይኖራቸውም ለመድበለ ፓርቲ ዲሞክራሲና ለሀገራቸው ዕድገት አስተዋፅዋቸውን ማበርከት ከሚፈልጉ ፓርቲዎች ጋር በጋራ ጉዳዮች ላይ ምክክሮችና ክርክሮች በተከታታይ ይደረጋሉ፡፡ በተመሳሳይ መንገድ የመንግስትም ሆነ የግል ኤሌክትሮኒክስ ህትመት ሚዲያዎች ከመንግስት ጋር ገንቢ ምክክር የሚያደርጉባቸው መድረኮች በተከታታይና በማያቋርጥ ሁኔታ በማመቻቸት ሚዲያዎች ለሀገራችን ልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እንዲሁም የመልካም አስተዳደር መስፈን በጐ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል፡፡

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ዜጎች የመደራጀት መብታቸውን ተጠቅመው የዴሞክራሲ ሥርዓቱ ይበልጥ እንዲጠናከር ለማድረግ ለሙያና ለብዙኃን ማህበራት ምቹ ሁኔታዎች ይበልጥ እንዲጠናከሩ ለማድረግ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ከዚህ አንፃር የምሁራንና የባለሙያዎች የተደራጀ ተሳትፎ እንዲጎለብት ምቹ ሁኔታዎች ይበልጥ እንዲጠናከሩ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡ በተመሳሳይ የብዙኃን ማህበራት በተለይም የወጣቶችና የሴቶች ማህበራት እንደዚሁም የባለኃብቶች አደረጃጀት ነፃነታቸውን ጠብቀው እንዲጠናከሩ በማድረግ በዴሞክራሲ፣ በልማት እና መልካም አስተዳደር እንቅስቃሴ ያላቸውን በጎ ሚና ለማሳደግ ዕቅድ ተይዞ ይሠራል፡፡

### 1.4.8 የሴቶችንና የወጣቶችን ብቃት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ

የሴቶችን ሁለንተናዊ ብቃት በማሳደግ በሀገሪቱ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር ግንባታ እንዲሁም በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በተደራጀ አኳኋን የነቃና ግንባር ቀደም ተሳትፎ እንዲያደርጉና ከውጤቱም በተገቢው መንገድ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም የሴቶችና የወጣቶች ፓኬጆች ትስስርና ተመጋጋቢነት ባለው ሁኔታ ተፈጻሚ እንዲሆን ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን የተለያዩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ዘርፎች የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ከግምት ውስጥ ያስገቡ እንዲሆኑ፣ ሴቶች በህብረት ሥራ ማህበራት በመደራጀት የብድርና ቁጣባ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የሥርዓተ ጾታ ዕኩልነትን ማረጋገጥ፣ ለሴት ተማሪዎች ምቹ የትምህርት ከባቢ ሁኔታ መፍጠር፣ የሴት መምህራን ቁጥርን ከፍ ማድረግ፣ የጾታ ዕኩልነትን በሥራ ሥምሪት፣ በመሬትና ሌሎች ቋሚ ዕሴቶች ባለቤትነት ማሳደግ፣ ጐጂ የሆኑ ባህሎችን ለምሳሌ በሴቶች ላይ በሚደረግ የኃይል ጥቃት፣ በፍትህ ሥርዓቱ ተደራሽነት እና በሴቶች ላይ ህገወጥ ድርጊት ፈፃሚዎች ላይ ወቅታዊ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም ሴቶችን በፖለቲካና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ዕኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠውና ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

ወጣቶች የዛሬ አፍላ የልማትና የዴሞክራሲ ኃይሎችና የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎች እንደመሆናቸው በትምህርት የታነፁና የተገነባ አቅም እንዲኖራቸው ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡ የወጣቶችን ሁለንተናዊ ብቃት በማሳደግ በሀገሪቱ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም ልማታዊ አስተዳደር ግንባታ እንዲሁም በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በተደራጀና በተቀናጀ አኳኋን የነቃና ግንባር ቀደም ተሳትፎ እንዲያደርጉና ከውጤቱም በተገቢው መንገድ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ ይህንን በማድረግ በሀገሪቱ ወጣቶች አካበባቢ ከሥራ ስምሪት ጋር ተያይዞ የሚታየውን የተሳታፊነትና ፍትሐዊ ተጠቀቃሚነት ጥያቄ ለመመለስ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡ እንዲሁም የሴቶችና የወጣቶች ፓኬጆች ትስስርና ተመጋጋቢነት ባለው ሁኔታ ተፈጻሚ እንዲሆን ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን የተለያዩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ዘርፎች የወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ከግምት ውስጥ ያስገቡ እንዲሆኑ፣ ወጣቶች በህብረት ሥራ ማህበራት በመደራጀት የብድርና ቁጣባ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በተለይም ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከቴክኒክ ሥልጠና ማዕከላት ተመርቀው የሚወጡ ወጣቶች ያገኙትን ዕውቀትና ክህሎት የወደፊት የሀገራችን ተስፋ በሆኑ አምራች ዘርፎች ማለትም ግብርና፣ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችና ዲጂታል ቴክኖሎጂ ላይ ተሠማርተው የወደፊት የሀገራችን ልማታዊ ባለሀብቶች መፍለቂያ እንዲሆኑ ሁሉን-አቀፍ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ከሴቶችና ወጣቶች ብቃትና ተጠቃሚነት ማሳደግ ጋር በተገናኘ የድህረ 2015 የልማት አጀንዳ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ግቦች ሀገራችን ለዘርፉ ካስቀመጠቻቸው የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር ተጣጥመው ተፈፃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

### 1.4.9 ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት

ሁሉን-አቀፍ ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት መገንባት ወሳኝ ነው፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አስፈላጊ እርምጃዎች አስቀድሞ ካልተወሰዱ እ.ኤ.አ. እስከ 2050 ባለው ጊዜ በኢትዮጵያ የሙቀት መጠን ከ1.7 ዲግሪ ሴንቲግሬድ እስከ 2.1 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሊያድግ እንደሚችል ተገምቷል፡፡ ይህ የሙቀት መጠን የምግብ ዋስትና እንዳይረጋገጥ፣ የተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች (ለምሳሌ ወባ፣ ትኩሳት፣ ኮሌራና የመሳሰሉት) በወረርሽኝ መልክ እንዲከሰቱ፣ የመሬት መጎሳቆልና የመሠረተ ልማት ውድመት እንዲከሰት ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህንን አደጋ ለመቀነስና የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችልና ኢትዮጵያን በ2017 የመጀመሪያ ደረጃ መካከለኛ ገቢ ላይ ከደረሱ ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተቀመጠውን ራዕይ መሠረት የደረገ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ ተቀርጾ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የትግበራ መርሐ ግብር እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በተፋሰስ ልማት በህዝባዊ ንቅናቄ ሰፊ ጥረት የተደረገና አጥጋቢ ውጤት እየተመዘገበበት ሲሆን በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመንም ይህ መልካም ጅምር በተለየ ትኩረት ተጠናክሮ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በዚህ የተፋሰስ ልማት ላይ ተመሥርቶ የሀገራችንን ወጣቶች በዘመናዊና የላቀ ዋጋ በሚያወጡ የግብርና ሥራዎች ላይ በማሠማራት ራሳቸው ተጠቅመው ሀገራችንን በማልማት የበኩላቸውን የማይተካ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል፡፡

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት የተፈጥሮ ልማትና ሀብት አስተዳደርን ማጠናከር፣ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር መጣጣም (Adaptation to Climate Change) እና የከባቢ አየር ሙቀት ሳቢ ጋዞች ልቀት ሥርየት (Mitigation of Greenhouse Gases) ዋነኛ ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ማድረግ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስትራቴጂ መሠረታዊ አቀጣጫዎች የከባቢ ሙቀት ሳቢ ጋዞች ልቀትን በመቀነስ ለምግብ ዋስትናና ለአርሶ-አርብቶ አደሩ ገቢ መሻሻል በሚረዳ ሁኔታ የሰብልና የእንስሳት ምርትን ማሻሻል፣ የካርቦን ልቀትን ለመቀነስና ለኢኮኖሚና ሥነ ምህዳራዊ አገልግሎት ለማዋል ካለው ፋይዳ አኳያ ደንን መጠበቅና ማልማት፣ ከታዳሽ ኃይል ምንጭ የኤሌክትሪክ ኃይል በሠፊው በማመንጨት ለአገር ውስጥና ለቀጠናው ገበያ ማቅረብ እና ዘመናዊና ኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በትራንስፖርት፣ ኢንዱስትሪና በሕንጻ ኮንስትራክሽን ዘርፎች በመጠቀም ረገድ ዕመርታዊ ለውጥ ማምጣት የተለየ ትኩረት ይሰጣል፡፡

የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ በሁሉም ደረጃዎች በሚዘጋጁ ዕቅዶች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እንዲካተትና ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ አፈፃፀሙን በቅርብ የመከታተል፣ የመገምገምና አስፈላጊ ድጋፎችን የመስጠት አቅጣጫ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት ጠንካራ ተቋም መፍጠር፣ የሚያስፈልገውን የፋይናንስ ፍሰት ለማሟላትና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ትብብርን ለማጠናከር የመንግስትን፣ የግሉን ዘርፍ እና የልማት አጋሮችን የሚያሳትፍ የተቀናጀና የተደራጀ ጥረት ይደረጋል፡፡ በአረንጓዴ ኢኮኖሚ መስክ የምርምር ተቋማት እንዲገነቡ ወይም እንዲስፋፉ፣ የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲሁም ሌሎች ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ይደረጋል፡፡ ከአረንጋዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ጋር በተያያዘ የድህረ 2015 የልማት አጀንዳና ሌሎች ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የልማት ግቦች ማሳካት ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

### 1.5 የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች ትንበያ ማጠቃለያ

በዕቅድ ሰነዱ በማክሮ ኢኮኖሚ እና በዋና ዋና የኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት ዘርፎች በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት (2007) የተደረሰበትን የአፈፃፀም ግምትና በዚሁ ላይ በመመሥረት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የመጨረሻ ዓመት (2012) ይደረስባቸዋል የተባሉ ዋና ዋና ግቦች ትንበያ ማጠቃለያ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል (ሠንጠረዥ 1.1)፡፡

ሠንጠረዥ1.1 የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የማክሮኢኮኖሚና የዋና ዋና ዘርፎች ዋና ዋና ግቦች ትንበያ ማጠቃለያ

| ተ.ቁ. | የዘርፍ አመልካች | መለኪያ | መነሻ ዓመት (2007) | የሚደረስበት ግብ (2012) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | **የማክሮ ኢኮኖሚ አመልካቾች** | | | |
| | አጠቃላይ ኢኮኖሚ (Macro Economy) | | | |
| | ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት | መቶኛ | 11.4 | 10.8 |
| | የግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች ዕድገት | መቶኛ | 9.6 | 7.8 |
| | የኢንዱስትሪ ዘርፍ ዕድገት | መቶኛ | 22.2 | 17.2 |
| | የማኑፋክቸሪንግ ዕድገት | መቶኛ | 19.2 | 24.1 |
| | የአገልግሎት ዘርፍ ዕድገት | መቶኛ | 9.4 | 10.0 |
| | የአገልግሎት ዘርፍ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ | መቶኛ | 43.4 | 40.4 |
| | አገራዊ ኢንቨስትመንት ከጠቅላላ የሀገር ውሰጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 36.3 | 41.3 |
| | አገራዊ ቁጠባ ከጠቅላላ የሀገር ውሰጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 19.5 | 29.6 |
| | የወጪ ንግድ አገልገሎትን ጨምሮ ከጠቅላላ የአሀር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 12.8 | 20.6 |
| | የገቢ ንግድ አገልግሎትን ጨምሮ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 29.6 | 32.3 |
| | የሀገር ውሰጥ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውሰጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 14.4 | 18.8 |
| | የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውሰጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 12.9 | 17.2 |
| | የግል ቁጠባ (አገራዊ) | መቶኛ | 13.8 | 20.2 |
| | የመንግሥት ቁጠባ (አገራዊ) | መቶኛ | 5.7 | 9.4 |
| | ጠቅላላ የመንግስት ወጪ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 18.7 | 22.6 |
| | የካፒታል ወጪ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 10.1 | 14.4 |
| | የመደበኛ ወጪ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 8.6 | 8.2 |
| | የድህነት ተኮር ዘርፍ ወጪ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 11.7 | 14.6 |
| | የበጀት ጉድለት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ (በገበያ ዋጋ) | መቶኛ | -2.9 | -3.1 |
| | **የኑሮ ደህንነት ሁኔታ** | | | |
| | ከአጠቃላይ ድህነት መስመር በታች የሚኖረው ሕዝብ ብዛት | መቶኛ | 29.6(2003) | 16.7 |
| | **የስራ ስምሪትና ስራ አጥነት** | መቶኛ | | |
| | **የህዝብ ብዛት በሚሊዮን** | ቁጥር | 89.0 | 99.7 |
| | የህዝብ ብዛት ዕድገት በመቶኛ | መቶኛ | 2.4 | 2.2 |
| | በሥራ ላይ የተሰማራው የሰው ኃይል ከጠቅላላው ህዝብ ያለው ድርሻ በመቶኛ | መቶኛ | 53.1 | 53.1 |
| | የሥራ አጥነት መጣኔ በመቶኛ | መቶኛ | 4.5 | 3.2 |
| | የወጣት ጥገኛ ህዝብ መጣኔ በመቶኛ (Youth Dependency Ratio) | መቶኛ | 72 | 65 |
| | ዕድሜያቸው 65 እና ከዚያ በላይ የሆነ ህዝብ መጣኔ በመቶኛ (Old Age Dependency Ratio) | መቶኛ | 5.08 | 4.97 |
| | **የፋይናንሻል ሴክተር** | መቶኛ | | |
| | የባንክ ቅርንጫፎች ቁጥር | ቁጥር | 2322 | 4671 |
| | አነስተኛ የገንዘብ ተቋማት የሚቋቋሙባቸው ቀበሌዎች ከጠቅላላ የገጠር ቀበሌዎች | መቶኛ | | 50 |
| | **የወጪ ንግድ** | መቶኛ | | |
| | የማኑፋክቸሪንግ የወጪ ንግድ ገቢ ከጠቅላላው ያገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ | መቶኛ | 0.9 | 3.1 |
| | የግብርና ምርት የወጪንግድ ገቢ ከጠቅላላው ያገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ | መቶኛ | 4.4 | 6.5 |
| | የኢንዱስትሪ ምርቶች ወጪ ንግድ ከጠቅላላ የሸቀጦች ወጪ ንግድ ገቢ ያለው ድርሻ | መቶኛ | 17.7 | 30.4 |
| | የማኑፋክቸሪንግ የወጪ ንግድ ገቢ ከጠቅላላ የሸቀጦች ወጪ ንግድ ገቢ ያለው ድርሻ | መቶኛ | 13.4 | 25.9 |
| | የግብርና ምርቶች ወጪ ንግድ ከጥቅል አገራዊ ምርት ያለው ድርሻ | መቶኛ | 4.4 | 6.5 |
| | የኢንዱስትሪ ምርቶች ወጪ ንግድ ከጥቅል አገራዊ ምርት ያለው ድርሻ | መቶኛ | 1.1 | 3.6 |
| | የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢ ከጠቅላላው ያገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ | መቶኛ | 6.4 | 11.8 |
| 2 | **ግብርናና ገጠር ትራንስፎርሜሽን** | | | |
| | **የግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ** | መቶኛ | 41.1 | 35.6 |
| | **የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ** | መቶኛ | | |
| | በዋና ዋና ሰብሎች የሚገኘው ምርት መጠን | ሚ/ኩንታል | 270.3 | 414.0 |
| | የዋና ዋና ሰብሎች ተጨማሪ እሴት ከሀገር ውስጥ ምርት የሚኖራቸው ድርሻ | መቶኛ | 29.4 | 25.8 |
| | የአገዳ ሰብል ምርታማነት | ኩ/ሄክታር | 29 | 41.90 |
| | የአገዳ ሰብል ምርት | ሚ/ኩ | 115 | 169.2 |
| | የብርዕ ሰብል ምርታማነት | ኩ/ሄክታር | 19.5 | 30.9 |
| | የብርዕ ሰብል ምርት | ሚ/ኩንታል | 123 | 195.8 |
| | የጥራጥሬ ሰብል ምርታማነት | ኩ/ሄክታር | 16.4 | 24.0 |
| | የጥራጥሬ ሰብል ምርት | ሚ/ኩንታል | 24.4 | 37.4 |
| | የቅባት ሰብል ምርታማነት | ኩ/ሄክታር | 9 | 12.7 |
| | የቅባት ሰብል ምርት | ሚ/ኩ | 7.9 | 11.8 |
| | የቡና ምርታማነት | ኩ/ሄክታር | 7 | 11.1 |
| | የቡና ምርት | ሺ/ቶን | 548.2 | 1102.6 |

**ከሠንጠረዥ 1.1 …የቀጠለ**

| ተ.ቁ. | የዘርፍ አመልካች | መለኪያ | መነሻ ዓመት (2007) | የሚደረስበት ግብ (2012) |
|---|---|---|---|---|
| | **የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ** | | | |
| | ዝርያቸዉ የተሻሻሉ የዳልጋ ከብቶች ብዛት | በቁጥር | **779147** | **4902000** |
| | የዳልጋ ከብት ስጋ ምርታማነት | ኪ/ግ ካርካስ | 107 | 138 |
| | የስጋ ምርት | ሺ/ቶን | 1321 | 2103 |
| | የዲቃላ ከብቶች የወተት ምርታማነት | ሊትር በቀን | 8 | 12 |
| | የወተት ምርት | ሚ/ሊትር | 5304 | 9418 |
| | የዘመናዊ ቀፎ የማር ምርታማነት | ኪ/ግ በቆረጣ | 20 | 30 |
| | የማር ምርት | ሺ/ቶን | 60.7 | 123.9 |
| | **የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና አጠቃቀም** | | | |
| | ተክልሎ እንዲያገግም የተደረገ መሬት | ሚ/ሄክታር | 11.7 | 22.5 |
| | በማህበረሰብ ተፋሰሶች ስነ ህይወታዊ ዘዴዎች የተሸፈነ መሬት | ሚ/ሄክታር | 12.162 | 41.35 |
| | በዘመናዊ አነስተኛ መስኖ የለማ መሬት | ሚ/ሄክታር | 1.3 | 1.7 |
| | **የምግብ ዋስትና፣ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት** | | | |
| | የአደጋ መከላከልና ዝግጁነትን ለማጎልበት የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት | ሺ.ህ ቶን | 405 | 3000 |
| | አደጋ የሚያስከተለውን ጉዳት ለመከላከል የመጠባበቂያ የገንዘብ መጠን | ሚሊዮን ብር | 123 | 415 |
| | የገጠር ሴት አርሶ አደር ኤክስቴንሽን ተጠቃሚ መጣኔ | መቶኛ | 20 | 30 |
| | የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆነ ህዝብ | ሚሊዮን | 3.5 | 8.3 |
| | የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተመራቂ የሆኑ የቤተሰብ ሃላፊዎች | ሚሊዮን | 0.16 | 1 |
| | **የግብርና ግብዓት አቅራቦትና አጠቃቀም** | | | |
| | የቀረበ ምርጥ ዘር መጠን | ሚ/ኩንታል | 1873778 | 3559924 |
| | የቀረበ ማዳበሪያ መጠን | ሜትሪክ/ቶን | 1223309 | 2062106 |
| | **በአየር ንብረት ለዉጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት ግንበታ** | | | |
| | የአረንጓዴ ልማት ቴክኖሎጅ ተጠቃሚ የተደረጉ አባዎራ/እማወራዎች ብዛት | ቁጥር | | 100000 |
| | የተቀነሰ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠን | ሚ/ሜትሪክ ቶን | | 147 |
| | የአካባቢ ብክልትን ለማስቀረት የተወገዱ በካይ አደገኛ ነገሮች መጠን | ቶን | | 200 |
| | የደን ዘረፍ ለአጠቃላይ የአገር ዉስጥ ምርት ያበረከተዉ ድርሻ | መቶኛ | 4 | 8 |
| | የደን ሽፋን በመቶኛ | መቶኛ | 15.5 | 20 |
| 3 | **ኢንዱስትሪ** | | | |
| | ኢንዱስትሪ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 15.6 | 22.8 |
| | ማኑፋክቸሪንግ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው | መቶኛ | 4.6 | 8.0 |
| | መካከለኛና ከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 3.4 | 5.9 |
| | የማኑፋክቸሪንግ ወጪ ንግድ ከጠቅላላ የሸቀጦች ወጪ ንግድ ዋጋ የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 13.4 | 25.9 |
| | በመካከለኛና ከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ የሚፈጠረው የስራ ዕድል | ቁጥር | 380,000 | 750,000 |
| | አነስተኛና ጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 1.2 | 2.0 |
| | ከመካከለኛ እና ከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚገኝ የውጭ ምንዛሪ መጠን | ሚሊዮን ዶላር | | 4657 |
| 4 | **ማዕድን** | | | |
| | ማዕድን ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ | መቶኛ | 1.7 | 2.3 |
| | የወርቅ ምርት | ቶን | 14.421(2006) | 33.1 |
| | ከማዕድን ምርት የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ | ቢሊዮን ዶላር | 0.515(2006) | 3.2 |
| 5 | **መሠረተ ልማት** | | | |
| | **መንገድ** | | | |
| | ክረምት ከበጋ የሚያስኬድ የመንገድ ርዝመት | ኪ.ሜ | **120000** | 220000 |
| | በሁሉም አየር ፀባይ ከሚያስኬድ መንገድ ለመድረስ የሚወስደው ግዜ | ሰዓት | **1.5** | 0.8 |
| | በሁሉም አየር ፀባይ ከሚያስኬድ መንገድ ከ5 ኪ.ሜ. በላይ ርቀው የሚገኙ አከባቢዎች መጣኔ | መቶኛ | **33.6** | 13.5 |
| | በጥሩ ይዞታ ላይ የሚገኙ መንገዶች መጣኔ | መቶኛ | **70** | 80 |
| | የአስፋልት መንገዶች መጣኔ (ratio of Paved road) | መቶኛ | **13** | 16 |
| | የመንገድ ጥግግት | ኪ.ሜ/1000ሜ2 | **109** | 200 |
| | የመንገድ ጥግግት | ኪ.ሜ/1000ሰው | **1.3** | 2.3 |
| | **ባቡር** | | | |
| | አጠቃላይ የባቡር መንገድ ርዝመት | ኪ.ሜ | | 1545 |
| | የተጠናቀቁና ወደ አገልግሎት የገቡ የባቡር ፕሮጀክቶች በመቶኛ | መቶኛ | | 100 |
| | የቀላል ባቡር ትራንስፖርት ለማግኘት በአማካይ የሚጠበቅበት ጊዜ | ደቂቃ | **0** | 3 |
| | ዓመታዊ ብሔራዊ የባቡር መረብ የጭነት /Freight/ ትራንስፖርት አገልግሎት | በሚሊዮን ቶን | **0** | 12 |

ከሠንጠረዥ 1.1 …የቀጠለ

| ተ.ቁ. | የዘርፍ አመልካች | መለኪያ | መነሻ ዓመት (2007) | የሚደረስበት ግብ (2012) |
|---|---|---|---|---|
| | **ኢነርጂ** | | | |
| | የመብራት አገልግሎት ሽፋን | መቶኛ | 60 | 90 |
| | የኃይል ማመንጨት አቅም | ሜጋ ዋት | 2267 | 17346 |
| | የማከፋፈያ መስመር ግንባታ ርዝመት | ኪ.ሎ ሜትር | 12825 | 21728 |
| | ከውሀ የሚመነጭ ሃይል | ሜጋ ዋት | 1953.5 | 13957 |
| | ከንፋስ የሚመነጭ ኃይል | ሜጋ ዋት | 171 | 1222 |
| | ከጸሐይ የሚመነጭ ኃይል | ሜጋ ዋት | | 300 |
| | ከጂኦ ተርማል የሚመነጭ ኃይል | ሜጋ ዋት | 7 | 577 |
| | ከቆሻሻ የሚመነጭ ኃይል | ሜጋ ዋት | | 50 |
| | ከስኳር የሚመነጭ ኃይል | ሜጋ ዋት | | 474 |
| | ከባዮማስ የሚመነጭ ኃይል | ሜጋ ዋት | | 258 |
| | የኤሌክትሪክ አገልግሎት ያገኙ ደንበኞች ብዛት | ሚሊዮን ቁጥር | 2.455 | 6.955 |
| | አመታዊ የኤሌክትሪክ የነፍስ ወከፍ ፍጆታ | ጌዋሰ | 86 | 1269 |
| | አጠቃላይ የኃይል ብክነት | መቶኛ | 22.3 | 11 |
| | **ቴሌኮሙኒኬሽን** | | | |
| | የመደበኛ ስልክ ጥግግት በመቶኛ (tele density) | መቶኛ | 10.5 | 54.0 |
| | የመደበኛ ስልክ ተጠቃሚዎች ብዛት | ሚሊዮን ቁጥር | 3.1 | 10.4 |
| | የሞባይል ስልክ ተጠቃሚዎች ብዛት | ሚሊዮን ቁጥር | 40.0 | 103.6 |
| | የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብዛት | ሚሊዮንቁጥር | 9.6 | 56.0 |
| | የሞባይል አገልግሎት ስርፀት | መቶኛ | 43.9 | 100 |
| | የብሮድባንድ ኢንተርኔትና ዳታ ደንበኞች ብዛት | ሚሊዮንቁጥር | 1.59 | 39.1 |
| | የናሮው ባንድ ኢንተርኔትና ዳታ ደንበኞች ብዛት | ሚሊዮንቁጥር | 8 | 16.9 |
| | **ውሀ** | | | |
| | አጠቃላይ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፍን በዕትእ-2 ስታንዳርድ አገልግሎት ደረጃ | መቶኛ | 58 | 83 |
| | የገጠር የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፍን በዕትእ-2 ስታንዳርድ አገልግሎት ደረጃ | መቶኛ | 59 | 85 |
| | የከተማ መጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፍን በዕትእ-2 ስታንዳርድ አገልግሎት ደረጃ | መቶኛ | 51 | 75 |
| | በመካከለኛና ከፍተኛ መስኖ የለማ መሬት | ሄክታር | 658,340 | 954,000 |
| | **ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት** | | | |
| | የሎጅስቲክስ የአፈፃፀም ጠቋሚ (Logistics Performance Index ) | ቁጥር | 2.59 | 3.07 |
| | የገቢ ዕቃዎች ባህር ወደብ ላይ አማካይ የቆይታ ጊዜ | ቀን | 40 | 3 |
| | የሎጅስቲክስ ወጪ ከሀገሪቱ ጠቅላላ የሀገር ዉስጥ ምርት ያለዉን ድርሻ | መቶኛ | 30 | 22 |
| | በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የሚጓጓዘዉ የሀገሪቱ ጀነራል ካርጎ ሽፋን | መቶኛ | 30 | 90 |
| | የወጪ ጭነት በሀገር ዉስጥ በኮንቴይነር አሽጎ መላክ መጠን | መቶኛ | 7 | 100 |
| | በትራፍክ አደጋ ምክንያት በየ10000 ተሽከርካሪ የሚደርሰዉን የሞት አደጋ ብዛት | ቁጥር | 58 | 27 |
| | በራስ አቅም የገቢ ዕቃዎችን የማጓጓዝ አቅም | ቶን | 391000 DWT | 881000 DWT |
| | **አቪየሽን** | | | |
| | በዓለም አቀፍ የሲቪል አቪየሽን ድርጅት እንዲሟሉ የሚጠበቁ የሴፍቲና ሴኩሪቲ ኦዲት ጉድለቶች የተሟሉበት ደረጃ ምጣኔ | መቶኛ | 95 | 100 |
| | የገቢ መንገደኞች ማስተናገጃ ጊዜ | ደቂቃ | | 60 |
| | የወጭ መንገደኞች ማስተናገጃ ጊዜ | ደቂቃ | | 45 |
| | አዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት ዓመታዊ መንገደኞችን የማስተናገድ አቅም | ሚሊዮን | 5 | 18 |
| | አለም አቀፍ የበረራ ጣቢያዎች ብዛት | ቁጥር | 81 | 127 |
| 6 | **የከተማ ልማትና ቤቶች ኮንስትራክሽን** | | | |
| | በከተማ የልማታዊ ሴፍቲኔትፕሮግራም የተፈጠረ የሥራ ዕድል | በቁጥር | _ | 2,800,000 |
| | በከተማ ምግብ ዋስትና እጦት ለተጋለጡ ዜጎች የተደረገ የቀጥታ ድጋፍ | በቁጥር | _ | 1,050,000 |
| | በከተሞች የተገነቡ የመኖሪያ ቤቶች | በቁጥር | 157,070 | 750,000 |
| | የአረንጓዴ ልማትና የህዝብ መናፈሻ መሬት አጠቃቀም ሽፋን | በመቶኛ | _ | 30 |
| 7 | የሰው ሀብት ልማት | | | |
| | ትምህርትና ሥልጠና | | | |
| | የአንደኛ ደረጃ ንጥር ተሳትፎ በመቶኛ | መቶኛ | 95.2 | 100.0 |
| | የሥርዓተ ፆታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ጥምርታ | መቶኛ | | 1.0 |
| | ተግባር ተኮር ጎልማሶች ትምህርት ምጣኔ በመቶኛ | መቶኛ | | 95.0 |
| | በከ/ትምህርት ተቋማት የቅድመ ምረቃ ትምህርት ተሳትፎ | ቁጥር | 387565 | 597685 |
| | ሙያዊ ብቃታቸው የተረጋገጡ መምህራን መጣኔ በመቶኛ | መቶኛ | 20 | 70 |
| | የመምህር ተማሪ ጥምርታ | | | 1:19 |
| | ጤና | | | |
| | የጤና አገልግሎት ሽፋን በመቶኛ | መቶኛ | 94 | 100 |
| | ከአምስት ዓመት በታች ያሉ ህፃናት ሞት መጣኔ ከ1000 | ቁጥር | 68 | 30 |
| | ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ የህፃናት ሞት መጣኔ ከ1000 | ቁጥር | 46.4 | 19.3 |
| | የእናቶች ሞት መጣኔ ከ100000 | ቁጥር | 420 | 199 |
| | የጨቅላ ህፃናት ሞት መጣኔ ከ1000 | ቁጥር | 27 | 10 |
| | የህዝቡን የመኖር ዕድሜ (Life Expectancy) | ዓመት | 64.6 | 69 |
| | አጠቃላይ የውልደት መጠንን (Total Fertility Rate) | ቁጥር | 4.1 | 3 |
| | የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ምጣኔ (CPR) | መቶኛ | 42 | 55 |

ከሡንጠረዥ 1.1 ...የቀጠለ

| ተ.ቁ. | የዘርፍ አመልካች | መለኪያ | መነሻ ዓመት (2007) | የሚደረስበት ግብ (2012) |
|---|---|---|---|---|
| | በሰለጠኑ ባለሙያዎች በመታገዝ የወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን | መቶኛ | 41 | 95 |
| | ከ5 ዓመትበታች ያሉ የህፃናት መቀጨጭ/መቀንጨር (Stunting) | መቶኛ | 40 | 21 |
| | ከ5 ዓመት በታች ያሉ የህፃናት ክብደት መቀነስ (Wasting) | መቶኛ | 9.7 | 4.9 |
| | የፐንታቫለንት ሶስት ክትባት ሽፋን | መቶኛ | 82 | 96 |
| | የተሻሻለ የመጸዳጃቤት ያላቸው አባወራዎች/እማወራዎች ሽፋን | መቶኛ | 21 | 93 |
| | በኤች አይቪ/ኤድስ ቫይረስ አዲስ የሚያዙ ሰዎች መጠን (HIV/AIDS Incidence) | መቶኛ | 0.03 | 0.01 |
| | በአዮዱን የበለጸገ ጨው የሚጠቀሙ ቤተሰብ ሽፋን | መቶኛ | 15 | 80 |
| | የፐንታቫለንት ሶስት ክትባት ሽፋን | መቶኛ | 82 | 96 |
| | የተሻሻለ የመጸዳጃቤት ያላቸው አባወራዎች/እማወራዎች ሽፋን | መቶኛ | 21 | 93 |
| | በኤች አይቪ/ኤድስ ቫይረስ አዲስ የሚያዙ ሰዎች መጠን (HIV/AIDS Incidence) | መቶኛ | 0.03 | 0.01 |
| | በአዮዱን የበለጸገ ጨው የሚጠቀሙ ቤተሰብ ሽፋን | መቶኛ | 15 | 80 |
| | የማህበራዊ ደህንነት | | | |
| | የተቋቋሙና ድጋፍ የተደረገላቸው የድጋፍና እንክብካቤ ጥመረቶች (CCC) ብዛት /በቀበሌ/ | ቁጥር | 1324 | 17351 |
| | ማህበራዊ ድጋፍ /ሶሻል ሴፍቲኔት/ ያገኙ ዜጎች (በዓይነትና በገንዘብ) ብዛት | ቁጥር | 1204346 | 6434400 |
| | የማህበራዊና የስነልቦና ምክርና ድጋፍ አገልግሎት ያገኙ ተጠቃሚዎች ብዛት | ቁጥር | 167880 | 795293 |
| | የአካላዊ ተሃድሶ አገልግሎት ያገኙ አካል ጉዳተኞች ብዛት | ቁጥር | 208634 | 734941 |
| | የአረጋውያን ማዕከላት ብዛት | ቁጥር | 1 | 13 |
| | በማህበራዊ ዋስትና የተሸፈኑ የግል ድርጅቶች ብዛት | ቁጥር | 119700 | 174700 |
| | የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ | | | |
| | ቁልፍ የሥራ ገበያ አመልካቾች (KILM) | ቁጥር | 9 | 12 |
| | በሥራ ላይ የተሰማራው የሰው ኃይል መረጃ አሰባሰብ ሽፋን በመቶኛ | መቶኛ | 10 | 50 |
| | በስምምነት የተፈቱ የሥራ ክርክሮች ብዛት በመቶኛ | መቶኛ | 60 | 75 |
| | የማስፈጸም አቅም ግንባታ | | | |
| | የተፈጠሩ ግንባር ቀደም አመራሮችና ፈጻሚዎች | መቶኛ | 15 | 65 |
| | ተልዕኳቸውን በተሟላ ቅልጥፍናና ውጤታማነት ያሳኩ ተቋማት | መቶኛ | 70 | 100 |
| | መልካም አስተዳደር | | | |
| | የህዝብ እርካታና አመኔታ ደረጃ | መቶኛ | 60 | 85 |
| | የተጐሣቆሉና የደቀቁ የከተማ አካባቢዎች ሽፋን | መቶኛ | 50 | 30 |
| | የገቢ ምርቶች ላይ የሚደረግ ምርመራ | ቁጥር | 869194 | 1529375 |
| | የወጪ ምርቶች ላይ የሚደረግ ምርመራ | ቁጥር | 835510 | 1267333 |
| | የህጋዊ ስነልክ የመለኪያ መሣሪያዎችን ትክክለኝነት ማረጋገጥ | ቁጥር | 1307250 | 15687600 |
| | ከማረሚያ ቤት ውጪ አማራጭ የቅጣት አፈፃፀም ማስተግበሪያ ስርዓት ዝርጋታ | መቶኛ | 40 | 100 |
| | የታራሚዎችን የባህሪ መሻሻል በመመዘን የይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ | መቶኛ | 60 | 95 |

# ምዕራፍ II
# የማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፍ ዕቅድ

## 2.1 የማክሮ ኢኮኖሚ ዋና የፖሊሲ ግቦች

የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓላማዎች እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2017 ሀገራችንን የመጀመሪያ ደረጃ መካከለኛ ገቢ (Lower Middle Income) ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተቀመጠውን ሀገራዊ ራዕይ ለማሳካት የተጀመረውን ፈጣን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ጉዞ በላቀ ደረጃ ለመፈጸም ሁለተኛው ምዕራፍ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፍ ዕቅድ የሚከተሉትን ዋና ዋና ግቦች መሠረት ያደረገ ነው፡፡

ሀ) ባለሁለት አሀዝ አመታዊ የኢኮኖሚ ዕድገትን በማስቀጠል በመሠረታዊ የዕድገት አማራጭ ኢኮኖሚው በአማካይ በ11 በመቶ እንዲያድግ ማድረግ፣

ለ) የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት፣

ሐ) የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ማድረግ፣

- የዋጋ ንረትን በነጠላ አሀዝ መገደብ፣
- የውጭ ምንዛሬ ተመን የተረጋጋና ለወጪ ንግድ ተወዳዳሪነት አመቺ ሁኔታ መፍጠር፣
- የበጀት ጉድለት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በየዓመቱ በአማካይ ከ3 በመቶ እንዳይበልጥ ማድረግ፣
- የሀገር ውስጥ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ በዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት ወደ 18.8 በመቶ ማሳደግ፣

መ) የሀገር ውስጥ ቁጠባን ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ 29.6 በመቶ ማድረስ፡፡ ይህንን በማደረግም ኢንቨስትመንት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በዕቅዱ መጨረሻ ዓመት ወደ 41.3 በመቶ እንዲሆን ማድረግ

## 2.2 የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ግቦች ዝርዝር ትንተና

### 2.2.1 ባለሁለት አሀዝ ዓመታዊ ዕድገትን አጠናክሮ በማስቀጠል በመሠረታዊ የዕድገት አማራጭ ኢኮኖሚው በአማካይ በ11 በመቶ እንዲያድግ ማድረግ

በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ወቅት በርካታ የልማት ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን በአራት የትግበራ ዓመታት በየዓመቱ በአማካይ ከ10 በመቶ በላይ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ አመርቂ ውጤቶችና መልካም ተሞክሮዎችም ተመዝግበዋል፡፡ በቀጣይ ለሚካሄዱ የልማት ሥራዎችም ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡ በእነዚህ ዓመታት የተመዘገቡ አመርቂ የልማት ውጤቶችን፣ መልካም ተሞክሮዎችን፣ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችንና ፈተናዎችን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የኢኮኖሚ ዕድገቱ በሁሉም የልማት ዘርፎች በሚደረጉ የተቀናጁና የተደራጁ ጥረቶች የሚገኝ ድምር ውጤት እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ኢኮኖሚውን ከአቅርቦት አንፃር በመሠረታዊ የዕድገት አማራጭ በአማካይ በየዓመቱ 11 በመቶ ለማሳደግ ስትራቴጂክ ግብ ተቀምጧል፡፡ የሰብል ምርት ዕድገትን መሠረት ያደረገ የከፍተኛ ዕድገት አማራጭም በዕቅዱ ውስጥ እንዲካተት የተደረገ ሲሆን በዚህ አማራጭ ዋና ዋናዎች የሰብል ምርቶች በእጥፍ ለማሳደግ በዕቅድ የተያዘ በመሆኑ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት 12.2 በመቶ እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ የእነዚህ

ዋና ዋና የሰብል ምርቶች ከጠቅላላ የግብርና ምርት ያላቸው ድርሻ 40 በመቶ እንደሚሆን ተገምቷል፡፡ ሆኖም የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቃኘው በመሠረታዊ የዕድገት አማራጭ (Base Case Scenario) ላይ በመመሥረት ነው፡፡

**i) ለመሠረታዊ የዕድገት አማራጭ ዕቅዱ መነሻ የተደረጉ ታሳቢዎች**

ባለሁለት አሀዝ የኢኮኖሚ ዕድገትን በተጠናከረ ሁኔታ ለማስቀጠልና በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የ11 በመቶ ዓመታዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ግብን ለማሳካት የሚከተሉት ታሳቢዎች ተወስደዋል፡፡

**ሀ) የኢኮኖሚ ዘርፎችን በተመለከተ**

**በግብርና ዘርፍ፡-** የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተያዘው ግብ ተጠናክሮ የሚተገበርበት እንደሚሆንና የምርጥ አርሷደሮችን ተሞክሮ ወደ ሌሎች አርሷደሮች ለማስፋፋት፣ ከፍተኛ ዋጋ በሚያወጡ ምርቶች ላይ ለማተኮርና ሰፋፊ እርሻዎች ላይ ትኩረት ለመስጠት ዕቅድ ተይዟል፡፡

**በኢንዱስትሪ ዘርፍ፡-** በተለይ ትኩረት እንደሚሰጥበት ታሳቢ ተደርጎ የተወሰደው በዋናነት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ሲሆን፣ በዘርፉ የሚደረግ ኢንቨስትመንት የወጪ ንግድን በማሳደግና የገቢ ንግድን በመተካት ላይ ያተኮረ ይሆናል፤ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ተገንብተው ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አንቨስትመንት የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች በገበያና በፋይናንስ አቅርቦት በኩል ያለባቸውን ችግር በተቀናጀ ሁኔታ ለመፍታት ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ በተለይ በክልሎች በተቋቋሙ የሊዝ ፋይናንስ ተቋማትና በኢትዮጵያ ልማት ባንክ በሚዘረጋ የሊዝ ፋይናንስ ክንፍ የፋይናንስ ችግርን ለመፍታት ይሠራል፡፡ አነስተኛ የማኑፋክቸሪንግ ተቋማት ከሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ጋር በሚኖራቸው የገበያ ትስስር የተቀናጀ ሥራ ይሰራል፤ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት፣ የማስተላለፍና የማከፋፈል አቅምም በዕቅዱ ዓመታት ይጠናከራል ተብሎ ስለሚገመት የኤሌክትሪክ ኃይል ችግር ሙሉ በሙሉ ይቀርፋል፡፡ በተጨማሪ ለኤክስፖርት ግኝትም አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

**በአገልግሎት ዘርፍ፡-** ቱሪዝም ከተለያዩ ዘርፎች በተለይም ከሆቴል፣ ከትራንስፖርት እና ከፋይናንስ ተቋማት ጋር ያለውን የጠበቀ ግንኙነት መሠረት በማድረግ ዘርፉ እንዲጠናከር ከፍተኛ ሥራ ይሠራል፡፡ ኢኮኖሚያችን በፍጥነት በሚያድግበት ወቅት በመጀመሪያ ተጠቃሚ የሚሆነው የሀገር ውስጥ ንግድና የገቢና ወጪ ንግድ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ በትራንስፖርት አገልግሎት በፋይናንስ ተቋማት የብድርና የገንዘብ ዝውውር አገልግሎት ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው እነዚህ አገልግሎቶች በከፍተኛ ሁኔታ እንዲያድጉ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ከስጋት አኳያ የተወሰዱ ታሳቢዎችን በተመለከተ ያልታሰበ የተፈጥሮ አደጋ (ለምሳሌ ድርቅ) በኢኮኖሚ ዕድገታችን ላይ እንደ ስጋት ተደርጎ መወሰድ ይገባዋል፡፡ ከ40 በመቶ በላይ የሚሆነው አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት በግብርና ላይ የተመሠረተ በመሆኑና የኢንዱስትሪውና የአገልግሎቱ ዘርፍ ዕድገት ህልውና በዚሁ ዘርፍ ላይ ጥገኛ ስለሆነ ያልታሰበ የተፈጥሮ አደጋን መቋቋም የሚያስችል አቅም መፍጠር ካልተቻለ አደጋው በሚከሰትበት ጊዜ በዕቅዱ የተያዘውን ዓመታዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ አዳጋች ይሆናል፡፡ በዚህ በኩል በቂ የምግብ እህል መጠባበቂያና የውጭ ምንዛሬ መጠባበቂያ ክምችት እንደሚያዝ ዕቅድ መያዙ ተገቢ ነው፡፡

**ለ) የዓለም ኢኮኖሚን በተመለከተ**

በዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ትንበያ መሠረት የዓለም ኢኮኖሚ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት በ2007 ከተገመተው 3.0 በመቶ በ2011 የበጀት ዓመት 4.0 በመቶ እንደሚደርስ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ትንበያዎች ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል የታዳጊ አገሮች አማካይ ዓመታዊ የኢኮኖሚ ዕድገት በ2007 ከተገመተው 5.0 በመቶ በማንሰራራት በ2012 የበጀት ዓመት 5.2 በመቶ እንደሚደርስ ይኸው ትንበያ ያሳያል፡፡ ይህም ለዕቅዳችን መሳካት አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ሌላው መካከለኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል በአለም አቀፍ ደረጃ በ2002 1.8 ቢሊዮን የነበረ ሲሆን በ2011 የበጀት ዓመት 4.9 ቢሊዮን እንደሚደርስ ትንበያዎቹ የሚያሳዩ በመሆኑ በዓለም ገበያ ተፈጥሯዊ (Organic) የሆኑ የግብርና

ምርቶችና የቀላል ኢንዱስትሪ ምርት ፍላጎት እንዲጨምር ያደርጋል የሚል ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ይህም በአወንታዊ መልኩ የተያዘ ታሳቢ ነው፡፡

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የግብርና ዘርፍ በየዓመቱ በአማካይ የ8.0 በመቶ ዕድገት የሚያስመዘግብ ሲሆን የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎችም በቅደም ተከተል የ19.8 በመቶ እና የ10.1 በመቶ አማካይ ዕድገት እንደሚያስመዘግቡ ይጠበቃል፡፡ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ከሁሉም ዘርፎች በላቀ ደረጃ በማደግ የ19.8 በመቶ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት የሚያስመዘግብ ሲሆን ለዚህ ፈጣን ዕድገት ማኑፋክቸሪንግ 23.9 በመቶ፤ ኤሌክትሪክ፣ ጋዝና ውሃ 33.8 በመቶ እና ኮንስትራክሽን 14.7 በመቶ፣ እንዲሁም የማዕድን ዘርፍ 17.8 በመቶ ዕድገት አስተዋፅኦ እንደሚያደርጉ ተተንብዮዋል፡፡ በአገልግሎት ዘርፍ የሚጠበቀው የ10.1 በመቶ ዕድገት ከንግድና ትራንስፖርት አገልግሎት 12.3 በመቶ እና ከሌሎች አገልግሎቶች 7 በመቶ የሚመነጭ ይሆናል፡፡

**ሠንጠረዥ 2.1 ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት በመሠረታዊ የዕድገት አማራጭ በ2003 በተሠራበት ዋጋ በመቶኛ**

| ዘርፍ | የ2003-2006 አማካይ አፈፃፀም | የ2007 የአፈፃፀም ግምት | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | የ2008-2012 ትንበያ (አማካይ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች | 6.6 | 9.6 | 8.2 | 8.0 | 7.9 | 7.9 | 7.8 | 8.0 |
| የኢንዱስትሪ ዘርፍ | 20.0 | 22.2 | 21.8 | 20.8 | 20.3 | 19.1 | 17.2 | 19.8 |
| ማኑፋክቸሪንግ | 13.0 | 19.2 | 23.4 | 23.7 | 24.0 | 24.1 | 24.1 | 23.9 |
| ከፍተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪ | 17.2 | 15.1 | 23.4 | 23.6 | 23.8 | 24.9 | 25.2 | 24.2 |
| አነስተኛና ጥቃቅንኢንዱስትሪ | 4.4 | 5.0 | 23.5 | 24.0 | 24.5 | 22.0 | 21.0 | 23.0 |
| የአገልግሎት ዘርፍ | 10.7 | 9.4 | 10.3 | 10.2 | 10.1 | 10.0 | 10.0 | 10.1 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት | **10.1** | **11.4** | **11.2** | **11.1** | **11.1** | **11.0** | **10.8** | **11.0** |

## ii) ለከፍተኛ ዕድገት አማራጭ የተወሰዱ ታሳቢዎች

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመን ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን አርሶ አደሮች ውጤት ወደ ሌሎች አርሶ አደሮች በማስፋፋት የዋና ዋና ሰብሎችን ምርት በእጥፍ ለማሳደግ እንደሚቻል ዕቅድ ተይዟል፡፡ በዚህም መሠረት የግብርናን ዘርፍ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት በመሠረታዊ አማራጭ ከነበረው 8.0 በመቶ ወደ 11 በመቶ ከፍ እንደሚያደርገው ተተንብዮዋል፡፡ ለዚሁም በዋናነት አስተዋፅኦ የሚያደርገው ዋና ዋና የሰብል ምርቶች በ16 በመቶ እንደሚያድግ ተተንብዮዋል፡፡ የእነዚህ የዋና ዋና የሰብል ምርቶች ከጠቅላላው የግብርና ምርት ተጨማሪ እሴት ያላቸው ድርሻ በአማካይ 40 በመቶ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ይህ የዕድገት ጭማሬ በሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ዕድገት ላይ ሊኖረው የሚችለው የግብረ መልስ አስተዋጽኦ (Feedback) ሳይካተት በግብርና ዕድገት ምክንያት ብቻ በዕቅዱ ዘመን አማካይ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት በከፍተኛ የዕድገት አማራጭ 12.2 በመቶ እንደሚደርስ ተተንብዮዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 2.2. ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት በከፍተኛ የዕድገት አማራጭ (በመቶኛ)**

| ዘርፍ | የ2003-2006 አማካይ አፈፃፀም | የ2007 የአፈፃፀም ግምት | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | የ2008-2012 ትንበያ (አማካይ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች | 6.6 | 7.2 | 11.0 | 10.8 | 10.8 | 11.1 | 11.3 | 11.0 |
| የኢንዱስትሪ ዘርፍ | 20.0 | 24.3 | 21.8 | 20.8 | 20.3 | 19.1 | 17.2 | 19.8 |
| ማኑፋክቸሪንግ | 13.0 | 19.2 | 23.4 | 23.7 | 24.0 | 24.1 | 24.1 | 23.9 |
| የአገልግሎት ዘርፍ | 10.7 | 7.0 | 10.3 | 10.2 | 10.1 | 10.0 | 10.0 | 10.1 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት | 10.1 | 9.6 | 12.4 | 12.3 | 12.3 | 12.3 | 12.0 | 12.2 |

### 2.2.2 የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመዋቅራዊ ለውጡ መለኪያ ተደርገው የሚወሰዱ ሁለት ጠቋሚዎች ናቸው፡፡ እነሱም የኢንዱስትሪ ተጨማሪ እሴት በተለይ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ተጨማሪ እሴት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) ያለው ድርሻ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማምጣት የማኑፋክቸሪንግ ምርቶች የገቢ ንግድን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት እና የማኑፋክቸሪንግ ምርት የወጪ ንግድ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ ናቸው፡፡

#### ሀ) የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ 8.0 በመቶ ማድረስ

የግብርና ምርት ዕድገት ተጠናክሮ እንዲቀጥልና አማካይ ዓመታዊ ዕድገቱ 8 በመቶ እንዲደርስ ግብ ተጥሏል፡፡ ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር እውን ለማድረግ በዕቅዱ ዘመን የኢንዱስትሪ ዘርፉን አማካይ ዓመታዊ ዕድገት 19.8 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለሚደረገው የመዋቀራዊ ለውጥ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እነደሚኖረው የሚጠበቀው የማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፍ በዕቅዱ ዘመን በአማካይ የ23.9 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ 8.0 በመቶ እንደሚደርስ ግብ ተጥሏል፡፡ በመሆኑም ግብርና ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ ትርጉም ባለው መልኩ እንደሚቀንስ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ አንፃር የግብርና ዘርፍ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በ2007 ከነበረበት የ41.0 በመቶ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ (2012) ወደ 35.6 በመቶ ዝቅ እንደሚል ትንበያው ያሳያል፡፡ ዝርዝሩ ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ 2.1 እና ቀጥሎ በሰንጠረዥ 2.3 ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 2.3 የዋና ዋና ዘርፎች በመሠረታዊ የዕድገት አማራጭ ከጠ/የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በመቶኛ**

| ዘርፍ | የ2007 የአፈፃፀም ግምት | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች | 41.0 | 39.9 | 38.8 | 37.7 | 36.6 | 35.6 |
| የኢንዱስትሪ ዘርፍ | 15.6 | 17.1 | 18.6 | 20.1 | 21.6 | 22.8 |
| ከዚህ ውስጥ ማኑፋክቸሪንግ | 4.6 | 5.1 | 5.7 | 6.3 | 7.1 | 8.0 |
| ከፍተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪ | 3.4 | 3.8 | 4.2 | 4.7 | 5.2 | 5.9 |
| አነስተኛና ጥቃቅንኢንዱስትሪ | 1.2 | 1.4 | 1.5 | 1.7 | 1.9 | 2.0 |
| የአገልግሎት ዘርፍ | 43.4 | 43.0 | 42.7 | 42.2 | 41.9 | 41.6 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

የኢንዱስትሪ ዘርፍ ከሁሉም ዘርፎች በላቀ ፍጥነት የሚያድግ በመሆኑ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ ለ2007 ከተገመተው 15.6 በመቶ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ ዓመት (2012) ወደ 22.8 በመቶ እንደሚያድግ ግብ ተጥሏል፡፡ የአገልግሎት ዘርፍ ድርሻ ከግብርና እና ከኢንዱስትሪ ቀሪውን 41.6 በመቶ ድርሻ እንደሚይዝ የሚጠበቅ ሲሆን ይህም በ2007 ከነበረበት 43.4 በመቶ በ1.8 መቶኛ ነጥብ እንደሚቀንስ ያሳያል፡፡ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ ደግሞ በ2007 ከተገመተው 4.6 በመቶ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (በ2012) ወደ 8.0 በመቶ እንደሚያድግ ግብ ተቀምጧል፡፡ የሜታልና የኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍን በማጠናከርና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማምጣት ወሳኝ የገቢ ምርቶችን በመተካት (Import Substitution) የውጭ ምንዛሪ ማዳን እና ለወጪ ንግድ ዕድገት ዘርፉ የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ማስቻል በማኑፋክቸሪንግ መዋቅራዊ ለውጡ ዋና መሣሪያዎች ይሆናሉ፡፡

ሠንጠረዥ 2.4. በከፍተኛ የዕድገት የዋና ዋና ዘርፎች አማራጭ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በመቶኛ

| ዘርፍ | የ2007 የአፈፃፀም ግምት | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች | 39.1 | 38.6 | 38.1 | 37.6 | 37.2 | 36.9 |
| የኢንዱስትሪ ዘርፍ | 16.1 | 17.5 | 17.8 | 20.1 | 21.4 | 22.3 |
| ከዚህ ውስጥ ማኑፋክቸሪንግ | 4.8 | 5.2 | 5.8 | 6.4 | 7.0 | 7.8 |
| የአገልግሎት ዘርፍ | 44.8 | 44.0 | 43.2 | 42.3 | 41.5 | 40.7 |
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

## ለ) የሸቀጦች የወጪ ንግድ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ 11.8 በመቶ ማድረስ

የሸቀጦች የወጪ ንግድ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ በ2012 ወደ 11.8 በመቶ ለማድረስ ግብ ተቀምጧል፡፡ ለዚህ ግብ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ተስፋ የተጣለበት የማኑፋክቸሪንግ የወጪ ንግድ ድርሻ በ2007 ከተገመተው 0.9 በመቶ በ2012 3.1 በመቶ እንደሚደርስ ይጠበቃል፡፡ የግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ ድርሻም በተመሳሳይ ጊዜ ከ4.4 በመቶ ወደ 6.5 በመቶ እንደሚያድግ ግብ ተጥሏል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ በሠንጠረዥ 2.6 ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 2.5 ሸቀጦች ወጪ ንግድ ትንበያ ከ2008 እስከ 2012 (ገቢ በሚልዮን የአሜሪካን ዶላር)

| ዝርዝር | የመነሻ ዓመት (2007) ግምት | ትንበያ | | | | | በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (ድርሻ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | |
| ጠቅላላ ወጪ ንግድ ገቢ | 3,983 | 5,101 | 6,876 | 8,797 | 11,084 | 13,968 | 100 በመቶ |
| የግብርና ምርቶች ወጪ ንግድ | 2,769 | 3,438 | 4,286 | 5,267 | 6,374 | 7,710 | 55 በመቶ |
| ➢ መደበኛ የግብርና ምርቶች | 2,427 | 3,016 | 3,747 | 4,566 | 5,451 | 6,494 | |
| ቡና | 857 | 1,071 | 1,339 | 1,607 | 1,870 | 2,173 | |
| የቅባት እህሎች | 724 | 904 | 1,135 | 1,413 | 1,710 | 2,048 | |
| ጥራጥሬዎች | 270 | 337 | 421 | 526 | 658 | 822 | |
| አትክልትና ፍራፍሬ | 51 | 63 | 79 | 99 | 118 | 142 | |
| የቁም ከብት | 205 | 257 | 324 | 409 | 513 | 647 | |
| ጫት | 321 | 383 | 448 | 512 | 581 | 660 | |
| ➢ አበባ | 218 | 261 | 341 | 442 | 574 | 746 | |
| ➢ ሌሎች የግብርና ምርቶች | 124 | 161 | 198 | 258 | 348 | 470 | |
| የኢንዱስትሪ ምርቶች ወጪ ንግድ | 706 | 1,060 | 1,888 | 2,375 | 3,160 | 4,249 | 30 በመቶ |
| ➢ ማኑፋክቸሪንግ | 532 | 887 | 1,354 | 1,849 | 2,582 | 3,613 | |
| ቆዳና የቆዳ ውጤቶች | 160 | 206 | 273 | 368 | 505 | 706 | |
| ስጋና የስጋ ውጤቶች | 84 | 109 | 144 | 195 | 266 | 372 | |
| የጨርቃጨርቅ ውጤቶች | 137 | 181 | 267 | 392 | 549 | 767 | |
| ስኳርና ሞላሰስ | 133 | 163 | 305 | 380 | 491 | 659 | |
| ምግብና መጠጥ | 17 | 29 | 51 | 88 | 152 | 265 | |
| ኬሚካል | 0.05 | 28 | 50 | 63 | 81 | 101 | |
| ፋርማሲቲካል | 0.49 | 30 | 55 | 69 | 89 | 111 | |
| የብረታብረትና ኢንጅነሪንግ ውጤቶች | 0.00 | 92 | 121 | 181 | 303 | 448 | |
| የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች | 0.34 | 49 | 89 | 114 | 146 | 182 | |
| ➢ ኤሌክትሪክ ሀይል | 173 | 173 | 534 | 526 | 579 | 636 | |
| የማዕድን ወጪ ንግድ | 508 | 603 | 702 | 1,155 | 1,551 | 2,009 | 15 በመቶ |

ሠንጠረዥ 2.6 የሸቀጦች ወጪ ንግድ ትንበያ ከጠቅላላ አገራዊ ምርት ያለው ድርሻ በመቶኛ

| ዝርዝር | የመነሻ ዓመት ግምት | ትንበያ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| **ጠቅላላ የሸቀጦች ውጪ ንግድ ገቢ (2+3+4)** | **6.4** | **7.2** | **8.5** | **9.6** | **10.7** | **11.8** |
| **የግብርና ምርቶች ወጪ ንግድ** | **4.4** | **4.9** | **5.3** | **5.8** | **6.1** | **6.5** |
| ➢ መደበኛ የግብርና ምርቶች | 3.9 | 4.3 | 4.7 | 5.0 | 5.2 | 5.5 |
| ➢ አበባ | 0.3 | 0.4 | 0.4 | 0.5 | 0.6 | 0.6 |
| ➢ ሌሎች የግብርና ምርቶች | 0.2 | 0.2 | 0.2 | 0.3 | 0.3 | 0.4 |
| **የኢንዱስትሪ ምርቶች ወጪ ንግድ** | **1.1** | **1.5** | **2.3** | **2.6** | **3.0** | **3.6** |
| ➢ ማኑፋክቸሪንግ | 0.9 | 1.3 | 1.7 | 2.0 | 2.5 | 3.1 |
| ➢ ኤሌክትሪክ ሀይል | 0.3 | 0.2 | 0.7 | 0.6 | 0.6 | 0.5 |
| **የማዕድን ወጪ ንግድ** | **0.8** | **0.9** | **0.9** | **1.3** | **1.5** | **1.7** |

በመጀመሪያ የወጪ ንግድን ድርሻ በማሳደግ በኩል ታሳቢ የተደረገው በግብርና ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ዕቅድ የተያዘ በመሆኑና ዘርፉ ለውጭ ገበያ በሚውሉና ከፍተኛ ዋጋ በሚያወጡ ምርቶች ላይ ያተኮረ ዕቅድ መያዙ ነው፡፡ ሌላው የወጪ ንግድን ድርሻ ለማሳደግ የተቀመጠው ታሳቢ በኢንዱስትሪ ዘርፍ በማኑፋክቸሪንግ ኤክስፖርት የሚያስገኘው ዕድገት አንዱ ሆኖ በአብዛኛው ከማኑፋክቸሪንግ የሚገኘው ተጨማሪ ምርት ለወጪ ንግድ ይውላል የሚለው ነው፡፡ በማዕድን ዘርፍ የወጪ ንግድን ለማሳደግ የተቀመጠው በዕቅዱ ዘመን አዲስ የሚገቡ የማዕድን ምርት አይነቶችን ታሳቢ በማድረግ የማዕድን ኤክስፖርትም ዕድገት እንደሚኖረው ግብ ተቀምጧል፡፡

### 2.2.3. የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ማድረግ

የተረጋጋና ዝቅተኛ የዋጋ ንረት ዕድገት ለፈጣንና ፍትሐዊ ልማት ምቹ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን በመጪዎቹ አምስት ዓመታት የዋጋ ንረት መጣኔ በነጠላ አሀዝ ተገድቦ እንዲቆይ ለማድረግ የሚያስችል እና የተረጋጋ የብር የውጭ ምንዛሬ ተመን የሚያረጋግጥ የገንዘብ ፖሊሲ ተፈፃሚ ይደረጋል፡፡

ዝቅተኛና የተረጋጋ የዋጋ ንረትን በሚመለከት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የዋጋ ንረት በእቅዱ ዘመን በአማካይ 8 በመቶ እንዲሆን ግብ ተጥሏል፡፡ ዋጋን ለማረጋጋት ከአቅርቦት አንፃር በመጀመሪያ ደረጃ የግብርና ምርትና ምረታማነት ግብን ማሳካት ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ሌላው ታሳቢ ተደርጎ የተወሰደው የግብርና ምርታማነት ሲያድግ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ፣ ለኢንዱስትሪዎች ግብዓትና ለወጪ ንግድ ከዋለው ምርት የሚተርፈውን በተጠና የገበያ ማረጋጊያ ዋጋ ከአርሶ አደሩ በመግዛት ወደ ምግብ እህል ክምችት ማስገባት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የምግብ እህል ክምችትን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (2012) 5 ሚሊዮን ቶን ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ ታሳቢ ተደርጎ የተወሰደው የገቢ ንግድን በሚተኩ የኢንዱስትሪ ምርቶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሰራ ስለሚጠበቅ ከዘርፉ የሚገኘው የምርት አቅርቦት ለዋጋ መረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ነው፡፡

ከፍላጎት አንፃር ዝቅተኛና የተረጋጋ የዋጋ ንረትን ለመጠበቅ የሚያስችል የገንዘብ ፖሊሲ መከተል ያስፈልጋል፡፡ በቀጣዮቹ አምስት ዓመታት የፋይናንስና የባንክ ኢንዱስትሪ ልማቱ የሚጠይቀውን ፋይናንስ የማቅረብ ብቃት ያለው እንዲሆን የሚያስችሉ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ የፋይናንስ ኢንዱስትሪው በተለይ በቀጣይ የተያዙትን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪና የኤክስፖርት ልማት ዕቅዶች በወሳኝነት የመደገፍ ብቃት እንዲኖረው ይደረጋል፡፡ የተጀመሩ የባንክና ፋይናንስ የመረጃ ሥርዓት፣ አስተማማኝ የክፍያና የገንዘብ ማስተላለፍ ሥርዓት፣ የአውቶሜሽን የአይቲ ትግበራ እንደዚሁም የሞደርናይዜሽን ማሻሻያዎች ተሟልተው እንዲተገበሩና ለውጡ ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሸጋገር ይደረጋል፡፡ የቤቶች ቁጠባ ኘሮግራምን ጨምሮ አዳዲስ የቁጠባ መሳሪያዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ በተለይ በገጠር አካባቢዎች የገንዘብ ተቋማትን ተደራሽነት በማስፋት ቁጠባን የማበረታታት አቅጣጫ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

ከፍላጎት አንፃር ዝቅተኛና የተረጋጋ የዋጋ ንረት ለመጠበቅ የሚያስችል የፊስካል ፖሊሲ መከተል ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ አጠቃላይ የበጀት ጉድለት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2007 የበጀት ዓመት ከነበረበት ብዙም ለውጥ ሳያሳይ በሁለተኛው አምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በአማካይ 2.9 በመቶ ብቻ እንዲሆን ግብ ተቀምጧል፡፡ ከዚህ ውስጥ 0.9 በመቶ የሚሆነውን ከውጭ ብድር እና 2.0 በመቶ ከሀገር ውስጥ ብድር የሚሸፈን ይሆናል፡፡ ከዋጋ ንረት ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚወሰደው ብድር በመሆኑ በማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ትንተና መሠረት የዋጋ ንረትን በነጠላ አሀዝ (8 በመቶ) መገደብ በሚያስችል ሁኔታ መንግሥት ከባንኩ የሚወስደው ብድር መጠን ተተንብዮዋል፡፡ ቀሪው የበጀት ጉድለት ደግሞ የመንግሥት የግምጃ ቤት ሰነድ በመሸጥ እንደሚሸፈን ዕቅድ ተይዟል፡፡

የተረጋጋና የወጪ ንግድን የሚያበረታታ የውጭ ምንዛሬ ተመን መኖር የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ለማስፈን አንዱ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ባለፉት ዓመታት የሀገራችን የውጭ ንግድ ሚዛን በእጅጉ እየሰፋ መጥቷል፡፡ ከገቢ ንግድ ወጪ በወጪ ንግድ ገቢያችን የሚሸፈነው በአማካይ ሩብ ያህሉ ነው፡፡ ይህንን ሰፊ የውጭ ንግድ ክፍተት ትርጉም ባለው ሁኔታ ለማጥበብ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የወጪ ንግድ ገቢን በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ቁልፍ ጉዳይ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ በተጨማሪ የወጪ ንግድ ምርቶቻችንን ከማበረታታትና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ከማድረግ አንፃር የብር የውጭ ምንዛሬ ተመን ሚዘናዊነቱን የጠበቀ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

### 2.2.4 የሀገር ውስጥ ቁጠባ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻን 29.6 በመቶ ማድረስ ይህንን በማድረግም ኢንቨስትመንት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻው በዕቅዱ መጨረሻ ዓመት ወደ 41.3 በመቶ እንዲሆን ማድረግ

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ይመዘገባል ተብሎ ለሚጠበቀው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት አንዱና ዋናው ምንጭ ኢንቨስትመንት ነው፡፡ በተለይ በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርና፣ በመሠረተ-ልማት፣ በማህበራዊ ልማት ዘርፎችና በሌሎች መስኮች የሚከናወነው የግልና የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ከማረጋገጥ አንፃር ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህንን ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ፍላጎት ለማሟላት የሚያስፈልገው ፋይናንስ በአብዛኛው ከሀገር ውስጥ ቁጠባ እንደሚሸፈን ይጠበቃል፡፡

ከዚህ በታች በሠንጠረዥ 2.7 እንደተመለከተው በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን (2008-2012) ጠቅላላ ኢንቨስትመንት (የግልና የመንግሥት) ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በአማካይ 40 በመቶ እንደሚሆን የተተነበየ ሲሆን ጠቅላላ የመጨረሻ ፍጆታ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2007 ከነበረበት 80.5 በመቶ በ2012 ወደ 70.5 በመቶ ዝቅ እንደሚል በመተንበዩ ጠቅላላ የሀገር ውሰጥ ቁጠባ (የግልና የመንግሥት) በአማካይ 29.6 በመቶ እንደሚደርስ ግብ ተጥሏል፡፡ በሌላ በኩል በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የወጪ ንግድ ገቢ አገልግሎትን ጨምሮ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ከፍተኛ ዕመርታ በማሳየት በ2007 ከነበረበት 12.8 በመቶ በ2012 ወደ 20.6 በመቶ የሚያድግ ሲሆን የገቢ ንግድ ወጪ አገልግሎትን ጨምሮ በ2007 ከነበረት 29.6 በመቶ በ2012 ወደ 32.3 በመቶ ያድጋል፡፡ በዚህም መሠረት የሀብት ክፍተት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2007 ከነበረበት 16.8 በመቶ በ2012 መጨረሻ ወደ 11.7 በመቶ ዝቅ እንደሚል ትንበያው ያሳያል፡፡

በሁለተኛው አምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የግል ቁጠባ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2007 ከተገመተው 13 በመቶ በ2012 የበጀት ዓመት 18.9 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ ይህም ግብ እንዲሳካ በመጀመሪያ ደረጃ ከገንዘብና የፋይናንስ ፖሊሲ አኳያ የወለድ ተመን ከዋጋ ንረት ጋር ተቀራራቢ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የግልና የመንግሥት ባንኮች በካፒታል እንዲጠናከሩ በማድረግና ቅርንጫፎቻቸውን በሀገሪቱ ክልሎች እንዲያስፋፉ እንደዚሁም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት (MFIs) እንዲከፍቱ የሚያበረታታ የፖሊሲ እርምጃ በመውሰድ 80 በመቶ የሚሆን አባወራ የቁጠባ ሂሣብ እንዲኖረው የሚያስችል ሥራ ይሠራል፡፡ ከዚሁ በተጓዳኝ ኮንትራታዊ ቁጠባ ማለትም የግል የጡረታ ዋስትና፣ የጤና ዋስትናና የኢንሹራንስ አረቦን ሽያጭ የመሳሰሉ የቁጠባ ዘዴዎች የሚጠናከሩበት ስትራቴጂ ተግባራዊ እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በተለይ የግል ጡረታ ዋስትና ሁሉንም ሠራተኞች መሸፈን በሚያስችል ሁኔታ አዋጁ እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

**ሠንጠረዥ 2.7 ጠቅላላ ፍጆታ፣ ኢንቨስትመንትና የሀብት ክፍተት በጊዜው የገበያ ዋጋ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በመቶኛ**

| | አማካይ 2003-2006 | 2007 የአፈፃፀም ግምት | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | የ2008-2012 (አማካይ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ጠቅላላ የመጨረሻ ፍጆታ** | **80.4** | **80.5** | **79.0** | **76.6** | **74.1** | **71.8** | **70.5** | **74.5** |
| የግል ዘርፍ የመጨረሻ ፍጆታ | 71.7 | 71.5 | 70.0 | 67.8 | 65.5 | 63.4 | 62.1 | 65.8 |
| የመንግሥት የመጨረሻ ፍጆታ | 8.7 | 9.0 | 9.0 | 8.8 | 8.6 | 8.4 | 8.4 | 8.7 |
| **ጠቅላላ ኢንቨስትመንት** | **36.2** | **36.3** | **37.8** | **39.2** | **40.1** | **40.9** | **41.3** | **39.9** |
| የመንግሥት ኢንቨስትመንት (የልማት ድርጅቶችን ጨምሮ) | 15.2 | 15.5 | 16.1 | 16.7 | 17.2 | 17.8 | 18.0 | 17.2 |
| የግል ኢንቨስትመንት | 21.0 | 20.8 | 21.7 | 22.4 | 22.9 | 23.1 | 23.3 | 22.7 |
| **የወጪ ንግድ አገልግሎትን ጨምሮ** | **13.7** | **12.8** | **14.3** | **15.7** | **17.2** | **18.7** | **20.6** | **17.3** |
| **የገቢ ንግድ አገልግሎትን ጨምሮ** | **30.4** | **29.6** | **31.1** | **31.4** | **31.4** | **31.4** | **32.3** | **31.5** |
| **የሀብት ክፍተት** | **-16.7** | **-16.8** | **-16.8** | **-15.8** | **-14.2** | **-12.7** | **-11.7** | **-14.3** |
| **ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቁጠባ** | **18.0** | **19.5** | **21.0** | **23.4** | **25.8** | **28.2** | **29.6** | **25.6** |
| **ጠቅላላ ብሔራዊ ቁጠባ = የሀገር ውስጥ ቁጠባ+የውጭ ቁጠባ** | **44.7** | **36.3** | **37.8** | **39.2** | **40.1** | **40.9** | **41.3** | **39.8** |
| **ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ** | **100** | **100** | **100** | **100** | **100** | **100** | **100** | **100** |

የመንግስት ቁጠባን 10.7 በመቶ በማድረስ ረገድ፣ ባለፉት ዓመታት ተፈፃሚ የሆነው የፊስካል ፖሊሲ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት አሁን በሥራ ላይ ያሉትን የታክስ ፖሊሲዎች በውጤታማነት በማስተዳደር የታክስ ገቢን በማሳደግ በካፒታል ኢንቨስትመንት የኢኮኖሚ ዕድገትንና ድህነት ቅነሳን በሚያፋጥኑ ቁልፍ ዘርፎች ላይ በማተኮር እንዲቀጥል የመንግስት ቁጠባን ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ በ2007 ከተገመተው 6.5 በመቶ በ2012 መጨረሻ 10.7 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ ለዚህም ባለፉት ዓመታት በመተግበር ላይ የቆየውን የታክስ ማሻሻያ ኘሮግራም አጠናክሮ በማስቀጠል የግብር አሰባሰብና አስተዳደር ሥርዓቱን ማጎልበት ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ የግብር ክፍያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተና የህግ አክባሪነት ስሜት በግብር ከፋዩ ህብረተሰብ ውስጥ ማስረፅ እንዲሁም የግብር ሰብሳቢ ተቋማትን የማስፈጸም አቅም በማጎልበት በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ ያለውን የገቢ አሰባሰብ አቅም ማሳደግ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በሀገሪቱ ውስጥ በግብር ሥርዓቱ ያልታቀፉ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ወደ ግብር ሥርዓቱ በማስገባት የታክስ መሠረት የማስፋት ተግባር ይከናወናል፡፡

የመንግሥት ጠቅላላ ገቢ (ዕርዳታን ጨምሮ) በ2007 ከነበረበት ብር 199.8 ቢሊዮን በሁለተኛ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት (2012) ወደ ብር 627.6 ቢሊዮን ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሏል፡፡ ይህንን ግብ ለማሳካት የታክስ ገቢ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በ2007 ከተገመተው 12.9 በመቶ በ2012 ወደ 17.2 በመቶ እንደሚደርስ ግብ ተጥሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 2.8 የሁለተኛው የዕድገት ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የገቢና ወጪ ትንበያ (በቢሊዮን ብር)**

| ዝርዝር | የ2006 አፈፃፀም | የ2007 አፈፃፀም ግምት | የ2008-2012 ትንበያ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| **ጠቅላላ ገቢ የውጭ እርዳታን ጨምሮ** | **158.1** | **199.8** | **243.7** | **297.6** | **380.4** | **484.8** | **627.6** |
| የሀገር ውስጥ ገቢ | 146.2 | 183.0 | 224.9 | 278.7 | 361.3 | 464.8 | 605.2 |
| የታክስ ገቢ | 133.1 | 164.2 | 202.6 | 249.0 | 325.7 | 421.7 | 551.4 |
| ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | 13.1 | 18.7 | 22.3 | 29.7 | 35.6 | 43.1 | 53.8 |
| የውጭ እርዳታ | 11.9 | 16.8 | 18.8 | 18.9 | 19.1 | 20.0 | 22.4 |
| **ጠቅላላ ወጪ** | **185.5** | **237.2** | **287.9** | **351.4** | **443.0** | **566.8** | **726.1** |
| መደበኛ ወጪ | 78.1 | 108.8 | 125.5 | 148.0 | 180.1 | 218.5 | 264.6 |
| የካፒታል ወጪ | 107.4 | 128.3 | 162.4 | 203.5 | 262.9 | 348.3 | 461.5 |
| ከጠቅላላ ወጪ ውስጥ የድህረ ተኮር ዘርፍ ወጪ | 126.8 | 147.9 | 186.4 | 234.9 | 295.9 | 372.9 | 469.8 |
| የመንግስት ቁጠባ | 68.1 | 74.1 | 100.7 | 132.2 | 182.7 | 247.9 | 342.3 |
| የበጀት ጉድለት | -27.4 | -37.4 | -44.2 | -53.8 | -62.6 | -82.0 | -98.5 |
| የበጀት ጉድለት አሸፋፈን | 27.4 | 37.4 | 44.2 | 53.8 | 62.6 | 82.0 | 98.5 |
| ከውጭ የሚገኝ ብድር (የተጣራ) | 20.5 | 15.9 | 16.2 | 17.4 | 19.0 | 21.1 | 29.0 |
| ከሀገር ውስጥ ብድር (የተጣራ) | 13.5 | 21.5 | 28.0 | 36.4 | 43.6 | 60.9 | 69.5 |

ጠቅላላ የመንግሥት ወጪ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ብር 726.1 ቢሊዮን የሚደርስ ሲሆን ከዚህ ውስጥ መደበኛ ወጪ ብር 264.6 ቢሊዮን እና የካፒታል ወጪ ብር 461.5 ቢሊዮን የሚይዝ ይሆናል፡፡ ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን ለማስወገድ የሚረዱ የድህነት ተኮር ዘርፎች ወጪ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ብር 469.8 ቢሊዮን የሚደርስ ሲሆን ይህም ከጠቅላላ የመንግስት ወጪ 64.7 በመቶ ድርሻ ይይዛል፡፡ በመሆኑም ጠቅላላ የመንግስት ቁጠባ በ2007 ከተገመተው 74.1 ቢሊዮን ብር በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ (2012) ወደ 342.3 ቢሊዮን ብር እንደሚደርስ የተተነበየ ሲሆን ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2007 ከነበረበት 6.5 በመቶ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ወደ 10.7 በመቶ እንደሚደርስ ትንበያው ያሳያል፡፡ የመንግስት ገቢና ወጪ በጊዜው የገበያ ዋጋ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ እና የመንግስት ቁጠባ ትንበያ ቀጥሎ በሠንጠረዥ 2.9 ተመልክቷል፡፡

የመንግሥት ወጪ ትንበያ ከተጠቀመባቸው የስሌት ዘዴዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ (1) የፋይናንስ ፍላጎትና ከጠቅላላ የፋይናንስ አቅም ግምት ጋር በማስተሳሰር ማስላት፣ (2) ዋነኛ የሀገሪቱ የልማት አጀንዳ በሆኑ ዕድገትን የሚያፋጥኑና ድህነትን ለማስወገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸውን ዘርፎች የፋይናንስ ፍላጎት ከግምት ውስጥ ማስገባት (3) በሚቀጥሉት አምስት አመታት የመንግሥትን አገልግሎት መስፋፋትና የዋጋ ንረትን ሁኔታ ከግምት ማስገባት እና (4) የመደበኛ ወጪዎችን ከሀገር ውስጥ በሚገኝ ገቢ መሸፈን እና የካፒታል ወጪዎችን በሚመለከት በመካሄድ ላይ ላሉ ነባር ኘሮጀክቶች ቅድሚያ መስጠትና በመንግሥት ፖሊሲና ስትራቴጂ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው አዳዲስ ኘሮጀክቶች እንዲካተቱ ማድረግ እና በተለይ ለግብርና ዘርፍ መሠረት ልማት ግንባታን የሚያስፈልግ የፋይናንስ ፍላጎትን ከግምት ውስጥ ማስገባት ናቸው፡፡

**ሠንጠረዥ 2.9 የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመንግስት የወጪና የገቢ ትንበያ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ (በገበያ ዋጋ) በመቶኛ**

| ዝርዝር | የ2006 አፈፃፀም | የ2007 አፈፃፀም ግምት | የ2008-2012 ትንበያ | | | | | አማካይ (2008-2012) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | |
| **ጠቅላላ ገቢ የውጭ እርዳታን ጨምሮ** | **15.8** | **15.8** | **16.0** | **16.3** | **17.2** | **18.2** | **19.5** | **17.5** |
| **የሀገር ውስጥ ገቢ** | **13.9** | **14.4** | **14.8** | **15.3** | **16.4** | **17.5** | **18.8** | **16.5** |
| የታክስ ገቢ | 12.0 | 12.9 | 13.3 | 13.6 | 14.8 | 15.8 | 17.2 | 14.9 |
| ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | 1.9 | 1.5 | 1.5 | 1.6 | 1.6 | 1.6 | 1.7 | 1.6 |
| የውጭ እርዳታ | 1.9 | 1.3 | 1.2 | 1.0 | 0.9 | 0.8 | 0.7 | 0.9 |
| **ጠቅላላ ወጪ** | **17.6** | **18.7** | **18.9** | **19.2** | **20.1** | **21.3** | **22.6** | **20.4** |
| መደበኛ ወጪ | 7.4 | 8.6 | 8.2 | 8.1 | 8.2 | 8.2 | 8.2 | 8.2 |
| የካፒታል ወጪ | 10.2 | 10.1 | 10.7 | 11.1 | 11.9 | 13.1 | 14.4 | 12.2 |
| ከጠቅላላ ወጪ ውስጥ የድህረ ተኮር ዘርፍ ወጪ | 12.1 | 11.7 | 12.2 | 12.9 | 13.4 | 14.0 | 14.6 | 13.4 |
| የመንግስት ቁጠባ | 6.5 | 6.5 | 6.6 | 7.2 | 8.3 | 9.3 | 10.7 | 8.4 |
| **የበጀት ጉድለት** | **-1.8** | **-2.9** | **-2.9** | **-2.9** | **-2.8** | **-3.1** | **-3.1** | **-3.0** |
| የበጀት ጉድለት አሸፋፈን | 1.8 | 2.9 | 2.9 | 2.9 | 2.8 | 3.1 | 3.1 | 3.0 |
| ከውጭ የሚገኝ ብድር (የተጣራ) | 1.3 | 1.3 | 1.1 | 0.9 | 0.9 | 0.8 | 0.9 | 0.9 |
| ከሀገር ውስጥ ብድር (የተጣራ) | 0.5 | 1.7 | 1.8 | 2.0 | 2.0 | 2.3 | 2.2 | 2.1 |

## 2.3 የፋይናንሲንግ ዕቅድ (Financial Plan)

የማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፍ ዕቅድን የተሟላ የሚያደርገው በአራቱም የማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፎች ማለትም በአገር ውስጥ ምርት ትንበያ፣ በበጀት ትንበያ፣ በውጭ ንግድ ትንበያ እና በገንዘብ ትንበያ መካከል መጣጣምና መናበብ መቻላቸውን ሲረጋገጥ ነው፡፡ መጣጣማቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችለው የፋይናንስ ዕቅድ ተብሎ የሚታወቀው ነው፡፡ አጠቃላይ የፋይናንስ ዕቅድ በሁለት ይከፈላል፡፡ ይኸውም በጀት ነክ የፋይናንስ ዕቅድና ከበጀት ውጭ የሆነ የፋይናንስ ዕቅድ በሚል ነው፡፡

### 2.3.1 በጀት ነክ የፋይናንስ ዕቅድ

ቀጥሎ በሠንጠረዥ 2.10 እንደተመለከተው በዕቅዱ ዘመን ከአገር ውስጥ ገቢና ከውጭ እርዳታ የሚገኝ ገቢ የጠቅላላ የበጀት ወጪን (የካፒታል ወጪን ጨምሮ) 85.6 በመቶ እንደሚሸፍንና ቀሪው 14.4 በመቶ

በበጀት ጉድለት እንደሚታይ ያሳያል፡፡ ከዚህ የበጀት ጉድለት ውስጥ 30.1 በመቶ የሚሆነው በውጭ ብድር የሚሸፈን ሲሆን ቀሪው 69.9 በመቶ የሚሆነው ደግሞ ከአገር ውስጥ በብድር እንደሚሸፈን ግብ ተጥሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 2.10 በጀት ነክ የፋይናንስ ምንጭ** (Budgetary Financing) **(በቢሊዮን ብር)**

| መግለጫ | 2007 የመነሻ ዓመት | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | የ2008-2012 ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢና የውጭ ዕርዳታ | 199,800.0 | 243,700.0 | 297,600.0 | 380,400.0 | 484,800.0 | 627,600.0 | 2,034,100.0 |
| ጠ/የሀገር ውስጥ ገቢና የውጭ ዕርዳታ ከጠ/የወጪ ያለው ድርሻ (%) | 84.3 | 84.6 | 84.7 | 85.9 | 85.5 | 86.4 | 85.6 |
| ጠቅላላ ወጪ | 237,100.0 | 287,900.0 | 351,500.0 | 443,000.0 | 566,800.0 | 726,100.0 | 2,375,300.0 |
| የበጀት ጉድለት የውጭ ዕርዳታ ጨምሮ | -37,300.0 | -44,200.0 | -53,900.0 | -62,600.0 | -82,000.0 | -98,500.0 | -341,200.0 |
| የበጀት ጉድለት አሸፋፈን | 37,300.0 | 44,200.0 | 53,900.0 | 62,600.0 | 82,000.0 | 98,500.0 | 341,200.0 |
| • ከውጭ ሀገር የሚሸፈን | 15,800.0 | 16,200.0 | 17,500.0 | 19,000.0 | 21,100.0 | 29,000.0 | 102,800.0 |
| • ከሀገር ውስጥ የሚሸፈን | 21,500.0 | 28,000.0 | 36,400.0 | 43,600.0 | 60,900.0 | 69,500.0 | 238,400.0 |
| የበጀት ጉድለት አሸፋፈን ከጠ/ ወጪ ያለው ድርሻ በመቶኛ | 15.7 | 15.4 | 15.3 | 14.1 | 14.5 | 13.6 | 14.4 |

### 2.3.2 ከበጀት ውጪ የሆነ የፋይናንስ ምንጭና የኢንቨስትመንት ፋይናንስ ፍላጎት

ከበጀት ውጭ የሆነ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ፋይናንስ ምንጭን በተመለከተ ከዚህ በታች በሁለተኛው አምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ከባንክና አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ቁጠባ፣ ከቦንድና ኮንትራታዊ ቁጠባ ምንጮች በአጠቃላይ 1.9 ትሪሊዮን ብር እንደሚሰበሰብ ተተንብዮዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ ባንኮችና አነስተኛ የገንዘብ ተቋማት በቁጠባና ብድር ተመላሽ የሚሰበሰቡት 1.8 ትሪሊዮን ብር (93.7 በመቶ) ድርሻ ያለው ሲሆን፤ የኮንትራታዊ ቁጠባ የቦንድ ሽያጭን ጨምሮ ከሌሎች የፋይናንስ ምንጮች የሚሰበሰበው ደግሞ 120 ቢሊዮን ብር (6.3 በመቶ) እንደሚሆን ትንበያው ያሳያል፡፡

ከላይ የተቀመጠውን ፋይናንስ ለመሰብሰብ የባንኮች ቁጠባ በአማካይ የ30.9 በመቶ ዓመታዊ እድገት እንደሚያሳይ ግብ የተጣለ ሲሆን ይህንን እቅድ ለማስፈፀም ባንኮች በካፒታልና በዘመናዊ የክፍያ ሥርዓት ተጠናክረው ቅርንጫፎቻቸውን በ2007 ከሚገመተው 2,322 በእጥፍ በማሳደግ 4671 ያደርሳሉ የሚል ታሳቢ ተቀምጧል፡፡ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ተደራሽነታቸውን ቢያንስ 50 በመቶ በሚሆኑ የገጠር ቀበሌዎች እንደሚያስፋፉ ግብ ተጥሏል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የረጅም ጊዜ የፋይናንስ ገንዘብ ለማሰባሰብ የሚያስችለውን የቁጠባ ቦንድ መሸጥ እንደሚጀምር በዕቅድ ተይዟል፡፡

በአጠቃላይ በሁለተኛው የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በማክሮ ማእቀፍ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ኢኮኖሚው ለተለያዩ ዘርፎች ሊያቀርብ የሚችለው የፋይናንስ ምንጭ ከዚህ በላይ የቀረበ ሲሆን የፋይናንስ ድልድሉ በየዓመቱ በሚደረገው የፋይናንሺያል ፕሮግራም በቅድሚያ ትኩረት ለሚሰጣቸው ይደለደላል፡፡

## 2.4 የሥራ ፈጠራና የድህነት ቅነሳ ዕቅድ

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት ከአጠቃላይ ድህነት መስመር በታች የሚኖረው የህዝብ መጣኔ ወደ 16.7 በመቶ ዝቅ እንደሚል ትንበያው ያመለክታል፡፡ ይህ ትንበያ ፈጣን፣ ሁሉን አቀፍ እና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገትና ማህበራዊ ልማት በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ ተፈፃሚ በማድረግ የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡ የድህነት ቅነሳው ምግብ ነክና ምግብ ነክ ያልሆኑ የድህነት ገፅታዎችን ያካተተ መሆኑ ደግሞ የበለጠ ውጤታማ እንደሆነ ያሳያል፡፡ የዕድገትና የድህነት ቅነሳ ቁርኝትን (Growth Poverty Linkages) አስመልክቶ በቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ የመስክ ጥናት መረጃዎች ላይ ተመስርቶ በተካሄደው የትንተና ጥናት ውጤት መሰረት በ1997 የ1 በመቶ ኢኮኖሚ ዕድገት በ1.7 በመቶ ድህነትን የቀነሰ ሲሆን በ2003 በተደረገው የድህነት ትንተና ጥናት ደግሞ የ1 በመቶ ኢኮኖሚ ዕድገት ድህነትን

በ1.943 በመቶ መቀነስ እንዳስቻለ ጥናቱ ያመለክታል፡፡ ይህም ባለፉት 12 ዓመታት የኢኮኖሚ ዕድገቱ ፈጣን ብቻ ሳይሆን ድህነት ተኮር እንደነበረ ያረጋግጣል፡፡ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በድህረ 2015 የልማት አጀንዳ ድህነትን እ.ኤ.አ. በ2030 ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት ከደረሰበት ስምምነት አንፃር ሀገራችን ይህንን ግብ ለማሳካት በሚቀጥሉት ዓመታት ፈጣን ዕድገቱን ለማስቀጠልና ድህነትን ለማጥፋት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች የተደራጁና የተቀናጁ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

## 2.5 የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማኔጅመንትና ተቋማዊ ብቃትን ማጠናከር

**የብሔራዊ ፕላን ዝግጅትና የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ አቅም ግንባታ ዕቅድ በተመለከተ፡-** የሚፈለገው የሰው ኃይል እንዲሟላ በማድረግ በነባር ፕሮግራሞች ለምሳሌ በኢኮኖሚክ ሞዴሊንግ፣ የእስካሁን የአገራችንን ተሞክሮዎች በመቀመርና ሌሎች መልካም ተሞክሮ ካላቸው አገሮች ልምድ በመቅሰም /Bench marking/ ሁሉን አቀፍ ወጥነት ያለው የፕላን አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስርዓትን መዘርጋትና መፈፀም፣ በድህነት ትንተና…ወዘተ እና ሌሎች አዳዲስ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት የሰው ኃይሉን የሙያ ዕውቀትና ክህሎት ለማሻሻል፣ ለማሳደግና ለማዳበር ታቅዷል፡፡ በተለያዩ የመንግስት አስተዳደር ዕርከኖች የሚተገበሩ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና የተለያዩ የሴክተር ፕሮግራሞች በረጅም፣ በመካከለኛ እና በአጭር ዘመን ሀገራዊ የልማት ፕላኖች የማስተባበሪያ መሣሪያነት ቅንጅት፣ ትስስርና ተመጋጋቢት ተፈጻሚ እንዲሆኑ የሚያስችሉ አሠራሮችና ተቋማዊ አደረጃጀቶች በየደረጃው የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ጥናት ለማካሄድ ታቅዷል፡፡

**የሞነተሪ ፖሊሲ ማኔጅመንት አቅም ግንባታ ዕቅድ በተመለከተ፡-** የተጀመሩ የአቅም ግንባታ ሥራዎች የበለጠ ተጠናክረው የሚካሄዱበት ሁኔታ እንደሚኖር የታቀደ ሲሆን በተለይ ባንኮች በቁጥርም ሆነ በሚኖራቸው የሠራተኛ ብዛት ከፍተኛ ዕድገት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከሌሎች ባንኮች ጋር በተጠናከረ ሁኔታ በቅንጅት ብድር ለመካከለኛና ትላልቅ ፕሮጀክቶች እንዲሰጥ የሊዝ ፋይናንስ ደግሞ ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች መስጠት የሚችልበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡

**የፊስካል ፖሊሲ ማኔጅመንትና አቅም ግንባታ ዕቅድ በተመለከተ፡-** የተጀመሩ የአመለካከት የዕውቀትና ክህሎት ማሻሻያ ሥርዓቶች እና ሥልጠናዎችን በተደራጀና በተቀናጀ መልክ ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡ በይበልጥ ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን የፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያግዙ ተጨባጭ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡ በሁሉም ደረጃ በሁሉም የመንግሥት ተቋማት ውጤታማና ግልጽ፣ የኪራይ ሰብሳቢነት ቀዳዳዎችን ሊዘጋ የሚችል የፋይናንስ ሥርዓት ተፈፃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

**የገቢዎችና ጉምሩክ አቅም ግንባታ ዕቅድ በተመለከተ፡-** የሰው ሃብት አመራርና ልማት ማሳደግ፣ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ማስፋት፣ የተገልጋዮች ትምህርትና ግንኙነት ማሻሻል፣ የተገልጋዮች አገልግሎትና ድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓትን ማሻሻል ፤ የህግ ማስከበርና ገቢ አሰባሰብ ሥርዓትን ማሻሻልና ማስፋፋት በዕቅዱ ከተያዙ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

**የመንግሥት ስትራቴጂክ የልማት ድርጅቶችን አመራር ማጠናከር በተመለከተ፡-** የመንግሥት ስትራቴጂክ የልማት ድርጅቶች ከተሰጣቸው ተልዕኮ እና ከሚያስተዳድሩት ሀብት አንፃር ብቁና ተወዳዳሪ ሆነው የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት በበቂና በጥራት ማቅረብ እንዲችሉ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት አመራርና የሰው ኃይል እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡

## 2.6 ማጠቃለያ

ሀ) በ2017 ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተቀመጡትን ባለሁለት አሀዝ የኢኮኖሚ እድገት ግብ ለማሳካት ኢንቨስትመንትን በቀጣይነት እንዲኖረው ጠቅላላ አገራዊ ኢንቨስትመንት ከአገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ በ2007 35 በመቶ ከደረሰበት በ2012 ወደ 41.3 በመቶ ለማሣደግ ግብ ተጥሏል፡፡ ለዚህ ግብ መሳካት ደግሞ የሀገር ውስጥ ቁጠባ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ በ2007 የሀገር ውስጥ ቁጠባ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የነበረው ድርሻ 19.5 በመቶ

ሲሆን በ2012 ወደ 29.5 በመቶ በማሳደግ የተጣለውን ግብ ለማሳካት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የቁጠባ ባህልን በኅብረተሰቡ ማስረጽና ቁጠባን የሚያበረታቱ የፋይናንስና ሌሎች የቁጠባ ስልቶችን ሥራ ላይ በማዋል ረገድ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

ለ) በኢንዱስትሪ፣ ግብርናና በአገልግሎት ዘርፎች የተዘረዘሩትን የኢንቨስትመንት ዕቅዶች እውን ለማድረግ የሀገር ውስጥ ቁጠባን ከማሳደግ ጎን ለጎን የውጭ ምንዛሪ የማፍራት አቅማችንን ማሳደግ ወሳኝ ነው፡፡ በተለይ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አብዛኛው ለኢንቨስትመንት የሚውሉ ማሽነሪዎችና ጥሬ እቃዎች ከውጭ የሚገቡ በመሆናቸው በቂ የውጭ ምንዛሪ ማቅረብ የማይቻልበት ሁኔታ ከተፈጠረ የተቀመጠውን የኢንቨስትመንት ግብ ማሳካት አይቻልም፡፡ ይህ ደግሞ ተመልሶ በኢኮኖሚ እድገት ተጽእኖ በማድረግ የሀገር ውስጥ ቁጠባ እንዲቀጭጭ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ የውጭ ምንዛሪ የማፍራት አቅማችንን ለማሳደግ ከተቀመጠው ዕቅድ በላቀ የወጪ ንግድ እድገት ማምጣት የሚቻልበትን ሁኔታ መፍጠር፤ የገቢ ምርትን የሚተኩ ኢንዱስትሪዎች በዓይነትና በጥራት እንዲስፋፉ የተቀመጠውን ግብ ማሳካት እና ሌሎች የውጭ ምንዛሪ ምንጮች (እንደ ሐዋላና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት)

ሐ) በጥቅሉ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት (2008 -2012) ከመንግስት በጀት ለካፒታል (ለኢንቨስትመንት) ፕሮጀክቶች የሚመደብ ብር 1.44 ትሪሊዮን ሲሆን ከበጀት ውጪ ደግሞ ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክት በብድር እንደሚቀርብ የተተነበየው የተገመተ ብር 1.28 ትሪሊዮን ይደርሳል፡ ፡ በመሆኑም በአጠቃላይ በዕቅዱ ዓመታት ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ብር 2.72 ትሪሊዮን እንደሚመደብ ትንበያዎች ያሳያሉ፡፡

መ) የውጭ ምንዛሬ አቅማችንን ለማሳደግም ሆነ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማሳካት በመዋቅራዊ ለውጥ ረገድ አመርቃ ማምጣት ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ሥራ በቀጣይነት መሥራት ይጠይቃል፡፡

# ምዕራፍ III
# የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ልማት ዕቅድ

## 3.1. የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት ዕቅድ

### 3.1.1. ግብርናና የገጠር ትራንስፎርሜሽን

#### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ግብርና የኢኮኖሚ ዕድገት ዋነኛ ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል ለማድረግ አገራዊ የኢኮኖሚ ራዕያችን፣ የግብርና ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እና የመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም እንደመነሻ ተወስደዋል፡፡ በመሆኑም የአነስተኛ አርሶና አርብቶ አደሩ ግብርና አሁንም ዋናው የግብርና ዕድገት መሠረት ሆኖ እንዲቀጥልና የአነስተኛ አርሶና አርብቶ አደሩ ግብርና ፈጣን እድገት እንዲያረጋግጥ የማስፋት ስትራቴጂውን አሟልቶ መተግበር፣ የልማት ቀጠናዎችን መሠረት ያደረገ የግብርና ልማት መከተል እና ሌሎች በግብርና ግብዓትና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ ያሉ ችግሮችን መፍታት ትኩረት የሚሰጣቸዉ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ የግል ባለሀብቱ በግብርና ልማት ላይ የሚኖረው ድርሻ ከፍ እንዲል በማድረግ ሀገሪቱ ለያዘችው ልማትና ከድህነት ለመውጣት የምታደርገውን ጥረት እንዲያግዝ ትኩረት ይሰጣል፡፡

የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃን በማጎልበት አስተማማኝ የግብርና ልማት ለማረጋገጥ እንዲቻል የግብርና ልማት ዕቅዶች በይዘትም በትግበራም ከአርንጓዴ ልማት ራዕይ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማስቻል ከዚሁ ጋር የመስኖ ልማትን ማስፋፋት ሌሎች የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የብዝሀ ህይወት ጥበቃ በማጠናከር የማህበረሰቡን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት በማሳደግ ዙሪያ በርካታ ሥራዎች ይሰራሉ፡፡ የአርሶ አደሩን ገቢ በፍጥነት ለማሳደግ አርሶ አደሩ የላቀ ዋጋ ወዳላቸው ምርቶች ማምረት እንዲሸጋገር ማድረግና የግብርና ግብይትን በተቀላጠፈ አካሄድ ተግባራዊ ማድረግ፣ በገጠር ፈጣን ዕድገት የሚፈጥረውን ዕድል በመጠቀም የወጣቶችንና ሴቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ሌሎች ትኩረት የሚሰጣቸዉ ይሆናል፡፡

ለሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካትና መሠረታዊ አቅጣጫዎቹን ለመተግበር አስፈላጊ የሆኑ ስርዓቶችን አሟልቶ መገንባት፣ ደረቅና ከፊል ደረቅ በሆኑ አካባቢዎች የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የኑሮ ማሻሻያና የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ የሚያረጋግጡ ስራዎችን መስራት በሚቀትሉት አምስት ዓመታት ትኩረት ይሠጣቸዋል፡፡

#### 1. ዓላማዎች

የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የግብርና ዘርፍ ዋና ዓላማ በዘርፉ ፈጣንና ዘላቂነት ያለው ዕድገት በማምጣት የህዝቡን ተጠቃሚነት በየደረጃው ማረጋገጥና በአጠቃላይ ኢኮኖሚውና በዘርፉ ደረጃ መዋቅራዊ ለውጥ እንዲመጣ ማስቻል ነው፡፡ በተጨማሪም የዘርፉን ምርታማነት በማሳደግ ለኢኮኖሚው የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ማሳደግና ለማክሮ ኢኮኖሚው መረጋጋት ያለውን ወሳኝ ሚና መጫወት የሚያስችል የማምረት አቅም መገንባት ናቸው፡፡ በዘርፉ የሴቶችና የወጣቶችን እንዲሁም የዘርፉን ተዋናዮች በተደራጀ አግባብ በማሳተፍ ለልማቱ የሚጠበቅባቸውን እንዲያበረክቱና ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ የዘርፉ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው፡፡

#### 2. ዋና ዋና ግቦች

የሁለተኛውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተጥለዋል፡፡

### 2.1. የሰብል ምርታማነትና ምርት

ሀ) የአገዳ ሰብል ምርታማነትን በመነሻ ዓመት (2007) ከነበረበት 28.5 ኩንታል በሄክታር በ2012 ወደ 41.9 ኩንታል በሄክታር በማሳደግ አጠቃላይ ዓመታዊ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት (2007) ከነበረበት115 ሚሊዮን ኩንታል በ2012 ወደ 171.78 ሚሊዮን ኩንታል ማድረስ፣

ለ) የብርዕ ሰብል ምርታማነትን በመነሻዉ ዓመት (2007) ከነበረበት19.5 ኩንታል በሄክታር በ2012 ወደ 30.8 ኩንታል በሄክታር በማሳደግ አጠቃላይ ዓመታዊ ምርቱን በመነሻው ዓመት(2007) ከነበረበት 123 ሚሊዮን ኩንታል በ2012 ወደ 184.22 ሚሊዮን ኩንታል ማድረስ፣

ሐ) በጥራጥሬ ሰብል ምርታማነት በመነሻዉ ዓመት(2007) ከነበረበት 16.4 ኩንታል በሄክታር በ2012 ወደ 24 ኩንታል በሄክታር በማሳደግ አጠቃላይ ዓመታዊ ምርቱን በመነሻው ዓመት(2007) ከነበረበት 24.4 ሚለዮን ኩንታል በ2012 ወደ 38.75 ሚሊዮን ኩንታል ማድረስ፣

መ) የቅባት ሰብል ምርታማነት በመነሻዉ ዓመት (2007) ከነበረበት 8.99 ኩንታል በሄክታር በ2012 ወደ 12.7 ኩንታል በሄክታር በማሳደግ አጠቃላይ ዓመታዊ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት (2007) ከነበረበት 7.9 ሚለዮን ኩንታል በ2012 ወደ 11.5 ሚሊዮን ኩንታል ማድረስ፣

### 2.2. የቡና ምርታማነትና ምርት

በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የቡና ምርታማነትን በ2007 ከተመዘገበው 7.04 ኩንታል በሄክታር በ2012 መጨረሻ ላይ ወደ (10.83) ኩንታል በሄክታር በማሳደግ የቡና ምርት በ2007 ዓ.ም ከተደረሰበት 548.2 ሺህ ቶን በ2012 መጨረሻ ወደ 1102.62 ሺህ ቶን ለማሳደግ ግብ ተቀምጧል።

### 2.3. የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና አጠቃቀም

የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃንና አጠቃቀምን ለማጎልበት በሦስት ንዑስ ዘርፎች በዋናነት በገጠር መሬት አስተዳደር፣ በተፋሰስ ልማት ስራዎችና በአነስተኛ መስኖ ማስፋፋት ዙሪያ የሚከተሉት ግቦች ተጥለዋል። በዚህም መሠረት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በ359 ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ 28.6 ሚሊዮን ማሳዎች ላይ የሁለተኛ ደረጃ ቅየሳና ምዝገባ ሥራ በማካሄድ ለ7.2 ሚሊዮን አባወራዎች/እማወራዎች የመሬት ይዞታ የመጠቀም መብታቸውን የሚያረጋግጥ ሠርተፍኬት ለመስጠት ግብ ተጥሏል። የሀገሪቱን የመሬት አጠቃቀም ለማሻሻል የሚያስችል በቀጣዩ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንድ ሀገራዊ መሪ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ይዘጋጃል። በቀጣዩም በዘጠኙም ክልሎች ክልላዊ መሪ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ዕቅድ በማዘጋጀት ከዚህም ውስጥ በሰባቱ ክልሎች ተግባራዊ ለማድረግ ግብ ተጥሏል። በተጨማሪም ለ456 ወረዳዎች የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ የሚዘጋጅ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የ300 ወረዳዎችን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግና በተመሳሳይ ህብረተሰቡን አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በ6,521 ቀበሌዎች ውስጥ በማዘጋጀት ከዚህም ውስጥ በ3,970 ቀበሌዎች ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ግብ ተጥሏል።

የተፋሰስ ልማት ስራዎችን በማጠናከር ረገድ በ2007 መጨረሻ ላይ ከተደረሰበት የ60,460 የልማት ዕቅድ የተዘጋጀላቸው የማህበረሰብ ተፋሰሶች በ2012 መጨረሻ የልማት እቅድ የሚኖራቸውን የማህበረሰብ ተፋሰሶች 93,713 ለማድረስ ግብ ተጥሏል። በሌላ በኩል በ2007 መነሻ ዓመት የተደረሰበትን ተከልሎ እንዲያገግም የተደረገ የ11.74 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በ2012 መጨረሻ 22.54 ሚሊዮን ሄክታር ከንክኪ ነፃ ተደርጎ የተከለለና ያገገመ መሬት እንዲኖር የታቀደ ሲሆን በ2007 መነሻ ዓመት የተደረሰበት እና የተለያዩ የፊዚካል አፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ተግባራዊ የተደረገበትን 20.2 ሚሊዮን ሄክታር የማህበረሰብ ተፋሰሶች በ2012 መጨረሻ ወደ 27.23 ሚሊዮን ሄክታር ለማድረስ ግብ ተጥሏል። በተመሳሳይ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 7,735 ኩንታል ፈርጀ ብዙ ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉ የተለያዩ ዝርያ ያላቸው

የዛፍ ዘሮችን በማሰባሰብ የሚሰራጭ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነው ምርታማ የሆኑ የፍራፍሬ ዝርያዎች ይሆናሉ፡፡ በ2007 መጨረሻ ከተደረሰበት 12.162 ሚሊዮን ሄክታር የማህበረሰብ ተፋሰሶች ስነ ህይወታዊ ዘዴዎች የተሸፈነ መሬት በ2012 ወደ 18 ሚሊዮን ሄክታር ከፍ ለማድረግ ግብ የተጣለ ሲሆን በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የለሙ አካባቢዎችን ጨምሮ በየጊዜው እድሳትና ጥገና የሚፈልጉ ተፋሰሶችን በመለየት በዕቅድ ዘመኑ ለ4.7 ሚሊዮን ሄክታር መሬት እድሳትና ጥገና ለማድረግ ዕቅድ ተይዟል፡፡ በተጨማሪም የህብረተሰቡን የላቀ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በሚለሙት የማህበረሰብ ተፋሰሶች አማካይነት የሚፈጠረውን የልማት እድል በመጠቀም በገጠር 1.5 ሚሊዮን ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዷል፡፡

የመስኖ ልማትን ለማስፋፋት በ2007 መጨረሻ ላይ የተደረሰበትን 2.4 ሚሊዮን ሄክታር በመርሃ ግብሩ ዘመን 1,743,000 ሄ/ር በተጨማሪ በመስራት በ2012 መጨረሻ ወደ 4,043,000 ሄክታር መሬት ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በዘመናዊ አነስተኛ መስኖ የለማው 1,492,000 ሄክታር መሬት የመስኖ አውታሮች የማሻሻልና ጥገና ተደርጎላቸው እንዲስፋፉ ግብ ተጥሏል፡፡ በተመሳሳይ በቀጣይ አምስት ዓመታት 8,720 የተለያዩ የውሃ አማራጮች (የመስኖ አውታሮች) በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ለመገንባት የታቀደ ሲሆን በ2012 መጨረሻ 80 ከመቶ የሚሆኑት አነስተኛ ማሳ ተጠቃሚ አርሶ/ከፊል አርሶ አደሮች ቢያንስ አንድ የውሀ አማራጭ እንዲኖራቸው በማድረግ ከዚህ ውስጥ 50 ከመቶ የሚሆኑት ዘመናዊ የመስኖ እርሻን ሙሉ ፓኬጅ እንዲጠቀሙ ለማድረግ ግብ ተጥሏል፡፡

በሌላ በኩል የተለያዩ የስነ-አካላዊና የስነ-ህይወታዊ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ስራዎች የተከናወኑባቸውና ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ተከልለው እንዲያገግሙ የሚደረጉ 9 ተፋሰሶችን እያንዳንዳቸው በአማካይ 250 ሄክታር በጠቅላላው 2250 ሄክታር የሚሸፍን መሬት ላይ የካርቦን ክምችት ለውጡን ለማወቅ እንዲቻል በየዓመቱ በተከታታይ በዚሁ መሬት ላይ የካርቦን ይዘቱን የመለካት ሥራ ለማከናዎን ታቅዷል፡፡

## 2.4. የእንስሳት እና ዓሣ ምርታማነትና ምርት

የእንስሳትን ምርታማነት ማሳደግ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ልዩ ትኩረት የሚሠጠው ሲሆን ከዲቃላ የወተት ከብቶች በ2007 በቀን የሚመረተውን 8 ሊትር በ2012 መጨረሻ 12 ሊትር ማድረስና የዳልጋ ከብት ስጋ ምርታማነትን በ2007 ካለበት 107 ኪሎ ግራም ካርካስ ክብደት በ2012 መጨረሻ 138 ኪሎ ግራም ለማድረስ ግቦች ተጥለዋል፡፡ በተጨማሪም ከአንድ ዘመናዊ (ባለፍሬም) ቀፎ በአንድ ቆረጣ የሚገኝ አማካይ የማር ምርት በ2007 ካለበት 20 ኪሎ ግራም በ2012 መጨረሻ ወደ 30 ኪሎ ግራም ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሏል፡፡

የንዑስ ዘርፉን ምርት ለማሳደግ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የሚከተሉት ግቦች ተጥለዋል፡፡ በአገሪቱ የሥጋ (የከብት፣ የበግ፣ የፍየል፣ የግመልና የዶሮ) ምርት በ2007 መጨረሻ ከነበረበት 1,321 ሺህ ቶን በ2012 መጨረሻ ላይ 2,103 ሺህ ቶን ለማድረስ ግብ የተጣለ ሲሆን የወተት ምርትን (ከከብት፣ ከፍየል፣ ከግመል) በ2007 መጨረሻ ከደረሰበት 5,304 ሚሊዮን ሊትር በ2012 መጨረሻ ላይ 9,418 ሚሊዮን ሊትር ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ በተመሳሳይ የእንቁላል ምርትን በ2007 ከደረሰበት 163 ሚሊዮን እንቁላል በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ላይ ወደ 3,938 ሚሊዮን እንቁላል ማድረስ፣ እንዲሁም የአገሪቱን የማር ምርት በ2007 መጨረሻ ከደረሰበት 60.7 ሺህ ቶን በ2012 መጨረሻ ወደ 123.9 ሺህ ቶን ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

## 2.5. ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የግብርና ምርምርን በማጠናከር ምርትና ምርታማነትን ማሻሻል

በግብርና ምርምር በአራት ንዑስ ዘርፎች ማለትም በሰብል፣ በእንስሳት፣ በአፈርና ውሃ እንዲሁም በግብርና ሜካናይዜሽን የግብርና ቴክኖሎጂዎች የሚቀርቡ ሲሆን የሚወጡ ቴክኖሎጂዎች ሁሉንም ስነ-ምህዳሮች ማለትም በቂ ዝናብ ላላቸው፣ ለሌላቸው፣ በመስኖ ለሚለሙና የአርብቶ አደሩን አካባቢዎች ከግምት ውስጥ ያስገቡ ይሆናሉ፡፡ በዚህም መሰረት በቀጣይ ዓመታት በሰብል፥ በግብርና ሜካናይዜሽን፥ በባዮ ቴክኖሎጂ እና

በግብርና ጥራትና ስነ-ምግብ ምርምር 308 ምሉዕ ቴክኖሎጂዎች የሚቀርቡ ሲሆን 448 በተጠቃሚው እጅ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን የሚያሻሽሉ ጥናቶች ይቀርባሉ፡፡ በተመሳሳይ በሰብል፣ በግብርና ሜካናይዜሽን፣ በባዮ ቴክኖሎጂ እና በግብርና ጥናትና ስነ-ምግብ፣ ግብርና ኢኮኖሚክስና ኤክስቴንሽን፣ ባዮሜትሪክስ፣ ጂ.አይ.ኤስ እና አግሮ-ሜትሮሎጂ 622 ዕውቀትና ኢንፎርሜሽን የሚቀርቡ ሲሆን በእንስሳት፣ በንብና በሐር እና በአፈርና ውሃ ምርምር 466 ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎች በቀጣዩ  አምስት ዓመታት እንደሚወጡ በዕቅድ ተይዟል፡፡

## 2.6. ዘላቂነት ያለው ሀገራዊ የብዝሀ ህይወት ጥበቃና የማህበረሰቡን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ

የብዝሀ ህይወት ጥበቃን ለማጠናከርና የህዝቦችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በንዑስ ዘርፉ የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተጥለዋል፡፡ በወካይ የግብርና ስነምህዳር በማህበራዊ ዘር ባንኮች የተነበሩ የአዝርዕትና ሆርቲካልቸር ዝርያ/አይነቴ በመጀመሪያው የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ ከተደረሰባቸው 14 ዝርያዎችና 19 አይነቴዎች በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ 24 ዝርያዎች እና 69 አይነቴዎች ለማድረስ ግብ የተጣለ ሲሆን በጂን ባንክ የተነበሩ የአዝርዕትና ሆርቲካልቸር ዝርያ እና ናሙና በ2007 ከተደረሰባቸው 52 ዝርያዎችና 70,316 ናሙናዎች በ2012 ወደ 77 ዝርያዎችና 73,416 ናሙናዎች ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በተመሳሳይ በመስክ ጂን ባንክ የተነበሩ የአዝርዕትና ሆርቲካልቸር ዝርያ እና ናሙና በ2007 ከተደረሰባቸው 10 ዝርያዎችና 6,205 ናሙናዎች በ2012 ወደ 22 ዝርያዎችና 7,155 ናሙናዎች ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡

በዘቦታ የተነበረ የደንና ግጦሽ መሬት ዕፅዋት ዝርያን በ2007 ከተደረሰበት 600 በ2012 ወደ 1000 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን ተሰብስቦ በጂን ባንክ የተነበረ የደንና ግጦሽ መሬት ዕፅዋት ዝርያና የዘር ናሙናን እንደቅደም ተከተላቸዉ በ2007 ከነበረበት 260 እና 1,998 በ2012 ወደ 560 እና 3,246 ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ በተመሳሳይ ተሰብስቦ በመስክ ጂን ባንክ የተነበረ የደንና ግጦሽ መሬት ዕፅዋት ዝርያ እና የዘር ናሙናእንደቅደም ተከተላቸዉ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ (2007) ከነበረበት 454 እና 706 በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ 654 እና1506 ለማድረስ ታቅዷል፡፡

የተቋቋመ የመስክ ጂን ባንክን ቁጥር በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ከነበረበት 14 በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ 19 ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርማሽን ዕቅድ ዘመን ከአራት ንኡስ ዝርያዎች የተሰበሰበ 30,000 የእንስሳት አባላዘር ቀስም የተነበረ ሲሆን በሁለተኛዉ የእድገትና ትራንስፎርማሽን የዕቅድ ዘመን አጠቃላይ ስድስት ንኡስ ዝርያዎች እና 2 ዝርያዎችን በኢዘቦታ ለማንበር የተሰበሰበ አባላዘር 132,600 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በዘቦታ የተነበሩ የእንስሳት ዝርያዎች/ንኡስ ዝርያዎች 15 ሲሆኑ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመን ይህንን መጠን ወደ 36 ለማሳደግ ታቅዷል፡

በመጨረሻም የአገሪቱን ብዝሀ ሕይወት ስብጥርና ስርጭት መረጃ ለማሳደግ በዘርፉ እስከአሁን የተካሄዱ ጥናቶችን በመዳሰስ እና ተጨማሪ ጥናቶችን በማካሄድ የአገሪቱን የብዝሀ ሕይወት ሀብት ስብጥርና ስርጭት የያዘ ካታሎግ በአራት ዘርፎች በማዘጋጀት ይታተማል፡፡

## 2.7. የምግብ ዋስትና፣ አደጋ መከላከልና ዝግጁነትን ማጠናከር

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት አቅምን ለማጎልበት የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አሁን ካለበት ከ405,000 ሜትሪክ ቶን ወደ 1.5 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ከፍ ለማድረግና ምግብ ነክ ያልሆነ ክምችት መጠንን ከ700 ሺህ ወደ 1422 ሺህ ለማሳደግ ግቦች ተጥለዋል፡፡ ከ2008-2012 ባለው ጊዜ ውስጥ አደጋ የሚያስከተለውን ጉዳት ለመከላከል ይቻል ዘንድ በዕቅዱ መነሻ ዓመት (2007) ያለውን 123.4 ሚሊዮን ብር የመጠባበቂያ ገንዘብ ወደ ብር 415 ሚሊዮን ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡

በመጀመሪው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አመታት በተለያዩ ድንገተኛ አደጋዎች ሳቢያ ጉዳት ለሚያጋጥማቸው ወገኖች በእቅድ ዓመቱ መጀመሪያ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ የነበረው ለ1.1 ሚሊዮን ህዝብ የነበረና በዕቅዱ መጨረሻ ዓመት ወደ 2 ሚሊዮን እንደሚደርስ ተሰልቶ የነበረ ሲሆን ከዚህ በተሻለ ሁኔታ ድንገተኛ የአደጋ ክስተት ቢከሰት ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ዝግጁነት ለመገንባት በመቻሉ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ከመነሻው ለ1.5 ሚሊዮን ህዝብ ድጋፍ ማድረግ እንደሚቻል ታሳቢ ተደርጎ ዕቅዱ ተዘጋጅቷል፡፡ የወረዳ ሪስክ ፕሮፋይል ጥናትን በተመለከተ ከ2008-2012 ባለው ጊዜ ውስጥ የ400 ወረዳዎችን ሪስክ ፕሮፋይል ለማጥናት የታቀደ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ ከወረዳ አደጋ ተጋላጭነት ጥናት ጋር ለማስተሳሰር ሲባል 677 ወረዳዎችን በኔትወርክ የማገናኘት ስራ ለማከናወን ግብ ተጥሏል፡፡

የምግብ ዋስትናን በተመለከተ ከ2008 እስከ 2012 ባለው ጊዜ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ እንደሚሆን የተገመተው ህዝብ 5.1 ሚሊዮን ሲሆን ባለፉት 3 ዓመታት ጊዜያዊ የምግብ ዋስትና ችግር ገጥሟቸው በአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ሲደገፉ የነበሩ 3.5 ሚሊዮን ተረጂዎችን በመጨመር ፕሮግራሙ ወደ 8.3 ሚሊዮን የሚደረስ ህዝብ ተጠቃሚ እንዲያደርግ ታቅዷል፡፡ በተመሳሳይ የሴፍቴኔት ፕሮግራሙ ከሌሎች የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች ጋር ተሳስሮ እንዲተገበር በማድረግ አሁን በ2007 ካለው 161,310 የቤተሰብ ሃላፊዎች (አባወራ እና እማወራ) የልማታዊ ሴፍቲኔት ተመራቂ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ በ2012 ወደ 1,000,223 የቤተሰብ ሃላፊዎች (አባወራ እና እማወራ) ወይም 5,001,116 ተመራቂዎች ለማድረስ ታቅዷል፡፡

በሌላ በኩል ከ2008-2012 ባለው ጊዜ ውስጥ የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎችን ቀዳሚ የብድር ተጠቃሚ በማድረግ በቤተሰብ ደረጃ ጥሪት እንዲገነቡ የሚደረግ ሲሆን አሁን ያለውን 233,400 በቤተሰብ ደረጃ የቤተሰብ ፓኬጅ ብድር በማግኘት ጥሪት ከገነቡት ስር የሰደደና ጊዜያዊ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸው (አባወራና እማወራ) የቤተሰብ ኃላፊዎች በእቅድ ዘመኑ ማብቂያ ወደ 628,850 (አባወራና እማወራ) የቤተሰብ ኃላፊዎች ለማድረስ ታቅዷል፡፡

በተጨማሪም በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በአለፉት ዓመታት ተግባራዊ በተደረገው የሰፈራ ፕሮግራም በተለያዩ ቦታዎች የሰፈሩ ቤተሰቦች የምግብ ዋስትናቸውን በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲያረጋግጡ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም እንደአስፈላጊነቱ በተመረጡ አካባቢዎች በክልል ውስጥ ሠፈራዎች እንዲካሄዱ ይደረጋል፡፡

### 3. የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

#### 3.1. የማስፈፀም አቅም ግንባታ ፕሮግራም

በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በግብርናው ዘርፍ መሰረታዊ ለውጥ የሚሹ በርካታ ጉዳዮች የተለዩ ሲሆን የአቅም ግንባታ ስራዎችን ከመፈጸም ባሻገር የአሰራር ስርዓት መዘርጋትን ይጠይቃል፡ ፡ በዚህም መሰረት በየስራ ዘርፎቹ የተመላከቱት እንደተጠበቁ ሆነው በእፅዋት ጥበቃና ስርዓት፣የእፅዋት ጤናና ጥራት ቁጥጥር፣ የግብርና ግብዓት አቅርቦትና የብድር አቅርቦት፣ የቡና ልማት ኤክስቴንሽን ስርዓት፣ የከተማ ግብርና፣ የገጠር ወጣቶች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ድጋፍ፣ አውትግሮወር እና ኮንትራት ግብርናና የግብርና ምርቶች ግብይት ላይ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

የማስፋት ስትራቴጂውን በተሟላ መንገድ መፈፀም እንደዋነኛ አቅጣጫ የተቀመጠ ሲሆን በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ስትራቴጂውን ለማሳካት በተደረገ ርብርብ ስትራቴጂውን የማስፈፀም አቅም በእጅጉ ጎልብቷል፡፡ የተደራጀ የልማት ሠራዊት በተፈጥሮ ሃብት መስክ የተገነባ፣ በመስኖና ሰብል ልማትም መገንባት የተጀመረ በመሆኑ ይህንኑ በተሟላ መልኩ በሁሉም ግንባሮች የመገንባትና ወደ ተሟላ የመፈፀም አቅም ማለትም ከእያንዳንዱ ንዑስ ምዕራፍ ተግባር ባሻገር በርካታ ሥራዎችን በተመሳሳይ ጊዜ በሚፈለገው መጠንና ጥራት መፈፀም ወደ ሚችል ደረጃ ማድረስ ዋነኛው

የርብርብ ማዕከል ይሆናል፡፡ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የግብርና ልማት ግቦች የሚሳኩት ይህንኑ አቅም ወደ ተሟላ የመፈፀም ብቃት በማድረስ ብቻ መሆኑ ላይ የአመለካከት አንድነት መኖሩ ሲሆን ይህንንም በእንስሳት ልማት ዘርፍ ለመድገም ርብርብ ይደረጋል፡፡

ሌላኛው ለእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግቦች መሳካት የላቀ ትኩረት ተሰጥቶት ሊተገበር የሚገባው ጉዳይ ቢኖር የቴክኖሎጂ ሽግግር ስርዓቱን በተሟላ መንገድ መገንባት ነው፡፡ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስርዓቱ የምርምርና የኤክስቴንሽን ስርፀት ስርአቶችን አጣምሮ የያዘ በመሆኑ በሁለቱም የስርዓቱ አካሎች ሊተገበሩ የሚገባቸዉን ለይቶ ማስቀመጥ ተገቢ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የግብርና ምርምር ስርዓቱን ለማጎልበት እንዲቻል ያሉበትን የአቅም ችግሮች የማቃለል ሥራ ይሰራል፡፡ የሰው ኃይሉን ያለውን ለማብቃትና ብቃት ያላቸውንም ወደ ስርዓቱ ለማስገባት ሰፊ ሥራ ይሰራል፡፡ ከዚህ አኳያ ተመራማሪዎችን በተቋሙ ውስጥ ይዞ ለማቆየት በመንግስት የተወሰደውን ርምጃ ውጤት ሊያመጣ በሚችል አግባብ በመጠቀም ያሉትን ማቆየትና ከስርዓቱ ውጭ ያሉትንም በብቃታቸው ላይ ተመስርቶ የማስገባት ሥራ ይሰራል፡፡ ተቋሙ ያለበትን የአቅም ችግር ለማቃለል የተነደፈውን የአቅም ግንባታ ኘሮጀክት በመንግስት በማፀደቅና ፋይናንስ በማስመደብ ወደ ትግበራ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

ቴክኖሎጂ በፍጥነት ከውጭ ቀድቶ በማስገባት ረገድ ያለውን ጉድለት ለመሙላት የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በተለይ ከየአገሮች የምርምር ተቋማት ሊገኝና ለሀገራችን ሊውል የሚችለውን በፍጥነት እያስገባ በምርምር እንዲላመድ በመደገፍ ለመስራት እየተደረገ ያለውን ዝግጅት በፍጥነት በማጠናቀቅ በተሟላ መልኩ እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ከዓለም አቀፍ የግብርና ምርምር ተቋማት ጋር ያለውን ትስስር የአገራችን ጥቅም በሚያስጠብቅ አግባብ በማጠናከር ቴክኖሎጂ የሚያገኝበትና በፍጥነት የሚያላምድበት ሁኔታ ይበለጥ እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡

የኤክስቴንሽን ስርዓቱን በተመለከተ ስርዓቱ አዋጭና ውጤታማ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ከማስተዋወቅና በፍጥነት ከማስፋፋት ጋር ተያይዞ ያሉበትን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል የኤክስቴንሽን ስትራቴጂ እየተዘጋጀ ያለ በመሆኑ ይህንኑ በሁሉም ደረጃ ያሉ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ፈጥኖ በማጠናቀቅ ለሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዝግጁ የሚደረግ ይሆናል፡፡

የግብርና ምርት ግብይት ስርዓቱን በተመለከተ የኢትዮጵያ ምርት ገበያን ማጠናከር እንደተጠበቀ ሆኖ ከምርት ገበያው በታች ያሉ ስርዓቶችን የማስተካከል ሥራ ተገቢው የአመራር ትኩረት አግኝቶ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ ከግብርና ምርቶች ግብይት አኳያ ወሳኝ ተቋማት የህብረት ሥራ ማህበራት በመሆናቸው የሚታየውን ተገቢዉን የፖለቲካ አመራር ያለመስጠት ጉድለት በማረም በስፋትና በጥራት የሚደራጁበትና ዋና ተዋናይ የሚሆኑበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ለዚህም ሲባል የተነደፈውን የህብረት ሥራ ማህበራት ስትራቴጂ በፍጥነትና በተሟላ ሁኔታ መተግበር ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ ከግብይት አኳያ ሌላው ትኩረት ተሰጥቶት ሊተገበር የሚገባው የግብይት መሠረተ ልማት የሚፈጠሩ ክላስተሮችን ተከትሎ የማሟላት ጉዳይ ይሆናል፡፡ በክላስተሮቹ ላይ ተመስርቶ የገበያ ትስስር ከኤክስፖርትና ከኢንዱስትሪዎች ጋር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡

ከገጠር የፋይናንስ ስርዓት አኳያ የተደራሽነትን ችግር የሚፈታና በገጠር የሚፈጠረውን ሀብት ተከትሎ ሊቆጠብ የሚገባውን ገንዘብ በአግባቡ ለማስተናገድ የሚችል የገጠር ፋይናንስ ስርዓት እንዲገነባ ይደረጋል፡፡ በዚህ ረገድ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማትን ማጠናከርና ከባንክ ጋር ያላቸውን ትስስር ማጎልበት የሚገባ ሆኖ ሁሉንም ቀበሌ ለመድረስ የሚያስችል አቅምና ከአዋጭነት አኳያ ሞዴል የሚጎላቸው በመሆኑ የገጠር የቁጠባና ብድር የህብረት ሥራ ማህበራትን በስፋት የማቋቋም ሥራ ይሰራል፡፡ በገጠር ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራትና በሌሎች የህብረት ሥራ ማህበራት ጥምረት የህብረት ሥራ ባንክ እንዲኖር ይሰራል፡፡ የተጀመረውን የግብዓት ግብይት ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በቫውቸር የአሰራር ስርዓት የሚያስተሳስር ሥራ ደረጃ በደረጃ እንዲሰፋ የማድረግ ሥራ ይሰራል፡፡ እንዲሁም የግብዓት ብድር በክልሎች በጀት መያዣነት ከሚሰራበት ለማውጣት የተቀረፀው አሰራር ታይቶ፣ ዳብሮና ፀድቆ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

በገጠር የትምህርትና ጤና አገልግሎትን በጥራት በማስፋፋት በገጠር የህዝቡን የማምረት አቅም ለመገንባት የተጀመረው እንቅስቃሴ በዋነኛነት በሴክተሮቹ የልማት ዕቅድ ላይ ተመስርቶ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የገጠር ሁለተናዊ የመንገድ ተደራሽነት፣ የገጠርና ማዕከላት የንፁህ ውሃ አቅርቦት፣ የኤሌክትሪክና የስልክ ተደራሽነትና ሽፋን በዘርፎቹ የአምስት ዓመት ዕቅድ በመመራት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ከትምህርት አኳያ ለግብርና ስራም ባለዉ ልዩ ትርጉም አንፃር የጎልማሶች ትምህርት ከአርሶአደሩ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራ ጋር ተሳስሮ የእስካሁኑን አዝጋሚ አፈፃፀም በሚያሻሽል አግባብ እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

በአጠቃላይ በዘርፉ የታቀዱ ግቦችን ለማሳካት የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም ግንባታ ላይ ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን ከባለድርሻ አካላት ጋር በተቀናጀ መልኩ ለመስራት የጋራ መድረኮች የሚዘጋጁ ይሆናል፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የዘርፉን ሁለንተናዊ አቅም ለማሳደግ በሰው ሃይል፣ በአሰራር ስርዓትና በአደረጃጀት የአቅም ግንባታ የሚደረግ ሲሆን አሁን ያለውን የህዘቡን ተሳትፎና ንቅናቄ ለማስቀጠል በርካታ የአቅም ማጎልበትና የአደረጃጀት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

### 3.2. የሰብል ምርታማነትንና ምርትን በተመለከተ

የሰብል ምርትንና ምርታማነትን ለማሳደግ በርካታ ስትራቴጂዎች ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆን እነዚህም በዋናነት የማስፋት ስትራቴጂውን በላቀ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ ናቸው፡፡ በግብርና ግብዓት አቅርቦት እና በግብርና ኤክስቴንሽን ዙሪያ በርካታ ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የአፈር ለምነትን ለማሻሻል የግብርና ምርምር ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡ የግብርና ግብይትን ዘመናዊ ማድረግና የግብርና ማህበራትን ማሳደግ ግብርናውን ዘመናዊ ከማድረግ አንፃር በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ትኩረት የሚሠጣቸው ናቸው፡፡

#### የግብርና ግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም

የግብርና ግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በግብርና ግብዓቶች አቅርቦት እና ስርጭት የታዩ ጠንካራ ጎኖችን አጎልብቶ በመሄድ እና የታዩትን ደካማ ጎኖች/ተግዳሮቶች በማስወገድ እንዲሁም እስከአሁን ያልተሞከሩ አዳዲስ አማራጮችን በመለየት የግብርና ግብዓት በወቅቱና በሚፈለገው መጠን እንዲቀርብ በማድረግ በግብርናው ዘርፍ በመመዝገብ ላይ ያለውን የኢኮኖሚ እድገት ቀጣይነት ባለው መልኩ በማስቀጠል የህዝቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የዘርፉ ዓላማ ነው፡፡

በመሆኑም በ2007 1,873,778 ኩንታል የነበረውን የምርጥ ዘር አቅርቦት በ2012 መጨረሻ 3,**559,924** ኩንታል ለማድረስና በ2007 1,223,309 ሜትሪክ ቶን የነበረውን የማዳበሪያ አቅርቦት በ2012 2,062,106 ሜትሪክ ቶን ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ በተጨማሪም የግብርና ግብዓት አጠቃቀምን ለማሳደግ በ81 ወረዳዎች ብቻ በናሙናነት የተሞከረውን የቮውቸር የግብዓት ብድር ስርዓት በሁሉም ክልሎችና ወረዳዎች ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ይህም ማለት አርሶ አደሩ የሚፈልገውን ግብዓት ለመጠቀም የብድር አቅርቦት እንዳይገድበው በሙከራ ደረጃ ላይ ያለው አዲሱ የግብርና ግብዓት የብድር ስትራቴጂ/ ስርዓት ሙሉ በሙሉ የሚተገበር ይሆናል፡፡ ለዚህም ከገጠር ብድርና ቁጠባ ተቋማት፣ ከክልል ግብርና ቢሮዎች እና ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በቅንጅት የሚሰራ ይሆናል፡፡

የዘር አቅርቦትን በተመለከተ በርካታ ተግባራት የሚከናወኑ ሲሆን የመነሻ ዘሮችን አቅርቦት መቅረፍ፣ ድርጅቶችና አርሶ አደሮች  እንዲሁም የመንግስት ዘር አባዢ ድርጅቶች ያለባቸውን የክህሎትና የማቴሪያል ችግር በመለየት አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የጥራጥሬ እና የቅባት ሰብሎች ዘር አቅርቦት እጥረት በዋናነት የተያያዘው ከሰብሎቹ ምርታማነት ዝቅተኛ መሆንና ከበሽታ መጠቃት ጋር በመሆኑ ይህን ችግር በመቅረፍ አቅርቦቱን ለማሳደግ በመጀመሪያ በግብርና ምርምር ማዕከላት ምርታማ የሆኑ እና በሽታን የሚቋቋሙ ዝርያዎች እንዲወጡ በጋራ ይሰራል፡፡

የፌደራል እና የክልል ዘር ኢንተርፕራይዞች ያለውን ሰፊ ክፍተት ለመሙላት የሚያስችላቸው የመነሻ ዘር የማባዣ የእርሻ ማሳ እና ተፈላጊው የካፒታል እና ተቋማዊ አቅም በፌደራል እና በክልል እንዲመደብላቸው እና አቅማቸውን አሳድገው እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡

ዘር በወቅቱ እንዲቀርብ እና የቀረበ ዘር ከስርጭት ሰንሰለት መንዛዛት ጋር ተያይዞ ጥቅም ላይ ሳይውል የሚከርምበትን ችግር ለመቅረፍ በሙከራ ትግበራ ላይ ያለው የቀጥታ ዘር ስርጭት ስርዓት በሁሉም ክልሎችና አካባቢዎች በሂደት እየሰፋ እንዲሄድ ይደረጋል፡፡

**የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ማስፋፋት**

የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ውጤታማ በሆነ መልኩ በአርሶና አርብቶ አደር አካባቢዎች ማስፋፋት የሰብልንና እንስሳትን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ይህም በዋናነት አርሶ አደሩን ከማማከርና ከማስተማር በተጨማሪ መሠረታዊ ሥልጠናዎችን መስጠትና የአርሶና አርብቶ አደሩን የአመለካከት ችግሮችን መቅረፍ ያጠቃልላል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ የነበረውን የአርሶ አደር ተጠቃሚ ቁጥር ከ14,014 ሺህ ወደ 16,776 ሺህ፣ የአርብቶ አደር ኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ቁጥር ከ718 ሺህ ወደ 858 ሺህ እንዲሁም የከፊል አርብቶ አደር የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ከ468 ሺህ ወደ 569 ሺህ በአጠቃላይ የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ አርሶ/አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ቁጥር ከ15,200 ሺህ ወደ 18,237 ሺህ ከፍ ለማድረግ ታቅዷል፡፡ በተመሳሳይ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ 20 ከመቶ የነበረውን የገጠር ሴት አርሶ አደር ተጠቃሚ ቁጥር በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የገጠር ሴቶችና ወጣቶች የግብርና ኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ቁጥር ወደ 30 ከመቶ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ ዓመት 35 በመቶ የነበረውን የሙሉ ፖኬጅ ተጠቃሚ ቁጥር ወደ 80 በመቶ የማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡

በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ዓመት የነበረውን 4,300 የተተኪ ባለሙያዎች ሥልጠና በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ 24,325 የሚደርስ ሲሆን በግብርና መካናይዜሽን 9,000 የልማት ሰራተኞችን በደረጃ 4፣ 9,010 የግብርና ልማት ባለሙያዎችን በስፔሻላይዜሽን እንዲሁም በየአመቱ 0.8 ሚሊዮን የገጠር ወጣቶች በተለያዩ ሙያዎች /በሰብል ልማት፣ በእንስሳት ሀብት ልማት፣ በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ፣ በመስኖ ልማት ወዘተ/ እንዲሰለጥኑ በማድረግ 4 ሚሊዮን ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ በተመሳሳይ አርሶ አደሮችን በተመረጡ እና በመረጡት የልማት መስክ በደረጃ እና በብቃት አሀድ በማሰልጠን የብቃት ምዘና ማካሄድን በተመለከተ ከ6,414,263 በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ወደ 10,330,232 እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

የአርሶና አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን መገንባትና ማጠናከር የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቱን አሰጣጥ የተቀላጠፍ ስለሚያደርገው በሚቀጥሉት አምስት አመታትም ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን አሁን የተገነቡትን 11,000 ማሰልጠኛ ማእከላት ወደ 18,000 ክፍ እንዲሉ ይደረጋል፡፡ በቁሳቁስ የማሟላት ስራ በመስራት የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ በአጠቃላይ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቱን ውጤታማ በማድረግ የማስፋት ስትራቴጂውን ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ በሚያግዝ መልኩ የሚቃኝ ይሆናል፡፡

**የህብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር**

የህብረት ስራ ማህበራትን በማጠናከር የአርሶ አደሮችንና አርብቶ አደሮችን የገብያና የግብዓት አቅርቦት ችግር ለመፍታት በሚቀጥሉት ዓምስት ዓመታት ጥረት ይደረጋል፡፡ የህብረት ሥራ ማህበራት ለአባሎቻቸው የሚሰጡት አገልግሎት ጥራት ያለው፣ ተደራሽ እንዲሆንና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን እንዲቀርፉ ለማድረግ 64,401 መሠረታዊ፣ 324 የህብረት ስራ ማህበራት ዩኒየኖችን እና 4ቱን ክልላዊ

የህብረት ሥራ ፌዴሬሽኖችን በማጠናከር የአባላትን የነፍስ ወከፍ ገቢ አባል ካልሆነው የህብረተሰብ ክፍል ገቢ የ5 በመቶ ብልጫ እንዲኖረው ማስቻል ናቸው፡፡

በህብረተሰቡ ጥያቄ መሠረት በተጠኑና በተመረጡ የሥራ መስኮች አዳዲስ የህብረት ሥራ ማህበራትን በማደራጀት በ2007 በጀት ዓመት የተደረሰበትን አፈፃፀም መነሻ በማድረግ በ2012 መጨረሻ የመሠረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር ከ59,401 ወደ 64,401 እና የህብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖችን ቁጥር ከ314 ወደ 324 ከፍ እንዲል የሚደረግ ሲሆን የሴቶችን የአባላትን ተሳትፎ 50 በመቶ እና የወጣቶች ተሳትፎ ደግሞ ከ30 በመቶ በላይ ለማድረስ ታሳቢ በማድረግ የመሠረታዊ ህብረት ስራ ማህበራትን የአባላት ቁጥር ከ13,786,707 (ወንድ 9,814,102 ሴት 3,972,605) ወደ 20,680,062 (ወንድ 10,340,031 ሴት 10,340,031) እና የዩኒየን አባል መሠረታዊ ማህበራትን ቁጥር ከ7,903 ወደ 64,401 በማድረስ የአባላትን ተሳትፎ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ የካፒታል መጠናቸውም የመሠረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት ከብር 4,160,223,051 ወደ ብር 8,320,446,102 የህብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖችን ከብር 962,967,500 ወደ ብር 3,851,870,000 እና የህብረት ስራ ፌዴሬሽኖችን ደግሞ ብር 2.5 ቢሊዮን እንዲደርስ በማድረግ የአባላትን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ግቦች ተጥለዋል፡፡ በተመሳሳይ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ልዩ ትኩረት እና ድጋፍ በመስጠት ነባር የህብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከርና በተመረጡ የስራ ዘርፎች ላይ በፌደራል ድጋፍና በክልሎች የጋራ ትብብር 2,000 መሠረታዊ እና 7 የህብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን አዳዲስ የህብረት ሥራ ማህበራትን ለማደራጀት ግብ ተጥሏል፡፡

የህብረት ሥራ ማህበራት ከተቋቋሙበት ዓላማ አንፃር በሚያደርጉት የስራ እንቅስቃሴ አባሎቻቸውን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማሳተፍ በሚያስችል ሁኔታ እንዲንቀሳቀሱ ትኩረት ሰጥቶ በመደገፍ የአባላት የባለቤትነት ስሜት የተሟላ እንዲሆን የሚያስችል የክትትልና የድጋፍ ስራ መስራት፣ሁሉም ማህበራት በተማረና ግንባር ቀደም በሆነ ጠንካራ አመራር እየተመሩ እንዲጠናከሩና በወቅቱ የህብረት ሥራ ማህበራቱን በመምራት ላይ የሚገኙት አመራሮች እንዴት እንደሚመሩና ምን የአሰራር ስልትና አቅጣጫ ተጠቅመው ተጨባጭ ውጤት ማስመዝገብ እንዳለባቸው ለማወቅ እንዲችሉ የሚያደርግ ተከታታይ የሆነ የግንዛቤና የአቅም ግንባታ ሥራ መስራት፣ነባር □ህብረት ስራ ማህበራትን በማጠናከር እና አዳዲስ የኅ/ሥራ ማህበራትን በማደራጀት በኩል የተጠናከረ ድጋፍ መስጠት፣የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚ□ደርጉት የግብይት የሥራ እንቅስቃሴ ሂደት ተገቢውን ሙያዊ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ የተጠናከረ የግብይት እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ መደገፍ፣የኅብረት ሥራ ማህበራትን በተጠና እና በተመረጠ መንገድ የአሰራር አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ የግብርና የኅብረት ሥራ ማህበራትን፣የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማህበራትንና የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራትን በግብይት ሥራ ላይ ተደጋግፈው እንዲሰሩ የማስተሳሰርና የማጠናከር ሥራ ይሰራል፡፡

**የግብርና ኢንቨስትመንትን ማበረታታት**

በግብርና ዘርፍ የግሉን ዘርፍ በማበረታታት የግብርናን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ አንዱ የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን ይህም በዋናነት በሆልቲካለቸር ልማትና በሰፋፊ እርሻዎች ልማት ላይ ያተኩራል፡ ፡ በመሆኑም የአበባ ልማት በ2007 በጀት ዓመት ይከናዎናል ተብሎ ከተሰላው ግምታዊ የግብ አፈፃፀም በመነሳት አጠቃላይ የመሬት ልማቱ በ2012 መጨረሻ ላይ 3066.4 ሄክታር ለማድረስ፣ በአትክልት ንዑስ ዘርፍ ደግሞ በ2007 መጨረሻ ከነበረበት 1443.4 ሄክታር መሬት በ2012 መጨረሻ 2325.4 ሄክታር ለማድረስና በፍራፍሬ ንዑስ ዘርፍ ደግሞ በ2007 መጨረሻ ከሚኖረው 10783.2 ሄክታር መሬት በ2012 መጨረሻ ወደ 11314.8 ሄክታር መሬት ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በኸርብስ ንዑስ ዘርፍ በ2007 በጀት ዓመት ከነበረው 138.4 ሄክታር የመሬት ልማት በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ማለትም በ2012 በጀት ዓመት ላይ 447.3 ሄክታር እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

በሌላ በኩል የሆርቲካልቸር ምርትን በማሳደግ ከዘርፉ የሚገኘውን የወጪ ንግድ ዘርፍ የገቢ እቅድ በተመለከተ ከአበባ ልማት በ2012 መጨረሻ 455 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት የታቀደ ሲሆን ከአትክልት

የወጪ ንግድ ደግሞ የሚገኘውን ገቢ በ2012 መጨረሻ 75.8 ሚሊዮን ዶላር ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ ከፍራፍሬ ኤክስፖርት የሚገኘው ገቢ በ2012 29.66 ሚሊዮን ዶላር ለማድረስ የታቀደ ሲሆን ከሽርብስ ኤክስፖርት የሚገኘው ገቢ ደግሞ በ2012 መጨረሻ 16.6 ሚሊዮን ዶላር እንዲደርስ ታቅዷል፡፡ በአጠቃላይ በ2012 ከሆርቲካልቸር የወጪ ንግድ የሚገኘውን ገቢ በ2012 መጨረሻ 577 ሚሊዮን ዶላር ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ የተጣሉትን ግቦች ተፈፃሚ ለማድረግ አዳዲስና ምርታማ የሆኑ የሆርቲካልቸር ዝርያዎችን መምረጥና ለገበያ ማቅረብ እዲሁም ገበያ ተኮር የሆኑ ዝርያዎችን የማልማት ስራዎች ይከናዎናሉ፡፡

ሌላው የግል ባለሀብቱ በግብርናው ዘርፍ የሚበረታታበት በሰፋፊ የእርሻ ልማቶች ሲሆን በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በተጠናከረ ሁኔታ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ለዚህም ለሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት ምቹ የሆኑ መሬቶችን በመለየትና ለሀገር ውስጥና ለውጭ ልማታዊ ባለሀብቶች በማስተላለፍና ተገቢውን የመሰረተ ልማት አገልግሎትና ሌሎች ድጋፎች በማመቻቸት፣ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር ስርዓት በመዘርጋት ህብረተሰቡን የልማቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ብሎም ዘርፉ ለሀገር ውስጥ ምርት አቅርቦትና በወጪ ንግድ ረገድ ያለውን ድርሻ በማጎልበት የኢኮኖሚ እድገታችንን ማፋጠን ነው፡፡

በመሆኑም በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በጥቅሉ ለኢንቨስትመንት እንዲሆን የተለየ መሬት 500 ሺህ ሄክታር ሲሆን ይህም በ2012 መጨረሻ በሀገር ደረጃ የተለየውን መሬት አጠቃላይ ስፋት 4.315 ሚሊዮን ሄክታር ያደርሰዋል፡፡ በተመሳሳይ ጊዜ የተለዩ መሬቶችን የማጥራት ስራ በስፋት ለማከናወን እቅድ የተያዘ ሲሆን በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የተጣራው የመሬት ስፋት 1.343 ሚሊዮን ሄክታር እንደሚደርስ ግብ የተቀመጠ ሲሆን እስከ 2007 መጨረሻ በአጠቃላይ እንደሚከናወን ከሚጠበቀው 1.1 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ጋር ሲደመር እስከ ሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ድረስ በአጠቃላይ የሚጣራውን መሬት ስፋት 2.443 ሚሊዮን ሄክታር ያደርሰዋል፡፡ የተለየ መሬትን ወደ ፌደራል ኢንቨስትመንት ቋት በማስገባት ረገድ ለሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የተያዘው ዕቅድ 335.5 ሺህ ሄክታር ሲሆን አሁን ካለው 2.2 ሚሊዮን ሄክታር ጋር ሲደመር በአጠቃላይ እስከ 2012 መጨረሻ የሚኖረው አፈጻጸም 2.54 ሚሊዮን ሄክታር ይደርሳል፡፡ መሬት ማስተላለፍን በተመለከተ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ወደ ባለሀብት የሚተላለፈውን የመሬት መጠን 671.8 ሺህ ሄክታር ለማድረስ ግብ የተጣለ ሲሆን አሁን ከተገመተው 2.4 ሚሊዮን ሄክታር ጋር ሲደመር 3.1 ሚሊዮን ሄክታር ያደርሰዋል፡፡

በግብርናው ዘርፍ የግሉን ኢኮኖሚ ተሳትፎ ለማሳደግ በርካታ ተግባራት የሚከናወኑ ሲሆን የዘርፉን የመፈጸምና የመስፈጸም አቅም መገንባት፣ የጉልበት ሰራተኛ አቅርቦት ችግሮችን ለመፍታት ለሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት እንዲፈታ መስራት፣ የመልካም አስተዳደርና ኪራይ ሰብሳቢነት ችግሮችን በህዝብ ንቅናቄ በመፍታት ምቹ የኢንቨስትመንት አካባቢ መፍጠር፣ እስከ አሁን ለባለሀብቶች የተላለፉ መሬቶች (2.3 ሚሊዮን ሄክታር) በተሟላ ሁኔታ ወደ ልማት እንዲገቡ ማድረግ፣ ተከታታይ የመሬት አጠቃቀም ግምገማ በማድረግና ክትትልና ድጋፍ በመስጠት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ ብሎም ዘርፉ ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት የላቀ ድርሻ እንዲያበረክት ማድረግ፣ ህዝብ ያልሰፈረባቸው፣ መንግስት ለተለያዩ አገልግሎቶች በእቅድ ያልያዛቸው ሰፋፊና ለግብርና ኢንቨስትመንት ተስማሚ የሆኑ መሬቶችን በመለየትና በማዘጋጀት በመሬት ባንክ ማደራጀትና ለባለሀብት በአግባቡ ማስተላለፍ፣ የተለያዩ የገጠር መሰረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲሟሉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በትጋት መስራት፣ በዘርፉ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች እንዲሳተፉ ማበረታታት፣ የውጭ ባለሀብቶችን በጥንቃቄ መሳብ፣ የግብአት አቅርቦት ማመቻቸትና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ተግባራት ማከናወን ትኩረት የሚሰጣቸው የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ናቸው፡፡

### 3.3. የእንስሳትን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ

ሀገሪቱ ያላትን የእንስሳት ሀብት አቅም በአግባቡ ለመጠቀምና ከዘርፉ የምታገኘውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም ለማሳደግ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን ዘርፉን ለማሳደግ የእንስሳትን ዝርያ በማሻሻል፣ የእንስሳት ጤና ሽፋን፣ የአገልግሎት ጥራትና ቁጥጥርን በማሳደግ፣ የእንስሳት መኖ ምርትን በማሻሻል ረገድ በርካታ ተግባራት ተፈፃሚ ይሆናሉ።

በመሆኑም የእንስሳት ዝርያን ለማሻሻል በቀጣዩ 5 ዓመታት ዝርያቸው የተሻሻሉ የዳልጋ ከብት ብዛት በ2007 መጨረሻ ካለው 779,147 ወደ 4,902,000 ማድረስ፣ የመስክ ማዳቀል አገልግሎት ውጤታማነትን/Field Artificial Insemination Efficiency/ በ2007 ካለው የድቀላ ድግግሞሽ በአማካኝ 2.4 ዶዝ አባለዘር የጥቂ ድግግሞሹን 2.0 ማድረስ፣ፈሳሽ ናይትሮጂን በ2007 ካለበት 465,000 ሊትር በአማካይ በዓመት በ6.95% በማሳደግ 650,000 ሊትር ምርት ማድረስ፣ ፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማዕከላት በ2007 ካለው 21 ወደ 30 ማሳደግ፣ የአባለዘር ምርት በፌዴራልና በክልል አምስት ላቦራቶሪዎች የሚመረት አባለዘር አሁን ካለበት 1 ሚሊዮን ወደ 5.3 ሚሊዮን ማድረስና ዓመታዊ የማዳቀል አግልግሎት ከ1.75 ሚሊዮን ወደ 5.2 ሚሊዮን ማድረስ ዋና ዋና ግቦች ናቸው።

የእንስሳት ጤና ሽፋንን በተመለከተ አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ጥራት ያለው የእንስሳት በሽታ መከላከያ ክትባት አመታዊ ምርት አሁን ካለበት 226 ሚሊዮን ዶዝ ወደ 306 ሚሊዮን ዶዝ ማሳደግ፣ የወረዳዎች ወርሃዊ የበሽታ ክስተት ሪፖርት የመላክ ምጣኔ በ2007 ካለበት 45 በመቶ ወደ 85 በመቶ ከፍ ማድረግ፣ በሞባይል ላይ የተመሰረተ የበሽታ ክስተት ሪፖርት የሚደረግባቸውን ጣቢያዎች ከ300 ወደ 3600 ማሳደግ፣ የእንስሳት ጤና ክሊኒክ አገልግሎት ተዳራሽነት በ2007 ከደረሰበት 60 በመቶ ወደ 85 በመቶ ማሳደግ፣ የእንስሳት ልየታ ምዝገባና የሆልዮሽ ክትትል ትግበራን በመጀመር ከእቅዱ መጀመሪያ አመት 17.5 ሺህ እንስሳትን በማቀፍ በእቅዱ መጨረሻ 400 ሺህ እንስሳት እንዲታቀፉ ማድረግ፣ በአርብቶ አደር አካባቢ የበጎችና ፍየሎች የደስታ መሰል በሽታ ክስተትን ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር፣ የበጎችና ፍየሎች የውጭ ጥገኛና ሌሎች የቆዳ በሽታዎችን በመቆጣጠር በእንስሳቱ ላይና በሌጦው ላይ የሚደርሰውን የጥራት ጉድለት መቀነስ፣ከቆላ ዝንብና ከገንዲ በሽታ ነጻ የሆነ መሬት ስፋት በ2007 ካለበት 58,500 ካ.ኪ.ሜ በ2012 91,500 ካ.ኪ.ሜ ማድረስ፣ በስጋት ላይ የተመሰረተው የክትባት አገልግሎት ሽፋን አሁን ካለበት 70 በመቶ ወደ 95 በመቶ ከፍ እንዲል ማድረግ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የእንስሳት መኖ ምርትን ማሻሻል በተመለከተ የመኖ ምርት በ2007 ካለበት 68 ሚሊዮን ቶን ወደ 184 ሚሊዮን ቶን ለማድረስ፣ የለማ የወል ግጦሽ መሬትና ሬንጅላንድ በ2007 ከደረሰበት 1.32 ሚሊዮን ሄክታር በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ 4 ሚሊዮን ሄክታር ማድረስ፣የግል ግጦሽ ልማትን በተመለከተ በ2007 ከደረሰበት 59,452 ሄ/ር በአማካይ በየአመቱ 22 በመቶ በማሳደግ በዕቅድ ዓመቱ መጨረሻ 160681 ሄክታር ማድረስ፣ጥራቱ ተረጋግጦ ወደ ሃገር የሚገባ የመኖ መጠን ከ1.2 ሺህ ቶን ወደ 2 ሺህ ቶን ማሳደግ፣የመኖ ምርቶች ጥራትና ደህንነት ምርመራና አሰራር መመርያ መስፈርት ያሟሉ አምራቾች በ2007 ከደረሰበት 40 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማሳደግ፣ አጠቃላይ (annual and perinnials) የመኖ ዘር ምርት አሁን ካለበት 2.2 ሺህ ቶን በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 8.9 ሺህ ቶን፣ የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርት ከ1.5 ሚሊዮን ቶን ወደ 3.3 ሚሊዮን ቶን ለማሳደግ ታቅዷል።

### 3.4. የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና አጠቃቀም

በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና አጠቃቀም ዙሪያ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ባለድረሻ አካላት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ለማድረግ ለዚህም ምቹ ሁኔታዎች የሚፈጠሩ ይሆናል። በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የታየውን የህዝብ ንቅናቄ በማስቀጠልና ህዝቡን ከተፈጥሮ ሀብት ጥበቃው ተጠቃሚ የሚሆንበት ስልቶች የሚቀየሱ ይሆናል። በሌላ በኩል የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና አጠቃቀምን ለማሳደግ በቂ እርጥበት የሚያገኙ አካባቢዎች የዝናብ ውሀን በላቀ ደረጃ በመጠቀም የግብርና ምርታማነትና ምርትን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ እና በእርጥበት አጠር አካባቢዎች ውሀን መያዝና አነስተኛ የመስኖ ልማትን

በመጠቀም ልማትን ማፋጠንና የአካባቢውን አፈርና ውሃ መጠበቅ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ የተፈጥሮ ሀብትን መልሶ ለማቋቋምና ያሉትን በአግባቡ ለመጠቀም የእንስሳት ሀብት ልማት ከተፈጥሮ ሀብት ልማት ጋር ተቀናጅቶ ይተገበራል፡፡

### 3.5. ዘላቂነት ያለው ሀገራዊ የብዝሀ ህይወት ጥበቃና የማህበረሰቡን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ

ዘላቂነት ያለው የብዝሀ ህይወት ጥበቃን ለማሳዳግ የብዝሀ ሕይወት የዘቦታና ኢዘቦታ ጥበቃን በይዘትና ሽፋን በማሳደግ ረግድ በርካታ ስራዎች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ ይህንን በማድረግና ዘላቂነት ያለው የብዝሀ ህይወት አጠቃቀምን በማጠናከር የአገሪቱንና የማህበረሰቡን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ የተላያዩ የሰብልና የአዘርዕት ዝርያዎችን በማቅረብ በርካታ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ የወራሪና መጤ ዝርያዎች ዝውውርና መስፋፋትን መቆጣጠርና በሀገሪቱ ብዘሀ ሕይወት ሀብት ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት በመቀነስ ዙሪያ በርካታ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ በአጠቃላይ ዘላቂ የብዝሀ ህይወት ጥበቃን ለማሳደግና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መመሪያዎችና ማኑዋሎች ተዘጋጅተው ተግባረዊ ይደረጋሉ፡፡

### 3.6. የምግብ ዋስትና፣ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት

አደጋን ለመከላከልና የምግብ  ዋስትናን ለማረጋገጥ የተለያዩ ስትራቴጂዎች ተነድፈው ተግባራዊ እየተደረጉ ሲሆን በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመንም ተጠናከረው የሚቀጥሉ ይሆናል፡፡ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነትን ለማጎለበት የመጠባበቂያ የምግብ ክምችት አቅምን ማሳደግ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓትን ማሻሻልና እንዲሁም በድንገተኛ አደጋ ወቅት አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ምግብ-ነክ ያልሆነ ክምችትን መያዝ ዋና ዋና ስትራቴጂዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም  የመጠባበቂያ ፈንድ መገንባት ሌላው ስትራቴጂ ነው፡፡ በሌላ በኩል አደጋን ለመከላከል የወረዳ አደጋ ተጋላጭነት ጥናት(Woreda Disaster Risk Profile) ማካሄድ ሌላው የማስፈፀሚያ ስልት ነው፡፡ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ረግድ የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራምን የማጠናከርና ሌሎች ተጓዳኝ የምረቃ ፕረግራሙን የሚያበረታቱ ተግባራት የሚከናዎኑ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ውጤታማ የሰፈራ ፕሮግራምን ማጠናከርና የቤተሰብ ጥሪትን ለመገንባት የሚያስችል የብድር አቅርቦት ስርዓትን ማሻሻል በቀጣይ አምስት ዓመታት ተግባራዊ የሚደረጉ የማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

### 3.7 የአርብቶ አደሩ አካባቢ የግብርና ልማት

በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በአርብቶ አደሩ አካባቢ ለእንስሳትና ለሰው መጠጥ ውሃ የማዳረስ፣ የከርሰ ምድርና ገፀ-ምድር ውሀን በመጠቀም የመስኖ ስራ ማስፋፋት፣ የአርብቶ አደር ግብርና ኤክስቴሽን ስርዓቱን ማጠናከር፣የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማትንና መሰረተ ልማትን በተቀናጀ መልኩ መተግበር፣ የተቋማዊ አቅም ግንባታ ሥራ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል፡፡ በዚሁም መሰረት ለሰውና እንስሳት መጠጥ አገልግሎት የሚውሉ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ተቀርፀዉ ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆን ለመስኖ ሊውል የሚችለውን የገጸ-ምድርና የከርሰ ምድር ውሃን በመጠቀም አዋጪ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን በመምረጥ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በተለዩ የልማት ኮሪደሮች ተደራሽ የሚያደርጉ መንገዶችና ድልድዮች እንዲገነቡ የሚደረጉ ሲሆን በተመረጡ የልማት ማዕከላት የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አግልግሎት መስጫ ተቋማት ተሟልተው አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ የማስፈጸም አቅም ከመገንባት አንጻር ከተፋሰስ ልማት ፕሮግራም ጋር ተያይዞ የክልሎቹን የማስፈጸም አቅም መገንባት ወሳኝ ተግባር ተደርጎ የተወሰደ በመሆኑ በተለይ በውሃና መንገድ ግንባታ የሚታየውን የማስፈጸም አቅም ማነቆ ከመፍታት አንጻር ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

### 3.1.2 የኢንዱስትሪ ልማትና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ

#### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

የኢንዱስትሪ ዘርፍ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2017 ለተፈጥሮ አካባቢ ምቹ የሆነና ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ በአፍሪካ ቀዳሚና በአለምቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ፣ ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም ቀላል የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የመገንባት፣ የስትራቴጂክ ከባድ ኢንዱስትሪዎችን ልማት በማፋጠንና በማሳደግ በኢንዱስትሪ የዳበረች ሀገር ለመፍጠር የሚያስችሉ ኢንዱስትሪዎችን መሠረት የመጣል ራዕይ አስቀምጦ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ከዚህ አንፃር በ2017 ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ እንዲሁም ከፍተኛ ካፒታል የሚጠይቁ ከባድ ኢንዱስትሪዎች በዘርፉ ልማት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ የሚይዙበት ይሆናል።

በዚህም መሠረት በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት (2008-2012) ሰፊ የሰው ጉልበት የሚጠቀሙ በዓለም አቀፍ ደረጃ በምርታማነት፣ በጥራት እና በዋጋ ተወዳዳሪ የሆኑ ቀላል የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ንዑስ ዘርፍ ለመገንባት ለዘርፉ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ በተለይም የከፍተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው አስተማማኝ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ እንዲሆን የሚደረግ ሲሆን የኢንዱስትሪያል ኢንጂነሪግና የቴክኖሎጂ አቅም የሚዳብርበትም ይሆናል። ከዚህ አንፃር ለነባር ኢንዱስትሪዎች አቅም ማሳደግ፣ ለአዳዲስ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት፣ የውጭና የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶችን በብዛትና በጥራት ለመሳብ፣ ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን ልማት ከቀላል ኢንዱስትሪዎች ልማት ጋር ለማስተሳሰር፣ ከባድ የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ፣ የኬሚካልና የፋርማሲቲካልስ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። ኤክስፖርትና ስትራቴጂክ ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች መተካት ተመጋጋቢ ሆነው መፈፀማቸው ይረጋገጣል።

ከዚህም በተጨማሪ ቀጣይነት ያለው የኢንዱስትሪ ልማትንና ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ የሚያስችሉ የዘርፍና የንዑስ ዘርፍ ፖሊሲዎች ተቀርፀው ተግባራዊ ይደረጋሉ። ነባሮቹን ፖሊሲዎች ከውጤታማነት ጋር በማስተሳሰር የሚጠበቀውን ውጤት ለማረጋገጥ የተሟላ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል። ለዚህም ሁለንተናዊ አቅምን የመገንባት፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የማስፋፋትና ክላስተሮች እንዲፈጠሩ የማድረግ፣ በውጭና በአገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶች መካከል የገበያ፣ የቴክኖሎጂና የማኔጅመንት ዕውቀት ሽግግር ለማረጋገጥ የሚያስችል ትስስር የመፍጠር፣ ስትራቴጂክ የሆኑና የገበያ ክፍተቶች የሚታይባቸውን የሥራ መስኮችን የመለየት እና በመንግስት ጣልቃገብነትና በጋራ ልማት እንዲሁም በተናጠል የሚሠሩ የልማት መስኮች የማመቻቸት ሥራዎች በከፍተኛ ትኩረት ተይዘው የሚከናወኑ ይሆናል።

በዘርፉ በአጠቃላይና በማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፍ በተለይ ብቃት ያለው አመራርና አደረጃጀት መፍጠር፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማስፈን፣ በአህጉርና ዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማብቃት፣ የግብርናና ኢንዱስትሪን፣ የባለድርሻ አካላትን፣ የመንግሥትንና የግሉን ዘርፍ፣ የሰራተኛንና የባለሃብት ቅንጅቶችን በላቀ ደረጃ ማሳደግ፣ በማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፍ ዕድገት የሁሉንም ህብረተሰብ በተለይም የወጣቶችና የሴቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ ነጻ ውድድርን የሚያሰፍን፣ ማህበራዊ ልማትን የሚደግፍ፣ የአካባቢ ተጽእኖን የማያስከትል አረንጓዴ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዕድገትን ማረጋገጥ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው።

#### 2. ዓላማዎች

በሚቀጠሉት አሥር ዓመታት የዘርፉ ዋና ዓላማ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን በምርትና ምርታማነት፣ በኤክስፖርት ድርሻ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ቀዳሚና የመሪነት ሥፍራ እንዲይዝ ማድረግ ነው። በዚህ መሠረት በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ዕሴት የመጨመር አቅም በማሳደግ የማኑፋክቸሪንግ ምርቶችን በዓይነት፣ በብዛትና በጥራት በማምረት

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ እንዲሆን ማድረግ፣ ስትራቴጂክ ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በሚመረቱ ምርቶች በመተካት የውጭ ምንዛሬን ማዳን እና የኢንዱስትሪ ዘርፉ በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነቱን ሥፍራ እንዲይዝ የማስቻል ዓላማዎች ተይዘው ይሠራሉ፡፡

ከፍ ብሎ በተገለፁ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዓላማዎች ሥር (1) ከፍተኛ የምርትና የምርታማነት ዕድገት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የኢኮኖሚ አወቃቀር ትራንስፎርሜሽን ለማምጣት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ወሳኝ የዕድገት ሞተር መሆን መቻሉንና ዕድገቱም ቀጣይነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ (2) የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን የዕድገት እመርታ ለማሳካት ከቀጣይ ዕድገቶች ጋር የተጣመረ ጠንካራ የሰው ሃብት ልማት ውጤቶችን በማረጋገጥ ለልማታዊ ባለሀብት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ ልማታዊ አስተሳሰብ መገንባት፣ የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጮችን መዝጋት (3) የአገር ውስጥ ባለሀብት በማኑፋክቸሪንግ የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ እንዲሰማራ ምቹ ሁኔታ መፍጠርና ስኬታማ ሽግግር እንዲኖር ማድረግ እና (4) የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ዕድገትና ተወዳዳሪነትን ቀጣይነት ያለው ለማድረግ የሚያስችሉ ደጋፊ ፖሊሲዎችን፣ የህግ ማዕቀፎችን፣ አደራጃጀቶችንና አሰራሮችን ማመቻቸትና ተግባራዊነታቸውን ማረጋገጥ የሚሉት በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ተፈፃሚ የሚደረጉ ንዑስ ዓላማዎች ናቸው፡፡

## 3. የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ግቦች

የኢንዱስትሪውን ዘርፍ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በየዓመቱ በአማካይ በ20 በመቶ ለማሳደግ እና ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ በ2006 ከነበረት 14.3 በመቶ በ2012 ወደ 22 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ በተመሳሳይ ጥቃቅንና አነስተኛን ጨምሮ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን በየዓመቱ በአማካይ 24 በመቶ በማሳደግ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ በ2007 ከነበረበት 4.6 በመቶ በ2012 ወደ 8 በመቶ ከፍ ለማድረግ ግብ ተቀምጧል፡፡ የጥቃቅንና አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ፈጣን ዕድገት በማረጋገጥ እና ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸውን ድርሻ በየዓመቱ በአማካይ በ0.38 በማሳደግ በ2007 ካለበት 1.3 በመቶ በ2012 ወደ 3.2 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡

በ2012 ይደረስበታል ተብሎ የተያዘው የ8 በመቶ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ ግብ ሊሳካ የሚችለው በአብዛኛው በአግሮ-ፕሮሴሲንግ ኢንዱስትሪዎች ዙሪያ በሚሠሩ የተቀናጁና የተደራጁ ሥራዎች ነው፡፡ ይህም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው የዕድገት ግብ ከግብርና ዘርፍ ጋር በጥብቅ ተሳስሮና ተመጋግቦ መፈፀም እንዳለበት ግድ ይላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኬሚካልና ፋርማሲቲካልስ ኢንዱስትሪዎች፣ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች፣ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች፣ የብረታብረትና ኢንጂኔሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣ የስጋ፣ ወተትና ማር ኢንዱስተሪዎች የአይ.ሲ.ቲና ኤሌክትሮኒክስ ኢንዱስትሪዎች፣ የፔትሮ-ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች፣ የባዮ-ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪዎች ተጠናክረውና ተስፋፍተው በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ለተቀመጠው የዕድገት ግብ ስኬት የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ዝርዝር ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ በኢንዱስትሪ ዘርፍና በማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፍ የተቀመጡ ግቦችን በማሳካት በኢኮኖሚው ውስጥ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ታቅዷል፡፡

ከሥራ ስምሪት አንፃር በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በመካከለኛና በከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በአጠቃላይ ለ750 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ግብ ተጥሏል፡፡ የሚፈጠረው የሥራ ዕድል 60 በመቶ እስከ መካከለኛ የዕውቀት ደረጃ ለሚጠይቁ ሥራዎች፣ 20 በመቶ ከፍተኛ የዕውቀት ደረጃ ለሚጠይቁ ሥራዎች እና 20 በመቶ ሴቶች ለሚሳተፉባቸው የልማት ሥራዎች የታቀደ ነው፡፡

ኤክስፖርትን በሚመለከት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ በአጠቃላይና የመካከለኛ እና የከፍተኛ ኢንዱስትሪ በተለይ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የውጭ ምንዛሬ ገቢን ከማስገኘት አንፃር ከፍተኛ

ዕመርታ እንደሚያስመዘግብ ይጠበቃል፡፡ በዚህም መሠረት የመካከለኛ እና የከፍተኛ ኢንዱስትሪ ኤክስፖርት ገቢ በ2006 ከነበረበት 0.398 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በየዓመቱ በአማካይ የ98 በመቶ ጭማሪ በማስመዝገብ በ2012 ወደ 4.657 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡ ይህ የኤክስፖርት ግብ በአብዛኛው ከስኳር፣ ከጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች እንደሚመነጭ የሚጠበቅ ሲሆን የቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ ሥጋና የሥጋ ውጤቶችና ማር፣ ምግብና መጠጥ፣ ፋርማሲቲካልስ፣ የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ውጤቶች፣ የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች፣ ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች የበኩላቸውን ድርሻ እንዲያበረክቱ የሚያስችል ዝርዝር ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

### 3.1 የጨርቃጨርቅና አልባሣት ኢንዱስትሪ ዋና ዋና ግቦች

የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪውን የማምረት አቅም፣ ምርታማነት፣ የምርት ጥራት እና ተወዳዳሪነት በማሻሻል፣ ጥራት ያለውን ኢንቨስትመንት በብዛት መሣብ፣ አስተማማኝና ጥራቱን የጠበቀ የግብአት አቅርቦትን በማረጋገጥ፣ የገበያና የግብአት ትስስር እንዲፈጠር በማድረግ፣ የኤክስፖርት አፈጻጸሙን በከፍተኛ ደረጃ በማሣደግ፣ ሰፊ የሥራ እድል በመፍጠርና ለመዋቅራዊ ለውጥ ያለበትን ድርሻ እንዲወጣ በማድረግ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ (በ2012) 8.7 ቢሊዩን የአሜሪካ ዶላር ዋጋ ያላቸው ምርቶችን በማምረት 1 ቢሊዩን የአሜሪካን ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ለማግኘት ታቅዷል፡፡ ይህንን ግብ ለማሳካት የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም 94,922 ቶን መዳመጫ፣ 313.28 ሺህ ቶን ፈትል፣ 757.72 ሚ.ካ.ሜ ሽመና፣ 179.66 ሺህ ቶን ኒቲንግ፣ 592 ሚ.ካ.ሜ ማጠናቀቂያ ውብን፣ 14.47 ሺህ ቶን ማጠናቀቂያ ኒቲድ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ የኢንዱስትሪዎቻችን አማካይ የማምረት አቅም አጠቃቀም በ2012 ወደ 80 በመቶ ያድጋል፡፡ እንዲሁም የአልባሣት ምርታማነትን 12 ደቂቃ በቲሸርት ለማድረስ፣ የጥሬ ጥጥ ምርትን ወደ 1.4 ሚሊዩን ቶን ለማድረስ እና 99,653 ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ግብ ተጥሏል፡፡

### 3.2 የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዋና ዋና ግቦች

የላቀ የቴክኖሎጂ ብቃትንና የምርትና ምርታማነት አቅምን በማሣደግ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን ወደ ንዑስ ዘርፉ በመሣብና ወደ ሥራ በማስገባት፣ ቀጣይነት ያለው አስተማማኝ ልማትን በማረጋገጥ፣ ሁለንተናዊ የመፈፀም አቅም በማጐልበት፣ የውጭ ምንዛሪን በማሣደግ፣ እሴት የሚጨምርና ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ የግብይት ሥርዓት በመፍጠር፣ ቅንጅታዊ ሥራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት 8.4 ቢሊዩን የአሜሪካን ዶላር ዋጋ ያላቸው ምርቶችን ማምረት እና 800 ሚሊዩን የአሜሪካን ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ለማስገኘት ግብ ተጥሏል፡፡ ይህንን ግብ ለማሳካት ምርታማነትን ወደ 6.96 ጥንድ ጫማ /በሰው ቀን/ እና 9.93 ጥንድ ጓንት /በሰው ቀን/ ለማሣደግ፣ አማካይ የአቅም አጠቃቀምን በአማካይ 85 በመቶ ለማድረስ፣ የማምረት አቅምን ወደ 551.1 ሚሊዩን ካ.ጫ ቆዳ ማድረስ፣ 75.2 ሚሊዩን ጥንድ ጫማ፣ 12.78 ሚሊዩን ጥንድ ጓንት፣ የቆዳ ዕቃዎችን 2.75 ሚሊዩን፣ የቆዳ አልባሣትን ወደ 0.45 ሚሊዩን ለማድረስ ግቦች ተጥለዋል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ በአጠቃላይ 94,000 ለሚሆኑ ዜጎች አዲስ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዷል፡፡

### 3.3 የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ዋና ዋና ግቦች

የዲዛይንና የማኑፋክቸሪንግ አቅም በመገንባት የብረታ ብረትና ስቲል ውጤቶች፣ የማሽነሪና ኢኩዊኘመንቶችን፣ የአውቶሞቲቭና ሌሎች ተሽከርካሪዎች የኤሌክትሮኒክስና ኤሌክትሪካል ምርቶችን ለማምረት ሌሎች ኢንዱስትሪዎችን ለመደገፍና የምርት መጠን ጥራትና ምርታማነትን ለማሣደግ፣ ስትራቴጂክ የገቢ ምርቶችን ለመተካትና ለኤክስፖርት ምርቶች የገበያ መዳረሻን ለማስፋት ብር 376 ቢሊዩን ዋጋ ያላቸው የብረታብረት ምርቶችን ማምረት፣ የብረታብረት የነፍስ ወከፍ ፍጆታን በ2012 ወደ 813.41 ኪ.ግ ማድረስ፣ በ2012 ኤክስፖርት ገቢን ወደ 527 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማሣደግ እና ለ46,000 ዜጎች

የሥራ እድል መፍጠር የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የብረታብረትና ኢንጂኔሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ዋና ዋና ግቦች ናቸው፡፡

## 3.4 የሥጋ፣ ወተትና ማር ኢንዱስትሪ ዋና ዋና ግቦች

የኢንዱስትሪውን የማምረት አቅም አጠቃቀም በማሻሻል፣ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ የተሻለ ተሞክሮ ካላቸው ተቋማት ጋር በማስተሳሰር፣ የምርቶችን መጠንና ጥራት በማሻሻል ገበያን በማስፋፋት የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ በኢኮኖሚው ወስጥ ያለውን ድርሻና የኤክስፖርት ገቢን ማሳደግ፣ የውጭ ምንዛሬን ለማዳን 92.2 ሺ ቶን የሥጋና እርድ ተረፈ ምርት፣1.7 ሺ ቶን የተቀነባበረ የማር ምርት፣0.6 ሺ ቶን የተቀነባበረ የሰም ምርት፣ 2.6 ሺ ቶን የተቀነባበረ የዓሳ ምርት፣ 8.3 ሚሊዮን ሊትር የወተትና የወተት ውጤቶች ምርት ወደ ውጭ መላክ እና 470 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ገቢ ለማስገኘት ግብ ተጥሏል፡፡ በተጨማሪም 9.56 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ዕቅድ ተይዟል፡፡

## 3.5 የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት ኢንዱስትሪ ዋና ዋና ግቦች

በሀገር ውስጥ የሚገኙ መሠረታዊ ግብዓቶችን በመጠቀም ለግብርናና ኢንዱስትሪ ዘርፎች ኤክስፖርት ግብዓት የሚያቀርቡ መሠረታዊ የኬሚካል ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም የውጭ ምንዛሬ ለማዳን በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት የኮንስትራክሽን ግብዓት ምርቶችን 25.67 ቶን ለማድረስ እና ከኮንስትራክሽን ግብዓቶች ምርት ኤክስፖርት 100 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ግብ ተጥሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኢንዱስትሪውን የአጠቃቀም አቅም ወደ 90 በመቶ ማሳደግ፣ የመሰረታዊ ኬሚካል ምርትን ወደ 368000 ቶን ማሳደግ፣ የሶዳ አሽ ምርትን ወደ 200,000 ቶን ማሳደግ፣ የማዳበሪያ ምርትን ወደ 1.95 ሚ.ቶን ማድረስ፣ የሣሙናና ዲተርጀንት ምርትን ወደ 260,000 ቶን ማድረስ የፐልፕና ወረቀት ምርትን ወደ 600,000 ቶን እና የፕላስቲክና ተዛማጅ ምርቶችን ወደ 180000 ቶን ማድረስ የኢንዱስትሪው ዋና ዋና ግቦች ናቸው፡፡

## 3.6 የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ዋና ዋና ግቦች

የምርት ጥራትን በማሻሻልና የወጪ ንግድ ስራዎችን ቀልጣፋ በማድረግ የኤክስፖርት ግኝትን ለማሳደግ፣ የገቢ ምርቶችን ለመተካት፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሃብቶችን በመሳብ በአዳዲስ ኢንቨስትመንት በማሳተፍ በዕቅድ ዘመኑ የመጨረሻ ዓመት የምግብ ምርት መጠን በ2007 ዓ.ም ከነበረበት 3.8 ሚሊዮን ቶን ወደ 8.8 ሚሊዮን ቶን፣ የምግብ ኢንዱስትሪ አቅም አጠቃቀም ከ56 በመቶ ወደ 90 በመቶ፣ እንዲሁም የመጠጥ ኢንዱስትሪ አቅም አጠቃቀም 100 በመቶ በማድረስ ምርትና ምርታማነቱን ማሳደግና ከዘርፉ የሚገኘውን የውጪ ምንዛሬ ገቢ በ2007 ከደረሰበት 100 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወደ 450 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ በተጨማሪም የስኳር ዓመታዊ ምርትን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 4.9 ሚሊዮን ቶን በማድረስ 1200 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጪ ምንዛሬ ገቢ ማስገኘት ዋና ዋና ግቦች ናቸው፡፡

## 3.7 የፋርማሲዩቲካልስ ኢንዱስትሪ ዋና ዋና ግቦች

በፋርማሲዩቲካልስ ኢንዱስትሪ ነባር የፋርማሲዩቲካልስ፤ የህክምና መገልገያ አምራችና የኮስሞቲክስ ኢንዱስትሪዎችን አቅም በማሳደግና አዳዲስ ፋብሪካዎችን በማቋቋም ከውጭ የሚገቡ መሠረታዊ የመድኃኒት ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርቶች ለመተካትና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የኢንዱስትሪውን የማምረት አቅም በ2007 ከነበረበት 80 በመቶ ወደ 90 በመቶ በማሳደግ የኤክስፖርት ገቢን ከ15 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወደ 110 ሚሊዮን ዶላር ከፍ ማድረግ እና የኢንዱስትሪውን የሀገር ውስጥ ገበያ ድርሻ ከ25 በመቶ ወደ 50 በመቶ የማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሥራ ዕድል ፈጠራን ከ3000 ወደ 6900 ከፍ ለማድረግ ታቅዷል፡፡

## 3.8 የካይዘን ፍልስፍና ትግበራ ዋና ዋና ግቦች

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የካይዘንን የአመራር ፍልስፍና ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በማስረጽ፣ በማስፋፋት፣ ጥራትና ምርታማነታቸውን በቀጣይነት በማሻሻልና ለተወዳዳሪነት በማብቃት፡-

(ሀ) የኢንዱስትሪ ትራንስፎርሜሽንን በሚመለከት የመጀመሪያ ደረጃ ካይዘንን ከ75-100 በሚሆኑ የኤክስፖርት ኩባንያዎች ላይ በመተግበር በ2012 ከ20 በመቶ እስከ 30 በመቶ ጥራትና ምርታማነትን የማሻሻል፤ የሁለተኛ ደረጃ ካይዘንን ከ50-75 በሚሆኑ የኤክስፖርት ኩባንያዎች ላይ በመተግበር በ2012 ከ20 በመቶ እስከ 25 በመቶ ጥራትና ምርታማነትን የማሳደግ፤ የመጀመሪያ ደረጃ ካይዘንን ከ50-75 በሚሆኑ ስትራቴጂክ ገቢ ምርት ኩባንያዎች ላይ በመተግበር በ2012 ከ25 በመቶ እስከ 35 በመቶ ጥራትና ምርታማነትን የማሻሻል እና የሁለተኛ ደረጃ ካይዘንን ከ25-35 በሚሆኑ የስትራቴጂክ ገቢ ምርት ኩባንያዎች ላይ በመተግበር በ2012 ከ20 በመቶ እስከ 25 በመቶ ጥራትና ምርታማነትን የማሻሻል ግቦች ተጥለዋል፡፡

(ለ) በኢንዱስትሪው ዘርፍ ብቃት ያለው የሰው ኃይል ማፍራትን በሚመለከት የመጀመሪያ ደረጃ ካይዘንን ከ35-50 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በአማካይ 40 በመቶ ወደ 100 በመቶ የብቃት መመዘኛ ፈተና የማሳለፍ፤ የሁለተኛ ደረጃ ካይዘንን በመተግበር ከ35-50 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት 100 በመቶ የብቃት መመዘኛ ፈተና ማለፍ የማስቻልና የቴክኖሎጂ ሽግግርና የኢኖቬሽን አመራርን የማሳደግ፤ የመጀመሪያ ደረጃ ካይዘንን በመተግበር ከ15-25 ዩኒቨርሲቲዎች የትምህርትና ምርምር ሥራዎችን ጥራትና ምርታማነት የማሻሻል፤ የሁለተኛ ደረጃ ካይዘንን በመተግበር ከ10-15 ዩኒቨርሲቲዎች የትምህርትና ምርምር ሥራዎችን ጥራትና ምርታማነት በማሻሻል በአመራር፤ በኢንጂነሪንግና በሳይንስ በኢንዱስትሪው ተፈላጊ የሆነ ብቃት ያለው ባለሙያ የማፍራትና በፒ.ኤች.ዲ. ዲግሪ ከ5-10 ተመራቂዎችን (ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) እና ከ5-10 ተመራቂዎችን (ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ) በካይዘን ፍልስፍና የማሰልጠን ግቦች ተጥለዋል፡፡

## 3.9 የኢንዱስትሪ ፓርኮች እና ክላስተሮች ልማት ዋና ዋና ግቦች

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን እና ክላስተሮችን በማልማትና ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የውጭና የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት በስፋት በመሳብ፣ ዘመናዊ የሥራ አመራር ልምድ በአገር ውስጥ እንዲጎለብት በማድረግና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ በማስቻል፣ በዋነኛነት የውጭ ንግድን በማስፋፋት፣ ከውጭ የሚገቡ የኢንዱስትሪ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርቶች በመተካት፣ የውጭ ምንዛሬ ገቢያችንን ለማሳደግ እና የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገታችንን ለማፋጠን (1) በሁለተኛው የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ 7 ሚሊዮን ካሬ ሜትር መሬት የማምረቻ ቦታዎችን በማዘጋጀት በማኑፋክቸሪንግና ተዛማጅ ዘርፎች ላይ ለሚሰማሩ ባለሃብቶች ማቅረብ (2) አራት የተቀናጁ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ፓይለት ፕሮጀክቶችን በማልማት በሚሊዮን የሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ምርት ከኢንዱስትሪ ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ በማድረግ በግብርና ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር የአግሮ ኢንዱስትሪ ምርቶች የኤክስፖርትና የሀገር ውስጥ ገበያ ድርሻ እንዲጨምር በማድረግ የገጠር ትራንስፎርሜሽንና የግብርናና ኢንዱስትሪ ትስስር እንዲሳለጥ ማድረግና (3) ክልሎችና ከተሞች ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ ለሚሸጋገሩ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ባለሃብቶች ደረጃቸውን የጠበቁ የኢንዱስትሪ ክላስተሮችና ፓርኮች እንዲያለሙ ድጋፍ በማድረግ ተጨማሪ ባለሃብቶች ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እንዲቀላቀሉ ማድረግ ዋና ዋናዎቹ ግቦች ሲሆኑ ከዚሁ ጋር በማያያዝ ለ700 ሺህ ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዷል፡፡

## 4. የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ዕድገት ከማፋጠንና መሠረቱን ከማስፋት አንፃር ጥራት ያለው ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም የኤክስፖርት ግኝትን ለማሳደግ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለመፍጠርና የኢንዱስትሪዎች ትስስርን ለማጠናከር የተለያዩ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ ከእነዚህ ፕሮግራሞች መካከል ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 4.1 የማስፈጸም አቅም ግንባታ ፕሮግራም

በዚህ ፕሮግራም የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን እና ተጠሪ ተቋማትን የሰው ሃይል በማብቃት እና አስፈላጊ ግብአቶችን በማሟላት የማስፈጸም አቅም እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡ ኢንስቲትዩቶች የምርምር እና ስርጸት አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ በማድረግ የግል ባለሃብቱን ለመደገፍ የሚያስችላቸውን ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን የማፈላለግ፣ እነዚህን መረጃዎች የማደራጀት፣ የማላመድና ወደ ግሉ ዘርፍ ለማስተላለፍ የሚያስችል ቁመና እንዲኖራቸው በአለም አቀፍ ደረጃ ብቃት ካላቸው ተመሳሳይ ተቋሞች ጋር የቁርኝት መረሃግብሮች በመተግበር የማስፈጸም አቅማቸው እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ ከዚህ አንጻር የአመራርና የሙያተኞች አቅም ግንባታ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

አዳዲሶቹ ኢንስቲቱዩቶች የተሟላ መሰረተ ልማት እንዲኖራቸው በማድረግና ነባሮቹን በማጠናከር የማስፈጸም አቅም ግንባታ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በቀጣይ ለሚኖሩ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች ተቋማትን በማደራጀት ለቀጣይ የኢንዱስትሪ ዕድገት መደላድል ይፈጠራል፡፡ ኢንስቲቱዩቶችን ከዩኒቨርስቲዎች እና ከሌሎች የምርምር ተቋማት ጋር በማስተሳሰር ከውጭ አገር የተገኙ ምርጥ ተሞክሮችን ማላማድ እና ተቋማዊ በማድረግ አገራዊ የምርምር እና ስርጸት አቅም እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ በዚህ ረገድ እየተሻሻሉ የመጡትን የጋራ መድረኮች ገምግሞ የተጠናከሩ በማድረግ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል ሥራ የሚሰራ ሲሆን ዘርፉንና ንዑስ ዘርፎችን በብቃት ለመምራት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና የህግ ማዕቀፎችም ይዘጋጃሉ፡፡

### 4.2 የምርታማነት፣ የጥራትና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ፕሮግራም

ልማታዊ ባለሀብትን የማጎልበቻ ብቸኛው መንገድ ኪራይ መሰብሰብ ሳይሆን የማያቋርጥ የምርታማነትና የምርት ጥራት ማሻሻል ሥራ እንደሆነ የእስካሁኑ ተሞክሮዎች ያረጋግጣሉ፡፡ ይህን ለማሳካት እንዲቻል የተቋቋሙት ኢንስቲትዩቶችና በቤንችማርኪን ፕሮግራም አለምአቀፍ ደረጃ ያደረሷቸውን ሞዴል ኩባያዎች በመፍጠር ረገድ የተሰሩትን ሥራዎችና ተሞክሮዎች መሰረት በማድረግ ስኬቱ በዘርፍ ደረጃ እንዲሰፋ ይደረጋል፡፡ የኢንስቲትዩቶቹም የመደገፍ አቅምና የትኩረት አቅጣጫ በቁርኝት ፕሮግራም እንዲጠናከርና እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡ የባለሀብቱንና የሰራተኛውን አስተሳሰብና ባህርይ በመለወጥ ለማያቋርጥ ምርታማነትና የምርት ጥራት እና ዓለምአቀፍ ተወዳዳሪነት እንዲተጋ ለማድረግ የሚያስችለው የካይዘን ፍልስፍና በተወሰኑ ፋብሪካዎች ደረጃ ስኬት ማስመዝገብ ያስቻለ ቢሆንም በስፋት ባለመተግበሩ በዘርፉ የምርታማነትና የምርት ጥራት ዕድገት ላይ ሚዛን የሚደፋ ለውጥ ሳያመጣ ቀርቷል፡፡ በመሆኑም በቀጣዩ የዕቅድ ዘመን በተጠናከረና ስፋት ባለው መልኩ የሚተገበር ይሆናል፡፡

ለዘርፉ ምርታማነት ማነስ አንዱ ምክንያት የነባር ኢንዱስትሪዎች ቴክኖሎጂ ኋላ ቀርና መሻሻል የማያሳይ መሆን ነው፡፡ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ዕድገት በመወሰን ረገድ የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ወሳኝና መሰረታዊ ነው፡፡ በመሆኑም የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪውን ልማትና ዕድገት ማፋጠን ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ያሏቸውን ኋላ ቀር ቴክኖሎጂዎች እንዲያሻሽሉና በአዲስም እንዲተኩ እንዲሁም የተቋማቸውን የሙያ አቅም ለማሳደግ እንዲነሳሱ የሚያበረታቱ የኢንዱስትሪ ፖሊሲዎች ተቀርጸው እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡

ለማኑፋክቸሪንግ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚቀርበው የሰው ኃይል ክብዛት በተጨማሪ ጥራትን መሰረት ያደረገ እንዲሆን የተጀመሩ የኢንዱስትሪና የትምህርት ተቋማት ትስስር እየተካሄዱ ባሉ የአቅርቦት-ፍላጎት ጥናቶች ግኝት መሰረት እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ በአጠቃላይ ምርታማነትን፣ ጥራትንና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታን አስመልክቶ ከ3-4 የሚደርሱ ፕሮጀክቶች ተዘጋጅተው በዕቅድ ዘመኑ የሚተገበሩ ሲሆን ደጋፊ ፖሊሲዎችም ይዘጋጃሉ፡፡

## 1.3 የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ፕሮግራም

ይህ ፕሮግራም ትኩረት የሚያደርገው ለኢንዱስትሪው ልማት ተጨማሪ ጥራት ያለው የግል ኢንቨስትመንትን ለመሳብ በሚያስችሉ ተግባራት ላይ ነው፡፡ ፈጣን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለማምጣት አዳዲስ የውጭ ኢንቨስትመንትን ከመሳብ ባለፈ ያገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ይበረታታል፡፡ ከዚህ አንጻር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተቀርጸው ይተገበራሉ፡፡

**ጥራት ያለው የውጭ ኢንቨስትመንት፡-** የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን እመርታ ለማረጋገጥ በሚቀጥሉት አስርተ ዓመታት ውስጥ ጥራት ያላቸው የውጭ ኢንቨስትመንቶችን በከፍተኛ ሁኔታ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሰረት ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምንጭ የሆኑ አገሮችን በመለየትና በአለም-አቀፍ ደረጃ ታዋቂነት ያላቸው ኩባንያዎች ላይ ትኩረት በማድረግ እንዲመጡ የፕሮሞሽንና የማግባባት ስራ ይሰራል፡፡ በዚህ ረገድ አሰራሮችን በአግባቡ የማደራጀት፣ የመመልመያ አግባብ የመወሰን፣ ባለሀብቶቹ ሲመጡም የማስተናገጃ ሥርዓቶችን የማመቻቸት ሥራዎች የሚሰሩ ሲሆን በዝርዝር ፕሮጀክቶችም የሚተገበሩ ይሆናል፡፡

**የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንት፡-** የኪራይ ሰብሳቢነት አማራጮችን ደረጃ በደረጃ በመዝጋት ሀገራዊ ባለሀብቱ ከኮንስትራክሽን፣ ከንግድና አገልግሎት ዘርፍ የሚመለመልበት፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የሚሸጋገርበት፣ የተማረው ወጣት በሥራ ፈጣሪነትና በኢንተርፕሪነርሺፕ አስተሳሰብ እንዲቀረጽ በማድረግና ሁሉን አቀፍና ቀልጣፋ ድጋፍ በመስጠት በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚደረገው የኢንቨስትመንት መጠንና ውጤታማነት ከፍተኛ እመርታ እንዲያስመዘግብ የሚያስችል ሥርዓት ተመቻችቶ በዚህ ንዑስ ፕሮግራም ይተገበራል፡፡

## 4.4 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ፕሮግራም

የተለያዩ አገሮች ተሞክሮዎች እንደሚያሳየው ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን የሽግግር ሂደት በመምራት ረገድ የመንግስት ሚና ወሳኝነት አለው፡፡ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ባስመዘገቡ የኤሲያ አገሮች ስትራተጂክ እና የገበያ ክፍተት ባለበት ለኢኮኖሚው ትራንስፎርሜሽን ወሳኝ የሆኑ የልማት ድርጅቶች በመንግስት የተያዙ ሲሆን እነዚህ ተቋማት ኢኮኖሚውን እና የግሉን ሴክተር በመምራት እና በማገዝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ እነዚህ አገሮች በግብርና፣ በንግድ፣ በማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ በኃይል አቅርቦት፣ በመሰረተ-ልማት ግንባታ፣ በትራንስፖርት እና በቴሌኮም አገልግሎት ላይ የተሰማሩ የልማት ድርጅቶች አሏቸው፡፡

በተለይ በመጀመሪያው የእድገት ምዕራፋቸው የግሉ ሴክተር ደካማ በመሆኑ፣ ኢኮኖሚውን በፍጥነት ወደ ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር የመንግስት ልማት ድርጅቶችን በማቋቋም ልማቱን እንዲመሩ አድርገዋል፡፡ የገበያውን ክፍተት በመከተል ጠንካራ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን በመገንባት፣ ሥራ ላይ እንዲገቡ በማድረግና በቀጣይም ወደ ግል ይዞታ በማስተላለፍ ጠንካራ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍን መፍጠር እንደሚቻል ታይቷል፡፡ በመሆኑም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ፕሮግራም የግል ባለሃብቱ ሊሳተፍባቸው በሚችልባቸው መስኮች የተሰማሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ደረጃ በደረጃ ወደ ግል ዘርፍ የማስተላለፍ

ስራ ተፋጥኖ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ለተፋጠነ የኢኮኖሚ ዕድገትና ለፍትሀዊ የህብረተሰብ ተጠቃሚነት ቁልፍ ሚና ያላቸው ስትራቴጂክ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በምርትና አገልግሎታቸው እንዲሁም በፋይናንስ አቋማቸው አህጉራዊና አለምአቀፍ ተወዳዳሪነት ደረጃ ላይ የደረሱና ድንበር ተሻጋሪ የሆነ ብቃትን የገነቡ ለማድረግ የሚያስችሉ አሰራሮችና አደረጃጀቶች በዚህ ፕሮግራም ይተገበራሉ፡፡

## 4.5 አዳዲስ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ የልማት ፕሮግራም

የኢኮኖሚውን ዕድገትና ይህን ተከትሎ የሚመጣውን የማህበራዊ ዘርፍ ለውጥና የህብረተሰብ ፍላጎቶች ማስተናገድ የሚያስችሉ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን ማልማትና ለዚህም አስፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎችንና ደጋፊ አሰራሮችን ማመቻቸት ይጠይቃል፡፡ አዳዲስ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎችንና ምርቶችን በማስፋፋትና የኢንዱስትሪ ትስስር በመፍጠር ዕድገቱ ለውጭ የኢኮኖሚ መዋዠቅ እንዳይጋለጥ ይከላከላል፣ የአገር ውስጥ እና የውጭ ንግድ አማራጮችን ያሰፋል፣ የካፒታልና የሠራተኛን ምርታማነትን ያሳድጋል፣ ከአካባቢው አገሮች ወይም የቀጠና ኢኮኖሚያዎች ጋር ትስስርንና ቅንጅትን ያፋጥናል፡፡ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የማስፋፋት ፕሮግራም ተጨማሪ አዳዲስ ዘርፎችን በመምረጥና በነዚህ መስኮች ኢንቨስትመንትን መሳብና ማስፋፊያን ማበረታታት ላይ ያተኩራል፡፡ ከዚህ አኳያ ዓለም-አቀፍ የእሴት ሰንሰለትን፣ የአገሪቱን እምቅ ሃብት፣ የገበያ ፍላጐትን እና የሥራ ዕድል መፍጠርን ግምት ውስጥ በማስገባት ዘርፉን ለማስፋፋት አቅም ያላቸው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ መስኮች ተመርጠዋል፡፡ ዘርፉን ወደ የባዮቴክኖሎጂ፣ ፔትሮ-ኬሚካል፣ ኤሌክትሪካልና ኤሌክትሮኒክስና ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ሶፍትዌር እና ሃርድዌር ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች) ኢንዱስትሪዎች በአዲስ መልክ እንዲቋቋሙ ተለይተዋል፡፡ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ንዑስ ዘርፍ አዲስ የልማት ፕሮግራም ተፈፃሚ ለማድረግ የባዮቴክኖሎጂ፣ የፔትሮ-ኬሚካል፣ የኤሌክትሪካልና ኤሌክትሮኒክስ እና የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪ ልማት ንዑስ ፕሮግራሞች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ የብረታብረት ኢንጂኔሪንግ ኢንዱስትሪው የደረሰበትን የልማት ደረጃ በማጤን በየጊዜው የታሪፍ ፖሊሲ ክለሳ ይደረጋል፡፡

## 4.6 የኢንዱስትሪ ፓርኮች እና ክላስተሮች ልማት ፕሮግራም

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ፕሮግራም በመሬት አጠቃቀም ላይ የሚታዩውን ኪራይ ሰብሳቢነት ለማስቀረት፣ የሎጅስቲክስና የጉምሩክ አገልግሎት ችግሮችን ለማስወገድ፣ መሰረተ-ልማቶችን በማሟላት ኢንቨስትመንቶች ያለብዙ ውጣ ውረድ እንዲስፋፉና በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ምርት እንዲሸጋገሩ ለማድረግ፣ በመካከለኛና ትላልቆቹ እና በአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች መካከል ትስስር ለማመቻቸትና ክላስተር ለመፍጠርና በዚህም የቴክኖሎጂ፣ የአመራረትና የአመራር ዘዴን ለማስተላለፍ፣ የሥራ ዕድልን ለማሳደግ፣ የአገር ውስጥ ሀብትን በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመጠቀምና አረንጓዴ የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን ለማጠናከር ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሳሪያ ነው፡፡

በዚህ ፕሮግራም ለኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት በተለዩትና ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው ስትራቴጂክ ቦታዎች በመንግስት፣ በግል ወይም በቅንጅት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማልማት ኢንቨስትመንትን በስፋት የመሳብ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ሲሆን የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮችንም በማልማት የግብርናና የኢንዱስትሪ ትስስር የማጠናከር ስራ ይሰራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ክልሎች እና ከተሞች ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ ለሚሸጋገሩ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ባለሃብቶች አለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁና ከሌሎች ኢንዱስትሪዎች ጋር የተጠናከረ ትስስር የሚኖራቸው የኢንዱስትሪ ክላስተሮችና ፓርኮች እንዲለሙ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

## 4.7 የጥቃቅንና አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ፕሮግራም

የኢኮኖሚ ዕድገታችንን በማፋጠን በከተማና በገጠር ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠርና ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል ማረጋገጥ የሕዝባችንን ገቢ ለማሻሻልና ድህነትን ለመቀነስ ያስችላል፡፡ ከዚህ አንፃር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪና ቀጣይነት ያለው ፈጣን ልማት የሚያስመዘግቡ፣ የገጠር ልማትን ለማስቀጠልና ለኢንዱስትሪው ልማት አስተማማኝ መሠረት የሚጥሉ እንዲሆኑ ለማስቻል በተለይ በከተሞች ሰፊ መሠረት ያለው ልማታዊ ባለሀብት በመፍጠር የኢንተርፕራይዞች ልማት ይስፋፋል፡፡ ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ልማት እንደ ዕድገት ደረጃቸው አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠትና በማጠናከር እስከ 2 በመቶ የሚደርሱት ወደ ቀጣይ ኢንዱስትሪ ሽግግር እንዲያድጉ ይደረጋል፡፡ ይህንንም ተፈፃሚ ለማድረግ ሀገራዊ ምርትን በማሳደግ፣ በሥራ ፈጠራ ክህሎት፣ በመንግስት ድጋፍና ፋሲሊቴሽን እና በኤክስቴንሽን አገልግሎት እና ዘመናዊ የመረጃ አደረጃጀት ሥርዓት በማጠናከር ዙሪያ የተቀናጁና የተደራጁ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

(ሀ) የኢንተርፕራይዞች ልማትና ጠቅላላ ሀገራዊ ምርት ማሳደግን በሚመለከት የእድገት ደረጃቸውን ታሳቢ ያደረገ ችግር ፈቺ ድጋፎችን በተቀናጀ መልኩ በመስጠት እስከ 2 በመቶ የሚደርሱ ኢንተርፕራይዞች (62,500 ኢንተርፕራይዞች) ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ እንዲሁም 10,000 ኢንተርፕራይዞች ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡

(ለ) የሥራ ፈጠራ ክህሎትን በሚመለከት በአምስት ክልሎች የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን በማጠናከር በ35 ዩኒቨርስቲዎች የኢንተርፕርነርሺፕ ልህቀት ማዕከላትን በማቋቋምና በማጠናከር ዕጩ ተመራቂዎች የሥራ ባህልና ክህሎት እንዲያዳብሩ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም ወደ ኢንዱስትሪው የሚገቡ 100 ሺህ አንቀሳቃሾች የሥራ ፈጠራ ክህሎት (ኢንተርፕረነርሺፕ) ሥልጠና እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡

(ሐ) የመንግስት ድጋፍ እና ፋሲሊቴሽንን በሚመለከት በሁሉም ክልሎችና ከተሞች 2,247 የሚሆኑ ነባርና አዲስ ደረጃቸውን የጠበቁና ሁሉን አቀፍ አገልግሎቶች ማቅረብ የሚችሉ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ማዕከላትን በማቋቋምና በማጠናከር የኢንተርፕራይዞችን ምርታማነት በማሳደግ በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ያለው ዕድገት እንዲፋጠን ይደረጋል፡፡ የጥቃቅንና፣ አነስተኛ ኢንዱስትሪ ዕድገትን በማፋጠን የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ ለማሳደግ የተጣለውን ግብ ለማሳካት ይሠራል፡፡ በዚሁ መሰረት በኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው ወደ ስራ ለሚገቡ አንቀሳቃሾች 9,000 ሄክታር የለማ መሬት በማዘጋጀት፣ 15 ሺህ ሼዶች እና 600 ሕንፃዎች በመገንባት ወደ ሥራ እንዲገቡ ይደረጋል:: የቅድመ ብድር ቁጠባን በተመለከተም አስቀድመው እንዲቆጥቡ በማድረግ ብር 21 ቢሊዮን (ከዚህ ውስጥ ብር 17 ቢሊዮን ወይም 80 በመቶ ህዝቡን የተለያየ ስልት ነድፎ ሞብላይዝ በማድረግ ከቁጠባ ከሚገኝ) የብድር አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ከተሰጠው ብድር ውስጥም በዕቅድ ዘመኑ ብር 19 ቢሊዮን (94 በመቶ) እንዲመለስ ይደረጋል::

ኢንተርፕራይዞች ምርትና ምርታነታቸውን የሚያሳድግና ጥራት ያለው ምርት ማምረት እንዲችሉ 50,000 ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም ኢንተርፕራይዞችን በክላስተር በማሰባሰብና የማምረቻ ቦታ በማመቻቸት በብረታ ብረትና እንጨት 202፣ በጨርቃ ጨርቅና ቆዳ ውጤቶች 202 እና በአግሮ ፕሮሰሲንግ 202 በድምሩ 606 ህንጻዎች በክላስተር ተገንብተው በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፉ ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው ወደ ሥራ ለገቡና ለሚገቡ አዳዲስ መካከለኛ 10,000 ኢንተርፕራይዞች በኢንዱስትሪ ዞን ውስጥ የማምረቻ ቦታ በማመቻቸት በተመጣጣኝ ዋጋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ የእሴት ሰንሰለት ጥናት የተጠናላቸው እና ወደ ውጭ የሚላኩ 16 ምርቶችን በመለየት ከጥሬ ዕቃዎች ጀምሮ እስከ ገበያ ባሉት የምርት ሂደቶች ተሳታፊ የሆኑ ተዋናዮች የማስፈጸም አቅማቸው ይገነባል፡፡ የሚያጋጥሟቸውን ማነቆዎች በመፍታት ተጠቃሚ እንዲሆኑ

በማድረግና የሀገር ውስጥ ገበያ እድሎችን አሟጦ በመጠቀም የብር 50.2 ቢሊዮን እንዲሁም ከሀገር ውጭ 1.0 ቢሊዮን ዶላር የገበያ ትስስር በመፍጠር የኢንተርፕራይዞች የገበያ ተወዳዳሪነት እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

(መ) የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥን በሚመለከት ለ2,280 አሰልጣኞች የመሠረታዊ የሥራ ፈጠራ አስተሳሰብና ክህሎት ሥልጠና እና በንግድ ልማት አገልግሎት (BDS) የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል፡፡ የሙያ ብቃት ደረጃቸውም በምዘና ይረጋገጣል፡፡ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ዝግጁ የሆኑና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚካሄድባቸው 4,341 ፕሮቶታይፖችን ዝግጁ በማድረግ በየክልሉ ትኩረት በተሠጣቸው የሥራ መስኮች 2,448 የተሻሻሉ የመሣሪያ ዓይነቶች ተመርተው ይሰራጫሉ:: ለ750 ሺህ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የካይዘን አተገባበር ቴክኒክ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በመስጠት እንዲተገብሩት ይደረጋል፡፡

(ሠ) ዘመናዊ የመረጃ አደረጃጀት ሥርዓት ማጠናከርን በተመለከተ አስተማማኝ፣ ደረጃውን የጠበቀ እና ደህንነቱ የተረጋገጠ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ከፌዴራል እስከ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ተቋማት ድረስ ይዘረጋል፡፡ የሥራ አጥ እና ተያያዥ መረጃዎች በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ ተጣርተው እንዲያዙ ይደረጋል፡፡

### 3.1.3 የማዕድን ልማት

### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

በማዕድን ዘርፍ የመጀመሪያው አምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ የነበረው የውጭ ምንዛሬን ማስገኘትና ለሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆኑ ማዕድናት እንዲመረቱ በማድረግ ለዚህ ተብሎ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ማዳን ነበር፡፡ ይኸው የትኩረት አቅጣጫ በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመንም በመሠረታዊነት የሚያገለግል ይሆናል፡፡ የዘርፉን አስፈጻሚ አካላት የማስፈጸም አቅም መገንባት፣ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፕሮሞሽን ሥራ መስራትና ጥራት ያለውን መረጃ በማቅረብ አቅም ያላቸውን ባለሀብቶችን መሳብ፣ ኢንዱስትሪዎች ለሚፈልጉት የማዕድን ምርት ቅድሚያ በመስጠት እንዲለሙ ማድረግ፣ ከኢንዱስትሪው ልማት ቀድመው እንዲገኙ ማድረግ፣ የውጭ ገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት እና በማዕድናት ላይ ዕሴት በመጨመር የውጭ ምንዛሬ አቅምን ማሳደግ፣ ዘላቂ የማዕድን ልማት መሰረት በማድረግ የአካባቢ ጥበቃና የማሕበረሰብ ልማትን ማረጋገጥና ለዜጎች ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የትኩረት አቅጣጫ ይሆናሉ፡፡

### 2. ዓላማዎች

የማዕድን ዘርፍ የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋና ዋና ዓላማዎች (1) የፖሊሲ፣ የህግ ማዕቀፎችን፣ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በማሻሻል፣ ዓለም አቀፍ ልምዶችና ተሞክሮዎችን በመቀመርና በሥራ ላይ በማዋል የዘርፉን የማስፈፀም አቅም ወደ ላቀ ደረጃ ማሳደግ፤ (2) በማዕድን ላይ እሴት በመጨመር ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬና የሀገር ውስጥ የመንግስት ገቢን ትርጉም ባለው ሁኔታ ማሳደግ፤ (3) የማዕድን ግብዓት ለሚያስፈልጋቸው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች አስፈላጊውን ግብዓት በማቅረብ የውጭ ምንዛሬን በማዳንና በማስገኘት የኢንዱስትሪውን መዋቅራዊ ሽግግር ማፋጠን፤ (4) የማዕድን ኢንዱስትሪው አስተዳደርና አካባቢ ጥበቃው ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን በማድረግ ለዜጎች ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር፤ (5) የልማት ሥነ ምድር ካርታ ሽፋን፣ ጥራትና ተደራሽነትን በማሳደግ፣ አቅምና ልምድ ያላቸውን ልማትዊ ባለሀብቶች በመምረጥና በመሳብ የማዕድን ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት ናቸው፡፡

## 3. ዋና ዋና ግቦች

ለኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆኑ ማዕድናት ምርት መጠንን ለማሳደግ እና ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ እና የሀገር ውስጥ ገቢ ሊያሳድጉ የሚችሉ ዋና ዋና ግቦች ተጥለዋል፡፡

በዘመናዊ እና በባህላዊ መንገድ ተመርቶ ለገበያ የሚቀርበውን የወርቅ መጠን አሁን ካለበት 14421 ኪ.ግ በአማካይ 19 በመቶ በየዓመቱ በማሳደግ በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 33124.6 ኪ.ግ ለማድረስ፣ ከማዕድን ዘርፍ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ በየዓመቱ በአማካይ 45 በመቶ በማሳደግ አሁን ካለበት 515 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 3.2 ቢሊዮን ለማድረስ፣ ከማዕድን ዘርፍ የሚገኘውን የሀገር ውስጥ የመንግስት ዓመታዊ ገቢ አሁን ካለበት 385 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በየዓመቱ በአማካይ 13 በመቶ በማሳደግ በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 710 ሚሊዮን ለማድረስ ግቦች ተጥለዋል፡፡ የልማት የሥነ-ምድር ካርታ ሽፋን ፣ ጥራትና ተደራሽነትን በ1:250,000 መስፈርት አሁን ካለበት በአማካይ 55.5 በመቶ በ2012 ወደ 100 በመቶ ማሳደግ እና የማዕድን ፍለጋን አሁን ካለበት በአማካይ 785 ካሬ ኪሎ ሜትር በየዓመቱ በአማካይ 11 በመቶ በማሳደግ በ2012 ወደ 1,291 ካሬ ኪሎ ሜትር በማሳደግ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው ማዕድናት የአለኝታ ጥናትን ማጠናቀቅ እና በኩባንያዎችና በባህላዊ ማዕድን ሥራ የተፈጠረውን የሥራ ዕድል አሁን ካለበት 440 ሺ በእጥፍ በማሳደግ በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 880 ሺህ ማድረስ ለዕቅድ ዘመኑ የተቀመጡ ግቦች ናቸው፡፡

### 3.1 የማስፈፀም አቅም ግንባታ ፕሮግራም

የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ የዘርፉን የሰው ኃይል በማብቃት እና ተቋሙን በመገንባት፣ አስፈላጊ ግብአቶችን በሟሟላት እንዲሁም ህጎችን፣ አሰራሮችን እና አደረጃጀቶችን በማሻሻል የዘርፉን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች በውጤት ለማስፈፀም የሚያስችል የማስፈፀም እና የመፈፀም አቅም እንዲጎለብት ማድረግ ነው፡፡

የሰው ሀብት ልማት ንዑስ ፕሮግራምን በተመለከተ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመቀናጀት 304 ጂኦሎጂስቶች፣ ጂኦፊሲስቶች እና ጂኦኬሚስቶችን፣ 35 የማዕድን መሀንዲሶች፣ 32 የፔትሮሊየም መሀንዲሶች፣ 29 ማይኒንግ ኢኮኖሚስቶች፣ 23 የፔትሮሊየም ኢኮኖሚስቶች እና 20 ጂኦሞሎጂስቶች ማሰልጠን ሲሆን በልማት ዕቅዱ ዘመን በአጠቃላይ 519 ባለሙያዎችን በመቅጠርና በማሰልጠን ወደ ሥራ የማስገባት ግቦች ተቀምጠዋል፡፡

የተቋም ግንባታ ንዑስ ፕሮግራምን በተመለከተ የጂኦሳይንስ ላብራቶሪ (Automatic Absorption, Oilshow Analyzer, Elemental Analayzer, XRF Machine, ICPMS) የመሳሰሉት እና የኮር መቆፈሪያ ሪጎች በአዳዲስ መሳሪያዎች መተካት፣ የጂኦሳይንስ ላብራቶሪ ዓመታዊ አማካይ የናሙና ምርመራን አሁን ካለበት 45,354 ወደ 69,366 እና የድሪሊንግ አገልግሎት መስጠት በዓመት አሁን ካለበት 8,000 ሜትር ወደ 20,000 ሜትር ከፍ ማድረግ፣ አንድ የጂሞሎጂ ኢንስቲትዩት ማቋቋም እና የፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር ሥራዎች ሙሉ በሙሉ በድህረ ገፅና በካዳስተር የተደገፈ እንዲሆን ማድረግ የታቀዱ ዋና ዋና ግቦች ናቸው፡
:

### 3.2 የሥነ-ምድር ካርታ ሽፋን እና ጥራት ማሳደግና የማዕድን ፍለጋ ፕሮግራም

የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ መሠረታዊ የጂኦሣይናስ፣ የጂኦኬሚስትሪ፣ የጂኦፊዚክስ እና የሥነ-ምድር አደጋዎች ጥናት በማካሄድ የሀገሪቱን የልማት ሥነ-ምድር መረጃ ሽፋን፣ ጥራት እና ተደራሽነትን በማሳደግ የግብርናን ምርት የሚያሳድጉ እና ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውሉ ማዕድናት ፍለጋ ማካሄድ፣ ለመሠረተ

ልማት የሚያገለግሉ መረጃዎችን መሰብሰብ እና የውጭ ምንዛሪ ለማፍራትና ለማዳን የሚያስችሉ ማዕድናት ፍለጋና ጥናት ማካሄድ ነው፡፡

ለማዕድናት ፍለጋና ጥናት ወሳኝ የሆነው የኤርቦርን ጂኦፊዚክስ ጥናት አሁን ካለበት 30 በመቶ በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 100 በመቶ ሽፋን ማድረስ፤ በ1፡250,000 መስፈርት የሀገሪቱን የጂኦሎጂ ካርታ ሽፋን አሁን ካለበት 82 በመቶ በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 100 በመቶ ሽፋን ማድረስ እና በዚሁ መስፈርት የጂኦሃዛርድ ጥናት ሽፋን አሁን ካለበት 29 በመቶ በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 100 በመቶ እንዲሸፍን ማድረግ፤ የማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግምት ጥናት በ 1፡2000 -1፡20,000 መስፈርት አሁን ካለበት 784.8 ካሬ ኪሎ ሜትር ወደ 1,291 ካሬ ኪሎ ሜትር ከፍ ማድረግ፤ የብረት ማዕድን ፍለጋና ጥናት አሁን ካለበት 3.5 ካሬ ኪሎ በ2012 ወደ 15 ካሬ ኪሎ ሜትር ከፍ ማድረግ፤ የደለል ወርቅ ፍለጋና ክምችት ግምት አሁን ካለበት 7.3 ካሬ ኪሎ ሜትር በልማት ዕቅዱ መጨረሻ ወደ 10 ካሬ ኪሎ ሜትር ከፍ ማድረግ፤ የሴራሚክስ ማዕድናትና የላይምስቶን ዕብነበረድ ማዕድን ፍለጋና ጥናት አሁን ካለበት 370 ካሬ ኪሎ ሜትር በልማት ዕቅዱ መጨረሻ ወደ 470 ካሬ ኪሎ ሜትር ከፍ ማድረግ እና የጀምስቶን ማዕድን ፍለጋና ጥናት አሁን ካለበት 34 ካሬ ኪሎ ሜትር በልማት ዕቅዱ መጨረሻ ወደ 289 ካሬ ኪሎ ሜትር ከፍ ማድረግ የቀጣዩ አምስት ዓመት ዋና ዋና ግቦች ናቸው፡፡

## 3.3 ኢንቨስትመንትን የማስፋፋት ፕሮግራም

የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የፕሮሞሽን ሥራ በመሥራት አቅም እና ልምድ ያላቸውን ባለሀብቶች ወደ ዘርፉ በመሳብ በልማት ዕቅዱ መጨረሻ የሀገሪቱ ዋና ዋና ማዕድናት ለምተው ለኢኮኖሚው ግንባታ እንዲውሉ ማድረግ ነው፡፡

በብረት፣ በድንጋይ ከሰል፣ በፖታሽ፣ በወርቅ፣ በሴራሚክስ ማዕድናት፣ በተፈጥሮ ነዳጅና ጋዝ፣ በሲልካ ሳንድና በመሳሰሉት ማዕድናት ላይ ለ20 ትላልቅ የዓለማችን የማዕድን ኩባንያዎችን ጨምሮ 121 የማዕድን ምርመራና ምርት ፍቃዶችን መስጠት፤ ለዓለማችን ትላልቅ የማዕድን ኩባንያዎች 10 የነዳጅ ፍለጋና ምርት ክፍፍል ስምምነቶች ፈቃዶችን በመስጠት የ 3D እና 2D የነዳጅ ፍለጋ የሳይስሚክ ጥናቶች እንዲካሄዱ ማድረግ፤ እንዲሁም ጥልቅ የነዳጅ ፍለጋ ጉድጓድ ቁፋሮ አሁን ካለበት 6 ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ተጨማሪ 25 ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ በማካሄድ የሀገራችን የፔትሮሊየም አለኝታ እንዲታወቅ ማድረግ ይገኙበታል፡፡

## 3.4 የማዕድን ምርት እና የውጭ ምንዛሬ ማሳደግ ፕሮግራም

**ከወርቅ ምርት አንፃር** በኩባንያዎች የሚመረተውን የወርቅ ምርት መጠን አሁን ካለበት 5,421 ኪሎ ግራም በየዓመቱ በአማካይ 25 በመቶ በማሳደግ በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 16,543.6 ኪሎ ግራም እና በባህላዊ ማዕድን አምራቾች የሚመረተውን የወርቅ ምርት መጠን አሁን ካለበት 9,000 ኪሎ ግራም በየዓመቱ በአማካይ 13 በመቶ በማሳደግ በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 16,581 ኪሎ ግራም ለገበያ ማቅረብ ሲሆን በአጠቃላይ የወርቅ ምርትን አሁን ካለበት 14,421 ኪሎ ግራም በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 33,124.6 ኪሎ ግራም ማድረስ ናቸው፡፡

**ከጌጣጌጥ ማዕድናት ምርት አንፃር** አሁን ያለውን 150 ኪ.ግ ዕሴት የተጨመረበት የኦፓል ማዕድን ምርት መጠን 20 በመቶ እሴት በመጨመር በ2012 ሙሉ በሙሉ 900 ኪ.ግ (100 በመቶ) እሴት በመጨመር ለገበያ ማቅረብ፣ ከኦፓል ውጭ ያሉ ጥሬ የጌጣጌጥ ማዕድናት አሁን ያለውን 10,000 ኪ.ግ በእጥፍ በማሳደግ በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 20,000 ኪ.ግ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ይገኙበታል፡፡

**ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማዕድናት ምርት አንፃር** ከ2010 ጀምሮ ፖታሽ ወደ ምርት እንዲገባ ማድረግ፣ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ከሚፈልጉት ግብዓት በየዓመቱ በአማካይ 20 በመቶ ማቅረብ እና በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 0.38 (60 በመቶ) ሜትሪክ ቶን ፖታሽ ማዕድን ለሚጠቀሙ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት ማዋል፤ በ2007 በጀት ዓመት ለውጭ ገበያ ቀርቦ የነበረውን 42,126 ሜትሪክ ኩብ ዕብነበረድ በየዓመቱ 12 በመቶ በማሳደግ በ2012 መጨረሻ ላይ 74,240 ሜትሪክ ኩብ ማድረስ እና በ66,645,000 ቶን የድንጋይ ከሰል እና 14,752,000 ቶን የሴራሚክስ ማዕድን ዝርዝር ጥናት በማካሄድ ለልማት ዝግጁ ይደረጋል፡፡

**ከተፈጥሮ ጋዝ ምርት አንፃር** የካሉብና ሂላላ የተፈጥሮ ጋዝ ክምችቶችን ከ2010 በጀት ዓመት ጀምሮ ወደ ምርት በማስገባት በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 7.7 ቢ.ኪ.ሜ የተፈጥሮ ጋዝ ለገበያ ማቅረብ ነው፡፡

**ከውጭ ምንዛሬ ግኝት አንፃር** በኩባንያዎች አሁን የተገኘውን 130 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ በልማት ዕቅዱ መጨረሻ ወደ 778 ሚሊዮን ዶላር ከፍ ማድረግ እና በባህላዊ ማዕድን አምራቾች አሁን የተገኘውን 385 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ በልማት ዕቅዱ መጨረሻ ወደ 896 ሚሊዮን ዶላር ከፍ ማድረግ፤ በልማት ዕቅዱ መጨረሻ ከፖታሽ 1 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማግኘት፣ ከተፈጥሮ ጋዝ ሽያጭ ከ2010 በጀት ዓመት ጀምሮ በየዓመቱ በአማካይ 294 ሚሊዮን ዶላር ማግኘትና በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 526 ሚሊዮን ዶላር ማድረስ እና በአጠቃላይ ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ በየዓአመቱ በአማካይ በ45 በመቶ በማሳደግ አሁን ካለበት 515 ሚሊዮን ዶላር በልማት ዕቅዱ መጨረሻ 3.2 ቢሊዮን ዶላር ማድረስ ይገኙበታል፡፡

### 3.5 የማዕድን ዘርፍ የአካባቢ ጥበቃና የማህበረሰብ ልማት ፕሮግራም

የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ በዘርፉ የልማት ሥራዎች ምክንያት በአካባቢና በማህበረሰብ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች እንዲቀንሱ በማድረግ እና የሙያ ጤንነትና ደህንነት አፈፃጸምን በመከታተል በልማቱ አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ አካላት ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ በማዕድን ማውጣት ምክንያት ጉዳት የደረሰበትና በቀጣይ ጉዳት ሊደርስበት የሚችልን 1,485 ሄክታር መሬት ወደ ነበረበት በመመለስ እንዲያገግም ማድረግ እና ኩባንያዎች በሚያለሙበት አካባቢ ለሚገኙ ማህበረሰቦች አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ለመገንባት የሚያስችል በልማት ዕቅዱ ዘመን 59.2 ሚሊዮን ብር በጀት እንዲመድቡ ማድረግ ናቸው፡፡

## 4. የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

### 4.1 የማስፈፀም አቅም ግንባታ ፕሮግራም

ከሰው ሀብት ልማት ንዑስ ፕሮግራም አኳያ በሀገር ውስጥ የሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ከማዕድን ኢንዱስትሪው ልማት ጋር የተቃኙ እንዲሆኑ በማድረግ እና ዘርፉ የሚጠይቀውን አዳዲስ የትምህርት መስኮች እንዲከፈቱ ቅንጅታዊ አሰራርን በመዘርጋት የዘርፉ የሰው ኃይል ችግር እንዲፈታ ይደርጋል፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ልምድና አቅም ካላቸው ሀገሮች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አማካሪዎችንና ምሁራንን በመቅጠርና ከታውቁ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር በመስራት የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር አጫጭር ሥልጠናዎችን በመስጠት ሰራተኛው ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር እንዲተዋወቅ ይደረጋል፡፡ ባለሙያዎችን በዘርፉ ለማቆየትና የባለሙያ ፍልሰትን ለመቀነስ የሚያስችል የማበረታቻ ሥርዐት ይዘረጋል፡፡ የአስር ዓመት የሰው ኃይል ፍላጎት ጥናት በማካሄድ ዘርፉ የሚፈልገውን የሰው ኃይል በዓይነትና በመጠን በመለየት በዘርፉ ያለውን የሰው ኃይል ችግር ለዘለቄታው ለመፍታት የሚያስችል ሥራ

ይሠራል። ኩባንያዎችና ክልሎች ያለባቸውን የአመለካከት፣ የዕውቀትና የሰለጠነ የሰው ኃይል ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል የአቅም ግንባታ ሥራ ይሠራል።

ከተቋም ግንባታ ንዑስ ፕሮግራም አኳያ የዘርፉን የወደፊት የዕድገት አቅጣጫ የሚያመለክት የማዕድን ፖሊሲ ጥናት እንዲጠናቀቅ እና በሥራ ላይ እንዲውል የሚደረግ ሲሆን ለዚህም በዘርፉ አቅምና ልምድ ያላቸው ዓለም አቀፍ አማካሪዎችን እና ምሁራንን በመቅጠር ጥናቱ እንዲካሄድ ይደረጋል። በማዕድን ዘርፍ ችግር መፍታት ላይ ያተኮሩ የምርምር ተቋማትን በማቋቋም ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ምርምርና ጥናት በማካሄድ ተወዳዳሪ እንዲሆን የሚያስችሉ ሥራዎች ይሠራሉ። በማዕድን ዘርፍ አመራር ውጤታማ ከሆኑ የዓለማችን ሀገሮች ልምድ በመቀመርና ጥናት በማካሄድ ለዘርፉ የቴክኖሎጂ ሽግግር መሠረት ለመጣል የሚያስችሉ ሥራዎች ይሰራሉ። ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የጂኦሳይንስ ላብራቶሪ ማዕከላት እንዲስፋፉ ተገቢውን የማበረታቻ ሥርዐት በመዘርጋት እና በመደገፍ ባለሀብቶች በዚህ ዘርፍ እንዲሠማሩ እና ደረጃቸውን የጠበቁ የናሙና ምርመራዎች በሀገር ውስጥ እንዲካሄዱ በማድረግ ኢንቨስትመንቱ እንዲስፋፋ ይደረጋል።

### 4.2 የሥነ-ምድር ካርታ ሽፋን እና ጥራት ማሳደግና የማዕድን ፍለጋ ፕሮግራም

ከሌሎች ሀገሮች ልምድና ተሞክሮ በመቀመር እና የውጭ አቅምን ጭምር በመጠቀም ለማዕድናት ፍለጋና ጥናት ወሳኝ የሆነው የኤርቦርን ጂኦፊዚክስ ጥናት ይካሄዳል። ለማዕድናት መገኛ አመቺነት ያላቸውን አካባቢዎችን በመምረጥ እና ቅድሚያ በመስጠት የተቀናጀ የጂኦሎጂ፣ የጂኦኬሚስትሪና የጂኦፊዚክስ እንዲሁም የሙከራ ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራዎች በማካሄድ የክምችት ግምት መረጃዎች እንዲሰባሰቡ እና እንዲዘጋጅ ይደረጋል። የማኑፋክቼሪንግ ኢንዱስትሪው እና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እንዲሁም የዓለም ገበያው ለሚፈልጋቸው ማዕድናት ቅድሚያ በመስጠት ጥልቀት እና ስፋት ያላቸው ጥናቶች ይካሄዳሉ። ወደ ተቋሙ የሥነ-ምድር መረጃ ቋት ያልተሰባሰቡ የጂኦሳይንስ መረጃዎችን በተጠናከረ ሁኔታ ለማሰባሰብ እንዲቻል በክልሎች የሚገኙ የሥነ-ምድር መረጃዎች በተፋጠነ ሁኔታ ወደ ተቋሙ የሥነ-ምድር መረጃ ቋት ይገባሉ። የመረጃ ሽፋንና ጥራትን ለማሳደግ የሚያስችሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እና አሰራሮችን ልምድ ካላችው ሀገሮች በመቅሰም፣ በዘርፉ የታወቁ አማካሪዎችን እና ምሁራንን በመቅጠር ጭምር የልማት መረጃ ሽፋንና ጥራት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያድግ ይደረጋል።

### 4.3 ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት ፕሮግራም

ስለሀገሪቱ የማዕድን እና ፔትሮሊየም ሀብት አለኝታ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት ደረጃውን የጠበቀ የማስተዋወቅ ሥራ ይሠራል። አቅምና ልምድ ያላቸውን የውጭ ኢንቨስተሮች የመምረጥ፣ የማግባባትና ወደ ልማት የማስገባት ሥራ ይሠራል። በማዕድን ኢንዱስትሪው አስተዳደር የሚስተዋሉ የህግ ክፍተቶችን ሙሉ በሙሉ በመፍታት እና ግልፅነትና ተጠያቂነትን በማስፈን ለማዕድን ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል። በዘርፉ ልምድ ካላቸው ሀገሮች እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አማካሪዎችንና ምሁራንን በመቅጠር ጭምር ለዘርፉ ዕድገት የረዥም ጊዜ ማስተር ፕላን በማዘጋጀት የማዕድን ሀብት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የሚለማበት አቅጣጫ እንዲቀምጥ ይደረጋል። ትላልቅ የዓለማችን የማዕድን ኩባንያዎች ወደ ሀገራችን ገብተው በማዕድን ልማት እንዲሰማሩ በማድረግ በተለይም በወርቅ፣ በታንታለም፣ በፖታሽ፣ በድንጋይ ከሰል፣ በፔትሮኬሚካል፣ በተፈጥሮ ጋዝ፣ በብረት በፎስፌት፣ በዕምነበረድ እና በሌሎች ለኢንዱስትሪ ግብዐት ቅድሚያ በሚሰጣቸው ማዕድናት ልማት ላይ እንዲሰማሩ የሚያስችል አሠራር ተግባራዊ ይደረጋል። ከፍተኛ የማዕድን አለኝታ ያለባቸውን አካባቢዎች በመለየት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለልማቱ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶች እንዲዘረጉና እንዲሟሉ ይደረጋል። በውላቸው መሰረት ለሚሰሩ ልማታዊ ባለሀብቶች እና ስትራቴጂካዊ የሆኑ ማዕድናትን በማምረት ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውና ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እንዲሁም ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ባለሀብቶች የማበረታቻ ፓኬጅ

በማዘጋጀት በሥራ ላይ ይውላል፡፡ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሳይስሚክ ጥናት በማካሄድ እና ጥልቅ የነዳጅ ፍለጋ ጉድጓድ ቁፋሮ እንዲካሄድ በማድረግ የነዳጅ ፍለጋው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡ ከዚህ በፊት ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት ያልሆኑ የዘርፉ ሥራዎች እየተጠኑ ክፍት የሚደረጉበት ሁኔታ እንዲፈጠር በማድረግና የዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲመጣ በማድረግ የሀገር ውስጥ ባለሀብት አቅሙን ይገነባል፡፡

### 4.4 የማዕድን ምርት እና የውጭ ምንዛሬ ማሳደግ ፕሮግራም

ልማታዊ ባለሀብቶችን በማበረታታት እና በመደገፍ፣ የማዕድን ህጎችን በማሻሻል፣ የዓለም አቀፉን የማዕድን አሰራር በመቀመር እና በማስፋፋት በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውና በገበያ ላይ ተፈላጊነት ያላቸው የተለያዩ ማዕድናት እንዲመረቱ ያደርጋል፡፡ የምርመራና የምርት ፈቃድ የወሰዱ ኩባንያዎች ወደ ምርት እንዲገቡና ከዚህ በፊት ያልተመረቱ አዳዲስ ማዕድናትን ጨምሮ በኩባንያዎቹ የሚመረቱ ማዕድናት በመጠንና በዓይነት እንዲጨምር ይደረጋል፡፡ ለባህላዊ ማዕድን አምራቾች ምርትን የሚያሳድጉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ከቀረጥና ከታክስ ነፃ እንዲገቡ በማድረግና በሰፊው በሥራ ላይ በማዋልና በማላመድ እንዲሁም የአመራረት ዘዴ ሥልጠናዎችን በመስጠት የማዕድን ምርት በመጠንም በአይነትም እንዲጨምር ይደረጋል፡፡ በባህላዊና አነስተኛ ደረጃ ማዕድን ሥራ ላይ የተሠማሩትን ወደ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ እንዲሸጋገሩ በመደገፍ ምርትና ምርታምነት እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር፣ የክልሎችን የማስፈፀም አቅም በመገንባት በባህላዊ መንገድ የሚመረቱ ማዕድናት መጠንና ዓይነት እንዲጨምር ይደረጋል፡፡ በማዕድን ዘርፍ ዘመናዊ የሥራ አመራር ልምድ በሀገር ውስጥ እንዲጎለብትና በሙያና ዕውቀት የተካነ በርካታ የሰው ኃይል በማፍራት ለዜጎች በርካታ የሥራ ዕድል በመፍጠር ዘርፉ የራሱን ጉልህ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ይደረጋል፡፡

የሌሎች ሀገሮችን ልምድና ተሞክሮ ቀምሮ ተግባራዊ በማድረግ በተለይም በኦፓል፣ በታንታለምና በሌሎች ማዕድናት ላይ እሴት ጨምሮ ለገበያ እንዲቀርቡ በማድረግ የውጭ ምንዛሬው ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲጨምር ይደረጋል፡፡ ለገበያ ማዕድናት የሚያቀርቡ አካላት እሴት ጨምሮ በማቅረብ አስተሳሰብ እንዲቀረፁ፣ የተሻለ የገበያ መረጃ፣ ተገቢውን ድጋፍና ማበረታቻ እንዲያገኙ በማድረግ በዓለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን በማጥናት፣ በማፈላለግ፣ በማስፋፋት እና ተወዳዳሪ ሆኖ ወደ ገበያው ዘልቆ በመግባት ከዘርፉ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ እንዲጨምር ይደረጋል፡፡

በሀገር ውስጥ በህጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ የማዕድናት አምራቾችን በውጭ ሀገር ካሉ በዘርፉ ከተሰማሩ አካላት ጋር በማስተባበር፣ የኮንትሮባንድና ህገ ወጥ የማዕድን ዝውውር እና ንግድን በመቆጣጠር ህጋዊ የንግድ ሥርዐት እንዲሰፍን ይደረጋል፡፡ በክልል ያሉትን የወርቅ ግዢ ማዕከላትም በማስፋፋት እና ተጨማሪ የግብይት ማዕከላትን በማቋቋም ከማዕድናት የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡ እሴት ተጨምሮባቸው ለገበያ ለሚቀርቡ የጌጣጌጥ ማዕድናት በተለያዩ ክልሎች የሙከራ የግብይት ማዕከላትንና የጌጣጌጥ ማዕድናት ፓርኮችን በማቋቋም አምራቾችና ነጋዴዎች በሂደት ወደ ሥራው ለመግባት የሚያስችላቸው ሁኔታ እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ የባህላዊ ማዕድን አምራቾችንና በከበሩ ድንጋዮች ማስዋብ ዕደ-ጥበብ ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላትን አቅም የመገንባት፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በማደራጀት ለዜጎች ተጨማሪ የሥራ ዕድል የመፍጠር ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

### 4.5 የማዕድን ዘርፍ የአካባቢ ጥበቃና የማህበረሰብ ልማት ፕሮግራም

በመንግስትና በግሉ ዘርፍ ኩባንያዎች የሚካሄዱ የማዕድን ልማት ሥራዎች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የጥናት ሰነዶችን በመመርመርና አተገባበራቸውን በመከታተል ልማቱ በአካባቢ ላይ ጉዳት ሳያደርስ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ ነባርና አዳዲስ ዘመናዊ የማዕድን ልማት ሥራዎች እና የባህላዊ ማዕድናት ምርት

እንቅስቃሴዎች በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖዎች እንዳያደርሱ የዘርፉ ፈቃዶች በአግባቡ እንዲተዳደሩ፣ የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡ እንዲጠበቅ እና በልማቱ ምክንያት የተጎዱ አካባቢዎችም ተመልሰው እንዲያገግሙ ይደረጋል፡፡ ዘርፉን ለማልማት የፈቃድ ስምምነት ሰነድ የተፈራረሙ አልሚዎች በሚያለሙበት አካባቢ ለሚገኙ ማህበረሰቦች የልማት ፕሮጀክት በጀት እንዲመድቡ፣ በልማቱ ምክንያት የሚፈናቀሉ የማህበረሰብ ክፍሎች መልሰው እንዲቋቋሙ እና ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችሉ ሥራዎች ይሰራሉ፡፡ ከማዕድን ልማት ጋር በተያያዙ የአካባቢ ጥበቃና የማህበረሰብ ልማት ምርጥ ተሞክሮዎችን ከዓለማችን ግንባር ቀደም ከሆኑ አምስት ሀገሮች በመቀመር በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ተጣጥመው እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡ ከክልሎችና ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጋር የሥራ ስምምነት እንዲኖር በማድረግ እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

### 3.1.4 የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት

የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት ዕቅድ መነሻዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም የተገኙ ተሞክሮዎችን በግብዓትነት መወስድና የተጀመሩ ሥራዎችን ማስቀጠል፣ ሀገሪቱ በ2017 መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ የያዘችውን ራዕይ ለማሳካት አስተዋጽዖ ማድረግን፣ በመካከለኛ ገቢ ካሉ አገሮች የዘርፉ ምርጥ ተሞክሮዎች፣ በመሠረተ ልማት በተለይ በኤሌክትሪክ ዘርፍ ልማት የኢኮኖሚውን የመዋቅር ለውጥ የተከተለ እንዲሆን ማድረግ፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦት የማመጣጠን፣ የመሠረተ ልማት ዕድገት ፍላጎት መር ስትራቴጂን እንዲከተል ማድረግን እንዲሁም ከመሠረተ ልማት አኳያ አህጉራዊና ዓለማቀፋዊ ስምምነቶችና ፕሮግራሞችን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

በመሠረተ ልማት መስክ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች በጥቅል ሲታይ የኢኮኖሚውን ፈጣን ዕድገትና መዋቅራዊ ለውጥ የሚደግፍ መሠረተ ልማት ማሟላት፣ ሠፊ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ ጠንካራ የማስፈጸም አቅም ያለው ተቋም መፍጠር፣የህዝብ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣ ያልተማከለ የመሠረተ ልማት ሥርዓት መገንባት፣ የፋይናንስ ማነቆን መፍታት፣ አዋጭነትንና ፍትሐዊነትን ማረጋገጥ፣ በተቀናጀ ሁኔታ የመሠረተ ልማትን ማቀድና ማስተዳደር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በኢኮኖሚ መሠረተ ልማት መስክ የታዩ ማነቆዎችን በማስወገድ የአገሪቱን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ትራንስፎርሜሽን ማሳለጥ፣ የመሠረተ ልማት ተደራሽነትን በመጨመርና ጥራቱን በማረጋገጥ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ ለተልዕኳቸው ብቁ የሆኑ የመሠረተ ልማት ተቋማት በመፍጠርና በማጠናከር ለቀጣይ ዕድገት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ መሠረተ ልማትን ከኢንዱስትሪና ከቴክኖሎጂ ልማት ጋር አስተሳስሮ በመፈጸም የልማቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ፣ ከጎረቤት አገሮች ጋር የመሰረተ ልማት ትስስር በማጠናከር የኢኮኖሚ ትስስሩን ማጎልበት ዋና ዋና የመሠረተ ልማት ዓላማዎች ናቸው፡፡

አጠቃላይ የመሠረተ ልማት ዕቅድ ማስፈጸሚያ ፕሮግራሞች (ሀ) **ሥር ነቀል የተቋማዊ ለውጥ ፕሮግራም፣** የፕሮግራሙ አጠቃላይ ይዘት ተቋሞቻችን በተልእኮዋቸው ዙሪያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግ በአለም አቀፍ ደረጃ ምርጥ የሆኑ አቻ ተቋማትና የሚከተሉት ንድፈ ሃሳብ መሰረት በማድረግ ተቋማዊ ለውጥ ለማካሄድ ነው፡፡

**(ለ) የአገልግሎት አቅርቦት የማሻሻያ ሥራ ፕሮግራም፣** የፕሮግራሙ ይዘት በመሰረተ ልማት ተቋሞች የሚሰጡ አገልግሎቶች አለም አቀፍ ስታንዳርድ የጠበቀ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሃዊ እንዲሆኑ በማድረግ የልማታዊ ባለሃብቱና የህዝቡን እርካታ ለማረጋገጥ ነው፡፡

**(ሐ) የአገር ውስጥ አቅም ግንባታ ፕሮግራም፣** የፕሮግራሙ ይዘት በመሰረተ ልማት ተቋሞች የሚካሄዱ ግንባታዎችና አገልግሎቶች በአገር ውስጥ አቅም ለማስራት ተፈላጊ የአቅም ግንባታና ማበረታቻዎች እንዲሁም አስፈላጊ የህግ ማእቀፎች የሚነደፉበት ነው:: በሂደትም ወደ ውጭ አገር ወጥተው ሊሰሩ የሚችሉ ኩባንያዎች የሚፈለፈሉበት ሁኔታ መፍጠር ተገቢው ትኩረት ይሰጠዋል::

**(መ) የተኪ ምርቶች ፕሮግራም፣** ለበርካታ የመሰረተ ልማት ግንባታና አገልግሎት ስራዎች በውጭ ምንዛሪ የሚገቡ በርካታ ግብአቶች ደረጃ በደረጃ በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት በታቀደ አግባብ የሚሰራበት፣ የአገራችን የኢንዱስትሪ እድገት መነሻ የሚሆንበትና በጥቅሉ የአገራችን የቴክኖሎጂ አቅም የሚዳብርበት ፕሮግራም ነው::

**(ሠ) የፋይናንስ አማራጮች ማፈላለግና መጠቀም ፕሮግራም፣** የፕሮግራሙ መሰረታዊ ይዘቱ ለመሰረተ ልማት ግንባታና ጥገና የሚያስፈልገው ፋይናንስ በወቅቱ ከአዋጪ ምንጭ የሚለይና ተግባራዊ የሚያደርግ ነው:: ከአገር ውስጥ ቁጠባ፣ ብድር ከአገር ውስጥና ውጭ፣ ልዩ ብድር ከአገሮችና ገቢ የሚጨምርበት አግባብም በዚሁ ማዕቀፍ የሚሸፈን ነው::

**(ረ) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት አጠቃቀም ፕሮግራም፣** የመሰረተ ልማት ተቋሞች በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለማድረግ መታጠቅ ከሚገባቸው አንዱ የማነጅመንትና የኦፐረሽን ስራዎቻቸው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ ነው:: ስለሆነም በዚህ ፕሮግራም ተፈላጊ የሆኑ ዘመናዊ ትጥቆች ኩባንያዎቻችን ለማስታጠቅ አስፈላጊው ስራ የሚጠቃለልበት ነው::

**(ሰ) የሕዝብ ተሳትፎ ፕሮግራም፣** በዚህ ፕሮግራም ማህበረሰቡ በግንባታውና በጥበቃው ቀጥታ ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል የጋራ መግባባት በመፍጠር ህዝቡ በንቃት የራሱን ድርሻ እንዲጫወት ማድረግ ይሆናል:: ከዚሁ ጋር በተያያዘም ህብረተሰቡ የሚታዩ ዝንፈቶች በትግል እንዲታረሙ ለማድረግ የሚያስችል አቅም እንዲኖረውም ጭምር ነው::

**(ሸ) የሥራ ዕድል ፈጠራ ፕሮግራም፣** የመሰረተ ልማት ስራዎች ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚጠይቁና በርካታ የስራ እድል በግንባታው ሂደትና በአገልግሎት አሰጣጡ ይፈጠራል:: በመሆኑም በዚህ ፕሮግራም መሰረተ ልማትና የስራ እድል በዝርዝር እየታየ የስራ እድል በስፋት የሚፈጠርበት ሁኔታ ይሸፈናል:: እና
(ቀ) የካሳና ቦታን ከንብረት ነጻ የማድረግ ፕሮግራም፣ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ለማካሄድ ከዝግጅት ጀምሮ የሚያጋጥመው አንዱ ችግር መሰረተ ልማት የሚዘረጋባቸው ቦታዎች ከማንኛውም ንብረት ነፃ ማድረግና የሚከፈሉ ካሳዎች ላይ የሚታዩ ማጭበርበሮች ናቸው:: በዚህ ፕሮግራም ችግሮቹን በማቃለል የመሰረተ ልማት ስራዎቻችን በፍጥነት ወደ ትግበራ የሚገቡበት ስርአት በመቅረፅ ተቋማዊ ምላሽ ለመስጠት የሚጠቅም ነው::

***ሀ) መንገድ***

***ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች፣*** በመንገድ መሠረተ ልማት ዋና ዋናዎቹ የትኩረት አቅጣጫዎች በተከታታይ የተመዘገበውንና የወደፊት የኢኮኖሚ ዕድገትን ማረጋገጥ የሚችል የትራንስፖርት መሠረተ-ልማት ግንባታ መረብን በጥራትና በመጠን በማስፋፋት አቅርቦቱን ማሻሻል ናቸው::
***ዋና ዋና ዓላማዎች፣*** የዘርፉ ዋና ዋና ዓላማዎች ደግሞ የመንገድ መሠረተ ልማት አቅርቦትን ማሳደግ፣ የነባር መንገዶችን ደረጃ ማሳደግ እና ማሻሻል፣ለመንገድ ሀብት አስተዳደር ቅድሚያ ትኩረት የመስጠት፣ የትራንስፖርት ወጪን በመቀነስ ለሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገት ድጋፍ መስጠት ናቸው::

***ዋና ዋና ግቦች፣*** በዕቅዱ ዘመን የዘርፉ ዋና ዋና ግቦች ክረምት ከበጋ የሚያስኬድ መንገድ ርዝመት በ2007 ከነበረበት 120,000 ኪ.ሜ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 220,000 ኪ.ሜ ከፍ ማድረግ፣የ560 ኪ.ሜ የዋና መንገዶች፣ የ3,765 ኪ.ሜ የአገናኝ መንገዶችና የ15,000 ኪ.ሜ የገጠር መንገዶችን ደረጃ ማሳደግ፣ አማካይ ክረምት ከበጋ የሚያስኬዱ መንገዶች ላይ ለመድረስ የሚወስደውን ጊዜ ከ1.5 ሰዓት ወደ 0.8 ሰዓት ዝቅ

ማድረግ፣ በዕቅዱ ዘመን ክረምት ከበጋ ከሚያስኬዱ መንገዶች ከ5 ኪ.ሜ. በላይ ርቀው የሚገኙ አካባቢዎችን መጣኔ ከ33.6 በመቶ ወደ 13.5 በመቶ ዝቅ ማድረግ፣ የመንገድ ጥግግትን ከ109 ኪ.ሜ ወደ 200 ኪ.ሜ/ካሬ ኪ.ሜትር ከፍ ማድረግ፣ በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኙ መንገዶች ከ70 በመቶ ወደ 80 በመቶ ከፍ እንዲል ማድረግ እና የአስፋልት መንገዶች ድርሻ (Paved road ratio) ከአጠቃላይ የመንገድ ሽፋን ከ13 በመቶ ወደ 16 በመቶ ከፍ የማድረግ ናቸው፡፡

**የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች፣** የመንገድ ዘርፍን ዕቅድ ለማስፈጸም የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች በሥራ ላይ ይውላሉ፡፡ ይኸውም፣ የኮንትራት አስተዳደር፣ ዲዛይን ማኔጅመንት፣ የመንገድ ሃብት አስተዳደር እና የሌሎችን የሥራ ክፍሎችን አቅም ማሳደግ፣ የወረዳ መንገድ ዴስኮች የኮንትራት አስተዳደር አቅምን ማሳደግ እና ያለባቸውን የባለሙያ እና የቁልፍ ቁሳቁሶችን እጥረት ለማቃለል ድጋፍ መስጠት፣ የግሉ ዘርፍ በመንገድ ልማት ያለውን ተሳትፎ ማሳደግ፣ የመንገድ ፕሮጀክቶች ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ዝርዝር የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት በማካሄድ በግንባታው ምክንያት በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መለየት እና መፍትሄዎችን መንደፍ እና ተግባራዊ ማድረግ፣ የፕሮጀክቶች ቅድመ ዝግጅት ጥናቶች እና የፕሮጀክቶቹ ግንባታ በሚካሄድበት ወቅት የአካባቢው ህዝብ ተሳትፎን ማጠናከር፣ከገቢዎች እና ጉሙሩክ ባለሥልጣን ጋር ተቀራርቦ በመሥራት የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የቀረጥ ሂደትን ማሳጠር፣የመንገዶች ወሰን በማስከበር ሂደት ከአካባቢ መስተዳድሮች ጋር በቅርበት በመሥራት ሂደቱት ማቀላጠፍ ናቸው፡፡

### ለ) ባቡር

**ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች፡-** በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ዘመናዊ የባቡር ኢንዱስትሪ አካዳሚ ተደራጅቶ አገልግሎት መስጠት እንዲጀምር ማድረግ፣ የተለያዩ የባቡር ኢንዱስትሪ ስታንዳርዶችን ማዘጋጀት፣ የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን በባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የዓለም አቀፍ የባቡር ኢንዱስትሪ ማህበር (UIC) መስፈርቶችን ያሟላ እና ተቀባይነት ያለው ድርጅት እንዲሆን ማድረግ እና በባቡር መሠረተ ልማት ግንባታ፣ ኦፐሬሽንና አገልግሎት ችግር ፈቺ ምርምሮች ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ ዋና ዋናዎቹ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው::

**ዋና ዋና ዓላማዎች፡-** የዘርፉ ዋና ዋና ዓላማዎች የባቡር መሠረተ ልማት አቅርቦትን ማሳደግ፣የመንገደኛና የጭነት የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት በተመጣጠነ ዋጋ ማቅረብ፣ በዘርፉ የግሉን ዘርፍ እና የመንግሥት ትብብራዊ አሠራርን ማሳደግ ናቸው፡፡

**ዋና ዋና ግቦች፡-** በዕቅዱ ዘመን የባቡር ዘርፍ ዋና ዋና ግቦች በጠቅላላው የ2782 ኪሎ ሜትር ሀገራዊና የአዲስ አበባ ከተማ ቀላል ባቡር ኔትወርክ ግንባታ ማካሄድ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 2741 ኪሎ ሜትር ሀገራዊ የባቡር ኔትወርክ በአምስት ኮሪደሮችና በስድስት መስመሮች የሚገነባ ነው፡፡ የሀገራዊ ኔትወርክ ግንባታ በዕቅዱ ዘመን የባቡር ዘርፍ ዋና ዋና ግቦች በአምስት ኮሪደሮችና በስድስት መስመሮች በጠቅላላው የ2,782 ኪሎ ሜትር ሀገራዊ የባቡር ኔትወርክ ግንባታ መቀሌ-ሃራ ገበያ (268 ኪ.ሜ)፣ሃራ ገበያ - አሳይታ (229 ኪ.ሜ)፣ አሳይታ-ታጁራህ ወደብ (210 ኪ.ሜ)፣ አዋሽ-ሃራ ገበያ (389 ኪ.ሜ)፣ አዲስ አበባ/ሰበታ - ኢጃጂ - ጂማ - በደሌ-ቴፒ-ዲማ (740 ኪ.ሜ)፤ ሞጆ-ሀዋሳ-ወይጦ-ሞያሌ (905 ኪ.ሜ) የሚካሄድ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ቀላል የባቡር መስመር ግንባታ ደግሞ በሁለት ኮሪደሮች የ41 ኪ.ሜ. የሚሸፍን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ኮሪዶሮች አምስት የባቡር ፕሮጀክቶች ጥናት እና የፋይናንስ ማፈላለግ ሥራዎች የማካሄድ ግብ ተጥሏል፣ ይኸውም የወልድያ - ወረታ - ፍኖተ ሰላም (500 ኪ.ሜ)፣ ወረታ-መተማ (244 ኪ.ሜ)፣ መቀሌ - ሽሬ (368 ኪ.ሜ)፣ ኢጃጅ-ኩምሩክ (460 ኪ.ሜ) እና ኢተያ-ጊኒር (248 ኪ.ሜ) ናቸው፡፡

**የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች፣** የዘርፉን ዕቅድ ለማስፈጸም እንዲቻል የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስትራጂዎች ተነድፈዋል፡፡ ይኸውም፣ ከአበዳሪዎች ጋር የፋይናንስ ብድር ድርድር በማድረግ ስምምነት ላይ መድረስ፣ የተለያየ የጥናት እና የዲዛይን ሥራዎች እንዲያከናወኑ ማድረግ፣ የሃገር ውስጥና የውጭ ሀገር ባለሙያዎች በጥናት እና የዲዛይን ሥራው ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የአዲስ አበባ-ጅቡቲ የባቡር መስመር በማኔጅመንት ኮንትራክተር ለመጀመሪያዎቹ ዓመታት መመራት ስለሚኖርበት ዓለም ዓቀፍ ምርጥ

ማኔጅመንት ኮንትራክተር እንዲቀጠር ማድረግ የኢትዮጵያና የጅቡቲ መንግሥታትን የሁለትዮሽ ስምምነትን መሠረት ያደረጉት የባቡር ደንብ፣ የታሪፍ ሥርዓት፣ የጭነትና የመንገደኞች ስምሪት አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያዎች ተቀርፀው ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣ የግሉ ዘርፍ በባቡር ፕሮጀክት አዋጭነት ጥናት፣ ዲዛይን፣ በግንባታ ኮንትራክተርነት እና አማካሪነት ላይ እንዲሳተፍ ማድረግ እንዲሁም ባቡር ኢንዱስትሪ ላይ ያተኮረ ትምህርት እና ሥልጠና በመስጠት በባቡር ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ አስተዋጽዖ እንዲያደረጉ ማድረግ ናቸው፡፡

## ሐ) ኢነርጂ

**ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች፣** የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጨት፣ ማስተላለፍና ማከፋፈልን በተመለከተ ዋና ዋናዎቹ የትኩረት አቅጣጫዎች አገራችን በ2017 መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ለማድረግ የኢንደስትሪውን፣የግብርናና የአገልግሎት ዘርፎች የሚፈልጉትን ሀይል እስከ 2012 እንዲያገኙ ማድረግ፣ የግንባታ ወጪን የአገር ውስጥ ድርሻ ከ50 በመቶ በላይ ከፍ ማድረግ፣ ለልማት አስፈላጊ የምርምር እና ጥናት አቅምን ከፍ በማድረግ በምርምር የታገዘ የቴክኖሎጂ ማሻሻያ ማምጣት ናቸው፡፡ ከሀይል ማመንጫዎች ልማት አኳያ 1ኛ) የውሃ ሀይል ማመንጫ፣ 2ኛ) የጂኦተርማል ሀይል ማመንጫ፣ 3ኛ) ሀገራችን ከሌሎች የጎረቤት አገሮች በተሻለ ተወደዳዳሪ የምትሆንበት የንፋስ ሀይል ማመንጫ፣ እና 4ኛ) የፀሐይ ሀይል አቅርቦት በቅደም ተከተል ትኩረት የተሰጣቸው ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ የባዮማስ ሀይል ማመንጫዎችና ዲዝል ጀነሬተሮችን በመጠቀም ለመጠባበቂያ የሀይል ምንጭነት ማዋል ሌሎቹ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

የአማራጭ ኢነርጂ ልማትን በተመለከተ ከተያዙ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች መካከል የባለድርሻ አካላትን (የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን፣ የክልሎችንና ሌሎች) ዐቅም በመገንባት የአማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች ወይም ምንጭ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የማልማትና የማስፋፋት ሥራ በማካሄድ ህብረተሰቡ የዘመናዊ ኢነርጂ ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል አንዱ ነው፡፡ ሁለተኛው የትኩረት አቅጣጫ በጸሐይ፣ በንፋስ፣ በአነስተኛ ሀይድሮና ሌሎች የአማራጭ ኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎች ልማትና ሥርጭትን በማስፋፋት የትምህርትና የጤና ተቋማት፣ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚና ጥቃቅንንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች የሚስፋፉበትን ሁኔታ በመፍጠር ለፈጣን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት አስተዋጽዖ ማድረግ ነው፡፡ ሶስተኛው የትኩረት አቅጣጫ በባዮማስ ኢነርጂ ላይ በመሥራት የህብረተሰቡን የኢነርጂ አጠቃቀም በማሻሻል የማገዶ ፍላጎትን መቀነስና አዳዲስ የኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ ህብተረተሰቡን ተጠቃሚ በማድረግ በደን ሀብታችን ላይ ያለውን ጫና በመቀነስ በረሃማነትን መከላከል፣ በቤት ውስጥ ያለውን የአየር ብክለት በመቀነስ በሴቶችና በህጻናት ላይ በጢስ ምክንያት የሚከሰተውን የጤና ችግር መቀነስና ለማገዶ ፍለጋ ይውል የነበረውን ጊዜ በመቀነስ በምርት ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ ነው፡፡ አራተኛው የትኩረት አቅጣጫ የንፋስ ኢነርጂን ለኤሌክትሪክ አገልግሎትና የውሃ መሳቢያ ፓምፖች በመጠቀም ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ማዋል ናቸው፡፡

ከባዮ ፊውል ልማት አኳያ የባዮ ፊውል መረጃ ማሰባሰብና ማደራጀት፣ ባለሀብቱንና ህብረተሰቡን ባመሳተፍ ለሀገር ውስጥ ፍጆታና ለውጭ ገበያ የሚበቃ የባዮፊውል ነዳጅ ማምረት፣ የባዮፊውል የቴክኖሎጂ ስታንዳርዶችንና የአፈጻጸም መመሪያዎችን ዝግጅት በማስተባበር በዋናነት በትራንስፖርት ሴክተር የባዮፊውልን አጠቃቀም ማሳደግ፣ በካይ ጋዞችን በመቀነስ የሚገኝ ፋይናንስን ለመጠቀም የሚያስችሉ ሥራዎችን በስፋት ማከናወን፣ የባዮፊውል ልማትና ከልማቱ የሚገኘው ጥቅም ዘላቂ እንዲሆን ግንዛቤ መፍጠር፣ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

**ዋና ዋና ዓላማዎች፣** የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨትን፣ ማስተላለፍንና ማከፋፈልን በተመለከተ የዕቅዱ ዘመን የዘርፉ ዋና ዋና ዓላማዎች በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ኢትዮጵያ የአረንጓዴ ታዳሽ የኃይል ማመንጫዎችን የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮችን ባካተተ ሁኔታ በመገንባት ከራሷ ፍጆታ ተርፋ በምሥራቅ አፍሪካ የታዳሽ የሀይል ምንጭ ማዕከል እንድትሆን ማድረግ፣ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮችን

ባካተተ ሁኔታ የኃይል ማስተላለፊያ ኔትዎርክን ማስፋፋት፣ የአገር ውስጥንና የኤክስፖርት ፍላጎትን በአስተማማኝ ሁኔታ ማሟላት፣ አገልግሎቱን ለደንበኞች ያለውን ተደራሽነትን ከፍ ማድረግ፣ አስተማማኝ የኃይል ኤክስፖርት ገበያ ማዘጋጀት፣ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮችን ባካተተ ሁኔታ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ባልተዳረሰባቸው የአገሪቱ ከተሞችና መንደሮች ማዳረስ፣ አገልግሎት አሰጣጡን አስተማማኝና የተቀላጠፈ ማድረግ እና ኢኒስቲቲዩሽናል ትራንስፎርሜሽን ማምጣት ናቸው፡፡ ከአማራጭ ኢነርጂ አንፃር የቴክኖሎጂዎች ሽግግርና ሥርጭት እንዲፋጠን ማድረግ፣ የባዮ ፊውል ልማትን በሚመለከት የባዮፊውል ምርት ለቅየጣና ለቤተሰብ አገልግሎት እንዲውል ማድረግ፣ የሚሰራጭ/ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የኤታኖልና ባዮፊውል ምድጃ፣ ኤታኖልንና ባዮፊውልን በመጠቀም የውጭ ምንዛሪ ማዳን፣ የጃትሮፋ ተክልንና ባዮ ፊውልን በመጠቀም የካርቦን ልቀት ማዳን ዋና ዋናዎቹ ዓላማዎች ናቸው፡፡

**ዋና ዋና ግቦች፣** የኤሌክትሪክ ሀይል የማመንጨት ዐቅምን በ2007 ከነበረበት 2,220.5 ሜጋ ዋት በ2012 ወደ 17,347 ሜጋ ዋት ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ ከውሃ ሀይል ማመንጫ የሚገኘውን ሀይል ከ1,953.5 ወደ 13,957 ሜጋ ዋት፣ ከንፋስ ሀይል የሚገኘውን ከ171 ሜጋዋት ወደ 1,222 ሜጋዋት፣ ከጸሐይ 300 ሜጋዋት ሀይል፣ ከጂኦተርማል የሚገኘውን ሀይል ከ7.0 ሜጋዋት ወደ 577 ሜጋዋት፣ ከመጠባበቂያ/ጋስ ተርባይን/ከነዳጅ 509 ሜጋ ዋት፣ ከቆሻሻ 50 ሜጋዋት፣ ከስኳር 474 ሜጋዋትና ከባዮማስ 258 ሜጋዋት ሀይል እንዲመነጭ ግብ ተጥላል፡፡ የኤሌክትሪክ ሀይል የማምረት ዐቅምን ከ10,020.8 ጌ.ዋ.ሰ ወደ 63,207 ጌ.ዋ.ሰ ከፍ ማድረግ፣ አጠቃላይ የሀይል ማስተላለፊያ መስመር ርዝመትን በ2007 ከነበረበት 12,825 ኪ.ሜ በ2012 ወደ 21728 ኪ.ሜ ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ ባለ 500 ኪ.ቮ በ2012 በጀት ዓመት 1,240 ኪ.ሜ ለማድረስ ግብ የተጣለ ሲሆን ባለ 400 ኪ.ቮ በ2007 ከነበረበት 1,107 ኪ.ሜ በ2012 ወደ 2,137 ኪ.ሜ፣ የባለ 230፣132ና 66 ኪ.ቮ መስመርን በ2007 ከነበረበት 11,718 በ2012 ወደ 18,351 ኪ.ሜ ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሏል፡፡የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሽፋንን በ2007 ከነበረበት 60 በመቶ በ2012 ወደ 90 በመቶ ከፍ ማድረግና የደንበኞችን ብዛት በ2007 ከነበረበት 2.455 ሚሊዮን በ2012 ወደ 6.955 ሚሊዮን ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ የኤሌክትሪክ ፍጆታን አሁን ካለበት 86 ኪሎ ዋት ሰዓት በ2012 ወደ 1,269 ኪዋሰ ከፍ ማድርግና የሀይል ብክነትን አሁን ካለበት 22.3 በመቶ በ2012 ወደ 11 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ግብ ተጥሏል፡፡

ከአማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች አኳያ በዕቅዱ ዘመን በድምሩ 11.45 ሚሊዮን የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎች፣31,400 የባዮጋዝ ቴክኖሎጂ፣ 20,000 የቤተሰብ የባዮ ዘይት ምድጃ እና የባዮ ዘይት መጭመቂያ ቴክኖሎጂዎች ለማሰራጨት ግብ ተጥሏል፡፡ የፀሐይ ሀይል ቴክኖሎጂዎችን በተመለከተ 3,600,000 በፀሐይ ሀይል የሚሰሩ አነስተኛ ማሾዎች፣ 400,000 በፀሐይ ሀይል የሚሰሩ የቤተሰብ ሶላር ሲስተሞች፣ 3,600 በጸሐይ ሀይል የሚሰሩ የተቋማት ሶላር ሲስተሞች፣ 5,000 በፀሐይ ሀይል የሚሰሩ የውሃ ማሞቂያ መሳሪያዎች እና 3,600 በፀሐይ ሀይል የሚሰሩ ማብሰያዎች ለማሰራጨት ግብ ተጥሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 300 በውሃ ሀይል የሚሰሩ መሳቢያ ቴክኖሎጂዎች ሥርጭት፣ 105 ከአነስተኛ ወንዞች የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጨትና 33 የአማራጭ ቴክኖሎጂዎች ጥናትና ልማት ለማካሄድ ታቅዷል፡፡

ከባዮ ፊውል ልማት ጋር በተገናኘ 16.6 ሚሊዮን ሄክታር ለባዮፊውል ልማት የሚሆን መሬት መረጃ ማሰባሰብ፣ 500,327 ሄክታር መሬት በባዮዲዝል ሰብሎች መሸፈን፣ 1,375.23 ሚሊዮን ሊትር ባዮ ኢታኖል ማምረት፣ 450.3 ሚሊዮን ሊትር የባዮዲዝል ማምረት፣5 የባዮ ኢታኖል የመቀየጫ ፋሲሊቲዎች ማዘጋጀት፣16 የባዮ ዲዝል የመቀየጫ ፋሲሊቲዎች ማዘጋጀት፣64.4 ሚሊዮን የባዮ ኢታኖል ቅይጥ ማድረስ፣ በባዮ ፊውልና በባዮጋዝ ልማት ላይ ለሚሳተፉ 706 ባለሙያዎች በየደረጃው ስልጠና እንዲሰጥ ግብ ተጥሏል፡፡ በዚህም የጃትሮፋ ተክልን በመጠቀም 49.8-65.9 ቶን ካርቦን-ዳይኦክሳይድ በሄክታር እንዲሁም ኢታኖልን በመጠቀም 60 ቶን ካርቦን-ዳይኦክሳይድ በሄክታር የማዳን ግብ ተጥሏል፡፡

**የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች፣** የዘርፉ የዕቅድ ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች በራስ ሀይል ለማከናወን የሚያስችል አደረጃጀት በሁሉም በሀይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማከፋፈያ ጣቢያዎች መፍጠርና ያሉትን ማጠናከር፣ በራስ ሀይል ጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ ማካሄድ፣ የአገር ውስጥ ኮንትራክተሮችን/አነስተኛ

ጥቃቅን ማህብራትን/ ዐቅም በማሳደግ አስፈላጊ ግብዓቶችን እንዲያመርቱ፣ በግንባታ ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ የወጪ ምንዛሪ ድርሻን መቀነስ፣ አሁን በማኑፋክቸሪንግ ላይ የተሰማሩት በሴክተሩ የመሳተፍ ሚናቸው እንዲጎላ ሁኔታዎችን ምቹ ማድረግ፣ ከአገር ውስጥና ከውጪ ሊገኝ የሚችለውን ፋይናንስ መለየትና ተግባራዊ ማድረግ፣ የግል ባለሀብቱን ፖሊሲው በሚፈቅደው መሠረት በሀይል ማመንጫው ዘርፍ እንዲሳተፍ ማመቻቸት እና በአማራጭ ኢነርጂ ንዑስ ዘርፍ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች በዐቅም ግንባታ፣ በቴክኒካል ድጋፍና ክትትል፣ በማበረታቻና ድጋፍ፣ ሥርጸት፣ የገበያ ልማትን ማስፋፋትና ማሻሻል እንዲሁም በማስተዋወቅና ፕሮሞሽን ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ የባዮፊውል ቴክኖሎጂ የማላመድና የማስፋፋት ሥራው ወቅታዊነትና ዘላቂነት እንዲረጋገጥ ከምርምር ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ዘላቂ ኔትዎርክ በመፍጠር መሥራት፣ በባዮፊውል ልማት የሚካሄዱ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በየወቅቱ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት በመዘርጋት መከታተል ናቸው፡፡

**መ) የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ**

**ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች፣** የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማትን ከማፋጠን አኳያ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫዎች የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ዕድገት እና ህጋዊ ስርዓትና ደህንነትን ማረጋገጥ፣ የሰው ሀይል ልማት፣ የመረጃ ቴክኖሎጂን ለመንግስት አስተዳደር (E-gov) መጠቀም፣ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶችን ደረጃ ማሳደግ፣ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ዕውቀትን በህብረተሰቡ ውስጥ ማስረጽ፣ በዘርፍ የምርምርና የፈጠራ ስርዓትን መገንባትና ስታንዳርዶችን ማውጣት፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪን በማጠናከር የዘርፉን ተወዳዳሪነትና ተጠቃሚነት ማጎልበት ሲሆን በቴሌኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት ረገድ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎችና የሀገሪቱን ዜጎች በተለይም የገጠሩን የሀገራችን ክፍል የልማቱ ተጠቃሚ ለማድረግ የድምጽ እና ዳታ አገልግሎት ስርፀትና ስብጥርን ማሳደግ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ ይህንንም ለማከናወን የኔትወርክ አቅምና ተደራሽነትን በማሳደግ ዘመኑ ያፈራቸውን አዳዲስ ቴክሎጅዎች በመትከል የድምፅና ፈጣን የኢንተርኔት አገልግሎቶችን አቅምን ባገናዘበ መልኩ ማቅረብ፣ የሁለተኛው ትውልድ ድርሻን በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 93 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 47 በመቶ መቀነስ፣ ከብሮድባንድ ኢንተርኔት አገልግሎት የሚገኘውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማረጋገጥ እና የሚዘረጋውን ከፍተኛ የኔትወርክ አቅም አሟጦ ለመጠቀም እንዲቻል የግል አይሲቲ ድርጅቶች ተሳትፎን ማጎልበት፣ ብሔራዊ የብሮድባንድ ስትራቴጅ በመንደፍ ሁሉም የመንግስት ቢሮዎችና ህብረተሰቡ የብሮድባንድ ኢንተርኔት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አግባብ መፍጠር፣ ከፍተኛ አቅም ያለውና አስተማማኝ የመስተላለፊያ ኔትወርክ መዘርጋትና አለም አቀፍ የኢንተርኔት ሊንክ መፍጠር እንዲሁም በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች አሁን ካለው የድምጽና ናሮባንድ ኢንተርኔት አገልግሎት በተጨማሪ የብሮድባንድ ኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆኑበት ስልት ይፈጠራል፡፡ በፖስታ አገልግሎት መሰረተ ልማት ረገድ የትራፊክ መጠንንና የፖስታ አገልግሎት ሽፋንን ማሳደግ፣ የአገልግሎት ጥራት ደረጃን ማሻሻል እና መሰረታዊ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ አገልግሎቶችን መጨመር ትኩረት የተሰጣቸው አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

**ዋና ዋና ዓላማዎች፣** የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ዋና ዋና ዓላማዎች የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን በማሳደግ ዘርፉ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን ድርሻ ማጎልበት እና ሀገሪቱ የፈጣን ልማትና ዕድገት ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል፣ሁሉን አቀፍ የሆነ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎችና የህብረተሰብ ክፍል ደረጃ በደረጃ ማዳረስ ሲሆን በቴሌኮሙኒኬሽን ንዑስ ዘርፍ ደግሞ ተወዳዳሪና ምርታማ የሆነ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ፍትሀዊ በሆነ መልኩ በመላ ሀገሪቱ መዘርጋት፣ በዋጋና በጥራት ተወዳዳሪ የሆነ የቴሌኮም አገልግሎት ማቅረብ፣ ሁሉን አቀፍ የቴሌኮም አገልግሎት መፍጠር፣ የግሉ ዘርፍ ወቅታዊ የመገናኛና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ መጠቀም የሚያስችለውን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በራስ አቅም መስራት የሚያስችል አቅም መፍጠር፣ በሞባይል ስነ-ምህዳር ውስጥ ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር ቅርብ ግንኙነት በመፍጠር የግል ሴክተሩን በማበረታታት ዘርፉን ማጠናከር ናቸው፡፡ በፖስታ ንዑስ ዘርፍ ደግሞ ዋና ዋናዎቹ ዓላማዎች አዳዲስ አገልግሎቶችን መጀመር፣ መሰረታዊ የፖስታ አገልግሎትን

በበቂ ሁኔታ ማዳረስ፣የአገልግሎት ጥራትን (ፍጥነትና ደህንነትን) በሚፈለገው ደረጃ ማረጋገጥ እና የማስፈጸም አቅምን ማጎልበት ናቸው፡፡

**ዋና ዋና ግቦች፣** በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ዋና ዋና ግቦች የኮምፒውተር ተጠቃሚን ቁጥርና ስርጭት መጨመር፣ የአይሲቲ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን ማስፋፋት ሲሆን በቴሌኮሙኒኬሽን ንዑስ ዘርፍ ደግሞ የሞባይል ስልክ፣ የብሮድባንድ ኢንተርኔትና ዳታ፣ የናሮው ባንድ ኢንተርኔትና ዳታ እና የመደበኛ ስልክ ደንበኞች ብዛት በቅደም ተከተል በ2007 ከነበረበት 40 ሚሊዮን፣ 1.59 ሚሊዮን፣ 8 ሚሊዮን እና 3.05 ሚሊዮን ደንበኞች በ2012 ወደ 103፣ 39.1፣16.9 እና 10.4 ሚሊዮን ከፍ ለማድረግ፣ የሞባይል አገልግሎት ስርፀት በ2007 ከነበረበት 43.9 በመቶ በ2012 ወደ 100 በመቶ፣ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ የመደበኛ ስልክ ስብጥር (tele density) ከ10.5 በመቶ ወደ 54 በመቶ፣ የኢንተርኔት ዳታ ስብጥር (density) ከ3.3 በመቶ ወደ 10 በመቶ፣አለም አቀፍ ሊንክ አቅምን ከ20 Gbs ወደ 1485 Gbs ከፍ ለማድረግ ግብ የተጣለ ሲሆን የሞባይል አገልግሎትን የቆዳ ሽፋን አሁን ባለበት 85 በመቶ ላይ እንዲቆይ ማድረግ ዋና ዋናዎች ናቸው፡፡ የፖስታ መሰረተ ልማት ንዑስ ዘርፍ ዋና ዋና ግቦች ደግሞ የትራፊክ መጠንን በ2007 ከነበረበት 28.7 ሚሊዮን በ2012 ወደ 657.4 ሚሊዮን ከፍ ማድረግ፣ የአገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን ብዛት ከ1,000 ወደ 16,475 ከፍ ማድረግ፣ የፖስታ ባንክና የፖስታ ኢንሹራንስ የተጀመረባቸው ፖስታ ቤቶችን ቁጥር እያንዳንዳቸውን በ2012 70 ማድረስ ናቸው፡፡

**የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች፣** የዘርፉ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች በተመለከተ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት አውታሮችን በማስፋፋት ዘመናዊና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የግሉ ዘርፍ የሚያደርገውን አስተዋጽዖ ማጎልበትና በኢትዮ አይሲቲ ቪሌጅ እንዲገቡ በማድረግ የኢንፎረሜሽን ቴክኖሎጂ መጠቀሚያ መሳሪያዎችን በሀገር ውስጥ እንዲመረቱና ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ኤክስፖርት ማድረግ የሚቻልበትን ምቹ መደላድል መፍጠር፣ የመረጃ ሀብቶችንና አገልግሎቶችን ከማልማት ጋር የተያያዙ የህግ ማዕቀፎችን ማውጣትና ከዚህ በፊት ያሉትን ህጎችና ማዕቀፎች በልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ውስጥ በተቀናጀ ሁኔታ የማካተት ስራዎች ዋና ዋናዎቹ የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው፡፡ በቴሌኮም ንዑስ ዘርፍ የደንበኞችን ዕድገት ከግምት ውስጥ ያስገባ የኔትወርክ ማስፋፊያ ስራና ከፍተኛ አቅምና አስተማማኝ የማስተላለፊያ ኔትወርክ መፍጠር፣ የአገልግሎት ጥራትን ለማምጣት የሚያስችሉ የኔትወርክ ማትባት ስራ ማከናወን እንዲሁም በፖስታ ንዑስ ዘርፍ የመልዕክት ደህንነትና ፍጥነትን ማሻሻል፣የተጀመረውን ብሔራዊ የፖስታ አድራሻ ስርዓት በፍጥነት ተግባራዊ ማድረግ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ማውጣትና አገልግሎቱን ተደራሽነ ማድረግ የዕቅዱ ዘመን ዋና ዋናዎቹ የዘርፉ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች ናቸው፡፡

## ሠ) የመጠጥ ውሀ ሳኒቴሽንና መስኖ

**ዋና ወና የትኩረት አቅጣጫዎች፣** በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ንዑስ ዘርፍ የእቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች የመጠጥ ውሃ ተቋማትን ዘላቂ፣ አስተማማኝና ብቃት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ በማስቻል በዘርፉ መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥና የሴክተሩን ሁለንተናዊ የመፈፀም አቅም አጠናክሮ ማስቀጠል ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡ የከተማ ዉሃ አገልግሎቶችን የወጪ መጋራት አቅም በማጎልበትና መልካም አስተዳደርን በማስፈን የደምበኞች እርካታን ማረጋገጥ፤ ሰፊ የሰው ጉልበትና የአካባቢ ቁሳቁሶችን የሚጠቀሙ ቴክኖሎጅዎችንና ፀሀይንና ነፋስን የመሰለ የታዳሽ ሀይል ጉልበትን የሚጠቀሙ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም የግንባታ ወጪን መቀነስ ሌላዉ ትኩረት የሚደረግበት ተግባር ነው፡፡ በከተሞች የፍሳሽ ዉሃ ማስወገጃ ስርአት እንዲዘረጋ ማድረግ፤ ከውጭ የሚገቡ የዘርፉ ቴክኖሎጂዎችን በአገር ዉስጥ እንዲመረቱ ለግል ሴክተሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤ በዉሃ ተቋማት ግንባታና አስተዳደር ላይ የተጠቃሚዉን ህዝብ ሰፊ ተሳትፎ ለማረጋገጥ የህዝብ ንቅናቄ መፍጠር፤ የተጀመረዉን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎዎጅ የሚታገዝ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ግንባታ ይበልጥ ማጠናከር ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ የዘርፉን መሰረተ ልማት ግንባታ በ2012 ዓም መካከለኛ ገቢ ያላቸዉ አገሮች የደረሱበት ደረጃ ማድረስ፣ የግንባታ ወጪን መቀነስ፣ ከውጭ የሚገቡ የዘርፉ ቴክኖሎጂዎችን በአገር ዉስጥ እንዲመረቱ ለግል ሴክተሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ናቸው፡፡ የከርሰ ምድር ውሀን በአግባቡ ለማልማትና ለሚፈለገው አላማ ለማዋል ዘርፉ ከልማት ባንክ ብድር

የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲመቻችና እንዲሁም ለአጣዳፊ የስራ ፍላጎት አስቸኳይ የሆኑትን መሳሪያዎች (ሪጉች፣ የመለዋወጫና የቁፋሮ እቃዎች) ለወደፊቱ በበቂ ሁኔታ በአገር ውስጥ አከፋፋዮች በክምችት (stock) የሚያዙበት ሁኔታ የሚመቻች ሲሆን በሞዴልነት የሚያገለግል ከተግባራዊ የፕሮጀክት ስራዎች በተጓዳኝ ስልጠናና የምርምር ተግባራትን የሚያከናውን፣ በዘርፉ ክህሎት ባላቸው በፕሮፌሽናል ባለሙያዎችና ቴክኒሺያኖች የተዋቀረ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ድርጅቶች ከመንግስት ጋር በአክስዮን መልኩ እንዲቋቋሙ የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፎችን መስጠት፣ አገራዊ የውሃ ጥራት ስታንዳርድ ማውጣት፣ የግል ባለሃብቶች በመካከለኛና በሰፋፊ መስኖ ልማት ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ በማድረግ ራሳቸውንና ሃገሪቱን እንዲጠቅሙ የተቀናጀ ጥረት ማድረግ፣ ለመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማት መስፋፋት መሪ የሆኑ የፖሊሲ ማዕቀፎች እንዲሟሉ  በማድረግና ዓመታዊ የበጀት ምደባውን ከጊዜ ወደጊዜ በማሳደግ ዘርፉ በኢኮኖሚው ውስጥ ሊኖረው የሚችለውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡ የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣውን የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና እየረቀቀ ያለውን አኃዛዊ ትንበያ (Numerical weather prediction, NWP) ደረጃ በማመልከት ከሱፐር ኮምፒዩተሮች የተገኙ ዉጤቶችን እና ለአካባቢያችን አሀዛዊ የአየር ትንበያ Numerical Weather Prediction ሞዴሎችን በመደበኛ ኮምፒዩተር የመጠቀም አቅምን ማሳደግ ሌላው የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡

ዘርፉ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ሥራዎች የበኩሉን አስተዋፅኦ የሚያበረክትባቸው መስኮች ለግብርና ልማት ዘርፍ ስኬታማነት የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት Response Farming መሰረት ያደረገ የGras Root Meteorological Service (GRMS) አገልግሎትን መስጠት ተግባር፣ ለዉሀና ኢነርጅ ተኮር የHydro meteorology ትንበያና የምክር አገልግሎት መስጠት፣ በሽታን ለመከለከል የሚያስችል የጤና ሚቲዎሮልጂ ትንበያና የምክር አገልግሎትን ተግባራዊ ማድረግ፣ ለግንባታው ዘርፍ የሚቲዎሮልጂ መረጃን በመጠቀም ለግንባታ ሥራ ውጤታማነት ላይ እሴት እንዲጨምር ማድረግ በዕቅድ ዘመኑ ትኩረት የተሰጣቸው ተግባራት ናቸው፡፡ በአቪየሽን ሚቲዎሮልጂ አገልግሎት ዘመኑ የሚጠይቃቸዉን የቴክኖልጂ አሰራሮች መሰረት ያደረገ ለዉጥን በመተግበርና የአየር ሁኔታ ገፅታዎችን በማጥናት የሚያስከትሉትን ተፅዕኖዎች በቅድሚያ ለመተንበይ የሚያስችል ሳይንሳዊ መሠረት ያላቸው የትንበያ ዘዴዎችን /Prediction techniques/ የመገንባት ተግባር የሚከናወን ሲሆን በአገሪቱ ሊከሰት የሚችለውን የአየር ጠባይ መዛባትና ለውጥ እንዲሁም በተፈጥሮ ሀብት /Environmental Resources/ ላይ ሊደርስ የሚችለውን የአየር ብክለትና ሌሎች ጎጂ ክስተቶችን በቅድሚያ መረዳት የሚያስችሉ ስራዎችን ማከናዎን ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

**ዋና ዋና ዓላማዎች፣** በዕቅድ ዘመኑ በዘርፉ የሚከተሉት ዓላማዎች ተቀምጠዋል፡፡ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ማሳደግና የተሻሻለ የፍሳሽ አወጋገድ ስርዓት መፍጠር፣ የንፁህ መጠጥ ዉሃ አቅርቦት አገልግሎትን ደረጃ በማሻሻል ተደራሽነቱን ማስፋትና የከተሞች የዉሃ ፍሳሽ አወጋገድ ስርዓት ማሻሻል፣ የውሃ ሀብታችን መጠንና ጥራት በማወቅ በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተጽእኖ በመለየትና በማስራጨት የሃገሪቱን ኢኮኖሚ እንዲደግፍ ማስቻልና ሊደርስ የሚችለውን የጎርፍ አደጋ መከላከል፣  በብሔራዊ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ የውጭ ምንዛሪ ለማስገኘትና የግብርና ውጤቶችን እንደ ግብዓት ለሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች የጥሬ ዕቃዎችን ለማቅረብ መካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ እርሻዎችን ማልማትና ማስፋፋት ነው፡፡ ዘላቂ፣ ውጤታማና በአቅም ደረጃ ሊሠሩ የሚችሉትን የመስኖ እርሻዎች ማስፋፋት እና የመካከላኛና ሰፋፊ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን ጥናትና ዲዛይን በማጠናቀቅ በማንኛውም ጊዜ በባለሀብቱም ሆነ በመንግስት መልማት በሚችሉበት ደረጃ ላይ መገኘታቸውን ማረጋገጥ፣ በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ንዑስ ዘርፍ ደግሞ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለህብረተሰቡ ማዳረስና ሀገራችንን ከተለያዩ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋዎች መታደግ፣ እንዲሁም መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ እንድትሰለፍ ተገቢዉን ድጋፍ በብቃት መወጣት፤ ደረጃውን የጠበቀ (የWMO) የትንቢያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስፈርትን ያሟላ አገልግሎት መስጠት፤ በከፍተኛ ወጪ የሚገዙበትን የሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎች በሀገር ውስጥ ለማምረት ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጂት መስራት የሚሉታ ናቸው፡፡

ናቸው፡፡

**ዋና ዋና ግቦች፣** መጠጥ ውሃ፣ ሳኒቴሽንና መስኖ ልማትን በተመለከተ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ስታንዳርድ መሠረት የውሃ ሽፋንን 100 በመቶ ማድረስና በ2ኛው የዕድገትና ትርንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት ደረጃን በማሻሻል ከ25 ሊትር ለሰው በቀን ባላነሰና ከ1ኪ.ሜ ባልበለጠ ርቀት በማዳረስ ሽፋኑን በ2007 ከነበረበት 59 በመቶ በ2012 ወደ 85 በመቶ ከፍ ማድረግ፣ የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን አገልግሎትን 100ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 1፣ 80ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 2፣60ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 3 ፣50ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 4 እና 40ሊትር በሰው በቀን ለደረጃ 5 ባላነሰ ለከተሞች በማቅረብ በ2007 ከነበረበት 51 በመቶ በ2012 ወደ 75 በመቶ ከፍ ለማድረግ እንዲሁም አጠቃላይ አገራዊ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን በ2007 ከነበረበት 58 በመቶ በ2012 ወደ 83 በመቶ ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሏል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማት የብልሽት መጠንን በ2007 ዓ.ም ከነበረበት 15.5 በመቶ ወደ 7 በመቶ ለመቀነስ፣ የከተሞችን የውሃ ብክነት (UFW) በ2007 ከነበረበት 39 በመቶ ወደ 20 በመቶ መቀነስ፣ የሃገሪቱን የከርሰ ምድር ውሃ ሃብት አለኝታ ጥናት ሽፋን አሁን ካለበት 10 በመቶ ወደ 25 በመቶ ማሳደግ፣የተቀናጀ የተፋሰስ አስተዳደር እና ልማት በእቅድ ዘመኑ በሁሉም ተፋሰሶች ተግባራዊ በማድረግ የውሃ አካላት ስነ-ምህዳር ልማትና እንክብካቤ በመጀመሪያ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን ከነበረበት **1,000,000** ሄክታር ወደ **2,382,283** ሄክታር ያገገመ መሬት ከፍ ማድረግ ፣25 በመቶ የነበረውን የተፋሰስ ወቅታዊና የተደራጁ የመረጃ (Basin Information system and hydrological Information system) ሽፋን ወደ 63 በመቶ ከፍ ማድረግ፣ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር የሃይድሮሎጂ መረጃ ሽፋንና አቅርቦትን በዕቅድ ዘመኑ ወደ 95 በመቶ ለማድረስ ግቦች ተጥለዋል፡፡

**የመስኖ ልማት ንዑስ ዘርፍን በተመለከተ** በሦስት አስፈፃሚ አካላት የጥናት ዲዛይንና ግንባታ ስራ ለማከናወን ታቅዷል፡፡ ይኸውም በውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር አማካኝነት በዕቅድ ዘመኑ ለ250,000 ሄክታርና በ280,385 ሄክታር መሬት በቅደም ተከተል የመስኖ ልማት የጥናትና ዲዛይንና የግንባታ ሥራዎችን ለማከናወን፣ በስኳር ኮርፖሬሽን አማካኝነት በትግራይ፣በአማራ፣በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች 343,308 ሄክታር መሬት የሚሸፍን የሸንኮራ አገዳ ልማት የመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማት ግንባታ ለማከናወን፣ በክልሎች አማካኝነት ደግሞ በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች 330,307 ሄክታር መሬት የሚሸፍን የሸንኮራ አገዳ ልማትና የመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማት ግንባታ ለማከናወን ግቦች ተጥለዋል፡፡

**በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ:** የምድር የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ዝርጋታን በተመለከተ አሁን ያሉትን 18 አዳዲስ የሣይኖፕቲክስ ጣቢያዎች ወደ 28 ለማድረስ፣ አሁን ያሉትን 188 ዐቢይ ጣቢያዎች ወደ 241 ለማድረስ፣ አሁን ያሉትን 556 3ኛ ደረጃ ጣቢያዎች ወደ 718 ለማድረስ፣ አሁን ያሉትን 424 4ኛ ደረጃ ጣቢያዎች ወደ 924 ለማድረስ ግቦች ተጥለዋል፡፡

በተመሳሳይ የከፍታ የአየር መረጃ መዝጋቢና ሌሎች ዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች መገንባትን በተመለከተ አሁን ያለውን 1 የከፍታ አየር ጣቢያ ቁጥር 3 ለማድረስ፣1 የነበረውን የአየር ብክለት ጣቢያ ቁጥር 2 ለማድረስ፣ 2 አዳዲስ የራዳር ጣቢያዎችን ለመትከል፣ 1 የ GIS ፋሲሊቲ ላቦራቶሪ ለማቋቋም፣ 32 አዲስ Lightning Detection Network ለማቋቋም፣ 1 አዲስ Aircraft Meteorolojical Data Relay (AMDAR) ዝርጋታ ለማከናወን፣ 3 አዲስ የሜትሪዎሎጂ Research station ለማቋቋም፣ 29 አዲስ Spec. Agromet ለመትከል፣ 140 የነበረውን AWS ወደ 260 ለማሳደግ፣ 5 የነበረውን የአዉሮፕላን ጣቢያ ኤሌክትሮኒክስ ጣቢያዎች የAWOS/AVIMET/ SADIS ቁጥርወደ 11 ከፍ ለማድረግ ግቦች ተጥለዋል፡፡

የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች እና አጋዥ ቁሳቁሶች ምርትና ጥገና ማካሄድና ጥራት ያለዉ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰብን በተመለከተ አዲስ 2505 የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ አዉታሮችን (SMS/IVR) ለመዘርጋት፣ 90 ነበረውን የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ አዉታሮች (SSB Radio-25) ወደ 115 ከፍ

ለማድረግ፣ አዲስ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ አዉታሮች (GTS Communication-1) ለመዘርጋት ዕቅድ ተይዟል፡፡

የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎት ማከናወንን በተመለከተ በ24 ሰዓት ዉስጥ 2 ጊዜ የሚታደስ የአጭር ጊዜ የአየር ሁኔታ ትንበያን በማዘጋጀት እንዲሰጥ ለማድረግ፣ በየቀኑ የሚታደስ (update) የመካከለኛ ጊዜ የአየር ሁኔታ ትንበያን በማዘጋጀት እንዲሰራጭ ለማድረግ፣ በየቀኑ የሚታደስ ሆኖ ከ1-5 ቀናት የጊዜ ርዝማኔ ያለው የከተሞች የአየር ሁኔታ ትንበያ በማዘጋጀት ተጠቃሚዎችን ለማርካት እና አካባቢያዊ (Regional) የመካከለኛ ጊዜ የአየር ሁኔታ ትንበያ በሁለት አመት ውስጥ እንዲዘጋጅ ለማድረግ ግቦች ተቀምጠዋል፡፡

ለልማትና ለአቪዬሽን ሴክተር የሚቲዎሮሎጂ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ትንበያ አገልግሎቶች መስጠትን በተመለከተ አለም አቀፋዊና አህጉራዊ የትንበያ ሞዴሎችንና ውጤቶችን ወደ አካባቢያዊ ቦታዎች በመቀየር (Down Scaling) የትንበያን አቅም 100 በመቶ ማድረስ፣ የተሰጡ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ትንበያ አገልግሎቶችን ካለበት 100 ወደ 400 ከፍ ማድረግ፣ ለአርሶና አርብቶአደሩ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ተደራሽነት ካለበት 4000 ወደ 29600 ከፍ ማድረግ፣ በውሃና ኢነርጂ ዘርፍ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያንና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተደራሽነት ካለበት 500 ወደ 4938 ከፍ ማድረግ፣ በጤናው ዘርፍ የአገልግሎት ተደራሽነት ካለበት 1000 ወደ 9875 ከፍ ማድረግ፣ በአየር ሁኔታና ጠባይ፣ አየር ጠባይ ለውጥና አየር ጠባይ ብክለት ዘርፍ የተሠሩ ውጤታማ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን 20 ማድረስ የሚሉት ሌሎች ግቦች ሲሆኑ በተጨማሪም ለበረራ ደህንነት የተሰጠ የአቪዬሽን ሚቲዎሮጂ መረጃ ((METAR 85.2 በመቶ),(MET REPORT 0.6 በመቶ) AND (SYNOP 14.2 በመቶ) ካለበት 102800 ወደ 205800 ከፍ ማድረግ፣ ለአውሮፕላን አብራሪዎች የተሰጠ የበረራ ሰነድ (Flight Folder) ካለበት 164250 ወደ 328500 ከፍ ማድረግ፣ የከፍተኛ (SIGMET 50 በመቶ)ና ዝቅተኛ (AIRMET 50 በመቶ) በረራ መስመር መግለጫ ካለበት 730 ወደ 10950 ከፍ ማድረግ፣ የአዉሮፕላን ማረፊያ ማስጠንቀቅያ (AERODROME 50 በመቶ) እና (WINDSHEAR-Vertical and Horizontal 50 በመቶ) 600 ማድረስ የንዑስ ዘርፉ ግቦች ናቸው፡፡

**የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች፣** የዘርፉ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች በተመለከተ **ከመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ጋር በተያያዘ** ሁሉንም ባለድርሻ አካላት አቅም መገንባት እና የመጠጥ ዉሀና ፍሳሽ አገልግሎትን ስራ ከሚመለከታቸዉ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር ተቀናጅቶ መስራት፣ በውሃና ሳኒቴሽን የሴቶችንና የግሉን ሴክተር ተሳታፊነት ማረጋገጥ፣ ሴክተሩ ከአማካሪዎችና ኮንትራክተሮች ጋር የጀመረዉን መደበኛ የጋራ የዉይይት መድረክ አጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን የከተማ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎቶችና የውሃ ሳኒቴሽንና ሃይጂን ኮሚቴዎች የውሃ ተቋማትን አካባቢ መንከባከብና መልሶ ማቋቋም ስራ እንዲሰሩና በየወቅቱ የከርሰ ምድር ውሃ ያለበት ደረጃም እንዲመዘገብ የሚደርግበት ስርዓት የሚዘረጋ ይሆናል፡፡ **በከርሰ ምድር ውሃ፡** የአገር በቀልና የውጭ አማካሪ ድርጅቶች የከርሰምድር ውሃ አለኝታ ጥናት ስታንደርዶችን እንዲጠቀሙ ማገዝ፣ የከርሰምድር ውሃ መረጃን በመሰብሰብና በማጠናቀር ሂደት ውስጥ ክልሎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ፣ **በተፋሰስ ልማት** ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችሉ መርሀ ግብሮችን ማዘጋጀት የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ መፈራረም፣ በውሃ ሀብት በሁሉም የህግ ማዕቀፎች ላይ ለአስተዳደሪዎች፣ የዕቅድ እና ፖሊሲ አውጭዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች መስጠት ናቸው፡፡ **በመስኖ ልማት** ባለ ድርሻ አካላት ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉና በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የዲዛይን ግምገማ በዓለምዓቀፍ አማካሪ ድርጅቶች እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ የሀገር ውስጥ አማካሪና ተቋራጭ ድርጅቶች ከውጭ አማካሪና ተቋራጮች ድርጅቶች ጋር ተጣምረው የሚሰሩበትና ልምድ የሚቀስሙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

### ረ) ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ

**ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች፣** በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዘርፍ ዋና ዋናዎቹ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የትርንስፖርት አገልግሎት ቅልጥፍናን በማሳደግና የተቀናጀ የቅብብሎሽ ሥርዓት በመፍጠር የትራንስፖርት ወጪን ለመቀነስ እንዲሁም በትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት የግል ባለሃብቱን አቅም በመገንባት ጉልህ

ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ፣ በገጠር እያደገ የመጣውን ምርት ከዋና ዋና የገበያ ማዕከላት ጋር የሚኖራቸውን ቁርኝት ማረጋገጥ፣ የግብርናና የገጠር ኢኮኖሚ መሠረቱ የሠፋና ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆን ጥሬ ዕቃ ማቅረብ እንዲችል ከከተሞች ጋር ማስተሳሰር፣ የገጠር ቀበሌዎችንና ወረዳዎችን ከገበያ ማዕከላት ጋር እንዲመጋገቡ የሚያስችል የገጠር ትራንስፖርት ተደራሽነትን ማስፋፋት፣ በአገር ውስጥ የተገነቡት የደረቅ ወደብ አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ጥራት፣ ቅልጥፍናና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣ ለገቢና ወጪ ምርቶች የምንጠቀምባቸውን የትራንስፖርት ኮሪደሮች በቂ አቅም እንዲኖራቸው ደረጃቸውን ማሻሻል፣ ማስፋፋትና ማሳደግ፣ የአገሪቱ አሉታዊ መገለጫ የሆነውን የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ችግር መሠረታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ በዚህ ረገድ የመንገዶች ዲዛይን የትራፊክ ደህንነትን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፣ የትራንስፖርት ማኔጅመንት ሥርዓቱን በማሻሻል ቀልጣፋ የአገር አቋራጭ፣ የክልላዊና የከተማ ትራንስፖርትን በጥራትና በስፋት እንዲቀርብ ማድረግ፣ የመንገድ፣ የባቡር፣ የባህርና የአየር ትራንስፖርት ሥርዓትን በተቀናጀ ሁኔታ ማስፋፋት፣ የትራንስፖርት መሠረተ-ልማት ግንባታና አገልግሎት ማስፋፋት የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (Cross cutting issues) ያገናዘበ እንዲሆን ማድረግ ናቸው።

**ዋና ዋና ዓላማዎች፣** የትራስፖርት አቅርቦትና ተደራሽነትንና ጥራት ማሳደግ፣ በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት መቀነስ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶቻችንን የዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነትን የሚያሳድግ እንዲሆን ማስቻል፣ የልማታዊ ባለሀብቱን የኢንቨስትመንትና የንግድ እንቅስቃሴ በአስተማማኝ ሁኔታ የሚደግፍ እንዲሆን ማድረግ፣ የገቢና ወጪ ዕቃዎችን አጠቃላይ የትራንዚት ጊዜን እና ወጪ መቀነስ ዋና ዋናዎቹ የዘርፉ ዓላማዎች ናቸው።

**ዋና ዋና ግቦች፣** በዕቅዱ ዘመን በዘርፉ የተጣሉ ግቦች፣ በዓለም አቀፍ የሎጅስቲክስ የአፈፃፀም መለኪያ (Logistics Performance) ከ2.59 ወደ 3.07 ከፍ ማድረግ ወይም በዓለም የሀገሪቱን ደረጃ ከ104ኛ ወደ 57ኛ ማሻሻል፣የገቢ እና ወጪ ዕቃዎችን የትራንዚት ጊዜ በ50 በመቶ መቀነስ፣ የገቢ እቃዎች የባህር ወደብ ላይ አማካይ የቆይታ ጊዜን አሁን ካለበት 40 ቀናት ወደ 3 ቀናት ዝቅ ማድረግ፣ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የሚጓጓዘውን የሀገሪቱ የጀኔራል ካርጐ ሽፋንን በዕቅዱ መነሻ ዓመት ከነበረበት 30 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማድረስ፣ ከሀገሪቱ በኮንቴይነር ሊጓጓዝ የሚችል (containerzable cargo) የወጪ ጭነት በሀገር ውስጥ በኮንቴይነር አሽጐ መላክን ከ7 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማድረስ፣ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ደህንነትንና ሴፍቲን በ50 በመቶ በማሳደግ የካርቦን ልቀትን 10 በመቶ መቀነስ፣ አንድ የጭነት ተሽከርካሪ ዓመታዊ የኪ.ሜ ሽፋን በ2007 ከደረሰበት 99,900 በ2012 ወደ 121,000 ከፍ እንዲል ማድረግ፣ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ለማግኘት አማካይ የመጠበቂያ ጊዜን ከ30 ወደ 15 ደቂቃ ዝቅ ማድረግ፣ አንድ የአገር አቋራጭ አውቶቡስ ዓመታዊ የኪሜ ሽፋን ከ100,000 ወደ 105,000 ከፍ እንዲል ማድረግ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ በዓመት የተጓጓዙ ተሳፋሪዎች ብዛት በ2007 ከነበረበት 322 ሚሊዮን በ2012 ወደ 370 ሚሊዮን ከፍ እንዲል ማድረግ፣ በትራፊክ አደጋ ምክንያት በየ10,000 ተሽከርካሪ የሚደርሰውን የሞት አደጋ በዕቅዱ መነሻ ዓመት ከነበረበት 58 በ2012 ወደ 27 ዝቅ እንዲል ለማድረግ ግብ ተጥሏል።

ከአዲስ አበባ-ጅቡቲ በሚዘረጋው የባቡር መስመር በ2012 በዓመት ለ750,000 መንገደኞችና ለ7.5 ሚሊዮን ቶን ጭነት የትራንስፖርት አገልግሎት ይሠጣል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር የህዝብ ትራንዚት (LRT) አገልግሎት ይሰጣል። የግል ባለ ሀብቶች በባቡር ዘርፍ የልማት ፕሮግራም ላይ አዎንታዊ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል።

**የማስፈጸሚያ ስልቶች፣** የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ንዑስ ዘርፍ ማስፈጸሚያ ስልቶች የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ እና ወጪን ለመቀነስ የተለያዩ የአሠራር ስርዓቶችን በመዘርጋት የዘርፉ ባለሃብቶች በግል እና ከመንግሥት ጋር በመሆን በወደብ ልማት እንዲሳተፉ ማድረግ፤ የአገሪቱን የመንገድ ትራንስፖርት ፍላጎት ያገናዘበ የተሽከርካሪ አቅርቦት እንዲኖር ማድርግ፣ የእቃዎች የወደብ ላይ ቆይታን ማሳጠር፤ በውጭ የሚቀጠሩ የባህረኞችን ቁጥር ማሳደግ እና የሌሎች ሀገራትን መርከቦች ምዝገባ ማካሄድ፣ የሎጂስቲክስ ሥርዓቱ ሳይቆራረጥ ዘላቂ በሆነ መልኩ እየተገነባ እንዲሄድ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ (IT-based logistics service) እንዲሆን ማድረግ፣ በዘርፉ ችግር ፈቺ የሆኑ ምርምሮች፣ ጥናቶችና ሥልጠናዎችን ማድረግ፣ በዘርፉ የተሰማሩ ኦፐሬተሮችና ተቋማት በዕውቀት ላይ የተመሰረተ አገልግሎት እንዲሰጡ

ማድረግ፣ የዘርፉን ሬጉላቶሪ ተቋም በዕውቀት እንዲዳብር የሚያስችል የሎጅስቲክስ ኤክሴለንሲ ማዕከል ማደራጀት፣ በሀገር ውስጥ የሎጂስቲክ ማዕከላትን ማጠናከር እና ማስፋፋት እንዲሁም የሎጂስቲክስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (logistics service providers) አቅምን ማጠናከር የሚሉት ማስፈጸሚያ ስልቶች ይገኙበታል::

በተጨማሪ ዘርፉን በባለቤትነት የሚመራ ተቋማዊ አቅም እንዲኖርና በዋናነት የሃገሪቱን ማናቸውም የሎጂስቲክስ ጉዳዮች በማስተባበር የሚፈጽም አገናኝ ተቋም በመሆን የሚያገለግል ብሄራዊ የሎጅስቲክስ የቅንጅት ካውንስል (Ethiopian National Logistics Coordination council - ENALCO) ማቋቋምና የህግ ማዕቀፍ እንዲኖረው ማድረግ፣ የሎጂስቲክስ ስትራቴጂውን በብቃት ማስፈፀም እንዲቻል በዘርፉ ዕውቀትና ሙያ ያላቸውን ኤክስፐርቶች ያሰባሰበ የሥራ ክፍል የሎጂስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ቢሮ /LTO/ ማቋቋም፣ የተሻሻለ የንግድ ስርዓት /trade finance/ መዘርጋት፣ የተቀላጠፈ የኮሪደር ፋሲሊቲ እና ዘመናዊ የትራንዚት ትራንስፖርት ስርዓት መዘርጋት፣ ጠንካራ የሎጂስቲክስ መሰረተ ልማት ማሟላት፣ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ሥርዓት መገንባት፣ የኮንቴነራይዜሽን አሠራርን ማጎልበት እና የመርከብ ምዝገባ ፖሊሲን ተግባራዊ ማድረግ፣ በየደረጃው የሚገኝ የፖለቲካ አመራር የመንገድ ትራፊክ ደህንነት አጀንዳ እንዲሆን ማድረግ፣ የመንገድ የትራንስፖርት ሕግ አከባበርን ለማሳደግ ከትራፊክ ፖሊስ ጋር በቅንጅት መስራት ከባለድርሻ አካላት /ሕዝብ ክንፍ/ ጋር ያለውን ቋሚ መድረክ አጠናክሮ መቀጠል፣ የፌዴራልና የክልል ትራንስፖርት ተቋማትን ቅንጅት በአደረጃጀትና አሠራር ማሳደግ፣ የአውቶቡስ የትራንዚት አገልግሎት አሠራር በማስፋፋት የአገሪቱን ዋና ዋና ከተሞች በቀጥታ በትራንስፖርት የሚተሳሰሩበትን ሥርዓት መዘርጋት፣ ከፍተኛ የመጫን አቅም ያላቸው ተሽከርካሪዎች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

## ሰ) አቪዬሽን

**ዋና ዋና የትኩረት መስኮች፣** በዕቅዱ ዘመን የኤርፖርት መሠረተ ልማትን የማስፋፊያና የአዳዲስ ኤርፖርቶችን ግንባታ በሚፈለገው ስታንዳርድ ማዘጋጀት እና ማስተዳደር፣ አለም አቀፉ ሲቪል አቬሽን ተቋም የወጣውን ስታንዳርድ ያሟላ የአውሮፕላን አደጋን መጠን መቀነስ እና የዓለም አቀፉ ሲቪል አቪዬሽን ባወጣቸው /USOAP/ መስፈርቶች መሠረት የተቀመጡ ስታንዳርዶችን በሙሉ ማሟላት፣ የአየር ትራንስፖርቱ በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ምርቶች ምልልስ ላይ ያለውን ድርሻ ማሳደግ፣ተወዳዳሪ የሆነ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎትን ማስፋፋት፣ በቂ የውጭ ምንዛሪ ክምችትን ሊፈጥር እንዲችል ማድረግና፣ ለቱሪዝም ዘርፍ እድገት የሚያበረክተውን ድርሻ ማሳደግ ዋና ዋናዎቹ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

**የዘርፉ ዋና ዋና ዓላማዎች፣** የአየር ትራንስፖርት የበረራ ደህንነትና ጸጥታ (Aviation Safety and Security) ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ማስቻል፣ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎትን ተቋማዊ አቅም መገንባት፣ ብቃትና ተወዳዳሪነት ያለው የአየር ትራንስፖርት አገልግሎትን መስጠት እና የአየር ትራንስፖርት አገልግሎትን ተደራሽነት ማስፋት ናቸው፡፡

**ዋና ዋና ግቦች፣** በአለም አቀፉ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት እንዲሟሉ የሚጠበቁ የሴፍቲና ሴኩሪቲ ጉድለቶች የተሟሉበት ደረጃ መጣኔን በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 95 በመቶ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 100 በመቶ ከፍ ማድረግ፣ የገቢ መንገደኞችን የማስተናገጃ ጊዜን በ2012 ወደ 60 ደቂቃ እንዲሁም የወጪ መንገደኞችን ለማስተናገድ የሚወስደውን ጊዜ ወደ 45 ደቂቃ ዝቅ ማድረግ፣ በ2007 በጀት ዓመት የነበረውን አምስት ሚሊዮን ዓመታዊ የመንገደኞችን የማስተናገድ አቅም ወደ 18 ሚሊዮን ከፍ ማድረግ፣ በዕቅዱ መነሻ ዓመት የነበሩትን 20 የኤርፖርቶች በ2012 ወደ 25 ከፍ ማድረግ፣ በ2007 የነበረውን በየ10 ሺህ በረራ 3 የአደጋ አጋጣሚዎች ክስተት (nearmiss) መጠን በ2012 ወደ 1 ዝቅ ማድረግ ናቸው፡፡ የአውሮፕላኖችን ቁጥር በ2012 ወደ 113 ማድረስ፣ የአገር ውሰጥ መንገደኞች ቁጥርን በ2012 2.6 ሚሊዮን ማድረስ፣የዓለምአቀፍ መንገደኞች ቁጥርን በ2012 9.4 ሚሊዮን ማድረስ፣ የጭነት/Cargo/ አገልግሎትን በ2012 503.7 ሺህ ቶን ማድረስ፣ ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ በ2012 5.1 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማድረስ፣ የወጪ ንግድ ምርቶችን ለመደገፍ እንዲቻል በክልል ኤርፖርቶች ያሉትን ቀዝቃዛ መጋዘኖች ቁጥር ከ2 ወደ 3 ከፍ እንዲል ማድረግ፣ የአደጋ አጋጣሚ መጠንን በየ10 ሺህ በረራ 0.5 ማድረስ፣

የመንገደኛ መቀመጫ አቅርቦትን በቢሊዮን ኪ.ሜ በዕቅዱ መነሻ ዓመት ከነበረበት 30.1 ወደ 68፣ አለም አቀፍ የበረራ ጣቢያዎችን ብዛት ከ81 ወደ 127 እና የተጓዡ የዓለም አቀፍ መንገደኞች ብዛት በ2007 ከነበረበት 4.5 ሚሊዮን በ2012 ወደ 11.3 ሚሊዮን ማሳደግ ዋና ዋናዎቹ የዘርፉ ግቦች ናቸው፡፡

**የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች፣** የዘርፉ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች በተመለከተ የአውሮፕላን አደጋ ምርመራ ውጤትን መሠረት ያደረገ የአደጋ መከላከያ ሥራ ማከናወን፣ከኤርፖርት አገልግሎት ባለድርሻ አካላት ጋር ቀጣይነት ያለው  የተቀናጀ አሠራር ስርዓት እና በሁሉም ኤርፖርቶች የአቪዬሽን ደህንነት ሥራ-አመራር ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ፣ ኤርፖርቶች በ/ICAO/ መስፈርትና ተመራጭ አሠራሮችን /SARPS/ የተከተሉ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ኤርፖርት ሴኩሪቲና ፋሲሊቴሽን ኦዲትና ኢንስፔክሽን ሥራዎችን አጠናክሮ ማከናወን፣ የኤርፖርት ደረጃ ምደባ (Clasification) ጥናት ትግበራ ማካሄድ፣ በሁሉም አገልግሎት መስጫ ኤርፖርቶች የደህንነት አመራር ሥርዓት (Safety Management System) ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግና የተፈላጊውን የኤሮድሮም መስፈርት እንዲያሟሉ ማድረግ፣ የአውሮፕላንና የመንገደኞች እንቅስቃሴን ለማስተናገድ የሚያስችል አሠራር ስርዓት በመዘርጋት የመፈጸም አቅምን መገንባት፣ የግል አየር ትራንስፖርት አንቀሳቃሾችን (ኦፕሬተሮችን) ተሳትፎ ማሳደግ፣ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር፣ የአየር አገልግሎት ስምምነት መደራደሪያ ሃገራዊ ሰነድ / BASA Manual/ ዝግጅትና ትግበራ ማከናወን እና የአየር ትራንስፖርት ፖሊሲን/Air Transport Policy/ መተግበር ናቸው፡፡

### 3.1.5 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት

#### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

በዕቅድ ዘመኑ በንዑስ ዘርፉ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትንና ተግባርን በማዳከም፣ የኮንስትራክሽን የፕሮጀክት ግንባታ ወጪን ከ15 እስከ 20 በመቶ ዝቅ እንዲል ማድረግ፣ የካይዘንና የዘመናዊ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅሜንት ስርዓቶችን አቀናጅቶ መፈጸም፣ የሕንጻ መረጃ ሞዴል (Building Information Modeling (BIM)) እንደ ለውጥ መሳሪያ መጠቀም በዚህም የBIM ተጓዳኝ መሳሪያዎችና የካይዘን ፍልስፍና ተደጋግፈው በዘርፉ የላቀ ውጤት እንዲያስገኙ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ ሁሉንም የግንባታ ፕሮግራሞች የአቅም ግንባታ ማዕከል ማድረግ፣ ከዚህ አንፃር በኮንስትራክሽን ሥራ ላይ በላቀ ደረጃ የሚሳተፉ የኢንዱስትሪው ተዋንያኖች ፣የሙያ ፣የስራ ተቋራጭና አማካሪ የፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት ማሻሻል እና የዘርፉ ማህበራትም  በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚኖራቸው ተሳትፎ የማጎልበትና ከልማቱ ትይዩ የዘርፉን የማስፈፀም አቅም መገንባት ላይ ትኩረት ያደረገ የአፈፃፀም አቅጣጫ እንዲከተሉ ማድረግና በሁሉም ፈፃሚና አስፈፅሚ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በየደረጃው የሚታቀዱ የግንባታ ዕቅዶች ሀገራዊ ምህንድስናና ኮንስትራክሽን አቅም የምንፈጥርባቸውና በቀጣይነት ዘርፉ የሚጠናከርበት የክህሎትና ዕውቀት ማዕከል እንዲሆን ማድረግ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡

#### 2. ዓላማዎች

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን የማስፈፀም አቅም በማያቋርጥ ሁኔታ መገንባት፣ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ቀልጣፋና ውጤታማ የኮንስትራክሽን (አገልግሉትና ስራ) ግዥ እና ኮንትራት አስተዳደር አቅም መጎልበቱን value for money መገኘቱን ማረጋገጥ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪነት ብቃታቸውን ያጎለበቱ ሀገር በቀል የግንባታ ስራ ተቋራጮችና የዲዛይንና የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት አማካሪዎች እንዲለሙ ማድረግ፣ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ሁሉን አቀፍ የማስፈጸም አቅም ክፍተቶችን መሙላት፣ በዘርፉ የተወዳዳሪነት አቅምን ለመገንባት የሚያስችል (labor productivity rates, labor, material & equipment indexes)፣ የፕሮጀክት መረጃ፣ የፈቃድና የሬጉላቶሪ ሥርዓት ማስፈን፣ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በዕዉቀቱ፣በስነ-ምግባሩና በክህሎቱ ያደገና የበቃ የሰው ሃይል ስምሪት እንዲኖር ማድረግ፣ የሚታየውን የሙያ እጥረትና ስብጥር ከሚያስፈልገው መጠን ጋር ማመጣጠን፣ በአከባቢ እና በግንባታ ሂደት ለጤንነትና ደህንነት ትኩረት እና ምላሽ የሚሰጥ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መገንባቱን ማረጋገጥ፡፡
በሌላ በኩል በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የተሰማሩ አካላት የከተማ ልማት፣ቤቶች፣እንዲሁም፣ ኮንስትራክሽን አስፈጻሚ ባለቤቶች፣ የመሠረተ ልማት ተቋማት፣ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪ ድርጅቶችንና

የሙያ ማህበራት፣ የፋይናንስና ኢንሹራንስ ተቋማት በመደጋገፍ በቅንጅት የሚሰሩበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ የአገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪ ድርጅቶች፣ የግብዓት አቅራቢዎችና አምራቾች ለሥራ የሚያስፈልጋቸውን መሣሪያዎችና ማሽነሪዎች አቅርቦት አቅም ማጎልበት፣ በሀገሪቱ የኮንስትራክሽን ግብዓትና መሳሪያዎችን በራስ አቅም በማምረትና በማቅረብ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን አቅም መገንባትና የውጭ ምንዛሪ ጫናን መቀነስ፣ በጥናትና በምርምር ላይ በመመስረት በአለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ የአገነባብ ቴክኖሎጂዎችንና ዘዴዎችን ማስፋፋት እና የኢንዱስትሪውን አገልግሎቶች ጥራት ያላቸው፣ ወጪ እና ጊዜ ቆጣቢ እንዲሆኑ ማድረግ የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የንዑስ ዘርፉ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው፡፡

## 3. ዋና ዋና ግቦች

### 3.1 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አመራር አደረጃጀትና አሠራር ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አመራር አደረጃጀትና አሠራር ማሻሻልን በተመለከተ ዘመናዊና አለም አቀፍ ተወዳዳሪነቱን የጠበቀ የአርክቴክቸራል፣ የኢንጂነሪንግ፣ የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት እና የኮንትራት አስተዳደር አቅም ሙሉ በሙሉ መገንባት፣ የሥራ ተቋራጮችና የአማካሪ ኩባኒያዎች ልማትን በተመለከተ ከ70 በመቶ በላይ የሚሆነውን የግንባታ ፍላጎት በሀገር በቀል የኮንስትራክሽን ግንባታና የአማካሪ ኩባኒያዎች እንዲሸፈን ማድረግና ኤክስፖርት ስታንዳርድ ደረጃ ላይ ማድረስ፣ የንዑስ ዘርፉን ወሳኝ የቁጥጥር ተቋማዊ አቅምን ከመገንባትና ከመደገፍ ጋር በተያያዘ የንዑስ ዘርፉ፤ ተዋናዮች የሚታይባቸውን የማስፈጸም አቅም ውስንነት በመቅረፍ ተወዳዳሪነታቸውንና አፈጻጸማቸውን የማሻሻል ግብ ተጥሏል፡፡

### 3.2 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ምዝገባ፣ ተወዳዳሪነት ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም

በግልጽ የአፈጻጸምና ብቃት መለኪያዎች ያለፉ ሀገር በቀል የአርክቴክቸራል፣ የኢንጂነሪንግና የኮንስትራክሽን ማኔጀመንት ኩባኒያዎችን ቁጥር በብዛትና በጥራት ማሳደግ፣ በሌላ በኩል የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን የሠው ኃይል በተለይ የምህንድስና፣ የአርክቴክቸርና የኮንስትራክሽን ባለሙያዎችን ስነ-ምግባር፣ ክህሎት እና ብቃት ለማሻሻል በኢንዱስትሪው የሚፈለገውን ባለሙያ በመጠን፣ በዓይነትና በጥራት በማፍራት ለግንባታ ሥራዎች ጥራት፣ ወጪ እና ጊዜ ደረጃውን የጠበቀ የሙያ አገልግሎት የሚሰጥበት ደረጃ ላይ ማድረስ፣ የኮንስትራክሽን ሠራተኞች ጤንነት እና የተፈጥሮ አካባቢ ደህንነት ጥበቃን በተመለከተ በዕቅድ ዘመኑ ሀገር በቀል የኮንስትራክሽን ኩባንያዎቻችን ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የኮንስትራክሽን ሰራተኞች እና የተፈጥሮ አካባቢ አጠባበቅ ስርዓት እንዲተገብሩ የማድረግ ግብ ተጥሏል፡፡ የመንግስትና የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት ከማጠናከር አንጻር የተጠናከረና ሁሌም በመሻሻል የሚጓዝ እና የዳበረ ሀገራዊ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ይገነባል፡፡

### 3.3 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የግብዓት፣ የመሣሪያ፣ የቴክኖሎጂ፣ የፋይናንስና ኢንሹራንስ አቅርቦት አቅም ግንባታ ድጋፍ ፕሮግራም

የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች አቅርቦት፣ የአማካሪዎችና ስራ ተቋራጮችን፣ አቅም ግንባታን በተመለከተ አስፈላጊውን የፋይናንስ፣ የኢንሹራንስ፣ የመሳሪያና የቴክኖሎጂ አቅርቦት ድጋፍን በማመቻቸት ሀገር በቀል ኩባኒያዎቻችን በኮንስትራክሽንና ዲዛይን ዘርፍ ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ መስራት፣ የኮንስትራክሽን ግብዓት፣ አቅርቦትና ማምረቻ ተቋማትን ከማስፋፋት አንጻር ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታና ለዘርፉ ተወዳዳሪነት ወሳኝ በሆኑ የስሚንቶና ብረት ነክ እንዲሁም ፕላስቲክና ኮንስትራክሽን ነክ ኬሚካል አምራች ኩባኒያዎች አቅም እንዲጎለብት የማድረግ ግብ ተጥሏል፡፡

### 3.4 የሀገራዊ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅሜንት አቅም ግንባታ ፕሮግራም

የኢንዱስትሪውን ልማት ለማሳደግ ከከፍተኛ ትምህርት፤ ተመሳሳይ ተልዕኮ ፈጻሚ ከሆኑ (የሀገር ውስጥና ውጭ) ተቋማትና እንዲሁም ከሙያ ማህበራት ጋር በመተባበር በግንባታ ዕቃዎች፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር፤ በአማራጭ ዲዛይኖች እና በመሳሪያዎች አቅርቦት እና በአገነባብ ዘዴዎች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግና የተግባር ሥልጠና በመስጠት በምዘና ስርዓት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት መስጠት የፕሮግራሙ ዋና ዋና ግቦች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት የተሻሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምን በተመለከተ የግንባታ ኢንዱስትሪው የቴክኖሎጂ መጠቀም አቅሙን በማሳደግ ምርታማነቱንና ቅልጥፍናውን የማሳደግና ከሀገሪቱ የመንገድ፣ የባቡር፣ የህንጻ፣ የመስኖ፣የኃይል፣ የንጹህ ውሃ፣ የፍሳሽ ቆሻሻ መሰረተ ልማቶችና መሰል የሲቪል ስራዎች ግንባታ ፍላጎት ዕድገት ጋር ተያይዞ እየመጡ ያሉ አዳዲስና ውስብስብ ፕሮጀክቶችን ለመፈጸም የሚያስችል የፕሮጀክት ትግበራ ስልቶችን በመንደፍ የማስተዋወቅና የዘመናዊ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅሜንት አቅም ማጎልበት ግብ ተጥሏል፡፡

## 4. የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

የኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍን ዕቅድ ለማስፈጸም አራት ፕሮግራሞች የሚኖሩ ሲሆን እነዚህም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አመራር አደረጃጀትና አሠራር ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ምዝገባ፣ ተወዳዳሪነት ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የግብዓት አቅርቦት፣ መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ድጋፍ ፕሮግራም እና የሀገራዊ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅሜንት አቅም ግንባታ ፕሮግራም ናቸው፡፡

### 4.1 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አመራር አደረጃጀትና አሠራር ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የማስፈጸሚያ ፖሊሲ ህግና አሠራር ሥርዓትን በተመለከተ፡ በሀገሪቱ ኮንስትራክሽን የምቶት፣ የደህንነትና የጤና አጠባበቅ ሂደቶች፣ የኮንስትራክሽን ጨረታ፣ ውለታ፣ ዋስትና፣ ግጭት አፈታትና ይግባኝ ሥርዓቶች እንዲሁም በውስጡ የሚሳተፉ አካላት የሚመሩበት የዲዛይን፣ የግንባታ፣ የምክር፣ የቁጥጥር እና የማኔጅመንት ሁኔታዎችን የያዘ የኮንስትራክሽን ህግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ ለመንገድ፣ ለባቡር ፣ ለህንጻ ፣ለመስኖ፣ ለኃይል ፣ ለንጹህ ውሃ ፣ ለፍሳሽ ቆሻሻ መሰረተ ልማቶችና መሰል የሲቪል ስራዎች ዲዛይኖችና ግንባታዎች ደንቦች፣ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች እንዲዘጋጁና ለሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲዳረስ እንዲሁም ተግባራዊነታቸው እንዲረጋገጥ የሚያደርግ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ በጥናትና ምርምር የሚገኙ አዳዲስና የተሻሻሉ አማራጭ የግንባታ ቴክኖሎጂዎችና የአገነባብ ዘዴዎች ስታንዳርድ እንዲወጣላቸው ይደረጋል፡፡

የሥራ ተቋራጮችን አቅም ለመገንባት ፕሮጀክቶችን በንኡስ በመክፈል ወደ አብዛኛው ሥራ ተቋራጭ አቅም ማምጣት እና የመግቢያ መስፈርቶችን ለማመጣጠን የሚያስችል ማሻሻያ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የሽሙር (joint venture) አሰራርን ጨምሮ ሌሎች ከኮንስትራክሽን ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አሰራሮች እና ህጎች በመከለስ ማስተካከያ ይደረጋል፡፡ አንድ ተቋራጭ ሊይዘው የሚገባው የፕሮጀክት መጠን ካለው አቅም ጋር እንዲመጣጠን በማድረግ ያልተመጣጠኑ ፕሮጀክቶችን ከመያዝ ጋር የተገናኙ የአፈፃፀም ችግሮች ለመቀነስ የአገራችን ሥራ ተቋራጮች ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸማቸው (annual turnover) ለማሻሻል ትላልቅ እና በርካታ ፕሮጀክቶችን (on the basis of multi-layered subcontracting approach) እንዲያገኙ በማድረግ አካሄዱም ከድርጅቶቹ ውስጣዊ ጥንካሬ እና ከተመጣጠነ ውድድር ጋር እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በመንገድ፣ በህንጻ፣ በመስኖ፣ በኃይል ማመንጫና በባቡር መሠረተ ልማት ግንባታዎች የፕሮጀክት አስተዳደር ባለሙያዎች በብዛት እንዲፈጠሩ የኮንስትራክሽን አመራር ማብቃት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

በየሴክተሩና በማዘጋጃ ቤቶች የሚገኙ ባለሙያዎች፣ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የተሰማሩ የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለድርሻ አካላት ምዝገባ ምቹ፣ ቀልጣፋና በሙያ ምዘና የሚያልፉበት ሥርዓት

ይዘረጋል። የኮንስትራክሽን ሥራዎችን በጥራት፣ በጊዜ፣ በወጪ፣ በምቾት እንዲሁም በደህንነት በኩል ደረጃቸውን የሚያስጠብቅና በሚፈለገው ደረጃ መፈፀማቸውን የሚያረጋግጥ የመቆጣጠሪያ ሥርዓት ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል። የአማካሪዎች የአገልግሎት ክፍያ በውጤትና በፕሮጀክት አፈጻጸም መሰረት እንዲሆን ይደረጋል፣ በመጨረሻም የተሟሉና ወቅታዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መረጃዎች በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲሰባሰቡ ይደረጋል።

የአርክቴክቸራል፣ ኢንጂነሪንግ፣ የኮንስትራክሽን ማኔጀመንት እና የኮንትራት አስተዳደርን በተመለከተ፡ በከፍተኛ የግንባታ ዲዛይን ሥራ ላይ መሳተፍ የሚችሉ 10 ዓለም አቀፍ ተውዳዳሪነት አቅም ያላቸው የዲዛይን ኩባንያዎች እንዲቋቋሙ የደረጋል። የዲዛይን ኩባንያዎችን አቅም በፋይናንስ፣ በቴክኒክ፣ በቴክኖሎጂ እና በአሠራር የሚያጠናክር1ና ለሚዘጋጁ ዲዛይኖች ዕውቅና የሚሰጥ አንድ መንግስታዊ ተቋም እንዲደራጅ ይደረጋል። በተመሳሳይ የሚዘጋጁ ዲዛይኖችን መርምሮ ብቁ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ በአገር አቀፍ ደረጃ አንድ የከፍተኛ ባለሙያዎች ቡድን እንዲቋቋም ይደረጋል። የዲዛይን ኩባንያዎች በሚያዘጋጇቸው ዲዛይኖች ያለባቸውን ሃላፊነትና ተጠያቂነት የሚወስን አንድ የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ይውላል። በሌላ በኩል አገራዊ ፋይዳ ባላቸው ትላልቅ ፕሮጀክቶች (ሃይድሮ ፓወር፣ የሃይል ማስተላለፊያ ታወሮች፣ የባቡር ሐዲድ መስመር ዝርጋታ፣ የመንገድ ግንባታ) ላይ የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች የተሳትፎ ዕድል እንዲሰፋ የሚያረጋግጡ የግንባታ ግዢ የመወዳደሪያ መስፈርቶች እንዲሻሻሉ እና በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪ ድርጅቶች እርስ በርሳቸው እንዲሁም ከውጭ አቻዎቻቸው የአሠራር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ የሚያስችላቸው (Joint Venture) ሥርዓት ተቀርፆ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል። በተጨማሪም የኮንስትራክሽን ኮንትራት አስተዳደር እና የግንባታ ግዢ ሥራዎችን የሚመራ፣ የሚያስተዳደርና የሚያስተባብር መንግስታዊ ተቋም ይቋቋማል። የህንጻ ኮድ ተግባራዊ ለማድረግ አጋዥ የሆኑ 10 ተጨማሪ ስታንዳርዶች እና ዘመናዊ አገልግሎት መስጫ ቴክኖሎጂዎች ተዘጋጅተው ስራ ላይ እንዲውሉ ያደረጋል። በማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ መሠረት የሕንፃ አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያው ተግባራዊ በሚሆንባቸው 200 አዳዲስ ከተሞች አደረጃጀት እንዲፈጠርና የሰው ሃይል መዋቅር እንዲዘረጋ ለክልሎች ድጋፍና እገዛ ይደረጋል፣ አፈፃፀሙም በክትትልና ሪፖርት ይረጋገጣል። ሥራ ተቋራጮች በኮንትራት የሚይዟቸውን የግንባታ ውሎች በገበያ ዋጋ፣ የጥራት ደረጃ እና ጊዜ ገደብ ማስረከብ የሚችሉበት እና ካልቻሉም ተጠያቂ የሚሆኑበት የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል። በህንጻ ግንባታ ስራዎች እና አገልግሎት የምርታማነት እና ጥራት ቁጥጥር እና የፕሮጀክት አስተዳደር ምርጥ ልምድ የመቀመር እና በ100 ከተሞች የማስፋት ስራ ይከናወናል።

የሥራ ተቋራጮችና የአማካሪ ኩባኒያዎች ልማትን በተመለከተ በመካከለኛ ደረጃ አዳዲስ የስራ ተቋራጮችንና አማካሪዎችን በማቋቋም፣ መካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ ያሉ ነባር የሥራ ተቋራጮችንና አማካሪዎችን ደረጃ በማሳደግ የአገር ውስጥ የሥራ ተቋራጮችን ቁጥር በ2007 ካለበት ቢያንስ በ2000 እንዲያድግ እና አቅማቸው በየጊዜው እንዲያድግ ይደረጋል። በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች የልማታዊ ባለሃብት፣ ዘመናዊ የኮንስትራክሽን አመራርና አደረጃጀት እንዲኖራቸው ስልጠና ይሰጣል። በምክር አገልግሎት ዘርፍ የምህንድስና የትምህርት ክፍሎች ያሏቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ምሩቃኖቻቸውን ከሚቀበሉ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ጋር ስምምነት በማድረግ በምርምር ሥራዎች፣ በአዋጪነት ጥናቶች፣ እና በዲዛይን ሥራዎች ላይ በመሣተፍ ዘርፉን አግዘው የተቋማቸውን አቅም እንዲገነቡ ይደረጋል።

የንዑስ ዘርፉን ወሳኝ የቁጥጥርና ተቋማዊ አቅም ግንባታ ድጋፍን በተመለከተ፤ በፕሮግራም ዘመኑ ለሚገነቡ ግዙፍ እና ከፍተኛ ቴክኖሎጂ ለሚጠይቁ ፕሮጀክቶች በፌዴራል ደረጃ አንድ የሲቪል ኢንጂነሪንግ የጥናት እና ዲዛይን ማዕከል እንዲቋቋም ይደረጋል። ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ግብዓቶችን የሚያመርቱ 50 ድርጅቶችን በመለየትና በቴክኖሎጂ እንዲደገፉ በማድረግ የግንባታ ዕቃዎች በሚፈለገው መጠን፣ ዓይነትና

ጥራት በአገር ውስጥ የሚመረትበት አቅም ይፈጠራል፣ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የግንባታ ግብዓቶች የጥራት መፈተሻ ላቦራቶሪዎች እንዲቋቋሙ ይደረጋል፣ የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶችን ማዕከል በማድረግ የምህድስና ፋኩልቲ ያላቸው ዩኒቨርሲቲዎች በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጥናት፣ ዲዛይንና ማማከር አገልግሎት እንዲሳተፉ በማድረግ የቴክኖሎጂ አቅም እንዲዳብር ይደረጋል እንዲሁም በአካባቢ የግንባታ ግብዓቶች ላይም የምርምርና ስርፀት ሥራ ይከናወናል፡፡

## 4.2 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ምዝገባ፣ ተወዳዳሪነት ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም

የሥራ ተቋራጮችን እና አማካሪ ድርጅቶችን የማስፈፀም አቅም በመገንባት የአገር ውስጥ የግንባታ ፍላጎትን እንዲያሟሉ እንዲሁም ምርትና አገልግሎታቸው ኤክስፓርት ስታንዳርድ እንዲሆንና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚሆኑበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ የባለሙያዎች፣ አማካሪዎች፣ ተቋራጮች እና የግንባታ ግብዓት አቅራቢዎችን ብቃት ለማረጋገጥ የሚያስችልና የባለሙያዎችን መብትና ግዴታ እንዲሁም ግልጽነትና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ አኳኋን የተዘጋጀው የምዝገባ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ በሥራ ላይ ያለው የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባ አዋጅ ከንዑስ ዘርፉ ዕድገት ጋር እንዲጣጣምና የመሣሪያዎችን ብቃት፣ ጥራትና ደረጃ በሚወስን መልኩ እንዲሻሻል ይደረጋል፣ ማስፈፃሚያ ደንብና መመሪያም ይዘጋጅለታል፡፡ የመሣሪያዎች ብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶችን በማሻሻል በአገር ውስጥ የሚመረቱ እና ከውጭ የሚገቡ መካከለኛ እና ቀላል የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች በምዝገባ ሥርዓቱ ውስጥ በአቻ ግምት እንዲካተቱ እና በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የፕሮጀክት አገልግሎት አሠጣጥ አማራጮችን ያገናዘበ 100 ፐርሰንት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የምዝገባ ስርዓት ይዘረጋል፡፡

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሠው ኃይል፣ የአርክቴክቸራል፣ የኢንጂነሪንግና የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ባለሙያዎች ስነ-ምግባር፣ ክህሎት እና ብቃት ማሻሻያን በተመለከተ በሠራተኞችና በሙያ ማህበራት እና በመንግስት መካከል በሚደረጉ የህብረት ስምምነቶች የክህሎት ስልጠና የሚሰጥበት እና የክፍያ ተመጣጣኝነት የማረጋገጥበት የአሠራር ሥርዓት ይዘጋጃል፡፡ ያለንን ውሱን የሰለጠነ የሰው ኃይል በበለጠ ውጤታማነት ለመጠቀም በልዩ ልዩ ተቋማት ተቀጣሪነት የሚሰሩ እና ጥሩ የስራ አፈፃፀም ያላቸውን ባለሙያዎችን በማደራጀት፣ የአቅም ግንባታ ድጋፍ እና መነሻ የሥራ ትስስር በማድረግ መጠቀም እንደ አማራጭ ተወስዶ ይፈጸማል፣ እንዲሁም ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በቅንጅት በመስራት የተጀመረውን የምህንድስና/ ኢንጂነሪንግና የኮንስትራክሽን ማኔጀመንት ሥልጠና ተጠናክሮ እንዲቀጥል የማድረግ ስራዎች ይሰራሉ፡፡

የሕንፃ ዘርፍ ባለሙያዎች ክህሎት እና አመለካከት ማሻሻልን በተመለከተ፤ በህንጻ ዘርፍ የተሰማሩ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ መለስተኛና አነስተኛ ባለሙያዎች መረጃ በየዓመቱ ተለይቶ እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡ በምዘና፣ በምዝገባ እና በሥልጠና ሂደት የሴቶች ተሳትፎ መጠን እንዲጨምር እና ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡ የኮንስትራክሽን ሠራተኞች ጤንነት፣ የተፈጥሮ አካባቢ እና ደህንነት ጥበቃን በተመለከተ፤ ከዲዛይንና ግንባታ ሂደቶች ጀምሮ በኮንስትራክሽን የሥራ ቦታዎች ላይ የሠራተኛውን ደህንነትና ጤንነት ማስጠበቅ የሚያስችል አንድ አስገዳጅ ሕግ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ የሠራተኛውን ደህንነት መጠበቂያ እና መከላከያ አልባሳትና መሣሪያዎች አቅርቦትን የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች እንዲያሟሉ ይደረጋል፡፡ የሚገነቡ የግንባታ ውጤቶች ከዲዛይን ጀምሮ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እና ተደራሽ እንዲሆኑና እኩል አገልግሎት የሚሰጡበት አስገዳጅ ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፣ የግንባታ ፕሮጀክቶች ሲጠኑ የተፈጥሮና አካባቢ ተፅዕኖን ግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን አስገዳጅ የህግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ይውላል፡፡ የመንግስትና የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ አጋርነት ከማጎልበት አንጻር፤ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አስፈጻሚዎችና ተዋናዮች የስነ ምግባር ደንብ በማዘጋጀት በዘርፉ የተደራጁ የሙያ ማኅበራት ለዘርፉ የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ እንዲያሳድጉ ይደረጋል፡፡ የመንግስትን አወቃቀር እና አሰራር እንዲሁም የኢንዱስትሪዉን አወቃቀርንና ተዋንያኖች ከግምት ያስገባ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ

ምክር ቤት (Construction Industry Council) እንዲቋቋም ይደረጋል፣ እንዲሁም የሀገር ውስጥ የሙያ ማህበራት ከውጭ አቻዎቻቸው ጋር የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበት ምቹ ሁኔታ እንዲመቻች ይደረጋል።

## 4.3 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የግብዓት አቅርቦት፣ መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ድጋፍ ፕሮግራም

የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች አቅርቦት አቅም ግንባታን በተመለከተ፤ የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የፋይናንስ አቅማቸውን በማጎልበት የአገር ውስጥ የገበያ ፍላጎትን እንዲሸፍኑ ይደረጋል። ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር መካከለኛ የጥገና አቅም ያላቸው የመንግስትና የግል ተቋማት ወደ ከባድ መሣሪያዎች ጥገና እንዲሸጋገሩ ድጋፍ ይደረጋል። በተጨማሪም የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን በራስ አቅም ለመስራት የሚያስችል የፋይናንስ፣ የሰው ኃይል፣ ግብዓት አቅርቦት ይመቻቻል። የኮንስትራክሽን ግብዓት አቅርቦትና ማምረቻ ተቋማት ማስፋፋትን በተመለከተ ከፍተኛ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ዕጥረት በሚታይባቸው የብረትና ማጠናቀቂያ የግንባታ ዕቃዎች በጋራ ግዢ ሥርዓትና ጥብቅ የጥራት ቁጥጥር በመዘርጋት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡና የጥራት ደረጃን ጠብቀው እንዲመረቱ ይደረጋል፣ የግንባታ ዕቃዎችን በሚፈለገው መጠን፣ ዓይነትና ጥራት በሀገር ውስጥ ምርት ለማቅረብ የሚያስችል አቅም ይፈጠራል እንዲሁም ስትራቴጂክ ጠቀሜታ ያላቸው ግብዓቶችን የሚያመርቱ ድርጅቶችን በመለየት የሚደገፉበት ሁኔታ ይመቻቻል።

## 4.4 የሀገራዊ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅሜንት አቅም ግንባታ ፕሮግራም

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ነባራዊ ሁኔታ የትንተና ጥናት በማድረግና ክፍተቱን በመለየት የአቅም ግንባታ ሥራ ይከናወናል። የዲዛይን ዝግጅት መሠረታዊ ታሳቢዎችና መስፈርቶችን መሠረት አድርጐ የተሟላ የዲዛይን አተገባበር መመሪያና ማዕቀፍ (Design Guide Line) እንዲዘጋጅ ይደረጋል። ለመኖሪያ ቤት የሚሆን ወጪ ቆጣቢና ተስማሚ የግንባታ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ፍትሃዊና ተደራሽ የሆነ የመኖሪያ ቤት ጥናት ይከናወናል። የኮንስትራክሽን ማኔጅሜንት ሥርዓቱን ከመሠረቱ የሚቀይሩ የግንባታ ኘሮጀክት አሠራር ዘዴዎች (ካይዘይን፣ የተቀናጀ የኘሮጀክት ሥራ አመራርና ኢንፎርሜሽን ሥርዓት) በናሙና ትግበራ በማጋገጥ እንዲሰፋና አጠቃላይ የግንባታ አፈጻጸም ላይ ለውጥ እንዲመጣ ይደረጋል። የኮንስትራትክሽን ኢንዱስትሪውን ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ለማሻሻል የሚያስችሉ የኮንክሪትና አዳዲስ አሰራር ዘዴዎችና የፕሮጀክት ማኔጅመንት ዴሊቬሪ ሲስተሞች እንዲተዋወቁ ይደረጋል። እንዲሁም ሀገራዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አፈጻጸም ቁልፍ መለኪያዎች በጥናት እንዲለዩ ይደረጋል። ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት የተሻሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምን በተመለከተ የኮንስትራክሽን ምርምር ተቋማትን በማቋቋም ለቴክኖሎጂዎች ማስፋፊያነት እንዲያገለግሉ ለማድረግ የተለያዩ ድጋፎች ይደረጋሉ፣ ከትምህርትና ምርምር ተቋማት፣ ከጥራትና ደረጃ መዳቢዎች ኤጀንሲና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ዓለም አቀፍ የተሻሻሉ ወጪ ቆጣቢ አማራጭ የግንባታ ቴክኖሎጂዎችን፣ የዲዛይን ሶፍትዌሮችን በመምረጥ ከአገራችን ጋር በሚጣጣም መልኩ እንዲዘጋጁ ይደረጋል።

ለየግንባታ ዓይነቶች የተቋቋሙ የጥራት መፈተሻ ማዕከላት ብቃት ባለው ሰው ኃይልና በዘመናዊ የላቦራቶሪ መቆጣጠሪያ ቁሳቁሶች የተሟሉ እንዲሆኑ ድጋፎች ይደረጋሉ። የተገጣጣሚ ህንጻ አካላት በሀገር ውስጥ የማምረት ቴክኖሎጂ ማዕከል እንዲስፋፋ ይደረጋል፣ የተቀናጀ የህንጻ ግንባታ አቅርቦት /The integrated project delivery (IPD)/ ከካይዘን ፍልስፍና ጋር በማቀናጀት የዘርፉ መደበኛ የአሰራር ስርዓት እንዲሆን ይደረጋል። ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት አሰራር በሰፊው መጠቀምና ተደራሽ የሆኑ ግብዓቶች በመለየት የዘርፉን ተወዳዳሪነት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ስምምነት በተደረሰባቸው መለኪያ መስፈርቶች በሂደት የሚታየውን ለውጥ በመመዘን ወቅታዊ የሆነ ገጽታውን ማየት እንዲቻል ይደረጋል። እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግርና የተግባር ስልጠና የሚከናወንበት የልህቀት ማዕከል (Construction Centers of Excellence) ይደራጃል። የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት መሰረታዊ እውቀትን ማዕከል ባደረገ አግባብ በዘርፉ የሚሰማሩ

ባለሙያዎች በምዘና ስርዓት አልፈው አለምአቀፍ ተቀባይነት ያለው ሰርተፍኬት እንዲያገኙ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት አማካኝነት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### 3.1.6 ከተማ ልማትና ቤቶች

1. **ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች**

የከተሞች ልማታዊ መልካም አስተዳደር በአስተማማኝ ደረጃ የሚረጋገጥበት፤ ከተሞቻችን ከሀገር አቀፍና ክልል አቀፍ የልማት ዕቅድና ፕላን ጋር በተቀናጀ የከተማ ፕላን የሚመሩበት ፕላን ዝግጅትና አቅጣጫ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የተመጣጠነ እና ፍትሃዊ የአሰፋፈር ሥርዓት በመገንባት ኢኮኖሚያዊ ሚና ያላቸው ከተሞች ተመጋጋቢ ሆነው እንዲያድጉ ማድረግ፣ አርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን በከተሞች መስፋፋት ይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርግና የከተሞች መሬት በቁጠባ መጠቀምን የሚያጠናክር በቂ የካሳና የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ በመስጠት ለልማቱ የሚሆን መሬት በበቂ መጠን በቀጣይነት ማቅረብ፤ ፈጣን የከተማ እድገትን ታሳቢ ያደረገ የተቀናጀ መሰረተ ልማት ለማቅረብ የሚያስችል የቅንጅት፣ የጥራትና የፋይናንስ ሁኔታን የማመቻቸት ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ በሀገራችን ከተሞች የሚስተዋለውን የቤት ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም ለማስወገድ የተጀመረውን የቤት ልማት ፕሮግራም አጠናክሮ በማስቀጠል ከተሞቻችን መልሰው በሚያንሰራሩበት እና ዘላቂ ልማት በሚያረጋግጡበት አግባብ በማልማት ብሎም የከተሞቻችንን ዕድገት ቀጣይነት የሚያረጋግጥ አረንጓዴ ልማትን የሚያፋጥን የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጅ አቅጣጫ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡

2. **ዋና ዋና ዓላማዎች**

በቤቶች ልማትና አስተዳደር ፕሮግራም የዘርፉ ቀጣይ ዕቅድ አላማ በከተሞች ያለውን የቤት አቅርቦት በማሻሻል የመኖሪያ ቤት እጥረትን እና ተያያዥ ችግሮችን በመቅረፍ እያደገ የመጣውን ተጨማሪ የቤት ፍላጎት በበቂ ሁኔታ ለማስተናገድ የሚያስችል ሥርዓትና አቅም በመፍጠር ዘላቂነት ያለው የተሳለጠና የቤት ነክ ልማታዊ አገልግሎቶች ተጠናክረው እንዲቀርቡ ማድረግ ሲሆን በተቀናጀ የከተሞች መሰረተ ልማት አቅርቦት ፕሮግራም ደረጃውን የጠበቀና የተቀናጀ መሰረተ ልማት ለመዘርጋት የሚያስችል የፋይናንስ አቅም በማመቻቸት፣ የመሰረተ ልማትና አገልግሎት አቅራቢ ተቋማትን ትስስር በማጠናከር እና የቴክኖሎጂና የክህሎት ሽግግርን በማጎልበት ልማትን የሚያፋጥን፣ የህዝብ ተጠቃሚነትና ባለቤትነትን የሚያረጋግጥ የተቀናጀ የመሠረተ ልማት በቀጣይነት እና በተደማሪነት በከተሞች እንዲስፋፋ የማድረግ አላማ ተይዞ ይሰራል፡፡

የህበረተሰቡን የይዞታና የመጠቀም መብት እንዲሁም የንብረት ዋስትናን በማረጋገጥ፣ የከተሞችን መሬት በዘመናዊ አሰራርና ቴክኖሎጂ በተጠናከረ የመረጃ ሥርዓት በማደረጀት የነዋሪውን እርካታ፣ የከተሞችን ልማትና መልካም አስተዳደር ስኬት በማረጋገጥ ብሎም ከተሞችን በጠንካራ የልማታዊ ሠራዊት ቅኝትና የሥራ እድል ፈጠራን መሠረት በማድረግ የማልማት አላማ ተይዞ ይሰራል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አረንጓዴ ዕጽዋትን በማልማትና በመንከባከብ፣ እንዲሁም ከደረቅ ቆሻሻ ቀልዝን (Compost) በማምረትና ለአረንጓዴ ልማት ስራ በመጠቀም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ራዕይ ለማሳካት እና ለዜጎች ምቹ የመኖሪያና የመስሪያ አካባቢ ለመፍጠር እንዲሁም የከተሞችን ገፅታ ለመገንባት አላማ ተይዞ ይሰራል፡፡

በከተሞች የሚከናወኑ የልማት ሥራዎች የሴቶችን፣ የወጣቶችን፣ የአረጋውያንን፣ የህፃናትትና የአቅመ ደካማ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ እንዲሁም ከማንኛውም አደጋ ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን በማስቻል የኢኮኖሚ እድገቱ ተጠቃሚነታቸውን የማረጋገጥ ዓላማ ከግብ ለማድረስ መጠነ ሰፊ ርብርብ የሚደረግ ይሆናል፡፡

የከተማ ልማታዊ አመራር በየደረጃው መፍጠር፣ ከድህነት ወለል በታች እየኖሩ ያሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ከምግብ ዋስትና እጦትና ከድህነት እንዲወጡ እና ስራ ፈጥረው ገቢ እንዲያገኙ

ማስቻል፣ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ የከተማ ኘላን ዝግጅትና ትግበራ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ፣ የከተሞችን ልማትና መልካም አስተዳደር ስኬት ማረጋገጥ፣ ለዜጎች ምቹ የመኖሪያና የመስሪያ አካባቢ መፍጠር ዋና ዋናዎቹ የዘርፉ ዓላማዎች ናቸው፡፡

### 3. ዋና ዋና ግቦች

የዘርፉ ዋና ዋና ግቦች የከተማ ልማትና መልካም አስተዳደር የአቅም ግንባታ ሥራን የሚመራና የሚያስተባብር የከተማ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት በማዕከልና በየክልሉ በማቋቋም ለ50 ሺህ አመራሮች ሥልጠና በመስጠት አመራሩን፣ ፈጻሚውንና ሕዝቡን በማቀናጀት የከተማ ልማትና መልካም አስተዳደር ሥራን በማይቀለበስበት ደረጃ የማድረስ፣ የህዝቡን የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄ የመመለስ አቅማቸውን ለማሳደግ በሪጅዮፖሊስና ከፈርጅ አንድ እስከ ሦስት ያሉ ከተሞችን የገቢ መጠን 50 ቢሊዮን ማድረስ፣ በመረጃ መረብ የተሳሰረ፣ ዘመናዊ፣ የሚናበብ እና ደህንነቱ የተረጋገጠ የመረጃ ቋት ሥርዓት በፌደራል፣ በሁሉም ክልሎች የዘርፉ ተቋማትና በሜትሮፖሊስ፣ በሪጅዮፖሊስና ከፈርጅ አንድ እስከ ሦስት ባሉ ከተሞች አደረጃጀት የመፍጠር ግብ ተጥሏል፡፡ በሪጅዮፖሊስና ከፈርጅ አንድ እስከ ሦስት ባሉ ከተሞች ልማት፣ የህዝብና ባለሀብቱ የልማት አስተዋጽኦ 35 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡

በከተማ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ከ2 ሺህ በላይ የህዝብ ብዛት ባላቸው 972 ከተሞች ለሚገኙ 2,800,000 ሥራ አጦች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የመስራት አቅም የሌላቸውና ለምግብ ዋስትና እጦት የተጋለጡ 1,050,000 ዜጎች የቀጥታ ገንዘብ ድጋፍ /cash transfer/ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣ በከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ተግባር 8 ሺህ ለሚደርሱ የገጠር ማዕከላት ፈርጃቸውን መሠረት ያደረገ ፕላን እንዲዘጋጅላቸው ማድረግ፣ ለ20 የኢንዱስትሪ ፓርኮችና ዞኖች ልማት የሚያስፈልግ የለማ መሬት ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ማድረግ፣ የተጎሳቆሉና የደቀቁ የከተማ አካባቢዎችን ሽፋን ወደ 30 ከመቶ ማድረስ ናቸው፡፡ በተጨማሪም 750 ሺህ አዲስ መኖሪያ ቤቶች መገንባት፣ ደረጃውን የጠበቀ የከተማ ቤት አቅርቦት 70 በመቶ ማድረስ፣ በተሻሻሉ የመኖሪያ ቤቶች የሚኖረውን የገጠር ነዋሪ 25 በመቶ ማድረስ፣ በዕቅድ ዘመኑ 685 የገበያ ማዕከላት፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች 270 የማሳያ እና የመሸጫ ቤቶች በከተሞች እንዲገነቡ ማድረግ፣ የከተሞች የአረንጓዴ ልማትና የህዝብ መናፈሻ መሬት አጠቃቀም ሽፋንን 30 በመቶ ማድረስ እና የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ሽፋን እስከ ፈርጅ ሦስት በሚገኙ ከተሞች ከ90 በመቶ በላይ ማሳደግ የዘርፉ ዋና ዋና ግቦች ናቸው፡፡

### 4. የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

የዘርፉ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች በተመለከተ የከተማ ልማታዊ አመራር ሳይንስና ጥበብ ግንባታ ፕሮግራም፣ የከተማ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም፣ የከተሞች ልማታዊ መልካም አስተዳደርና የአቅም ግንባታ ፕሮግራም፣ የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ፕሮግራም፣ የከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ማሻሻል ፕሮግራም፣ የቤቶች ልማትና አስተዳደር ፕሮግራም፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት እና ሬጉላቶሪ ፕሮግራም፣የተቀናጀ የከተሞች መሠረተ ልማት አቅርቦት ፕሮግራም፣ የከተሞች የአረንጓዴ ልማትና የፅዳት ማሻሻያ ፕሮግራም ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

## 3.1.7 የንግድ ዘርፍ ልማት

### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የዘርፉን አቅም የበለጠ በማሳደግ በጥራትና በቅልጥፍና ተወዳዳሪ የንግድ አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስሩን የበለጠ የማጠናከር ተግባር ይከናወናል፡፡ በመሆኑም ቀጣይ የዘረፉን እቅድ አላማዎችና ግቦች ለማሳካት አምራቹን፣ የንግዱን ማህበረሰብና ሸማቹን ያረካና ውድድርን መሰረት ያደረገ ፍትሃዊ የንግድ አሰራር ስርዓትን የመፍጠር፣ ቀጣይነቱ የተረጋገጠ የገበያ ዕድል እንዲፈጠር በማድረግ የላቀ የውጭ ምንዛሬ የማስገኘት፣ የኪራይ

ሰብሳቢነት አመለካከትን የሚጠየፍና የሚታገል የንግድ ዘርፍ የለውጥ ሰራዊት ግንባታን አስተማማኝ ደረጃ ላይ የማድረስ፣ የህብረተሰቡን ጤንነት፣ ደህንነትና የሀገርን ጥቅም ለማስጠበቅ ከጥራት ደረጃቸው በታች የሆኑ ምርቶችና አገልግሎቶች በገበያ ላይ እንዳይውሉ ጠንካራ የኢንስፔክሽን ሥራ የማከናወን ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

በተመሳሳይ ለልማታዊ ባለሃብቶች የሚሰጠውን ሁሉን አቀፍ እገዛና ድጋፍ በማጠናከር በውድድር አሸናፊ ለመሆን የሚያስችላቸውን አቅም እንዲገነቡ ለማድረግ ጠንካራ የሬጉላቶሪ ስርዓት ይዘረጋል፡፡ የሸማቹን ህብረተሰብ ደህንነትና ጥቅም ማስጠበቅ፣ በዘርፉ ውስጥ ያሉ ባለድርሻ አካላትን፣ የንግዱን ማህበረሰብና የሸማቹን ህብረተሰብ ግንዛቤና አቅም የማጎልበት ተግባር ይከናወናል፡፡ አስተማማኝና ዘመናዊ የንግድ መረጃ ሥርዓት በማደራጀት በአለም አቀፍ፣በአካባቢያዊና በሁለትዮሽ የንግድ ግንኙነትና ድርድሮች የተጀመሩ ጥረቶችን አጠናክሮ በመቀጠል የሀገራችንን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡ ለዕቅዱ ተፈፃሚነት የንግዱን ዘርፍ በፌደራል፣ በክልል መንግስታትና በከተማ መስተዳደሮች ቅንጅትና ወጥነት ያለው አደረጃጀት በመፍጠር የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት ርብርብ ይደረጋል፡፡

## 2. ዓላማዎች

የንግዱ ዘርፍ ቀጣይ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዋና ዋና አላማዎች የዘርፉን የለውጥ ሰራዊት ግንባታ በቀጣይነት ማጠናከርና የመፈፀም አቅምን ማጐልበት፣ ዘመናዊ፣ ፍትሃዊና በውድድር ላይ የተመሰረተ የንግድ ስርዓት መዘርጋት፣ ቀልጣፋና የላቀ የገበያ ማስፋፊያና ትስስር ስርዓት መገንባት እና የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ ናቸው፡፡

## 3. ዋና ዋና ግቦች

የዘርፉን የቀጣይ አምስት አመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ለማሳካትና ተፈጻሚ ለማድረግ አሰራርና አደረጃጀትን በቀጣይነት ማሻሻል፣ ዕውቀትና ክህሎትን የማጎልበት እና የአመለካከት ለዉጥ የማምጣት ስራን ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ፣ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥን ሙሉ በሙሉ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ የመረጃ መረብ (online) ስርዓት በመዘረጋት የአገልግሎት አሰጣጡን ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ፣ ፈቃድ ከተሰጣቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ውስጥ 50 በመቶ ኢንስፔክት በማድረግ የገቢና የወጪ ምርቶችን በ2012 ወደ1,529,374.67 እና 1,267,333.05 ሜትሪክ ቶን በቅደም ተከተል የማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡

አስተማማኝና ዘመናዊ የንግድ መረጃ ሥርዓት በማደራጀትና ፀረ-ኪራይ ሰብሳቢነት ትግሉን በማጠናከር ከህግ ጥሰት የፀዳ፣ ግልጽ፣ በውድድር ላይ የተመሰረተ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው የላቀ ዘመናዊ ምርት ግብይት ሥርዓት መገንባት፣የህጋዊ ስነልክ የመለኪያ መሳሪያዎችን ትክክለኝነት ማረጋገጥን በፌዴራል፣ በክልሎችና በከተማ መስተዳደሮች በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 15,687,600 ማድረስ፣ ውጤታማ የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ተግባራትን ማከናወን ፣ ጠንካራ የንግድ ግንኙነትና ድርድር በማካሄድና ሀገሪቱን የዓለም አቀፍ የንግድ ትስስር ስርዓት አካል በማድረግ አስተማማኝ የወጪ ንግድ ገበያ እንዲኖራት ማስቻል፣አዳዲስ የግብርና ምርቶችን ወደ ግብይት ሥርዓቱ በማስገባት እና ዓመታዊ የግብይት አቅምን በማሣደግ የግብይት ተዋናዩን እርካታ ማሟላት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 4. የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

### 4.1 የንግድ አሰራርና አደረጃጀትን በማሻሻል የንግድ ዕውቀትና ክህሎትን ማጎልበት

የንግድ ውድድርን የሚገድቡ አሠራሮችና ሁኔታዎችን በማጥናት ጠንካራ የገበያ ውድድር ለማስፈን የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎችን የማውጣት ፣ ክፍተቶችን በመለየት ዕቅዱን ሊያሳኩ የሚያስችሉ ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲዘረጋ የማድረግ፣ በየደረጃው ያሉ አመራርና ፈፃሚ አካላት ዘርፉን በሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣

ስትራቴጂዎችና የህግ ማዕቀፎች ዙሪያ ተገቢውን ዕውቀትና ክህሎት እንዲኖራቸው በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡን ውጤታማ የማድረግ ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

ለሸማቹ ህብረተሰብ ብሎም ለንግዱ ማህበረሰብ የተለያዩ የህዝብ አደረጃጀቶችን በመጠቀም ሰፊና ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በማከናወን ዘርፉን የሚያጠናክር የአቅም ግንባታ ኢንስቲቱዩት በመገንባት የለውጥ ሰራዊት ግንባታን አስተማማኝ ደረጃ ላይ በማድረስና ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር ለዘርፉ ተዋንያኖች ቀጣይነት ያለው ስልጠና የመስጠት ስትራቴጃዊ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

## 4.2 የንግድ ግንዛቤን በማጎልበት የሸማቶችን መብት ማረጋገጥ

የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማጎልበትና የገበያ ግልፅነትን በማሳደግ፣ እንዲሁም ፀረ-ውድድር የሆኑ የንግድ አሰራሮችንና ተገቢ ያልሆኑ አሳሳች የንግድ ተግባራትን በመከላከል ሸማቹንና የንግዱን ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርግ ፍትሐዊ የንግድ ውድድር ለማስፈን ሰፊ ጥረት ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ በአመለካከትና በሥነ-ምግባር የታነጸ ፈጻሚ መፍጠር፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመስራት ኪራይ ሰብሳቢነትን መታገል፣ የኢንስፔክሽን ጣቢያዎችን የማስፋትና ስራዉን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የማድረግ እንዲሁም በመዳረሻ አገሮች የሚደረጉ የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሺን ሰራዎችን አስተማማኝ ደረጃ የማድረስ ስትራቴጂዎች ይተገበራሉ፡፡

## 4.3 በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ የተደገፈ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ መዘርጋት

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ አገልግሎትን ለማሻሻል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በሁሉም ክልሎች በአስተማማኝ ደረጃ እንዲዘረጋ የማድረግ፣ ከሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ ከክልሎች እና ከከተማ መስተዳደሮች ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን የማጠናከር እንዲሁም የባለድርሻ አካላትን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማጎልበት በእቅድ ዘመኑ የሚተገበሩ ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የንግድ መረጃን በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ በማስደገፍ ለንግድ ተዋንያኑ ለግብይት ውሳኔ የሚረዳ ወቅታዊና ተዓማኒነት ያለውን መረጃ በተከታታይነት እንዲያገኙ ማድረግ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደራጀና የተጠናከረ የንግድ መረጃ ማዕከል /Trade Point/ ማቋቋም፣ የተጀመረውን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሶፍትዌር ዝርጋታ በማጠናቀቅ በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 4.4 ዓለማቀፋዊና አካባቢያዊ የንግድ ትስስርን ማጠናከር

በዕቅድ ዘመኑ በንግድ ግንኙነትና ድርድር ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ሀገሪቱን የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ለማድረግ የተጀመረውን የድርድር ሂደት የማጠናቀቅ ተግባር ይከናወናል፡፡ ከአውሮፓ ህብረት ጋር የተጀመረውን የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት (EPA) ድርድር የማጠናቀቅና አካባቢያዊ ውህደትን (IGAD, COMESA,&Tripartite/COMESA-EAC-SADC) ለመፍጠር የሚያስችሉ ድርድሮችን በማጠናቀቅ የተገቡ ግዴታዎችን ተግባራዊ የማድረግ ስራዎች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ የገበያ መዳረሻዎችን የሚያስፋፉና የሚያጠናክሩ የሁለትዮሽ ስምምነቶችና ትብብሮች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን ለማሳካት ለድርድሮቹ የሚረዱ ጥናቶችን ማካሄድ፣ የህግ ፍተሻዎችን በማድረግ እንዲሻሻሉ ማድረግ፣ የድርድር ሰነዶችን ማዘጋጀት፣ የባለድርሻ አካላት ግብዓቶች የሚካተቱበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ ውጤታማ የቅንጅትና የትብብር ዘዴዎችን መቀየስ፣ የንግድ ድርድር ጉዳዮችን በየጊዜው በባለድርሻ አካላት እንዲታወቁ ማድረግ፣ የልማት አጋሮችን ድጋፍ አሟጦ መጠቀም፣ በንግድ ድርድር ክህሎት የሰለጠነ ተተኪ ሀይል ማፍራት፣ ስምምነቶችን ለመተግበር የሚያስችሉ ተቋማትን መገንባት እና የጋራ ፍላጎት ከሚያራምዱ ወገኖች ጋር ትስስር የመፍጠርና ሀገራዊ ጥቅምን በሚያስጠብቅ መልኩ መጠነ ሰፊ የባይላተራል፣ የአካባቢያዊና የመልቲላተራል ድርድሮችን የማድረግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

### 4.5 ዘመናዊ የንግድ መረጃ ስርዓትን በማደራጀት ሀገራዊ የግብይት ስርዓትን ማጠናከር

የዘመናዊ ምርት ግብይት ሥርዓት ግንባታን ለማረጋገጥ፣ የግብይት ተዋናዮችን በዋናነት የአርሶ አደሩን ተሳትፎ ለማጎልበት፣ብሎም የገበያውን ደህንነት አስተማማኝ ለማድረግ እና የኀብረተሰቡን ጥቅም ለማስጠበቅ እንዲቻል ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መረጃ እንዲያገኙ እና በግብይት ሥርዓቱ ሂደት ማነቆ የሚሆኑ አሠራሮችን በጥናት በመለየትና የመፍትሄ ሃሳቦችን በመተግበር የዘመናዊ ምርት ግብይት ሥርዓት ግንባታው እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው የላቀ ዘመናዊ የምርት ግብይት ሥርዓት ለመገንባት ፍትሃዊ እና ታዓማኒ የሚያደርጉ አዳዲስ አሠራሮችን በመተግበር፣ የኤሌክትሮኒክ ግብይትን ተግባራዊ በማድረግ እና በግብይት መድረክ የነበሩ አሠራሮችን በማሻሻል የግብይት ተዋናዮች በምርት ገበያው አሠራር ያላቸው አመኔታ እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ አዲስ የተቋቋመውን የወጪ ገበያ ማስፋፊያ አደረጃጀት በሰው ኃይልና በቁሳቁስ እንዲሟላ በማድረግ የተሟላ አቋም እንዲኖረው ማድረግ፣ የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ስትራቴጂ መቅረጽ፣ የአማካሪ ካውንስል በማቋቋም የወጪ ገበያ ማስፋፊያ ሥራን እንዲደግፍ ማስቻል፣ የገበያ ማስፋፊያ ጥናቶችን በማከናወን ለተግዳሮቶች ወቅታዊ ምላሽ የመስጠትና ዘመናዊ አሠራሮችን የመዘርጋት፣የአገሪቱን ምርት በማስተዋወቅና የገበያ ትስስር በመፍጠር ለምርቶቻችን አስተማማኝና ቀጣይነት ያላቸው የገበያ እድል የመፍጠር ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

### 3.1.8 ባህልና ቱሪዝም

### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

የተፈጥሮና ባህላዊ ቅርሶችን በመጠበቅና በማልማት የባህልና ቱሪዝም ምርቶችንና አገልግሎቶችን በማበልጸግና በማስፋፋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ በተለይም የሴቶችንና ወጣቶችን የሥራ ዕድል ማስፋት፣ የብዝኃ ባህልና መገለጫዎቻቸውን በእኩልነት እንዲለሙና እንዲጠበቁ ዕሴቶቻቸው እንዲጎለብቱ ማድረግ፣ የጠራና አስተማማኝ የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት ወደ ተግባር ሊለወጡ የሚችሉ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ለሴክተሩ ተቋማዊ አቅም ግንባታና አገልግሎት እንዲውሉ ማድረግ፣ የገጽታ ግንባታና የማስተዋወቅ ሥራዎችን በማጠናከር ከባህልና ቱሪዝም የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ማሳደግና የጠቅላላ ሀገራዊ ምርት/ገቢ ድርሻችን ወደ 5 በመቶ ማሳደግ፡፡

### 2. ዓላማ

የባህልና ቱሪዝም ዘርፍ ዋና ተልዕኮ ቅንጅታዊ አሠራርን በሁለንተናዊ መልኩ በማጠናከርና የማህበረሰብ ተሳትፎን በማጎልበት የባህልና ቱሪዝም ዘርፍ ለሀገራችን ዘላቂ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ዕምርታ የበኩሉን ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማድረግ ነው ፡፡ በዚህ መነሻነት የ2ኛው የዕድገትና ትንስፖርቴሽን ዕቅድ ዋና ዋና ዓላማዎች የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎችን በጥበቃና ልማት ማሳደግ፣ የመረጃ ሀብቶች ክምችት አጠቃቀም ማሳደግ፣ የባህል ኢንዱስትሪዎችን ልማትና የገበያ ትስስርን ማሳደግ ፣የባህላዊ ቅርሶችን ጥበቃና ልማት ማሳደግ፣ የቱሪዝም ገበያ ስርዓትን ማሻሻልና ውጤቱን ማሳደግ፣ የአገር ውስጥ ቱሪዝምን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዓይነት መጠንና ደረጃ ማሳደግ ናቸው፡፡

### 3. ዋና ዋና ግቦች

ሀ. የባህላዊ ቅርሶችን ጥበቃና ልማት ከማሳደግ አኳያ የሚንቀሳቀሱ ቅርሶችንና የስነ ሰብ የባህል ሀብቶችን ጠብቆ ለማቆየት በ20 የክልልና የዞን ዋና ከተሞች ደረጃቸውን የጠበቁ ሙዚየሞች ማደራጀትና ማጠናከር፣ 11 ባህላዊ ቅርሶችና ባህላዊ መልከዓ-ምድሮች በዓለም የባህል ቅርሶች መዝገብ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ የቅድመ ታሪክና የፓሊዮንቲዎሎጂ ቅርሶችን የሚያካትት የተንቀሳቃሽና ቋሚ ቅርሶችን

የምዝገባ ሽፋን 100 በመቶ ማድረስ ፣የኢትዮጵያ ብሔር ብሄረሰቦችና ሕዝቦችን የሚወክል 1 የስነ ሰብ ሙዚየም ማደራጀት፣

ለ. የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎችን ጥበቃና ልማት ከማሳደግ አኳያ 25 የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎችን በመከለልና የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ማቋቋም፣ ለዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ የሚውል ማሰልጠኛ ማዕከል ማቋቋም፣ በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ስር 1 ሀገር-አቀፍ የፓርክ ውስጥ ለውስጥ መንገድ ግንባታ ብርጌድ ማቋቋም፣ 4800 ኪ.ሜ. ነባርና አዳዲስ የፓርክ የበጋና የክረምት የውስጥ ለውስጥ መንገድ መስራት፣ 75 የስካውት ቤቶችንና 10 የፓርክ ጽ/ቤቶችን መገንባት፣ 30 ንፁህ የመጠጥ ውሃ ግንባታዎችን በመገንባት ቱሪስቶችን፣ ሰራተኞችንና ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ፣ በሰውና በዱር እንስሳት ላይ የሚደርሰውን ግጭት በማጥናት በ2007 ከነበረበት 90 በመቶ በ2012 ወደ 50 በመቶ መቀነስ፣ በጥበቃ ቦታዎች የሚፈፀሙ ህገ-ወጥ ሰፈራና ሌሎች ህገወጥ ድርጊቶችን 80 በመቶ መቀነስ፡፡

ሐ. የባህል ኢንደስትሪዎችን ልማትና የገበያ ትስስርን ከማሳደግ አኳያ በ11 የክልል ከተሞችና የፈጠራ ኢንደስትሪ ማዕከሎችን ማቋቋምና ማጠናከር፣ በ30 የክልልና የዞን ዋና ከተሞችና የከተማ አስተዳደሮች የቴአትርና ሲኒማ ተቋማት በመንግሥትና በማህበረሰብ ትብብር እንዲመሠረት ማድረግ፣ በ50 አህጉራዊና አለማቀፋዊ የባህል ፌስቲቫሎችና አውደ-ርዕዮች ተሳትፎ ማድረግ፣ የሀገሪቱን የሙዚቃ፣ የትያትርና የፊልም ንዑስ ዘርፍችን ለማሳደግ 2 የዕድገት ስትራቴጂ ማውጣት፣

መ. የዘርፉን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዓይነት፣ መጠንና ደረጃ ማሳደግን በተመለከተ የሆቴል የመኝታ ክፍሎችን ብዛት ከ20 ሺህ ወደ 58 ሺህ እንዲደርስ ድጋፍ ማድረግ፣ የሆቴል አልጋዎች ብዛት ከ25 ሺህ ወደ 104 ሺህ እንዲደርስ ድጋፍ ማድረግ፣ ደረጃ የተሰጣቸውን የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከ300 ወደ 1,000 ማድረስ፣ የአለም አቀፍ ብራንድ ያላቸው ሆቴሎችን ብዛት ከ3 ወደ 12 ማሳደግ ናቸው

ሠ. የቱሪዝም ማርኬቲንግና ብራንዲንግ ስትራተጂን በመተግበር የቱሪስት ቁጥር አሁን ካለበት 724 በዓመት በአማካይ በ20 በመቶ በማሳደግ ወደ 2 ሚሊዮን ማሳደግ ፣ ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ አሁን ካለበት 2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በየዓመቱ በ25 በመቶ በማሳደግ ወደ 6 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማድረስ፣ የቱሪስት የሀገር ውስጥ ቆይታ ጊዜን 15 ቀናት ማድረስ፣ 3 የቱሪዝም ገበያ ወኪል ጽ/ቤቶች ማቋቋም (አሜሪካ፣ አውሮፓ፣ እስያ) እና የቱሪስት መዳረሻዎችን በተለያዩ መንገዶች ማስተዋወቅ፣ የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ከማሳደግ አኳያ የአገር ውስጥ ቱሪስት ብዛት 15 ሚሊዮን ማድረስ፣ ከአገር ውስጥ ቱሪዝም በየዓመቱ 4 ቢሊዮን ብር ገቢ ማግኘት፣

ረ. የቋንቋዎች ልማትና አጠቃቀም ለማሳደግ አንድ የብሄራዊ የቋንቋዎች ትርጉም ተቋምና 3 ሀገራዊ የቋንቋ ምርምር ተቋምና ምክር ቤት ማቋቋም፣ ሁሉም የብ/ብ/ህ ቋንቋዎች በቁጥር ተለይተው እንዲመዘገቡና እንዲታወቁ ማድረግ፣ ተጨማሪ 20 የብ/ብ/ህ ቋንቋዎች በጽሁፍ ቋንቋነት እንዲለሙና አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣ 40 የብ/ብ/ህ ቋንቋዎች የአጠቃቀም ደረጃ ማሳደግ (የስራ፣ የትምህርት፣ የመገናኛ ብዘሃን፣ ወዘተ)፣ 5 በመጥፋት አደጋ ላይ ያሉ ቋንቋዎችን ማጥናት፣ መሰነድና መታደግ፣

ሰ. የመረጃ ሀብቶችን ክምችትና አጠቃቀም በማሳደግ ረገድ 383,510 የመረጃ ሀብቶችን በግዢ፣ በአዋጅ በስጦታና በግንኙነት ማሰባሰብ፣ በ11 የክልል ዋና ከተሞች የህዝብ ቤተመጻህፍቶችና ቤተመዛግብት እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ ማድረግ፣ በ15000 ቀበሌዎች የቀበሌ ማዕከላት የንባብ ቤቶች መመስረት፣ 4 የኢትዮጵያ ጥንታዊ ጽሁፎችንና መዛግብቶችን በዓለም የጥንታዊ መዛግብቶች ማህደር ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ፣ ሀገራዊና ክልላዊ የመረጃ አስተዳደር ስርዓት መገንባት፣

ሸ. በባህልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪዎች ብቃት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራት ከከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች፣ ከጥናትና ምርምር ተቋማትና ከሙያ ማህበራት ጋር የተቀናጀ የሥልጠና ኘሮግራም ማዘጋጀትና ብቃት በምዘና ሥርዓት ማረጋገጥ፣

## 4. የማስፈጸሚያ ስትራቴጂ

ከላይ የተጠቀሱትን የትኩረት አቅጣጫዎች መሠረት በማድረግ የተቀረፁ ግቦችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉት ስትራተጂዎች ተነድፈዋል፡፡ በዚህም መሠረት ለዘርፉ ልማት አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማት አቅርቦቶችን፣ የቁጥጥር ሥራዎችን፣ የሕግ ማዕቀፍና ተቋማዊ አደረጃጀቶችን እና የግምገማና የክትትል ስራዎችን ለማሻሻል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነት በማጎልበትና ቅንጅታዊ አሠራርን ማሳደግ ወሳኝ ስትራተጂ ነው፡፡

በዘርፉ የሚተዩ የመረጃ ክፍተቶችን እና በግንዛቤ እጥረት ምክንያት ለባህልና ቱሪዝም መስህቦች የሚሰጥ ትኩረት ማነስን ለማሻሻል ተከታታይነት እና ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች የሚሰሩ ሲሆን እነዚህን ግቦች ለማስፈጸም በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ የትምህርት ተቋማትን እና መገናኛ ብዙሃን መጠቀም አንዱ ስትራተጂ ሲሆን በተጨማሪም የትምህርት እና የምርምር ተቋማት ዘርፉ የሚፈልገውን የሰው ኃይል በሚፈለገው መጠን እና ጥራት እንዲያቀርቡ የድጋፍና የክትትል ስራዎችን በመሥራት ተፈጻሚ እንዲያደርጉ ይደረጋል ፡፡

በባህልና ቱሪዝም ዘርፍ በሀገራችን ያለውን የመረጃ ክፍተት ለመሙላት የመረጃ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን መሠረተ ልማቶች በመጠቀም የዘርፉ መረጃዎች በተደራጀ መንገድ እንዲደራጁ በማድረግ ለጥናትና ምርምር ስራዎች እንዲውሉ ማድረግ ዋና ዋና ስትራተጂዎች ናቸው፡፡

# 3.2 የሰው ሀብት ልማትና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ዘርፍ ልማት ዕቅድ

## 3.2.1. ትምህርትና ስልጠና

### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

በሁሉም የትምህርት ዕርከኖች የትምህርት ተሳትፎ፣ ጥራትና አግባብነትን ለማሻሻል በተቀናጀና በተደራጀ አኳኋን የትምህርት ልማት ሠራዊት ፓኬጁን መተግበር፣ የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርትን የማስፋፋት፣ ድጋፍ የሚሹ አካባቢዎችና የታዳጊ ክልሎች የትምህርትና ስልጠና ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ልዩ ድጋፍ የማድረግ አቅጣጫ ተይዟል፡፡ ዝርዝር እንዲሚከተለው ቀርቧል፡፡

**አጠቃላይ ትምህርት፡-** የመሰረታዊ ትምህርት አገልግሎትን ለሁሉም ለማዳረስና በትምህርት መስክ የተቀመጡ የሚሊኒየም የልማት ግቦችን ለማሳካት የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ግቦቹም እንዲሣኩ ይደረጋል:: ጥራቱን የጠበቀ፣ ፍትሐዊና ተደራሽ የሆነ የቅድመ መደበኛ፣ የመጀመሪያ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም ለማዳረስ ወጪ ቆጣቢና በህብረተሰቡ ሙሉ ተሳትፎ የተደገፈ መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ ስልቶች ትምህርት እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡ ለዚህም ፖሊሲውን መሠረት በማድረግ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፣ የትምህርት ጥራትን የማስጠበቅና ለዚህም የሚረዱ ግብዓቶችን የማቅረብ፣ የትምህርት ጥራት ፓኬጆችን የመተግበር፣ ደረጃዎችን የማውጣትና የመከታተል ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ በሌላም በኩል ተግባር ተኮር የሆነ የጎልማሶች ትምህርት በሁሉም አካባቢዎች እንዲዳረስ ይደረጋል::

**የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና፡-** የተቀየሰውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በተቀናጀና ጥራትን ባስተጠበቀ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ተገቢው የጥራት ማረጋገጫ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በዚህ መሰረት የመንግሥት ኢንቨስትመንትን በማጠናከርና የትብብር ሥልጠናን በተሟላ መልኩ ተግባራዊ በማድረግ የሀገራችን የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት በአጥጋቢ ሁኔታ እንዲሟላ ይደረጋል:: የሙያ ምደባ፣ የሙያ ደረጃ ዝግጅት፣ የብቃት ማረጋገጫና ምዘና የምስክር ወረቀት አሰጣጥና የሥርዓተ ትምህርት ቀረፃ የቴክኖሎጂ ሽግግር መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ይደረጋል:: የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሰልጠኛ ተቋማቱም ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች የቴክኖሎጂ ማዕከላት ሆነው እንዲያገለግሉ ይመቻቻል::

**ከፍተኛ ትምህርት፡-** በቀጣዩ አምስት ዓመት የመንግስትና የግል የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ይረጋገጣል፡፡ ለዚህም የዩኒቨርሲቲ የአመራርና የአስተዳደር ሥርዓትን ከማጠናከር ጎን ለጎን የስትራቴጂ ማዕከልና የትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ሚናቸውን እንዲወጡ ይደረጋል:: የቴክኖሎጂ ኢንስቲቱዩቶችም የማስፈጸም አቅም ይገነባል:: በሌላ በኩል ሁለንተናዊ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ልማትን በመተግበር ብቁ የመምህራን አቅርቦት ይረጋገጣል:: የተለወጡ ሥርዓተ ትምህርቶች ትግበራን በትምህርቱ አሰጣጥ፣ በተማሪዎች ምዘናና ፈተና እንዲሁም በውጤት አሰጣጥ ገጽታዎቹ ተጠናክሮ ይፈጸማል:: በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት ኢኮኖሚው በሚፈልገው የሰው ኃይል ብዛት፣ ዓይነትና ጥራት ይቃኛል:: ዩኒቨርስቲዎች ገቢን የማመንጨትና የማሳደግ አቅማቸውን እንዲገነቡና ለትምህርቱ አግባብነትና ጥራት ማጠናከሪያ እንዲያውሉት የሚያስችል ሥራ ይከናወናል:: በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጥናትና ምርምር ሥርዓት የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማዕከል ያደረገ እንዲሆን ይደረጋል:: የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመማር ማስተማር ሂደት አመቺ እንዲሆኑና በተለይ ደግሞ ለሴት ተማሪዎችና ልዩ ትኩረትና ድጋፍ በመስጠት ውጤታማ እንዲሆኑ ይደረጋል:: የከፍተኛ ትምህርት የጥናትና ምርምር ሥርዓት ለሀገሪቱ ልማትና ዕድገት ባላቸው ፋይዳ ይመራሉ::

## 2. ዓላማዎች

የትምህርት ዘርፉ አጠቃላይ ዓላማ የትምህርት ዘርፉን የማስፈጸም አቅም በመገንባት፣ የብቃት መለኪያዎችን በማውጣትና በማስጠበቅ፣ የትምህርት ጥራትና አግባብነትን፣ ፍትሃዊነትና ተደራሽነትን በየደረጃው ያረጋገጠ፣ ውጤታማ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓትን እውን ማድረግ ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹ በየደረጃው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ከአጠቃላይ ትምርህርት ረገድ** ዋና ዋና ዓላማዎች በተቀመጠው የትምህርት ጥራት (ስታንዳርድ) መሰረት ደረጃቸውን ያሻሻሉ ት/ቤቶችን መጠን ማሳደግ፣ ፍትሐዊ፣ ለሁሉም ተደራሽ የቅድመ መደበኛ፣ አጠቃላይ መደበኛ ትምህርት እንዲሁም የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተሳትፎን ማሳደግ እና አግባብነትና ጥራቱን ማስጠበቅ፣ በትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የሴቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥና፣ ሥርዓተ ትምህርትን ከስራ ፈጠራ ከቴክኖሎጅ ከዘላቂ ልማትና ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ አጋርነት ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ማድረግ፣ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትን በማስፋፋት የሃገሪቱን ሁለንተናዊ የልማት እንቅስቃሴ ማጠናከር ናቸው፡፡

**የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዋና ዓላማ** ከግብርና-መር ወደ ኢንዱስትሪ-መር ኢኮኖሚ ለሚደረገው ሽግግር ለተነደፉ ግዙፍ ፕሮጀክቶችና ልማት ፕሮግራሞች ተፈጻሚነትና ተወዳዳሪነት ተፈላጊውን ብቁ የሰው ሃይልና ቴክኖሎጂ ማቅረብ ነው፡፡ እንዲሁም የተጀመሩ የአርሶ/አርብቶ አደሩን የሙያ ብቃት ምዘናና የማብቃት ስራ በመላ ሀገሪቱ ማስፋፋት ፣የኢንዱስትሪውን የስራ ቦታ በስልጠና ማዕከልነት በመጠቀም የሰልጣኞችን ብቃት በምዘና ማረጋገጥና አደራጅቶ ወደ ስራ ማሰማራት፣ የልማት ፕሮግራሞችን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ከዩኒቨርስቲዎች ከምርምር ተቋማትና ከኢንዱስትሪው ጋር ቅንጅት ፈጥሮ መንቀሳቀስና ቴክኖሎጂን የመቅዳት አቅም ውስንነትና የማሻሻል ስራዎችን አጠናክሮ መቀጠል ናቸው፡፡

**ከከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ዋና ዓላማ** በሀገሪቱ የተጀመረውን ፍትሐዊ፣ ቀጣይና ፈጣን የኢኮኖሚ ልማትን ለመደገፍና ለማስቀጠል የሚያስችል ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ኃይል ማቅረብ ነው፡፡ እንደሁም ችግር ፈቺ የሆኑ ምርምሮች እንዲካሄዱና ቴክኖሎጂ የመፍጠር፣ የማከማቸትና የመጠቀም አገራዊ አቅማችን እንዲጎለብት ለማድረግ፣ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎትን ማሳደግ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራርና አስተዳደርን ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት መምህራን ልማትን በማጠናከር ትምህርትና ስልጠናው ተሳትፎውን ፍትሐዊ፣ አግባብነትና ጥራትን ያረጋገጠ እንደሆን ማድረግ ሌላው ዓላማ ነው፡፡

## 3. ዋና ዋና ግቦች

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) ከላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተጥላዋል፡፡

### 3.1. የአጠቃላይ ትምህርት ተሳትፎና ጥራት

በአጠቃላይ ትምህርት ተሳትፎ፣ ፍትሐዊነትና ተደራሽነት ረገድ የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎን በ2007 ካለበት 43.2 በመቶ በ2012 ዓ.ም ወደ 80 በመቶ፣ የአንደኛ ደረጃ (ከ1ኛ-8ኛ ክፍሎች) ንጥር ተሳትፎን አሁን ካለበት 92 በመቶ ወደ 100 በመቶ፣ የሴቶችንና የወንዶችን የትምህርት የተሳትፎ ልዩነትን በሁሉም እርከኖች ወደ 1:1፣ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን የ1ኛ ደረጃ (1-8) ትምህርት ህጻናት ጥቅል ተሳትፎ አሁን ካለበት 4.4 በመቶ ወደ 15 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ የአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎን አሁን ካለበት 39.3 በመቶ በ2012 ዓ.ም ወደ 74.2 በመቶ ለማድርስ ግብ የተጣለ ሲሆን በከተማ በገጠርና በክልሎች መካከል ያለውን የአጠቃላይ ትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ ልዩነት ለማጥበብ፣ የተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ተሳትፎ መጣኔን ወደ 95 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡

በትምህርት ጥራትና አግባብነት ረገድ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ሁሉም ትምህርት ቤቶችና የጉድኝት ማዕከላት በስታንዳርዱ መሠረት የሙያ ብቃታቸው በተረጋገጠ ርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች እንዲመሩ የሚደረግ ሲሆን ለየደረጃው ሙያዊ ብቃታቸው የተረጋገጡ መምህራንን መጣኔ በ2007 በጀት ዓመት ካለበት 20 በመቶ በ2012 ዓ.ም ወደ 70 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ በት/ቤት ደረጃ ምደባ መስፈርት (ስታንዳርድ) መሰረት በ2012 ዓ.ም 60 በመቶ የመጀመሪያ እና 75 በመቶ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ደረጃ 3 እና ከዚያ በላይ በላይ እንዲያሚሉ ታቅዷል፡፡

በዝቅተኛ ክፍሎች ደረጃ በደቂቃ 60 ቃላት አንብቦ መረዳት የሚችሉ ህጻናትን መጣኔ ለማሳደግ በትኩረት የሚሰራ ሲሆን በሳይንስ በሂሳብና ቋንቋ ትምህርቶች በሀገር አቀፍ ደረጃ የትምህርት ቅበላ ጥናት የ4ኛ እና 8ኛ ክፍል የአጥጋቢ ውህድ ውጤት (Composite) ከነበረበት /2007/ 40.06 በመቶ እና 35.3 በመቶ እንደ ቅደም ተከተሉ ወደ 65 በመቶ እና ወደ 60 በመቶ፤ በሳይንስ፤ በሂሳብና ቋንቋ ትምህርቶች በሀገር አቀፍ ደረጃ የትምህርት ቅበላ ጥናት የ10ኛና 12ኛ ክፍሎች የአጥጋቢ ውህድ ውጤትን (Composite score) ከነበረበት 40.6 በመቶ እና 45.5 በመቶ እንደ ቅደም ተከተሉ ወደ 65 በመቶ እና 70 በመቶ ለማሳደግ ጥረት ይደረጋል፡፡

ከቅድመ-መደበኛ እስከ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ያለው ሥርዓተ ትምህርት ከስራ ፈጠራና ቴክኖሎጅ ጋር ተሳስሮ እንዲከለስ ማድረግ እና ሁሉም የየእርከኑን ትምህርት ያጠናቀቁ ተማሪዎች ከየእርከኑ የሚጠበቀውን የስነ ዜጋና የስነ ምግባር ባህሪያትን የተላበሱ ስለመሆናቸው በጥናት ይረጋገጣል፡፡

የትምህርት ጥራትና አግባብነትን የሚያጠናና የትምህርት ሥርአቱን የሚደግፍ ከሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት እስከ ትግበራ ተቀናጅቶ የሚሠራ የጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ይቋቋማል፡፡ በዚህም የትምህርት ጥራትና አግባብነት ጋር የተያያዙ ችግሮቹን በማጥናት የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

### 3.2. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ረገድ ከላይ የተጠቀሱትን የቴ/ሙ/ት/ስ/ ዘርፍ ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉ የሰልጣኝ ልማት የሙያ ብቃት ምዘና አዋጭ ቴክኖሎጂ ማሸጋገር እና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተደራሽነት ፍትሐዊነት ጥራትና አግባብነት እንዲሁም ውጤታማነት አመላካቾች ላይ የተመሰረቱ ዋና ዋና ግቦች ተጥለዋል፡፡

የቴክኒክና ሙያ ስልጠናን ከማስፋፋት አንጻር በመንግስት በግል ዘርፍና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ተቋማትን የማስፋፋት ስራ በማከናወን የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋማትን ቁጥር አሁን ካለበት 1,329 ወደ 1,778 ለማሳደግና በዚህም በሀገሪቱ ዉስጥ በሚገኙ ሁሉም ወረዳዎች ቢያንስ አንድ ተቋም እንዲኖር ለማድረግና በዚህም የመደበኛ ሰልጣኞችን ቅበላ አሁን ካለበት 408,838 ወደ 598,729 ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

በሙያው የሰለጠኑ በቂ ሙያተኞችን ከማፍራት አንጻር ከሁሉም የልማት ኘሮግራሞች ውስጥ 50 በመቶው የሙያ ደረጃን የስራ መመሪያቸው አድርገው እንዲጠቀሙ ግብ ተጥሏል፡፡ የኢንዱስትሪ መዛኞችን ከማፍራት አንጻር ከ8ቱም ዘርፍ መሪ መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን አሁን ያለውን 29,838 የኢንዱስትሪ መዛኞች ወደ 61,112 ለማሳደግ እና በዘርፎች/በኢንዱስትሪው ከተሰማሩ በቴ/ሙ/ት/ስ/ ማዕቀፍ ከሚገኙ ሙያተኞች የ50 በመቶዎቹን ብቃት በምዘና ለማረጋገጥ ታቅዷል፡፡ በሌላም በኩል መደበኛ ስልጠና አጠናቀው ወደ ስራ ዓለም ከሚወጡ ዕጩዎች በምዘና ብቁ ሆነው ለኢንዱስትሪው የሚቀርቡ መጣኔን አሁን ካለበት 60 በመቶ ወደ 75 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች በምርት/አገልግሎት አቅርቦት በገበያ ተወዳዳሪ ለማድረግ ከእሴት ሰንሰለት ትንተና በመነሳት የተሸጋገሩ አዋጭ ቴክኖሎጂዎች አሁን ካለበት 3,000 ወደ 5,442 ለማድረስ እና በትኩረት ዘርፎች የተሰማሩ ነባር ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች በገበያ ተወዳዳሪ ለማድረግ በተሰጠ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የበቁ ጥ/አ/ኢንተርፐራይዝ አንቀሳቃሾች ቁጥር አሁን ካለበት 42,216 ወደ 342,310 ለማድረስ ታቅዷል፡፡

### 3.3. የከፍተኛ ትምህርት

የትምህርት ተሳትፎን ለማሻሻል የቅድመ ምረቃ መደበኛ ተማሪዎች ዓመታዊ ተሳትፎ ቁጥር በ2007 ካለበት 387565 ወደ 597685 ማሳደግ በዚህም የከፍተኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ 15% ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ የድህረ ምረቃ (የሁለተኛ ዲግሪ) ተሳትፎ ወደ 56000 የሶስተኛ ዲግሪ (ዶክትሬት ዲግሪ) ተሳትፎ ወደ 6500 ያድጋል፣ በዚህም ከአጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች የድህረ ምረቃ ድርሻ 10 በመቶ ይደርሳል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ በቅድመ ምረቃ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ በ2007 ካለበት 32 በመቶ በ2012 ወደ 45 በመቶ፣ በድህረ ምረቃ (ሁለተኛ ዲግሪ) በ2007 ዓ.ም ካለበት 22 በመቶ ወደ በ2012 ዓ.ም ወደ 35 በመቶ፣ በሶስተኛ ዲግሪ ደግሞ በ2007 ዓ.ም ካለበት 11 በመቶ ወደ 20 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጧል፡፡ እንዲሁም ከድህረ ምረቃ ትምህርት ውስጥ የሶስተኛ ዲግሪ ተሳትፎ ድርሻ 15% ለማድረስ ታቅዷል፡፡

የትምህርት ጥራትና አግባብነትን ለማስጠበቅ የ70፡30 የሳይንስና ቴክኖሎጂ እና የማህበራዊ ሳይንስ ምጣኔ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ እያንዳንዱ ተቋም ከአብዛኞቹ ሌሎች ተቋማት የሚለይበት እና የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታን ያማከለ ከ1 እስከ 3 የልህቀት መስክ ለይቶ ይተገብራል፡፡ ጥራትን በውጤታማነት ለማረጋገጥ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች የመመረቅ ምጣኔ 95 በመቶ ይደርሳል፡፡ ለዚህም ሁሉም ሥርዓተ ትምህርቶች በተቀናጀ የብቃት ተኮር ትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት መሠረት ይከለሳሉ፡፡

የመምህራን ልማትን በማጠናከር ጥራትን ለማሳደግ የመምህር ተማሪ ጥምርታ ወደ 1:19 ያድጋል፡፡ የመምህራን ብዛትም ወደ 33,030 ይደርሳል፡፡ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው የበቁ መምህራን ብዛት በ2007 ዓ.ም. ከነበረበት 58 በመቶ በ2012 ወደ 75 በመቶ፣ ሦስተኛ ዲግሪ ያላቸው በመማር ላይ ያሉና ያጠናቀቁ መምህራን ብዛት በ2007 ዓ.ም. ከነበረበት 15 በመቶ በ2012 ወደ 25 በመቶ ያድጋል፡፡

ከትምህርት ደረጃ ማሳደግ ባለፈ ሁለንተናዊ አቅም ለመፍጠር ሀገራዊ መስፈርትን መሰረት ያደረገ የመምህርነት ሙያ ብቃት መጨበጣቸው የተረጋገጠላቸው መምህራን ድርሻ 60 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፡፡

በመምህርነትም ፍትሃዊነት ለማሳደግም በከፍተኛ ትምህርት የሴት መምህራን ተሳትፎ በ2007 ዓ.ም ካለበት 12 በመቶ ድርሻ ወደ 25 በመቶ ለማሳድግ ግብ ተጥሏል።

የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ለማሳደግ (የሶስተኛ) ዲግሪ ደረጃ ያላቸው መምህራን ቁጥር እስከ 2005 ዓ.ም ከደረሰበት 2590 በ2012 ዓ.ም መጨረሻ በድምር 9909 ለማድረስ፣ በምርምር ላይ የሚሳተፉ መምህራን ድርሻ በ2005 ዓ.ም ካለው 10 በመቶ ወደ 40 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተቋም አመራር፣ አደረጃጀትና አሰራር ለማጠናከር አንድ ሀገራዊ የዩኒቨርሲቲዎች የከፍተኛ አመራር አቅም ግንባታ ማጎልበቻ ማዕከል ይቋቋማል። ሁሉም የክላስተር አስተባባሪ ተቋማት በምድባቸው ውስጥ ባሉት ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኘውን የመካከለኛ አመራር አቅምን በተከታታይ የሚገነቡበት ማዕከል ይመሰርታሉ። ሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የታችኛውን አመራር አቅም በቀጣይነት የሚገነቡበት ማዕከላት ያደራጃሉ። የሴት ከፍተኛ አመራር ተሳትፎ በ2005 ዓ.ም ካለበት ከ1 በመቶ ያነሰ ምጣኔ ወደ 25 በመቶ እንዲደርስ ይደረጋል።

## 4. የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

### 4.1. አጠቃላይ ትምህርት

የማስፈጸም አቅም ግንባታ ፕሮግራምን በመቅረጽና በመተግበር የመጀመሪያ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም ለማዳረስ የተያዘው ዕቅድ በአንድ በኩል መንግሥት የአቅም ግንባታና የመልካም አስተዳደር ፕሮግራሞችን በመቅረጽ የትምህርት ፖሊሲው በፈጻሚው በኩል በግልጽ ታውቆ እንዲተገበር በሌላ በኩል የዘርፉ ልማት በህብረተሰቡን ሙሉ ተሳትፎ የተደገፈ እንዲሆን በማድረግ ትምህርት እንዲስፋፋ ይደረጋል። ለዚህም ፖሊሲውን መሠረት በማድረግ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፣ የትምህርት ጥራትን የማስጠበቅ አፈጻጸሙንም የሚደግፉ ግብዓቶችን የማቅረብ፣ የትምህርት ጥራት ፓኬጆችን የመተግበር፣ ደረጃዎችን የማውጣትና የመከታተል ተግባራት ይከናወናሉ። በሌላም በኩል ተግባር ተኮር የሆነ የጎልማሶች ትምህርት በሁሉም አካባቢዎች እንዲዳረስ ይደረጋል።

የትምህርት ጥራትና ተገቢነትን ለማሻሻል በተቀናጀና በተደራጀ የትምህርት ልማት ሠራዊት ፓኬጁን መተግበር፣ የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት ማስፋፋት፣ ድጋፍ የሚሹ አካባቢዎችና የታዳጊ ክልሎች ነባር ብሔረሰብ የመምሕራን ቁጥር እንዲጨምር ይደረጋል። በየአካባቢው የመምህራን እጥረትን በመቅረፍ የትምህርት ጥራትን ማሻሻል፤ ሥርዓተ ትምህርቱን ከቴክኖሎጂ፣ ከዘላቂ ልማትና ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ አጋርነት መርሆች ጋር እንዲገናዘብ የማድረግ ሥራዎች ይሠራሉ።

የትምህርት ፍትሐዊነትና ተደራሽነትን ለማጐልበት የቅድመ መደበኛ ትምህርት የፖሊሲ ማዕቀፉንና ስትራቴጅውን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ፣ የተፋጠነ የዝግጁነት መርሐ ግብር አተገባበር መመሪያ በማዘጋጀት የቅድመ መደበኛ ትምህርትን አጠናክሮ መተግበር፣ ህዝቡንና ባለድርሻ አካላትን በልማት ሠራዊት አደረጃጀቶች በማሳተፍ የት/ቤቶችን ቅርበትና የርስ በርስ ትስስር ማሳደግ፣ በሥራ ላይ የሚገኙትን የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት ወደ መደበኛ የ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ማሳደግና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተጨማሪ ማዕከላትን መክፈትና ማጠናከር፣ የተጋላጭ ህጻናትን፣ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ህጻናት ትምህርት ተሣትፎን ለማሳደግ በወጣው ስትራቴጂ መሠረት አማራጭ የአገልግሎት አሰጣጥ ስልቶች እንዲስፋፉ ይደረጋል። የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎን ለማሳደግ የሚያስችል የማስፋፊያ ጥናት በማድረግ ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎትና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቅበላ አቅም መሰረት ያደረገ የአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ (9-10) እና የ2ኛ ደረጃ የመሰናዶ (11-12) ትምህርትን የማስፋፋት ሥራዎች ይሠራሉ። ተግባር-ተኮር የጎልማሶች ትምህርት እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጂዎች ተጠናክረው እንዲተገበሩ ይደረጋል።

## 4.2. ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና

ልማቱን ፈጣን ቀጣይና ፍትሃዊ ለማድረግም በየትኩረት መስኩ ተፈላጊውን የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ ለማቅረብ ውጤት ተኮር ስልጠና በጥብቅ ይተገበራል፡፡ የሙያ ደረጃ ምደባንና ብቃት ምዘናን በቀጣይ የኢንዳስትሪው ቻምበሮች በባለቤትነት እንዲመሩ በሚያስችል መንገድ ተደራጅተው ሚናቸውን መወጣት ወደሚችሉበት ደረጃ እንዲደርሱ ከህዝብ ክንፍና ተጓዳኝ መስሪያ ቤቶች ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡

የመደበኛና አጫጭር ስልጠና ፕሮግራም አጠናቃቂዎች ፕሮጀክት ቀርፀው፣ ተደራጅተው፣ መነሻ ካፒታል ቆጥበውና የሙያ ብቃታቸውን በምዘና በማረጋገጥ የሚሸጡትን ቴክኖሎጂ ይዘው እንዲወጡ በማድረግ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መፍለቂያ መሆናቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ ይመራል፡፡ በሌላም በኩል የተጀመረውን የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አደረጃጀት በማጠናከርና ቴክኖሎጂ ስራዊት በመፍጠር ፈጣን ልማትን ማስቀጠል በሚያስችል አካሄድ በየዘርፉ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በገበያ ተወዳዳሪ ማድረግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን ለይቶ በማቅረብና ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በማስተሳሰር አቅማቸውን የማሳደግ ይሰራል፡፡ አሰልጣኞችን በሁሉም ደረጃዎች ማለትም በA, በB እና በC ደረጃ በማፍራት አሁን ካለበት 32,977 አሰልጣኞች ወደ 68,488 አሰልጣኞች ለማድረስ ታቅዷል፡፡

## 4.3. የከፍተኛ ትምህርት

የተሳትፎ ግብን ታሳቢ በማድረግ የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቁጥርና የቅበላ አቅም እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ የመሰናዶ ትምህርት ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት በተሻለ ብቃት እንዲሸጋገሩ ለማድረግ ዩኒቨርሲቲዎችና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በተለይ በሳይንስና ሂሳብ መስኮች ላይ ትኩረት ሰጥተው በቅንጅት እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቅበላ አቅማቸውን ለማሳደግ እንዲችሉ ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ የትምህርት ፕሮግራሞች አከፋፈትና ክለሳ ከሀገራችን የሰው ኃይል ልማት ፍላጎት አቅጣጫ ጋር መጣጣማቸውን በሀገር አቀፍ የትምህርትና ሥልጠና ብቃት ማዕቀፍ ይረጋገጣል፡፡ ሁሉም ተቋማት ከሀገራዊ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ መረብ ተገናኝተው አለም አቀፍና አህጉር አቀፍ የትምህርትና የምርምር መረጃ በጋራ እንዲጠቀሙ ይደረጋል፡፡ የመምህራን አቅም ግንባታ ግብ ለማሳካት የድህረ ምረቃ ፕሮግራም እንዲስፋፋ በማዕከል ደረጃ ታቅዶ ይፈፀማል፡፡ ተከታታይነት ያለው የዩኒቨርሲቲ መምህርነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ስርዓት ይዘጋጃል፡፡ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማዕከል ያደረገ ሃገራዊ የከፍተኛ ትምህርት የምርምር አቅጣጫ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በጋራ ይሰራል፡ ፡ ሀገራዊ የከፍተኛ ትምህርት የአመራር አቅም ማበልፀጊያ ማዕከል ይደራጃል፡፡ ውጤታማ እና ቀልጣፋ የበጀት ድልድል እንዲኖር የጥቅል በጀት ቀመር ተዘጋጅቶ ተግባር ይደረጋል፡፡ ሃገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ዓለም-አቀፍ የግንኙነት ማእቀፍ ይዘጋጃል፡፡ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ በአለም አቀፍ መስፈርት መሰረት የመማር ማስተማሩን ትግበራ ከእውቀት እና ቴክኖሎጂ ማመንጨት ተልእኮዋቸው ጋር እንዲያቀናጁ ይደረጋል፡፡ ዘመናዊ አደረጃጀትና አሰራር ለመገንባት በለውጥ መሳሪያዎች ዙሪያ የተጀመሩት የሪፎርም ስራዎች ተቋማዊ ባህል ሆነው በዘላቂነት እንዲቀጥሉ ይደረጋሉ፡፡ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ከማስፋፋት ጎን ለጎን ጥራቱን የመጠበቅና ማሳደግ ሥራ ይሠራል፡፡

## 3.2.2. ጤና ዘርፍ ልማት

### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

የጤናውን ዘርፍ ተልዕኮ፣ ራዕይና ስትራቴጂ ለማሳካትና የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሚከተሉት የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡

ፍትሐዊ፣ ተደራሽ እንዲሁም ጥራቱን የጠበቀ የመሰረታዊ ጤና አገልግሎት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና እንክብካቤ በሁሉም የጤና ስርዓት ደረጃዎች ተጠናክሮ እንዲተገበር በማደረግ የላቅ

የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ዕውን ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡ በመረጃ ላይ የተመሠረተ የጤና ፖሊሲ ቀረጻ፣ ዕቅድ አወጣጥና ክትትልና ግምገማን እውን ለማድረግ የጤና ልማት ሠራዊትን በማጠናከር በዘርፉ ልማት የማሕበረሰብ ባለቤትነት የማረጋገጥ ስራ ይሠራል፡፡ በዚህም የዘርፉን አመራርና መልካም አስተዳደር ተግባራዊ የማድረግ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ የዘርፉን ልማት ለማፋጠን የሚያስፈገውን የሰው ኃይል፣ የፋይናንስ፣ የጤና መሰረተ ልማትና ጥራትና የላቀ ቴክኖሎጂን የሚጠቀም የጤና አገልግሎትን ለተገልጋዩ ለመስጠት የሚያስችል የጤና ተቋማትን ዘመኑ ባፈራቸው የሕክምና መሳሪያዎችና መድሐኒቶች ማሟላት እንደ አቅጣጫ ተይዟል፡፡

## 2. ዓላማዎች

የዘርፉ አጠቃላይ ዓላማ ፍትሐዊ፣ ተደራሽነትና ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት በማቅረብና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ህብረተሰቡ የራሱን ጤና ከተለያዩ የጤና ጠንቆች እንዲጠብቅ ማስቻል ነው፡፡ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የጤና ዘርፍ ዋነኛ ዓላማ ህብረተሰቡን በተለይ የእናቶችን፣ የህፃናትንና የወጣቶችን የጤና ሁኔታ ማሻሻል ሲሆን ይህም ጥራት ያለው የጤና ማበልጸግ፣ በሽታን መከላከል፣ የፈውስ ህክምና እና የድንገተኛ ጤና አገልግሎቶችን ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ማዳረስ እና ጤናማ የሆነ የአኗኗር ልማዶችን በግለሰብና በኅብረተሰብ ደረጃ ለማስረጽ የሚያስችል ጠንካራ የጤና ስርዓት እንዲገነባ ማድረግ ነው፡፡

## 3. ዋና ዋና ግቦች

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከላይ የተዘርዘሩቱን የዘርፉን ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተጥለዋል፡፡ አነዚህም፡-

**ጥራት ያለው ጤና አገልግሎት ተደራሽነትን በማሻሻልና በመከላከል** ላይ መሠረት ያደረግ የጤና ፖሊሲን፣ የሥርዓተ-ምግብ ስትራቴጂን አጠናክሮ በመተግበር የመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ሽፋንን ከ93 በመቶ ወደ 100 በመቶ ከፍ እንዲል ግብ ተጥሏል፡፡ በዚህም የህዝቡን የመኖር ዕድሜ (Life Expectancy) በ2007 ከነበረበት 64.6 በ2012 ወደ 69 ዓመት ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡

**የስነ-ተዋልዶ፣ የወጣቶች፣ እናቶችና ህፃናት ጤናን ከመጠበቅ** አንጻር ባለፉት ዓመታት መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ ሲተገብር ቆይቷል፡፡ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ከማሳካት አንጻር የሕፃናት ሞትን ከመቀነስ ረገድ አመርቂ ውጤት ቢመዘገብም የዕናቶችን ሞት ከመቀነስ ረገድ ግን ፈታኝ እንደነበር የእስካሁኑ አፈጻጸም አመላክቷል፡፡ የጤና መሠረተ-ልማትን ከማስፋፋት ጎን ለጎን የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራቱን በመጨመር የእናቶች ሞት ምጣኔን በ2007 ከነበረበት 420/100000 በ2012 ወደ 199/100000 ለመቀነስ ታቅዷል፡፡ በተመሳሳይ አጠቃላይ የውልደት መጠንን (Total Fertility Rate) ከ4.1 ወደ 3 ዝቅ ለማድረግ ግብ ተጥሏል፡፡ ለዚህም የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ምጣኔ (CPR) ከ42 በመቶ በ2012 ወደ 55 በመቶ ከፍ ለማድረግ፣ የቅድመ ወሊድ ክትትል በዕርግዝና ጊዜያቸው 4 ጊዜ ያገኙ ነፍሰ ጡር እናቶች ሽፋንን ከ32 በመቶ ወደ 95 በመቶ የማድረስ እቅድ ተጥሏል፡፡ በሰለጠኑ ባለሙያዎች በመታገዝ የወሊድ አገልግሎ ያገኙ እናቶች ሽፋን ከ41 በመቶ ወደ 95 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

**የሕጻናት ጤንነትን ከመጠበቅና ከመንከባከብ አንጻር** ከ5 ዓመት በታች ያሉ የህፃናት ሞት መጣኔን በ2007 ከነበረበት 68/1000 በ2012 ወደ 30/1000፣ ዕድሜአቸው ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ የህፃናት ሞት መጣኔ በ2007 ከነበረበት 46.4/1000 በ2012 ወደ 19.3/1000 መቀነስ ግብ ተጥሏል፡፡ እንዲሁም በህይወት የሚወለዱ የጨቅላ ህፃናትን ሞት(Neonatal Mortality Rate) መጣኔ በ2007 ከነበረበት 27/1000 በ2012 ወደ 10/1000 ዝቅ ለማድረግ፣ ከ5 ዓመት በታች ያሉ የህፃናት መቀጨጭ/መቀንጨር (Stunting) እና የህፃናት ክብደት መቀነስ (Wasting) በቅደም ተከተል በ2007 ከነበረበት 40 በመቶ እና 9.7 በመቶ በ2012 ወደ 21 በመቶ እና 4.9 በመቶ ለመቀነስ ታቅዷል፡፡ ይህን ግብ ለማሳካት ኤች አይ ቪ ኤድስ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሐኒት የሚወስዱ እናቶች ሽፋን ከ87 በመቶ ወደ 100 በመቶ

ለማሳደግ፣ የፕንታቫለንት ሶስት ክትባት ሽፋን ከ82 በመቶ ወደ 96 በመቶ ለማሳደግ፣ የኩፍኝ ክትባት ያገኙ ህጻናት ሽፋን ከ83 በመቶ ወደ 95 በመቶ ለማድረስ እና ሙሉ ለሙሉ ክትባት ያገኙ ህጻናት መጠን ከ77 በመቶ ወደ 95 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡ እንዲሁም ዕድሜያቸው ከ6-59 ወር የሆኑ ህፃናት የሚሰጠውን የቫይታሚን ኤ እንክብል ወደ 95 በመቶ ለማድረስ፣ በአዮዱን የበለጸገ ጨው የሚጠቀሙ ቤተሰብ ሽፋንን ከ15 በመቶ ወድ 80 በመቶ ለማድረስ እንዱሁም የሕብረተሰብ አቀፍ ሥርዓተ ምግብ ፕሮግራሞችን እንዲስፋፉ ታቅዷል፡፡

**ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ቁጥጥርን በተመለከተ** ለአዋቂዎች የሚሰጠውን የፀረ-ኤች.አይ.ቪ መድሐኒት ሽፋንን ወደ 90 በመቶ እንዲሁም ለሕጻናት የሚሰጠውን የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሐኒት ሽፋንድ 80 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ እንዲሁም በኤችአይቪ/ኤድስ ቫይረስ አዲስ የሚያዙ ሰዎችን መጠን (HIV/AIDS Incidence) በ2007 ከነበረበት 0.03 በመቶ በ2012 ወደ 0.01 በመቶ ዝቅ እንዲል ግብ ተጥሏል፡፡ የሁለም አይነት የቲቢ በሽታ ልየታን መጠንን ከ58 በመቶ ወደ 87 በመቶ ለማሳደግ፣ መድሐኒት የተላመደ የቲቢ በሽታ ልየታ ከ70 በመቶ ወደ 90 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ እንዲሁም በቲቢ ህክምና ሙሉ በሙሉ የዳኑ የቲቢ ሕሙማን መጣኔን ከ71 በመቶ ወደ 90 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡ በሌላ በኩል የወባ በሽታ ክስተትን በ75 በመቶ ለመቀበስ ታቅዷል፡፡ የስጋ-ደዌ በሽታን የማጥፋት ስትራቴጂን በመተግበር በሽታውን ሙሉ ለሙሉ የማጥፋት እቅድ ተይዟል፡፡ የጤና እና ጤና ነክ አደጋዎችን ከማስተዳደር አንጻር አስጊ በሽተኞችን ሙሉ ለሙሉ የመለየትና በልዩ ሁኔታ የመርዳት፣ ድጋፍ የተደረገላቸው በአደጋ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ በላቦራቶሪ የተረጋገጡ ወረርሽኞችን መቶ በመቶ ለማዳረስ ታቅዷል፡፡

**የአካባቢ ንጽሕና እና ጤናን በሚመለከት** የተሻሻለ የመጸዳጃ ቤት ያላቸው አባወራዎች/እማዎራዎች ሽፋንን በ2007 ከነበረበት 21 በመቶ በ2012 ወደ 93 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ በዚህም በየሜዳ ከመጸዳዳት ነጻ የሆኑ ቀበሌዎች ሽፋን ከ18 በመቶ ወደ 82 በመቶ የማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡

## 4. የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

4.1 **የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በዘላቂነት እና በየደረጃው በተጠናከረ መልኩ ማካሄድ፡-** ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ለማዳረስ በየደረጃው የአቅም ግንባታ ስራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ በዘርፉ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እና የዘርፉን አመራር አቅም መገንባት ሌላው የማስፈጸሚያ ስልት ሆኖ ይተገበራል፡፡ የጤናውን ዘርፍ ስርዓት ለማስፈን የጥናት እና ምርምር ውጤቶች ሥርፀት ይጠናከራሉ፡፡ በመረጃ የተደገፉ ወቅታዊ ውሳኔዎችን ለማሳለፍም ሆነ የረጅም ጊዜ ስልቶችን ለመቀየስ በጤናውም ሆነ ተያያዥነት ባላቸው ዘርፎች ውስጥ የሚደረጉ ምርምሮች የሚጎለብቱበት አሠራር ይዘረጋል፡፡ ለዚሁ አላማ ይረዳ ዘንድ የጤና አገልግሎት መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ትኩረት ተሰጥቶት የመረጃዎቹ አደረጃጀትና ተደራሽነት የበለጠ እንዲሻሻሉ ይደረጋሉ፡፡ የባለ ብዙ ዘርፎች ዕቅድን በማካተት የትብብር ስራዎች በታለመለት መልኩ ለመተግበር እንዲሁም የጤና አገልግሎት ቁጥጥርን በተገቢው መንገድ ለማከወን ክህሎትን የማዳበር ስራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡ ፡ የተጠቀሱትን የአቅም ማጎልበት ስራዎች በዘላቂነት እና በየደረጃው ለመፈፀም አገር በቀል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ከቴክኖሎጂ ጋር በማዋሀድ የመጠቀም ሥልት ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

4.2 **ህብረተሰቡን አሳታፊና ባለቤት ያደረገ የጤና ዘርፍ ስርዓት ግንባታን አጠናክሮ መቀጠል፦** የሕዝብ ንቅናቄን የበለጠ ለማጎልበት እና ከህብረተሰቡ ፍላጎት ጋር የሚራመድ ማህረሰብ-አቀፍ የጤና አገልግሎትን በሰፊው ለማስረጽ የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

4.3 **የመሠረታዊ ጤና ክብካቤ እና ከሆስፒታል አገልግሎቶች የሚኖራቸውን ትስስር ማጠናከር፦** የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት አሰጣጥን ከተጠቃሚው ህብረተሰብ ፍላጎት አንፃር በየወቅቱ በመፈተሽ የጤና አገልግሎት ፓኬጆችን እና አተገባበራቸውን የማሻሻል ሥራ ይሠራል፡፡ በመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ውስጥ የሚካተቱ የአገልግሎት አይነቶች ብዛትና ጥራት የህብረበተሰቡን ፍላጎት እና

አገልግሎቶቹን የማቅረብ አቅምን ባገናዘበ መልኩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡ የመሠረታዊ ጤና ክብካቤ ከህክምና አገልግሎት አሰጣጥን ሰንሰለት ጋር የሚኖረውን ትስስር የሚጠናከር ይሆናል፡፡

4.4 **የሰው ሃብት ልማትን ማጠናከር፡-** የሰው ሃብት ብዛት እና ጥራትን እንዲሁም ስብጥርን ከጤናው ዘርፍ ፍላጎት፣ ከሀገሪቱ አቅም አንፃር እንዲሁም ከሌሎች ተዛማጅ ስራዎች /ለምሳሌ የጤና ተቋማት መስፋፋት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቅበላ አቅም/ ጋር በተጣጣመ መልኩ በማቀድ ወደ ታለመለት ግብ በጥንቃቄ መንዝ ያስፈልጋል፡፡ የሁለተኛው ምዕራፍ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የከፍተኛ ጤና ባለሙያዎችን ፍልሰት ለመግታት በጥናት የተደገፈ የረጅም ጊዜ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል የማቆያ ስርዓት ይዘረጋል፡፡ ለግንባር ቀደም እና ለመካከለኛ ጤና ባለሙያዎች ግልጽ የሆኑ የዕድገት መሰላል መስመሮችን የመንደፍና አተገባበራቸውን የማቀላጠፍ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ የሰው ሃብት ልማት መረጃ አያያዝና አጠቃቀምን በዘመናዊ መልክ የማደራጀት ሥራዎች በመደገፍ ይተገበራሉ፡፡

4.5 **የግሉ ዘርፍ በጤና አገልግሎት ስርዓት ውስጥ የሚኖረውን ሚና ማሳደግ፡** የግል ባለሀብቶች በሆስፒታል፣ በመድሀኒትና ህክምና መገልገያ ቁሳቁስ ማምረት እና በሌሎች በዘርፉ ክፍተት በሚታይባቸው መስኮች ላይ እንዲሠማሩ በመንግስት የኢንቨስትመንት አቅጣጫ መሠረት በጤናው ዘርፍም ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያበረታቱ አሠራሮች ይዘረጋሉ፡፡ አገር በቀል የሲቪክ ማህበራትም የአገልግሎት ተደራሽነትንና ጥራትን ለማረጋገጥ በሚደረገው ርብርብ ውስጥ ከተቋቋሙለት አላማ በመነሳት ፋይዳ ያለው አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፡፡ በጤና ፖሊሲው በተጠቀሰው መሠረት ብዙ ያልተሰራበት የባህላዊ ህክምና ዘርፍም የበለጠ ትኩረት ይሰጣል፡፡

4.6 **የጤና ዘርፍ የገንዘብ ሥርዓትን አስተማማኝ ማድረግ፡-** የጤና ዘርፍ ወጪዎችን በአገር ውስጥ ምንጭ በአስተማማኝ ሁኔታ ለመሸፈን የሚደረገው ጥረት ከመቼውም ጊዜ በላቀ መልኩ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡ በእርዳታ የሚገኙ ሀብቶችም በመንግስትም ሆነ በአጋሮች በኩል ግልጽና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ለታለመለት አላማ መዋሉ ይረጋገጣል፡፡ ተግባራዊ የሚሆነው የጤና መድህን ስርዓት የጤናውን ዘርፍ በገንዘብ ከመደገፉም በላይ ህብረተሰቡን ከከፍተኛ የህክምና ወጪ እንዲታደግና የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆንበት አሠራር ይተገበራል፡፡

### 3.2.3 ሳይንስና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ

### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

በዕቅዱ ዘመን በሳይንስና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ረገድ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የቴክኖሎጂ ፍላጐትን መለየት፣ አግባብነት ያላቸውን እሴት አከል የቴክኖሎጂና ተዛማጅ መረጃዎችን በማደራጀትና በመተንተን አገልግሎት መስጠት፣ ቴክኖሎጂዎችን ለመቅዳት ወይም ለማላመድ እንዲያስችል የድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት፣ መደገፍና መከታተል እንደ አቅጣጫ ተይዟል፡፡ በምርምርና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ በኩል የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ባላቸው ዘርፎች የምርምር ማዕከላትን የማቋቋም፣ የምርምር መሠረተ ልማትን የማሟላትና የምርምርና ቴክኖሎጂ ፕሮጀክቶችን መደገፍ ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡ የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ በሀገር ደረጃ ምርምርና ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት የቴክኒክ ክህሎትና ሳይንሳዊ ዕውቀትና ብቃት ያለውን የሰው ኃይል ማፍራት እና በቂ አቅም መፍጠር፣ በጥራትና ብቃት፣ በተስማሚነትና ምዘና ዘርፍ፣ በሳይንስ፣ ቴክኖጂና ኢኖቬሽን መረጃ ልማት፣ በአእምሮአዊ ንብረት ጥበቃና ልማት ዙሪያ የሚተገበሩ ሌሎች የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

### 2. ዓላማዎች

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የሳይንስና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ዘርፍ የዕቅዱ ዓላማዎች ውጤታማ የሆኑ የውጭ ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለማላመድና

አሟጦ ለመጠቀም የሚያስችል የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕቀፍ ማዘጋጀት እና ሀገራዊ የምርታማነት አቅም መፍጠር፣ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን የሚደግፍ የጥራት መሰረተ ልማት አቅምን በማሳደግ ምርቶቻችንና አገልግሎቶቻችን በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ በጥራት እና በዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል፣ ልዩ ልዩ ፓኬጆችን እና የለውጥ ፕሮግራሞችን በመተግበር የቴክኖሎጂ ሽግግሩን ማፋጠን እንዲሁም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው በፍጥነት እንዲያድግና በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነት ሚናውን እንዲጫወት የተቋቋሙ የአቅም መገንቢያ ተቋማትን አቅም መገንባት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 3. ዋና ዋና ግቦች

ሀ) **በዕቅድ ዘመኑ (2008-2012) የኢኖቬሽን ስርዓት ዝርጋታ እንዲጠናከር በማድረግ ረገድ ፡-** በዚህም በተመረጡ የልማት መስኮች ሴክተር ተሻጋሪ የልማት ማነቆዎችን በምርምር ለመፍታት ብሄራዊ የምርምር አቅም መፍጠር፣ በተመረጡ የልማት መስኮች ባዮቴክሎጂን ለመጠቀም የሚያስችል ብሄራዊ አቅም መፍጠር፡ የህዋ ሳይንስና ቴክኖሎጂን ለልማት መጠቀም የሚያስችል አቅም መገንባት፣ ለምርምር የሚመደበው በጀት እየደገ እንዲመጣ የሚመደበው በጀት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2007 ከነበረበት 0.61 በመቶ ወደ 1 በመቶ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መረጃዎችን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በማሰባሰብ በማደራጀትና በመተንተን እሴት አክል መረጃዎች ለቴክኖሎጂ ሽግግር ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረግ ሲሆን መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች የምርምር ዩኒቶች እንዲያቋቁሙ ይበረታታሉ፡፡

ለ) **የቴክኖሎጂ ሽግግር አቅምን ለመገንባት የሚችል የላቀ ክህሎት ያለው የሰው ሀይል በመገንባት ረገድ፡-** በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ የ70፡30 ምጣኔ ስርዓት ቀጣይነት እንዲኖረው እና በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተማሪዎች በሂሳብና በሳይንስ የትምህርት ዓይነት ዝንባሌያቸው እንዲያድግ የመደገፍ እና የማበረታታት ሥራ ይሠራል፡፡ የዩኒቨርሲቲ፣ የምርምር ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስርን በማጠናከር በሃገር ውስጥ ባለሃብት እና በውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት አማካኝነት የገቡ የውጭ ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን ለማላመድ እና አሟጦ ለመጠቀም የሚያስችል የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕቀፍ ይፈጠራል፡፡ በዩኒቨርሲቲዎች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንኩቤሽን ማዕከላት እንዲቋቋሙ ድጋፍ የማድረግ፤ በሜጋ ፕሮጀክቶች ላይ የተግባር ልምምድ ያደረጉና ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን መማር፣ ማላመድ እና መጠቀም የሚችል እና ችግር ፈቺ የሆኑ ምርምሮችን ሊያካሂዱ የሚችሉ ተመራማሪዎችን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች የማፍራት ሥራ ይሠራል፡፡ የአእምሮ ባለቤትነት (የፓተንት) መረጃዎች፣ የጀኔቲክ ሃብቶችና አገር በቀል ዕውቀቶች ለቴክኖሎጂ ልማት እንዲውሉ የማድረግ፤ አረንጓዴ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት የመጠቀም እንዲሁም የጨረር አመንጪ ቴክኖሎጂዎች ህብረተሰቡን እንዳይጎዱ እና ጊዜያቸውን ሲጨርሱም በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርሱበት ሁኔታ እንዲወገዱ የማድረግ ተግባር ይከናወናል፡፡

ሐ) **የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ምርቶችና አገልግሎቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ በጥራትና በምርታማነት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል የጥራት መሰረተ ልማት አቅም በመገንባት ረገድ፡-** የጥራት መሰረተ ልማት የተቋማትን አቅም በማሳደግ እና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ በማስቻል የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ምርቶች እና አገልግሎቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ ከዚህ አንጻር አዳዲስ የምርት ደረጃዎችን በማዘጋጀትና በመከለስ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማገዝ፣ ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ ኢታሎኖች ወሰን ማስፋት፣ በተመረጡ የአለካክ፣ የፍተሻ፣ የሰርተፊኬሽን እና የኢንስፔክሽን መስክና ወሰን ዓይነቶች ዓለም ዓቀፍ ዕውቅና ማግኘት፣ የካሊብሬሽን እና የፍተሻ አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ፣ በፐርሶኔል ኮምፒተንሲ፣ የፍተሻ፣ የሰርተፊኬሽን እና የኢንስፔክሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን እክሪዲት ማድረግ፣ በዓለም አቀፍና አህጉራዊ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ተሳትፎን ማሳደግ ናቸው፡፡

*መ) **የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ሊደግፍ የሚችል የኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ ሰጪ ኢንስቲትዩቶች አቅም በመገንባት ረገድ፡-** በሁለተኛዉ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመን የነባር ተቋማት አቅም ያለማቋረጥ እንዲገነባ ማድረግና የታለመላቸውን ዓላማ ማሳካት የሚያስችላቸውን ድጋፍ ወቅቱ ከሚጠይቀው ፍላጎት ጋር በማስተሳሰር የመስጠት፣ ከፋሲሊቴሽን ይልቅ የተቋቋሙበትን ዓላማ በማስፈጸም ላይ እንዲያተኩሩና በዚህም አለምአቀፍ ደረጃን ያሟሉ የማድረግ ሥራዎች ይሰራሉ፡፡ ከዚህ አንጻር የሰው ኃይሉ ከፋሲሊቴሽን ይልቅ በምርምርና ስርፀት ላይ ትኩረት እንዲያደርግ፣ ቴክኖሎጂ ከመቅዳት በተጨማሪ ወደ ማሻሻልና ፈጠራ እንዲሸጋገር ማድረግ፣ የተቋማት ትስስርን በመፍጠር (ኢንዱስትሪውን ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከቴክኒክና ሙያ፣ ከምርምር ተቋማት) የሚፈለገው የሰው ኃይል ልማት የሚካሄዱበትንና በሥራ ላይም የሚሰለጥኑበት የምርምርና ስርጸት ስራዎች የሚዳብሩበት ሁኔታ እንዲመቻቹ ይደረጋል፡፡*

*አዳዲስ ለተቋቋሙት ኢንስቲትዩቶች (የምግብ፣ መጠጥና ፋርማሲዩቲካልስ፣ የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች፣ ሥጋና ወተት) መሰረተ ልማት ከማሟላት ጀምሮ የተሟላ ቁመና እንዲኖራቸው የማድረግ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ከዚህ አንጻር የኢንስቲትዩቶቹ አቅምና ብቃት በቁርኘት ፕሮግራም እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም አገሪቱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ መሰለፍ የምትችልበት ደረጃ ላይ ከደረሰች በኋላ ለሚኖረው ቀጣይ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ የኢንዱስትሪ መስኮችን (የባዮ-ቴክኖሎጂ፣ የመረጃና ኮሙኒኬሽን፣ የኤሌክትሪክ እና ኤሌክትሮኒክስ፣ የፔትሮ ሜካኒካል) መሰረት መጣል የሚያስችሉ አዳዲስ ተቋማትም የማደራጀት ሥራዎች በቀጣዩ የዕቅድ ዘመን የሚካሄዱ ይሆናል፡፡ ለማኑፋክቸሪንግ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚቀርበው የሰው ኃይል ከብዛት በተጨማሪ ጥራትን መሰረት ያደረገ እንዲሆን የተጀመሩ የኢንዱስትሪና የትምህርት ተቋማት ትስስር በአቅርቦት ፍላጎት ጥናቶች ግኝት መሰረት እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡*

## 4. የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

*ከላይ የተዘረዘሩትን ግቦች ለማሳካት የሚከተሉት ስትራቴጂዎች ተቀይሰዋል፡፡ እነዚህም፡- የኢኖቬሽን ሥርዓቱን ለማጠናከር ልምድ በመቀመር ተቋማዊ አደረጃጀቶችን መፍጠር፣ በኢኖቬሽን ስርዓቱ ተዋናዮች መካከል ያለውን ትስስር ማጠናከር፣ የቴክኖሎጂ መረጣ፣ ሽግግር አጠቃቀምና የአወጋገድ ሥርዓት መዘርጋት፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች የምርምር ዩኒቶች እንዲያቋቁሙ የማበረታታት ስልቶች ናቸው፡፡*

*በሁሉም ዘርፍ የተለዩ የለውጥ ፓኬጆች በጥራት የመተግበር ስልት ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ለዚህም የተጀመረውን የሠራዊት ግንባታ በተሟላ ሁኔታ መተግበርና እንደየፓኬጁ ባህሪይ የልማት አቅሞችን ለይቶ በተደራጀ ሁኔታ በውጤታማነት የማንቀሳቀስ፣ ፓኬጆችን መፈጸም የቴክኖሎጂ ሽግግርን መተግበር መሆኑን በአመለካከት ለመያዝ የሚያስችል የተጠናከረ ስራ የመሥራት፣ የተለያዩ የቴክኖሎጂ ፓኬጆችን ለመፈጸም የሚያስችል ተፈላጊ ክህሎት ፈጻሚው እንዲያግዝ ይደረጋል፡፡ የአደረጃጀትና የአሠራር ስርዓቱን ፈትሾ ተገቢውን ማስተካከያ የማድረግ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ እንዲሁም ትኩረት በተሰጣቸው የልማት መስኮች ላይ የሚካሄዱ ምርምሮችን አወዳድሮ መደገፍ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎችን አቅም በመሰረተ ልማት እና በሰው ሃይል የማጠናከር፣ የተመራማሪዎችን ቁጥር ማሳደግ፣ የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ ተቋማትንና ባለሙያዎችን የማበረታታት፣ አገር በቀል ዕውቀቶች ለቴክኖሎጂ ልማት እንዲዉሉ ማእቀፍ የመፍጠር ተግባራት ይከናወናሉ፡፡*

*የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከሉን ከሃገር ውስጥና ውጪ መሰል ተቋማት ጋር በመረጃ መረብ ማስተሳሰር፤ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማትን አቅም ማሳደግ፣ ምርቶች በደረጃ መሰረት እንዲመረቱ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፣ ተቋማት ወደ አክሪዲቴሽን እንዲመጡ ስርዓት መፍጠር፣ ስለ ጥራት መሰረተ ልማት በከፍተኛ ትምህርት ካሪኩለም ውስጥ በማካተት ስለጥራት ግንዛቤ ያለው አምራች ሃይል ማፍራት፣ ዓለም አቀፍ የውጭ ትብብር የዕውቀት ሽግግር የሚካሄድበትና የሰው ሃይል አቅም የሚገነባበት እንዲሆን አድርጎ የመመስረት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡*

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዉን ሊደግፍ የሚችል የኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ ሰጪ ኢንስቲትዩቶች አቅም በመገንባት ረገድ ሴክተሩን እንዲደግፉ የተቋቋሙት ተቋማት ብቃትና ክህሎት ያለዉ የአመራርና የባለሙያ አቅም እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ በኢንዱስትሪ ፍላጐት ላይ የተመሠረተ የዉስጥ አቅም ግንባታ ላይ ትኩረት በመስጠት አቅማቸው ይጠናከራል፡፡ በማኑፋክቸሪንግ (ጨርቃ ጨርቅ፣ ቆዳ፣ ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ)፣ በኢኮኖሚ መሠረተ-ልማት (ኮንስትራክሽን፣ ውሃና ኢነርጂ) ዘርፎች የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ላይ አትኩረው እንዲሰሩ የተለያዩ ኢንስቲትዩቶችን የምርምር አቅም ለማጠናከር ከሌሎች የምርምር ተቋማት ጋር ተቀናጅተው የሚሰሩበትና አቅማቸውን የሚያጠናክሩበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በተለይ ለብረታ ብረት ኢንዱስትሪ መሠረት ለመጣል ወሳኝ ሚና ያላቸውን ተቋማት (ሜቴክና በዙሪያው ያሉ ኩባንያዎችን) ትኩረት ሰጥቶ በመደገፍ የተጀመረውን የዲዛይንና ፋብሪኬሽን አቅማቸውን በማጠናከር ወደ ላቀ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

## 3.3 የማስፈፀም አቅም ግንባታና ልማታዊ መልካም አስተዳደር

### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

የሁለተኛው አምስት ዓመት የማስፈፀም አቅም ግንባታና ልማታዊ መልካም አስተዳደር የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻዎች በመጀመሪያ አምስት ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም የተገኙ ውጤቶችና ስኬቶች እንዲሁም በአፈጻጸም ሂደት የተገኙ ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም በመጀመሪያው የዕቅድ ዘመን ግምገማ የተለዩትን ክፍተቶችና ያልተጠናቀቁትን ተግባራት እንዲሁም መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች መሰረት በማድረግ ዕቅዱ አጠቃላይ አቅጣጫዎችንና የማስፈጸሚያ ስልቶችን ባካተተ መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡

መዋቅራዊ ለውጡን ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ መንግስታዊ መዋቅር በመፍጠር የሲቪል ሰርቪስ ሴክተር የልማት ዕድገቱ በሚጠይቀው ልክ የዜጎችና የመንግስትን ፍላጎት የሚያሳካ እንዲሆን የሚያስችል ርብርብ ይደረጋል፡፡ የሲቪል ሰርቪሱን አቅም በመገንባት እና ልማታዊ መልካም አስተዳደርን በማስፈን እንዲሁም ግልጽነትና ተጠያቂነትን በማስፈን ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነትን ከምንጩ በማድረቅ አገሪቱን ወደ ታለመው ራዕይ ለማድረስ አቅጣጫ ተይዟል፡፡ የሪፎርም ኘሮግራሞችንና ፓኬጆችን ተቋማዊ ባህል በማድረግ፣ ህገ መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በማክበርና በማስከበር ልማታዊ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍንና የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማጎልበት ህዝቡ የልማቱ ባለቤትና ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡

የታክስና የጉምሩክ አስተዳደር ሪፎርም ሥርዓቱን በተሟላ መልኩ በመተግበር ኢኮኖሚው ሊያመነጭ የሚችለውን ገቢ በወቅቱና በብቃት እንዲሰበሰብ ይደረጋል፡፡ በመንግስትና በግሉ ዘርፍ በሚታዩት ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ላይ በማተኮር የፀረ-ሙስና ትግሉ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በዚህም የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ከመሠረቱ ተንዶ የልማታዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የበላይነት እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡ ሌላው የትኩረት አቅጣጫ የባለድርሻ አካላትን ያረካ፣ ዘመናዊ፣ ፍትሃዊና በውድድር ላይ የተመሠረተ የንግድ ስርዓት በመዘርጋት ቀልጣፋና የላቀ የገበያ ማስፋፊያና ትስስር ስርዓት መገንባት እና የተፋጠነ አገራዊ የባለሀብት ትራንስፎርሜሽን እንዲረጋገጥ ማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የከተማ መሬት አስተዳደር ሥርዓትን በማጠናከርና ዘመናዊ በማድረግ መሬት ልማታዊ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ አቅጣጫ ተይዟል፡፡

### 2) ዓላማዎች

በዕቅድ ዘመኑ ህገ መንግስቱን በማስረፅ፣ የህግ የበላይነትን በማረጋገጥና ጠንካራና የተረጋጋ ፌዴራላዊ ስርዓት በመገንባት የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ፤ በለውጥ ሰራዊት ማዕቀፍ የለውጥ ሥራዎችን

በተሟላ መንገድ በመተግበርና ተወዳዳሪነትን በማጎልበት፣ ውጤታማ የፖለቲካ አመራርና ሲቪል ሰርቪሱን በመገንባት፣ ልማታዊ መልካም አስተዳደርን በማስፈን እና ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነትን ከምንጩ በማድረቅ የህዝቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡

## 3. ዋና ዋና ግቦች

### 3.1 የሰው ሀብት ልማትን ማጎልበት-

በፌደራል የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር እንዲሁም በክልሎች የሲቪል ሰርቪስ ቢሮዎችና በተዋረድ ያሉ ጽ/ቤቶች በአዋጅ የተሰጣቸውን ተግባርና ሀላፊነት መሰረት በማድረግ የማስተባበር፣ የመከታተልና የመደገፍ ስራቸውን አጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (በ2012 ዓ/ም) የመፈጸም አቅምን ደረጃ በደረጃ በማሻሻል የከፍተኛ፣ የመካከለኛ አመራሩ እና የፈጻሚውን ተልዕኮ የመፈጸም አቅም በአማካይ መቶ በመቶ /100%/ ለማድረስ ታቅዷል፡፡ሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ገብቶ የሚያገለግለው ሀይል የማልማቱ ጉዳይ ወደ ሲቪል ሰርቪሱ ከገባ በኋላ ከሚሰጡ ሥልጠናዎች በተጨማሪ ከምልመላው ሂደት ጀምሮ ብቁ አድርጎ ማዘጋጀት የሰው ሀይል ልማቱ የቅድሚያ አቅጣጫ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ባለፉት የልማት ዕቅድ ዘመናት ለሲቪል ሰርቪሱ በተለይም ለአመራሩ የአጫጭርና ረጅም ስልጠናዎችን በመስጠት ረገድ ትልቅ ሚና ሲጫወቱ የነበሩ ተቋማትን ለማጠናከር ታቅዷል፡፡ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመን በዕለት ተዕለት የአፈጻጸም ሂደት ጥሩ አፈጻጸም ያላቸውን የሚሸልምና የሚያበረታታ፣ የደከመውንና በቀጣይ ሊሻሻል የሚችለውን የሚደግፍ ከዚህ በታች የሆነውን ደግሞ አንገዋሎ የሚያወጣ አሰራር ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

### 3.2 የመንግስት ተቋማትን አሰራርና አደረጃጀት ውጤታማነት ማሻሻል

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ላይ ተቋማት በአደረጃጀትና በአሰራራቸው ሙሉ በሙሉ የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ኘሮግራሞች የአሰራር ሥርዓትና የተቋማት ባህል ሆነው ውጤታማነትን ማረጋገጥ የሚችሉበት ደረጃ ላይ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ ሁሉም ተቋማት በአሰራሮቻቸውና በአደረጃጃቶቻቸው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥን ባልተሸራረፈ መልኩ የተከተሉና የአገልግሎት አሰጣጣቸው ተገልጋዮችን የሚያረካ፣ ቀልጣፋና ተልዕኳቸውን በተሟላ ውጤታማነት መፈጸም የሚችሉ እንዲሆኑ አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ የውጤት ተኮር ስርዓት ትግበራው የተጠናከረ የመንግስት የአፈጻጸም አመራር ማዕቀፍ ይሆናል፡፡ ከላይ የተቀመጠው ዕቅድ አስተማማኝ በሆነ መልኩ እንዲፈጸም በዚሁ ግብ ስር የሚከናወነው ሌላው ተግባር መንግስታዊ አደረጃጀቶችን ከማጠናከር ጎን ለጎን ፈጻሚውን በለውጥ ሰራዊት አግባብ እንዲንቀሳቀስና የተጠናከረ የለውጥ ሰራዊት እንዲገነባ ማድረግ ነው፡፡

### 3.3 የአቅም መገንቢያ ተቋማት አቅምን ማሳደግ

የአቅም መገንቢያ ተቋማት ዋና ትኩረት የሲቪል ሰርቪሱን አመራርና ፈጻሚ በረጅምና በአጭር መርሀግብር ከማሰልጠን ጎን ለጎን በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲተገበሩ የቆዩትንና በመተግበር ላይ ያሉትን የተልዕኮ ማሳኪያ የለውጥ መሳሪያዎች መጀመሪያ በራሳቸው በተቋማቸው ላይ በመተግበር ከዚያም ሌሎች ተቋማት እንዲተገብሯቸው ለማድረግ የሚያስችል የስልጠና፣ የማማከርና የምርምር አገልግሎቶችን በመስጠት ድጋፍ ማድረግ ነው፡፡ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የአቅም መገንቢያ ተቋማትን የአቅም የማጎልበቱ ስራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡ በዚህም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ለውጡን የመደገፍ አቅማቸውን የተሟላ ደረጃ (100%) ላይ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመን በፊት ከነበሩት ተቋማት በተጨማሪ የመለስ ዜናዊ አካዳሚ በተጠናከረ ሁኔታ የአቅም መገንቢያ ተቋም ሆኖ የሚያገለግል ይሆናል፡፡ ሌላው በመጀመሪያው የዕድገትና

ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በጉድለት የተለየውና በሁለተኛው ዕትዕ ዘመን ትኩረት ተሰጥቶት በዚህ ግብ ውስጥ ሊከናወን የታቀደው ስራ ጥናት፣ ምርምርና የምርጥ ተሞክሮ ቅመራን ማጎልበት ነው፡፡

## 3.4 ልማታዊ መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ

በአገራችን ነባራዊ ሁኔታ መልካም አስተዳደርን የማረጋገጥ ጉዳይ የምርጫ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ማጠናቀቂያ የህዝብ እርካታና አመኔታ ደረጃ አሁን ካለበት 60 በመቶ ወደ 85 በመቶ የማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ ለመልካም አስተዳደር መስፈን ዋና መሳሪያ የሆነውን የግልፅነትና ተጠያቂነት ሥርዓት በሁሉም መንግስት ተቋማት ለመዘርጋት በሚቀጥለው የእቅድ ዘመን በፌዴራልና በክልል የመንግስት ተቋማት የዜጎች ቻርተርን በተሟላ ሁኔታ በመተግበር በተቋማት የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር የበለጠ እንዲጎለብት  የሚያስችሉ ስራዎች ይሰራሉ፡፡

## 3.5 የለውጥ ኮሙኒኬሽንን ማሳደግ

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ያለፈውን የአፈጻጸም ደረጃ እንደመነሻ በመውሰድ የተመዘገቡ ስኬቶችን አጠናክሮ በማስቀጠልና በለውጡ መሳሪያዎች ላይ የተሟላ መግባባትን በመፍጠር አመራሩና ሙያተኛው በሙሉ ለውጡን የተቀበለና አሟልቶ የሚፈጽም እንዲሆን፣ ዜጋው ለለውጡ ጠንካራ ድጋፍ ወደሚያደርግበት ብሎም ወደ ለውጥ ፈላጊነት ደረጃ ማሸጋገርና በመጨረሻም ለውጡ እንዳይቀለበስ ዘብ ወደሚቆምበትና ልማታዊ አስተሳሰብ የበላይነት የሚያገኝበት ደረጃ ላይ ለማድረስ ታቅዷል፡፡ የለውጥ ኮሙኒኬሽን ስራውን በስትራቴጂ የማስደገፍ፣ ለኮሙኒኬሽን የሚያግዙ ሁሉንም ሚዲያዎች አሟጦ የመጠቀም አቅምን ማጎልበት፣ የአመራሩንና የሲቪል ሰርቫንቱን የለውጥ ኮሙኒኬሽን አመለካከትና ክህሎት ማሳደግ፣ የዲያስፖራውን የለውጥ ደጋፊነት በኮሙኒኬሽን የማጠናከር ይህንንም ተከታታይነትና ቀጣይነት ባለው መልኩ በመፈጸም ለውጡን በመላው አገሪቱ በጠንካራ መሠረት ላይ በመትከል ስርዓት ሆኖ እንዲቀጥል የሚያስችሉ ስራዎችን ለማከናወን ዕቅድ ተይዟል፡፡

## 3.6 በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተደግፎ የመስራት አቅምን ማጎልበት

የግቡ አድማስ በዋነኛነት የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ሥራ አመራር መረጃ ሥርዓትን አጠናክሮ መተግበርንና የመንግስት ተቋማት የአፈጻጸም አመራር ማዕቀፍ የሆነውን ውጤት ተኮርን ሁሉን አቀፍ በሆነ ሶፍትዌር በመደገፍ አስተማማኝ ስርዓት በማድረግ ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አማካይነት ለምቶ ለትግበራ ዝግጁ የሆነውን የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ ሥራ አመራር መረጃ ሥርዓት ደረጃ በደረጃ  ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ ባሉ ተቋማት የመዘርጋት ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

## 3.7 የከተማ መሬት አስተዳደር ሥርዓትን ማጠናከርና ዘመናዊ ማድረግ

ያልተማከለ አስተዳደር በማጠናከር ከተሞች ገቢያቸውን የማሣደግ፣ ለልማት የመበደርና በአግባቡ የመጠቀም አቅማቸው ይጠናከራል፣ ለአፈጻጸሙም የህግና የአሰራር ማእቀፍ ተዘጋጅቶ በመንግስት እንዲፀድቅ ይደረጋል፡፡ ከተሞች ከቱሪዝም ገቢ እስከ 50 በመቶ እንዲጋሩና ለአገልግሎቶች ማሻሻል እንዲያውሉትም ይደረጋል፡፡ ለተለያዩ የልማት ስራዎች 150 ሺህ ሔ/ር እና ለ20 የኢንዱስትሪ ፓርኮችና ዞኖች ልማት የሚያስፈልግ የለማ መሬት ተዘጋጅቶ ይቀርባል፡፡ የተጐሣቀሉና የደቀቁ የከተማ አካባቢዎች አሁን ካሉበት 50 በመቶ ወደ 30 በመቶ እንዲቀንሱ ማድረግ፡፡ የተፋሰስ ልማት ስራዎች ስታንዳርድ ወጥቶላቸው ለየአካባቢው 500 ሺህ የሥራ እድል ይፈጠራል፡፡

## 3.8 የታክስና የጉምሩክ አስተዳደር ሥርዓቱን በተሟላ መልኩ መተግበር

በቀጣይ የእቅድ ዘመን የተጠናከረ የመልካም አስተዳደርን እውን ለማድረግ የሰው ኃይል አቅርቦት በወሣኝ ስራ መደቦች ላይ ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑ ያለውን የሰው ኃይል በ63.3 በመቶ በማሣደግ ቁጥሩን ወደ 15 ሺህ

ለማድረስ ታቅዷል። በራስ አቅም ተከታታይነት ያለው የውስጥ ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችል የሥልጠና ማዕከል ይገነባል። የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን በጣት ኣሻራ ማስደገፍን በተመለከተ በአገሪቱ ያሉ ግብር ሰብሣቢ ተቋማት በቀጥታ ምዝገባ እና ቀጥታ ባልሆነ ምዝገባ የጣት አሻራ የመሰብሰብ ሥራ በእቅድ ዘመኑ በመደበኛነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል። የሽያጭ መመዝቢያ መሣሪያ አቅርቦትና አጠቃቀምን ማስፋት ዋና ተግባር ይሆናል። ግብር ከፋዩች ወደ ቅ/ ጽ/ቤቶች ሣይመጡ ከስራ ቦታቸው ሆነው የሚፈለግባቸውን ግብርና ታክስ በኤሌክትሮኒክ የክፍያ ስርዓት መክፈል የሚችሉበት ስልት ይቀይሣል። የተገልጋዮች ቻርተር ተዘጋጅቶ ተግባር ላይ ይውላል።

### 3.9 የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱን በመተግበር የአገሪቱን ሀብት ለታለመለት ዓላማ ማዋል

በሥራ ላይ ያሉትን የፋይናንስ፣ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪየዎችና ማንዋሎችን በመመርመር የማሻሻያ ሥራዎች ይከናወናሉ። የኘሮግራም በጀት አሠራር በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ይዘረጋል። የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር የመረጃ ሥርዓት /IFMIS/ ደረጃ በደረጃ በመላ ሃገሪቱ በመዘርጋት የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት እንዲተዳደር ይደረጋል። የፀደቀውን የኢትዮጵያ ፋይናንሺያል ሪፖርቲንግ አዋጅ እና ደንብ በመተግበር በአገሪቱ የአካውንቲንግና ኦዲቲንግ ሥራዎች ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የጠበቁ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ለዚህም በኃላፊነት የሚያስፈጽም ብሔራዊ የአካውንታንቶችና ኦዲተሮች ቦርድ /National Accounting and Auditng Board/ የሚባል ራሱን የቻለ የመንግስት መ/ቤት እንዲቋቋም ይደረጋል፣ ለሒሣብና ኦዲት ሙያዎች ኘሮፌሽናል ሥልጠናና እውቅና የሚሰጥ ተቋም /Professional Training Istitute/ ይመሰረታል። የግዥ ሥርዓቱን ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስችል የኤሌክትሮኒክ የግዥ ዘዴ /e-procurment / በስራ ላይ ይውላል። እስካሁን በመንግሥት ፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደር በተበታተነ መልክ የሚሰጡ ሥልጠናዎች ተቋማዊ በሆነ መልክ እንዲካሄዱ ይደረጋል።

### 3.10 ዘመናዊ፣ ፍትሃዊና በውድድር ላይ የተመሰረተ የንግድ ሥርዓት መዘርጋት

የንግዱ ዘርፍ የተደራጀ የለውጥ ሰራዊትን የማስፈፀም አቅም በቀጣይነት በመገንባት ቁልፍና መሠረታዊ በሆኑ የሪፎርም ተግባራት ላይ እንዲረባረብ ይደረጋል። በአገር አቀፍ ደረጃ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ የተጀመሩ ስራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ። በንግድ ግንኙነትና ድርድር ረገድም ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ የንግድ ስርዓቱ ውስጥ ተጠቃሚ እንድትሆን ሠፋፊ የገበያ እድሎችን በማስፋት የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ለማሣደግ ጥረት ይደረጋል። ወቅታዊና ተደራሽ የሆነ መረጃ ለተጠቃሚዎች ለማድረስ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል። የንግዱን ዘርፍ አቅም ግንባታ ኢንስቲቲዩት በመገንባት ለዘርፉ ተዋንያኖች ቀጣይነት ያለው ስልጠና የመስጠት እስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደጋሉ።

የምርቶችና አገልግሎቶችን ጥራትና ደህንነትን ለመከታተል የገበያና ድርጅት ክትትል ሥራ በእቅድ ዘመኑ በየዓመቱ በተከታታይ ፈቃድ ከተሰጣቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ውስጥ በ 50% ምርመራ በማድረግ ባመለካከትና በሥነ ምግባር የታነፀ ፈጻሚ ይፈጠራል። በ2007 በጀት ዓመት በአማካይ በ869,193.74 ሜትሪክ ቶን የገቢ ምርቶችና 835,509.6 ሜትሪክ ቶን የወጪ ምርቶች ላይ የሚደረገውን የኢንስፔክሽን ሥራ በማጠናከር በ2012 በጀት ዓመት ወደ 1,529,374.67 እና 1,267,333.05 ሜትሪክ ቶን በቅደም ተከተል ይደርሳል። የ2007 በጀት ዓመት የአማካይ 1,307,250 አፈጻጸምን መነሻ በማድረግ የህጋዊ ስነልክ የመለኪያ መሣሪያዎችን ትክክለኝነት ማረጋገጥን በፌዴራል፣ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ በቁጥር 15,687,600 ይደርሳል።

### 3.11 የትራንስፖርትና የሎጀስቲክስ አገልግሎትን ተወዳዳሪ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ

የባህር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት አገሪቱ ለነደፈችው የማኑፋክቸሪንግ ኢንነዱስትሪ ትራንስፎርሜሽንና የኤክስፖርት ልማት መስፋፋት ከሚጫወተው ቁልፍ ሚና አኳያ በቀጣዩ የእቅድ ዘመን

ላይ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ የባህር ትራንስፖርት ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ተልእኮ እውን ለማድረግ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሚከናወኑ የሺፒንግ፣ ሎጂስቲክስና ድጋፍ ሰጪ ዋና ዋና ተግባራትን በተቀናጀ ሁኔታ ለአገልግሎት ሰጪና ለተገልጋይ አካላት የተሟላና ወጥነት ያለው ወቅታዊና /Real Time/ ተደራሽ የሆነ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

## 3.12 ህገ መንግሥቱን በማስከበር፣ በማስረጽ፣ የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ ጠንካራ ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መንግሥታዊ የፍትህ መዋቅር መፍጠር

የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ሰነዶችን በማዘጋጀት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ለወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ተገቢውን የሕግ ከለላ ለመስጠት የሚያስችል አሠራርና አደረጃጀት በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩን ውጤታማነት እና ቅልጥፍና የሚረጋገጥበትና የሚለካበት ዝርዝር ስርዓት በተለይም የማጥራት ምጣኔ፣ የማስቀጣት ምጣኔ ወዘተ በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በማስረጃ እጦት፣ በተከሳሽ አለመገኘትና በምስክርና በተከሰሽ አለመቅረብ ምክንያት የሚቋረጡ መዛግብትና የመንጠባጠብ ምጣኔ እንዲቀንስ ይደረጋል፡፡ የመንግስትና ሕዝብ ጥቅምን የማይጐዱ ቀላል ወንጀሎች በዕርቅ የሚያልቁበትን ስርአት በሁሉም ደረጃ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ‘ማንም ከወንጀል ድርጊቱ ማትረፍ ወይም መጠቀም የለበትም’’ የሚለውን የሕግ የበላይነትና የሞራል መርህ ለማስጠበቅ የወንጀል ፍሬዎችና ወንጀሉን ለመፈጸም የዋሉ ንብረቶች እንዲወረሱ ይደረጋል፡፡ በወንጀል የተገኘ ንብረት ሙሉ በሙሉ ተመላሽ ይሆናል፡፡ የሙስና ወንጀል ተጠርጣሪዎችን የመመርመር፣ የመክሰስና በፍርድ ቤት የማስቀጣት እንዲሁም የሙስና ወንጀል ፍሬ የሆኑ የመንግስትና የህዝብ ሃብትና ንብረቶችን የማስመለስ አቅም እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

የፍትሃብሄር ፍትህ አስተዳደር ስርዓትን ማሻሻል፡- የልማታዊ መንግስት፣ የልማታዊ ባለሀብትና የዜጋውን ጥያቄ ሊያስተናግድ በሚችል አግባብ እንዲሁም በልማታዊ መንግስት ጽንሰ ሃሳብ የተቃኘ የዳኝነት ተቋም ለመፍጠርና የዳኝነት ፖሊሲ ለመቅረጽ የሚያስችል ጥናት ተካሂዶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የግብር ጉዳይ ይግባኝ አወሳሰን ፍትሀዊነቱ ይረጋገጣል፡፡ በልማት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያላቸው የንግድ ጉዳዮች በተለየ ችሎት የሚታዩበትን ስርዓት በጥናት የመለየት ስራና የተጀመረውን የንግድ ህግ የማሻሻል ስራ አገሪቱ በአሁኑ ወቅት ከምትከተለው የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ፍልስፍና ጋር በተጣጣመና ፈጣን ልማትን ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት እንዲያግዝ በሚያስችል መልኩ እንዲቀጥልና ተጠናቆ ተግባር ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ በፍትሐብሔር ጉዳዮች የወንጀል ሰለባዎች ለደረሰባቸው ጉዳት የሚካሱበትን ስርአት ይዘረጋል፡፡ በፍትሃብሄር ጉዳዮች ላይ የሚንጠባጠቡ መዝገቦች ቁጥር የመቀነስና የተፋጠነና በአጭር ጊዜ የሚወሰን ጉዳይ (SUMMARY AND ACCELERATED PROCEEDINGS) የክርክር ስርዓትን ማጠናከር ተኩረት ተሰቷቸው ይሰራሉ፡፡በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ የፍትሀብሄር ውሣኔዎች እውነት ላይ የደረሱና የሚፈፀሙ እንዲሆኑ አስገዳጅ ትርጉም የተሰጣቸው የሰበር ውሳኔዎች ታትመው እንዲሰራጩ፣ የሚሰጡ ውሳኔዎችም ከህገ-መንግስቱ ጋር የተገናዘቡ ይሆናሉ ስለመሆናቸው እንዲረጋገጡ ይደረጋል፡፡

የሚንጠባጠቡ መዝገቦች ብዛት ዝቅ እንዲል፣ ውሣኔ የሚያገኙ መዝገቦች ቁጥር ከፍ እንዲል፣አሁን ያለው የማጣራት አቅም እንዲጐለብት፣ የጥፋተኝነት ምጣኔ ከፍ እንዲል፣ የመዝገቦች መጨናነቅን ዝቅ እንዲል፣ የክምችት ምጣኔ አሁን ካለበት መጠን እንዲቀንስ፣ የመዝገቦች የቆይታ ጊዜ ቢያንስ ከስድስት ወር በታች እንዲሆንና የዳኛ መዝገብ ጥምርታ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ የሕዝብንና መንግስትን ጥቅሞች ለማረጋገጥ ልዩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዩች ላይ ተጨማሪ ችሎቶች በመክፈት አጥጋቢና ውጤታማ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ፍትሀዊ የሆነ የፍርድ ሂደት እንዲኖር ለማድረግ የተጀመሩት ስራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ የቀጠሮ እስረኛ ምጣኔ ዝቅ እንዲሁም የፍርደኛ እስረኛ ምጣኔ ከፍ ይላል፡፡ ከማረሚያ ቤት ውጭ ሌላ የአማራጭ ቅጣት ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

የጉዳዩች ፍሰት አስተዳደር አሁን ካለው ደረጃ ይሻሻላል፣ የቅጣት አወሳሰን ማኑዋል በገሪቱ በሙሉ ተግባራዊ ይደረጋል፣ የቅጣት አወሣሰን መመሪያ ባልተዘጋጀላቸው ጉዳዩች ለተመሣሣይ ወንጀሎች ተመሣሣይ ቅጣት ለመቀበል እንዲቻል መመሪያ ይዘጋጀል፣ የፍርድ አፈፃፀምን ሥርዓት ትክክለኛ መረጃ ማግኘት የሚያስችለውና የተጀመረው ስርአት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ከፍ/ቤት ውጪ ያሉ አማራጮች ማለትም በእርቅ፣ በግልግል እና በመሣሰሉት የሙግት መፍቻ አቅጣጫዎች ህብረተሰቡ እንዲቀጠም ተገቢው ድጋፍ ይሰጣል፡፡ የወሣኝ ኩነቶች ምዝገባ የሚከናወንባቸውን ተቋማትን አቅም መገንባት፣ በየደረጃው በተጠናከረ ሁኔታ ስርአቱን መዘርጋትና የዜጐች መሠረታዊ የመረጃ /የልደት፣ የጋብቻ እና የሞት ወዘተ../ ሥራ በዚህ እቅድ ዘመን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የህግ የበላይነትን መረጋገጥ ለማጐልበት በጥናትና ምርምር በመታገዝ ከህገ መንግስቱ ከአለም አቀፍና ወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥመው የተዘጋጁ ረቂት ህጐች ፀድቀው ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡
የዓቃቤ ህግና የመርማሪ ፖሊስ ጥምርታን በማጠናከር መዝገቦችን የመመርመርና የማጣራት አቅም አሁን ካለበት ደረጃ የበለጠ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ የታራሚዎች አስተዳደር፣ መያያዝ፣ ማረምና ማነጽን ውጤታማ ለማድረግ በእቅድ ዘመኑ በማረሚያ ቤቶች ታራሚዎችን በአግቡቡ አርሞ ለማውጣት ሀገራዊ የታራሚዎች አያያዝና ጥበቃ ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የታራሚ መኖሪያ ቤቶችንና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን በማጠናከር ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የይቅርታና የአመክሮ አሰጣጥ የመረጃ ጥራትን ተመርኩዞ ይካሄዳል፡፡

## 3.13 የዘርፉን የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች አካታችነትን ማጎልበት

የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች በመንግስት ተቋማት ውስጥ የበለጠ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲተገበሩ በፌደራል ደረጃ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር፣ በክልሎች ደግሞ በሲቪል ሰርቪስ ቢሮዎች አማካይነት ተገቢው የአፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን አካትቶ በመተግበር ዙሪያ ያለውን የግንዛቤ ክፍተት ለመድፈን ጥረት ይደረጋል፣ በዚህ ዘርፍ ሊካተቱ ከሚገባቸው ውስጥ ኤች አይ ቪ ኤድስን፣ ሥርዓተ ፆታ፣ የሥነ ህዝብ ጉዳይ፣ የአካባቢና የአየር ንብረት፣ ዋነኞቹ ናቸው፡፡

## 4. የማስፈጸሚያ ስልቶች

የመንግስትና የህዝብ አደረጃጀቶች ተልዕኮአቸውንና የለውጥ ፓኬጆችን ውጤታማ ማድረግ በሚያስችል መልክ በመቃኘት የለውጥ ሰራዊት ግንባታው ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ የመንግስት ተቋማት ቅልጥፍናና ውጤታማነትን እያሻሻሉ ለመሄድ እንዲያስችላቸው በየደረጃው ያለውን አመራርና ፈጻሚ በትምህርት፣ በስልጠና፣ በልምድ ልውውጥ፣ በተግባራዊ እንቅስቃሴና በመሳሰሉት መንገዶች እያበቁ የመሄድ ሥራ ይቀጥላል፡፡ ይህንንም በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥሉ የአቅም መገንቢያ ተቋማት አቅም እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

ለመልካም አስተዳደር መስፈን ዋና መሳሪያ የሆነውን የግልፅነትና ተጠያቂነት ሥርዓት ለመዘርጋት በሚቀጥለው የእቅድ ዘመን በፌዴራልና በክልል የመንግስት ተቋማት የዜጎች ቻርተርን በተሟላ ሁኔታ በመተግበር በተቋማት የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር የበለጠ እንዲጎለብት የሚያስችሉ ስራዎች ይሰራሉ፡፡
ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት አቅርቦት እንዲሻሻል በማድረግ፣ የአጠቃቀሙን አቅም በማሣደግ፣ የታክስ ሥርዓት ማሻሻያ ስራን ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመስራት እንዲሁም የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ወደ ክልሎች በማስፋት የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት እንዲጠናከር ይደረጋል፣

የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥና የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትን ለማፋጠን በጥናትና ምርምር በመታገዝ ከህገመንግስቱ፣ ከአለምአቀፍና ወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥመው የተዘጋጁ ረቂቅ ህጎች ፀድቀው ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በጥብቅና ሙያ የሚሰማሩ ባለሙያዎች ብቃትና ሙያዊ ስነምግባራቸውን

ያከበሩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስርአት በመዘርጋት፣ በፍትህ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ ያላቸው ሚና እንዲጐለብት ይደረጋል፡፡ ልማታዊ የንግድ ሥርዓትን በመፍጠር ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ስር-ነቀል ለውጥ ይካሄዳል፣ የባለብዙ ዘርፍ ስራዎችን አካቶ የመተግበር ሥራ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመንም ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

## 3.4 የሕዝብ ተሳትፎ፣ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና ብሔራዊ መግባባት

### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

በገጠርም ሆነ በከተማ የፈጣን ልማታችን ዋስትና የህዝባችን አቅም ነው፡፡ በመጀመሪያው የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም በተለይ የህዝቡን እምቅ አቅም በመጠቀም በስኬት መንገድ ረጅም ርቀት ተጉዘናል፡፡ በገጠር አርሶ አደሩ እውቀቱን፣ ጉልበቱን፣ መሬቱንና መላ የተፈጥሮ ሃብቱን አዋህዶ ጥቅም ላይ በማዋል በምግብ ሰብል ራሳችንን ያስቻለን ውጤት አስመዝግቧል፡፡ አርሶ አደሩ በነፃ ፍላጎቱ በወል የስምሪት መስኮች ላይ በጋራ በመዝመት በአካባቢ ጥበቃና በተፋሰስ ልማት ረገድ አስደናቂ ለውጥ አምጥቷል፡፡ ባለፉት አራት የዕቅድ አፈፃፀም ዓመታት በተመዘገቡ ውጤቶችና ለውጦች ህዝባችን በየደረጃው ፍትሐዊ ተጠቃሚነቱን አረጋግጧል፡፡ እነዚህን መልካም ስኬቶች በህዝቡ የነቃ፣ ነፃና የተደራጀ ተሳትፎ አጠናክሮ ማስቀጠልና የኢኮኖሚያችንን መዋቅራዊ ሽግግር ማረጋገጥ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡

የምርጫ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደትን በሚመለከት የውድድር ምህዳሩን በላቀ ደረጃ ማስፋትና ህዝቡ በነፃ ፍላጎቱና በንቃት ላይ ተመስርቶ ዘላቂ ጥቅሙን በወሳኝ ድምፁ እንዲያረጋግጥ ማድረግ ነው፡፡ ፓርቲዎች በአጀንዳ እየተወዳደሩ ከምርጫ በኋላ የሚኖረውን ስትራቴጂክ መድረክ ባህሪ እንዲወስኑና በትውልዶች ቅብብሎች በሚፈፀመው የህዳሴ ጉዞ ውስጥ የራሳቸውን ገንቢ ሚና አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ፓርቲዎች እንዲፈጠሩ እንዲጎለብቱ መደገፍ፣ የህዝብ ምክር ቤቶች የፌዴራልም ሆነ የክልል ከፍተኛ የስልጣን አካላትና የህዝብ ሉአላዊነት መገለጫዎች ከመሆናቸው እና ሁሉንም የመንግስት አካለት የመደገፍ፣ የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነታቸው አንፃር ይህንን ከባድ ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት የሚያስችላቸው ሁለንተናዊ አቅም መገንባት፣ ለምክር ቤቶቹ ተጠሪ የሆኑ ተቋማትን አቅም መገንባት፣ የፍትህ አካላት የዜጋውን ሰላምና ደህንነት የማስጠበቅ በዚህም መልካም አስተዳደርን የማስፈን ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ መደገፍ በዕቅድ ዘመኑ የሚተኮርባቸው አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

የመገናኛ ብዙሃንና የኮሙኒኬሽን ብሄራዊ መግባባት የመፍጠር አቅማቸው ይበልጥ እንዲያድግና በህገ-መንግስታዊ ስርዓታችን መርሆዎች፣ በፀረ-ድህነት ትግልና ፈጣን ልማት የማረጋገጥ ራዕያችንንና አፈፃፀማችን፣ የዘላቂ ሰላም የማረጋገጥ ስራችን፣ ብዝሃነትን የማክበር አቋማችን፣ የህዳሴ ጉዞ ጅምር ስኬታችንና ሀገራዊ ገፅታችን፣ በትምህርት፣ በጤናና በመሰረተ ልማት መስፋፋት የተገኙ ውጤቶችን አጠናክረው እንዲያስቀጥሉ ድጋፍና ዕገዛ ይደረጋል፡፡ የኪነ-ጥበብ ዘርፍ የሀገራችን የመዝናኛ ኢንዱስትሪ የኒዮ-ሊበራል ተቋማት የሚያሰራጩትን ሰፊ የተዛባ መረጃ በትክክለኛ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የማቅረብ ብቃት እንዲገነባ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፡፡

### 2. የዕቅዱ ዓላማ

የዴሞክራሲ ተቋማትን እና የዜጎችን አመለካከት በመቅረጽ ላይ ወሣኝ ሚና ያላቸውን ተቋማት አቅም በመገንባት፣ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መሰረታዊ መርሆዎች፣ ዙሪያ በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በአጠቃላይ፣ ሃገራዊ አስተሳሰብ በመቅረጽ ላይ ከፍተኛ ሚና ባላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ደግሞ በተለይ ጥልቀት ያለው ተሳትፎና ሀገራዊ መግባባት እንዲፈጠርና፣ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ልዕልና በአስተማማኝ ደረጃ እንዲረጋገጥ ማድረግ የዴሞክራሲ ተቋማት፣ የሚዲያና የኮሙኒኬሽን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓለማዎች ናቸው፡፡

## 3. የዴሞክራሲ ተቋማት፣ የሚዲያና የኮሙኒኬሽን ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች

3.1 ምክር ቤቶች፣ የፍትህ አካላት እና ለምክር ቤት በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት የሕዝብ አሳታፊነትና ተደራሽነትን ማሣደግ፣ ለዚህም የተቋማቱን አቅም በመገንባት የመረጃ አያያዝ፣ አሳታፊነት እና በመረጃ ተደራሽነት ላይ እንዲሰሩ ማድረግ፣

3.1 የምክር ቤቶችን አቅም በማጎልበት ራዕዮቻቸውን እንዲያሳኩ ማብቃት (በመንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ በምክር ቤት አደረጃጀት፣ አሰራር እና ኃላፊነቶች፣ በሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ፣ በህገ-መንግስት እና በመሳሰሉት የምክር ቤቶች አባላትን የመፈፀም አቅም ማሣደግ፣ የምክር ቤቶችን ድጋፍ ሰጪ አካላት ማብቃት፣ የምክር ቤቶቹን የአደረጃጀትና የአሰራር ህግጋት ለሁሉም አካላት አጠቃቀም አመቺ እና ተደራሽ ማድረግ የምክር ቤቶችን የመወሰን አቅም ማሣደግ፣ የምክር ቤቶቹን እና አካላቱን ስራዎች ተደራሽ እና አሳታፊነት ማሣደግ)፣

3.2 ለምክር ቤቱ ቀጥታ ተጠሪ የሆኑ ተቋማትና የፍትህ አካላት አቅም ጎልብቶ መልካም አስተዳደርና ፍትህ በላቀ ደረጃ እንዲሰፍን እንዲሁም ለምክር ቤቶች ያላቸውን ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ በተግባር እንዲፈፅሙ ማስቻል፣

3.3 ሁሉም አካላት ስራቸውን በውጤታማነት ለመፈፀም፣ አሳታፊነትን ለማጠናከርም ይሁን ኪራይ ሰብሳቢነትን በቀጣይነት አምርሮ በመታገል ራእዮቻቸው ላይ ለመድረስ ተቋማዊ ቀጣይነት (Institutional Sustainability) ግንባታ አተኩረው እንዲሰሩ ማድረግ፣

3.4 በገጠርና ግብርና ልማት መስክ የአርሶ አደሩንና ከፊል አርሶ አደሩን እንዲሁም አርብቶ አደሩን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት፣ መሠረታዊ ጤናና መሰረተ-ልማት አገልግሎት ለማስፋፋት የሚያስችሉ መረጃዎችን በብቃትና በጥራት በማቅረብ ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ፣ የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን በማረጋገጥ ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ምቹ ሁኔታ መፍጠር፡

3.5 በከተማ ልማት የልማታዊ አስተሳሰብ የበላይነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ወቅታዊና ጥራት ያላቸው መረጃዎችን በማቅረብ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን የተቋቋሙ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ወደ ኢንዱስትሪ እንዲሸጋገሩ፣ አነስተኛ ጥቃቅን ተቋማት በቀጣይነት እንዲስፋፉ፣ ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ፣

3.6 በኢንዱስትሪ ልማት በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የሚታዩ ችግሮችን የሚፈቱና ልማታዊ ባለሀብቶችን የሚያጎለብቱ ወቅታዊና ጥራት ያላቸው መረጃዎችን በማቅረብ በኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲፈጠር ማድረግ፣ የምርትና አገልግሎት ዓለም አቀፍ የውድድር ብቃት ማሳደግ፣

3.7 በመሰረተ ልማት ግንባታ የተመዘገቡ ስኬቶችን በማጠናከር የህዝብ መሰረታዊ ፍላጎቶች እንዲሟሉና ህዝቡ ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችሉ ወቅታዊ መረጃዎችን በጥራት በማቅረብ በአገልግሎት ጥራታቸው የተመሰገኑና ህዝቡ በባለቤትነት የሚንከባከባቸው የመሰረተ ልማት ተቋማት እንዲሆኑ ማድረግ፣

3.8 በሰው ኃይል ልማት በተለይም በትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሚታዩ የጥራት ችግሮችን በመቅረፍ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በብቃት ለመገንባት የሚችል ትውልድ ለመቅረፅ የሚያስችሉ ወቅታዊ መረጃዎችን በጥራት በማቅረብ በአመለካከት፣ በእውቀትና በክህሎት የላቀ ብቃት ያለውና በመረጃ የዳበረ ማህበረሰብ መገንባት፣

3.9 የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ስራችን ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑን ያገናዘበና የዴሞክራሲያችን ልዩ ባህርያት ላይ የተመሰረቱ እንዲሁም የኒዮ-ሊበራል አስተሳሰብን በብቃት የሚመክት፣ ወቅታዊ መረጃዎችን በብቃትና በጥራት በማቅረብ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲያዊ ስርዓአት በመገንባትና ዘላቂ ሰላም በማረጋገጥ ሂደት መንግስት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የህዝብ አደረጃጀቶችና የሙያ ማህበራት መገናኛ ብዙሃን ኃላፊነታቸውን በብቃት እንዲወጡ ማድረግ።

3.10 የሀገራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን መሠረት በማድረግ የተቀረፀው የውጭ ግንኙነት ስራችን ላይ ወቅታዊ መረጃዎች በብቃትና በጥራት በማቅረብ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲያችን ማጎልበት በጋራ ጥቅም፣ በሰላምና በመቻቻል መርህ ላይ የተመሰረተ የሁለትዮሽን ክፍለ አህጉራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ማጠናከር፣ ሀገራዊ ገፅታችን በህዳሴ ጉዟችን በተመዘገቡና በሚመዘገቡ ስኬቶች መጠን እንዲታወቅ ማድረግ፣

3.11 የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ በሀገራችን እያስመዘገበ ያለውን ፈጣን እድገት በመልማት ላይ ለሚገኙ ሀገራት የተሻለ አማራጭ መሆኑን የሚያስገነዝቡ መረጃዎች በብቃትና በጥራት በማቅረብ /በውጭ ቋንቋዎች/ በጎረቤት ሀገራትና በአፍሪካ አዎንታዊ የለውጥ ፍላጎት መፍጠር፣

3.12 የትምህርትና ስልጠና ተቋማት አዲሱን ትውልድ በመሰረታዊ የለውጥ እሴቶች በመቅረፅ ቁልፍ የብሄራዊ መግባባት ተቋማት እንዲሆኑ ማድረግ፣ ለዚህ የሚያስፈልግ የካሪኩለም ማሻሻያ ማድረግ፣ በተለይም የሚዲያና ኮሙኒኬሽን እንዲሁም የኪነ-ጥበብ ባሙያዎች የትምህርትና የስልጠና ተቋማት ስርዓተ-ትምህርት /ካሪኩለም/ በልማታዊ ኮሙኒኬሽን እንዲመራ ማድረግ፣ የኒዮ-ሊበራል ካሪኩለም በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ካሪኩለም መተካት፣ የህግና የኢኮኖሚክስ የትምህርት መስኮችም በዚሁ እንዲቃኙ ማድረግ፣

3.13 የህዝብ አደረጃጀቶች /የብዙሃን ማህበራት/ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ማህበራዊ መሰረት የሆኑትን ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አርሶ አደሮችና ሰራተኞች መብትና ጥቅም በማስከበርና ስትራቴጂክ እቅዱን በማሳካት የላቀ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱበት የብቃት ደረጃ ማድረስ፣ የእምነት ተቋማትና ቤተሰብ ለብሄራዊ መግባባት አስተዋፅኦ የሚያበረክቱበት ሁኔታ ማመቻቸት፣

3.14 በትምህርት ተቋማት መስፋፋት በፍጥነት እያደገ የመጣውን የባለሙያ መጠን በየዘርፍ በሚደራጁ የሙያ ማህበራት በማሳተፍ አብዛኞቹ ባለሙያዎች የሚጠበቅባቸውን ሙያዊና ሃገራዊ ኃላፊነት እንዲወጡ፣ የፖሊሲና ቴክኖሎጂ ሽግግር ጥናትና ምርምር የማካሄድ አቅማቸው በቀጣይነት እንዲገነባና መብትና ጥቅሞቻቸው እንዲከበሩላቸው ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

3.15 የኪነ-ጥበብ ዘርፍ /የመገናኛ ኢንዱስትሪው/ በስፋትና በጥራት ወደ አዲስ ምዕራፍ በማሸጋገር የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና በጎ ሃገራዊ ገፅታ ግንባታ አቅም በቀጣይ መገንባት፣ በዘርፉ ስኬታማ የሆኑትን ሃገራት ልምድ በመቀመር የዜጎች የፈጠራና በጎ አስተሳሰብ የመገንባት አቅም ማጎልበት፣

3.16 የሚዲያና ኮሙኒኬሽን እንዲሁም የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ስርዓተ-ትምህርት በልማታዊ ኮሙኒኬሽን እንዲመራ ማድረግ፣ የኒዮ-ሊበራል ካሪኩለም በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ካሪኩለም መተካት፣ የህግና የኢኮኖሚክስ የትምህርት መስኮችም በዚሁ እንዲቃኙ ማድረግ፣

## 4. የማስፈፀሚያ ስልቶች

የዘርፉ ቁልፍ ክፍተት የተቋማዊ ቀጣይነት ግንባታና ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ለመገንባት የሚያስችሉ ትክክለኛና የተተነተኑ መረጃዎች በብቃትና በጥራት የማቅረብ ብቃታችን ዝቅተኛ መሆኑ ነው። የዚህ ችግር ምንጭ ደግሞ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ለመገንባት የሚያስችሉ መረጃዎችን የማቅረብ ኃላፊነት የተጣለባቸውን የብሄራዊ መግባባት ተቋማት የማስፈፀም ብቃት ችግር ነው። ይህም የስትራቴጂክ መድረኩን ግቦች ለማሳካት አሁን በስራ ላይ ባሉት ተቋማት ፈጣን ለውጥ

ማምጣትና በስትራቴጂክ መድረኩ የተለያዩ ብሄራዊ መግባባት ተቋማት በመፍጠር የሚፈፀም ነው። የስትራቴጂው ማስፈፀሚያ ስልቶች የሚያተኩሩት በተቋማዊ ግንባታ ማጠናከርና ማስቀጠል እንዲሁም የብሄራዊ መግባባት ተቋማት የማስፈፀም አቅም ወደ አዲስ ምዕራፍ በማሸጋገር ላይ ነው።

4.1 ለተቋማዊ ቀጣይነት (INSTITUTIONAL SUSTAINABILITY) ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸው የምክር ቤቶችን አባላት ድጋፍ ሰጪ አካላት ማብቃት (የመካከለኛ አመራሩን እና የፈፃሚውን በተቀናጀ እና ተከታታይነት ባለው ሁኔታ አቅም መገንባት፣ የመረጃ አያያዝን ዘመናዊ፣ ተደራሽ ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ፣ ምክር ቤቶች እና አካላቱ ብቃት ያለው የአፈፃፀም ማኑዋል እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን የያዙ ሰነዶች የገነቡ እንዲሆኑ ማስቻል፣

4.2 ም/ቤቶችን የፍትህ አካላትና ለም/ቤት ቀጥታ ተጠሪ ተቋማትን የአመራርና የፈፃሚ አካላት አቅም በመገንባት የአመለካከትና የኪራይ ሰብሳቢነትን በብቃት የሚታገሉ ውጤታማ ስራ የሚያከናውኑ እና ተደራሽ እንዲሆኑ ማብቃት፣

4.3 የምክር ቤቶች አካላቶቻቸውና በቀጥታ ለምክር ቤት ተጠሪ የሆኑ ተቋማት የተቋማቸውን ግብ ሊያሳኩ አቅጣጫዎች እና ግብ ተኮር ተግባራትን በግልፅ ያስቀመጠ እቅድ በጋራ የምክክር መድረክ የሚመሩበት አሰራር ማዳበር፣

4.4 ምክር ቤቶች እና አካላቱ የፍትህ አካላትና ለምክር ቤቱ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት አደረጃጀት፣ አሰራር እና ስራዎቻቸውን ለህዝብ የሚያደርሱበት እና ህዝቡም በእንቅስቃሴያቸው የላቀ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችላቸው የግልፅነትና መረጃን ተደራሽ የማድረግ አሰራር ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በዚህም የራሳቸውን የመረጃ አደረጃጀት እና ተደራሽ ማድረግ ከማጠናከር ባሻገር የመንግስት እና የግል የመገናኛ ብዙሃንን፣ የመረጃ ቴክኖሎጂን፣ እና የመሳሰሉትን በመጠቀም እንዲሁም የገፅ ለገፅ አሳታፊነትን በማጠናከር ህዝቡ በእነዚህ አካላት ያለውን ተሳትፎ ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል።

4.5 አሁን በስራ ላይ ያሉት የብሄራዊ መግባባት ተቋማት ላይ ፈጣን ለውጥ ማምጣት የዘርፉ ቀዳሚ ስልት ይሆናል። በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈፃፀም ላይ በተደረገው ግምገማ ላይ እንደተጠቀሰው የመገናኛ ብዙሃንና ኮሙኒኬሽን ተቋማትና ሌሎች የብሄራዊ መግባባት ተቋማት ቁልፍ ችግር የማስፈፀም ብቃት ችግር ነው። በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ዋነኛው ችግር የአመለካከት ችግር ሲሆን የእውቀትና የክህሎት ችግርም ጎልቶ ይታያል። ስለዚህ የስትራቴጂክ መድረኩ ቁልፍ ክፍተት በሆነው የብሄራዊ መግባባት ተቋማት ችግር ማለትም ወቅታዊ፣ የተደራጀና የተተነተነ መረጃ በጥራትና በብቃት የማቅረብ እጥረት ለመፍታት የሚያስችል ስልት መከተል ያስፈልጋል። ይህ የአቅም ግንባታ ተግባር የአደረጃጀት ለውጥ፣ የአመለካከት ጥራት፣ በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የመገናኛና ኮሙኒኬሽን እወቀትና ክህሎት በመገንባት የሚፈፀም ነው። ይህ ስራ የመንግስት የተማከለ የመረጃና ኮሙኒኬሽን አቅም (Brain Center) መፍጠር፣ ዲጂታላይዜሽን ማፋጠን፣ በሰው ኃይላችን ፈጣን የአመለካከትና የክህሎት ለውጥ ማምጣትን ያካትታል።

4.6 አዳዲስ የብሄራዊ መግባባት ተቋማት በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን የሚታየው የብሄራዊ መግባባት ተቋማት የማስፈፀም ብቃትና የመረጃ ክፍተት አሁን በስራ ላይ ያሉትን ተቋማት የማስፈፀም ብቃት በማሳደግ ብቻ የሚሸፈን አይደለም። አሁን ያሉን ተቋማት ከህዝቡ የመረጃ ፍላጎት የሚሸፍኑት 40 በመቶ እንደማይበልጥ የሚጠቁሙ ጥናቶች አሉ። በሀገራችን ዋነኛው የመረጃ ምንጭ ኢ-መደበኛው ኮሙኒኬሽን /የግለሰብ/ማህበረሰብ የእለት ተእለት ግንኙነት/ እንደሆነ በተለያዩ ጥናቶች ታይቷል። ስለዚህ አሁን ያሉንን ተቋማት ከማጠናከር ጎን ለጎን አዳዲስ የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት የማስፋፋት፣ የመዝናኛ ኢንዱስትሪውን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ያስፈልጋል። የመንግስት፣ የግልና የማህበረሰብ የኤፍ.ኤም ጣቢያዎችን ማስፋፋት፣ የቴሌቪዥን ስርጭት ቻናሎችን በብዙ እጥፍ ማሳደግ፣ አዳዲስ የህትመት ውጤቶችን በስፋት ማቅረብ፣ የማህበራዊ

ሚዲያ አገልግሎት ላይ ስር-ነቀል ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የሚዲያ/ብሮድካስት ባለስልጣን ቁልፍ ሚና መጫወት ይጠበቅበታል፡፡ የመዝናኛ ኢንዱስትሪው ከባህላዊ አሰራር በማውጣት በአለማችን ታዋቂ የሆኑት የሆሊውድ፣ ቦሊውድ የመዝናኛ ተቋማት የደረሱበት ደረጃ ለማድረስ የሚያስችሉ አቅጣጫዎችን በመቀየስ አዳዲስ የመዝናኛ ተቋማት የማደራጀት ስራው በአፋጣኝ መጀመር አለበት፡፡ ይህ ሁኔታ ከብዝሃነታችን ማለትም የብዙ ባህሎች ባለቤት ከመሆናችንና ከህዝባችን ብዛት አኳያም በአስቸኳይ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ አሁን ባለው የኮሙኒኬሽን ስራችን ላይ ፈጣን ለውጥ የማምጣት ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ዝቅተኛው የህብረተሰብ ክፍል መረጃ ለማድረስ የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር እንደ አንድ ስልት መታየት አለበት፡፡ አሁን እየተከናወነ ያለው የመንግስት መደበኛ የኮሙኒኬሽን /የህዝብ ግንኙነት/ ስራ የሚደግፉ የገጠርና የከተማ የኮሙኒኬሽን ፍሰቱን የሚያቀላጥፉ አደረጃጀቶችን የመፍጠር አማራጭ ማየት ይገባል የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ተፃራሪ የሆኑ መረጃዎች የሚሰራጩበት አንዱ ስልት ይህ ኢ-መደበኛ የኮሙኒኬሽን ስርዓት መሆኑን ያገናዘበ የማጥቃት ስልት ላይ የተመሰረተ አደረጃጀት መቀየስ ያስፈልጋል፡፡

4.7 የከፍተኛ ትምህርትና የስልጠና ተቋማት ስርዓተ-ትምህረት /ካሪኩለም/ ላይ ፈጣን ማስተካከያ በማድረግ በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የታነፁ የኮሙኒኬሽን፣ የሚዲያና የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎችን በማፍራት የብሄራዊ መግባባት ተቋማት ከኒዮ-ሊበራል አስተሳሰብ ተፅእኖ የተላቀቀ የሰው ሃይል እንዲኖራቸው የማድረግ ስልት መከተል ወሳኝ ነው፡፡ ይህ ስልት ከአጭር ጊዜ አኳያ ሲታይ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው በሚቀጠሩ ባለሙያዎች እያጋጠመ ያለውን የአስተሳሰብ ችግር በተከታታይ ትግል መቅረፍ የሚጠይቅ ሲሆን የካሪኩለም ለውጥ እስኪደረግ ድረስ ባለሙያዎችን እስከ ስድስት ወር ድረስ የአስተሳሰብ ግንባታ ለማካሄድ የሚያስችሉ የማሰልጠኛ ተቋማት እንዲያደራጁ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ እነዚህ የስልጠና ተቋማት አዲስ የሚቀጠሩ ባለሙያዎችን ብቻ ሳይሆን በስራ ላይ ያሉትን ኤዲተሮችና ባለሙያዎችንም ከግሎባላይዜሽን ጋር ተያይዞ የሚታዩ ለውጦችን ለመተንተንና ለመገንዘብ የሚያስችል እውቀትና ብቃት በቀጣይነት መገንባት የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡

4.8 የህዝብ አደረጃጀቶች /የብዙሃን ማህበራት/ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን ማህበራዊ መሰረት የሆኑትን ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አርሶ አደሮችና ሰራተኞች መብትና ጥቅም የማስከበርና ስትራቴጂክ እቅዱን የማሳካት ኃላፊነታቸውን በብቃት እንዲወጡ የሚያስችል አቅም በቀጣይነት በመገንባት የብሄራዊ መግባባት ሁኔታችንን ለማሳደግ የሚያስችል ስልት መከተል ያስፈልጋል፡፡ የብዙሃን ማህበራት በአሁኑ ወቅት እያበረከቱ ያሉትን አስተዋፅኦ ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ የሚያስችልና በጥናት ላይ የተመሰረተ የአቅም ግንባታ እቅድ በማዘጋጀት የሚፈፀም ይሆናል፡፡ የብዙሃን ማህበራት ተነፃፃሪ ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ማህበራት ከቀበሌ ም/ቤት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የህዝብ ውክልና ያላቸው ተቋማት፣ በሚዲያና በተለያዩ የአስተሳሰብ የትግል መድረኮች ወይም የብሄራዊ መግባባት ተግባራት በብቃት እንዲሳተፉ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡

4.9 የብሄራዊ መግባባት ተቋማት የማስፈፀም አቅም በቀጣይነት ለመገንባት የሚያስችሉ የመረጃና ጥናትና ምርምር ማዕከላት የማደራጀት ስራ የስትራቴጂክ እቅዳችን አንዱ ስልት ነው፡፡ በሀገራችን የሚታየውን የተደራጀና ወቅታዊ መረጃና የተተነተኑ መረጃዎች እጥረትና በሃሳብ ትግሉ ላይ ያተኮሩ የጥናትና ምርምር ስራዎች ክፍተት በአግባቡ ለመፍታት የሚያስችሉ ተቋማት ግንባታ ስልት መከተል የግድ ይላል፡፡ በአሁኑ ወቅት በተወሰኑ ተቋማት በጅምር ደረጃ የሚገኙ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የሚዲያ ሞኒተሪንግ ስራዎችን በመስኩ ልምድ ያላቸው ተቋማት ተሞክሮ በማጥናት ወደላቀ ደረጃ ማሸጋገር ያስፈልጋል፡፡

# ምዕራፍ IV
# የባለብዙ ዘርፎች ልማት ዕቅድ

## 4.1 የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ

### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

ሴቶችን በሀገሪቱ በየደረጃው በሚደረጉ የተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች በማሳተፍ በሀገር ደረጃ ለሚደረገው ድህነትን የማጥፋት ትግል የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማስቻል፣ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ሴቶች በሁሉም የልማት መስኮች እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑና የሴቶችንና የህፃናትን ተጠቃሚነት ያረጋገጡ ተቋማት እንዲፈጠሩ ማስቻል፣ የህጻናትን በተለይ ደግሞ በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ህጻናትን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ እና ህብረተሰቡ በሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ዙሪያ ንቁ ተሳታፊ ለማድረግ የሚያስችል የአመለካከት ለውጥ ማምጣት፣ የግንዛቤና ንቅናቄ ስራዎችን ማካሄድ ቁልፍ ጉዳይ ሆኖ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ የሴቶችን ሁለንተናዊ ብቃት በማሳደግ የሴቶች ማህበራት ማጠናከር፣ እንዲሁም የሴቶችንና ህጻናትን መብትና ደህንነት በማረጋገጥ በሴቶችና በህጻናት ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሀይል ጥቃቶች ማስወገድ፣ በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች የሴት ተማሪዎች ክበባት/ፎረሞች እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የሴቶችን የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ እንዲያድግ ማድረግ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

በተመሳሳይ የእናቶችና የህጻናት ሞት ምጣኔ ለመቀነስ፣ የቤተሰብ ምጣኔ፣ የቅድመ ወሊድና የድህረ ወሊድ፣ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፣ እናቶች በህክምና መስጫ ተቋማት እንዲወልዱ፣ በአመጋገብና ጤና አጠባበቅ ዙሪያ ግንዘቤ እንዲያገኙ፣ እንዲሁም የጡትና የማህጸን ካንሰር ምርመራ እንዲያደርጉ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል፡፡ እንዲሁም የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን ለማሻሻል የህጻናት መረጃ ቋት (ዳታ ቤዝ) በመመስረት ከክልሎችና ከፌደራል ተቋማት ጋር የማገናኘት ሥራ ይሰራል፣ የህጻናት ማህበራዊ ተጠቃሚነትም እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

### 2. ዓላማዎች

የሴቶችን ሁለንተናዊ ብቃት በመገንባት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ መስኮች እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤ በሀገሪቱ ልማት ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታዎች በመፍጠር የራሳቸውን ሚና እንዲያበረክቱ ማስቻል፣ እንዲሁም የህጻናትን መብትና ደህንነት ማረጋገጥ ነዉ፡፡

### 3. ዋና ዋና ግቦች

#### 3.1. የሴቶች ጉዳይ ንዑስ ዘርፍ

የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንጻር በቀጣይ የዕቅዕ ዘመን ሴቶች 4.13 ሚሊዮን በጥቃቅንና አነስተኛ፣ 1.79 ሚሊዮን በራስ አገዝ፣ 5 ሚሊዮን በህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በሌላ በኩል 6.2 ሚሊዮን ሴቶች የቁጠባ ባህላቸውን እንዲያሳድጉ በማድረግ 8.1 ቢሊዮን እንዲቆጥቡ የሚደረግ ሲሆን 2.24 ሚሊዮን ሴቶች 8.04 ቢሊዮን የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ሴቶችና ወጣቶች በቋሚነት በየአካባቢው የማምረቻ ቦታዎች የሚመቻችላቸው ሲሆን የሚያመርቷቸውን ምርቶች የሚያስተዋውቁበትና የሚሸጡበት ደረጃውን የጠበቀ አንድ ትልቅ የገበያ ማዕከል እንዲገነባ ማድረግና ለሚያመርቷቸው ምርቶች  የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ይደረጋል፣ በአጠቃላይ ሴቶችን በጥ/አ/ኢ ልማት ዘርፍ ያላቸውን ድርሻ በአሁኑ ወቅት ከሚገኝበት  ከ41.47 በመቶ ወደ 50 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተጥሎል፡፡

በግብርና ዘርፍ የሴቶችን ተጠቃሚነት በተመለከተ 13.1 ሚሊዮን ሴቶች በግብርና፣ 1.5 ሚሊዮን ከግብርና ውጭ ባሉ የስራ መስኮች እንዲሰማሩ በማድረግ በአሁኑ ወቅት 27 በመቶ የሆነውን ወደ 50 በመቶ ለማሳደግ

ግብ የተጣለ ሲሆን በሀገሪቱ የሚገኙ ሁሉም አማወራዎች የመሬት ተጠቃሚነት መብታቸው ማረጋገጥ እንዲሁም 5.8 ሚሊዮን ሴቶች የተስማሚ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

በኢኮኖሚ እጥረት ምክንያት ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ለ55000 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሴት ተማሪዎችና ለ50 የሴት ተማሪዎች ማህበራት የአቅም ግንባታ ስልጠና፣ የፋይናንስ እና የማቴሪያል ድጋፍ ይደረጋል፣ በተለያዩ ክልሎች የተገነቡ 10 ሆስቴሎች በቁሳቁስ ማጠናከር እንዲሁም 15 አዳዲስ ሆስቴሎች እንዲገነቡ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡ የሴቶችን ውሳኔ ሰጭነት ከማሳደግ አንጻር ሴቶች በህግ አውጪ አሁን ካለበት 27.8 በመቶ ወደ 40 በመቶ፣ በአስፈጻሚ የፖለቲካ አመራር አሁን ካለበት 9.2 በመቶ ወደ 30 በመቶ እና በህግ ተርጓሚ አሁን ካለበት ከ20.6 በመቶ ወደ 35 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡

በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሀይል ጥቃቶች እንዲሁም የሴቶች ህገወጥ ዝውውር እንዲወገዱ/እንዲቀንሱ ፣የሴት ልጅ ግርዛት አሁን ከአለበት ከ23.4 በመቶ ወደ 0.5 በመቶ፣ ጠለፋ ከ12.7 በመቶ ወደ 0.5 በመቶ እና ያለ ዕድሜ ጋብቻ ከ8 በመቶ ወደ 0.5 በመቶ ለመቀነስ ግብ ተጥሎል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ጥቃት ለሚደረስባቸው ሴቶች የአንድ መስኮት አገልግሎት እንዲያገኙ 11 ማዕከላት የማቋቋምና አገልግሎት በመስጠት ላይ 3 ማዕከላትም ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ የማጠናከር ስራዎች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ በየደረጃው የሚገኙ 10000 ሴት አደረጃጀቶችን እና 85000 አመራሮች አቅማቸውን የማሳደግ ሥራ ይሰራል፡፡ እንዲሁም ስምንት የተለያዩ ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋት፣ በሴቶች ዙሪያ የተለያዩ 45 ጥናቶችን ማካሄድ፣ የሴቶች የመረጃ ቋት/ዳታ ቤዝ ማጠናከርና ክልሎችንና ፌደራል ተቋማትን በኔትወርክ ማገናኘት የተያዙ ግቦች ናቸዉ፡፡

### 3.2. የህጻናት ጉዳይ ንዑስ ዘርፍ

የህጻናትን መብት ከማስከበር አንጻር በዕቅድ ዘመኑ በሀገሪቱ ከሚወለዱ 50 በመቶ ህጻናት በክብር መዝገብ የልደት ምዝገባ ሰርቲፊኬት እንዲያገኙ ይደረጋል፣ በሕፃናት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ማለትም ግግ ማውጣት አሁን ካለበት 14.7 በመቶ ወደ 0.5 በመቶ፣ እንጥል መቁረጥ አሁን ካለበት 32.81 በመቶ ወደ 0.5 በመቶ እንዲቀንሱ ይደረጋል፣ ለ18 ሚሊዮን የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ማሳደግ እንዲሁም የሚመለከታቸውን አካላት አቅም የመገንባት ሥራ ይሰራል፡፡

ከፌደራል ጀምሮ በ6 የክልል ከተሞች ህጻናት ጥቃት ሲደርስባቸው የሚያሳውቁበት ባለ ሶስት ዲጂት የስልክ መስመር እንዲዘረጋና በታችኛው እርከን ለህጻናት ተስማሚ የሆኑ ልዩ ችሎቶች እንዲቋቋሙ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡ ለ5 ሚሊዮን ህጻናት የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙ ይደረጋል፣ በህጻናት ማሳደጊያ የሚገኙ ህጻናትን ከቤተሰቦቻቸው ጋር የማገናኘትና የመደገፍ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ ህጻናት የቅድመ መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎቸው እንዲያድግ፣ ችግር ያለባቸው ደግሞ በልዩ ፍላጎት ትምህርት ተጠቃሚ እንዲሆኑና ሙሉ በሙሉ የክትባት አገልግሎት እንዲደርሳቸው ይደረጋል፣ 30 የአሠራር ማዕቀፎች ይዘረጋሉ እንዲሁም 6 ጥናቶችን ይካሄዳሉ፡፡

## 4. የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

የሴክተሩን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካት እንዲቻል በየደረጃው የለውጥ ሰራዊት በመገንባት የሴቶች የልማት ቡድኖች ለዕቅዱ ማስፈጸሚያነት አስኳል ሆነው እንዲያገለግሉ ይደረጋል፡፡ የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ የሁሉንም አካላት ዘርፈ ብዙ ምላሽ የሚሻ በመሆኑ በእቅዱ ዘመን የትብብር፣ ቅንጅትና ህብረ ኃይልን የማጠናከር ስራ የሚከናወን ሲሆን በዘርፉ ለሚካሄደው ልማት የተለያዩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ሀብት የማሰባሰብ ስራ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ በዘርፉ ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር የማስፋት ስራ በላቀ ደረጃ የሚፈጸም ሲሆን ልዩ ልዩ ጥናቶችን በማካሄድ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች የማመንጨት፣ የመጠቀምና ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት በመዘርጋትና በማጠናከር የመረጃ ተደራሽነትን የማስፋት ስራ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ በዘርፉ የተቀመጡ አላማዎችና ግቦች በአግባቡ መፈጸማቸውን የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲሁም የህጻናት መብትና ደህንነት መከበሩን ለማረጋገጥ በተጠናከረ የክትትል፣ የድጋፍ፣ የግምገማና ግብረ መልስ ስርአት የሚታገዝ ይሆናል፡፡

## 4.2 የወጣቶችና የስፖርት ዘርፍ

### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የወጣቶች ጉዳይ የበለጠ ትኩረት እንዲያገኝና በሁሉም የልማት መስኮች ወጣቶች እኩል ተሳታፊና ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በዕቅዱ ዘመን የንዑስ ዘርፉን ተልዕኮና ራዕይ ለማሳካት የባለድርሻ አካላት አቅምን ማጎልበት፣ የወጣቶችን ሁለንተናዊ ብቃት ማሳደግ እና የወጣቶችን ማህበራት ማጠናከር ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ የስፖርት ሴክተሩ የማስፈፀም አቅም በየደረጃው እንዲገነባ የሚደረግ ሲሆን የስፖርት ማህበራት አደረጃጀቶችም እንዲሻሻሉ ይደረጋል፡፡ በዕቅዱ ዘመን የስፖርት ፋሲሊቲዎች ይስፋፋሉ፣ በስፖርት ኢንቨስትመንት የባለሀብቶች ተሳትፎ እንዲያድግ ይደረጋል፣ የታዳጊ ወጣቶችና የባለሙያዎች ስልጠና ይስፋፋል፣ ውድድሮችንና ፌስቲቫሎችን በማዘጋጀት የህብረተሰቡ ተሣትፎና ተጠቃሚነት እንዲያድግ ይደረጋል፣

### 2. ዓላማ

የወጣቶችን ሁለንተናዊ ብቃት በመገንባት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ መስኮች እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤ በሀገሪቱ ልማት ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታዎች በመፍጠር የራሳቸውን ሚና እንዲያበረክቱ ማስቻል፣ የስፖርት ዘርፉን የማስፈጸም አቅም በመገንባት መላውን ህብረተሰብ ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግና በኢንተርናሽናል የስፖርት መድረኮች ውጤታማ የሆኑ ወጣት ስፖርተኞችን ማፍራት ነው፡፡

### 3. ዋና ዋና ግቦች

ወጣቶች በሁሉም ዘርፍ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በየደረጃው የሚገኙ 15 ሚሊዮን ወጣቶች የሚሳተፉበት የተለያዩ የግንዛቤና የንቅናቄ መድረኮችን ማካሄድ፣ በየደረጃው በሚገኙ 35 በመቶ በምክር ቤቶች፣ 40 በመቶ በአስፈጻሚና 40 በመቶ በህግ ተርጓሚ አካላት የወጣቶች ተሳታፊነት እንዲኖራቸው ተከታታይና ቋሚ የሆነ ስርዓት በመዘርጋት አቅማቸው ይገነባል፣ የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሳትፎን አሁን ከአላበት 12.1 ሚሊዮን ወደ 20 ሚሊዮን ማድረስ፣ 2284 ነባር ማዕከላትን በማጠናከርና አዳዲስ ማዕከላትም እንዲገነቡ በማድረግ የወጣት ማዕከላትን 3000 ማድረስ፣ በተገነቡ ማዕከላት 10 ሚሊዮን ወጣቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፣ በወጣት ልማት እና ተሳትፎ ዙሪያ የ20 ሚሊዮን የህብረተሰብ ክፍል ግንዛቤ ለማሳደግ ግብ ተይዟል፡፡

የወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንጻር በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 7.43 ሚሊዮን በጥቃቅንና አነስተኛ፣ 1.35 ሚሊዮን በህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በሌላም በኩል 2.5 ሚሊዮን ወጣቶች የቁጠባ ባህላቸውን እንዲያሳድጉ በማድረግ 12.5 ቢሊዮን እንዲቆጥቡ የሚደረግ ሲሆን 2.19 ሚሊዮን ወጣቶች 10.98 ቢሊዮን የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ለወጣቶች በቋሚነት በየአካባቢው የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎች የሚመቻችላቸው ሲሆን ለ2 ሚሊዮን የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ ይህም በአጠቃላይ ወጣቶች በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ያላቸውን ድርሻ በአሁኑ ወቅት ያለውን ከ59 በመቶ ወደ 90 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተጥሎል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በግብርና ዘርፍ 4.32 ሚሊዮን ወጣቶች ግብርናና 3.64 ሚሊዮን ከግብርና ውጭ ባሉ የስራ መስኮች እንዲሰማሩ በማድረግ በአሁኑ ወቅት 10 በመቶ የወጣቶች ተጠቃሚነት ወደ 30 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡

የወጣቶች ማህበራዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንጻር ለ6.22 ሚሊዮን ወጣቶች የተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት እንዲያገኙ፣ 2.5 ሚሊዮን ወጣቶች በስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዲሁም ወጣቶች ውስጥ የኤች አይ ቪ ኤድስ ስርጭት ወደ 0.5 ለማድረስ በትኩረት ይሰራል፡፡ 20,000 ወጣት አደረጃጀቶችን እና 400,000 አመራሮችን አቅም በመገንባት፣ የወጣቶችን የልማት ቡድን አሁን ካለበት 7

በመቶ ወደ 80 በመቶ ማድረስ፣ ከነዚህም ውስጥ 30 በመቶ ወደ ላቀ የአፈጻጸም ደረጃ እንዲሸጋገሩ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግ፣ በየደረጃው የሚገኙ አስፈጻሚ አካላትን የወጣቶች ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ እንዲያካትቱና ብሎም ተቋማዊ እንዲያደርጉ ተከታታይነት ያለው የአቅም ግንባታ ስራ የሚከናወን ይሆናል፡፡ አምስት የተለያዩ ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋት፣ 10 የአሰራር ማዕቀፎችን መዘርጋት፣ በወጣቶች ዙሪያ የተለያዩ 20 ጥናቶችን ማካሄድ እንዲሁም የወጣቶች የመረጃ ቋት/ዳታ ቤዝ ማጠናከርና ክልሎችንና ፌደራል ተቋማትን በኔትወርክ የማገናኘት ስራዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚሳኩ ግቦች ይሆናሉ፡፡

በስፖርት ኢንቨስትመንት የሚሳተፈውን የባለሀብት ቁጥር ከ81 ወደ 444 በማሳደግ የስፖርት ኢንዱስትሪውን ማስፋፋት፣ እንዲሁም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ቁጥር ከ12,428 ወደ 40,000 ከፍ ማድረግ፣ የስፖርት ማሰልጠኛ ማዕከላትን ቁጥር ከ9 ወደ 22 ማሳደግ፣ ብዛታቸዉ 75,260,726 የሚሆን የህብረተሰብ ክፍል በስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ፣ በትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም የሰልጣኝ ባለሙያዎችን ቁጥር አሁን ካለው ከ39,000 ወደ 78,703 ከፍ ማድረግ የተያዙ ግቦች ናቸዉ፡፡

በተጨማሪም በ17 የስፖርት ዓይነቶች የሚሰጠውን የታዳጊ ወጣቶች ስልጠና አሁን ካለው ከ21,575 ወደ 50,000 ማሳደግ፣ በ17 የስፖርት አይነት የኤሊት ስፖርተኞችን ስልጠና ከ5499 ወደ 13207 ማሳደግ፣ በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ውጤት የሚመዘገብባቸውን የስፖርት ዓየነቶች አሁን ካለው ከ12 ወደ 17 ማሳደግ፣ እንዲሁም የገቢ መሠረቶችን በማስፋት በዘርፉ የሚሰበሰበውን ገቢ ከ207,092,000 ወደ 2,370,164,147 በማሳደግ ቀስ በቀስ ስፖርቱ ከመንግስት ድጎማ ማላቀቅ የሚያስችል መሰረት መጣል የተያዙ ዋና ዋና ግቦች ናቸዉ፡፡

### 4. የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

የወጣቶችና ስፖርት ዘርፍ የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካት እንዲቻል በየደረጃው የለውጥ ሰራዊት በመገንባት የወጣቶች የልማት ቡድኖች ለዕቅዱ ማስፈጸሚያነት አስኳል ሆነው እንዲያገለግሉ ይደረጋል፡፡ የወጣቶች ጉዳይ የሁሉንም አካላት ዘርፈ ብዙ ምላሽ የሚሻ እንደመሆኑ መጠን በዕቅዱ ዘመን የትብብር፣ ቅንጅት እና ህብረ ኃይልን የማጠናከር ስራ የሚከናወን ሲሆን በዘርፉ ለሚካሄደው ልማት የተለያዩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ሀብት የማሰባሰብ ስራ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ የስፖርት ፋሲሊቲዎችን ማስፋፋትና ህጋዊነታቸውን ማረጋገጥ፣ የስፖርት ተሣትፎና ውጤታማነትን ማረጋገጥ፣ የትምህርት የስልጠና ፕሮግራሞችን ማጠናከር፣ የባለብዙ ዘርፍ ተግባራት አካቶ መተግበር፣ ውጤታማ የኮሚኒኬሽን ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግና ቅንጅታዊ አሠራርን ማጠናከር የማስፈፃሚያ ስልቶች ይሆናሉ፡፡

## 4.3 ሠራተኛና ማኀበራዊ ጉዳይ

### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

የዘርፉን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም በመገንባት፣ የተለያዩ ጥናትና ምርምሮችን በማድረግና የማህበራዊ ደህንነት ሥርዓትን በመዘርጋት አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያንን በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፤ የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎቶች ይስፋፋሉ፡፡ በሥራ ስምሪትና በሥራ ገበያ ብሄራዊ የምክክር ስርአቶች ይስፋፋሉ፣ የሥራ ሁኔታዎች ቁጥጥር አገልግሎት ሽፋን እንዲያድግ ይደረጋል፣ እንዲሁም የመረጃ አገልግሎትን በማስፋፋት የሀገሪቱን የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት እንዲጣጣም ይደረጋል፡፡ በሥራ ላይ የሚደርሱ የሞት አደጋ ክስተቶች እንዲቀንሱ ይደረጋል፣ የሥራ ሁኔታዎች ቁጥጥር ይጠናከራል፣ ሥራ ፈላጊዎች ሥራ እንዲያገኙ ድጋፍ ይደረጋል እንዲሁም ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶች ይሰጣሉ፡፡

### 2. ዓላማዎች

የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎትን በማስፋፋት የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን እንዲሁም የዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ የሥራ ስምሪትና የሥራ ገበያ መረጃ አገልግሎቶችን በማስፋፋት የሀገሪቱን የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት እንዲጣጣም ማድረግ እና የኢንዱስትሪ ሠላም በማስፈን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት እንዲያድግ የላቀ አስተዋፅኦ ማበርከት ናቸው፡፡

## 3. ዋና ዋና ግቦች

### 3.1 የማህበራዊ ደህንነት ንዑስ ዘርፍ

የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎችን እና መመሪያዎች አሁን ካሉበት 66 ወደ 243 ማድረስ፣ የማህበራዊ ጥበቃ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሥርአት መዘርጋት፣ በፌደራልና በክልሎች የተናበበና የተቀናጀ የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት ኘላት ፎርሞችን አሁን ካሉበት 14 ወደ 67 ማድረስ፣ የማህበረሰብ የድጋፍ ጥምረቶችን አሁን ካሉበት 1,590 ቀበሌዎች ወደ 17,388 ቀበሌዎች ማስፋፋት የተያዙ ግብች ናቸዉ፡፡ የማህበራዊ ድጋፍ ተጠቃሚ የሆኑ በድህነት ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን አሁን ካሉበት 1204346 ወደ 6434400 ለማሳደግ፣ ለተለያዩ የማህበራዊ ኑሮ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የሥነ ልቦና የምክርና ድጋፍ ተጠቃሚ ዜጎችን አሁን ካሉበት 167,880 ወደ 795,293 ለማሳደግ፣ የማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት የግንዛቤ ማስጨበጫና ሥልጠና ያገኙ ዜጎችን አሁን ካሉበት 20,527,658 ወደ 57,133,145 ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡ ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላትን አሁን ካሉበት 16 ወደ 31 ለማሳደግ፣ የሰው ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፍ፣ የፊዝዮቴራፒ እና የተለያዩ አገልግሎቶች አሁን ካሉበት 208,634 ወደ 734,941 ለማሳደግ፤ የአረጋውያን ማዕከላትን አሁን ካለበት አንድ ወደ 13 ለማሳደግ የተያዙ ግቦች ናቸዉ፡፡

የማህበራዊ ዋስትና ሽፋንን በማጠናከር በመንግሥት ሥራ ላይ የተሰማሩ ዜጎችን ምዝገባ አሁን ካለበት 2350000 ወደ 2850000 ማድረስ፣ በግል ድርጅቶች ሥራ ላይ የተሰማሩ ዜጎችን የማህበራዊ ዋስትና ሽፋን አሁን ካለበት 880000 ወደ 1430000 ማሳደግ፣ በግል ማህበራዊ ዋስትና የተሸፈኑ ድርጅቶችን ብዛት አሁን ካሉበት 119700 ወደ 174700 ማሳደግ እና የጡረታ ፈንድ አሁን ካለበት 14.2 ቢሊዮን ብር ወደ 28 ቢሊዮን ብር ማሳደግ በማህበራዊ ደህንነት ንዑስ ዘርፍ የተጣሉ ዋና ዋና ግቦች ናቸው፡፡

### 1.2 የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ንዑስ ዘርፍ

በዕቅድ ዘመኑ የአገሪቱን የሰው ኃይል ሀብት ፍላጎትና አቅርቦት ለማጣጣም ወቅታዊ ጥራታቸውን የጠበቁ ቁልፍ የሥራ ገበያ አመልካቾች (KILM) ዝግጅት አሁን ከተደረሰበት 9 ወደ 12 ማሳደግ፣ እንዲሁም በሲቪል ሰርቪስ መ/ቤቶች በግል ድርጅቶችና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች በሥራ ላይ የተሰማራውን የሰው ኃይል መረጃ አሰባሰብ ሽፋን አሁን ከደረሰበት 10 በመቶ ወደ 50 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተይዟል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሁለትዮሽ የሥራ ቦታ ትብብርና ማህበራዊ ምክክር ሥርዓቶችን ከ2,884 ወደ 23,255 ማሳደግ፣ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዶችን አሁን ካሉበት 15 ወደ 26 ማሳደግና ማጠናከር፣ ከሚቀርቡ የሥራ ክርክሮች መካከል በስምምነት የሚፈቱትን አሁን ካሉበት 60 በመቶ ወደ 75 በመቶ ማድረስ፣ብሔራዊ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት ሥርዓት መዘርጋት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ንዑስ ዘርፍ የተያዙ ዋና ዋና ግብች ናቸው፡፡

## 4. የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

ነባር የማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረቶች እንዲጠናከሩና አዳዲሶቹም እንዲቋቋሙ በማድረግ መላው ህብረተሰብ ተገቢ አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ንቅናቄ መፍጠር፣ የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎት የሚሰጡ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፡፡ ዓለምአቀፍ የልማት አጋሮች የቴክኒክና የፋይናንስ እገዛ እንዲያደርጉ በማስተባበር የዘርፉን የሰው ኃይል በመጠንና በዓይነት ለይቶ ማፍራትና ማብቃት፣ ጥናትና

ምርምሮች፣ እንዲሁም ፖሊሲዎችና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ማዋል፣ የልማት ሠራዊትን መገንባትና ሥርዓተ-ጾታ መካተቱን ማረጋገጥ፣ እንዲሁም የስራዎችን ስኬታማነት ለመለካት የሚያስችሉ የተጠናከሩ የድጋፍ፣ የክትትልና የግምገማ ሥርዓቶችን መዘርጋት የዕቅዱ ማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

## 4.4 የአካባቢ እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት

### 1. የትኩረት አቅጣጫዎች

በሁሉም ደረጃ በዘርፉ የተያዙ ግቦችን ስኬታማ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት ለመፍጠር፤ የሰው ኃይል፣ የፋይናንስና የቴክኖሎጂ አቅርቦትን ማጠናከር፣ ህብረተሰቡን በተደራጀ የልማት ሠራዊት እንዲንቀሳቀስ በማድረግ በአካባቢ፣ በደን ልማት፣ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲሁም በጥምር እርሻ ደን በማሳተፍ ኢኮኖሚያዊና ሥነምህዳራዊ ተጠቃሚነቱን ለማረጋገጥ ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን የህዝብ ክንፍ፣ የባለድርሻ አካላት እና የልማት አጋሮቻችንን አስተዋጽኦ ማሳደግ፤ ወጣቶችና ሴቶች የደን መሬቶችን በማልማት እና የተፈጥሮ ደኖችን በመንከባከብ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ትኩረት ይደረጋል፡፡ በአርብቶ አደር /ቆላማ/ አካባቢ የሚካሄደውን የአካባቢና የደን ልማት ሥራ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በቴክኖሎጂና በቴክኒክ ልዩ ድጋፍ የሚደረግ ሲሆን ዘርፉን ለማዘመን የግሉ ዘርፍ በስፋት ተዋናይ የሚሆንበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ የደን ውጤቶች የግብይት ሰንሰለትን በማሻሻል ወይም በመፍጠር ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ጥረት ይደረጋል፡፡

ከከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዞ በሚመጣ የአኗኗር ለውጥ እንዲሁም በኢንዱስትሪ ዕድገት የሚመጣውን የአካባቢ ብክለት ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት የሚዘረጋ ሲሆን ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ በሁሉም ደረጃዎች በተሟላ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን ትኩረት ይሰጣል፡፡

### 2. ዓላማዎች

የዘርፉ የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓላማ በሀገሪቱ እየመጣ ያለውን ፈጣን እና ፍትሐዊ ልማት ዘላቂና አካባቢያዊ ደህንነትን ያረጋገጠ እንዲሆን በማስቻል በ2017 ሀገሪቱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍ በምታደርገው እንቅስቃሴ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስልት በሁሉም ዘርፍ መተግበሩን ማረጋገጥ ነው፡፡ በተጨማሪም የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን በማሻሻል ከደን ሀብት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ስነምህዳራዊ አስተዋጽኦ ማሳደግ ሌላው የዘርፉ አላማ ነው፡፡

### 3. ዋና ዋና ግቦች

#### 3.1 ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት ግንባታን በተመለከተ

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ አንዱ የዕቅዱ መሠረታዊ አቅጣጫ በመሆኑ ይህንን ተፈፃሚ ለማድረግ በዚህ ዘርፍ የሚከተሉት ግቦች ተጥለዋል፡፡

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ላይ በየደረጃው ላሉ 31,000,000 ህብረተሰብ አካላት ግንዛቤና ተሳትፎ ለማሳደግ እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ እና በሌሎች የዘላቂ ልማት ለተሰማሩ 80400 አስፈጻሚ አካላት ዕውቀትና ክህሎት ለማሳደግ ግቦች ተጥለዋል፡፡ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን በላቀ ደረጃ ለመፈፀም የሚያስችል የፋይናንስ ግኝት ማሳደግ እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ እና ዘላቂ ልማት የላቀ አፈጻጸም የሚውል 100ሺ አባወራና እማወራ የአረንጓዴ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ድጋፍ

የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልት ላይ የተመለከቱ ዘርፍ አቀፍ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ተግባራትን በማስተባበር፣ በመደገፍና በመፈጸም የ147 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መቀንስ የሚተገበር ሲሆን ይህም በዋናነት ከሁሉም በአረንጓዴ ልማት ግንባታ ቅድሚያ ከተሰጣቸው ዘርፎች ማለትም በአፈር፣ በቤት እንስሳት፣ በደን፣ በኢነርጂ፣ በመጓጓዣ፣ በኢንዱስትሪ ዘርፍና በከተማ ልማት ዘርፎችና ንዑስ ዘርፎች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል በሀገራችን የኢንዱስትሪና የከተሞች መስፋፋት እና የኑሮ ለውጥን ተከትሎ እየመጣ ያለውን የአካባቢ ሀብቶች ብክነትና ብክለት በአጥጋቢ ሁኔታ ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ለማረጋገጥ ሁለት መቶ ቶን አደገኛ ነገሮችን አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ማስወገድ እና ሃምሳ የሚደርሱ የተበከሉ አካባቢዎችን ለማጽዳት፤ በብክለት ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅእኖዎችን ለመከላከልና ለመቀነስ እና ከሁለት ሺህ ሕዝብ በላይ ባላቸው 150 ከተሞች አካባቢን ጽዱና አረንጓዴ እንዲሆኑ የሚያስችል እርምጃዎች መወሰዳቸውን በማረጋገጥ ዜጎች በንጹህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖሩ ለማድረግ ግቦች ተጥለዋል፡፡

### 3.2. የደን ዘርፍ ልማትን በተመለከተ

የደን ዘርፍ ለአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት የሚያበረክተውን ድርሻ ከነበረበት 4 ፐርሰንት ወደ 8 ፐርሰንት በማሳደግ የሃገሪቱ የደን ሃብት በዘላቂነት በመጠበቅና በመንከባከብ ስነ ምህዳራዊ ጠቄሜታቸውን ማሳደግና የደን ዘርፍን ሃገራዊ ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ ለማሳደግ ግቦች ተጥለዋል፡፡ በተመሳሳይ የሀገሪቱን የደን ሃብትና መሬት ለይቶ በመከለል፣ በመመዝገብና በመጠበቅ በምርምር የተደገፈ ልማት በማካሄድ የደን ሽፋኑን በ2007 ዓ.ም ከተገመተበት 15.5 በመቶ ወደ 20 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በተጨማሪም የአካባቢ ደህንነት መብቶች፣ የደን ሃብት ልማት ጥበቃና ተጠቃሚነት የሚረጋገጥበት ሥርዓት ማዘጋጀት እና መከበራቸውን ለማረጋገጥ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚቀርቡ አካባቢያዊ እና የደን የፈቃድ ጥያቄዎች ለዘላቂ ልማት ያላቸውን አስተዋጽኦ በማረጋገጥ ለ8000 ተገልጋዮች የይሁንታ ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት፣ የልማት ተቋማት የአካባቢ ህጎች እና ደረጃዎች አሟልተው መገኘታቸውን ለማረጋገጥ ክትትልና ቁጥጥር በማካሄድ 20 የህግ ተከባሪነት ደረጃን የሚያሳይ ዘገባ ማዘጋጀት፤ የህዝብ፣ የአካባቢ እና የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አሳታፊና ያልተማከሉ የአካባቢ መንከባቢያ ሥርዓቶች ለማዘጋጀት ግቦች ተጥለዋል፡፡

አገራዊ የአካባቢና የደን ልማት እቅዶችን አስተማማኝና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ለማቀድና ስኬታማ አፈጻጸምን ለመከታተል የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ስርአት መዘርጋት እና አገራዊና አለም አቀፋዊ የአካባቢ ሁኔታና ለውጥ ዘገባዎችን በማዘጋጀት ረገድ አለም አቀፍ የአካባቢና የደን ሁኔታና ለውጥ 8 ዘገባዎችን ለማዘጋጀት፤ አገራዊ የአካባቢና የደን ልማት እቅዶችን አስተማማኝና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ለማቀድና ስኬታማ አፈጻጸምን ለመከታተል፣ ለአካባቢ ምርምር እና ለህብረተሰቡ ወቅታዊና ተአማኒ መረጃን ለማድረስ የሚያስችል 3 የመረጃ ስርአት ለመዘርጋትና ተደራሽነቱን ለማረጋገጥ ታቅዷል፡፡

## 4. የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

### 4.1 የማስፈፀም አቅም ግንባታ ፕሮግራም

ከላይ የተጣሉ ግቦችን ለማሳካትና ተፈፃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የተቋሙን የማቀድ፣ የማስፈጸም፣ የመከታተል እና የመገምገም አቅም የማሳደግ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ የአካባቢና የደን መዋቅር በሁሉም ክልሎች እስከታችኛው የአስተዳደር እርከን እንዲደራጅ ለማድረግ ክትትል የሚደረግ ሲሆን የዘርፍ መስርያ ቤቶችና እስከታች ባለው መዋቅር ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመፈጸም የሚያስችል አደረጃትን እንዲፈጠሩ አስፈላጊው ድጋፍ ይሰጣል፡፡ የክልሎችን የአቅም ግንባታ ፍላጎት እና

የቴክኒክ አቅም እጥረት ለመለየት የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የማካሄድ፣ ለደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን እና ግብአቶችን ለይቶ በየደረጃው የማሟላት፣ በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የተለያዩ አጫጭር እና መደበኛ ስልጠናዎችን የማቀድ እና የማስፈጸም ተግባራት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡ በሚመለከታቸው የዘርፍ መስርያ ቤቶችና ክልሎች ሀብት የማፈላለግ እና ፕሮጀክት የመፈፀም ብቃት ለማሳደግ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን የውስጥ ክትትል እና ግምገማ ስርአት በተጠናከረ መልኩ ይዘረጋል፡፡

### 4.2 ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት ግንባታን በተመለከተ

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመግንባት በተለያዩ ዘርፎች ግቦች የተጣሉ ሲሆን ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ እንያንዳንዱ ዘርፍ የሚቀንሰውን የሙቀት ሳቢ ጋዞች ልቀት ለመተግበር የሚያስችለው ዘርፋዊ የልቀት የቅነሳ የድርጊት መርሐግብር እንዲያዘጋጅ የማገዝና ክትትል የማድረግ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ ይህም በዋናነት ለእያንዳንዱ ዘርፍ የልቀት ቅነሳውን ለመተግበር የሚያስችል የዓቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግና ዘርፉ የልቀት ቅነሳውን ለመተግበር የሚያስችል ከዓለም ዓቀፍ ተቋማት የገንዘብ ድጋፍ በማፈላለግ አግባብነት ላላቸው ዘርፎች እንዲደርስ የማድረግ ተግባራት የሚከናዎኑ ሲሆን የሚቀንሰውን የሙቀት አማቂ ጋዞች መጠን ለማወቅ የሚያስችል የልቀት መጠን መለኪያ፣መመዘገቢያ እና ማረጋገጫ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

አሳታፊና ዘርፍ አቀፍ የማጣጣሚያ መርሐግብሮችን፣ እቅዶችንና ትግበራን በመደገፍና በማቀናጀት የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን የሚቋቋም ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ በርካታ ስልቶች ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆን በአገር አቀፍ ደረጃ ስምምነት የተደረሰባቸው 20 ለአየር ንብረት ለውጥ የማጣጣም ጉዳዮች ተግባራንትን መከታተል፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማጣጣም ጉዳዮች በሁሉም ደረጃዎችና ባለድርሻዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጥ እና በዕቅድ ዘመኑም ይህንኑ የተመለከቱ የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋምና የዘላቂ ልማት ማረጋገጫ 5 ዘገባዎች የሚዘጋጁ ይሆናል፡፡

በተጨማሪም በአገር አቀፍና አለም አቀፍ ደረጃ በአየር ንብረት ዙሪያ ከሚሰሩ የልማት አጋሮች ጋር በቅንጅት በመስራት የፋይናንስ አቅምን ለማጠናከርና ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመውሰድ ጥረት ይደረጋል፡፡ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳታፊነት ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት በሁሉም ደረጃ የሴቶችን፣ ወጣቶችና የግሉን ዘርፍ የሚያሳትፍ ስርዓት ይዘረጋል፡፡

### 4.3 የደን ዘርፍ ልማት

የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ትምህርትና ምርምርን ለማጠናከር በየደረጃው ያሉ ፈጻሚ አካላትን አቅም ለመገንባት የሚያስፈልገውን የስልጠና፤ የትምህርት እና የምርምር ፍላጎት መለየት፣ ትምህርት እና ስልጠና ከሚሰጡ ተቋማት ጋር አብሮ መስራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ ፈጻሚ አካላት አስፈላጊውን ትምህርት እና ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ለንዑስ ዘርፉ የተቀመጡ ስትራቴጂዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የደን ምርምር በማካሄድ ልማቱን በእውቀትና በቴክኖሎጂ መደገፍ በምርምር ለተገኘ መረጃ፣ ቴክኖሎጂ እና ዕውቀት ቅድመ ማስተዋወቅ ስራ የሚሠራ ሲሆን የምርምር ማዕከላት፣ ንዑስ ማዕከላት እና ላቦራቶሪዎች እንዲቋቋሙ ይደረጋል፡፡ ከውጪ ሀገር የሚገቡ የዛፍ ዘሮች እና የተለያዩ የደን ውጤቶች ላይ የበሽታ እና ተባይ መቆጣጠርያ ስርአት ለመዘርጋት እና ተግባራዊ ለማድረግ ቅድመ ሁኔታዎች የሚሟሉ ሲሆን ከተባይ፣ ከበሽታ፣ ከእሳት፣ ከአደገኛ ተስፋፊና መጤ ወራሪ ዕፅዋት መስፋፋት እና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ተግዳሮቶች በምርምር የተደገፈ መፍትሄ የሚዘጋጅላቸው ይሆናል፡፡

የተለያዩ የደን ልማት ፓኬጆች እና ማኑዋሎችን በማዘጋጀት የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠት እና የአህዝቦት ስራዎችን መስራት ሌላው የማስፈፀሚያ ስልት ሲሆን በደን ልማት ለሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች እና ማህበራት አስፈላጊውን መረጃ እና ድጋፎችን (የመሬት አቅርቦት፣ የቴክኒክ፣ የህግ፣ የገበያ፣ የብድር፣

የኢንሹራንስ) እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ምርጥ ተሞክሮዎችን የማስፋፋት፣ የዛፍ ዝርያ እና የዘር ምንጭ ዞኖችን የመለየትና የመጠበቅ፣ ለደን ልማት የሚውል የዛፍ ዝርያ እና የቦታ ጥምረት ማንዋል እና ለዚህ ዓላማ የሚያገለግል ሀገራዊ ካርታ የማዘጋጀት ስልቶች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ ማዕከላዊ የዛፍ ዘር አቅርቦት እና ስርጭት ስርአት የሚዘረጋ ሲሆን የዛፍ ዘር አመራረጥ፣ አሰባሰብ እና አያያዝ ፕሮቶኮል ይዘጋጃል፡፡ በተመሳሳይ በ11 የክልል ከተሞች ላይ የከተማ ደን አያያዝ ማሻሻል እና ልማቱን የማስፋፋትና ለ3.4 ሚሊዮን ሄክታር ምርት ሰጪ ደኖች የደን አያያዝ እቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

የአካባቢ ደህንነት መብቶች፣ የደን ሃብት ልማት ጥበቃና ተጠቃሚነት የሚረጋገጥበት ሥርዓት የሚዘጋጅና እና መከበራቸውን የሚረጋገጥ ሲሆን የህዝብ፣ የአካባቢ እና የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አሳታፊና ያልተማከሉ የአካባቢ መንከባከቢያ ሥርዓቶች ይዘጋጃሉ፡፡ የደን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ህጎችን በየደረጃው ባለ አመራር፣ ባለሙያና በህብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ እንዲያዝ ይደረጋል፡፡ የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ተግባራዊ በማድረግ ተፈፃሚነታቸው ላይ ክትትል ይደረጋል፡፡ በአካባቢ ጉዳይ ላይ የወጡ ህጎችን ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ማድረግ፤ ህጎች ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በትግበራ ሒደት ክትትል፣ ቁጥጥር እና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ በማካሄድ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ ትግበራ የገቡ ፕሮጀክቶችን በወጡ የአሰራር መመሪያዎች መሰረት መተግበራቸውን እና በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ አለማድረሳቸውን በክትትልና ግምገማ የማረጋገጥ ሥራ ይሰራል፡፡

## 4.5 ሥነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች

በሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ የተቀመጡ ዓላማዎችን ለማሳካት በቀጣዩ የአምስት ዓመት እቅድ ዘመን የስነሕዝብ ፖሊሲና ፕሮገራሞችን የሚያስፈጽሙና የሚተገብሩ የፌደራል የዘርፍ አስፈጻሚ አካላት የሚመለከታቸውን የስነሕዝብ ተግባራት የዘርፍ ዕቅዶቻቸው ውስጥ አካተው እነዲተገብሩ ማስቻል፤የስነህዝብ ጉዳዮችን አሰተሳሰሮ ማስኬድ እንዲቻል ሁሉም አጋሮች የግንዛቤና ንቅናቄ ስራዎችን እንዲያካሂዱ ማድረግ፣ የባለድርሻ አካላትን አቅም ማሳደግ አቅጣጫዎች ናቸው፡፡ እንዲሁም የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን ለማሻሻል የሥነሕዝብ መረጃ ቋት (ዳታቤዝ) በመመስረት ከክልሎችና ከፌደራል ተቋማት ጋር የማገናኘት ሥራ እንዲሁም ፖሊሲ ተኮር የሥነሕዝብ ናልመት ምርምሮችን በማከናወን ወቅታዊ የሥነሕዝብ መረጃ ተጠቃሚነት እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የስነሕዝብ ፖሊሲን ከመተግበር አንፃር የእናቶችና የህጻናት ሞት ምጣኔ ለመቀነስ፣ የቤተሰብ ምጣኔ፣ የቅድመ ወሊድና የድህረ ወሊድ አገልግሎት ሽፋን ከፍ እንዲል እንዲሁም እናቶች በህክምና መስጫ ተቋማት እንዲወልዱ እና የአገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል፣ የሴቶች ትምህርት ተሳትፎ እንዲጨምር፣ ያካባቢ ደህንነት እንዲሻሻል፣ ከሚመለከታቸው የዘርፍ መስሪያ ቤቶች ጋር አጋርነት በመፍጠር የቅንጅት ሥራ መሥራት የዘርፉ ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

እየታየ ያለውን የውልደት መጠን የመቀነስ አዝማሚያ እንዲቀጥል ለማድረግ በመወሰድ ላይ ያሉ እርምጃችን አጠናክሮ መቀጠል፣የህዝብ ቁጥር እድገት ምጣኔን ከኢኮኖሚ አቅም ጋር ማጣጠም የሚችሉ እርምጃችን አጠናክሮ መቀጠል፣ በዲሞግራፊ ምጣኔና በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የተፈጥሮ አካባቢ ግቦች መካከል ሚዛናዊ ሁኔታ እንዲፈጠር በማድረግ የአገሪቱን ዲሞግራፊያዊ ሽግግር ማፋጠን፣ ከውልደት መጠን መቀነስና ከአምራች ኃይል ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ ሊፈጠር የሚችለውን የዲሞግራፊያዊ ትርፍ ድርሻ አገሪቱ እንድትጠቀም ማስቻል፣ የወጣቶችን (15-29) ሥራ አጥነት መቀነስ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰት በዕቅድ ላይ ኢኮኖሚያዊ ስልቶችን በመዘርጋት የፈለሰውን የሰው ኃይል በምርታማ ስራ ላይ እንዲሰማራ ማድረግ፣ የእናቶች፣ ህጻናትና ልጆች ሞትን መቀነስ፣ ተደራሽ ያልሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የተዋልዶ ጤና ሁኔታ ማሻሻል፣ አረጋውያንና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች የጤናና የማህበራዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ የሚካሔደውን ጥረት አጠናክሮ መቀጠል፣ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ቁጥርን ለመቀነስ እየተወሰደ ያለውን አዎንታዊ እርምጃ አጠናክሮ መቀጠል፣ የምርምር ግብአቶችን ተቋማዊ በማድረግ በውሳኔ አሰጣጥ ረገድ የውሳኔ ሰጪ አካላት ዋና መሳሪያ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የሥርዓተ ጾታ እኩልነትንና የሴቶችን ብቃት ለማረጋገጥ የሚደረጉ

ጥረቶችን አጠናክሮ መቀጠል፣ የዘላቂ ልማትንና የተፈጥሮ አከባቢ እንክብካቤ ስራን አጠናክሮ መቀጠል፣ በሁሉም የአደረጃጀት እርከን የሚታቀዱ የልማት ዕቅዶች በትክክለኛ መረጃን ላይ ተመስርተው እንዲታቀዱ የሥነ-ህዝብና ልማት መረጃዎችን ይበልጥ ተደራሽ ማድረግ፣ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትንና የሲቪክ ማህበራትን ተሳትፎ ይበልጥ ማጠናከር የዘርፉ ዓለማዎች ናቸው፡፡

በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በተዘጋጀው የመካከለኛ አማራጭ የህዝብ ብዛት ትንበያ መሠረት የህዝብ በዛት በ2007 ከነበረበት 89.8 ሚሊዮን በ2012 የበጀት ዓመት 100.2 ሚሊዮን እንደሚደርስ፣ የህዝብ ብዛት ዕድገት መጣኔ በ2007 ከነበረበት 2.4 በመቶ በ2012 ወደ 2.1 በመቶ እንደሚቀንስ፣ አጠቃላይ የወሊድ መጣኔ በ2007 ከነበረበት 4.2 በመቶ በ2012 ወደ 3.7 በመቶ እንደሚቀንስ፣ ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት የህዝብ ድርሻ በ2007 ከነበረበት 41 በመቶ በ2012 ወደ 38.2 በመቶ እንደሚቀንስ የኢኮኖሚ ጥገኝነት መጣኔ በ2007 ከነበረበት 77 በመቶ በ2012 ወደ 70 በመቶ እንደሚቀንስ እና በከተማ የሚኖረው የህዝብ መጣኔ በ2007 ከነበረበት 19.5 በመቶ በ2012 ወደ 21.8 በመቶ እንደሚያድግ የሚያሳዩ ግቦች ተቀምጠዋል፡፡

በመረጃ አሰባሰብ፣ዝግጅትና ትንተና መስክ የባለሙያዎችን አቀም ማጎልበት፣በመምርምር ፍላጎት ጥናት አማካኝነት ፖሊሲ ተኮር የምርምር ፍላጎትን መለየትና ከምርምር ውጤት ተጠቃሚዎች፣ የምርምር ተቋማት እና በግል ጥናት ከሚያድርጉ ተመራማሪዎች ጋር ምክክር በማድረግ የምርምር አጀንዳን ማዘጋጀት፣በሥነሕዝብ ፕሮግራም አመራር የሥነሕዝብ ፈጻሚ አካላት ባለሙያዎችን ክህሎትና የቴክኒክ ብቃት በማሳደግ የሥነ ህዝብና ልማት ዕቅድ ዝግጅትን ማጎልበት፣ ሁሉንም የሥነሕዝብ ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ ብሄራዊ የሥነህዝብ ግብረ ኃይል በማቋቋም የሥነሕዝብ ፖሊሲን በተቀናጀ ሁኔታ መተግበር ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች ይሆናሉ፡፡

# ምዕራፍ V
# በዕቅዱ አፈፃፀም ሂደት የሚጠበቁ ዕድሎችና ስጋቶች

ከመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም ከተገኙት ተሞክሮዎች አንዱና ዋነኛው ትልልቅ አገራዊና ከባቢያዊ ፋይዳ ያላቸው /እንደህዳሴው ግድብ እና ግልገል ግቤ 3 እንዲሁም የባቡር ፕሮጀክቶች/ በቁርጠኝነት እንዲጀመሩ የተደረገበትና ትግበራቸውም በመፋጠን ላይ ያለበት በመሆኑ፣ በአገር ደረጃ ከፍተኛ በራስ የመተማመን መንፈስ መፈጠሩ ነው፡፡

በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2003-2007) የትግበራ ሂደት ቁልፍ በሆኑ ሀገራዊ የልማት ጉዳዮች ዙሪያ ከሀገሪቱ ጫፍ እስከ ጫፍ ከፍተኛ ህዝባዊ መነሳሳትና የጋራ የልማት መንፈስ ተፈጥሯል፡፡ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በተከናወኑ የተቀናጁና የተደራጁ የልማት ሥራዎች በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና በተፋሰስ ልማት ምርጥ ተሞክሮዎች ተመዝግበዋል፡፡ በሌላ በኩል ባለፉት አራት ዓመታት የዓለም ኢኮኖሚ ከፍተኛ ፈተናዎች ገጥመውታል፡፡ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጀመሪያዎቹ ሁለት የትግበራ ዓመታት (2003 እና 2004) የዓለም የምግብና የነዳጅ ዋጋ ከፍተኛ ዕድገት አሳይቶ ነበር፡፡ ይህም የበለጸጉ አገሮችን ኢኮኖሚ በተለይም የምዕራባዊያን ኢኮኖሚ ከሚጠበቀው በታች በዝቅተኛ የዕድገት ምህዋር ውስጥ እንዲጓዝ አድርጎታል፡፡ እነዚህን መሰል ክስተቶች በሀገር ውስጥ ዋጋና በወጪ ምርት ዕድገታችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድረዋል፡፡ በቅርብ ጊዜ የበለፀጉ ሀገሮች ኢኮኖሚ /ምዕራቡ ዓለም/ በተወሰነ ደረጃ መነቃቃት ቢያሳይም አሁንም ዕድገቱ አዝጋሚ መሆኑን የተለያዩ የጥናት ውጤቶች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ አንፃር የዓለም አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት መቀዛቀዝና በዓለም ደረጃ የሚከሰት የዋጋ አለመረጋጋት በቀጣይም ለሀገራችን ኢኮኖሚ ዕድገት የስጋት ምንጭ መሆናቸው አይቀርም፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት መልካም አጋጣሚዎች/ዕድሎች እንደሚኖሩ የሚጠበቅ ሲሆን በተቃራኒው ስጋቶች እንደሚኖሩ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም የዕቅዱ ዘመን ዕድሎች የሚጠበቁ ስጋቶችና የመከላከያ ስትራቴጅዎች በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 5.1 ዕድሎች

ባለፉት ዓመታት እየተመዘገበ የመጣውን የልማት ውጤት ቀጣይነት ለማረጋገጥና በኢኮኖሚው ውስጥ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል የመንግስት ቁርጠኝነት መኖርና ይህም በተጨባጭ ሥራ ላይ ባሉ አመቺ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የተረጋገጠ መሆኑ፣ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ሂደት ሕዝብን በማንቀሳቀስ በልማት ሠራዊት አግባብ የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች ቀጣዩን ዕቅድ በተሻለ ለመተግበር ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸው፣ ባለፉት ሁለት አሥርተ ዓመታት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በተከናወኑ የተደራጁና የተቀናጁ የልማት ሥራዎች በኢኮኖሚ ዕድገት፣ በማህበራዊና መሠረተ ልማት እንዲሁም በልማታዊ መልካም አስተዳደር ከፍተኛና ቀጣይነት ያላቸው ውጤቶች መመዝገባቸውና በዚህም የሀገራችን ገጽታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየረ መምጣቱ፡፡ በቀጣይም ሰፊ የኢንቨስትመንት ዕድሎች በመኖራቸው እነዚህን ዕድሎች አማጥጦ በመጠቀም ዕቅዱን ለማሳካት ርብርብ ይደረጋል፡፡ በተለይ በአሁኑ ወቅት የዓለም የነዳጅ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱ በሀገራችን እንደ አንድ ትልቅ ዕድል የሚወሰድና በአግባቡ የምንጠቀምበት ይሆናል፡፡

በተጨማሪም በሀገር ውስጥ የፋብሪካ ጥሬ ዕቃዎችን በስፋት የማምረት፣ በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማቅረብ የሚያስችል አቅም እየተፈጠረ መሆኑ፣ የማንፋክቸሪንግ ዘርፍ ጠንካራ ውድድር ያለበት ቢሆንም ዘርፉ ለሚያመርታቸው ምርቶች በአለም ደረጃ ሰፊ የገበያ ዕድል ያለ መሆኑ፣ በተለያዩ ሀገራት የታዳጊ አገሮችን የወጪ ንግድ ለመደገፍ የተሰጡ ዕድሎች በተለይ የአፍሪካን ዕድገት ለማፋጠን የተሰጡ እንደ የአፍሪካን ዕድገት ለማፋጠን ወደ አሜሪካ ገበያ ከቀረጥ ነፃ ለመላክ የተሰጠ ዕድል /“AGOA”/ እንዲሁም በአውሮፓ ህብረት ሁሉንም ነገር ከጦር መሣሪያ በስተቀር (Every Thing But Arms) የመሳሰሉ ዕድሎች ስምምነት መኖር ለኤክስፖርት ገበያው የሚፈጥረው ተጨማሪ ዕድል ሰፊ በመሆኑ እነዚህን

መልካም አጋጣሚዎች በአግባቡ በመጠቀምና ሥራ ላይ በማዋል በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት ከመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም የላቀ ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል፡፡

## 5.2 ስጋቶች

ዕቅዱን ለማስፈፀም የሚጠይቀው ከፍተኛ ፋይናንስ በመሆኑ ይኸው በሚፈለገው መጠንና ጥራት ላይመጣ ይችላል፡፡ ስጋቶች የዕቅድ ስኬታችንን ሊያደናቅፉ የሚችሉና በተጨባጭ ከመከሰታቸው በፊት የመከላከያ ስትራቴጂ ሊዘጋጅላቸው የሚገቡ አደጋዎች ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ስኬታማነት ሊፈታተኑ ይችላሉ ተብለው ከሚታሰቡ ስጋቶች መካከል የድርቅ ተጋላጭነት፣ የኪራይ ሰብሳቢነት አደጋ በአመለካከትም ሆነ በተግባር፣ ኢኮኖሚያችን እየሰፋና እየተወሳሰበ ከመሄዱ አንፃር የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ውስንነት የግብርና ምርቶች ጥራታቸው ተጠብቆ ለገበያ በወቅቱና በአስተማማኝ ሁኔታ የሚቀርቡበት አምራችና ሸማቹን ተጠቃሚ የሚያደርግ ግልጽና ቀልጣፋ የግብይት ሥርዓት ተሟልቶ አለመደራጀት፣ የንግድ ሥርዓታችን ግልጽነት ተወዳዳሪነትና ቅልጥፍና የጎደለው መሆኑ፣ የዓለም ኢኮኖሚ መቀዛቀዝ በወጪ ንግዳችን (በውጭ ምንዛሬ ግኝታችን) ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖና በዓለም ደረጃ ሊከሰት የሚችል የዋጋ አለመረጋጋት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የአፈፃፀም ሂደት ላይ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ ይችላሉ ተብለው የሚጠበቁ ስጋቶች ናቸው፡፡

## 5.3 የስጋት መከላከያ ስትራቴጂዎች

ከሁሉም በላይ ያሉትን ዕድሎች አሟጦ መጠቀም ዋነኛው የስጋት መከላከያ ስትራቴጂ መሆን አለበት፡፡ ከፍ ብሎ የተቀመጡ ስጋቶች በተጨባጭ ከመከሰታቸው በፊት ለመከላከል የተደራጁና የተቀናጁ የልማት ሥራዎች በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች እንዲከናወኑ ይደረጋል፡፡ የድርቅ ተጋላጭነትን ከመከላከል አንፃር በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች የህዝቡን ግንዛቤ ይበልጥ በማስፋትና በማዳበር በተለይ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ልማት በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የአፈፃፀም ሂደት ያገኘናቸው ምርጥ ተሞክሮዎች በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በተሟላ ሁኔታ ይተገበራሉ፡፡ የኪራይ ሰብሰቢነት አደጋዎችን ለመከላከል በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎችን የዜጎችን ግንዛቤ በማሳደግ እና የተደራጁና የተቀናጁ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ በመንግስት መዋቅርና በግሉ ዘርፍ አስተምህሮን ማዕከል ያደረጉ የመከላከያ ስልቶች ተፈፃሚ ይደረጋሉ፡፡ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅምን ከማጠናከር አንፃር በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በሁሉም ዘርፎች የማስፈፀሚያ ስትራቴጂ ቅድሚያ ትኩረት እንዲሰጠው ተደርጓል፡፡ ይህ ስትራቴጂ በእያዳንዱ ዘርፍ በተቀመጠው አግባብ መፈፀሙን በቅርብ የመከታተልና ድጋፍ የመስጠት ሥራ ይሠራል፡፡

የዓለም ኢኮኖሚ መቀዛቀዝንና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊከሰት ከሚችል የዋጋ አለመረጋጋትን በሀገር ውስጥ በሚወሰዱ እርምጃዎች መቀልበስ እንደማይቻል የታወቀ ቢሆንም ከዚህ ጋር ተያይዞ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ሊከሰት የሚችለውን አደጋ ለመቀነስና ለመከላከል ይቻላል፡፡ ይህንን ዕውን ለማድረግ ለውጭ ንግድ የምናቀርባቸውን ሸቀጦች በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም የገቢ ንግድ ስትራቴጂክ ሸቀጦችን አቅም በፈቀደ መጠን በሀገር ውስጥ በሚመረቱ ሸቀጦች ለመተካት ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡ በተጨማሪም የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ከምንጊዜውም በላቀ ደረጃ በማሳደግ በቂ የሀገር ውስጥ የምግብ አቅርቦትን ለማረጋገጥ፣ ለቀላል የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በዓይነት፣ በመጠን እና በጥራት ግብዓት ለማቅረብ እና የግብርናውን ዘርፍ የወጪ ንግድ ሸቀጦች አቅርቦት በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራትና በዋጋ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡

# ምዕራፍ VI
# የአፈፃፀምና ክትትል ግምገማ ሥርዓት

በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንደተመለከተው የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ዋና ዓላማ መንግስት ያወጣቸውን የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መሠረት በማድረግ የተዘጋጀው የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች መሳካታቸውን በአጠቃላይ ኢኮኖሚ እና በክፍላተ ኢኮኖሚዎች ደረጃዎች መከታተል፣ መገምገምና ማስተካከያ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ በወቅቱ የእርምት እርምጃ በመውሰድ የልማት እንቅስቃሴውን በተገቢው መንገድ መምራት ማስቻል ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በሚመነጩ የሰርቬይና የቆጠራ መረጃዎችን ጨምሮ ከየዘርፍ አስፈፃሚ አካላት በሚቀርቡ የአፈፃፀም መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ በቅርብ የመከታተሉ ሥራ እንደተጠበቀ ሆኖ የዕቅዱን አፈፃፀም በመስክ ክትትል መረጃዎች ጭምር በማጠናከር አስፈላጊ ድጋፎች ይደረጋሉ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ በተሟላ የአፈፃፀም መርሀ ግብር ላይ በመመሥረት የሚካሄዱ የመስክ ክትትል ሥራዎች በተለይ በትላልቅ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ የሚያተኩሩ ይሆናል፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ የፕላን ክትትልና ግምገማ ሥርዓቱን የመምራትና የማስተባበር ኃላፊነት የተጣለበት የብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት (2008-2012) የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ ለመምራት የሚያስችል የክተትልና ግምገማ ሥርዓት ለማጠናከር ሀገራዊ የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱን ጉድለቶች በጥናት በመለየት በተለያዩ ደረጃዎች የማሻሻያና የማጠናከሪያ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡ በዚህም መሠረት የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ለፖሊሲ ውሳኔ መሠረት የሚሆኑ ወቅታዊ፣ የተሟሉና ተአማኒነት ያላቸው መረጃዎችን በሰርቬይ፣ በቆጣራ፣ ከአስተዳደራዊ ምንጭ እና በመስክ ክትትል በማመንጨት እና በመተንተን ለተጠቃሚዎች በወቅቱ ለማድረስ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡

ከዚህ አንፃር በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በአገራዊ ክትትልና ግምገማ ዙሪያ የተሟሉ ጥናቶችን በማካሄድ የአሠራር፣ የአደረጃጀትና እና በሰው ኃይል አቅም ግንባታ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የብሔራዊ ስታቲስክስ ልማት ስትራቴጂን ማዕከል በማድረግ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በየደረጃው ከተቀመጡ ግቦች አንፃር አስፈላጊ የክትትል መረጃዎች በአግባቡ እንዲያዙ፣ እንዲደራጁ፣ እንዲተነተኑና ለተጠቃሚዎች በወቅቱ እንዲቀርቡ ከፍተኛ የክትልና ድጋፍ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡ በተለያዩ ደረጃዎችና አካላት ለሚዘጋጁ የአፈፃፀምና ግምገማ ሪፖርቶች ከጊዜና ከይዘት አንፃር ስታንዳርዶች እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡

በተሟላ የአፈፃጸም መርሐ ግብር በመታገዝና በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ በተለይ በትላልቅ ፕሮጀክቶች ላይ በማተኮር የሚከናወኑ የመስክ ክትትልና ግምገማ ሥራዎች ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን የሚመለከታቸውን አስፈፃሚ አካላት አስተባብሮ በመምራት የሚፈፀሙ ይሆናል፡፡ በመስክ ክትትል በሚገኙ መረጃዎች ላይ በመመሥረት ለሚመለከተው አስፈፃሚ አካል ድጋፎች ይደረጋሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተመረጡ የሴክተር ፕሮግራሞች የአፈፃጸም ስኬት ላይ ጥናቶችን በማካሄድ ለፖሊሲ ዝግጅት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች እንዲመነጩ ይደረጋል፡፡ በከፍተኛ አመራር ደረጃ ትልልቅ ፕሮጀክቶች በመስክ ምልከታ የታገዘ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ይካሄዳል፡፡

በመጨረሻም የፕላን አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሪፖርት ከተዘጋጀ በኋላ ለብሄራዊ ፕላን ካውንስል ቀርቦ ውይይት ከተደረገበትና ከዚያም በሚገኝ ግብረ መልስ መሠረት አስፈላጊ ማስተካከያዎች ተደርገው ከዳበረ በኋላ የሚፀድቅ ይሆናል፡፡